አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሃ-ግብር

የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ምንጩ፣ መገለጫዎቹና ተግባሩ

በፎክሎር የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት

በ

ጌታዋ ሞላ ታረቀኝ

አማካሪ፦ አህመድ ሐሰን (ዶ/ር)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሚያዚያ 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቤተ-መጻሕፍት
Addis Ababa University
Libraries

የድኅረ ምረቃ መርሃ-ግብር

ዐፄ ይማኖት መቻቻል እሴት በወለሞ፤ ምንጩ፣ መገለጫዎቹና ተግባሩ

በፎክሎር የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት

በ

ጌታዋ ሞላ ታረቀኝ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሚያዚያ 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሃ-ግብር

የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ምንጩ፣ መገለጫዎቹና ተግባሩ

በ

ጌታዋ ሞላ ታረቀኝ

ሚያዚያ 2008 ዓ.ም.

<u>የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ</u>

.....	.....	.....
አማካሪ	ፊርማ	ቀን
.....	.....	.....
የውጭ ፈታኝ	ፊርማ	ቀን
.....	.....	.....
የውስጥ ፈታኝ	ፊርማ	ቀን

የአጥኚው ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምርምር አሰራር ደንብ የሚጠይቀውን ማንኛውንም መስፈርት ወይም መመዘኛ የሚያሟላና የእኔ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑን፤ እንዲሁም በውስጡ የተገለገልኩባቸውን ሁሉንም የመረጃ ምንጮች በአግባቡና ሙሉ በሙሉ የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ሥም፦ ጌታዋ ሞላ ታረቀኝ

ፊርማ፦.....

ቀን፦ 15/08/07

ምስጋና

በመጀመሪያ ማስተዋሉን፣ ትእግስቱን፣ ብርታቱንና ጽናቱን ሰጥቶ እዚህ ደረጃ ላደረሰኝ ቸሩ እግዚአብሔር ምስጋናዬ ይድረሰው።

ከጥናቱ መነሻ እስከ ፍፃሜው ሃሳብ እያፈለቁ ጥናቱን በማዳበር፣ ለጥናቱ የሚያገለግሉ መፃሕፍት በመጠቆምና በማዋስ፣ የጥናቱን አቅጣጫ በትክክል በመምራት፣ ጥናቱን ደጋግመው በማንበብና በማረም ያማከሩኝን ዶክተር አህመድ ሐሰንን ከልብ አመሰግናለሁ።

የሙሽርነት ጊዜሽን ጭምር ለዚህ ጥናት መስዋዕት ያደረግሽው ውዷ ባለቤቴ ተክለወይን ሃዳሙ ከአክብሮት ጋር አመሰግንሻለሁ።

የትምህርት እድሉን በመስጠትና ከዚያም በኋላ ልዩ ልዩ ድጋፎችን በማድረግ ላስተማረኝ ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (EBC) ከፍያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ይህ በፎክሎር የፍልስፍና ዶክትሬት ማሟያ ጥናት እዚህ ደረጃ ሊደርስ የቻለው በተሰበሰቡ የምርምር መረጃዎች አማካይነት ነው። እነዚህ መረጃዎች የተሰበሰቡት ደግሞ ከቤተ መፃሕፍትና ከመስክ ነው። በዚህ መሰረት ከቤተ መፃሕፍት ለተሰበሰቡት መረጃዎች ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም (IES) ቤተ መፃሕፍት ሰራተኞች ምስጋናዬ ይድረሳቸው። ከመስክ ለተሰበሰቡት የምርምር መረጃዎች ደግሞ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝን ሁሉ በጣም አመሰግናለሁ። የወሎ ደጋጎች ከራማ እንዲጠብቃቸውና በረካቸውም እንዲደርሳቸው እመኛለሁ።

በመጨረሻ፤ ግን ደረጃው እኩል የሆነ ምስጋና ላስተማሩኝ፣ በየደረጃው ጥናቱን በማንበብና በማረም ላበለፀጉትና የምርምር ሥራዎቻቸውን ለዚህ ጥናት የተገለገልኩባቸው ምሁራንን፤ እንዲሁም ልዩ ልዩ ድጋፎችን ላደረገልኝ የዚህ ፕሮግራም ትምህርት ክፍልና የክፍሉን ሰራተኞች በሙሉ አመሰግናለሁ።

ጌታዋ ሞላ ታረቀኝ

ሚያዚያ 2008 ዓ.ም.

ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና.....iii
ማውጫ.....iv
ሠንጠረዥ.....x
ካርታ.....x
ሥዕላዊ መግለጫ.....x
ፎቶግራፍ.....x
አጠቃሎ.....xii

ምዕራፍ አንድ

1.መግቢያ.....1

1.1፦ የጥናቱ አደረጃጀት.....8

1.2፦ አካባቢያዊ ዳራ.....10
1.3፦ የጥናቱ አስፈላጊነት (statement of gap).....14

1.4፦ የጥናቱ ዳራ.....17
1.5፦የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች.....20

1.6፦የጥናቱ ዓላማዎች.....23
1.6.1፦የጥናቱ ዋና ዓላማ.....23
1.6.2፦ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች.....23
1.7፦ የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች.....23
1.7.1፦ የጥናቱ ዓብይ የምርምር ጥያቄዎች.....23
1.7.2፦ የጥናቱ ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች.....23
1.8፦ የጥናቱ ፋይዳ (ጠቀሜታ).....24

1.9፦ የጥናቱ ወሰን.....25
1.10፦ የጥናቱ ውስንነት.....31
1.11፦ ያጋጠሙ ችግሮችና የተበጁላቸው መፍትሄዎች.....32

ምዕራፍ ሁለት

2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት (ክለሳ ድርሳናት).....34
2.1፦ ሃይማኖትን መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ የመረመሩ ሥራዎች.....35
2.2፦ በሃይማኖት ዙሪያ ወሎ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች.....38
2.3፦ በሃይማኖታዊ እሴቶች (ትውፊቶች) ወሎ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች.....47
2.4፦ በሃይማኖት መቻቻል እና በሃይማኖት ሰበብ በተከሰቱ ግጭቶች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች.....53

ምዕራፍ ሦስት

3፦ የጽንሰ-ሃሳብ፣ የንድፈ-ሃሳብ ማብራሪያዎች እና የጥናቱ ዘዴዎች.....69
3.1፦ ፎክሎር.....69
3.1.1፦ ‹‹ፎክ››.....70
3.1.2፦ ‹‹ሎር››.....72
3.2፦ የጥናቱ ንድፈ ሃሳብ.....74
3.2.1፦ ዓውዳዊ ንድፈ ሃሳብ (contextual theory).....76
3.3፦ የጥናቱ ሥልት (Research Approach).....79
3.3.1፦ አይነታዊ የጥናት ዘዴ.....80
3.3.2፦ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Research Methods).....83
3.3.2.1፦ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች.....84

3.3.2.1.1፦ ምልከታ.....84
3.3.2.1.2፦ ቃለመጠይቅ.....88
3.3.2.2፦ ካልኣይ የመረጃ ምንጮች.....91
3.4. የመረጃ አቀባዮች ምርጫ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች፣ መቼቶች እና አንፃር...94
3.4.1፦ የመረጃ አቀባዮች ምርጫ..... 94
3.4.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች.....98
3.4.3፦ የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃር.....98
3.4.4፦ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች.....100
3.5፦ የ"ትሪያንጉሌሽን" መርህ.....101
3.6፦ የጥናቱ የትንተና ሥልት.....102

ምዕራፍ አራት

4፦ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ሥረ-መሠረት በኢትዮጵያ.....105
4.1፦ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ሥረ-መሠረት በወለኖ.....111
4.1.1፦ ታሪካዊ ሁነቶች በወለኖ.....114
4.1.2፦ የጋብቻ ትስስር እና የዘር ሐረግ ትውፊት በወለኖ.....118
4.1.3፦- የትንቢት ትውፊት በወለኖ.....126
4.1.4፦ የፈረስና የዋፋ ውጊያ ትውፊቶች በወለኖ.....132
4.1.5 ፦የርስት ትውፊት በወለኖ.....136
4.1.6፦ የመብት ጥያቄ ትውፊት በወለኖ.....138
4.1.7፦ የገበያ ትውፊት በወለኖ.....148

ምዕራፍ አምስት

5፡- የሃይማኖት መቻቻል እሴት እና ሃይማኖታዊ ትውፊቶች በወለሞ.....155

5.1፡- የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለሞ፤ በእምነቶቹ ተከታዮች አብነት.....155

5.2፡- የክርስትና ሃይማኖት ትውፊቶች በወለሞ.....168

5.2.1፡-ዝክር.....169

5.2.2፡- ጥምቀት.....171

5.2.3፡- ፀበል.....174

5.2.4፡- ወረ-ካለሞ ተክለሃይማኖት.....177

5.3፡- የእስልምና ሃይማኖት ትውፊቶች በወለሞ.....188

5.3.1:- ወልይ በወለሞ.....190

5.3.2፡- የመርሣው ጌታ.....193

5.3.3፡- አበጋር በወለሞ.....196

5.3.4፡- ወዳጃ በወለሞ.....198

5.4፡- የክርስትናና የእስልምና ትውፊቶች ተራክቦ በወለሞ.....203

5.4.1:- የቆለሞ ተማሪና ደረሳ በወለሞ.....205

5.4.2:- ጠንቋይና ጥንቆላ በወለሞ.....210

5.4.3፡- ዛርና ባለዛር በወለሞ.....212

5.4.4፡- አድባር (ቆሌ) በወለሞ.....219

ምእራፍ ስድስት

6፡- የሃይማኖት መቻቻል እሴት እና ማኅበራዊ መስተጋብር በወለኖ (social interaction)....227

6.1፡- የሃይማኖት መቻቻል እሴት እና የጉርብትና ትውፊቶች በወለኖ.....227

6.1.1፡- ጉርብትና በደስታ.....230

6.1.1.1፡- የሠርግ ትውፊት በየጁ ሃዳ.....231

6.1.1.1.1፡- የሠርግ ሥርአት በየጁ ሃዳ.....236

6.1.1.1.2፡- የሽማግሌ አላላክ ትውፊት በየጁ ሃዳ.....236

6.1.1.1.3፡- የሠርግ ዝግጅት በየጁ ሃዳ.....238

6.1.1.1.4፡- የሚዜ (የጫጉላ) ትውፊት በየጁ ሃዳ.....245

6.1.1.1.4.1፡- ሚዜና እርድ በየጁ ሃዳ.....248

6.1.1.1.4.2፡- ሚዜና የጉርብትና ትውፊት በየጁ ሃዳ.....249

6.1.1.1.5፡- የሼነቻ (የተወፈሌ) ወዳጃ በየጁ ሃዳ.....253

6.1.1.2፡- ልደት.....257

6.1.1.2.1፡- ፋጢማ ቆሪ.....257

6.1.1.2.2፡- ጉማታ (አራስ መጠየቅ).....259

6.1.1.2.3፡- በወለኖ የአበልጅ ትውፊት 263

6.1.1.2.4.፡- ማስመረቅ.....265

6.1.1.2.5፡- በወለኖ የልጅ አስተዳደግ ትውፊት 266

6.1.1.3፡- በወለኖ የክብረ-በዓላት ትውፊቶች 274

6.1.2፡- ጉርብትና በወለኖዎች የእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቶች.....278

6.1.2.1፦ በወለሞ የሰላምታ ትውፊት 281

6.1.2.2፦ በወለሞ የቡና ሥርዓት 285

6.1.2.3፦ በወለሞ የአርሂቡ ትውፊት 294

6.1.2.4፦ ግጭትና የግጭት አፈታት ሥርዓት በወለሞ.....296

6.1.3፦ ጉርብትና በሥራ.....302

6.1.3.1፦ ወንፈል/ ጂጊ በወለሞ.....302

6.1.3.2፦ በወለሞ የቀንጃና የበዓላት ትውፊቶች 308

6.1.3.3፦ በወለሞ የአግማስ ትውፊት 311

6.1.4፦ ጉርብትና በሃዘን.....316

6.1.5፦ ጉርብትና በቅሬ (እድር).....324

6.2፦ በወለሞ የሃይማኖት መቻቻል እሴት እና የዘመኑ መንፈስ 327

ማጠቃለያና ይሁንታ.....336

ማጠቃለያ.....336

ይሁንታ.....345

ዋቢ መፃሕፍት.....346

የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1፦ በሰሜን ወሎ ዞን የኦርቶዶክስ ክርስትናና እስልምና እምነት ተከታዮች ስብጥር በቁጥርና በመቶኛ ሲገለጽ፡፡.....27

የካርታ ማውጫ

ካርታ አንድ፦ የሰሜን ወሎ ዞን በኢትዮጵያ በሰሜን፤ በአማራ ክልል ደግሞ በምስራቅ አቅጣጫ እንደሚገኝ የሚያመላክት ካርታ.....28

ካርታ ሁለት፦ ጥናቱ የተካሄደባቸው ወረዳዎች፡፡.....29

የሥዕላዊ መግለጫ ማውጫ

ሥዕላዊ መግለጫ አንድ፦ የየጁ ወረሴህ የዘር ሐረግና የጋብቻ ትስስር፡፡.....121

ሥዕላዊ መግለጫ ሁለት፦ የወረሂመኖ ኢማሞች (ማማዶች) የዘር ሐረግና የጋብቻ ትስስር፡፡.....122

ሥዕላዊ መግለጫ ሦስት፦ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ በአካባቢው የቡና ሥርዓት ትውፊት ተምሳሌትነት ሲገለጽ 339

የፎቶግራፍ ማውጫ

ፎቶግራፍ 1፦ ቁልፍ የወንድ መረጃ አቀባዮች ናሙና፡፡.....96

ፎቶግራፍ 2፦ ቁልፍ የሴት መረጃ አቀባዮች ናሙና፡፡.....97

ፎቶግራፍ 3፦ በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች ትብብር የተሰራው የቂሌ-ሃዳሜ ቅ/ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን....158

ፎቶግራፍ 4፦ በቤተ-ክርስቲያኑ የምረቃ ሥነ-ስርዓት ወቅት የአካባቢው ሙስሊም ወጣቶችና ሕፃናት.....159

ፎቶግራፍ 5፦ ቤተ-ክርስቲያኑ ተጠናቆ ሲመረቅ ከአካባቢው ሙስሊም ነዋሪዎች በስዕለት መልክ ከተሰጡ ፍየሎች በከፊል፡፡.....159

ፎቶግራፍ 6፦ የ121 ዓመት የእድሜ በለፀጋ እንደሆኑ የሚናገሩት ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፡፡.....165

ፎቶግራፍ 7፦ የወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት አካባቢያዊ ገጽታና ቤተ-ክርስቲያን፡፡.....177

ፎቶግራፍ 8፦ ወ/ሮ ሙሉ ደሳለኝ፤ የወረ-ካሎ ተ/ሃይማኖት ዓመታዊ ንግሥ ላይ፤ ነሐሴ 24ቀን 2007 ዓ.ም.....178

ፎቶግራፍ 9፦ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አማረ፣ የወረ-ካሎ ተ/ሃይማኖት ዓመታዊ ንግሥ ላይ፣ ነሐሴ 24ቀን 2007 ዓ.ም.....179

ፎቶግራፍ 10፦ ሰሚራ ከህመሟ ለመፈወስ በተክለ ሃይማኖት የንግሥ ዕለት፣ መስቀል ታሸታ፣ እምነት ተቀብታና ፀበል ይዛ.....180

ፎቶግራፍ 11፦ በወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት ዓመታዊ ንግሥ ላይ የሙስሊሞቹና የክርስቲያኖቹ አለባበስ.....181

ፎቶግራፍ 12፦ ሙስሊሞቹ ያመጡትን ስዕለት ሲሰጡና የወጣቶቹ ሙስሊሞች አቀማመጥ.....182

ፎቶግራፍ 13፦ በወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት የንግሥ እለት ሙስሊሞቹ ፀበል ለመውሰድ ሲጠባበቁና እምነት ሲቀበሉ.....184

ፎቶግራፍ 14፦ በእለተ ተክለሃያማኖት ሌሊት ሲዘንብ በማደሩ የአካባቢው ገጽታ ተለውጦ እንዳደረ.....185

ፎቶግራፍ 15፦ ሙስሊሞቹና ክርስቲያኖቹ ሕፃናት በክርስቲያኑም በሙስሊሙም ቤት እየዞሩ "ሶለል" ሲጫወቱ.....269

ፎቶግራፍ 16፦ የሰላምታ ትውፊት በወሎ.....284

ፎቶግራፍ 17፦ በሙስሊም ልቅሶ ጊዜ ወንዶቹ ወደመቃብር ቦታ ሲሄዱ፣ሴቶቹ ሸኝተው ሲመለሱ (ውርጌሳ)...319

አጠቃለ

ይህ ጥናት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለ ምን ማለት እንደሆነ፤ በምን እንደሚገለጽና ምንን እንደሚገልጽ ተንትኖ ለመግለጽ የተካሄደ ጥናት ነው። ዋና ዓላማውም በወለ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦችን እርስ በርስ አስተሳስረውና አስተባብረው፣ አግባብተውና አስማምተው፣ አዛምደውና አዋህደው ድርና ማግ በመሆን በፍቅርና በሰላም ይዘዋቸው የሚጓዙ መሰረታዊ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶችን (common-bond/ fabric) ማጥናት ነው።

ጥናቱ የተመራው በዓውዳዊ ንድፍ ሃሳብ የፍልስፍና መርህ ሲሆን፤ መረጃዎቹ የተሰበሰቡትና የተደራጁት ደግሞ በአይነታዊ የጥናት ሥነ-ዘዴ ነው። መረጃዎቹ የተተነተኑት በዓውዳዊ የንድፈ-ሃሳብ መርህ አማካይነት ሲሆን፤ የተተነተኑት መረጃዎች የተሰበሰቡት ከካልዓይና ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ነው። ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡት መረጃዎች ከቤተ-መፃሕፍት ውስጥ ነው። ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡት መረጃዎች ደግሞ በምልከታና በቃለ-መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በዋናነት እሴቶቹ በሚገኙበት ባህላዊና ማኅበራዊ ዓውድ ውስጥ ነው። ለዚህም በተለያዩ ጊዜያት አጥኚው ለአምስት ወራት ያህል መስክ ላይ በመቆየት ምልከታ አካሂዷል። ከ18 አጠቃላይና ከ23 ቁልፍ መረጃ አቀባዮችም በቃለ-መጠይቅ ዘዴ መረጃዎችን ሰብስቧል።

እነዚህን መረጃዎች በማደራጀትና በመተንተን በተገኘው ውጤት መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለ የወለዬዎች አብሮነት ማለት ነው። የወለዬዎች የእርስ በርስ ትስስር ማለት ነው። የወለዬዎች መረዳዳትና መደጋገፍ፣ መተዛዘንና መተሳሰብ፣ መከባበርና መተባበር፣ አብሮ መስራት፣ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት፣ አብሮ ማዘንና አብሮ መደሰት፣ ባጠቃላይ በሰላምና በፍቅር አብሮ መኖር ማለት ነው።

ከመገለጫዎቹ አንፃር ደግሞ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለ፤ በወለዬዎች የማህበራዊ ኑሮ መስተጋብር ዘይቤ ይገለፃል። በሃይማኖቶቹ ትውፊቶች አማካይነት ይገለፃል። በወለ ደጋጎችና በወለ አድባር ጭምር ይገለፃል። በማኅበረሰቡ አርአያዎች፣ ትዕምርቶችና ሥርዓተ-ከበራዎች አማካይነት ይገለፃል። በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለ የተለያዩ ትውፊቶች ውጤት ነው። የፎክሎርና የሃይማኖት ቡራኬ ነው፤ የዱዓና የቱፍታ በረከት ነው። የመላዕክት፣ የፃድቃን፣ የነቢያትና የሰማዕታት ችሮታ ነው፤ የፈጣሪም ፀጋ ነው። የተፈጥሮና የወለዬዎች መስተጋብር ስጦታ ነው፤ የገበያም እሴት ነው። የወለዬዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ብሂል ትሩፋት ነው።

ይህም የሚያሳየው የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለ ከመለያየት ይልቅ፤ መሰባሰብን ወይም አንድነትን፣ ከመናናቅ ይልቅ፤ ትህትናና መከባበርን፣ ከመጠራጠር ይልቅ፤ መተማመንን፣ ከኔ ይልቅ ላንት መባባልን፣ ወይም አንተ ትብስ-አንቺ-ትብሽ የሚል የማኅበራ ኑሮ መስተጋብር ዘይቤን ነው።

ይህ ማለት ግን በአሁኑ ጊዜ እነዚህ የአብሮነት እሴቶች እንዳሉና እንደነበሩ ቀጥለዋል ማለት አይደለም። ባንዳሩ በእሴቶቹ ላይ ለውጦች እየታዩ ነው። ለውጥ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ውስጥ የነበረ፣ ያለና የሚኖር ተፈጥሯዊ ሂደት ነው። መሰረታዊው ቁምነገር ግን በለውጡ ምክንያት የሚመጣው ውጤት አወንታዊ ወይም አሉታዊ ክስተት ከመሆኑ ላይ ነው። ከዚህ አንፃር በወለዬዎች የአብሮነት መሰረት በሆኑ እሴቶች ላይ አሉታዊ መንፈስ ያላቸው ለውጦች እየታዩ ነው።

ምእራፍ አንድ

1. መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ ወቅታዊ የመነጋገሪያ አጀንዳ ከሆኑ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ "የሃይማኖት መቻቻል" ርዕሰ ጉዳይ ነው። በመሆኑም የሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ ከቤተ-መንግሥት እስከ ቤተ-እምነት፤ ከሊሂቃኑ እስከ ብዙሃኑ የጋራ ርዕሰ ጉዳይ በመሆን በተደጋጋሚ ሲነገር ይሰማል።

በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ የመንግሥት አጀንዳ ሆኖ፤ በየደረጃው ያሉ የመንግሥት አካላት እርስ በርስ ወይም ከህዝብ ጋር በመሆን ይወያዩበታል፤ ይመክሩበታል። የሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን አጀንዳ ሆኖ፤ ዘወትር አየር ላይ ያውሉታል፤ አምዳቸው ላይ ይጽፉታል። የሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት አጀንዳ ሆኖ፤ ጉባዔ አቋቁመው እርስ በርስ ሃሳብ ይለዋወጡበታል፤ ምዕመናንን ያስተምሩበታል። የሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አጀንዳ ሆኖ፤ ፖለቲከኞች አቋም ይይዙበታል፤ ርዕዮተ-ዓለም ያራምዱበታል። የሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ የተመራማሪዎች አጀንዳ ሆኖ፤ ጥናትና ምርምር ያካሂዱበታል። ባጠቃላይ የሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ የመንግሥት፣ የህዝብ፣ የቤተሰብና የግለሰብ አጀንዳ ጭምር ሆኖ፤ በተለያዩ አካባቢዎች ውይይት ይደረግበታል።

ነገር ግን እነዚህ አካላት "መቻቻል" የተሰኘውን ጽንሰ-ሃሳብ የሚገልጹት፤ ጽንሰ-ሃሳቡን እንደ ተረዱበት መንገድ፣ እንደ እይታቸውና እንደየእምነታቸው ሁኔታ ወይም እንደየግል ፍላጎታቸውና እንደሚያራምዱት አጀንዳ መጠን ነው። ለምሳሌ መቻቻል በኢትዮጵያ በእንግሊዝኛው "Tolerance" ከተሰኘው ጽንሰ-ሃሳብ አንፃር ይገለፃል። መቻቻል በኢትዮጵያ ከፖለቲካ ፍጆታ አንፃር ይገለፃል። መቻቻል በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ከሚገለገሉበት ጽንሰ-ሃሳብ አንፃር ይገለፃል። መቻቻል በኢትዮጵያ ከጥናትና ምርምር ውጤቶች አንፃር ይገለፃል። መቻቻል በኢትዮጵያ ከሃይማኖት መቻቻል መርህ አንፃር ይገለፃል። መቻቻል በኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ ራሱ ከፈጠረውና ከሚኖርበት የማኅበራዊ ኑሮ ዘይቤ ላይ ተመስርቶ ከሚያወራው የመቻቻል እሴት አንፃር ይገለፃል።

ምንም እንኳ መቻቻል በኢትዮጵያ የብዙሃን አጀንዳና በእየለቱ ተደጋግሞ ሲነገር የሚደመጥ ርዕሰ ጉዳይ ቢሆንም፤ ብዙሃኑን የሚያግባባና የሚያስማማ ጽንሰ-ሃሳብ አይደለም፡፡ ባንፃሩ አሻሚና ግልጽነት የጎደለው ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት መቻቻል የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ አንድምታው (ፍችው ወይም ትረጉሙ) በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ነው፡፡ ለምሳሌ መቻቻል ማለት በሌላው፤ "ጥሩ ነገር አይደለም ግን ቻለው! ዋጠው! ታግሰው ወይም ታግሰህ አሳልፈው! አለያም ሆድ ከአገር ይሰፋል እንደሚባለው ነገሩን ለፈጣሪ ሰጥተህ ተወው!...ወዘተ" እንደማለት ይሆናል፡፡

እንዲሁም መቻቻል የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ታጋሹ ክፍል ትዕግሰቱ እያለቀ ሲሄድ፤ "በቃ! እስከሁን ድረስ ታግሼዋለሁ! ችየዋለሁ! የትዕግስትም ልክ አለው! እስከመቸ ድረስ እታገሰዋለሁ! እችለዋለሁ! እለማመጠዋለሁ!...ወዘተ" ብሎ ወደ ግጭት ሊያመራ እንደሚችል ወይም ጽንሰ-ሃሳቡ የግጭት መንስዔ ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁም አንድምታ አለው፡፡ ባንፃሩ መቻቻል የሚለው ጽንሰ- ሃሳብ ከላይ እንደተገለፀው አሉታዊ አንድምታ ያለውን ያህል አወንታዊ አንድምታ ወይም ፍች አለው፡፡

"መቻቻል" የሚለውን የአማርኛ ሐረግ (ቃል) ደስታ ተክለ ወልድ፤ <u>ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፤</u> በ1962 ዓ.ም[1] እትሙ፤ ገፅ፣ 1278፣ ላይ "መሸካከም፣ መወሳሰን፣ መጣወር" ሲል ይፈታዋል፡፡ በዚህ መሰረት "መቻቻል" ማለት መረዳዳት፣ መደጋገፍ፣ መተጋገዝ፣ መተሳሰብ፣ መተዛዘን፣ ከእኔ ይልቅ ላንተ ወይም አንተ-ትብስ፣ አንቺ ትብሽ መባባል...ወዘተ የሚሉትን ጽንሰ-ሃሳቦች ያዘለ ትርጉም አለው፡፡

በሌላ በኩል ይሄ ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች መቻቻል የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ የሚተረጉሙት በተለይ፤ "እስላምና ክርስቲያን በወሎ፤ አንድ አካል አንድ አምሳል ወይም ጥርስና ከናፍር ስለሆኑ፤ የሚቻቻሉበት ነገር የላቸውም!››[2] በሚል አንድምታ ነው፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን ነጥቦች በምክንያትነት ይጠቅሳሉ፡፡

> በጉርብትና ብቻ ሳይሆን፤ በሥጋ ዝምድና ተሳስረህ፤ እስላምና ክርስቲያን ሁነህ በአንድ ቤት ውስጥ አብረህ እየኖርክ፤ ተመሳሳይ ባህል፣ ወግና ልማድ እያለህ፤ በአንድ ቅሬ-በሃዘንና በደስታ ሳትነጣጠል፣ አንድ በሬ አቀናጅተህ ሁለት አርዝህ እያረስክ፤ በወንፈሉ፣

[1] በዚህ ጥናት ውስጥ ሁለት አይነት የዘመን አአቆጣጠሮች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህም የምዕራባውያኑና የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ናቸው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በኋላ የምእራባውያኑን የዘመን አቆጣጠር ስንጠቀም በሌላው ቁጥሩን ብቻ እንዳለ አስቀምጠናል፡፡ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር ስንጠቀም ደግሞ "ዓ.ም." የሚል መለያ ተጠቅመናል፡፡

[2] ዓለ መሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አንጦ- 04 ቀበሌ፡፡

በጂጊው፣ በአንድ ማጭድ፣ በአንድ ላዳ፣ በአንድ መንሽ፣...ወዘተ አብረህ እየሰራህ፣ አብረህ እየበላህና አብረህ እየጠጣህ፤ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ አንድ ሆኖ የሚኖርበትን ባህል እንዴት መቻቻል ትለዋለህ!? መቻቻል የሚባለው እኮ ለልዩነት ምክንያት የሆነ ነገር ኑሮ አንዱ ሲያጠፋ ሌላው ያነን ጥፋት እየቻለ ሲኖር ነው፡፡ መቻቻል የሚባለው ፊሊጥ የመጣውም እኮ አሁን ነው፡፡ ቃሉም ከአሁን በፊት ተነግሮም ተሰምቶም አይታወቅም፡፡ ለምን? በወሎ ክርስቲያን ትሆን እስላም ትሆን እሚጠይቅህ የለም፡፡ እሚጠይቅህ ሥጋ ትበላለህ አትበላም? ላይ ብቻ ነው፡፡ አልበላም ብትልም ለምን አልበላህም ብሎ ፀብም የለም፡፡ ለምን? በወሎ ከክርስቲያኑም ከእስላሙም ቤት "አይዋ እከሌ እንዴት አደራችሁ!?" ብለህ ገብተህ በልተህ ጠጥተህ የምትወጣበት ቤት ስለሆነ፡፡ እንግድህ ከተቻቻሉ ሊቻቻሉ እሚችሉት እንኳ አሁን ነው፡፡ ለምን? አሁን እየመጣ ያለው ነገር ከበድ ስለሚል፡፡ ይኸም በአንዳንድ አጉል ግለሰቦች ባዕዳዊ አስተሳሰብ እየመጣ ስለሆነ፡፡ ምናልባት ይኸ አስተሳሰብ በጋራ ያስተሳሰሩንን እሴቶች ሊያጠፋቸው ስለሚችል፡፡ ምክንያቱም አብሮ መስራቱ ከቀረ፤ አብሮ መብላቱ፣ አብሮ መጠጣቱ ከቀረ፤ መረዳዳቱና መተጋገዙ ከቀረ፣ መተዛዘኑና መተሳሰቡ ከቀረ "አይ! እኔ ሃይማኖቴን ብቻ መሰረት አድርጌ ነው እምኖረው ከሌላው ጋር አልደባለቅም ካልኩኝ መቻቻል ያነየ ሊኖር ይችላል፡፡ አሁን ግን በጋራ ያስተሳሰሩን እሴቶች ስላሉ ምኑን ከምን እናቻችለዋለን?[3]

በዚህ ጥቅስ መሰረት መቻቻል የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ ይዘ ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች "መቻቻል እሚባል ነገር እኛ ጋር መወራት የለበትም!" የሚል አቋም አላቸው፡፡ ባንፃሩ የአካባቢው ነዋሪዎች በወሎ ያለውን የእርስ በርስ ትስስር የሚገልጹት ክርስቲያንና ሙስሊም በወሎ "አንድ አካል አንድ አምሳል" ወይም ክርስቲንና ሙስሊም በወሎ "ጥርስና ከናፍር ናቸው!"[4] በሚል ተምሳሌታዊ ውክልና ነው፡፡ በዚህ ውክልና መሰረት የወተት አረፋ የመሰለ ጥርስ ያለ ከናፍር፤ ውብ ከናፍር ደግሞ ያለ ጥርስ ውበት እንደሌለው ሁሉ፤ በተመሳሳይ በወሎ ክርስቲያኑ ያለ ሙስሊሙ፤ ሙስሊሙ ያለ ክርስቲኑ ምንም ነው፡፡ ይህንን እውነታ በተጨባጭ በዚህ ጥናት በምእራፍ አምስትና በምእራፍ ስድስት ውስጥ በተነሱ የጋራ እሴቶች አማካይነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

እንዲሁም ክርስቲያንና ሙስሊም በወሎ "አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው!" የሚለውን ተምሳሌታዊ ውክልና ሼህ አሰን[5] ዓሊ ሞሐመድ የሚገልጹት ክርስቲያንና ሙስሊም በወሎ "ልብስ ነነ!"[6] በሚል ተምሳሌታዊ ማብራሪያ ነው፡፡ ይህም ማለት አንዱ ያለሌላው "ርቃን" ነው፡፡ ርቃን ደግሞ ገመና ነው፡፡ ከሰውነት ጎዳና መውጣት ነው፡፡ በመሆኑም ገመና የሚሸፈነው በልብስ ነው፡፡ በዚህ ተምሳሌታዊ አገላለጽ መሰረት በወሎ ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ፤ ሙስሊሙ ለክርስቲያኑ ገመና ከታች ልብሱ ነው፡፡ ያለዚያ አንዱ ያለሌላው

---

[3] አድኖ ተካየ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 02 ቀበሌ፡፡

[4] ዓሊ መሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 9 ቀን 20007 ዓ.ም› ሐብሩ- አንጦ-04 ቀበሌ፡፡

[5] "አሰን፣ ይመር፣ ይማም ወዘተ." የተሰኙት መጠሪያ ሥሞች በወሎ የተለመዱ የአማርኛ መጠሪያ ሥሞች ናቸው፡፡ በአረብኛው ግን "ሐሰን፣ ዑመር፣ ኢማም፣ ወዘተ. የሚል ትርጉም አላቸው (Rukya 2013 : 194)፡፡ ከዚህ አንፃር መረጃ አቀባዩ በአካባቢው ልማድ መሰረት የሚጠሩት "ሐሰን" ተብለው ሳይሆን "አሰን" ተብለው ነው፡፡

[6] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ፡፡

ርቃን ነው። በዚህ መሰረት በወሎ ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ፤ ሙስሊሙ ለክርስቲያኑ ውበቱና ድምቀቱ ነው። ክብርና ኩራቱ ነው። ግርማ ሞገሱ ነው። ስለዚህ "የሃይማኖት መቻቻል" ማለት በወሎ ወይም በዚህ ጥናት ውስጥ የጀማውን ፍች መነሻ የሚያደርግ ጽንሰ-ሃሳብ ሆኖ፤ የሃይማኖት መቻቻል ማለት በወሎ፤ አንዱ የሌላውን እምነት፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ የአኗኗር ዘይቤ ወይም የማኅበራዊ ሕይወት ፍልስፍና፤ ባህል፣ ወግና ልማድ፣ ደንብና ሥርዓት...ወዘተ ተቀብሎና አክብሮ በጋራ ከመኖር ባለፈ፤ አንዱ የሌላውን እሴት እስከመጋራት ይደረሳል (አጽንዖት የኔ)። በሌላ አገላለጽ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ማለት በወሎ ክርስቲያኑ እና ሙስሊሙ ያለውን ይዞ ጎን ለጎን በሰላምና በፍቅር ከመኖር በዘለለ ተሰባጥሮና እርስ በርሱ ተሳስሮ የጋራ እሴት ፈጥሮ፣ ከዚያም ሲያልፍ አንዱ የሌላውን የሃይማኖት ትውፊት ጭምር በጋራ እየተገለገለ በጉርብትናም ይሁን በአንድ ጣሪያ ሥር ሦስት ጉልቻ መስርቶ በሰላምና በፍቅር አብሮ እስከመኖር ይደርሳል።

ከዚህ አንፃር "የሃይማኖት መቻቻል እሴት" ማለት በወሎ ወይም በዚህ ጥናት ውስጥ አብሮነት ማለት ነው (አጽንዖት የኔ)። ከሃይማኖቶቹ መርሆዎች ጋር ከተገናኙ ጉዳዮች በስተቀር በሌሎቹ የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቶች ግን አንድ ሆኖ ወይም ተዋህዶ መኖር ማለት ነው። ይህም ማለት ከሃይማኖት አንፃር የራስን ይዞ የሌላውን አክብሮ በሌሎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብሮች ግን ተሰባጥሮና ተዋህዶ በሰላምና በፍቅር አብሮ መኖር ማለት ነው። መረዳዳትን፣ መደጋገፍን፣ መተሳሰብን፣ መተዛዘንን፣ አብሮ መስራትን፣ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣትን፣ ወዘተ. መሰረት የሚያደርግ ነው። ከመናናቅ ይልቅ- መከባበርን፤ ከጥላቻ ይልቅ- ፍቅርና ሰላምን፤ ከፍርሃትና ሥጋት ይልቅ- ተረጋግቶ መኖርን፤ ከጥርጣሬ ይልቅ- መተማመንን፤ ከመለያየት ይልቅ-አንድነትን ወይም መሰባሰብን፣ ከእኔ ይልቅ ላንተ ወይም አንተ-ትብስ፣ አንች-ትብሽ መባባልን...ወዘተ የሚወክል ጽንሰ-ሃሳብ ነው።

ከዚህ ውጭ በተካሄደው ጥናት መሰረት የሃይማኖት መቻቻል ማለት በወሎ ክርስቲያኑ ሙስሊሙን፤ ወይም ሙስሊሙ ክርስቲያኑን መሸከም ወይም መቻል አለያም መታገስ ማለት አይደለም። ወይም የቻይ (Tolerator) እና ተቻይ (Tolerated) ጉዳይ አይደለም። የዎሎዬዎች ባህላዊና ማኅበራዊ ዓውድም በተጨባጭ የዚህ አይነቱን አስተሳሰብ አይፈቅድም። ባንፃሩ የሃይማኖት መቻቻል በወሎ በተለያዩ የጋራ እሴቶች አማካይነት እርስ በርስ የመገናኘትና እርስ በርስ የመተሳሰር፣ የመዋሃድና የአብሮነት ጉዳይ ነው። የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር

ዘይቤ ነው። (አጽንዖት የኔ)። ለዚህ ደግሞ ወለዮዎች[7] የተለያዩ የመግናኛ መንገዶችና የመተሳሰሪያ ክሮች አሏቸው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም በነዚህ የጋራ እሴቶች አማካይነት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለዮ ምን ማለት እንደሆነ፣ እንዴትና በምን እንደሚገለጽ አና ምንን እንደሚገልጽ መመርመር ነው።

ኢትዮጵያ ሦስቱ ቀደምትና ታላላቅ ሃይማኖቶች (የአይሁድ፣ የክርስትናና የእስልምና) በቅድሚያ የገቡባትና የተስፋፉባት ሀገር ናት (Trimingham 1965: 15-30; Sergew 1970: 1-6; Ephraim 2008: 116-118)። የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት ሃይማኖቶቹ ወደ ኢትዮጵያ የገቡትም ሆነ የተስፋፉት ከውጭ በተደረገ ግፊት ወይም በኃይልና በግዳጅ ሳይሆን ከውስጥ በመነጨ የራስ ፍላጎትና ስሜት ነው። በመሆኑም በሌሎች ዓለማት እንደሆነው ሁሉ በኢትዮጵያ ሃይማኖቶቹን ያስፋፉ አባቶች (ሐዋርያት) ደም አልፈሰሰም፤ እንግልት አልደረሰም (Kefyalew 2005: 2; Sergew 1970: 5)።

ባንፃሩ ኢትዮጵያ በሃይማኖት ሰበብ እንግልትና ስደት ለደረሰባቸው የሌላ አገር ህዝቦች ጥላና ከለላ በመሆን ትታወቃለች። ለምሳሌ በክርስትናው በኩል ከሶሪያ እንደመጡ የሚነገርላቸው ዘጠኙ ቅዱሳን (አረጋዊ፣ ጴንጤሊዮን፣ ገሪማ፣ አፍጼ፣ ጉባ፣ አሌፍ፣ የማታ፣ ሊቃኖስ እና ሴሀማ) የሚጠቀሱ ሲሆን፤ በእስልምናው በኩል ደግሞ በነብዩ መሐመድ ዘመን ከመካና መዲና እንደመጡ የሚነገርላቸው ሰሓባዎች አብነቶች ናቸው (Hussein 2001: 31; Trimingham 1965: 44; Ephraim 2008: 117; Sergew 1972: 181-184)።

የተለያዩ ድርሳናት እንደሚያስረዱት ሃይማኖቶቹ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ብቻ ይዘው የገቡ አልነበሩም። ባንፃሩ ሃይማኖቶቹ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ይዘው የገቡት የበቀለበትን አካባቢና ማኅበረሰብ ባህል-ወግና ልማድ፤ ማኅበራዊ ግንኙነትና የአስተዳደር ዘይቤ፣ ሣይንስና ፍልስፍና...ወዘተ ሁሉ ይዘው ጭምር ነው (Schwab 1985: 92; Braukämper 1984: 166-167; Assefa 1992: 2-4; Hussein 2001: 22)። በሌላ በኩል እነዚህ ሃይማኖቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡ በኋላ ከአገሬው ህዝብ ባህል፣ ወግና ልማድ ጋር ሰላማዊ የሆነ ግንኙነት ፈጥረዋል። ከዚህ አንፃር ሃይማኖቶቹ ከነባሩ እሴት ጋር ተቻችሎ ከመኖር

---

[7] በዚህ ጥናት ውስጥ "ወለዮዎች" ማለት፣ ክርስቲያኖቹንና ሙስሊሞቹን ባንድነት ለመጥራት ተፈልጎ ነው። ወይም የተጠኝወቹን ሥም ለመጥቀስ ታስቦ ነው። በዚህ የተነሳ "ወለዮዎች" የሚለው ስም በሁሉም ምዕራፎች ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቀሶ ይገኛል። ይህም የሆነበት ምክንያት የሚጠኑት የማኅበረሰብ ክፍሎች እነሱ ስለሆኑ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ ሊጠቀሱ ግድ ስለሆነ ነው። ይህም ማለት "ወለዮዎች" የሚለው አገላለጽ በዚህ ጥናት ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ከተጠቀሱ የዚህ ጥናት ቁልፍ ቃላት መካከል አንዱ በመሆኑ ነው።

አልፊው የእትብት ዝምድና እስከመፍጠር ደርሰዋል (Alula 1994: 933; Mengistu 1997: 7; Tesfaye 2013: 12)::

በዚህ መሠረት በኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና የሁለቱ ቅልቅል ውጤት የሆኑ የጋራ እሴቶች በርካታ ናቸው፡፡ በዚህም ኢትዮጵያና ህዝቦቿ ሃይማኖቶቹን በሰላምና በፍላጎት በቅድሚያ የተቀበሉ አገርና ህዝቦች ብቻ ሳይሆኑ፤ ተቻችሎ አብሮ በመኖር ጭምር የዓለም ሁሉ ተምሳሌቶች ናቸው (Ephraim 2008: 8)::

በመሆኑም በኢትዮጵያ ሃይማኖት ብቻውን የማንነት መገለጫ ምልክት ወይም የእርስ በርስ መተሳሰሪያ ክር አለያም መገናኛ ድልድይ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያውያን የየግል እምነታቸውን እንደያዙ እርስ በርስ የሚተሳሰሩባቸው ሌሎች በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው፡፡ ለአብነት ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ቢለያዩ በተለያዩ የአኗኗር ዘይቤዎች ወይም ባህል፣ ወግና ልማዶች ይገናኛሉ፤ ይተሳሰራሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ቢለያዩ በእትብት ዝምድና የተሳሰሩባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ቢለያዩ፤ በታሪክ፣ በአስተዳደሩና በማኅበራዊ ጉዳዮች ሁሉ ይተሳሰራሉ፤ ይገናኛሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ቢለያዩ፤ ወንዙ፣ ጋራውና ሸንተረሩ ሳይቀር ያገናኛቸዋል፤ ያስተሳስራቸዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ቢለያዩ የኢትዮጵያ አንድነትና ለአላዊነት የአብሮነት ቃል ኪዳናቸው መገለጫ ነው፡፡ ለዚህ አባባል የሚከተሉት የሼህ ሁሴን ጅብሪል ስንኞች አብነቶች ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ አገራችን ራሷን ተሰርታ ተብላ ልክክ
ተቀብታዋለች በሀምበር በምስክ
ትሸታቸዋለች ለሮማ ለቱርክ
በሰማይ አይሮፕላን በመሬት ላይ ታንክ
እየመጡ ቀሩ እያሉ ልክክ
ኃይለሥላሴ ነው ባሏማ በልክ
እኛም ዱዓ አርገናል ሥላሴ ይባርክ /አጸንያት የኔ/ (ቦጋለ፤1984፡ 57)፡፡

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው በኢትዮጵያ ተቻችሎ የመኖር ባህልና የጠነከረ አንድነት የኢትዮጵያውያን ልዩ መገለጫ መሆኑን ነው፡፡ ከነዚህ የመቻቻል እና የአንድነት መገለጫዎች መካከል እንዱ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ነው፡፡ የተሰመረበት የጥቅሱ ስንኝ የሚያረጋግጠውም ይህንኑ እውነታ ነው፡፡ ምክንያቱም “ዱዓው” የእስልምናውን ትውፊት

የሚወክል ሲሆን፤ "ሥላሴዎች" ደግሞ የክርስትናውን እሴት ይወክላሉ፡፡ ገጣሚው ግን በወለሞ ከእስልምናው ታላላቆች መካከል አንዱ የሆኑት ትንቢት ተናጋሪ ሼህ ሁሴን ጅብሪል ናቸው፡፡ ኢትዮጵያውያን ልዩ ልዩ የሃይማኖት መቻቻል ስልቶች እና ከስልቶቹ የሚመነጩ በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው፡፡ እነዚህ እሴቶች ደግሞ ኢትዮጵያውያን ተከባብረውና ተቻችለው በሰላም አብሮ ለመኖር የሚገለገሉባቸው የጋራ እሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህ እሴቶች ከቤተሰብ የሚወረሱ፣ ከማኅበረሰቡ የሚጠኑና የሚቀሰሙ የኢትዮጵያውያን መለያ ትውፊቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ትውፊቶች በበኩላቸው ከላይ እንደተጠቀሰው ከመለያየት ይልቅ፤ መሰባሰብን ወይም አንድነትን፣ ከመናናቅ ይልቅ፤ ትህትናና መከባበርን፣ ከመጠራጠር ይልቅ፤ መተማመንን፣ ከኔ ይልቅ ላንተ መባባልን፣ ወይም አንተ ትብስ-አንቺ-ትብሽ መባባልን፣ መተጋገዝን፣ መረዳዳትን፣ መደጋገፍን፣...ወዘተ የሚያስተምሩ እሴቶች ናቸው፡፡ ተግባራዊ የሚደረጉትም የትውልዱን ጊዜና ዘመን በሚባርኩ፣ ትውልዱን በሚመክሩና በሚገስጹ፣ ትውልዱን በሚያስተምሩና በሚያስማሙ፣ የሀገርንና የህዝብን አንድነትና ሠላም በሚያፀኑ... ወዘተ የትውልዱ አርአያዎች (Models) አማካይነት ነው፡፡

ምንም እንኳን የሃይማኖት መቻቻል እሴት የኢትዮጵያና የህዝቦቿ ልዩ መገለጫና ለሌላው ዓለም ሁሉ ተምሳሌት የሆነ ፀጋ ቢሆንም፤ ከአሁን በፊት በኢትዮጵያ በሃይማኖት መቻቻል እሴት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ይህ ነው የሚባል ራሱን የቻለ ጥናትና ምርምር አልተካሄደም፡፡ ከሃይማኖት ጋር በተገናኘ የተካሄዱ በርካታ ጥናቶች ቢኖሩም፤ ዋና ዓላማቸው ግን በሃይማኖቶቹ አነሳስ፣ አገባብና ሥርጭት፣ ስለ ሃይማኖቶቹ አስተምህሮ ወይም መርህ፣ ሃይማኖቹ ከቤተ-መንግሥቱና ከየቤተ-እምነቶቹ ጋር ስለነበራቸው ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

እንዲሁም ሃይማኖቶቹ ስለገጠሟቸው መልካምና መጥፎ አጋጣሚዎች የሚያትቱ ናቸው፡፡ በተለይ የብዙዎቹ ጥናቶች ትኩረት በክርስትናና እስልምና ሃይማኖት መካከል የነበረው ግጭትና ፉክክር ነው፡፡ በዚህም እነዚህ ቀደምት ጥናቶች ግንኙነታቸው በዋናነት ከጀማው ህዝብ ጋር ሳይሆን ከፖለቲካው፣ ከኢኮኖሚውና ከሃይማኖቶቹ ሊሂቃን (Elites) ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ (ዝርዝሩን በጥናቱ አስፈላጊነትና በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ውስጥ ይመልከቱ)፡፡ በአንፃሩ የዚህ ጥናት መነሻ (ትኩረት) የእሴቶቹ ባለቤቶች በሆኑትና እሴቶቹም በሚሰሩበት በህዝቡ አኗኗር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በማኅበረሰቡ የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ወይም የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በዚህ መሠረት የዚህ ጥናት ዋና የምርምር ርዕሰ ጉዳይ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶችን ምንጭ፣ መገለጫዎችና ፋይዳ መርምሮ መግለጽ ነው። ምርምሩ የሚካሄደው በፎክሎር የእውቀት ዘርፍና የምርምር ሳይንስ አማካይነት ሲሆን፤ የምርምሩ አካባቢ ደግሞ ወሎ ነው። የሚጠኑት የማኅበረሰብ ክፍሎችም የአካባቢው ነዋሪዎች የሆኑ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው። ለጥናቱ ነዋሪዎቹ የተመረጡበት ዋና ምክንያት ለሃይማኖት መቻቻል እሴት መሠረት የሆኑ ልዩ ልዩ የጋራ መገለጫዎች ስላሏቸው ነው። ከቦታ አንፃርም እንዲሁ በኢትዮጵያ በሃይማኖት መቻቻል እሴቶች ከሚጠቀሱ አካባቢዎች መካከል አንዱ ወሎ በመሆኑ ነው (Mesfin 1991: 18; Fekadu 1973: 45; Østebø 2008: 183; Husssein 1994: 796; Kalklachew 1997: 80)::

1.1፦ የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት ስድስት ምእራፎች አሉት። ምእራፍ አንድ የጥናቱን መግቢያ ጨምሮ፤ ጥናቱ የሚካሄድበት አካባቢና ማኅበረሰብ አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ ተብራርቶ የቀረበበት ክፍል ነው። በዚህም በጥናቱ መግቢያ የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ምን እንደሆነ ተብራርቷል። በጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ ውስጥ ደግሞ የአካባቢውንና የማኅበረሰቡን ትውፊቶች ወይም እሴቶች ሊያሳይ የሚችል ምስል ለመፍጠር ተሞክሯል። እንዲሁም ጥናቱ የሚሞላው የጥናት ክፍተት ወይም ጥናቱ ያመጣል ተብሎ የሚገመተው አዲስ ነገር ምን ሊሆን እንደሚችል የተብራራው በዚህ ምእራፍ በጥናቱ አስፈላጊነት (statement of gap) ውስጥ ነው። ከዚህም ሌላ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ ዓላማዎች፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ ፋይዳ፣ ወሰን፣ የጥናቱ ውስንነቶች እንዲሁም በዚህ ጥናት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተበጁላቸው መፍትሄዎች የተብራሩት በዚህ ምእራፍ ውስጥ ነው።

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የቀረበው የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተዛማጅ ጥናቶችን ለመመርመር የተሞከረው የተወሰኑ ጥያቄዎችን መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህም በዋናነት ቀዳሚዎቹ አጥኚዎች ምን አጠኑ? አጥንተውስ ምን አገኙ? ምን ክፍተት ደፈኑ? ምን አይነት ክፍተትስ አለባቸው? የሚሉት ነጥቦች ናቸው። ባንፃሩ ይኸኛው ጥናት ሊደፍነው ወይም ሊሞላው የሚችለውን ክፍተት አጉልቶ ለማሳየት ተሞክሯል። ባጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በሃይማኖት መነሻ በመላው ኢትዮጵያ፣ ከዚያም በወሎና ባካባቢው ላይ የተካሄዱ ጥናቶችን ጨምሮ፣ በሃይማኖታዊ እሴቶች (ትውፊቶች)፣ በሃይማኖት መቻቻል እና በሃይማኖት ግጭቶች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ተመርምረዋል። ክለሳ የተካሄደባቸው እነዚህ

ጥናቶች በኢትዮጵያና በዓለም አቀፍ ደረጃ በተካሄዱ የጥናትና ምርምር ሴሚናሮች ላይ የቀረቡ ጽሑፎችን ጨምሮ፤ በዋናነት ለሁለተኛና ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ የምርምር ሥራዎች ናቸው፡፡

ምእራፍ ሦስት የጽንሰ-ሃሳብ፣ የንድፈ-ሃሳብ እና የጥናቱ ዘዴዎች የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ የጽንሰ-ሃሳብ ማብራሪያዎቹ ከፎክሎር ጋር የተገናኙ መሠረታዊ ነጥቦች ናቸው፡፡ እነዚህን ነጥቦች አብራርቶና ፈር አስይዞ መሄድ ለዚህ ጥናት ከፍተኛ ፋይዳ ስላለው ጽንሰ-ሃሳቦቹን ማብራራት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ተብራርተው ቀርበዋል፡፡ ጥናቱ የትኛውን ንድፈ-ሃሳብ መሰረት በማድረግ እንደተጠና፣ ወይም ጥናቱ የተመራበትና መረጃዎቹ የተተነተኑበት ንድፈ ሃሳብ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ቀርቧል፡፡ የቀረበው ንድፈ-ሃሳብ በዋናነት ዓውዳዊ ንድፈ ሃሳብ ሲሆን፤ በውስጡ ሊካተቱ የሚችሉ የክዋኔ (performance)፣ የጠቀሜታ (functional)፣ የትርጓሜ (interpretive) እና የእውቀት (cognitive) ንድፈ ሀሳብ መርሆዎችም እንደ አስፈላጊነቱ ጥናቱ የተገለገለባቸው የንድፈ ሃሳብ መርሆዎች ናቸው፡፡ የጥናቱ የአጠናን ዘዴ የተብራራው በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሲሆን፤ የዘዴው አይነት፣ ንድፍ፣ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ስልቶች ሁሉ በዚሁ ምእራፍ ውስጥ ተካተው ቀርበዋል፡፡

የምዕራፍ አራት ዋና ዓላማ ደግሞ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ይህ ጥናት በሚካሄድበት ዓውድ ውስጥ ከወሎዬዎች አጠቃላይ፤ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር የተገናኙ በአብዛኛው ፎክሎራዊ የሆኑ እሴቶችን በመመርመር ለምዕራፍ አምስትና ለምዕራፍ ስድስት መሰረት መጣል ነው፡፡ በመሆኑም የምእራፍ አራት ገለፃና ትንታኔ በዋናነት የማኅበረሰቡን ባህላዊና ማኅበራዊ ዓውድ (Socio-Cultural Framework) የሚመለከት ርዕሰ-ጉዳይ ነው፡፡

የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ በእምነቶቹ ተከታዮችና በሃይማኖቶቹ ትውፊቶች አማካይነት እንዴት እንደሚገለጽ የተለያዩ አብነቶች ቀርበው የተመረመሩት በምዕራፍ አምስት ውስጥ ነው፡፡

በምእራፍ ስድስት ውስጥ ደግሞ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ በወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ብሂል አማካይነት እንዴት እንደሚገለጽና ምንን እንደሚያሳይ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የምርምሩ ዋነኛ ትኩረት ደግሞ የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር መገለጫ የሆኑት የጉርብትና (Neighbourhood) ትውፊቶች ናቸው፡፡ በመጨረሻም

የጥናቱ ማጠቃለያ፣ ይሁንታዎችና ጥናቱ የተገለገለባቸው ዋቢ-መፃሕፍት ተጠቅሰዋል፡፡

1.2፦ አካባቢያዊ ዳራ

ቀደምት አጥኚዎች እንደዓፋት ወሎ መጠሪያ ሥያሜውም ሆነ ወሰኑ በተለያዩ ጊዜያት ሲቀያየር የኖረ የኢትዮጵያ ክፍል ነው፡፡ በዚህም የወሎ ወሰን አንድ ጊዜ ሲሰፋ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲጠብ የኖረ አካባቢ ነው፡፡ ቀደም ባሉት ዘመናት የወሰን አከላለልና አጠራር መሰረት ወሎ በሰሜን ከበጌምድርና ከትግራይ፣ በምዕራብ ከጎጃም፣ በደቡብ ከሸዋ፣ በምስራቅ ከሐረርጌ ጠቅላይ ግዛቶች ወይም ክፍለ ሀገራት ጋር ይዋሰን ነበር (Gashawe 2003: 3)፡፡ በተመሳሳይ መጠሪያ ሥያሜውም፤ ላኮመልዛ፣ ቤተ-አምሐራ፣ ወሎ፣ ወሎ አውራጃ፤ ወሎ ጠቅላይ ግዛት፣ ወሎ ክፍለ ሀገር እና አሁን ደግሞ ሰሜንና ደቡብ ወሎ በመባል ይጠራል (እንደላይኛው 3)፡፡

"ወሎ" የሚለው መጠሪያ ሥያሜ ከኦሮሞ መስፋፋት ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ግንኙነቱም የኦሮሞ ጎሳ ከሆነው ከባሬንቱማ በኩር ልጅ ከከረዩ ጋር ነው፡፡ ይኸውም ከረዩ ከነበሩት ስድስት ልጆች መካከል ሁለተኛ ልጅ ከሆነው ከ"ወሎ" ጋር የእትብት ዝምድና አለው፡፡ ዝምድናውም ከመጠሪያ ስሙ የሚጀምር ነው፡፡ ምክንያቱም "ወሎ" የያዘው አካባቢ ሁሉ በስሙ የሚጠራ "የሥሙ መጠሪያ" ሥያሜ ነው (Rukya 2013: 28)። ይህንንም አለቃ ታየ "አገሩ ጥንት ላኮመልዛ ይባል ነበር፡፡ የወሎ ልጆች ከያዙት በኋላ ግን ያገሩን ስም ለውጠው ባባታቸው ስም ወሎ አሉት" በማለት ጽፈዋል (ታየ 1958 ዓ.ም.፤ 40)፡፡ (ለበለጠ ማብራሪያ ገጽ 114-115 ይመልከቱ)

ወሎ በኢትዮጵያ ታሪክና ባህል ውስጥ ሰፊ ቦታ ያለው የኢትዮጵያ ክፍል ነው። ወሎ የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች መኖሪያና የኢትዮጵያ ባህል፣ ወግና ልማድ መሰረት ከሆኑ አካባቢዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ወሎ የጥንታዊና ታሪካዊ ሥፍራነቱን በግልጽ የሚመሰክሩ በዓለም ደረጃ የሚደነቁና የሚታወቁ የጥንታዊ ቅርሶች ባለቤት ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች አማካይነት የማኅበረሰቡ ጥበብ፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ዳብሮ፤ ብዙ ታሪካዊና ጥንታዊ የሆኑ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሃብቶች የሚገኙበት ቦታ በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ወሎ የራሱንና የአዋሳኞቹን ብሔረሰቦች ባህል፣ ወግና ልማድ ጭምር አጣምሮ የያዘ በመሆኑ የበርካታ እሴቶች ባለቤት ነው፡፡ ባንፃሩ በርሃብ፣ በድርቅና በቸነፈርም ከኢትዮጵያ ህዝብ አልፎ የዓለም ህዝብ ወሎን አይዘነጋውም። ለወሎ አንብቷል፤ ለወሎ እረድቷል፤ በወሎም ተዝናንቷል።

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት ውስጥም የወሎ ድርሻ ከፍተኛ ነው:: ለአብነት ወሎ ከዛጌ ሥርዎ- መንግሥት እስከ ሰለሞናዊው ሥርዎ-መንግሥት (ለአፄ ይኩኖ አምላክ) መነሻ በመሆን አገልግሏል:: ወሎ የወረሂመኖ ኢማሞችን (ማመዶች) እና የየጁ ወረሴህዎችን (ዘመነ መሳፍንት) አስተናግዷል:: የአፄ ቴዎድሮስ ዳግማዊ እና የአፄ ዮሐንስ አራተኛ ሥርአተ-መንግሥታትም ወሎን ጎሻሽመውት አልፈዋል:: አፄ ምኒልክ እና አፄ ኃይለ ሥላሴም ከወሎ ሕዝብ ጋር በአምቻና ጋብቻ ተዛምደው የየራሳቸውን አሻራ ትተው አልፈዋል (Trimingham 1965; Taddesse 1972; Asnake 1983; Fekadu 1990; Hussein 2001; Gashaw 2003; Crummey 1975)::

ወሎ የሙዚቃና የጥበብ አገር ነው:: መንፈሳዊው መንዙማ[8] እንደ መስኖ ውሃ የሚፈስበት፣ ሃገረሰባዊው ሙዚቃ እንደ ጠጅ የሚንቆረቆርበት ስፍራ ነው ወሎ:: ለአብነት ወሎ የትዝታ፣ የባቲ፣ የአምባሰል እና የአንቺ ሆዬ ለኔ የሙዚቃ ቅኝቶች ምንጭ ነው:: ወሎ የውበት፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የደግነትና እንግዳ ተቀባይነት ምድር ነው::[9] ስለ ወሎ ውበት እንዲህ ሲሉ ተቀኝተውለታል::

> አገሯ ወዲያ ነው ወደ መሃል የጁ
> ሲሠራት የዋለው እምላክ በቀኝ እጁ (የወሎ የጋራ ሕዝባዊ ግጥሞች)[10]

ወሎ በሃይማኖት፣ በቋንቋና በባህል የሚለያዩ ህዝቦች በሰላምና በመቻቻል የሚኖሩበት አካባቢ ብቻ ሳይሆን፤ አንዱ ከሌላው በመጋባት በደምና በሥጋ የተዋሀዱበትና በእትብት ዝምድና የተሳሰሩበት መሬት ነው:: በወሎ ክርስቲያን ወይም ሙስሊም መሆን ልዩነትን አያመለክትም:: ለአብነት ቄስ አህመድ ወይም መምሬ ጌታቸው መሐመድ አለያም ቀሲስ ዮሴፍ ኢድሪስ፣ ሼህ ገብሬ፣ አለቃ ይማም፣ ከበደ መሐመድ፣ መኮንን ሐሰን፣ ካህሳይ ዓሊ፣ ዮሐንስ መሐመድ... ወዘተ የሚሉት መጠሪያ ስሞች የእስላም ወይም የክርስቲያን መጠሪያዎች ናቸው:: "ባባቱ ገብረየስ በእናቱ ፋጡማ" የሚለው አባባል የሚሰራውም ለወሎዬዎች ነው (Mesfin 1991: 18-19; Rukya 2013: 26-33)::

---

[8] "መንዙማ" የእስልምና እምነት ተከታዮች መንፈሳዊ ዜማ፣ ውዳሴ፣ ምሥጋና "Islamic panegyrics". (Hussein 2001: 2005).

[9] ባንዛሩ "ከወሎ ጎረቤት ይሻላል ባዶ ቤት" በሚል ፎክሎራዊ ብሂል የወሎ ሰው ሲገለጽ ይሰማል:: ነገር ግን ለዚህ አባባል በጥናት የተረጋገጠ መነሻ ምክንያት እስካሁን አልተገኘም::

[10] በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱትሥነ-ቃሎች ወይም ቃላዊ-ግጥሞች በሙሉ የጋራ የሆኑ ሕዝባዊ ግጥሞች ኖቸው:: በመሆኑም ንብረትነታቸው የህዝብ ነው:: ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ ከቃላዊ ግጥሞቹ ቀጥሎ የተጠቀሱት ግለሰቦች ወይም መረጃ አቀባዮች ቃላዊ ግጥሞቹ የተገኙባቸው ምንጮች እንጂ፣ የቃላዊ ግጥሞቹ ባለቤቶች ወይም ደራሲያን አለያም ገጣሚያን አደሉም:: እንዲሁም አጥኚው ከዚህ በኋላ ምንጭ ሳይጠቅስ እሱ የሚያውቃቸውን ቃላዊ ግጥሞች ሲጠቀም "የወሎ የጋራ ህዝባዊ ግጥሞች" ማለቱ ነው::

በወሎ እስላም ወይም ክርስቲያን መሆን ትዳር መስርቶ ልጅ አፍርቶ በአንድ ጣሪያ ስር ከመኖር አያግድም:: በወሎ ሃይማኖት ባል ወይም ሚስት አለያም ልጆች የፈለጉትን እምነት ከመከተል አይከለክልም (Mesfin 1991: 19):: በሀዘን፣ በደስታ፣ በሥራ፣ በእድር፣ በእቁብ፣ ባጠቃላይ በየትኛውም የማኅበራዊ ግንኙነት ሃይማኖት በወሎ የልዩነት ምንጭ አይደለም:: ልዩነት ቢኖር በአምልኮ ስርአትና አንዱ ያረደውን ሌላው አለመብላቱ ብቻ ነው:: ነገር ግን በወሎ ሁሉም የየራሱን ፀሎት አድርሶ በአንድ ማዕድ መመገብ ባህል ነው:: "አርሂቡ" በወሎ የዚህ እሴት መገለጫ ነው (Berhanu 1998; Rukya 2013):: አንዱ ያረደውን ሌላው አይበላም ሲባልም ቄስ ወይም ሼህ የባረከውን ለማለት እንጂ፤ በወሎ የሚዜ ባህል መሠረት ክርስቲያን ወይም ሙስሊም ሚዜ ያረደውን ሌላው እንዲበላ የተፈቀደ ነው (Kalklachew 1997: 47):: የወሎ ህዝብ ራሱን የሚጠራው "ወሎዬ" በማለት ነው:: ተወልዶ ባደገበት አካባቢ መጠራት ሲፈልግ ደግሞ "የጁየ፣ ላስቴ፣ ሳይንቴ፣ ደላንቴ፣ ዋድሌ...ወዘተ" በማለት ራሱን ይገልፃል::

በወሎ ውስጥ ከሁለቱ እምነቶች ጎን ለጎን በርካታ ሃገረሰባዊ ዕምነቶችም ይከወናሉ:: እነዚህ ሃገረሰባዊ ዕምነቶችና ልማዶች ደግሞ ከሁለቱ እምነቶችና የእምነቱ ተከታዮች ጋር የጠበቀ ቁርኝት አላቸው:: በወሎ በሃገረሰባዊው ዕምነትና ልማድ አማካይነት የተዘራው ያፈራል፤ የመከነው ይወልዳል:: የተጣላው ይታረቃል፤ የራቀው ይቀርባል:: ያጣው ያገኛል፤ የነገደው ያተርፋል፤ ተብሎ ይታመናል:: "በሼሆቹ፤ በደጎቹ ወሎ መጀን!" እንዲሉ:: በእስልምናው በኩል እንደ ጀማ ንጉሥ፣ ገታ፣ ደባቶች፣ ዳና፤ ከረምና መርሳ አባገትየ ያሉት ቅዱሳን ስፍራዎች ለሁለቱ እምነት ተከታዮች እንደበረከት ምንጭ ተደርገው ይቆጠራሉ:: የፈውስ ተምሳሌቶችም ናቸው (Hussein 1990; 2001):: በክርስትናው በኩል ደግሞ እንደ ላሊበላ፣ ደብረ አቡነ አሮን ገዳም፣ ገነተ-ልዑል ማርያም፣ ግሼን ማርያም፣ ተድባበ ማርያም፣ አትሮንስ ማርያም፣...ወዘተ ተጠቃሽ የክርስትናው የትውፊት ቦታዎች ናቸው::

በረኸም ታሪኩ እንደሚታወቀው ወሎ የዑለሞች[11] መፍለቂያ ነው:: ወሎ የወልይ[12] አገር ነው:: የጀማ ንጉሥ ሼህ፣ የዳናው ሼህ፣ የከረሙ ሼህ፣ የኢጋምሳው ሼህ፣ የአባ በድሩ ሼህ፣ የአባ ገትየው ሼህ፣ የጫሊው ሼህ፣ የገራዶው ሼህ፣ የአልቡኮው ሼህ፣ የተንታው ሼህ፣ የቃሉው ሼህ እና ሌሎች የወሎ ደጋጎችና አራት ዓይናዎች መፍለቂያቸውም መኖሪያቸውም ወሎ ነው:: የነሱ ከራማም ሆነ በረከት ከሁለቱ እምነት ተከታዮች ጋር በእጅጉ የተሳሰሩ ናቸው:: ለአብነት በእነሱ አማካይነት የተጣላው ይታረቃል፤ ቂም የቋጠረው ቂሙ ይሽራል:: የጠፋው ይገኛል፤

---

[11] "ዑለሞች" የእስልምና ሃይማኖት ምሁራን ወይም ሊቃውንት፤ (ጌታቸው 1984 ዓ.ም፤18)::

[12] "ወልይ" የእስላም ብፁአን (ነብይ) ወይም ቅዱሳን አባቶች፤ (Muslim Saints) (Fkadu 1990:236).

የተሰወረው ይገለጣል። በዱዓቸውና በቱፍታቸው የታመመው ይድናል፤ የተለከፈው ይፈወሳል። እንዲሁም ወልዮቹ ከመንፈሳዊው ተልእኳቸው በተጨማሪ የባህላዊ እሴቶቹ መሰረቶች ናቸው።

በወሎ አድባሩ፣ አውጋሩ፣ ወልዩ፣ አበጋሩ፣ ሼሁ፣ ቃልቻው፣ ደረሳው፣ ደብተራው፣ ባለ ውቃቢው (ጠንቋዩ) መጠሐፍ ገላጩም ሳይቀር፤ ባጠቃላይ ማኅበረሰቡ ሁሉ ከሀገረሰባዊ ልማድ ወይም ከፎክሎር ጋር የጠበቀ ቁርኝት አላቸው። ለምሳሌ ምርቃን፣ እርግማን፣ ሰላምታ፣ ቤተሰባዊ ትስስር፣ ድግስ፣ ጀባታ፣ ውቃቢ (አውሊያ)፣ አግማስ፣ የሾተላይ፣ ውቅራት (ንቅሳት)፣ ዋርሳ፣ ሙሃለል፣ ሲርያ፣ ተርቲም፣ ወዳጃ (ሃጀት)፣ እርፎ መረባ፣ ዱበርቲ፣ ፋጢማ ቆሪ፣ ጥንቆላ፣ ወንፈል፣ ጂጊ (ደቦ)፣ አድባር (ቆሌ)፣ ገድ፣ ፋል፣ ቡዳ፣ ጠጠር ጣይ፣ መራ-መውጣት፣ ወፋ ውጊያ፣ ሽምግልና...ወዘተ የአካባቢው የሃገረሰባዊ ልማድ ዘርፎች ናቸው (ጌታዋ፣ 2004 ዓ.ም)።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት ምንም እንኳን ከግማሽ ምእተ-ዓመት ወዲህ በተደጋጋሚ በድርቅና ችነፈር የተመታ አካባቢ ቢሆንም በተፈጥሮ ሃብትና በአየር ንብረት ረገድ ወሎ የታደለ መሬት ነው (Mesfin 1991; ጌታቸው 1984፤ ዓ.ም.)። ወሎ የንግድ መፍለቂያ፣ መነኻሪያና መተላለፊያ መስመርም ነው (Hussein 2001)። ወሎ አየር ንብረቱ ተስማሚ ነው። በወሎ ውርጭ፣ ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ ቆላና በረሃማ ተብለው የሚከፈሉ አምስት አይነት የአየር ንብረት ያላቸው አካባቢዎች ይገኛሉ። እንደ አየር ንብረቶቹ ሁኔታም ሁሉም የአዝርዕት (የሰብል) አይነቶች፣ የቤት፣ የዱር እንስሳት እና እጽዋት ይገኛሉ።

በአካባቢው በኢትዮጵያ ብቻ ከሚገኙ እጽዋት እንደ ጅብራ ከዱር እንስሳት ደግሞ የጭላዳ ዝንጀሮና የሰሜን ቀይ ቀበሮ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ብቻ ከሚገኙ የአዕዋፍ ዝርያዎች ውስጥም በርካታዎች በአካባቢው ይገኛሉ (Gashaw 2003; Fekadu 1990; ጌታቸው፣ 1984 ዓ.ም)። ወሎ በጥቅሉ በእንስሳትና በሰብል ምርት የታወቀ አካባቢ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ። ትርሚንግሃም እንደፃፉት። "በየጁ ከጦር መሳሪያ በስተቀር ሁሉም ሞልቶ የተትረፈረፈ ነው። የጁ በምርቱና በእደ ጥበብ ውጤቱ የታወቀና ለኑሮ ተስማሚ አካባቢ ነው።" በማለት ገልፀውታል (Trimingham 1965; 195)። ወሎ በሥጋ፣ በማርና ወተትም ብዙ ተብሎለታል፤ ስንኝ ተቋጥሮለታል፤ ዘፈን ተቀንቅኖለታል። የሚከተሉትን ስንኞች ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

አንባሰል ለገደል ምን ያሸሚጥጡታል፤
ገብስ ባይዘሩበት ማር ይቆርጡበታል፤
ፈረስ ባያሥጋልብ፤ ልጅ ይወጣበታል።

የእህል አገር ሃራ፣ የጥጥ አገር ጋፍራ
ጣይ ሲሆን አቢራ፤ ዝናብ ሲሆን ለሳ መጋሌ ስመራ።።ብለው ይቀኙለታል።።

ነዋሪዎቹ በዚህ መልክ የሚገልጹት ወሎ ቆላማው አካባቢ በቀንደ ረግሾሞቹ "ሃርሙ" ተብለው በሚጠሩት የቁም እንስሳቱ ይታወቃል። በቆላ በግና ፍየሉም ተጠቃሽ ነው። በደጋማው አካባቢ ደግሞ በደጋ በግና ፈረስ ወሎ ስሙ የተጠራ አካባቢ ነው። የፈረስ ግልቢያና የፈረስ ላይ ውጊያ በወሎ የተለመደ ብቻ ሳይሆን ፈረስ የአካባቢው ታዋቂ ግለሰቦች መለያና መጠሪያም ስም ነበር[13] (Hussein 2001)።

በወሎ ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ሐይቆችና ወንዞች ይገኛሉ። ለአብነት ተከዜ፣ ኧርጣ፣ ጥርጊያ፣ ጎሊና፣ ጎቱ፣ አላውሃ፣ ጨረቲ፣ መሬ፣ ሆርማት፣ ቦርከና፣ በሽሎና ገራዶ ወንዞች እና የሎጋ ሐይቅ ይጠቀሳሉ (ጌታቸው፣ 1984 ዓ.ም.)። እነዚህ ወንዞችና ሐይቆች ከአካባቢው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና ውበት አኳያ ከመስኖ አገልግሎት አልፈው ለዘመናዊ መናፈሻና ቱሪዝም አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ሃብቶች ናቸው። በዚህ መሰረት ይሄ ጥናት የሚካሄደው ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አካባቢያዊ ዳራዎች ውስጥ ነው።

1.3፦ የጥናቱ አስፈላጊነት (statement of gap)

በአንድ የምርምር ርእሰ ጉዳይ ላይ በተለያዩ የእውቀት ዘርፎች አማካይነት ጥናትና ምርምር ሊካሄድ ይችላል።። በሌላ አገላለጽ አንድን ርዕሰ ጉዳይ ይበልጥ ለማረጋገጥ ጥናቶች ተደጋግመው ሊደረጉ ይችላሉ።። መሠረታዊው ጉዳይ ግን ተከታዮቹ ጥናቶች የቀደሙት ጥናቶች ያልደፈኑት ወይም ያልሞሉት ክፍተት ምን እንደሆነ በግልጽ በማሳየት ያንን ክፍተት መሙላት መቻላቸው ነው።። ወይም ቀዳሚዎቹ ጥናቶች ያላሳዩት፤ ባንዳሩ እነሱ (ተከታዮቹ ጥናቶች) አዲስ ነገር ማሳየት መቻላቸው ነው።። በዚህ መሠረት የዚህ ንዑስ ርዕስ ዋና ዓላማም እነዘዚህን ነጥቦች በግልጽ ማሳየት ነው።። የሃይማኖት መቻቻል እሴት በኢትዮጵያ ከአንዱ ትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ ሲወርድና ሲወራረስ መጥቶ አሁን ካለንበት ዘመን ላይ ደርሷል። የዚህ አይነቱ ተከባብሮና ተቻችሎ የመኖር ባህል ኢትዮጵያውያን ከሌላው ዓለም ተለይተው የሚታወቁበት እሴት ነው። በዚህም ኢትዮጵያውያን እንደ ቅርሶቻቸውና የተፈጥሮ ሃብቶቻቸው ሁሉ በሃይማኖት መቻቻል እሴቶቻቸውም ጭምር ይታወቃሉ።። (Ephraim 2008: 120; Elrich 2003: 383; Abdi 2007፡1-4)። ተቆርጦ የቀረ ያለ ይመስላል።።

---

[13] በፈረስ ስም መጠራት በወሎ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ነገሥታትና የጦር መሪዎች መጠሪያም እንደነበር ድርሳናት ያስረዳሉ። ይህ ልምድ ግን ከ1966 ዓ.ም ወዲህ የቀጠለ አይመስለኝም።

ምንም እንኳን ቀደምሲል አንደተጠቀሰው በኢትዮጵያ በሃይማኖት መቻቻል እሴት ላይ እራሱን የቻለ ጥናትና ምርምር ባይካሄድም (ውዱ 2004 ዓ.ም.፤ 218)፤ በሀገሪቱ በተለይ ከክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ጋር በተገናኘ በሀገር ውስጥና በውጭ አገር ምሁራን አማካይነት በርካታ ጥናቶችና ምርምሮች ተካሂደዋል:: (Trimingham 1965; Abir 1968; 1978; Taddesse 1972; Caulk 1972; Crummey 1975; Merid 1974; Hussein; 1984; 1992; 2001; 1984; 1988; 1989; 1990; 1994; 2006)፡፡ እነዚህ ጥናቶች በሁለት ምድብ ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ:: የመጀመሪያዎቹ ምድብ ባጠቃላይ ሃይማኖቶቹን ከታሪክ፣ ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከባህልና ማኅበራዊ ጉዳዮች አንፃር ያጠኑ ናቸው:: የጥናቶቹ ዋና ሃሳብ ወይም ጭብጥ ደግሞ የቤተ እምነቶቹን ታሪካዊነት ጨምሮ፤ የሃይማኖቶቹን ታሪካዊ ዳራ (አነሳስና ስርጭት) ሃይማኖቶቹ ስለገጠሟቸው መልካምና መጥፎ አጋጣሚዎች፣ የፖለቲካውና የሃይማኖቶቹ ግንኙነቶች፣ በሃይማኖቶቹ መካከል ስለነበረው ፉክክርና ግጭት፣ እንዲሁም በየዘመኑ ስለነበሩና አሁንም ድረስ ስላሉ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች የሚገልጹ ናቸው (Hussein 1984; Ephraim 2008; Ahmed 2008)::

በሁለተኛ ደረጃ ሊመደቡ የሚችሉት የምርምር ስራዎች ትኩረት ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ በሃይማኖት ሰበብ በተከሰቱ ግጭቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: የነዚህ ጥናቶች መሰረታዊ ጭብጥ በሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትናና እስልምና እምነት ተከታዮች መካከል በሃይማኖት ሰበብ የተቀሰቀሱ ግጭቶችን መመርመር ነው:: በዚህም ጥናቶቹ የግጭቶቹን መንስዔና ያስከተሉት ውጤት ምን እንደነበር መርምረው ገልፀዋል (Tekalign 2008; Zelalem 2010; Mohammed 2010; Haileyesus 2011) ::

ከላይ በሁለት ምድብ የተጠቀሱት ጥናቶች ተጠቃለው ሲመረመሩ የጥናታቸው ርዕሰ ጉዳይና ዓላማ እንደተጠበቀ ሁኖ፤ ጥናቶቹ ያልሞሉት ወይም ያልደፈኑት የጥናት ክፍተት (Research-Gap) እንዳለ ይታያል፡፡ ይኸውም እነዚህ ጥናቶች ከሃይማኖት መቻቻል እሴት አንፃር ኢትዮጵያውያን እርስ በርስ የሚገናኙባቸውን ድልድዮች ወይም እርስ በርስ የተሳሰሩባቸውን ክሮች በመመርመር ምንጫቸውን፣ መገለጫቸውንና ፋይዳቸውን አላጠኑም:: ወይም የሁለቱን እምነት ተከታዮች መስተጋብር (የእርስ በርስ ግንኙነት) አለያም የሁለቱ እምነት ተከታዮች ተቻችለው በጋራ ለመኖር የተጠቀሙባቸውንና አሁንም የሚጠቀሙባቸውን የጋራ እሴቶች

አላጠኑም፤ አልመረመሩም፡፡ በንፃሩ የእነዚህ ጥናቶች ትኩረት የሃይማኖት ልዩነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ዝርዝሩን በክለሳ ድርሳን ውስጥ ምእራፍ ሁለትን ይመልከቱ፡፡

እነዚህ ጥናቶች ሁሉም ደጋግመው እንደሚጠቅሱት ኢትዮጵያ ብዙ አይነት ባህል፣ ብዙ አይነት ቋንቋና ሃይማኖት ያላቸው ህዝቦች የጋራ መኖሪያ መዚየም ናት (Trimingham 1965: 5)፡፡ የነዚህ ህዝቦች ባህል፣ ቋንቋና ሃይማኖት ቢለያይም ባንፃሩ ተቻችለው በአንድነት፣ በሰላምና በፍቅር የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ ከአሁን በፊት ተደጋጋሚና ተፈታታኝ የፖለቲካ ውዝግቦች፣ ጦርነቶች፣ ድርቅ፣ ርሃብና ችነፈር ቢገጥማቸውም ለዘመናት አንድነታቸውን ጠብቀው ለዚህ ዘመን ደርሰዋል፡፡[14]

ለዚህ የበቁበት መሰረታዊ ምክንያት ግን እንዲሁ በአጋጣሚ ይሆናል ተብሎ አይገመትም፡፡ ይልቁንም ለዘመናት ኢትዮጵያውያንን አስተባብረውና አስተሳስረው ይዘዋቸው የሚጓዙ የጋራ እሴቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ ለኢትዮጵያውያን የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም አብሮነት መሰረት በመሆን የሚያገለግሉ ወይም ኢትዮጵያውያንን ለዘመናት ድርና ማግ በመሆን አስተባብረውና አስተሳስረው፣ አግባብተውና አስማምተው፣ እንዲሁም አዋህደው በጋራ ይዘዋቸው የሚጓዙ መሰረታዊ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች ምንጫቸው፣ መገለጫቸውና ተግባራቸው ምንድን ነው? የሚለው የምርምር ጥያቄ ከላይ በተጠቀሱት ጥናቶች አልተመለሰም ወይም አልተጠናም፡፡

በዚህ መነሻ ይህ ጥናት የሚደፍነው የምርምር ክፍተት ወሎን እና የዚያ አካባቢ ነዋሪ የሆኑ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የጥናቱ መነሻ በማድረግ ከላይ የተጠቀሰውን ጥያቄ በመመለስ ይሆናል፡፡ በሌላ አባባል የሁለቱን እምነት ተከታዮች የሃይማኖት መቻቻል ስልቶችን እና የስልቶቹ መሰረት የሆኑ የጋራ እሴቶችን በፎክሎር አማካይነት መርምሮ መግለጽ የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋነኛ የምርምር ርዕሰ ጉዳይ (Issue) የሁለቱን እምነት ተከታዮች በሰላምና በፍቅር

---

[14] ለዚህ አባባል ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ ከሚችሉ ከጥቂቶቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች መካከል አንዱ ወሎ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም በፖለቲካዊው ጉዳይ ቢሉ በኢኮኖሚያዊው፣ በሰው ሰራሽም ቢሉ በተፈጥሮ አመጣሽ ችግሮች፣ በሃይማኖታዊውም ቢሉ በዓለማዊው ጉዳይ ተፈታታኝ፣ ታሪካዊና ወቅታዊ ሁኔታዎች የገጠሙት እንደ ወሎ እና የወሎ ኗሪ ህዝብ ያለ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም የወሎ ህዝብ ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በነበሩት ዘመናት ኑሮው ሲመሰቃቀል የኖረ ህዝብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይኸም ሁኖ ወሎ በተቃራኒው የሰላምና የፍቅር ምድር ነው፡፡ የመቻቻል አድባር ነው፡፡ የሃይማኖትና የባህል አምባ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ወሎ ለዚህ ጥናት ትክክለኛ አካባቢ ይመስለኛል፡፡

በአንድነት ይዘዋቸው የሚጓዙ የጋራ እሴቶችን የሚያጠና ሁኖ፤ በጥናቱ መግቢያ ላይ የተብራራው ርዕሰ ጉዳይ ነው::

1.4፦ የጥናቱ ዳራ

የታሪክ ሰነዶች፣ የሥነ-ፍጥረት ጥናትና ቅዱሳት መፃሕፍትም ጭምር እንደሚያስረዱት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ከሌላው አለም ተለይተው የሚታወቁባቸው የራሳቸው የሆኑ በርካታ ተፈጥሯዊና መንፈሳዊ እሴቶች አሏቸው (Ephraim 2008: 8-24; Gish 1996: 3):: ተፈጥሯዊ ከሆኑት መገለጫዎች ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ የመልክዓ ምድር አቀማመጧ ነው:: በዚህም ኢትዮጵያ "የ13 ወር ፀጋ" የሚለውን ስያሜ ጨምሮ፤ አምስት በሚደርሱት የዓየር ንብረቶቿ ተለይታ ትታወቃለች::

ከዓየር ንብረቷ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ የብርቅዬ አዕዋፍ፣ የቤትና የዱር እንስሳት፣ አዝርእትና እጽዋት መገኛ ናት:: በሌላ በኩል ታላቁን የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ ጨምሮ፤ ከኤርታሌ እሳተ ገሞራ እስከ ዳሽን ተራራ የኢትዮጵያ ልዩ መገለጫዎች ናቸው:: ኢትዮጵያ ባሏት ወንዞችና ሐይቆች አማካይነት "የአፍሪካ የውኃ ማማ" የሚል ስያሜም ተሰጥቷታል:: ከወንዞች አንጻር ዓባይ፣ ተከዜ፣ ባሮ፣ ገናሌ፣ ዋቢሼበሌ፣ ጊቤ፣ አዋሽ ይጠቀሳሉ:: በሐይቆች በኩልም ጣና፣ ላንጋኖ፣ አብያታ፣ ሻላ፣ ሐዋሳ፣ አባያና ጫሞ የዚህ አባባል አብነቶች ናቸው (Bahru 1991:1-2)::

ከዚህም ሌላ ኢትዮጵያ የጥንታዊ ስልጣኔ ባለቤት፣ የጥንታዊ ሥነ-መንግሥት፣ የጥንታዊ ታሪክ፣ የጥንታዊ አኗኗር ዘይቤ፣ ወግና-ልማድ፣ የጥንታዊ ቅርስና ባህል ባለቤት ናት:: እንዲሁም የተለያዩ ቋንቋና ባህል ያላቸው ህዝቦች ተቻችለውና ተከባብረው በሰላም የሚኖሩባት አገር ኢትዮጵያ መሆኗን የማኅበራዊና የሰብአዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች ጽፈዋል:: በዚህም ኢትዮጵያ የመቻቻል እሴት ባለቤት መሆኗን አረጋግጠዋል:: የነፃነት ተምሳሌት የሚለው መገለጫም የኢትዮጵያና የህዝቦቿ መለያ እሴቶች ናቸው (Ephraim & Felder 1984: 71-83; Right 1986: 204 ; Gish 1996: 3-17; Bahru 1991: 2-4)::

በሌላ በኩል መልክ ግቡነት፣ ሰላምና ፍቅር፣ በራስ መተማመን፣ ጀግንነት፣ አገር ወዳድነት፣ መተባበር፣ መረዳዳት፣ ይቅርባይነት፣ ታማኝነት፣ ሰው አክባሪነት፣ ትህትና፣ ደግነት፣ ለሕግ ተገዥነት፣ ሥነ ምግባርና እንግዳ ተቀባይነት ኢትዮጵያውያን ተለይተው የሚታወቁባቸው እሴቶች መሆናቸውን ድርሳናት ያስረዳሉ (Munro 2002: viii):: ለአብነት የግሪካውያንን አማልእክት ጨምሮ ከተለያዩ የዓለም አገራት የመጡ ሰዎች ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል፤

በኢትዮጵያውያንም ተስተናግደዋል:: እነሱም ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን መልካምነትና እንግዳ ተቀባይነት መስክረዋል:: ለዚህም ኢትዮጵያውያን "ነውር" የሌለባቸው ህዝቦች (The Blameless Ethiopians) እስከ ማለት ደርሰዋል:: ይህንንም የዘመናችን ተመራማሪዎችም ሆኑ ከክርስቶስ ልደት በፊት የኖሩት ግሪካውያኑ ገጣሚው ሆሜር እና ታሪክ ፀሐፊው ሄሮዳቱስ ሳይቀሩ ጽፈውታል (እንደላይኛው)::

ሁለተኛው የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን መለያ የሆነው ርዕሰ ጉዳይ ደግሞ ሃይማኖታዊው አሴት ነው:: መረጃዎች እንደሚያስረዱት ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ያሉት ሦስት ቀደምትና ትላልቅ ሃይማኖቶች የሚገኙባት አገር ናት:: በመሆኑም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የአይሁድ፣ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ[15] (Erlich 2003; Ephraim 2008):: እነዚህ ጥናቶች እንደሚሉት የሃይማኖቶቹ መገኘት ብቻም ሳይሆን እምነቶቹ ከተነሱባቸው ቦታዎች ይኖሩ ከነበሩ ህዝቦች በስተቀር ኢትዮጵያውያን እምነቶቹን የተቀበሉ የመጀመሪያ ህዝቦች ናቸው::
ለዚህም ከአሪት አምልኮተ እግዚአብሔር አንፃር ንግሥት ማክዳ (ሳባ) ቀዳሚ ናት:: በክርስትናው በኩል ደግሞ በወንጌላዊው ፊልጶስ እጅ የተጠመቀው የንግሥት ሕንደኬ ጃንደርባ ባኮስ ይጠቀሳል:: በእስልምናውም እንዲሁ ኢትዮጵያዊው ቢላል ቀዳሚ ነው:: ኢትዮጵያውያን የሚታወቁት እምነቶቹን በመቀበል ብቻም ሳይሆን፤ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ባለቤት በመሆንም ጭምር ነው:: ለዚህም በርካታ መገለጫዎች አሏቸው (Ephraim 2008; Ahmed 2008; Yassin 1984; የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ 2000 ዓ.ም.፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ 1994 ዓ.ም)::

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የሃይማኖት መቻቻል ጽንሰ-ሃሳብ የመነጨው ከክርስቶስ ልደት በፊት ስድስት መቶ ዓመተ-ዓለም ቀደም ብሎ በፋርስ ንጉስ ታላቁ ሳይረስ (Cyrus) አይሁዶችን ከእንግልት ነፃ እንዲሆኑ ካደረገበት ዘመን ጀምሮ ነው:: በዋናነት ተግባራዊ ተደረገ የሚባለው ግን በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሃይማኖት የተሃድሶ ለውጥ ንቅናቄ ወይም "ሪፎርሜሽን" ዘመን ነው (ውዱ፣ 2004 ዓ.ም፤ 204-205)::

---

[15] በ2007 (እ.ኤ.አ.) የኢትዮጵያ ህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሃይማኖት ስብጥር የኦርቶዶክስ፣ የፕሮቴስታንት፣ የካቶሊክ፣ የእስልምና፣ የጥንታዊ አምልኮና ሌሎች ተብሎ በስድስት ምድቦች ይከፈላል:: በነዚህ ውስጥ ደግሞ በርካታ ስብጥሮች ይገኛሉ::

የዚህ ዘመን የሃይማኖት መቻቻል-ጽንሰ ሃሳብ መሰረታዊ መርህ ግን አንዱ ለሌላው እምነቱን በነፃነት እንዲያመልክ መፍቀድና ልዩነትን መቀበል፣ በቁጥር የበላይነት ያለው ክፍል በቁጥር አናሳ ለሆነው ክፍል የሚሰጠው ግምትና የሚኖረው ቅን አመለካከትን ጨምሮ፤ የሃይማኖት ነፃነት፣ እኩልነትና የሰዎችን ሰብአዊ መብት ሁሉ የሚያጠቃልል አስተሳሰብ ነው (እንደላይኛው፤ 204-205)::

ከዚህ አስተሳሰብ እንደምንረዳው የዚህ መርህ ቀጥታ ግንኙነት ከመንግሥትና ከሕገመንግሥት ወይም ከሕግ ድንጋጌዎች ጋር የተሳሰረ ነው:: ይህም ማለት ከእምነቶቹ ተከታዮች የእርስ በርስ ግንኙነት ጋር ሳይሆን፤ ከሊሂቃኑ ጋር የተገናኘ ነው:: ባንፃሩ በኢትዮጵያ ያለው የሃይማኖት መቻቻል እሴት ምንጩ በቀጥታ የማኅበረሰቡ ባህል ውጤት ነው:: ከራሱ ከማኅበረሰቡ ማንነት መንጭቶ ከዚያው የሚቀዳ እሴት ነው:: ወይም በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል እሴት የሚመነጨው ከሕግ ድንጋጌ ውስጥ ሳይሆን (የሕግ ድንጋጌ ቢኖርም) ከእንግዳ ተቀባይነት ዘመናትን የዘለቀ ባህል ውስጥ ነው:: ከኢትዮጵያውያን የእርስ በርስ ግንኙነት ዘይቤ ነው:: በዚህም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በኢትዮጵያ ያለ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ ከሃይማኖቶቹ አገባብ ይጀምራል (Yassin 1984)::

በዚህ መነሻ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ኢትዮጵያ ሦስቱ ሃይማኖቶች በቅድሚያ የገቡባትና የተስፋፉባት አገር ብቻ ሳትሆን፤ የሃይማኖቶቹ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ህዝቦቿ አንዱ የሌላውን እምነት በማክበር፣ ከዚያም ሲያልፍ የሃይማኖቶቹን ትውፊቶች በጋራ በመጠቀም፣ በመከባበር፣ በመተሳሰብ፣ በመተዛዘን፣ በመተጋገዝ፣ በመረዳዳት፣ በሰላምና በፍቅር ተቻችለው ለዘመናት በአንድነት አብረው የኖሩባትና አሁንም የሚኖሩባት አገር ናት (Ephraim 2008:8)::

ነገር ግን በኢትዮጵያ የተከሰቱ የሃይማኖት ግጭቶችን ባጠቃላይ በሀገሪቱ የሃይማኖት መቻቻል መኖር አለመኖር መለኪያ አርገው የሚከራከሩ አካላት አሉ:: ይህም የሆነበት ምክንያት እነዚህ አካላት በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻልን የሚረዱት ከእምነቶቹ ተከታዮች አንፃር ሳይሆን፤ ከፖለቲካና ከሃይማኖት መሪዎቹ አንፃር በመሆኑ ነው:: በግልጽ እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት በሃይማኖት ምክንያት በርካታ ግጭቶች ተከስተዋል:: ለምሳሌ ዮዲት-ጉዲት፣ አህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) እና አፄ ሱስንዮስ እንዲሁም አፄ ዮሐንስ አራተኛ ከኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች እና ከሙስሊሞች ጋር ያካሂዷቸው ግጭቶች ለአብነት ይጠቀሳሉ::

ነገር ግን በተለይ የክርስተናና የእስልምና ሃይማኖት ግጭቶች መንስዔ አንዱ የሃይማኖት ተከታይ ከሌላው የሃይማኖት ተከታይ ጋር ያደረጓቸው ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች ሳይሆኑ፤ መሰረታዊ መንስዔያቸው ሃይማኖትን ሰበብ በማድረግ የሀገሪቱን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ለመያዝ የተደረጉ ግጭቶች እንደነበሩ ጥናቶች ይገልፃሉ:: (Trmingham 1965: 65; Ahmed 2008: 140-57):: በነዚህ ጥናቶች መሰረት የሃይማኖት ግጭት ሰበብ በኢትዮጵያ የእምነቶቹ ተከታዮች ሳይሆኑ ከፖለቲካውና ከሃይማኖቶቹ ሊሂቃን (elites) ጋር የተያያዘ ነው:: በሌላ በኩል በኢትዮጵያ የተካሄዱ የሃይማኖት ግጭቶች፤ ክርስትናው ከእስልምናው፤ እስልምናው ከክርስትናው (inter Faith) ጋር ከአካሄዱት ግጭት ይልቅ፤ የሃይማኖት ግጭት ሊባሉ የሚችሉት፤ ሃይማኖቶቹ እርስ በርስ (Intra Faith) ወይም ክርስትናው ክክርስትናው እና እስልምናው ከእስልምናው ጋር ያካሄዷቸው የሃይማኖት መርህ (doctrinal) ግጭቶች በዋናነት ሊጠቀሱ እንደሚችሉ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ይገልፃሉ:: የዚህ ጥናት አቀራቢም በዚህ ሃሳብ ይስማማል::

1.5፦ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ የተለያዩ አነሳሽ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: ለምሳሌ አንድ ንድፈ ሃሳብ የጥናት መላ ምት (Hypothesis) ለመንደፍ በሚያሳድረው ተፅዕኖ፣ የአንድን ችግር ምንነት ለማወቅና መፍትሄ ለመፈለግ በሚፈጠር መነሳሳት፣ እንዲሁም ከማኅበራዊ ሕይወት አስተውሎት በሚመነጩ ስሜቶች እና ከአጥኚው ልምድ፣ ትምህርትና ስልጠና ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ (Hammersley & Atkinson 1991):: ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት በተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ምክንያት የሆኑ ነጥቦች አራት ናቸው::

የመጀመሪያው ምክንያት በዚህ ጥናት የተነሳው የምርምር ርዕሰ ጉዳይ በራሱ ሊጠና የሚችል ወቅታዊ አጀንዳ (Current Issue) በመሆኑ ነው:: ምክንያቱም የሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ዓለማቀፋዊ ይዘት ያለው አጀንዳ ነው:: በዚህም የሃይማኖት መቻቻል እሴቶችን አጥንቶ ፋይዳቸውን መግለጽ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለሌሎች አገሮችና ዜጎችም ጭምር ምሳሌ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል:: በመሆኑም ጥናቱ ይኖረዋል ተብሎ የሚገመተው ፋይዳና በጥናቱ ሊገለገሉ ይችላሉ ተብለው የተገመቱ አካላት የዚህ ጥናት ተጨማሪ አነሳሽ ምክንያቶች ናቸው:: ዝርዝሩን ከጥናቱ ፋይዳ ይመልከቱ::

ከዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተገናኘው ሁለተኛ አነሳሽ ምክንያት ደግሞ በተደጋጋሚ ከጥናቱ አቅራቢ ማኅበራዊ ሕይወት አስተውሎት ከተቆሰቆሱ አነሳሽ ምክንያቶች የመነጨ ጉዳዮች ናቸው:: ምክንያቱም የዚህ ጥናት አቅራቢ ተወልዶ ያደገው ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ነው[16]:: በዚህም የተለያዩ የማኅበራዊ ሕይወት አስተውሎቶች አሉት:: ለአብነት አጥኚው ባደገበት አካባቢ በሙስሊሙ ሼህ ሲመረቅ፣ በክርስቲያኑ ቄስ ሲባረክ አድጓል:: የሁለቱ እምነት አባቶች ለእሱ ልዩነት አልነበራቸውም:: ቤተሰቦቹም የክርስትና እምነት ተከታዮች ቢሆኑም፤ "እነ ሼህ እከሌን ወይም እነ እመት ፋጡማን ፀበል ቅመሱ ብለህ ጥራ!" ተብሎ በተደጋጋሚ ተልኮ ያውቃል:: ፀበል ቅመሱ ሲባልም ጠላ ብቻ ተዘጋጅቶ ሳይሆን ለሙስሊሙም የሚሆን "ቡቅሬ" ተዘጋጅቶ ነው:: ባንባሩ ቤተሰቦቹም ሆኑ እሱ በአረፋ፣ በመውሊድ፣ በረመዳን እና በሌሎች በዓላት ወቅት ወደ ሙስሊም ጎረቤቶች ተጠርተው ሲሄዱ ያስታውሳል::

እንዲሁም በእሱ የእድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ የእስልምና እምነት ተከታይ እኩዮቹ ጋር በጥምቀት አብረው ጨፍረዋል፤ ገናንም አብረው ተጫውተዋል:: ጅራፍ በጋራ ተጋርፈዋል፤ ሆያ ሆዬንም አብረው ብለዋል:: የቡሄ ዳቦ እና የአብዶየ ቂጣ[17] እየተጋገረላቸው በጋራ በልተዋል:: በዚህ በተሳሰረ ግንኙነት ምክንያትም በመጠሪያ ስምም ሆነ ባለባበስ ወይም ባጊያጊያጥ እሱም ሆነ ሙስሊም ጓደኞቹ ምንም አይነት ልዩነት አልነበራቸውም:: የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት እና የክርስቲያን የሙስሊም ልዩነት መለያም አልነበሩም:: ለአብነት የዚህን ጥናት አቅራቢ ወላጅ ክርስቲያን አባቱ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲሄድ የሚገፋፉትን ያህል ሙስሊም አዛውንት ጎረቤቱም ያባቱን ያህል ቤተ ክርስቲያን መሄድ እንዳለበት ምክር ለግሰውት ያውቃሉ::

ባጠቃላይ በእድሜም ይሁን በያታ የሁለቱ እምነት ተከታዮች የጋራ የሆኑ ገናን እሴቶች፣ ምግባሮችና የሰው ለሰው ግንኙነቶች በርካታ ነበሩ:: ከዚህ አንፃር ጥናት አቅራቢው በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ ተወልዶ ማደጉ አንድ ጥያቄ እንዲያነሳ ምክንያት ሁኖታል:: ይኸውም

---

[16] የፎክሎር ጥናት በተወላጁ ወይም በውስጣዊ (Emic/ Insider) አንፃር ሲጠና የራሱ የሆኑ በርካታ ጠንካራ ጎኖች ያሉትን ያህል፣ ክፍተቶችም እንዳሉበት የሰብአዊ ሳይንስ ምሁራን ይገልጻሉ:: ተመራማሪው የእሴቶቹን አወንታዊ ጎን ብቻ መመልከቱ ወይም ከመረጃ አቀባዮች ያገኛቸውን መረጃዎች ሳይጠራጠር መቀበሉ ከክፍተቶቹ መካከል ለአብነት የሚጠቀሱ ነጥቦች ናቸው:: ነገር ግን በፎክሎር ጥናት ይህንን ክፍተት ለመሙላት የተለያዩ ሚዛንማዊ አማራጮች አሉ::

[17] "የአብዶየ ቂጣ" ማለት በወሎ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በዕለተ-ረቡዕ ለሰዱቃ ሥርዓት የሚጋገር ቂጣ ነው:: በዚህ ዕለት በየቤቱ የሚታለብ ወተትም ተገፍቶ ቅቤ እንዲወጣው አይደረግም:: ባንባሩ የታለበው ወተት ለጎረቤት ልጆች ይሰጣል:: ወደ መስጊድም ይላካል:: ቂጣም ተጋግሮ የጎረቤት ልጆች በወተት እንዲበሉ ይደረጋል:: የጎረቤት ልጆች ሲባልም ሙስሊም ክርስቲኖችን ማለት ነው:: ስለዚህ አብዶየን የእስላም ክርስቲያኑ ልጆች በጉጉት የሚጠብቁት ዕለት እንደሆነ ይነግራል::

አሁን ላይ ሆኖ ያንን ያለፈ ዘመን ወደ ኋላ ተመልሶ ሲያስታውሰው የሁለቱን እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች አስተሳሰሮ፣ አግባብቶና አስማምቶ ይዟቸው የሚጓዝና ለዘመናት በአንድነት ያቆያቸው አንድ የጋራ እሴት መኖር አለበት፤ የሚል ሃሳብ እንዲያነሳ ምክንያት ሆኖታል። በሌላ በኩል ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሃይማኖት ሰበብ የሚታዩ ክስተቶችን ጨምሮ፤ በወሎ ቀደም ሲል በፍፁም ያልነበሩ አሁን ግን አልፎ አልፎ የሚታዩ ሃይማኖትን መነሻ ያደረጉ ግጭቶች መከሰት ጀምረዋል። በዚህ መነሻ ያንን መልካም እሴት ምን ክፉ ነገር ገጠመው? ምን አይነት በሽታስ ተጣባው? የሚሉ ጥያቄዎች ስላጫሩበትና በዚህ መነሻ መልካም እሴቶችን መርምሮ ለመግለጽ ሲል ለዚህ ጥናት ሦስተኛ አነሳሽ ምክንያት ሁኖታል።

አራተኛው አነሳሽ ምክንያት ደግሞ ከአጥኚው ከፊል ልምድ፣ ትምህርትና ምርምር የመነጩ ጉዳዮች ናቸው። ምክንያቱም አጥኚው በትምህርት ላይ በነበረበት ወቅት ወደ አካባቢው ተጉዞ መጠነኛ ጥናት አካሂዷል (ጌታዋ፣ 2004፣ዓ.ም)። በዚህ ወቅት በተለይ ወደ ገጠሩ አካባቢ ዘልቆ ሲገባ ስለ እሴቶቹ ይበልጥ ማወቁና መረዳቱ ስሜቱን ስቦታል፤ ፍላጎቱና ተነሳሽነቱ በውስጡ እንዲፀነስም ምክንያት ሁኖታል። ስለሆነም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ቢካሄድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል የሚል ተስፋ አድሮበታል፡፡ በመሆኑም መነሻ ምክንያቶቹ እነዚህ ከዚህ በላይ የተገለጹት ነጥቦች የሆኑት ይሄ ጥናት የሚከተሉትን ዋናና ዝርዝር ዓላማዎችን ለማሳካት ተካሂዷል።

1.6፡- የጥናቱ ዓላማዎች

ጥናቱ ዋናና ዝርዝር አላማዎች አሉት። ዋና ዓላማውም ሆነ ዝርዝር ዓላማዎቹ ጥናቱ ለምን እና ምን ለማግኘት ታስቦ እንደተካሄደ መንገድ የሚመሩና አቅጣጫ የሚጠቁሙ የጥናቱ ክፍል ናቸው። በሌላ አገላለጽ የጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች ጥናቱ እንዲጠና ያስፈለገበት ምክንያት ምን እንደሆነና ምን ለማግኘት እንደታሰበ ፍንጭ የሚሰጡ ነጥቦች ናቸው። የጥናቱ ዓላማዎች የተደራጁት ዝርዝር ዓላማዎቹ ከዋናው የጥናቱ ዓላማ ውስጥ የመነጩ ሁነው፤ እርስ በርስ ትስስር (ግንኙነት) እንዲኖራቸው ተደረጎ ነው።

1.6.1፦ የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በወለኖ የክርስትናና[18] የእስልምና እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦችን እርስ በርስ አስተሳስረውና አስተባብረው፣ አግባብተውና አስማምተው፣ አዛምደውና አዋደው ድርና ማግ በመሆን በፍቅርና በሰላም ይዘዋቸው የሚጓዙ መሰረታዊ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶችን (common-bond/ values) ማጥናት ነው።

1.6.2፦ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- በወለኖ ማኅበራዊ መስተጋብሮቹ፣ ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ፣ ሃይማኖታዊ ትውፊቶቹ ወይም የሁለቱ ቅልቅል ለሃይማኖት መቻቻል እሴት ያላቸውን ፋይዳ መመርመር።

- የታሪክ መዛግብት እንደሚያስረዱት የወለኖ ህዝብ ማኅበራዊ ሕይወቱ ከወለኖ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። በዚህ መሰረት እነዚህ ሁነቶች በወለኔዎች አብሮነት ላይ ትተው ያለፉትን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አሻራ መርምሮ መግለጽ።

- አሁን ያለውን የዘመን መንፈስ መነሻ በማድረግ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለኖ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ፍንጭ መስጠት።

1.7፦ የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ዓቢይና ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች አሉት። እነዚህ የምርምር ጥያቄዎች ደግሞ በተቻለ መጠን ከጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች ውስጥ እንዲመነጩ ተደርጎ የተዘጋጁ ናቸው።

1.7.1፦ የጥናቱ ዓብይ የምርምር ጥያቄዎች

- ❖ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለኖ ምን ማለት ነው? ምንን ያሳያል? በምን እና እንዴት ይገለፃል?

1.7.2፦ የጥናቱ ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች

- በወለኖ ሙስሊሙን እና ክርስቲያኑን እርስ በርስ የሚያስተሳስሩ የጋራ እሴቶች የትኞቹ ናቸው? ፋይዳቸውስ?

---

[18] ከዚህ በኋላ በዚህ ጥናት ውስጥ "ክርስትና" የሚለው አገላለጽ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትናን ብቻ የሚመለከት አገላለጽ ነው። "የክርስትና እምነት ተከታዮች" ሲባልም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ተከታዮችን ብቻ ይመለከታል።

- የክርስትናውና የእስልምናው ትውፊቶች ለሃይማኖት መቻቻል እሴት ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው? ከእምነቶቹ ተከታዮች ጋር ያላቸው ትስስርስ?

- በወሎ የሃይማኖት መቻቻል እሴትን አስመልክቶ ምን ተጠና? ምን ተባለ? ይሄኛው ጥናትስ እንዴት አየው? የሚሉት ጥያቄዎች ተመርምረው መልስ አግኝተዋል።።

1.8፦ የጥናቱ ፋይዳ (ጠቀሜታ)

ይሄ ጥናት እውቀት ከማመንጨት፣ ከማሰራጨት፣ ጥቅም ከመስጠትና ከማቆየት አንፃር ቢያንስ ቢያንስ የሚከተሉት ስድስት ፋይዳዎች ይኖሩታል፤ ተብሎ ይገመታል:: የዚህ ጥናት የመጀመሪያው ፋይዳ በጥናቱ የተነሳውን የምርምር ክፍተት አጥንቶ መመላት ነው:: ሁለተኛው ፋይዳ ደግሞ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ በመመርመር የሁለቱን ሃይማኖት እምነት ተከታዮች የጋራ እሴቶች ፋይዳ ፈልቅቆ ማውጣት ይሆናል:: በዚህም ኢትዮጵያውያን ለረዥም ዘመናት ይጠቀሙባቸው የነበሩ የጋራ እሴቶቻቸውን ፋይዳ በመጠቆም ወቅቱ ከሚጠይቀው ሁኔታ ጋር አጣጥሞ መጠቀም እንደሚገባ ፍንጭ ይሰጣል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ እነዚህ እሴቶች ለጋራ መግባባት ወሳኝ በመሆናቸው ለሃገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት አስፈላጊነታቸውንም ይጠቁማል:: ጥናቱ ይህንን በማድረጉም ለቀጣይ ተመራማሪዎች የውይይትና የምርምር በር ይከፍታል::

ጥናቱ የሚከተለው የምርምር ስልት (Research Approach) ደግሞ የዚህ ጥናት ሦስተኛ ፋይዳ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል:: ይህም ማለት ጥናቶች እንደሚያሳዩት በማኅበራዊና በሰብአዊ ሳይንስ የምርምር ዘርፎች እውቀቶች ተቀራራቢና ተደጋጋፊ ናቸው:: በተለይ የሥነ-ጽሑፍ፣ የሥነ ልሳን፣ የታሪክ፣ የሥነ ልቡና፣ የሶሽዮሎጂና አንትሮፖሎጂ የጥናት ዘርፎች ከፎክሎር ጥናት ወይም የእውቀት ዘርፍ ጋር የእትብት ያህል ዝምድና አላቸው:: ፎክሎርን ማጥናት፣ መመርመርና መረዳት የሚቻለውም በአንድ ገጽታው ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አቅጣጫዎች በመመርመር ነው (Ben-Amos 1975: 166; Dundes 1965: 1-3; Goldstein 1964: 2; Bauman 1983: 367; Dorson 1972: 2-5):: በመሆኑም ይሄ ጥናት የነዚህን ምሁራን አስተሳሰብ መሰረት በማድረግ የሌሎች እውቀት ግብአቶችን ይጠቀማል:: በዚህም አዲስ አይነት የጥናት አቅጣጫ አሳይቷል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል::

ጥናቱን የመጠቀም ጉዳይም የዚህ ጥናት አራተኛው ፋይዳ ነው:: በዚህም ቢያንስ፣ ቢያንስ ሦስት የተለያዩ አካላት የዚህ ጥናት ቀጥታ ተጠቃሚዎች ናቸው:: እነዚህ አካላት ተመራማሪዎች፣ የፖሊሲ አውጭዎችና አስፈፃሚዎች እንዲሁም የእሴቶቹ ባለቤቶች ራሳቸው ናቸው:: ከዚህ አንፃር ጥናቱ የሌሎች ተቀራራቢ የእውቀት ግብአቶችን የሚጠቀም በመሆኑ የሌሎች የትምህርት ዘርፎች ተመራማሪዎች ሁሉ በመረጃና የምርምር መነሻ ሃሳብ ምንጭነት ሊገለገሉበት ይችላሉ:: በተመሳሳይ ፖሊሲ አውጭዎች፣ አስፈፃሚዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ሁሉ በመረጃ ምንጭነት ሊገለገሉበት ይችላሉ::

አምስተኛው የዚህ ጥናት ፋይዳ ደግሞ ለባህሉ ባለቤቶች ወይም ለዜጎች ያበረክታል ተብሎ የሚታሰበው አስተዋጽዖ ነው:: ይህም ማለት የእሴቶቹ ባለቤቶች ማንነትና ምንነታቸውን ይበልጥ ይረዱበታል፤ ይገልጹበታል:: ሌሎች አካላትም ልምድ ይቀስሙበታል:: እነዚህ አካላት የሥነ-ልቡና ጥንካሬያቸውን ይገነቡበታል፤ አንድነታቸውንም ያጠናክሩበታል:: ለምሳሌ ጥናቶች እንደሚሉት ከአሁን በፊት የኢትዮጵያውያን ባህል፣ ወግና-ልማድ በሌሎች አካላት ባህል፣ ወግና-ልማድ በቀጥታ አልተለወጠም፤ አልተተካም፤ አልተደመሰሰም (Levine 2008:36-7):: በዚህም ኢትዮጵያውያን የኔ የሚሉት የራሳቸው የሆነ እሴት ባለቤቶች ናቸው:: የኔ የሚለው የራሱ እሴት ያለው ዜጋ ደግሞ በአንድነትና በመረዳዳት ወደፊት የመራመድ ጉልበቱ አስተማማኝ ነው:: ጉልበቱም የእድገት፣ የልማትና የለውጥ ሞተር ነው፤ ተብሎ ይታሰባል::

በመሆኑም ይሄ ጥናት ይህንን እውነታ ወይም ይህንን ጉልበት በተለይ ለወጣቱ ትውልድ የማሳየት ፋይዳ ሊኖረው ይችላል ተብሎ ይታመናል:: ይህም ማለት ወጣቱ ትውልድ በዚህ ጥናት ላይ ተመስርቶ የሃገሩን አወንታዊ የጋራ እሴቶች እንዲያውቅ፣ እንዲጠብቅና እንዲንከባከብ እድል ይፈጥርለታል:: እንዲሁም ኢትዮጵያውያን በየራሳቸው ጓዳ፣ በየራሳቸው መንገድ፣ ከራሳቸው አካባቢና የሕይወት ተሞክሮ ጋር አዋህደው የሚጠቀሙባቸው በርካታ እሴቶች አሏቸው:: በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የሚነሱ ርዕሰ ጉዳዮች ለተከታይ ትውልድ እንዲተላለፉ (እንዲቆዩ) ማድረግ የዚህ ጥናት ስድስተኛ ፋይዳ ነው:: እነዚህ ፋይዳዎች ይኖሩታል ተብሎ የሚገመተው ይሄ ጥናት በጥናት ርዕሰ ጉዳይና በቦታ በሚከተለው ሁኔታ የተወሰነ ነው::

1.9፦ የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የሚካሄደው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ ሦስት የገጠር ወረዳዎችና ሦስት የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ነው:: የሚጠኑት የማኅበረሰብ

ክፍሎችም በነዚህ ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ የሚገኙ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው:: የተጠናው ርዕሰ ጉዳይ ደግሞ ለነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች አብሮነት ምንጭ ናቸው ተብለው የተገመቱ የጋራ የፎክሎር ዘርፎች ወይም እሴቶች ናቸው:: እነዚህ እሴቶች ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ አለያም የሁለቱ ቅልቅል የሆኑ ጉዳዮች ናቸው::

በተለይ በሃይማኖታዊ ትውፊቶችና በሃገረሰባዊ ልማድ ክንውኖች የሚገለጹ የፎክሎር ዘርፎች የዚህ ጥናት መሰረቶች ናቸው:: ከሁለቱም ሃይማኖቶችና አማኞች ጋር የተገናኙ ባህላዊ እምነቶች፣ አምልኮዎች፣ ፌስቲቫሎች፣ ሃገረሰባዊ መድሃኒቶች፣ ሃገረሰባዊ ሙዚቃ፣ የሃይማኖት ሥርአት ክንውኖች፣ ሀገረሰባዊ ክብረ በዓላትና ልዩ ልዩ ልማዳዊ ድርጊቶች የዚህ ጥናት ግብአቶች ናቸው:: እንዲሁም ከነዚህ ክንውኖች ጋር አብረው የሚሄዱ ቃላዊና ቁሳዊ የፎክሎር ዘርፎችም የዚህ ጥናት ግብአት ናቸው:: በተጨማሪም የአካባቢውና የማኅበረሰቡ መስተጋብር፤ እንዲሁም የሁለቱ እምነት ተከታዮች ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለተካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችም እንዳስፈላጊነቱ በዚህ ጥናት ውስጥ ተብራርተው ቀርበዋል::

ለዚህ ጥናት አካባቢውና የአካባቢው ማኅበረሰብ የተመረጡባቸው ምክንያቶች (በጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሁኖ) ሦስት ናቸው:: በአጥኚው እምነት በነዚህ እሴቶች ላይ ጥናት ለማካሄድ ከእሴቶቹ ጋር ትውውቅ ያስፈልጋል:: ትውውቁም እሴቶቹን ከሥረ-መሰረታቸው ጠንቅቆ ከማወቅ ጀምሮ በትምህርትና ስልጠና ጭምር የታገዘ መሆን ይኖርበታል:: ከዚህ አንፃር የዚህ ጥናት አቅራቢ በማኅበራዊ ሕይወት አስተውሎትም ሆነ፣ በትምህርት፣ እንዲሁም በፍላጎት ከእሴቶቹ ጋር የቅርብ ትውውቅ ስላለው አካባቢውን ለመምረጥ አንደኛ ምክንያት ሁኖታል::
ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በጥናቱ አስፈላጊነት ውስጥ እንደተገለፀው በነዚህ የጋራ እሴቶች ላይ የተካሄደ ጥናት በነዚህ አካባቢዎች አለመኖሩ ነው:: ጥናቱ ከሚካሄድባቸው አካባቢዎች ጋር የተገናኘው ጉዳይ ደግሞ ሦስተኛው ምክንያት ነው:: በ2007 የኢትዮጵያ ህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ህዝብ ቁጥር 17,221,976 ነው:: ከዚህ ውስጥ የሰሜን ወሎ ህዝብ ቁጥር 1,500,303 ነው:: ይህ ቁጥር ከጠቅላላው የክልሉ ህዝብ ብዛት 8.7 በመቶ ይይዛል:: የዞኑ ህዝብ ከሃይማኖት ስብጥሩ አንፃር የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች 1,241,363 ሲሆኑ፤ የእስልምና እምነት ተከታዮች 256,242 ናቸው:: ይህም እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአጠቃላዩ የዞኑ ህዝብ ብዛት የ82.7 በመቶ እና የ17 በመቶ ድርሻ

አላቸው:: በዚህ መሠረት የሌሎች ሃይማኖት እምነት ተከታዮች ቁጥር 0.3 በመቶ በታች በመሆኑ በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም:: በሌላ በኩል የሁለቱ ሃይማኖት እምነት ተከታዮች ስብጥር ዞኑ ካሉት 11 ወረዳዎች አንጻር ሲታይ በሚከተለው ሰንጠረዥ የተገለፀውን ይመስላል::


ተ.ቁ	የወረዳዎቹ ስም	የወረዳዎቹ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት	የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ብዛት		የእስልምና እምነት ተከታዮች ብዛት	
			በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ
1	ቡግና ወረዳ	75,486	74,871	99.19%	507	0.67%
2	ራያና ቆቦ ወረዳ	221,958	183,952	82.88%	36,615	19.91%
3	ግዳን ወረዳ	158,428	157,813	99.60%	577	0.36%
4	መቄት ወረዳ	226,644	215,897	95.34%	10,701	4.72%
5	ዋድላ ወረዳ	128,170	124,423	97.08%	3,719	2.90%
6	ደላንታ ወረዳ	127,771	115,989	90.78%	11,769	9.21%
7	ጉባላፍቶ ወረዳ	139,825	212,064	86.58%	18,626	13.32%
8	ሐብሩ ወረዳ	192,742	44,237	22.95%	148,114	76.85%
9	ወልድያ ወረዳ	46,139	37,135	80.48%	8,519	18.46%
10	ላስታ ወረዳ	117,777	115,013	97.65%	2,727	2.32%
11	ዳውንት ወረዳ	65,363	50,969	77.98%	14,368	21.98%

ሠንጠረዥ 1:- በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ወሎ ዞን መስተዳድር የኦርቶዶክስ ክርስትናና እስልምና እምነት ተከታዮች ስብጥር በቁጥርና በመቶኛ ሲገለጽ::
ምንጭ:- በማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ (CSA)፣ የ2007 የኢትዮጵያ ህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት::


ከላይ በሰንጠረዡ ከተዘረዘሩት 11 ወረዳዎች ውስጥ ለዚህ ጥናት ከገጠር ወረዳዎች፤ ራያና ቆቦ፣ ጉባላፍቶና ሐብሩ፤ ከከተማ አስተዳደሮች ደግሞ፤ ወልድያ፣ ቆቦ እና መርሳ ከተማዎች ተመርጠዋል:: እነዚህ የገጠር ወረዳዎች እና የከተማ አስተዳደሮች ለዚህ ጥናት የተመረጡበት መሰረታዊው ምክንያት የሃይማኖቶቹ ስርጭትና የወረዳዎቹ ኩታ ገጠም መሆን እንደተጠበቀ ሁኖ ሃይማኖቶቹና የእምነቶቹ ተከታዮች ከወረዳዎቹ ጋር ታሪካዊ ትስስር ስላላቸው ነው:: ምክንያቱም እነዚህ ወረዳዎች በቀድሞው አጠራር የየጁ አውራጃ ወረዳዎች ነበሩ:: የጁ አውራጃ ደግሞ የሁለቱ ሃይማኖቶች እምነት ተከታዮች ባህል-ወግና ልማድ የተቀላቀለበትና የተዋሃደበት ቦታ ነው:: ይህም ማለት አካባቢው ለዚህ ጥናት የተመረጠው የባህሉን ውክልና መሰረት አድርጎ ነው::

ጥናቶች እንደሚያስረዱት የጁ አውራጃ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንዱ የሃገሪቱን የወግ እቃ የያዘ መዳይ (A lady's Jewel case) ነው ማለት ይቻላል:: ምክንያቱም የጁ አውራጃ በውስጡ

በርካታ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን አካቶ የያዘ አውራጃ ነው። (Trimingham 1965; Fekadu 1990; Hussein 2001)



<u>ካርታ አንድ</u>፦ የሰሜን ወሎ ዞን በኢትዮጵያ በሰሜን፣ በአማራ ክልል ደግሞ በምስራቅ አቅጣጫ እንደሚገኝ የሚያመለክት ካርታ።



<u>ካርታ ሁለት</u>፦ የሰሜን ወሎ 11 ወረዳዎች እና ከነዚህ ወረዳዎች ውስጥ ጥናቱ የተካሄደባቸው አካባቢዎች፡፡ በዚህ መሰረት ቀይ፣ ቢጫና ግራጫ ቀለም የተቀቡት አካባቢዎች ይህ ጥናት የተካሄደባቸው የገጠር ወረዳዎች ናቸው፡፡ አረንጓዴ ቀለም የተቀባው አካባቢ ወልዲያ ከተማ አስተዳደር ሲሆን፣ ቆቦና መርሳ ከተማ አስተዳደሮች ደግሞ በራያና ቆቦ እና በሐብሩ ወረዳዎች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም ቆቦ ወረዳ ከደቡባዊ ትግራይ ዞንና ከአፋር ክልል ጋር የሚዋሰን ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሐብሩ ወረዳ ከአፋር ክልልና ከደቡብ ወሎ ዞን ምስራቃዊ ወረዳዎች ጋር ይዋሰናል፡፡ ጉባለፍቶ ወረዳ ደግሞ ከሰሜን ወሎ ወረዳዎች ውስጥ ከጊዳን፣ ከመቄት፣ ከዋድላና ደላንታ ወረዳዎች ጋር የሚዋሰን ሲሆን፣ ከደቡብ ወሎ ዞን ወረዳዎች ውስጥ ደግሞ ከአንባሰል ወረዳ ጋር ይዋሰናል፡፡

ለአብነት የየጁ ወረሴህ[19] የተጸነሰው ሐብሩ ወረዳ መርሳ አባገትየ ውስጥ ነው:: አፀናነሱም ከአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) እና ከኦሮሞ መስፋፋት ጋር ይገናኛል:: ግንኙነቱ ደግሞ

[19] የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት "ወረሴህ" የሚለው መጠሪያ "ወረ-ሼህ" ከሚለው መጠሪያ የተወረሰ ነው:: ነገር ግን ‹‹ወረሼዎቹ ለስልጣን ብለው ወደ ክርስትና ሃይማኖት ሲሄዱ የተሰጣቸው መጠሪያ ነው:: ወረሴህ የተባሉት ማተብ ካሰሩ በኋላ እነ ጓንጉል አባ ሲሩ፣ እነ ራስ ዓሊ ማተብ ካሰሩ በኋላ እንጂ፣ ቀድሞ ወረሴህ አይባልም::

በአካባቢው በአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) ጦርነት ጊዜ አብረውት ከነበሩ ትውልዳቸውም፤ አመጣጣቸውም ከዓረብ አገር ከሆነ ዑመር[20] ከተባሉ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ግለሰብ ጋር ነው (Fekadu 1990; Trimingham 1965)። ድርሳናት እንደሚያስረዱት በዘመኑ የኦሮሞ መስፋፋት በአካባቢው ደርሶ ስለነበር እንግዳው ዑመር ከአካባቢው የኦሮሞ ባላባት ጋር ተጋብተው እስልምናን እያስተማሩ ወልደው ከብደው መኖር ጀመሩ (Fekadu 1990: 19-20)። ከጊዜ በኋላ ከሳቸው የዘር ሐረግ የሚመዘዝ አባ ሴሩ ጓንጉል የተባለ ሕፃን ተወለደ። ይሄ ሕፃን አድጎ በተራው ሁለት ታሪካዊ ክስተቶችን ወለደ። የመጀመሪያው ክስተት ከላስታው የክርስቲያን ገዥ መደብ ጋር ጋብቻ መመስረቱና የክርስትና እምነት ተከታይ በመሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የማሰራቱ ጉዳይ ነው።[21] ሁለተኛው ክስተት ደግሞ በዱዓ የተፀነሰ ነበርና በኋላ "ታላቅም- ራስም" የተባለ ልጅ መውለዱ ነው።

ይህ ብላቴና ታላቁ ራስ ዓሊ ጓንጉል ነው። ታላቁ ራስ ዓሊ ጓንጉል በተራው የየጁ ወረሴህን (ዘመነ መሳፍንትን) ወለደ። ዘመነ መሳፍንት በበኩሉ ከ1750ዎቹ እስከ 1850ዎቹ (Hussein 2001: 208) ለአንድ ክፍለ ዘመን ለሚጠጋ አመታት ጎንደር ቤተ- መንግሥት ድርስ ዘልቆ በመግባት ያሻውን ሲያደርግ ቆይቶ (ሲሾም ሲሽር) እሱም በተራው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የራሱን አሻራ ትቶ አለፈ። ነገር ግን የዘመነ መሳፍንት ፍፃሜ ያማረ አልነበረምና የአገሬው ህዝብ የተሰናበተው፤

እኒህ ወርሴዎች ምንድን ነው መላቸው፤
ተሰብረው አለቁ እንደ ብርሌያቸው።

የሚባው ‹ወረ-ሼህ› ነው›› (ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 10 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ-ገዶ)። አለቃ ታየ በበኩላቸው "ግራኝ አህመድ ኢትጵያን ባጠፋ ጊዜ በሺህ515 ዓ. ም. ከባህር ማዶ ከዓረብ አገር ሸህ ዑመር የሚባል የብር ዘንግና የብር እርኮት አሲዞ መጣና በየጁ ገብቶ ተቀመጠ። ሸህ ዑመር ብዙ ሴቶች አግብቶ ብዙ ልጆች ወለደ። መንደሩ ቢበዛ ወረሸህ ተባለ። አሁን ወረሴህ የሚባሉ የእነሱ ዘሮች ናቸው። ወረሸህ ማለት የሺህ መንደር ማለት ነው። ልጆቹ ከወረሺህ ወረሴህ የሚባልን ስም ተቀበሉ (አለቃ ታየ፤1958 ዓ.ም.፤ 49)" በማለት ጽፈዋል።

[20] ግራዝማች ብሩ ይማም እንደሚሉት ሼህ ዑመር የአፄ ልብነ ድንግል የልጅ ልጅ ናቸው። ይኸውም ከአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) ጦርነት በፊት በቱርኮች ምክንያት የአፄ ልብነ ድንግል ልጆች ፊጥቆርና ሚናስ የመን አገር ነበሩ። በዚህ ወቅት ፊጥቆር በጣም መልኩ ያማረ ቆንጆ ስለነበረ የየመን ንጉሥ ልጃቸውን አጋቡት። በዚህ መሰረት ሼህ ዑመር ተወለዱ። ከዚያም በአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) ጦርነት ጊዜ ወደ አባታቸው አገር ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የጁ መርሳ ላይ ሰፈሩ። (ግራዝማች ብሩ ይማም፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 13 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ)። የዚህ ጥናት አቅራቢ ከላይ የተጠቀሰውን ታሪክ ለማጣራት ባደረገው ሙከራ ግን ሼህ ዑመር የአፄ ልብነ ድንግል የልጅ ልጅ ስለመሆናቸው በታሪክ መዛሕፍት የተፃፈ መረጃ አላገኘም።

[21] ጓንጉል አባሴሩ በ1760 አካባቢ እንዳሰሩት የሚነገርለት የጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ከወልዲያ ከተማ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ 10 ኪ.ሜ. ያህል ርቀት ላይ አማየ ሚጫ በሚባለው አካባቢ ይገኛል። ይህ ቤተ-ክርስቲያን አሁንም ድረስ በፀበሉ ፈዋሽነት ይታወቃል (Fekadu 1990: 25)።

የሚለውን ስንኝ ቋጥሮ ነበር። ባጠቃላይ በነዚህ ወረዳዎች ከአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) እና ከኦሮሞ መስፋፋት ጋር በተያያዘ በርካታ ሁነቶች ተከስተው አልፈዋል። በዚህም በክርስትናና እስልምና እምነት ተከታዮች መካከል አያሌ መስተጋብሮች ወይም የሰው ለሰው ግንኙነቶች ተፈጥረዋል። የባህል መወራረሶች ተካሂደዋል። በዚህም የሁለቱን እምነት ተከታዮች የእርስ በርስ ግንኙነቶች ይበልጥ የሚያስተሳስሩ የጋራ እሴቶች ዳብረዋል፤ ጎልብተዋል። በዚህ ሂደት፤ በኋላ የመጣው ቀድሞ የነበረውን እሴት ሙሉ በሙሉ ሳያጠፋ ወይም ሳይደመስስ፤ ቀድሞ የነበረውም በተራው በኋላ የመጣውን አላስገባም ሳይል፤ ሁለቱም በመቻቻል፣ በመፈቃቀድ፣ በመፈቃቀር፣ በሰላምና በፍቅር ህብር ፍጥረው ለዘመናት መዝለቃቸውን የሚያሳዩ በርካታ አብነቶች በነዚህ አካባዎች ይገኛሉ።

ለምሳሌ በየጁ የክርስትና፣ የእስልምናና ነባሩ (አገር በቀሉ) የእምነት እሴቶች ተጎራብተው ከዚያም ሲያልፍ ተጋብተው በሰላም የሚኖሩ ስለመሆናቸው በርካታ ማሳያዎች አሉ። የእምነቶቹ ባለቤቶችም እንዲሁ አንዱ የሌላውን እምነት ከማክበርና ከመጠበቅ ባለፈ በመጋባት፣ የሌላውን ባህል በመውረስና የራስ በማድረግ በአንድነት የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው። በመሆኑም የየጁ ባህል ያማራ፣ የኦሮሞ፤ የትግራይ፣ ያገውና የአፋር ማኅበረሰብ እሴቶች ውህድ ነው (ጌታቸው፣ 1984 ዓ.ም፤ 7)።

በዚህ መሠረት እነዚህ ወረዳዎች የሁለቱ እምነት ተከታዮች ባህላዊና ሃማኖታዊ እሴቶች የተቀላቀሉባቸውና በተጨባጭ ተግባራዊ የሚደረጉባቸው አካባቢዎች ስለሆኑ ለዚህ ጥናት ተመርጠዋል። (ለበለጠ ማብራሪያ ምዕራፍ አራትን ይመልከቱ)። በዚህ መነሻ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ምንጩ ከዚሁ ብዝሃነት ጋር ሊያያዝ ስለሚችል እነዚህ ሦስት የገጠር ወረዳዎች እና ሦስት የከተማ አስተዳደሮች ከሌሎች ወረዳዎች በተለየ ሁኔታ ለዚህ ጥናት ተመርጠዋል።

1.10፦ የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት በሁሉም ነገር የተሟላ ወይም ፍጹም ነው፤ ተብሎ አይታሰብም። ምንም እንኳን ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም፤ ጥናቱ የተለያዩ ውስንነቶች ሊኖሩበት እንደሚችል ይገመታል። የውስንነቶቹ ምክንያቶች ደግሞ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ባህርይና ከወቅቱ ነባራዊ ሁኔታዎች ውስጥ የሚመነጩ ናቸው። በጥናቱ ባህርይ ምክንያት ሊከሰቱ ይችላሉ ተብለው ከሚገመቱ ውስንነቶች መካከል አንዱ በዚህ የጥናት ርእሰ ጉዳይ ላይ

የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች በተለያየ መንገድ በተደረገ ፍለጋ (ንባብ) አለመገኘታቸው ነው። ከዚህ አንፃር አጥኚው ተጨማሪ እውቀት ለማደርጀትና ለመገብየት የሚያስችል አጋጣሚ አግኚቷል ተብሎ ሙሉ በሙሉ መናገር አይቻልም። የዚህ አይነቱ ሁኔታ ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከጥናቱ ውስንነት ጋር ሊገናኝ ይችላል ተብሎ ይታሰባል። እንዲሁም በዚህ በውድድር ወይም በፉክክር በተሞላ የማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ የሃይማኖት መቻቻል አንድ አይነት ገጽታ ሊኖረው አይችልም። በመሆኑም ይሄ ጥናት ሁሉንም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሊያረካ ይችላል ተብሎ አይገመትም።

ሁለተኛው ከጥናቱ ባህርይ ሊመነጭ የሚችለው ውስንነት ደግሞ "writing a PhD thesis is the work of many" ከሚለው አስተሳሰብ ጋር የሚገናኝ ነው። ይህም ማለት ጥናቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተለያዩ አካላት ውጤት ነው። በዚህ መሰረት የነዚህ አካላት ተባባሪነት ወይም መልካም ፍቃደኝነት የጥናቱን ክፍተት እንደሚሞላ ሁሉ፤ አለመተባበራቸው ደግሞ በጥናቱ ላይ ክፍተት ይፈጥራል። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ሂደት በርካታ ወርቃማ ጊዜያት በሆነ ባልሆነው ምክንያት ባክነዋል። ባንፃሩ የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ በባህርይው "ስሱ" (sensitive) የሆነ፣ ተመላልሶና ተደጋግሞ በጥንቃቄ የሚሰራ ነው። በዚህ መሰረት ርዕሰ ጉዳዩን መልሶና መላልሶ ከመመርመር አንፃር በመጠኑም ቢሆን በጥናቱ ላይ የራሱ የሆነ ውስንነት ፈጥሯል። ከዚህም ሌላ ከወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውና ለጥናቱ ውስንነት ምክንያት የሆኑ ነጥቦች ደግሞ በንዑስ ርዕስ 1.11 የተጠቀሱት ጉዳዮች ናቸው።

1.11፦ ያጋጠሙ ችግሮችና የተበጁላቸው መፍትሄዎች

ይህንን ጥናት ከፍፃሜ ለማድረስ የተለያዩ መሰናክሎች (ችግሮች) አጋጥመዋል:: በዚህ ጥናት ሂደት ያጋጠመ የመጀመሪያው ችግር ከሃይማኖት አክራሪነት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው። ምንም እንኳን የዚህ ጥናት አቅራቢ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማካሄድ ፅኑ ፍላጎት የነበረውና ጥናት በማካሄዱም ደስተኛ ቢሆንም፤ ያለማጋነን በአሁኑ ጊዜ ከሃይማኖት ጋር በተገናኘ ርእሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ማካሄድ በእሳት የመጫወት ያህል ነው። ምክንያቱም ርእሰ-ጉዳዩ በሆነ ባልሆነው ሆድ ይብሰዋል። ክልብሽ ይለዋል። ለምሳሌ ይሄ ጥናት ከሃይማኖት መርህ ወይም ከሃይማኖት አስተምህሮ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ጉዳይ አይደለም። ግንኙነቱ ከፎክሎር ጋር ነው።

ነገር ግን ከሃይማኖት መቻቻል ጋር የተያያዙ ርዕሰ ጉዳዮች ሲነሱ የቢሮክራሲውን ውጣ ውረድ ጨምሮ፤ በመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችም ሆነ በነዋሪዎች (በመረጃ ሰጭዎች) ዘንድ ከፍተኛ

የሆነ የመጠራጠር ስሜት ነበር:: "በሰላምና በፍቅር በምንኖርበት ቀዬ ደሞ ምን ልታመጡብን ነው!?" የሚለው የጥርጣሬ ስሜት የአብዛኞዎቹ ጥያቄ ነበር:: በመሆኑም ብዙዎቹ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ አልነበሩም:: ነገር ግን ችግሩ ጎልቶ የሚታየው በከተሞች አካባቢ በመሆኑና የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በገጠርና በከተሞች ላይ በመሆኑ በከተሞች አካባቢ ማግኘት ያልተቻለውን መረጃ በገጠሩ አካባቢ፤ በተመሳሳይ በገጠሩ አካባቢ ማግኘት ያልተቻለውን መረጃ በከተሞች አካባቢ ማግኘት ተችሏል:: ከዚህም ሌላ የአጥኚው የአካባቢው ተወላጅ መሆን፣ መረጃ የመሰብሰብ ልምዱና ሙያውም ችግሮቹን አቃሎለታል::

ሁለተኛው በዚህ ጥናት ወቅት ያጋጠመ ሌላው ችግር ደግሞ የጊዜ ጉዳይ ነው:: የጊዜ ጉዳይ ሲባል ግን ለዚህ ፕሮግራም የተመደበው ጊዜ አንሶ ሳይሆን፤ ይህንን ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎች አለመኖራቸው ነው:: በዚህም ከዚህ ጥናት ጋር በተያያዘ የተለያዩ ችግሮች ተከስተዋል:: ለምሳሌ የዚህ ጥናት ርዕስ በወቅቱ ሳይፀድቅ ረዥም ጊዜ ቆይቷል:: ከፀደቀ በኋላም ቢሆን ማለፍ የሚጠበቅበትን ሂደት ለማለፍ የወሰደው ጊዜ ቀላል አይደለም:: ነገር ግን አጥኝው መስራት የሚገባውን ሥራ ቀድሞ እየሥራ ስለሚጠብቅ የባከነውን ጊዜ በራሱ መንገድ አካክሷል::

በዚህ ጥናት ሂደት ያጋጠመ ሦስተኛው ችግር ደግሞ የገንዘብ ጉዳይ ነው:: በዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት ለዚህ ጥናት የሚያስፈልገውን ወጭ ሁሉ ዩኒቨርሲቲው መሸፈን አለበት የሚል እምነት የለውም:: ነገር ግን አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በዩኒቨርሲቲው በኩል የሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ "እንዳያማ ጥራው..." አይነት ነገር ነው:: ይህም ሆኖ ዓላማና ፍላጎት ካለ የማይፈታ ችግር የለምና በገንዘብ በኩል ያለውን ችግር አጥኚው በራሱ መንገድ ተወጥቶታል:: በፎክሎር የትምህርት ዘርፍ በትምህርት ክፍሉ ከዓመትና ሁለት ዓመት በፊት ቀድመው የተሰሩ የሦስተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናቶች በጊዜው ቤተ-መፃህፍት ውስጥ ገብተው አገልግሎት እንዲሰጡ አለመደረጋቸው አራተኛው ችግር ነው::

ምዕራፍ ሁለት

2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት (ክለሳ ድርሳናት)

በምዕራፍ አንድ በንዑስ ርዕስ 1.2 እንደተመለከተው የጥናቱን አካባቢያዊ ዳራ ለመዳሰስ ተሞክሯል። በመሆኑም በዚህ አካባቢያዊ ዳራ ውስጥ ይሄ ጥናት ካነሳው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተገናኘ ቀደም ሲል ምን ተጠና? ምን ውጤትስ ተገኘ? ምን አይነት ክፍተትስ አለ? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ተገቢ ይሆናል። የዚህ ምእራፍ ዋና ዓላማም ጥናቶችን በመመርመር እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ነው።

ተመራማሪዎች እንደሚሉት በአንድ የጥናትና ምርምር ሂደት ውስጥ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ማድረግ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት። ይኸውም የተመራማሪውን እውቀት ያደረጃል፤ ያበለጽጋል። ሃሳቡንም ያጎለብታል። በዚህም የቀደሙትን ሥራዎች መነሻ ወይም ማንፀሪያ (Bench-mark) በማድረግ የእውቀት ሽግግር አለያም ተራክቦ እንዲኖር ያደርጋል። እንዲሁም የተሰራውንና ያልተሰራውን ለይቶ ለማወቅ ስለሚያስችል ተደጋጋሚና ተመሳሳይ ጥናትና ምርምር እንዳይካሄድ ይረዳል። በዚህም አዲሱ ጥናት ይዞት በተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ብቻ ያነጣጥራል። በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ያነጣጠረ ጥናት ደግሞ የቀደሙት ጥናቶች ያልደፈኑትን ወይም ያልሞሉትን የእውቀት ክፍተት (Knowledge-Gap) በትክክል በመድፈን ይዞት የተነሳውን ዓላማ ያሳካል፤ አዲስ ነገር ማምጣቱንም በግልፅ ያሳያል (Creswel 2014)።

በዚህ ጥናት የተደረገው የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትም ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች መነሻ በማድረግ ነው። በምዕራፍ አንድ እንደተጠቀሰው ይሄ ጥናት የሌሎች እውቀት ግብአቶችን ይጠቀማል። በመሆኑም በዚህ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ውስጥ የፎክሎር የምርምር ውጤቶችን ጨምሮ፤ በሥነ-ጽሑፍ፣ በሥነ-ልሳን፣ በታሪክ፣ በሶሽዮሎጂ፣ በአንትሮፖሎጂ፣ በሳይኮሎጅ፣ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም፣ በሕግ፣ በሰላምና ደህንነት የትምህርት ዘርፎች ውስጥ የተካሄዱ ጥናቶች ተመርምረዋል። በዚህም ከዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሊገናኙ ይችላሉ፤ ተብለው የታመነባቸው የምርምር ውጤቶች እንደሚከተለው በሁለት ምድብ ተከፍለው ቀርበዋል። በመጀመሪያው ክፍል የሚገኙት የምርምር ሥራዎች ለዚህ ጥናት አጠቃላይ መነሻ ከመሆን ያለፈ ከዚህ ጥናት ጋር

ግንኙነት ስለሌላቸው የጥናቶቹን ዋና ሃሳብ ወይም ጭብጥ ብቻ በመግለጽ እንዲጠቃለሉ ተደርጓል። በዚሁ ክፍል በንዑስ ርዕስ 2.2 የተጠቀሱት ሥራዎች ግን ሰፋ ባለ መልኩ ተዳሰዋል። በሁለተኛው ክፍል የቀረቡት ጥናቶች ደግሞ ቢያንስ የምርምር ርዕሳቸው ከሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተገናኘ በመሆኑ፤ እያንዳንዱን ሥራ በቀረበበት በየራሱ መንገድ መርምሮ ማቅረብ አጥኚው የመረጠው የአቀራረብ መንገድ ወይም ሥልት ነው። አቀራረቡም ጥናቶቹ ያነሱትን ርዕሰ ጉዳይ ወይም ጭብጥ መሠረት ያደረገ ነው[22]።

2.1፦ ሃይማኖትን መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ የመረመሩ ሥራዎች

በዚህ ክፍል ውስጥ የተከለሱት ቀደምት ጥናቶች መነሻ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ፤[23] ወሎን ጨምሮ የሃገሪቱን ሌሎች አካባቢዎች ጭምር ይመለከታሉ። ተመራማሪዎቹ ግን ኢትዮጵያውያን እና የውጭ አገር ዜጎች ናቸው። የነዚህ ተመራማሪዎች ጥናት ዋና ዓላማ ሲመረመር የብዙዎቹ ጥናት ትኩረት ሃይማኖታዊ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተመሠረተ ነው።

የጥናቶቹ መነሻ አንዱ ክርስትና ሌላው እስልምና ሃይማኖት ነው። መነሻው ይህ ቢሆንም ክርስትናው እስልምናውን፤ እስልምናው ክርስትናውን ማንዐሪያ በማድረግ በዋናነት የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች መርምረዋል። ለማስረጃ የተጠቀሙባቸው ምንጮችም የአገር ውስጥና የውጭ አገር የታሪክ ሰነዶች፣ የነገሥታት መዋእለ ዜናዎች፣ የሃይማኖት አባቶች ገድላትና ተአምራት፣ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ የጉዞ ማስታወሻዎች፣ የሕይወት

---

[22] በዚህ ጥናት ውስጥ የተመረመሩት ሁሉም ቀደምት ጥናቶች ምልአት ቀርነታቸው ወይም ጥንካሬ ድክመታቸው የተገመገመው ከዚህ ጥናት ጋር ሊያገናኛቸው በሚችል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ብቻ እንጂ፣ ጥናቶቹ ከቀረቡበት የእውቀት ዘርፍ ወይም የጥናት ዓላማ አንፃር አይደለም።

[23] የዚህ ጥናት ክለሳ ድርሳን መነሻውን ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ያደረገው በተለያየ መንገድ በተደረገ ፍለጋ (ንባብ) በሃይማኖት መቻቻል እሴት ላይ በሌሎች አገሮች የተሰራ ጥናት ባለመገኘቱ ነው። ባንፃሩ በሌላው ዓለም የሃይማኖት መቻቻል የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ከሕግ ድንጋጌ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው። የሰብአዊ መብትና የሃይማኖት ነፃነት ጉዳይ ነው። ከፖለቲካና ከመልካም አስተዳደር ጋር የተቆራኘ አስተሳሰብ ነው። ከዚህ ባለፈ በእምነቱ ተከታዮች መካከል ያለውን መስተጋብር መሰረት ያደረገ ጥናት አልተገኘም። በመሆኑም የውጭው ዓለም የሃይማኖት መቻቻል ዘይቤ ምንጩ እንደ ኢትዮጵያ ከእምነቱ ተከታዮች ሳይሆን፣ መንግሥትና ሕገ - መንግሥት ነው። ይሄ ደግሞ የፎክሎር ጉዳይ ሳይሆን የፖለቲካ ሳይንስ ወይም የሕግ ትንታኔን የሚጠይቅ የጥናት ዘርፍ ነው። ባጠቃላይ በኢትዮጵያ እንደሚታየው በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ግማሹ ክርስቲያን ግማሹ ሙስሊም ሁኖ፣ በአንድ እድር፣ በአንድ እቁብ ወይም ፍጹም በሆነ መግባባት በሰላም ተጎራብቶና ተዛምዶ የሚኖር አለያም የአኗኗር ዘይቤ ያለው ማኅበረሰብ "በዚህ አገር አለ!" የሚል መረጃ እስካሁን በተደረገ ፍለጋ አልተገኘም። በዚህም የዚህ ጥናት ክለሳ ድርሳን በአገር ውስጥ ብቻ የተወሰነ ነው።

ታሪክ ጽሑፎች፣ ተመሳሳይ ቀደምት ጥናቶች፣ የመስሪያቤትና የግለሰብ ሰነዶች፣ ቃለመጠይቅና በውይይት የተሰበሰቡ መረጃዎች...ወዘተ ናቸው።።

በነዚህ የመረጃ ምንጮች ላይ የተመሰረቱት እነዚህ ቀደምት ጥናቶች አንዳንዶቹ እስልምና ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገባና እንዴት እንደተስፋፋ መርምረዋል።። ስለ አገባቡ፣ ስርጭቱና መስፋፋቱ ምክንያት ናቸው ያሏቸውን መሠረታዊ ጉዳዮች ተንትነዋል።። በዚህም ከመጀመሪያዎቹ የእምነቱ ተካታዮች ስደት እስከ ዘመኑ የንግድ ልውውጥ ሂደት፣ የውጭውንና የአገር ውስጡን ነባራዊ ሁኔታ ጨምሮ፤ ከኃይል እስከ ሰላማዊ መንገድ፣ ከውጭ አገር እስከ አገር ውስጥ የእምነቱ መሪዎችና አስተማሪዎች አስተዋጽኦ፣ ከአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ እስከ አገሪቱ ማኅበራዊና ባህላዊ ዳራ ለእስልምና እምነት መስፋፋት በነዚህ ጥናቶች ውስጥ ምክንያት ናቸው ተብለዋል።።

እንዲሁም በእስልምና ሃይማኖት በኩል የነበረውን የአስተምህሮ መርህ አንድነትና ልዩነት አሳይተዋል።። የልዩነቶቹን ምንጭ፣ ምክንያትና ውጤት አብራርተዋል።። በሂደት የገጠሟቸውን ውጣ ውረዶችም ገልጸዋል።። የእምነቶቹ አባቶች ለሃይማኖቶቹ መስፋፋት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ዘርዝረዋል።። በሌላ በኩል በእስልምናና በክርስትና እምነት መካከል የነበረው ግጭትና ፉክክር የጥናቶቹ ማጠንጠኛ መሠረታዊ ርዕሰ ጉዳይ ነው።። (Hussein 1984)።። ከዚህ አንፃር የሃይማኖቶቹ ሁኔታ የተጠናው ከሃገሪቱ የፖለቲካ ሂደት አንፃር ነው።።

በሌላ በኩል ክርስትናን መነሻና መድረሻ ያደረጉ ጥናቶች በተመሳሳይ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በክርስትናና በእስልምና እምነት መካከል የነበረውን ውጣውረድ ያጠኑ ናቸው።። የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታም በሃይማኖት ማንፀሪያነት ተንትነዋል።። ከዚህ በላይ ለተዘረዘሩት ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ጥናቶች ለአብነት ይጠቀሳሉ (Trimingham 1965; Abir 1968; 1978; Taddesse 1972; Caulk 1972; Crummey 1975; Merid 1974; Hussein 1984;1992; 2001)።።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጥናቶች ተጠቃለው ወይም ተጨምቀው ሲቀርቡ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች እርስ በርሳቸውን ያገናኟቸዋል፤ ያስተሳስራቸዋል።። ይኸውም በነዚህ ጥናቶች ውስጥ የክርስትናና እስልምና ግንኙት ሁልጊዜም ግጭት፤ ሁልጊዜም ትግል፤ ሁልጊዜም ውጣ ውረድ የተሞላበት ሁኖ መገኘቱ አንደኛው መሠረታዊ የጋራ መገለጫቸው ነጥብ ነው (Hussein

1984)። እንዲሁም የሁሉም ጥናቶች ትኩረት ሃይማኖት የፖለቲካ ህልውና ወይም የፖለቲካ ስልጣን የሃይማኖት መሣሪያ በመሆን በኢትዮጵያ ታሪክ፣ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳይ ውስጥ ቁልፍ ድርሻ እንደነበራቸው ማሳየት የጥናቶቹ ዋና ሃሳብ ወይም ቁምነገር አለያም ጭብጥ መሆኑ በአንደኛው ርእሰ ጉዳይ ውስጥ የሚጠቃለል የጋራ መገለጫ ነጥብ ነው።

ሁለተኛው የጋራ ነጥብ ደግሞ የሁለቱን እምነቶችና የእምነቱን ተከታዮች ከፖለቲካው ጉዳይ በመነጠል በታሪካዊውም ሆነ በኢኮኖሚያዊው፣ በሃይማኖታዊውም ሆነ በባህላዊው፣ አለያም በማኅበራዊው ሕይወት ውስጥ ሁለቱ የሃይማኖት ተቋማትና የተቋማቱ ባለቤቶች የነበራቸውን አወንታዊ የእርስ በርስ ግንኙነት አለመመርመራቸው ወይም መተባበራቸውንና መተሳሰራ ቸውን አለማሳየታቸው ነው። የመተባበሪያቸውና የመተሳሰሪያቸው ዘዴውና መንገዱ ምን እንደሆነ፣ እንዴት እንደሚሰራና እንዴት እንደሚያገለግል የሚሉት ነገር አለመኖሩ ነው።

በየዘመኑ የነበሩ የሁለቱ እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች የጋራ የሆኑ ገናን እሴቶች፣ ምግባሮች የሰው ለሰው ግንኙነቶች፣ የማኅበራዊና የግለሰባዊ አኗኗሮች የነዚህ ጥናቶች ትኩረት አለመሆናቸው ከላይ የተጠቀሱት ቀደምት ጥናቶች የጋራ መገለጫዎች ናቸው። በዚህ መሠረት የቀዳሚዎቹ ጥናቶችና የዚህ ጥናት ልዩነት እነዚህ በሁለተኛ ደረጃ የተዘረዘሩት ነጥቦች ናቸው። ይህም ማለት ቀዳሚዎቹ ጥናቶች በልዩነት ላይ ሲያተኩሩ ይሄ ጥናት ግን በአንድነት ላይ ያነጣጥራል፤ ለመቻቻል፣ ለመተሳሰብ፣ ለመረዳዳት፣ ለመደጋገፍ ቅድሚያ ይሰጣል።

በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት ከላይ ከተዘረዘሩት ቀደምት ጥናቶች በተለየ ሁኔታ በሰው ለሰው ግንኙነቶች ወይም በጀማው ህዝብ የጋራ እሴቶች (መስተጋብሮች) ላይ የተመሰረተ ሁኖ፤ የሁለቱ እምነት ተከታዮች የተሳሰሩባቸውን የጋራ ክሮች (common-bond) መርምሮ ፋይዳቸውን መግለጽ ነው። ይህ ማለት ግን ይሄ ጥናት በሁለቱ ሃይማኖቶች እምነት ተከታዮች መካከል ያሉ ልዩነቶችን አይመለከትም ማለት አይደለም። ባንዳሩ የመቻቻላቸው ምስጢር ነጥሮ እንዲወጣ የሚደረገው ከአንድነታቸውና ከልዩነታቸው ውስጥ ነው። ከሃዘን ደስታቸው፣ ከማግኘት ማጣታቸው ውስጥ ነው። በዚህ መሰረት ይሄ ጥናት የተመሰረተው ተመርጠው በሚጠኑ አወንታዊ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን፤ የተለያዩ ጉዳዮች ተብላልተውና ተጨምቀው ተጣርተው ነጥረው በሚወጡ ጉዳዮች ላይ ነው።

2.2፦ በሃይማኖት ዙሪያ ወሎ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች

ቀደም ሲል የተጠቀሱት ጥናቶች ክርስትናና እስልምና ወሎን ጨምሮ፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያሳለፉትን ሁነት የመረመሩ ሥራዎች ናቸው፡፡ በዚህ ንዑሰ ርዕስ ስር የቀረቡት ጥናቶች ደግሞ ወሎን እና አካባቢውን መነሻና መድረሻ ያደረጉ ሥራዎች ናቸው፡፡ ይህም ማለት የዚህን አካባቢ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች የሚለዩበት አንዱ ዋና ምክንያት አንድን የተወሰነ አካባቢ የጥናታቸው መነሻና መድረሻ ማድረጋቸው ነው፡፡

ይህ አካባቢ ደግሞ በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ጥንታዊና ታሪካዊ ጉዳዮችን አካቶ የያዘ እና ሁለቱ ሃይማኖቶችና የእምነቶቹ ተከታዮች በአንድነት የሚኖሩበት ሥፍራ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወሎ ጥንታዊና ታሪካዊ የክርስትና ሃይማኖት ቅርሶች እንዳሉ ሁሉ፤ በእስልምናውም በኩል የእምነቱን ቅዱሳን ቦታዎች ጨምሮ የቅዱስ ቁርዓን ጥንታዊ መፃሕፍትና ታሪካዊ መስጊዶች፤ አንዲሁም ከእስልምና ሃይማኖት ጋር ግንኙነት ያላቸው ቅርሶች በአካባቢው ይገኛሉ፡፡ በዚህም ሁለቱ ሃይማኖቶችና የእምነቱ ተከታዮች በአካባቢው ጥንታዊ መሠረት አላቸው (ጌታቸው፣ 1984 ዓ.ም፤ Hussein 1988; Taddesse 1972)፡፡

የጥናታቸውን ርዕሰ ጉዳይ በዚህ አካባቢ ያደረጉት እነዚህ ቀደምት ጥናቶች አንዳንዶቹ የእስልምና ሃይማኖትና ተያያዥ ጉዳዮችን በወሎ ከሥረ-መሠረቱ ሲመረምሩ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ የእምነቱን ተከታዮች የአምልኮ ሁኔታ፣ ማኅበራዊ ግንኙነት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ፣ ያጠኑ ናቸው፡፡ እንዲሁም ሌሎቹ በእምነቱ አባቶች ገድላትና ተአምራት፣ የማስተማር እና የእምነቱን ፍልስፍና የማስፋፋት ሂደት ላይ ሲያተኩሩ፤ ሌሎቹ ደግሞ የአካባቢውን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን መርምረዋል፡፡

በወሎ የእስልምናን ሃይማኖት ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር በማገናኘት በስፋት ያጠኑ (የመረመሩ) ኢትዮጵያዊ ምሁር ሁሴን አህመድ ናቸው፡፡ ተመራማሪው በተለያዩ ጊዜያት ባካባቢው የእስልምናን እምነት መነሻ በማድረግ በርካታ ምርምሮችን አካሂደዋል፡፡ የምርምራቸው መሰረታዊ ርዕሰ ጉዳይም የእምነቱን ቅዱስ ቦታዎችና ቅዱሳን አባቶች ጨምሮ፤ በወሎ የእስልምና እምነት መቼ እንደገባ፣ እንዴት እንደገባና እንደተስፋፋ፣ የት እና በነማን እንደተስፋፋ፣ በምን ሁኔታ ውስጥ እንደተስፋፋ፣ የሚመረምር ነው፡፡

እንዲሁም እምነቱ ያለፈባቸውን መልካምና መጥፎ አጋጣሚዎች፣ የአምልኮ ሥርአትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ነው። እስልምና በወሎ ከፖለቲካው፣ ከኢኮኖሚው፣ ከአስተዳደሩና ከማኅበራዊው ጉዳይ ጋር የነበረው ትስስር የሁሴን ጥናት ትኩረት የሰጠው ርእሰ ጉዳይ ነው። ከዚህም ሌላ በሁሴን ጥናት ውስጥ እስልምና በወሎ ከውጪው ዓለም ጋር (ከዓረብ አገራት) የነበረው ታሪካዊ ግንኙነት ተተንትኖ ቀርቧል። እነዚህ ነጥቦች ተተንትነው የቀረቡት በሚከተሉት የሁሴን ጥናቶች ውስጥ ነው (Hussein 1984; 1988; 1989; 1990; 1994; 2001; 2006)።

በሁሴን ጥናት መሠረት እስልምና ወደ ወሎ የገባው በተለያዩ ጊዜያት፣ በተለያዩ አጋጣሚዎችና ምክንያቶች ነው። ለዚህም በተለያዩ ወቅቶች ከዓረብ አገራት፣ ከሰሜን ምስራቅ ሸዋና ከደቡብ ምስራቅ ወሎ አጎራባች አካባቢዎች ወደ ወሎ የገቡ የሃይማኖትና የንግድ ሰዎች ለአብነት ተጠቅሰዋል (Hussein 2001)።

በሁሴን ጥናት ለእስልምና መስፋፋት በርካታ ምክንያቶች ተብራርተው ቀርበዋል። ለምሳሌ የአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) መስፋፋት፣ የንግድ ሰዎችና የሃይማኖቱ ሊቃውንት አስተዋጽዖ በምክንያትነት ተዘርዝረዋል። ከጥናቶቹ መረዳት እንደሚቻለው በተለይ በወቅቱ ባካባቢው የነበሩት የንግድ ማዕከላትና የንግድ መተላለፊያ መስመሮች ለእስልምና መስፋፋት ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው። ለዚህም ቃሉ እና ዳዋይ ከታጁራ ወደብ ጋር የነበራቸው ትስስር በማስረጃነት ቀርቧል (እንደላይኛው፤143)።

በሌላ በኩል ደግሞ ለሃይማኖቱ ጥልቅ እውቀት፣ ፍቅርና ስሜት የነበራቸው የእስልምና ምሁራን ለእምነቱ መስፋፋት መሠረት መጣላቸው ተብራርቷል። እነሱም በሁሴን ጥናቶች በስፋት ተዘክረዋል (Hussein 1989; 1997;2001)። እንዲሁም ለእምነቱ መንፈሳዊ ትምህርት መስጫ ማዕከላት በወሎ መመስረታቸውና መስፋፋታቸው ለእምነቱ መስፋፋት የነበራቸው ሚና መተኪያ የሌለው እንደነበር ጥናቱ ይገልፃል (Hussein 1988)።

የእምነቱ መሪዎችና የእምነቱ ማዕከላት ከአካባቢው ማኅበረሰብና በአካባቢው ከነበረው የፖለቲካ ሥልጣን መዋቅር ጋር የነበራቸው አንድነትና ልዩነትም ለእምነቱ መስፋፋት የራሳቸው ድርሻ እንደነበራቸው ጥናቶቹ ይገልጻሉ። በሁሴን ጥናት መሠረት በወሎ የተፈጠሩት የእስላም የአካባቢ ግዛቶችም ሃይማኖቱን ለማስፋፋት ከፍተኛ ሚና ነበራቸው (Hussein 2001)።

ከሁሴን ጥናቶች መረዳት እንደሚቻለው በወሎ እስልምና የተስፋፋው በሁለት መንገዶች አማካይነት ነው። ይኸውም አንደኛው በኃይል ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ በሰላማዊ መንገድ ነው። ለእምነቱ መስፋፋት ሚዛን የሚደፋው መንገድ ግን በሃይማኖቱ ሊቃውንት ብልሃትና ጥበብ አማካይነት በአብዛኛው በሰላማዊ መንገድ የተከናወነው ሂደት ነው። ለዚህም ከመነሻው የአካባቢው የእስልምና ባህል፣ ወግና ልማድ ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። የእምነቱ መመሪያ ሥርአቶችና መንፈሳዊ መርሆዎችም በወሎ እስልምና እንዲስፋፋ የየራሳቸውን ሚና ተጫውተዋል።

ለዚህ ማሳያ የሱፊ መርህ (ሥርአት/መመሪያ) በጥናቶቹ ውስጥ በስፋት ተብራርቷል። እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚታወቁት አራቱ የእስላም መዛሂብ (ሕግ) ሁለቱ በወሎ እንደሚገኙ ጥናቶቹ ጠቅሰው፤ ሻፊዒያና ሐናፊያ በስፋት ተብራርተዋል። ቃዲሪያ፣ ሻዝሊያ፣ ሰማንያ፣ ቲጃንያ፣ የተባሉት የወሎ እስልምና እምነት ሥርአቶችም በጥናቶቹ ውስጥ የተካተቱ ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው (Hussein 2001)። እንዲሁም በወሎ በተለያዩ ጊዜያት የእምነቱ ተከታዮች ስለሚጎበኟቸው የዚያራ ቦታዎችና የአምልኮ ተግባራት በሁሴን ጥናቶች ውስጥ በስፋት የተብራሩ ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው (Hussein 1990)።

ከዚህም ሌላ ከኦሮሞ መስፋፋትና በአካባቢው መስፈር ጋር ተያይዞ እስልምና ከአገር በቀሉ የአምልኮ ተግባር ጋር ያደረገውን "ጋብቻና ፍቺ" የሁሴን ጥናቶች ያብራራሉ። ለምሣሌ ጫት፣ ወዳጃና ዛር አሁንም ድረስ የዚህ አምልኮ መገለጫ ተግባራት እንደሆኑ ተብራርቷል። ድርጊቶቹም ከእስልምና ዶግማና ቀኖና (የሃይማኖት መመሪያ) ውጭ እንደሆኑ ተመልክቷል (Hussein 1984)።

በሁሴን ጥናት መሠረት በወሎ ለእስልምና መስፋፋት ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ አልነበረም። ለእምነቱ መስፋፋት መልካም አጋጣሚዎች እንደነበሩ ሁሉ መስፋፋቱን የሚገቱ መሰናክሎችም ገጥመውታል። ለዚህም በዋናነት የአፄ ዮሐንስ አራተኛ የሃይማኖት መመሪያ (አዋጅ) ለአብነት ተጠቅሷል። ከዚያም በኋላ የመጡት መሪዎች ለእስልምና ሃይማኖት የነበራቸው አወንታዊና አሉታዊ አመለካከት በማስረጃ ተተንትኖ ቀርቧል። የአሁኑ ዘመን ነባራዊ ሁኔታም ከእስልምና ሃይማኖት አንፃር ተቃኝቷል (Hussein 1994; 2001)።

ባጠቃላይ ሁሴን ወሎን መነሻ በማድረግ በተለያዩ ወቅቶችና የምርምር ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያካሂዷቸው ጥናቶች መሠረታዊ ጭብጣቸው ከላይ በዝርዝር በተጠቀሱት ነጥቦች ሊጠቃለሉ

ይችላሉ፡፡ እነዚህ ዝርዝር ጭብጦች አንድ ላይ ተጨምቀው ሲታዩ ደግሞ በአብዛኛው በዚያን ወቅት የነበረውን የፖለቲካ፣ የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚና የሃይማኖት ሁኔቶች መሠረት በማድረግ በወሎ የእስልምናን ሃይማኖትና የእምነቱን ተከታዮች ሁኔታ የሚመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የሁሴን ጥናቶች ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሌሎች ጥናቶች የሚለዩባቸው ባህርያት አሏቸው፡፡ ለምሣሌ በአንድ የተወሰነ አካባቢ ላይ ብቻ የተወሰኑ መሆኑ እንደ ተጠበቀ ሁኖ፤ በዋናነት ግን የተጠቀሙባቸው የመረጃ ምንጮች ወይም የመረጃ አጠቃቀም ስልታቸው ለአብነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የሁሴን የመረጃ ምንጮች በአበዛኛው በዚያው አካባቢ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ምንጮቹም የተሰበሰቡት አጥኚው ራሳቸው በቦታው ላይ በመገኘትና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳት ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ የሁሴን ጥናቶች በካልዓይ የመረጃ ምንጮች ላይ ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ በቀዳማይ የመረጃ ምንጮችም ጭምር የበለጸጉ ናቸው፡፡ እንዲሁም የሁሴን ጥናት ቃላዊ ተረክ (Oral History) ለታሪክ ጥናት እንዴት ሊያገለግል እንደሚችል አቅጣጫ የሚያሳይ ጥናት ነው፡፡

ነገር ግን የሁሴን ጥናት በአብዛኛው እስልምና ላይ ብቻ የተመሠረተ በመሆኑ ሌሎች ቀደምት አጥኚዎች እንዳደረጉት ሁሉ፤ የእሳቸው ጥናትም ከአብሮነት ይልቅ ልዩነት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ አልፎ አልፎም ቢሆን አጥኚው ለእስልምና ሃይማኖት ወገንተኝነት ይታይባቸዋል፡፡ ለምሳሌ አጥኚው የእስልምናን እድገትና ውድቀት የሚለኩት በየዘመኑ በነበሩ የፖለቲካ ሥርአቶች ሚዛን ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ አጥኚው እስልምናን ከፖለቲካ ሚዛን ላይ አውርደው ወሎ ውስጥ ያለውን የክርስትናና እስልምና እምነት ተከታዮች በጋራ ያስተሳሰራቸውን ክር አላጠኑም፡፡ የሁለቱ እምነት ተከታዮች ማንነት የሚገለጽባቸውን የጋራ እሴቶች አልመረመሩም፡፡ የጥናታቸው አካባቢም ቢሆን ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ መካከለኛው፣ ደቡብና ምስራቃዊው የወሎ ክፍል ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ስለዚህ ይሄ ጥናት ከሁሴን ጥናቶች የሚለየው በነዚህ ነጥቦች ምክንያት ነው፡፡

በሌላ በኩል ከሁሴን ጥናቶች ሌላ ወሎ ላይ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የጥናታቸው ማጠንጠኛ በማድረግ የተካሄዱ ጥናቶች አሉ፡፡ እነዚህ ጥናቶች በሁለት ምድብ ተከፍለው የሚታዩ ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ምድቦች እንደ ሁሴን ሁሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ

ትምህርት ክፍል ውስጥ የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው። የቀረቡትም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ነው (Asnake 1983; Fekadu 1990; Gashaw 2003)።

ሁለተኛዎቹ ምድቦች ደግሞ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በሶሻል አንትሮፖሎጂ፣ በውጭና በአገር ውስጥ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ የትምህርት ክፍሎች አማካይነት የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው። የጥናቶቹ ርዕሰ ጉዳይ የሃይማኖቶቹን እሴቶች የተመለከተ ነው። የቀረቡትም ለሦስተኛና ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ነው (kelklachew 1997; Berhanu 1998; Habtamu 2010; Assefa 1987; Rukya 2013; ሞላ፣ 1999 ዓ.ም.)። የነዚህ ስራዎች ክለሳ የታሪክ ትምህርት ክፍሎቹን በማስቀደም በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል።

በታሪክ ትምህርት ክፍል የተካሄዱት ጥናቶች በሦስት መሠረታዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ይኸውም በአንድ በተወሰነ የታሪክ ዘመን ውስጥ በወሎ የነበረውን ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መርምሮ ውጤቱን መግለጽ ነው። ከዚህ ውጤት ላይ ለመድረስ ደግሞ በነዚህ ጥናቶች ውስጥ ሃይማኖት ሰፊ ቦታ አለው። በዚህም ሃይማኖታዊው ጉዳይ ሦስቱንም ጥናቶች አንድላይ የሚያገናኝ የጋራ ክር ነው። ከጥናቶቹ መረዳት እንደሚቻለው ፖለቲካዊውም ይሁን አስተዳደራዊ ጉዳዩን አልያም ኢኮኖሚያዊውን ሁኔታ መርምሮ ለመረዳት ያለ ሃይማኖቶቹ ሚና አይቻልም። ምክንያቱም በወሎ የተካሄዱት የፖለቲካ፣ የአስተዳደርና የኢኮኖሚ ሽኩቻዎች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከሃይማኖቶቹ ጋር የተሳሰሩ እንደነበሩ ከጥናቶቹ መረዳት ይቻላል።

ለምሳሌ በወሎ የተካሄደውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና አስተዳደራዊ ጉዳይ (ሁኔታ) ከወረሂመኖ ኢማሜት ወይም ማመዶች ሥርዎ-መንግሥት ነጥሎ ማጥናት አይቻልም። የማመዶች ሥርአተ-መንግሥትም ያለ እስልምና ሃይማኖት ትርጉም አይኖረውም። እንዲሁም የወሎንም ሆነ አጠቃላይ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ለመረዳት ያለ የጁ ወረሴህ (ዘመነ-መሳፍንት) ሥርአተ-መንግሥት አይታሰብም። በጥናቶቹ መሰረት የየጁ ወርሴህ ደግሞ ከእስልምናና ክርስትና ሃይማኖት ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ነው።

ባጠቃላይ በነዚህ ጥናቶች መሠረት የፖለቲካው መሪዎች ከሃይማኖቶቹ መሪዎችና አባቶች፤ ሃይማኖቶቹ፣ የሃይማኖቶቹ መሪዎችና አባቶች ደግሞ ከፖለቲካው ጋር ጡት የተጣቡ ነበሩ።

በዚህም አንዱ በሌላው ውስጥ ይኖራል፤ ይገለፃልም። ጥናቶቹ እንደሚሉት ጡት መጣባቱ ያለምክንያት አልነበረም። ምክንያቱም የኢኮኖሚና የንግድ ቦታዎችን ለመመስረት፣ ለመቆጣጠርና ለማስፋፋት ሃይማኖቶቹ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው። ኢኮኖሚውን መቆጣጠር ማለት ደግሞ የፖለቲካውን በትረ-ሥልጣን መጨበጥ ማለት ነው። በዚህ መሠረት የነዚህ ሦስት ጥናቶች መሠረታዊ ርዕሰ ጉዳይ ወይም ጭብጥ ይህንን ሁነት መርምሮ መግለጽ ነው። ጥናቶቹ በተናጠል ከዚህ ቀጥለው ባጭሩ ተጠቃለው ቀርበዋል።

እስናቀ ዓለ "Aspects of the political History of wollo: 1872-1917" በሚል ርዕስ ከአፄ ዮሐንስ አራተኛ እስከ ልጅ ኢያሱ ፍፃሜ መንግሥት ድረስ በወሎ የተከናወኑ ፖለቲካዊ ሁነቶችን መርምረው ገልጸዋል። የአስናቀ ጥናት በዚህ የፖለቲካ ውጣ ውረድ ውስጥ ሁለቱ ሃይማኖቶችና የእምነቶቹ ተከታዮች ከፖለቲካ ሥርአቱ ጋር የነበራቸውን ትስስርና ሚና፣ ያገኙትን መልካም እድል እና የደረሰባቸውን መጥፎ አጋጣሚ በማስረጃ አስደግፈው ገልጸዋል።

ከጥናቱ መረዳት እንደሚቻለው በዘመኑ የነበሩ የአካባቢው ትናንሽ ገዥዎችም ሆኑ የሃገሪቱ መሪዎች ከወሎ መሬትና ሕዝብ ጋር የጠበቀ ቁርኝት ነበራቸው። ለዚህም እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ምክንያቶች እንደነበሯቸው የአስናቀ ጥናት ይገልፃል። ከዚህ ፍላጎታቸው ጋር ተያይዞም ከሃይማኖታዊው አንፃርም ይሁን፤ ከፖለቲካዊው ጉዳይ በወሎ በርካታ ክስተቶች ተከናውነው አልፈዋል። የፖለቲካ ልሂቃኑ እምነትን በሃይል ከማስቀየር ጀምሮ ለፖለቲካ ሥልጣን ሲሉ ራሳቸው በፍላጎት ሃይማኖታቸውን እስከመቀየር ደርሰዋል። እንዲሁም በአምቻና ጋብቻ መተሳሰሩን ጨምሮ፤ በሃይማኖት ተመሳስለዋል። በዚህ ሂደት ውስጥ በወሎ አንዱ ሲወድቅ፣ አንዱ ሲነሳ፤ አንዱ ሲደሰት ሌላው ሲከፋ፤ ዘመናት አልፈዋል። የአስናቀም ጥናት ርዕሰ ጉዳይ እነዚህን ፖለቲካዊ ክስተቶች በመረጃ እያጣቀሰ የሚያሳይ ነው።

የአስናቀ ጥናት ከሁሴን "Islam in Nineteenth-Century Wollo, Ethiopia, 2001" ጋር በብዙ መንገድ ይገናኛል፤ ይመሳሰላል፤ ይዛመዳል። የጥናታቸው አካባቢም በተመሳሳይ ሁኔታ ደቡብ ወሎ ላይ የተመሰረተ ነው። ጥናቱን ካካሄዱበት ዘመን አንፃር ግን የአስናቀ ጥናት በኩር ነው። የሁሴን ጥናት ደግሞ የአስናቀ ተከታይ ነው። ባጠቃላይ የአስናቀ ጥናት የሁለቱን እምነት ተከታዮች ማኅበራዊ ሁኔታ ከፖለቲካው አንፃር የሚዳስስ ቢሆንም ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋር የሚያገናኘው ጉዳይ ግን የለም።

የወሎ ህዝብ በተለያዩ ዘመናት ከማዕከላዊውም ይሁን ከአካባቢው ለበቀለ ገዥዎችና ሹሞች እድሜ ልኩን ገባርና አገልጋይ በመሆን ማኅበራዊ ሕይወቱን ሲገፋ መኖሩን የሚገልጸው ጥናት ደግሞ የፍቃዱ ቤኛ ሥራ ነው። ፍቃዱ "Land and Peasantry in Northern Wollo, 1941-1974, Yejju and Rayya and Qobbo *Awarajja*." በሚል ርዕስ ያካሄዱት ጥናት ለአጠራርና ለቁጥር አደጋች በሆኑ የመሬት ስሪቶች ወሎና የወሎ ህዝብ ምን ያህል የተቆራኘ እንደነበር የሚያሳይ ጥናት ነው። ህዝቡን በላዩ ላይ ተጭነውት የነበሩት የአካባቢው ገዥዎችም እንዲሁ በርካታ መሆናቸውንም የፍቃዱ ጥናት ይገልፃል። እነዚህ ገዥዎች ከአካባቢው አልፈው በጎንደር ቤተ መንግሥት ውስጥም አድራጊ ፈጣሪ እንደነበሩ ጥናቱ ያስረዳል። እንዲሁም ገዥዎቹ ከሁለቱ ሃይማኖቶች ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደነበሩም የፍቃዱ ጥናት ያብራራል። ለምሳሌ የየጁ ወረሴዎችም ሆኑ የአንባሰል ጐንጥራሮች፣ አለያም የዋግ ሹማምንቶች፤ ወረ-ቃሉዎችም ሆኑ የአውሳ ሱልጣኖች ወይም የወረሂመኖ ኢማሞች በፍቃዱ ጥናት መሠረት የዘር ሐረጋቸው የሚመዘዘው ከሃይማኖቶቹ ውስጥ ነው። በዚህም በወሎ የገዥና የተገዥ ልዩነት በመፍጠር የኢኮኖሚው አድራጊና ፈጣሪዎች ነበሩ።

በአካባቢው ተንሰራፍተው የነበሩት የመሬት ስሪቶች ደግሞ ከሃይማኖቶቹ ወይም ከእምነቶቹ መሪዎች ጋር የተገናኙ ነበሩ። የፍቃዱ ጥናት እንደሚያስረዳው ለዚህ ሁሉ መሠረቶቹና ተዋንያኖቹ ደግሞ ከአገር በቀሉ እምነት ጋር ግንኙነት የነበራቸው የየጁ ኦሮሞዎች ናቸው። ፍቃዱ በጥናታቸው ውስጥ ለጥናታቸው መነሻ ባደረጓቸው አካባቢዎች ላይ እጅግ በርካታ አካባቢዎችንና ታሪካዊ ሁነቶችን ተመልክተዋል። በጣም የሚገርመው ነገር የፈቃዱ ጥናት በሰፈር ውስጥ ሳይቀር የተከናወኑ ታሪካዊ ሁነቶችን ጭምር በስፋት ማጥናቱ ነው። የነዚህን ክስተቶች እውነተኛነት (ተአማኒነት) ለማረጋገጥ አጥኚው ያደረጉት ጥረት ሲታይ ደግሞ ጥናቱን ምን ያህል በፍላጎት እንደሰሩት ያስረዳል። ሌላው የፍቃዱ ጥናት ጠንካራ ጎን ሁሴን ቃላዊ ተረክን (Oral History) ለታሪክ ጥናት በሚገባ እንደተጠቀሙበት ሁሉ እሳቸውም ቃል ግጥምን ለታሪክ ጥናት መጠቀማቸው ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ የፎክሎር የእውቀት ዘርፍ ለታሪክ የእውቀት ዘርፍ (ጥናት) እንዴት ሊያገለግል እንደሚችል ማሳያ አብነት ነው።

በሌላ በኩል የፈቃዱ ጥናት ከ"1941-1974" በሚል የጊዜ ገደብ የተወሰነ ቢሆንም፤ የጥናቱ አብዛኛው ክፍል የሚሸፍነው ግን ከ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተከናወኑ ድርጊቶችን ነው። እንዲሁም በፈቃዱ ጥናት ውስጥ ተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳዮች በየምዕራፎቹ በተደጋጋሚ

ተጠቅሰው ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሁለት ነጥቦች በፈቃዱ ጥናት ውስጥ የሚታዩ እጥረቶች ናቸው፡፡

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የፈቃዱ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ በወቅቱ የነበረውን የመሬት ስሪት መነሻ በማድረግ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች ከታሪክ አንፃር ማጥናት ነው፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሥር ግን በርካታ ታሪካዊ ክስተቶች ተመርምረዋል፡፡ ከነዚህ ታሪካዊ ክስተቶች ውስጥ አንድ መሠረታዊ ቁም ነገር ነቅሶ ማውጣት ይቻላል፡፡ ይኸውም የአካባቢው ማኅበረሰብ ከላይ የተዘረዘሩት ታሪካዊ ክስተቶች ሲፈራረቁበት በመኖሯቸው ለዘመናት ደህይቶ፣ ታርዞና ተጎሳቁሎ በበሽታ ማቆ ሕይወቱን ሲገፋ የኖረ ህዝብ መሆኑን ማሳየቱ ነው፡፡ ይህም ሆኖ የአካባቢው ማኅበረሰብ እነዚህ ፈታኝና ተከታታይ የሕይወት ውጣ ውረዶች ቢገጥሙትም እንኳን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በባህልና በሌሎች ሁኔታዎች ሳይከፋፈል በጋራ ተደጋግፎ፣ ተቻችሎና ተከባብሮ የኖረ ህዝብ መሆኑን የፍቃዱ ጥናት ያስረዳል፡፡ በዚህም የሁለቱ እምነት ተከታዮች ከልዩነታቸው ይልቅ አንድነታቸውን አጎልብተውና አፅንተው፤ ለዚህ የሚረዷቸውንም የጋራ እሴቶች ፈጥረው የኖሩ ህዝቦች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ነገር ግን በፈቃዱ ጥናት ውስጥ የተዘረዘሩት ታሪካዊ ሁነቶች የአካባቢው ማኅበረሰብ በአንድነትና በሰላም ለመኖር የረዱትን እሴቶች የሚገልጹ ወይም የሚመረምሩ ሳይሆኑ፤ በአንፃሩ በወቅቱ የነበሩ ገዥ መደቦች የፈጸሙትን የሃብትና የሥልጣን ሽኩቻ፤ የልዩነት፤ ያለመረጋጋት የጭካኔ፣ የስግብግብነት፣ ከመተማመን ይልቅ ሰፍኖ የነበረውን የእርስ በርስ ጥርጣሬ የሚገልጹ ናቸው፡፡ ስለዚህ የወሎዬዎች የጋራ እሴቶች የፍቃዱ ጥናት ትኩረት አይደለም፡፡

በወሎ የማዕከላዊው መንግሥት የቢሮክራሲ መዋቅር (ሠንሠለት) ወይም የአገዛዝ ዘይቤ ምን አይነት ገጽታ እንደነበረው የሚያሳየው ጥናት ደግሞ የጋሻው መሐመድ የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጽሑፍ ነው፡፡ የጋሻው ጥናት ለታሪክ ትምህርተ ክፍል የቀረበ ሲሆን፤ "Administrative History of Wollo: 1941-1974" የሚል ርዕስ አለው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ርዕሰ ጉዳይ ወይም ጭብጥ በወሎ የነበረውን የአገዛዝ መዋቅር በመዘርዘር የመዋቅሩ ዓላማና ተግባር ምን እንደነበር መመርመር ነው፡፡ በዚህም ከማዕከላዊው መንግሥት እንደራሴዎች እስከ አካባቢው ጭቃ ሹሞች በወሎ ህዝብ ላይ ያደረሱትን ግፍ ይዘረዝራል፡፡ በጥናቱ መሠረት በወቅቱ የነበረው የአስተዳደር (የአገዛዝ) ዘይቤ ከህዝቡ ጥቅምና ፍላጎት

በተቃራኒ የቆመ ነበር። ምክንያቱም የመዋቅሩ ዓላማና ተግባር የሥርአቱን ህልውና በማስጠበቅ የሥርአቱን ሹማምንት ፍላጎት ከማርካት የዘለለ ትርጉም አልነበረውም።

የጋሻው ጥናት እንደሚያስረዳው የሹማምንቱ ፍላጎት ደግሞ በየትኛውም ሁኔታ ልጓም አልባ በመሆኑ፤ ለወሎ ህዝብ ሰሪ ባንገት ከመሆን ያለፈ የሚረካበት አጋጣሚ አልነበረውም። በዚህ መሠረት ህዝቡ በወቅቱ የነበረው ብቸኛ የምሬቱ መግለጫና መተንፈሻ መሣሪያ ፎክሎሩ እንደነበር ከጋሻው ጥናት መረዳት ይቻላል። የሚከተሉትን ቃል ግጥሞች ለአብነት እንጠቅሳለን።

እነ ደጃዝማች ቤት፣ እነ ቀኛዝማች ቤት፣ የለም ገላጋይ፤
እንብላ እንብላ ነው እንደ አልጋ ተባይ።

አልጋው ተባይ ሆነ ግኑ ቁንጫ፤
አላህ የወሎ ሰው አጣ መቀመጫ።

የነጭ ለባሽ ቀብር መቺ እንደዚህ ነበር፤
በታች አጋም አርጎ በላይ ቀጋ ነበር (Gashaw 2003;108)።

ከቃል ግጥሞቹ መረዳት እነደሚቻለው ህዝቡ ብሶቱን ለገዥዎቹም ለፈጣሪውም ማሰማቱን ነው። ገዥዎቹ ጆሮ ዳባ ልበስ ቢሉትም ፈጣሪው ግን የሰማው ይመስላል። ምክንያቱም ህዝቡ ትንቢትና ዛቻ ከማሰማት አልፎ ክንዱን ወደ ገዥዎቹ ግንባር መሰንዘር ይጀምራል። መልእክቱንም በሚከተሉት ቃል ግጥሞች ያስተላልፋል።

ያሁኑ ሰኔ አልፎ የሚመጣው ሰኔ፤
እንጃ መድረሻውን ጭቃና ምስለኔ።

አትውረዱ ጨሬ በርበሬ ብላችሁ፤
መሰንበት ይሻላል አልጫ በልታችሁ (እንደላይኛው፤ 12)።

ባጠቃላይ ከጋሻው ጥናት መረዳት የሚቻለው ቁም ነገር የወቅቱ የብልሹ አስተዳደርና አሰራር ምንጭ ሥልጣንን ያለ አግባብ መጠቀም ወይም በሥልጣን መባለግ ነው። የሥልጣን ምንፅፅ ደግሞ እውቀትና ጥበብ ሳይሆን በአምቻና ጋብቻ ላይ መመስረቱ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ቅጥ ላጣ የሙስናና የመተያያ (እጅ መንሻ)[24] ሥርአት መሠረት በመሆናቸው

[24] እንዳለመታደል ሆኖ የዚህ አይነቱ ባህል አሁን ባለንበት ዘመንም የቀጠለ ይመስላል። ልዩነቱ የዚያኔየው የሙስና መገለጫ "መተያያ" ወይም "የእጅ መንሻ" በሚል የሚገለጽ ሲሆን፤ ያሁኑ ዘመን ደግሞ "ኪራይ ሰብሳቢ" በሚል ብሂል መገለጹ ነው።

ሽማምንቱ በወለኦ ህዝብ ላይ ሕጋዊ ቀማኛ እንዲሆኑ ከለላ ሰጥቷቸዋል። በመሆኑም የወለኦ ሕዝብ ለዘመናት ፍትሕና መልካም አስተዳደር እንደናፈቁት ዘመናት ማለፋቸውን ጥናቱ የሚያነሳቸው መሠረታዊ ነጥቦች ናቸው።

በጋሻው ጥናት በአንድ የተወሰነ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የነበረ የአስተዳደር (የአገዛዝ) ዘይቤ ተጠንቶ ውጤቱም የሥርአቱ አስፈፃሚዎች ለወለኦ ህዝብ አገልጋይ ሳይሆኑ በተቃራኒው በህዝቡ ተገልጋይ የሆኑበትን አጋጣሚ ያመቻቸ የአገዛዝ ሠንሠለትና ሥልት እንደነበር አሳይቷል። ጋሻው እንደ ፍቃዱ ሁሉ ፎክሎርን ለታሪክ ጥናት ግብአት በማድረግ የተጠቀመ ተመራማሪ ናቸው። በዚህም በጋሻው ጥናት ውስጥ በፎክሎር አማካይነት በርካታ ታሪካዊ ሁነቶች ሊነሱ ችለዋል። ምንም እነኳን የጋሻው ጥናት የሁለቱን እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች የማኅበራዊ ሕይወት ውጣ ውረድ የሚገልጽ ቢሆንም፤ ከሁለቱ እምነት ተከታይዮች የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም የማኅበራዊ ሕይወት መስተጋብር አለያም የሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋር የሚገናኝ ርዕሰ ጉዳይ አላነሳም።

ከዚህ በላይ የቀረቡት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በታሪክ ትምህርት ክፍል ውስጥ ወለኦ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የጥናቶቹ ርዕሰ ጉዳይም ሃይማኖቶቹን ከታሪክ፣ ከፖለቲካና ከኢኮኖሚ ሁኔታዎች ጋር በማገናኘት የዘመኑን ነባራዊ ሁኔታዎች የመረመሩ ጥናቶች ናቸው። ነገር ግን የጥናታቸው ርዕሰ ጉዳይ ከሃይማኖቶቹ እሴቶች ጋር የተገናኘ ሌሎች ጥናቶች አሉ። እነዚህ ጥናቶች ያነሱትን ርዕሰ ጉዳይ ወይም ጭብጥ ብቻ መሠረት በማድረግ ከዚህ በታች ተጠቃለው ቀርበዋል።

2.3፦ በሃይማኖታዊ እሴቶች (ትውፊቶች) ወለኦ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ተዛማጅ ጥናቶች ደግሞ ከታሪክ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ውጪ፤ በሌሎች የትምህርት ክፍል ተማሪዎች አማካይነት የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው። ጥናቶቹ በሶሻል አንትሮፖሎጂ፣ በውጭና በአገር ውስጥ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች አማካይነት የተካሄዱ ምርምሮች ናቸው።

የምርምሮቹ ዋና ዓላማም በወለኦ ከሃይማኖት ጋር የተገናኙ ባህላዊ ክንውኖችን እና ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ማጥናት ነው። በዚህም ጥናቶቹ የሃይማኖቶቹን ተከታዮች የእምነት (የአምልኮ) ሁኔታ፣ ባሕል፣ ወግና ልማድ፣ እንዲሁም ማኅበራዊ ግንኙነት መርምረዋል። በወለኦ

ሃይማኖትን መነሻ በማድረግ ባህላዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ከመረመሩ አጥኚዎች መካከል አንዱ ከልክላቸው ዓለ ናቸው። የከልክላቸው ጥናት በሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ ሲሆን፤ የጥናቱ ርዕስ "Religion, Rituals, and Mutual Tolerance in Wollo: The Case of Kabe South west Wollo." የሚል ነው።

በዚህ የጥናት ርዕስ አማካይነት ከልክላቸው የሃይማኖት ፋይዳን ንድፈ ሃሳብ መነሻ በማድረግ እስልምናን እና የእምነቱን ተከታዮች መንፈሳዊ ተራክቦ መርምረዋል። እንዲሁም የእስልምናን መርሆዎች (የእምነቱን መመሪያዎች/ ሕግጋት) ማጠንጠኛ በማድረግ የእምነቱን ተከታዮች የአምልኮ ዘይቤ ፈትሸዋል። በዚህም ተመራማሪው ጥናታቸውን ባካሄዱበት አካባቢ ከእስልምና እምነት ጎን ለጎን የሚከናወኑ ልማዳዊ የአምልኮ ተግባራት መኖራቸውን ዘርዝረዋል። ለዚህም ዚያራ፣ ወዳጃና ፀበል መጠመቅ...ወዘተ ለአብነት ተጠቅሰዋል።

በሌላ በኩል ከልክላቸው ጥናቱን ባካሄዱበት አካባቢ በእስልምናና ክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል ሃይማኖት የልዩነት ምክንያት አለመሆኑን የተለያዩ አብነቶችን በመጥቀስ የእርስ በርስ ግንኙነቶችን ጠቁመዋል። ለምሳሌ የሃይማኖቶቹ ልዩነት እንደተጠበቀ ሁኖ በአካባቢው ከሥጋ (እርድ) በስተቀር ሌላ ጎልቶ የሚታይ የልዩነት ምንጭ አለመኖሩን ገልጸዋል። ጥናቱ እንደሚለው ሥጋም ቢሆን እንኳን በአንድ ቤት ውስጥ እና ምልክት ተደርጎበት በአንድ ገመድ ላይ ሊሰቀል እንደሚችል አብነት በመጥቀስ ገልጸዋል። በከልክላቸው ጥናት መሠረት የአካባቢው ማኅበረሰብ በሀዘን፣ በደስታ፣ በሥራና በሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች በመረዳዳትና በመደጋገፍ፣ በሰላምና በፍቅር ተቻችሎ የሚኖር ህዝብ ነው። ከዚህም ባለፈ ባል ወይም ሚስት አለያም ልጆች አንዱ የሌላ እምነት ተከታይ ሊሆኑ ይችላሉ።

ነገር ግን ከከልክላቸው ጥናት መረዳት እንደሚቻለው በአሁኑ ጊዜ "የእስልምና መሠረታዊ መርሆዎች ተጥሰዋል!" በሚሉ አካላት እነዚህ ግንኙነቶች ወይም የጋራ እሴቶች ፈተና እየገጠማቸው እንደሚገኝ አብነት እየጠቀሱ አብራርተዋል። በዚህም የአካባቢው ማኅበረሰብ ማኅበራዊ ግንኙነት መሠረት የሆኑ እንደ እድርና እቁብ የመሳሰሉ ማኅበራዊ ተቋማት በአሁኑ ጊዜ የሚገኙበት ነባራዊ ሁኔታ ማሳያ ሁኖ ቀርቧል። ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ያካተተው የከልክላቸው ጥናት ብዙ ጠንካራ ጎኖች አሉት። ለምሳሌ ርዕሰ ጉዳዩን በዚያን ወቅት አንስቶ ለማጥናት መሞከሩ በራሱ አንዱ ጠንካራ ጎኑ ነው። ምክንያቱም በወቅቱ የአክራሪነት ዝንባሌ

ለነባሩ የአብሮነት ባህል አደጋ ሊሆን እንደሚችል ፍንጭ የሰጠ የመጀመሪያ ሊባል የሚችል ጥናት ነበር። ከዚህም ሌላ አውድን መሠረት አድርጎ በአንድ የተወሰነ ጠባብ አካባቢ (ቀበሌ) ጥናቱ መካሄዱ ሁለተኛው ጠንካራ ጎኑ ነው። በዚህም አጥኚው ድርጊቶቹን ራሳቸው በቦታው ተገኝተው የድርጊቶቹን ባለቤቶችና ፈፃሚዎች በመጠየቅ መረጃ ሰብስበዋል።

ባጠቃላይ የከልክላቸው ጥናት ርዕሰ ጉዳይ የሃይማኖትን ፋይዳ መነሻ በማድረግ፣ ከእስልምና መርሆዎች እንፃር የእምነቱን ተከታዮች የአምልኮ ሥርአትና ሁኔታ መርምሮ መግለጽ ነው። በሌላ አባባል የከልክላቸው ጥናት የእስልምናውን መርህ (መመሪያ) እና የእምነቱን ተከታዮች የአምልኮ ሁኔታ (ዘይቤ) ከአካባቢው ልማዳዊ ድርጊት ጋር አገናኝቶ የሚያጠና ነው። የሁለቱ እምነት ተከታዮች ማኅበራዊ ግንኙነት በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሰውም የነዚህን መርሆዎች የአተገባበር ሂደት ለማሳየት ሲባል ነው።

ከዚህ ባለፈ የሁለቱን እምነት ተከታዮች የጋራ እሴቶች ማጥናትና ፋይዳቸውን ተንትኖ ማሳየት የከልክላቸው ጥናት ዓላማ አይደለም። የሁለቱ እምነት ተከታዮች የጋራ እሴቶች የትኞቹ እንደሆኑ፣ እንዴት እንደሚሰሩና ለምን እንደሚያገለግሉ ከልክላቸው አላጠኑም። የዚህ ጥናት ትኩረት ግን የጋራ እሴቶችና የሁለቱ እምነት ተከታዮች መስተጋብር ነው። የጥናቱ አካባቢና ስፋትም ከከልክላቸው ጥናት ጋር የተለያየ ነው።

ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በወሎ በእስልምናውም ሆነ በክርስትናው በኩል በርካታ ቅዱሳን አባቶችና እናቶች የሚገኙበት አካባቢ ነው። የወሎ ደጋጎችና አራት ዓይናዎች የሚገኙበት ቦታ ነው። እነዚህ ቅዱሳን፣ ደጋጎችና አራት ዓይናዎች የእምነቶቹን መመሪያዎች የሚያስተምሩ ሊቃውንት፣ ክስተቶችን የሚተነብዩ ነቢያት፣ ያዘነና የተከዘን የሚያጽናኑ ረዳት፣ የጠወለገን ተስፋ የሚያለመልሙ ብጹአን፣ የተጣላ በማስታረቅ ቂም የሚያሽሩ የአገር ሽማግሌዎች፣ የታመመን የሚፈውሱ መድኃኒቶች ናቸው። ባጠቃላይ ለዓለማዊውም ሆነ ለመንፈሳዊው ሕይወት ተጠሪና መንገድ መሪ አባቶች ናቸው (Hussein 2001; ጌታቸው፣ 1984፣ ዓ.ም)። ከዚህ አንፃር እነዚህን አካላት እና ከነሱ ጋር የተያያዙ ርዕሰ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ የተካሄዱ ጥናቶች አሉ። ከነዚህ ጥናቶች መካከል (Berhanu 1998; Assefa, 1987; Habtamu 2010; ሞላ፣ 1999፣ ዓ.ም.) ለአብነት የሚጠቀሱ ሥራዎች ናቸው።

የብርሃኑ ጥናት "Islamic Oral Poetry in Wollo: A Preliminary Descriptive Analysis." በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን፤ የአሰፋ ጥናት "Some Prominent Feature of the Menzuma Genre as Practiced in the Wollo Region" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። የሃብታሙ ጥናት ደግሞ "Thematic Approach to the Manzumas (poems) of Sheikh Muhammad Yassin (1895-1972) in South Wollo." የሚል ርዕስ አለው።

እነዚህ ጥናቶች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች ናቸው። የነዚህ ጥናቶች ርዕሰ ጉዳይ በወሎ ያለውን የመንዙማ ጭብጥ፣ ቅርጽና ይዘት ተንትኖ መግለጽ ነው። መንዙማዎቹ እንዴት እንደሚከወኑ፣ በማንና ለምን እንደሚከወኑ፣ የት እና መቼ እንደሚከወኑና በምን እንደሚከወኑ መርምሮ መግለጽ ነው። እንዲሁም ከመንዙማዎቹ ጋር የተያያዙ ቃል ግጥሞችን ተንትኖ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ማሳየት ነው።

እነዚህ ጥናቶች የአካባቢውን ባህላዊና ማኅበራዊ አውድ መነሻ በማድረግ የተካሄዱ ጥናቶች ቢመስሉም መሠረታዊ መነሻቸው ግን ቃላዊ ግጥሞቹ (text) ናቸው። ነገር ግን አጥኚዎቹ በዚህ ላይ ተመስርተው መንዙማ የራሱ የሆነ የአከዋወን ሥርአት፣ የመከወኛ ቦታ፣ የአከዋወን ሂደት፣ ደንብና ሥርአት ያለው መሆኑን አብራርተዋል። የመልእክቱን ስፋትና ጥልቀትም ለማሳየት ሞክረዋል። የእስልምና እምነት ተከታይ ምእመናን ለፈጣሪያቸውና ለሃይማኖቱ አባቶች ያላቸውን ጥልቅ ስሜትና ፍቅር እንዲሁም ክብር መግለጫ መሣሪያ መሆኑ በጥናቶቹ የመንዙማ ፋይዳ ሁኖ ተግልጿል። በመጨረሻም ጥናቶቹ መንዙማ የመንፈሳዊ እርካታ ምንጭ መሆኑን ያረጋግጣሉ። ከመንፈሳዊ ቃላዊ ግጥሞች አንፃርም ዘርፋቸው የተለያየ መሆኑን በመዘርዘር ተመሳሳይ ፋይዳ እንዳላቸው ማሳየት የጥናቶቹ ዓላማ ነው።

በሌላ በኩል "በጉባላፍቶ ወረዳ የሼህ ለጋ ባህላዊ የግጭት ቁጥጥርና አፈታት" በሚል ርዕስ ሞላ መኮንን ጥናት አካሂደዋል። የሞላ ጥናት በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ ነው። የሞላ ጥናት ዋና ዓላማ የሼህ ለጋን ልማዳዊ ደንብ አጠቃላይ ገጽታና ክዋኔ በመግለጽ ይዘቱን መተንተን ነው። የጥናቱ ጭብጥ ደግሞ የግጭት አፈታቱን ሂደት፣ ሥርአትና ደንብ መሰረት በማድረግ የማስፈጸሚያ ስልቶቹን መግለጽ ነው። ስለዚህ ከዚህ በላይ ተጠቃለው የቀረቡት አራት ጥናቶች ያነሱት መሠረታዊ ርዕሰ ጉዳይ የሃይማኖታዊ ቃል ግጥሞችንና የመንዙማዎቹን አጠቃላይ ምንነትና ፋይዳ

እንዲሁም የባህላዊ ግጭት አፈታት ሥልትና ሂደቱን እና የማስፈጸሚያ ስልቱን የተመለከቱ ናቸው።።

ምንም እንኳን በነዚህ ጥናቶች የተነሱት ርዕሰ ጉዳዮች የፎክሎር ዘርፎችና ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋር የሚገናኙበት በርካታ መገለጫዎች ቢኖሯቸውም የነዚህ ጥናቶች ትኩረት ቅርጽና ይዘት እንዲሁም በክዋኔዎቹ ሂደትና አፈጻፀም ላይ የተመሰረተ ነው።። ከዚህ ባለፈ የመንዙማዎቹ ክዋኔም ሆነ የግጭት አፈታቱ ሂደት ለሁለቱ እምነት ተከታዮች የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም አብሮነት እንዴት ሊያገለግሉ እንደሚችሉ አላጠኑም።። ይህም የጥናታቸው ዓላማና መነሻ አይደለም።። ስለዚህ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ከነዚህ ጥናቶች ጋር ግንኙነት የለውም።።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የወሎና የወሎ ማኅበረሰብ መገለጫ እሴቶች በርካታ ናቸው።። ከነዚህ እሴቶች መካከል አንዱ የአካባቢው ማኅበረሰብ መግባቢያ ቋንቋ ነው።። ለምሣሌ ወሎ ባነጋገር ለዛው ወይም ፊሊጡ ተለይቶ ይታወቃል (Amsalu & Habte Mariam Marecos 1969)። የወሎ ሰው በቋንቋው ተለይቶ መታወቁ ብቻ ሳይሆን ከቋንቋው ጋር በተያያዘ በርካታ መግለጫዎችና በርካታ እሴቶች አሉት።። እነዚህን እሴቶች መነሻ በማድረግም ተመራማሪዎች ወሎ ላይ ጥናት አካሂደዋል።። ከነዚህ ጥናቶች መካከል የሩቅያ ሐሰን ጥናት ይጠቀሳል።። የሩቅያ ጥናት "Ethnography of Communication of the Amharic Speaking Muslim Community of South Wollo." የሚል ርዕስ አለው።። ጥናቱ የቀረበው ለውጭ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ ነው።።

የጥናቱ አካባቢ ደግሞ ደቡብ ወሎ ዞን ውስጥ ሁኖ፤ ተሁለ ደሬ፣ ደሴ ዙሪያ፣ ደሴና ኩታበር ወረዳዎች ናቸው።። ጥናቱ የተካሄደባቸው ማኅበረሰቦችም በነዚህ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ የእስልምና እምነት ተከታይ የማኅበረሰብ ክፍሎች ናቸው።። የሩቅያ ጥናት ዋና ዓላማ እነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች በቋንቋቸው አማካይነት ያዳበሩትን እሴት መርምሮ ፋይዳውን መግለጽ ነው፤ የቋንቋውን ባህላዊ ገጽታ መመርመር ነው።።

በዚህ መሠረት የሩቅያ ጥናት የተጠኚዎቹ ማንነትና ምንነት በቋንቋቸው አማካይነት የሚገለጽ መሆኑን ተንትኖ ይገልፃል።። ቋንቋቸው ለተጠኚዎቹ የማኅበረሰብ ክፍሎች የእርስ በርስ ማያያዣ ክር እና መገናኛ ድልድይ ነው።። ይህም እንዴት እንደሚሰራ ለማሳየት በጥናቱ ውስጥ የተገለጸው የእርስ በርስ ግንኙነት ባህል አይነቱ ብዙ ነው።። ዘዴው፣ ስልቱ፣ የተለያየ

ነው፤ አሰራሩ ለየቅል ነው። ለምሣሌ በጥናቱ ውስጥ እንደተገለጸው የማኅበረሰቡን የአኗኗር ዘዬ ጨምሮ፤ ከሃገረሰባዊው የወሎ ሙዚቃ እስከ መንፈሳዊው የወሎ መንዙማ፣ ከቃላዊ ግጥም እስከ ምሣሌያዊ ንግግር፣ ከሰላምታ እስከ ዝምታ፣ ከሃገረሰባዊ ልማድ እስከ ሃገረሰባዊው ቁሳዊ ባህል...ወዘተ ይደርሳል።

የሩቅያ ጥናት በርካታ ጠንካራ ጎኖች አሉት። ከነዚህ መካከል አንዱ የሚጠናውን አካባቢና የተጠኚውን ማኅበረሰብ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዳራ ለጥናቱ በሚስማማ መንገድ አጣጥሞና አጣፍጦ ማቅረቡ ነው። በዚህም የሩቅያ ጥናት ለተለያዩ አካላት የመረጃ ምንጭ በመሆን የሚያገለግል ሥራ ነው። ጥናቱ አውድን መሠረት አድርጎ መካሄዱም ሁለተኛው የጠንካራ ጎኑ መገለጫ ነው። ሦስተኛው ነጥብ ደግሞ የጥናቱ ዘዴና የትንተና ስልቱ ነው። የሩቅያ ጥናት መነሻው የቋንቋ ጉዳይ ቢሆንም በጥናቱ ውስጥ ትንተና የተካሄደባቸው እሴቶች የፎክሎር ዘርፎች ናቸው። ነገር ግን የሩቅያ ጥናት ዋና ዓላማና የጥናት ርዕሰ ጉዳይ መነሻና መድረሻ የአማረኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ የእስልምና እምነት ተከታይ የማኅበረሰብ ክፍሎች ብቻ ናቸው። እሴቶቹ የተተነተኑትም ከነዚህ ተጠኚዎች አንፃር ብቻ ነው።

በዚህ መነሻ የሩቅያ ጥናት በወሎ የክርስትናና እስልምና እምነት ተከታዮች የእርስ በርስ ግንኙነት መሠረት የሆኑ የጋራ እሴቶችን የተመለከተ አይደለም። በአንፃሩ የአንደኛውን አካል የማኅበራዊ ሕይወት ዘይቤና የእርስ በርስ ግንኙነት ብቻ የሚመለከት ነው። ትኩረቱም የሃይማኖት መቻቻል ጉዳይ ላይ አይደለም። በመሆኑም የሩቅያ ጥናት የሁለቱን አካላት መስተጋብር ወይም የእርስ በእርስ ግንኙነት የማይመለከት በመሆኑ ይሄ ጥናት ይህንን የጥናት ክፍተት ስለሚደፍን ከሩቅያ ጥናት ይለያል።

ከዚህ በላይ የተካሄደው አጠቃላይ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በውጭ አገርና በኢትዮጵያውያን ምሁራን አማካይነት የተካሄዱ የጥናት ውጤቶች ሁነው፤ መነሻቸው ሃይማኖታዊ ጉዳይ ነው። ጥናቶቹ የተካሄዱትም የሃገሪቱን የተለያዩ አካባቢዎች ጨምሮ በብዛት ወሎ ውስጥ ነው። የጥናቶቹ መነሻ ሃይማኖታዊው ጉዳይ ቢሆንም ሃይማኖቶቹን ከተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር በማገናኘት በርካታ ሁነቶችን አጥንተዋል።

ነገር ግን ከተዘረዘሩት ጥናቶች ውስጥ አንዳቸውም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በወሎ የክርስትናና እስልምና እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦችን የሃይማኖት መቻቻል እሴት ወይም

የማኅበረሰቦቹን የዕርስ በርስ መስተጋብር አላጠኑም፡፡ አለያም የሁለቱ እምነት ተከታዮች አብሮ ለመኖር የተጠቀሙባቸውንና አሁንም የሚጠቀሙባቸውን የጋራ እሴቶች አላጠኑም፡፡ የሁለቱን እምነት ተከታዮች የአኗኗር ስልቶችና ከስልቶቹ የመነጩትን እሴቶች አልመረመሩም፡፡ በአንፃሩ የብዙዎቹ ጥናቶች ትኩረት አብሮነት ላይ ሳይሆን ልዩነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ልዩነት ላይ ያተኮሩበት ምክንያትም ሃይማኖቶቹን መነሻ በማድረግ በየዘመኑ የነበረውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን ለመረዳት ሲሉ ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከነዚህ ጥናቶች በተለየ ሁኔታ የጥናታቸውን ርዕሰ ጉዳይ የሃይማኖት መቻቻል ጽንሰ ሃሳብ ላይ በማድረግ የተካሄዱ ጥናቶች አሉ፡፡ የአንዳንዶቹ ጥናቶች መነሻ በቀጥታ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች ሲሆኑ የአንዳንዶቹ ደግሞ በሃገሪቱ የተከሰቱ የሃይማኖት ግጭቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች ካነሱት መሰረታዊ ርዕሰ ጉዳይ አንፃር ብቻ ከዚህ ቀጥሎ ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

2.4፡- በሃይማኖት መቻቻል እና በሃይማኖት ሰበብ በተከሰቱ ግጭቶች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች

በዚህ ጥናት መግቢያ እንደተጠቀሰው ኢትዮጵያ በዓለም ታሪክ ውስጥ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች በቅድሚያ የተመሰረቱባት አገር ብቻ ሳትሆን፤ ሃይማኖቶቹና የእምነቶቹ ተከታዮች በመከባበርና በመቻቻል በሰላም አብረው የሚኖሩባት አገር ናት፡፡ ጥናቶች እንደሚሉት ከአሁን በፊት "በኢትዮጵያ ሃይማኖት የአክራሪነት መነሻ ምክንያት በመሆን፤ የልዩነት፣ የጥላቻ፣ የግጭትና ብጥብጥ ምንጭ የሆነበት አጋጣሚ አልነበረም" (Trimingham 1965; 152)፡፡ ይሁን እንጂ ከአሁን በፊት በኢትዮጵያ የነበረው የሃይማኖቶቹና የእምነቶቹ ተከታዮች መገለጫ ይህ ቢሆንም፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እነዚህ የጋራ እሴቶች እየተሸረሸሩና መልካቸውን እየቀየሩ መምጣታቸውን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ከነዚህ ጥናቶች ውስጥ ከዚህ ጥናት ጋር ሊገናኙ የሚችሉት ብቻ ተመርጠው ከዚህ ቀጥሎ ተከልሰው ቀርበዋል፡፡

እነዚህ ጥናቶች ለውይይትና ለዲግሪ ማሟያ የቀረቡ የምርምር ውጤቶች ናቸው፡፡ ለውይይት የቀረቡትን በማስቀደም እነዚህ ጥናቶች ምን እንዳጠኑ፣ በጥናታቸው ምን እንዳገኙ፣ ያላጠኑት ርዕሰ ጉዳይ ምን እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ ከጭብጣቸው አንፃር ቀርቧል፡፡ በኢትዮጵያ ሁለተኛው

ሚሌኒየም ተጠናቆ ሦስተኛው ሚሌኒየም ሲብት አጋጣሚውን ምክንያት በማድረግ በኢትዮጵያ በትልልቅ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ጥናቶች ተካሂደዋል። ከነዚህ ጥናቶች መካከል አንዱ በ2000 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስብሰባ ማዕከል ኢትዮጵያ ባሏት የጋራ አገራዊ እሴቶች ላይ የተካሄደው ውይይት ነው። ውይይቱ የተካሄደው የምሁራንን ጥናት መነሻ በማድረግ ነው። ከዚህ ውስጥ "The Promise of Ethiopia፡ Public action; Civic Forgiveness; Creative Power." በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ለአብነት ይጠቀሳል። ኢትዮጵያውያን ያሏቸው የጋራ እሴቶች ምን ምን እንደሆኑ የሚያብራራው ይህ ጥናት የቀረበው በዶናልድ ሌቪን አማካይነት ነው (Levine 2008)።

በሌቪን ጥናት መሠረት ኢትዮጵያውያን በመካከላቸው ተግባብተው፣ ተረዳድተውና ተደጋግፈው በሰላምና በአንድነት ለመኖር የሚያስችሏቸው በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው። እነዚህ እሴቶች ደግሞ ለዘመናት በኢትዮጵያውያን የተገነቡና በሂደት የዳበሩ ናቸው። እሴቶቹም በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሩቅ ዘመን ሥረ-መሠረት አላቸው። በኢትዮጵያ ለረዥም ዘመናት ሕዝቡ ችግሮቹን ለመፍታት የሚጠቀምባቸው እንደ ችሎት፣ ማኅበር፣ ሸንጎ፣ እቁብ፣ እድር...ወዘተ ተቋማት ለአብነት ይጠቀሳሉ።

እንዲሁም ከሌቪን ጥናት መረዳት እንደሚቻለው በኢትዮጵያ ከአገራዊ ጉዳዮች እስከ ግለሰብ ያሉ ግጭቶች በባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች መፍትሄ ያገኛሉ። ይቅር መባባል የኢትዮጵያውያን ባህላዊ እሴት ነው። በኢትዮጵያ በውይይትና በሽምግልና የማይፈታ አንዳችም ነገር የለም። "ሰማይ ተቀደደ ቢለው፤ ሽማግሌ ይሰፋዋል!" አለ፤ አንዲሉ። በኢትዮጵያ ባህላዊው የፍትሕ ሥርአት ለረዥም ዘመናት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ስለመሆኑ ሌቪን በጥናታቸው አብራርተዋል። ማኅበረሰቡ የጋራ ችግሮቹን ለመፍታትና ማኅበራዊ ጉዳዮቹን ለማሳካት ማኅበር፣ እድር፣ እቁብና ሌሎች ጉዳዮች ወሳኝ ተቋማቶቹ ናቸው። እነዚህ ተቋማት ማኅበረሰቡ ተቻችሎና ተደጋግፎ በሠላም እንዲኖር መሠረቶች ናቸው። በዚህም አባላቱ የተቋማቱን ህልውና በጋራ ይጠብቋቸዋል። እንዲሁም ኢትዮጵያውያን የውጭ ወራሪዎች በተነሱባቸው ጊዜ ተባብረው ጠላትን ድል የሚመቱበት ባህል ባለቤቶች ስለመሆናቸው ሌቪን ገልጸዋል። ከዚህም ሌላ በሌቪን ጥናት መሠረት ኢትዮጵያውያን በገበያ፣ በንግድ ልውውጥ፣ በሃይማኖት፣ በጋብቻ፣ በሃዘንና በደስታ

በሚያደረጓቸው ግንኙነቶች የጠበቀ ትስስር ፈጥረዋል። አንዱ ከሌላው በተለያየ መንገድ ተዛምዷል፤ ተሳስሯል።

ባጠቃላይ በሌቪን ጥናት ውስጥ የተነሱት መሠረታዊ ነጥቦች ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ሁነው፤ የጥናቱ ጭብጥ ኢትዮጵያውያን ለረዥም ዘመናት ይጠቀሙባቸው የነበሩ ነባር የጋራ እሴቶቻቸውን በአሁኑ ወቅት ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ሥራ ላይ ማዋል ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን መግለጽ ነው። በባህላዊ ችሎት ሲካሄዱ የነበሩ ክርክሮች፣ በማኅበር፣ በእድርና በዕቁብ የሚታየው ትብብር፣ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ጠላት አገራቸውን ሲወር ለዘመቻ የሚነሳሱበት መንፈስ ሀገሪቱ ለዘመናት የተጠቀመችባቸው እሴቶች በመሆናቸው በአሁኑ ጊዜም አገልግሎት ላይ ማዋል ለአንድነት ጠቀሜታ እንዳላቸው መጠቆም ነው። እነዚህ እሴቶች የህዝቡ የራሱ ሃብቶች በመሆናቸው ከድህነት ለመውጣትና ለብሔራዊ መግባባት ወሳኝ መሆናቸውን መግለጽ ሌቪን በጥናታቸው ያነሱት ሌላው ጭብጥ ነው።

በዚህ መሠረት የሌቪን ጥናት ትኩረት የኢትዮጵያውያን የጋራ ማኅበራዊ ተቋማትና አገልግሎታቸው ላይ ነው። ምንም እንኳን እነዚህ ተቋማት ለጋራ መግባባት ወይም አብሮነት ወሳኝ ቢሆኑም ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋር የሚገናኙበት ሁኔታ በሌቪን ጥናት አልተገለጸም። ወይም እነዚህ ተቋማት ለሃይማኖት መቻቻል እሴት እንዴት መሠረት ሊሆኑ እንደሚችሉ ማሳየት የሌቪን ጥናት ዓላማ አይደለም። ነገር ግን የሃይማኖት መቻቻል እሴትን የጥናታቸው መነሻ ያደረጉ ሌሎች ሁለት ጥናቶች አሉ። እነዚህ ሁለት ጥናቶች በኤፍሬም ይስሐቅና በአህመድ ሐሰን የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች ናቸው።

ኤፍሬም ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ "Tolerance: Christianity and Islam in Ethiopia from a Historical Perspective." የሚል ርዕስ አለው። ኤፍሬም በዚህ ጥናት ውስጥ ሦስት መሠረታዊ ነጥቦችን አንስተዋል። ለዘመናት በተለያዩ እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን መካከል የነበረውን የእርስ በርስ ግንኙነት የተመለከተው ርዕሰ ጉዳይ አንዱ ነው። ሁለተኛው ርዕሰ ጉዳይ ደግሞ የኢትዮጵያ ባህል ከጎረቤት አገራት ባህል ጋር የነበረውን ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን፤ የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት ወይም አብሮነት ለማላላት ያደረጉትን ሙከራ የተመለከተው ክፍል ሦስተኛው ርዕሰ ጉዳይ ነው። በኤፍሬም ጥናት መሠረት ኢትዮጵያ በዓለም ላይ የሚገኙትን ሦስቱን ትላልቅና ቀደምት ሃይማኖቶች የያዘች አገር ናት። ለዚህም የአይሁድ፣ የክርስትናና

እስልምና እምነቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ይግኛሉ፡፡ በነዚህ እምነቶችና የእምነቶቹ ተከታዮች መካከል ከጥንት ጀምሮ አሁንም ድረስ የዘለቀ የመቻቻል እሴት አለ፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በሃይማኖት መቻቻል እሴት በምሣሌነት የምትጠቀስ አገር ናት፡፡

በሌቪን ጥናት መሠረት በተለያዩ ዘመናት በእምነቶቹ መካከል ተከስተው የነበሩት ግጭቶች መንስኤም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ለዚህም በኢትዮጵያ ክርስቲያኖቹም ሆኑ ሙስሊሞቹ በእምነት ምክንያት ሳይለያዩ የውጭ ወራሪዎችን በጋራ መመከታቸው በጥናቱ ማሳያ ሁኖ ቀርቧል፡፡ ኤፍሬም እንደሚሉት የኢትዮጵያውያን መገለጫ ይሄ ቢሆንም ባንዳንዱ የውጭ ኃይሎች አገሪቱን ለመውረርና ህዝቦቿንም ለመከፋፈል በነበራቸው ፍላጎት የሃይማኖት ልዩነትን ለመፍጠር ሞክረዋል፡፡ በዚህ አይነቱ ሙከራ የደቡብ ዓረቢያ ሀገራት፣ ግብፅ፣ አቶማን ቱርኮችና ሌሎች የአውሮፓ ሀገራት በጥናቱ ውስጥ ለአብነት ተጠቅሰዋል፡፡ የኤፍሬም ጥናት እንደሚለው የነዚህ አገራት ኢትዮጵያውያንን በሃይማኖት የመለያየት ሙከራ ያልተሳካው በኢትዮጵያውያን መተባበር፣ አንድነትና ጥንካሬ አማካይነት ነው፡፡ የሱዳን፣ የሶማሌና የሶሪያ ሙከራም በዚህ መልኩ መክሸፉን ከጥናቱ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ በጥናቱ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ሃይማኖትን ምክንያት በማድረግ የተከሰቱ ግጭቶች ምንጫቸው የነዚህ አገራት ጣልቃ ገብነት ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ግጭቶቹ ኢትዮጵዊ ገጽታ የላቸውም፡፡

በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ ተቻችሎ በመኖር በዓለም የምትታወቅና ለሌሎች ሀገራት ተምሣሌት መሆኗን የኤፍሬም ጥናት ይገልፃል፡፡ ባጠቃላይ ከዚህ በላይ በኤፍሬም ጥናት የተነሱት ነጥቦች የሃይማኖት መቻቻል በኢትዮጵያ ምን አይነት ሥረ-መሠረት እንዳለው አጠቃላይ ፍንጭ የሚሰጥ ነው፡፡ ነገር ግን የኤፍሬም ጥናት ዋና ትኩረት የግጭቶቹን ምንጭ ወይም ምክንያት ላይ እንጂ የመቻቻል እሴቶች ላይ አይደለም፡፡ ከዚህም ሌላ የኤፍሬም ጥናት የሃይማኖት ግጭቶች ምክንያት አጠቃላይ ታሪካዊ ቅኝት እንጂ በተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮችና አካባቢዎች ላይ ተመስርቶ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ላይ የተካሄደ ጥናት አይደለም፡፡

ሁለተኛው በሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተካሄደ ጥናት የአህመድ ሐሰን ጽሑፍ ነው፡፡ የአህመድ ጥናት “A Preliminary Note on Religious Tolerance in Ethiopia: Historical Review of Discourse about Islam” በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ይህ ጥናት እስልምናን በኢትዮጵያ በአራት ወቅቶች ከፋፍሎ መርምሯል፡፡ በዚህም በጥንታዊው፣

በመካከለኛው፣ ከዚያም እስከ 1960ዎቹ ዓ.ም. አጋማሽ እና 1980ዎቹ ዓ.ም. መጀመሪያ በነበሩት ዘመናት ውስጥ በኢትዮጵያ ከእስልምና ጋር የተገናኙ ሁነቶች ተመርምረዋል። በዚህ መሠረት በመጀመሪያው የዘመን ክልል ውስጥ በቅድሚያ ክርስትና በመቀጠልም እስልምና ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ በጽሑፉ ተብራርቷል። በዚህም ኢትዮጵያ እስልምናን በመቀበል ቀዳሚ ናት።

ከአህመድ ጥናት መረዳት እንደሚቻለው መካከለኛው ዘመን በሁለቱ እምነቶች መካከል ግጭቶች የተስተናገዱበት ወቅት ነው። የግጭቶቹ ምክንያት ግን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነትን ለመያዝ የተካሄዱ ሽኩቻዎች ናቸው። ለአብነት የአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) ወረራ ሃይማኖታዊ (ጂሃዳዊ) ይዘት እንደሌለው ጥናቱ ይጠቁማል። ለዚህም በጦርነቱ ወቅት አህመድ ግራኝን በማገዝ ክርስቲያኖቹ መሰለፋቸውን፤ ባንፃሩ ሙስሊሞቹ ከአፄ ልብነድንገል ጎን መቆማቸውን ማስረጃ ያቀርባል።

ከመካከለኛው ዘመን ፍፃሜ እስከ 1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት ድረስ በነበሩት ዘመናት ደግሞ አልፎ አልፎ በሙስሊሞች ላይ መገለል ቢኖርም ሰላም መስፈኑን የአህመድ ጥናት ያብራራል። በአበዛኛው ይሄ ዘመን የሃይማኖት መቻቻልና በሰላም አብሮ የመኖር ሁኔታ የሰፈነበት ወቅት ነበር። በድኅረ-ኢዮትየጵያ አብዮት ወቅት ደግሞ ሙስሊሞች በሀገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ እንደነበሩ የአህመድ ጥናት ይገልፃል።

በአህመድ ጥናት እንደተብራራው የሃይማኖት መቻቻል በኢትዮጵያ የዘመናት ሥረ-መሠረት አለው። ነገር ግን የአህመድ ጥናት መሠረታዊ ርዕሰ ጉዳይ የአገሪቱን የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች ታሪካዊ ዳራ ቢያብራራም የሁለቱን እምነት ተከታዮች የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም ትስስር የመረመረ አይደለም። ጥናቱ በህዝቦች መስተጋብር ወይም የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች ላይ ተመስርቶ የተካሄደ ጥናት አይደለም።

ባጠቃላይ የኤፍሬምና የአህመድ ጥናቶች መሠረታዊ ጭብጥ የሃይማኖቶቹን ታሪካዊ ዳራ በመመርመር በሂደት የገጠሟቸውን አወንታዊና አሉታዊ ጉዳዮች መግለጽ ነው። ከእምነቶቹ ተከታዮች አንፃርም ሁለቱም ለውጭም ሆነ ለውስጥ ኃይሎች ተጽእኖ ሳይሸነፉ አንድነታቸውን በማጠናከር ለዘመናት በሰላምና በመቻቻል የሚኖሩ ህዝቦች መሆናቸውን ማሳየት ነው። በዚህ መሠረት ጥናቶቹ የሃይማኖት መቻቻልን አጠቃላይ ሁኔታ የተመለከቱት ታሪካዊ ክስተቶቹን ወይም በዘመኑ የነበሩ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን መነሻ በማድረግ

እንጂ፤ ከዚህ ባለፈ አንድን የተወሰነ አካባቢና ማኅበረሰብ መነሻ በማድረግ የሃይማኖት መቻቻል እሴትን አላጠኑም፡፡

ጥናቶቹ የቀረቡበት ዓላማም የተወሰኑ አገራዊ የጋራ እሴቶችን ለማጎልበትና ለማጠናከር በሚል ርዕስ ለአንድ የተወሰነ የውይይት ፕሮግራም በመሆኑ አቀራረባቸው በቦታና በጊዜ የተወሰኑ (የተገደቡ) አይደሉም፡፡ ከዚህ አንፃር በአጠናን ዘዴያቸው፣ ባነሱት ርዕሰ ጉዳይና በመረጃ ምንጫቸው ጭምር ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያሉ፡፡ በዚህ መሠረት የሌቪንም ሆነ የኤፍሬም አለያም የአህመድ ጥናት ለዚህ ጥናት የታሪካዊ ዳራ ምንጭ በመሆን የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ እንደተጠበቀ ሁኖ፤ በነዚህ ጥናቶችና በዚህ ጥናት መካከል ሰፊ የጥናት ክፍተት አለ፡፡

በሌላ በኩል ግን የጥናታቸው ርዕሰ ጉዳይ ከሃይማኖት መቻቻልና ከሃይማኖት ግጭቶች ጋር የተገናኘ ሁኖ፤ በአንድ በተወሰነ ጊዜና ቦታ ውስጥ የተካሄዱ ጥናቶች አሉ፡፡ የነዚህ ጥናቶች ዓላማ ደግሞ በነዚህ ቦታዎችና ጊዜያት ውስጥ ከሃይማኖት ጋር በተገናኘ የተከሰቱ ሁነቶችን ያጠኑ ናቸው (Tekalign 2008; Afework 2009; Sibkete Ermias 2009; Zelalem 2010; Mohammed 2010; Haileyesus 2011)፡፡

ከነዚህ ጥናቶች መካከል አንዱ የአፈወርቅ ኃይሉ ጥናት ነው፡፡ የአፈወርቅ ጥናት በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ድኅረ-ምረቃ መርሃ-ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስ “Religious Tolerance in Addis Ababa, 1991-2008” የሚል ነው፡፡ በጥናቱ የተነሳው ርዕሰ ጉዳይም በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ውስጥ ያለውን የሃይማኖት መቻቻል ነባራዊ ሁኔታ መመርመር ነው፡፡ ርዕሰ ጉዳዩን ለመመርመር ደግሞ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመው መረጃ ሰብስበዋል፡፡ የሰበሰቧቸውን መረጃዎች በመተንተን የጥናቱን ግኝት ገልጸዋል፡፡ በዚህም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በኢትዮጵያ የዳበረ ሥረ-መሠረት ያለው መሆኑን ጠቁመው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥም ተመሳሳይ ሁኔታ መኖሩን አብራርተዋል፡፡

ነገር ግን ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ እነዚህን እሴቶች የሚሸረሽሩ ሁኔታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መምጣታቸውን የአፈወርቅ ጥናት አብራርቷል፡፡ ጥናቱ ለዚህ ምክንያት ናቸው፤ ያላቸውን ጉዳዮች ዘርዝሯል፡፡ ለምሳሌ ጤናማ ያልሆነ የሃይማኖት ፉክክር፣ አክራሪነትና ጽንፈኝነት፣ ከአንድነት ይልቅ ልዩነትን የሚያሰፋ ጉዳዮችን ማራገብና ማናፈስ፣ ሃይማኖቶቹን የልዩነት ምንጭ አስመስሎ ማቅረብ፣ ያለፉ አሉታዊ ድርጊቶችን እንደ አዲስ መቀስቀስ...ወዘተ ለአብነት ተጠቅሰዋል፡፡ በጥናቱ ግኝት መሠረት በአሁኑ ጊዜ የሃይማኖት

እኩልነትና ነፃነት ሕገ መንግስታዊ እውቅና ቢያገኝም መብትና ግዴታን ጠንቅቆ ባለመረዳት ወይም ሆነ ብሎ በማዛባት ለሃይማኖት መቻቻል ፈተና እየሆነ መምጣቱን ጥናቱ ይገልፃል። ለዚህ ደግሞ መንፈሳዊ ስብከቶች፣ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ ውጤቶች፣ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ጽሑፎች ከፍተኛ ድርሻ ይይዛሉ። እንዲሁም የመንግሥት ባለስልጣናት በየደረጃው ጣልቃ ገብነትና ወገንተኝነት ምክንያት ተደርገው ቀርበዋል። ሕጋዊ ሥርአቱን እና ሕገ-መንግሥቱን አለማስከበር በመንግስት በኩል የተጠቀሰ ችግር ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት መሠረት መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፤ የሚለው መርህ ነው።

አፈወርቅ እንደሚሉት ይህ ማለት ግን ሥርአት አልበኝነት ሲሰፍን መንግሥት ሕግና ሥርአት አያስከብርም ማለት አይደለም። የሕግ የበላይነትን አያረጋግጥም ማለት አይደለም። ከዚህም ሌላ የሃይማኖት አባቶችና ምእመናን በችግሮቹ ዙሪያ ውይይትና ምክክር አለማድረጋቸው ለልዩነቶቹ ምክንያት ሁነው ቀርበዋል። ጥናቱ እንደሚለው ምሁራንም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ጥናት አለማድረጋቸው ለችግሩ መባባስ አንዱ ምክንያት ነው።

የአፈወርቅ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ ድኅረ-1983 ዓ.ም ያለውን የሃይማኖት መቻቻል ሁኔታ ለማጥናት አይነታዊ፣ መጠናዊና የሁለቱን ቅልቅል የጥናት አይነት ተጠቅሟል። ነገር ግን ትንተናው የተካሄደው በቁጥርና በፐርሰንት ላይ ብቻ ተመስርቶ ነው። የጥናቱ የትንተና መነሻም ሃይማኖቶቹን በፊት ከነበሩት የፖለቲካ ሥርአቶችና አሁን ካለው የፖለቲካ ሥርአት ጋር በማነፃፀር ነው። የፖለቲካ ሥርአቶቹ ለሃይማኖቶቹ ከነበራቸው አሉታዊና አወንታዊ አመለካከት አንፃር የተቃኘ ነው። ለምሣሌ በአፈወርቅ ጥናት መሠረት ለእስልምና እምነት ተከታዮች አሁን ያለው የፖለቲካ ሥርአት ካለፉት ሥርአቶች የሚሻለው በአዲስ አበባ ከተማ ብዙ መስጊዶች እንዲገነቡ በማድረጉ ነው። የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮችም የሃይማኖት መቻቻልን የሚመዝኑት ከቀደሙት የፖለቲካ ሥርአቶች ይልቅ አሁን ካላቸው የአምልኮ ነፃነት አንፃር ነው።

በዚህ መሠረት የአፈወረቅ ጥናት ተጠቃሎ ሲታይ መሠረታዊ ትኩረቱ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ላይ ሳይሆን፤ የሃይማኖት ነፃነት ወይም የሰብአዊ መብት ጉዳይ ላይ ነው። ምክንያቱም የጥናቱ የመረጃ ሁኔታ፣ የትንተና ሥልቱና ከትንተናው የተገኘው ውጤት የሚያሳየው የሃይማኖት መቻቻል እሴት ወይም የነዋሪዎችን የእርስ በርስ መልካም ግንኙነት ወይም

መስተጋብር ሳይሆን የነዋሪዎቹን የአምልኮ ነፃነት ሁኔታ የተመለከተ ነው። ለምሳሌ ለነዋሪዎቹ የቀረቡት ጥያቄዎችም ሆኑ የተሰጡት መልሶች የሚያረጋግጡት ይህንኑ ነው። በመሆኑም በአፈወርቅ ጥናት መሰረት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ለዘመናት ያዳበሯቸው የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች ወይም የእርስ በርስ መስተጋብሮች በነዋሪዎቹ በራሳቸው አውድና የአጠናን ዘዴ አልተጠኑም። በነዋሪዎቹ ተፈጥረው ነዋሪዎቹ የሚገለገሉባቸው የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች የአፈወርቅ ጥናት አካል አይደሉም። በመሆኑም ይሄ ጥናት ከአፈወርቅ ጥናት በእጅጉ ይለያል።

ከሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የተካሄደ ሌላው ጥናት የስብክት ኤርምያስ ጥናት ነው። ጥናቱ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ሲሆን፤ ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የድኅረ-ምረቃ መርሃ-ግብር ትምህርት ክፍል የቀረበ ነው። ጥናቱ "The Dynamics of Religious Movement During the Late 19th & Early 20th Centuries: The Career of Shayky Zakaryas /Newaya Kerstos." በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ወይም ጭብጥ በጥናቱ ርዕስ በተገለጸው ዘመን፤ ደቡብ ጎንደር፤ ላይ ጋይንት ወረዳ ልዩ ስሙ ነገላ በተባለ አካባቢ ተወልደው በዚያው አካባቢ የኖሩትን የሼህ ዘካርያስ (ንዋየ ክርስቶስ)[25] የሕይወት ታሪክ፣ ያከናወኗቸውን መንፈሳዊ ተግባራትና ለሃይማኖት መቻቻል ያበረከቱትን አስተዋጽዖ ማጥናት ነው። በጥናቱ መሠረት ዘካርያስ ከእስልምና እምነት ተከታይ ቤተሰብ የተወለዱ ናቸው። በዚህም በእስልምናው ዘርፍ የጠለቀና የረቀቀ የመንፈሳዊ እውቀት ሊቅ ለመሆን ችለዋል።

ሃይማኖቱን በማስተማርም በርካታ መንፈሳዊ ተካታዮችና ተማሪዎች ነበሯቸው። ነገር ግን ከጊዜ በኋላ በእምነቱ መርሆዎች ወይም ሕግጋት ላይ በሚያነሷቸው ጥያቄዎችና በሚሰጧቸው ትርጓሜዎች ላይ ከሌሎች የእስልምና ሊቃውንት ጋር ልዩነታቸው እየሰፋ መጣ። የስብክት ኤርምያስ ጥናት መሠረታዊ ዓላማም ዘካርያስ ይህንን ልዩነት ለመፍታት የተጠቀሙበትን ብልሃት (ዘዴ) መግለጽ ነው።

ከጥናቱ መረዳት እንደሚቻለው በዚያን ዘመን ዘካርያስ ልዩነቱን ለመፍታት የተጠቀሙበት ዘዴ ፍፁም ሰላማዊና ምክንያታዊነትን መሠረት ያደረገ ነበር። ይኸውም ያለምንም ተጽእኖና

[25] ሼህ ዘካርያስ በሚከተሉት ስሞችም ይጠራሉ። እነዚህም አለቃ ንዋየ ክርስቶስ፣ ዘካርያ ጀብሪል፤ አባ ዘካርያስ፣ አባ በግዱ፣ ንዋየ ክርስቶስ፣ ጌታው፣ አለቃ፣ (ስብክት ኤርምያስ፣ 2009 ዓ.ም.፤ Hussein 2006.)።

አስገዳጅ ሁኔታ ሃሳብን በነፃነት በማንሸራሸር፣ በመከራከር፣ ምክንያትን ተርጉሞና ተንትኖ በማስረዳት ማሳመን ወይም በሌሎች ሃሳብ የማመን መርህ ነበር። ከጥናቱ መረዳት እንደሚቻለው ዘካርያስ ያለማንም ግፊት በራሳቸው ተነሳሽነትና በራሳቸው ህሊና ብቻ በመመራት መጀመሪያ የሁለቱን ሃይማኖቶች ፍልስፍና መርምረው ተረዱ። ከዚያም የተረዱትን ጉዳይ ያለምንም ፍርሃት በነፃነት ሃሳባቸውን ገለጹ። ከዚያም ተቃውሞ ቀረበባቸው። ነገር ግን በክርክር ወይም በውይይት ለማሳመን አልያም ለማመን ተዘጋጁ፤ በተግባርም በሥራ ተረጎሙት።

በዚህም የሃይማኖትን መርሆዎች ብቻ መነሻ በማድረግ ለመጀመሪያ ጊዜ የእምነቱ ተከታዮች በሁለት ጎራ ተከፍለው አገራዊ ጉባዔ ተጠርቶ ክርክር አካሄዱ። በወቅቱ የነበሩትን የሃገሪቱን ንጉሥ ጨምሮ፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ የዚያ ጉባኤ ታዳሚዎች እንደነበሩም ጥናቱ ይገልፃል። ጥናቱ እንደሚለው ክርክሩ በዘካርያስ አሸናፊነት ተደመደመ። ከዚህ በኋላ ዘካርያስ ያለማንም አስገዳጅነት "የተጠመቀ ይዳን፤ ያልተጠመቀ ይደይን" በሚለው የልዩነታቸው መርህ መሠረት ተጠምቀው ክርስቲያን ሆኑ። ከዚያም በፍላጎት ላይ ተመስርተው ሌሎችን አጠመቁ።

የስብከተ ኤርምያስ ጥናት ከዘካርያስ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጥያቄዎችንም ለመመለስ ሞክሯል። የሁለቱ እምነት ተከታዮች ስለዘካርያስ ያላቸውን ስሜትና አስተያየት ለማወቅ ጥረት አድርጓል። በግለሰቡ ላይ የሚታዩ ብሥጉታዎችን ለማጥራትም ሞክሯል። በጥናቱ መሰረት ክስተቱና ታሪኩ እንዳለ ሁኖ፤ በዚያን ዘመንም ሆነ አሁን በዚያ አካባቢ የሚገኙ የሁለቱ እምነት ተከታዮች በሰላምና በፍቅር በአንድት የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው። ጥናቱ እንደሚለው ዘካርያስ አሁንም ድረስ የሁለቱ እምነት ተከታዮች የልዩነት አጥር ሳይሆን መገናኛ ድልድይ ነው። የነፃነት፣ የራስ ፍላጎትና እምነት መገለጫ ተምሳሌት ነው። ነገሮችን በራስ ፍቃድ አውቆና መርምሮ በራሱ ህሊና የተመራ አርአያ ነው።

ባጠቃላይ የስብከተ ኤርምያስ የጥናት ጭብጥ ማሳረጊያ፤ ሰዎች እምነትን እንዲቀበሉ ወይም አማኝ እንዲሆኑ ማድረግ የሚቻለው በመስቀል ጦርነት፣ ወይም በጂሃድ፣ አለያም በኢትዮጵያ እነ አፄ ዮሐንስ አራተኛ እንዳደረጉት አዋጅ በማስነገር ሳይሆን፤ እንደ ዘካርያስ በራስ የእውቀት ልክ፣ በራስ የልብ መሻትና በራስ ፍቃድ ላይ ተመስርቶ ነው። የዚህ አይነቱ መርህ ደግሞ ለሃይማኖት መቻቻልና በአጠቃላይ ለሰው ልጆች ሰላምና ደህንነት መሠረት ነው። የስብከተ ኤርምያስ የጥናት ጭብጥም ይኸው መሠረታዊ ነጥብ ነው።

የስብከተ ኤርምያስ ጥናት አንድን ግለሰብ መነሻ በማድረግና ከዚያ ግለሰብ ጋር የተገናኙ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት እንዴት ጥናት ማካሄድ እንደሚቻል ምሣሌ የሚሆን ሥራ ነው። ጥናቱንም ሚዛናዊና ተአማኒ ለማድረግ የተደረገው ጥረት የጥናቱ ሌላው ጠንካራ ጎኑ ነው። በተለይ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴውና የመረጃ ምንጮቹ አደረጃጀት እንዲሁም የጥናቱን ዘዴ ምርጫና የትንተና ሥልቱ ላብነት የሚጠቀሱ ጠንካራ ጎኖች ናቸው። የርዕሰ ጉዳዩ ወቅታዊነትም በጠንካራ ጎኑ ሊጠቀስ ይችላል።

ነገር ግን የስብከተ ኤርምያስ ጥናት ዘካርያስ በክርክርና በውይይት ላይ የተመሰረተ መርህ መከተሉ ለሃይማኖት መቻቻል አብነት ሁኖ ከመጠቀሱ ውጭ፤ በእሱ ምክንያት የተገኙ የሁለቱን እምነት ተከታዮች የሚያያይዙ የጋራ እሴችን አይገልጽም። ወይም በዘካርያስ ምክንያት ሊገለጹ የሚችሉ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች በስብከተ ኤርምያስ ጥናት ውስጥ የሉም። ባጠቃላይ የስብከተ ኤርምያስ ጥናት በዘካርያስ ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ነው።

በሌላ በኩል የሃይማኖት ግጭቶችን መነሻ በማድረግ የተካሄዱ ጥናቶች አሉ። ከነዚህ ጥናቶች ውስጥ ከዚህ ጥናት ጋር ሊገናኙ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ጥናቶች ከዚህ በታች የቀረቡት ናቸው። ከነዚህ ጥናቶች መካከል የዘላለም ተመስገን ጥናት አንዱ ነው። የዘላለም ጥናት "The 2006 Religious Conflict in Didessa and Gomma Waradas of Western Oromia." በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። ጥናቱ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ድኅረ-ምረቃ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰራ ነው። የጥናቱ መሠረታዊ ርዕሰ ጉዳይ ደግሞ በርዕሱ በተጠቀሰው ጊዜና አካባቢ የተከሰቱ የሃይማኖት ግጭቶችን ማጥናት ነው። በዚህም የግጭቶቹን መነሻ ምክንያት፣ ሂደትና ውጤት መርምሯል።

ዘላለም ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ለማጥናት ያነሳሳቸው ምክንያት ኢትዮጵያ ለዘመናት የዳበረ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ባለቤት ሁና እያለ፤ በአሁኑ ጊዜ ግን የሃይማኖት ልዩነቶችን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች መበራከታቸው ነው። እንዲሁም አጥኚው እንደሚሉት የሃይማኖት እኩልነትና ነፃነት ከምን ጊዜውም በተሻለ ሁኔታ ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ባገኘበት በአሁኑ ወቅት የሃይማኖት ግጭቶች መበራከታቸው "ለምን?" የሚል ጥያቄ አጭሮባቸዋል።

ዘላለም ጥናቶችን ጠቅሰው እንደጠቆሙት ሃይማኖቶች የሰላም ምንጭ የመሆናቸውን ያህል በአንፃሩ የግጭትና የጥፋት ምክንያት የሚሆኑበት አጋጣሚም ብዙ ነው፡፡ ከሰላም ምንጭነታቸው አንፃር፤ ሃይማኖቶች ሰላምን፣ ፍቅርን፣ መቻቻልን፣ መከባበርን፣ ይቅር መባባልን...ወዘተ ይሰብካሉ፤ ያስተምራሉ፡፡ ግጭት በሚከሰትበት ወይም ሰላም በሚታወክበት ወቅትም ሰላም እንዲሰፍን የመምከር፣ የመገሰጽና የማስታረቅ ሚና አላቸው፡፡ ይህ ሁሉ ተግባር የሚከናወነው ደግሞ በእምነቶቹ አባቶች፣ በእምነቶቹ መሪዎችና በእምነቶቹ ተከታዮች አማካይነት ነው፡፡ ባንፃሩ የዚህን ተቃራኒ ተግባር በሚፈጽሙ አካላት አማካይነት ሃይማኖት ለሞት፣ ለስደት፣ ለሰቆቃ፣ ለሽብርና አለመረጋጋት ምክንያት ይሆናል[26]፡፡ ተመራማሪው በዚህ ጽንሰ ሃሳብ ተመርተው በኢትዮጵያ ተከሰቱ ያሏቸውን የሃይማኖት ግጭቶች አጥንተዋል፡፡ በዚህም የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅመው የሰበሰቡትን መረጃ በመተንተን ለግጭቶቹ ምክንያት ናቸው፤ ያሏቸውን ጉዳዮች እና የግጭቹ ውጤቶች ናቸው፤ ያሏቸውን የሕይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡

በዘላለም ጥናት ውጤት መሠረት ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ የተከሰቱት የሃይማኖት ግጭቶች ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ነበሯቸው፡፡ የውስጣዊዎቹም ሆኑ የውጫዊዎቹ ምክንያቶች ዓላማ በሃይማኖት ሽፋን የሃይማኖት አክራሪ ግለሰቦችና የተደራጁ ቡድኖች የራስን ፍላጎት፣ ሃሳብና እምነት በኃይል በሌሎች ላይ የመጫን ፍላጎት ነው፡፡ በዚህም አክራሪዎች የነሱን እምነትና ፍላጎት ሌሎች ግለሰቦች በኃይል እንዲቀበሉ አስገድደዋል፡፡ በዚህም የሰው ሕይወት ጠፍቷል፤ ሕግና ሥርአት ተጥሷል፡፡ ጥናቱ እንደሚለው ለዚህ ደግሞ የማዕከላዊውን መንግስት ጨመሮ የአካባቢው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጭምር በየደረጃው የግጭቶቹ ምክንያቶች እና ተጠያቂዎች ናቸው፡፡

አጥኚው እንደሚሉት ምንም እንኳን መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፤ የሚለው ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌ ቢኖርም፤ መንግሥት በርካታ ኃላፊነቶች አሉበት፡፡ ከዚህ አንፃር ግጭቶቹ በተከሰቱባቸው አካባቢዎች መንግሥት በፍጥነት የሕግ ልዕልና እንዲከበርና የዜጎች ሰብአዊ መብት እንዲጠበቅ አላደረገም፡፡ እንዲያውም የአካባቢው የመንግሥት የስራ ኃላፊዎች

[26]ይህ አባባል የአሁኑ ዘመን መገለጫ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ ከአፍጋኒስታን እስከ ናይጀሪያ፣ ከማሊ እስከ ሱማሊያ፣ ከሶሪያ እስከ ሊቢያ፣ ከኢራቅ እሰከ የመን...ወዘተ የሚታየው ነባራዊ ሁኔታ ከዚህ አባባል ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

የችግሩ ተካፋይ ሁነው ተገኝተዋል። ባጠቃላይ የዘላለም ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ትኩረት ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ጥናቱ በተካሄደባቸው ወረዳዎች ውስጥ በኦርቶዶክስ ክርስትናና እስልምና እምነት ተከታዮች መካከል የተከሰተውን የግጭት መንስኤ፣ የመንስኤውን ምክንያትና ውጤት መመርመር ነው። ግጭቱን መርምሮ መንስኤውን፣ ምክንያቱንና ውጤቱን በመግለጽ የመፍትሄ ሃሳብ መጠቆሙ ከወቅታዊነቱ አንፃር የጥናቱ ጠንካራ ጎኑ ነው። ነገር ግን የዘላለም ጥናት ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋር የተገናኘ ርዕሰ ጉዳይ አልተመለከተም። የሁለቱ እምነት ተከታዮች ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ አውድም አልተመረመረም። ስለዚህ የሁለቱ እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች የጋራ እሴቶች ተለይተው ስላልተጠኑ የሚታየው የጥናት ክፍተት ይሄው ርዕሰ ጉዳይ ነው።

የሃይማኖት ግጭቶችን መነሻ በማድረግ የተካሄደ ሌላው የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት የኃይለየሱስ ሙሉቀን ጥናት ነው። ጥናቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሰላምና ደህንነት ድኅረ ምረቃ መርሃ-ግብር የቀረበ ሲሆን፤ “Religious Tolerance & Tension between Orthodox Christianity & Islam, Religion in Gondor Town, North West Ethiopia.” የሚል ርእስ አለው። የጥናቱ ዋና ዓላማም የግጭቶቹን መንስኤ፣ ምክንያትና ውጤት መርምሮ መግለጽ ነው። አጥኚው ይህንን ዓላማ ለማሳካት የተከተሉት የጥናት ሥልት አይነታዊ ነው። በዚህም በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና በቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት መረጃ ሰብስበዋል። እንዲሁም የተለያዩ ሰነዶችን መርምረዋል። በነዚህ የመረጃ ምንጮች አማካይነት የግጭቶቹን ምክንያት ዘርዝረዋል።

በዚህም ለግጭት የሚያነሳሱ ሃይማኖታዊ ጽሑፎችና ሃይማኖታዊ ስብከቶች (ቅስቀሳዎች)፣ የማምለኪያ ቦታዎች ሽሚያ፣ የሕግ የበላይነትን አለማክበርና አለማስከበር፣ የሃይማኖት አክራሪነት፣ የዋህ የእምነቱን ተከታዮች መሣሪያ አድርጎ መጠቀም፣ ሃይማኖታዊ መብትና ግዴታን ለይቶ አለማወቅ ወይም እያወቁ መተላለፍ፣ ከነባሩ የማኅበረሰቡ ባህል፣ ወግና ልማድ ማፈንገጥ፣ ያለፉ አሉታዊ ክስተቶችን እንደ አዲስ አንስቶ ማራገብ፣ ውስጣዊና ውጫዊው ነባራዊ ሁኔታዎችና ሌሎች ጉዳዮች በጎንደር ከተማ ለተከሰተው የሃይማኖት ግጭት ምክንያት ተብለው የተዘረዘሩ ነጥቦች ናቸው።

በጥናቱ መሠረት የግጭቶቹ ቆስቋሾችና ፈጻሚዎች ደግሞ አክራሪ የሃይማኖት መሪዎችና የእምነቱ ተከታዮች ናቸው። እንዲሁም የስራ ባህርያቸው ከሃይማኖት ጋር የተገናኙ ተቋማትና ማኅበራት ሌሎች የግጭቱ ቆስቋሾች ተብለው የተጠቀሱ አካላት ናቸው። የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በየደረጃው፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና የውጭ ኃይላትም የግጭቶቹ ምክንያቶች ናቸው። የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው በነዚህ አካላት አማካይነት የተከሰተው ግጭት ውጤቱ ሃብትና ንብረት ከማውደም አልፎ የሰው ሕይወት አጥፍቷል። ክስተቱ ቀደም ሲል የነበረውን የሁለቱን እምነት ተከታዮች መልካም የሆነ የእርስ በርስ ግንኙነት፣ ትስስር፣ መደጋገፍና ወንድማዊ ግንኙነት ወደጥላቻ ስሜት በመቀየር ቁርሾ እንዲይዙ አድርጓል።

በኃይለየሱስ ጥናት እንደተመለከተው በነዚህ ግጭቶች ምክንያት ለዘመናት የአካባቢውን ማኅበረሰብ እርስ በርሱ በሰላም፣ በፍቅርና በአንድነት ተደጋግፎ እንዲኖር መሠረት የነበሩት የጋራ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች በመሸርሸር ላይ ናቸው። ይህንን አሉታዊ አካሄድ ለማስተካከል ደግሞ መንግሥት አስፈላጊውን ሕግ፣ ደንብና ሥርአት ከማበጀት አንስቶ፤ የሕግ ልዕልናን ማስከበርና ራሱም ማክበር እንዳለበት ጥናቱ ይጠቁማል። የእምነቶቹ መሪዎች፣ አባቶችና ምእመናንም የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ጥናቱ ይመክራል። በመጨረሻም የሃይማኖት ግጭቶች ጉዳይ አፋጣኝ መፍትሄና ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ አንገብጋቢ አገራዊ አጀንዳ መሆኑ በአጥኚው የጥናት ማጠቃለያ ላይ የተሰነዘሩ የይሁንታ ነጥቦች ናቸው።

በኃይለየሱስ ጥናት መሠረት የጉዳዩ ፈፃሚዎችም ሆኑ አስፈፃሚዎች ነባሩን የሃይማኖት መቻቻል እሴት የሚፃረሩና የሚቃወሙ አካላት ናቸው። በመሆኑም የጥናቱ ርእሰ ጉዳይ የነዚህን አካላት ማንነት፣ ፍላጎትና ዓላማ በማጥናት በነዚህ አካላት አማካይነት የተከሰተውን ግጭት፣ በግጭቱ የተገኘውን ውጤት በማሳየት፣ ሂደቱ በዚሁ ከቀጠለ ወደፊት ምን አይነት ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል የሚተነብይ ሥራ ነው። እንደ ኃይለየሱስ ሁሉ በሃይማኖት ግጭቶች ላይ የተካሄደው ሌላው ጥናት የመሐመድ ይማም የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ነው። ጥናቱ የቀረበው በተመሣሣይ ለሰላምና ደህንነት ድጎረ ምረቃ መርሃ ግብር ነው።

የመሐመድ ጥናት "Inter-Faith Relations in Urban Centers of North-Eastern Ethiopia (Amhara Natinal Regional State): The Case of Dásé, Kámbolcha and Kámesé" የሚል ርዕስ አለው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ እንደሌሎቹ ሁሉ የግጭቶቹን መንስኤ፣

ምክንያትና ውጤት መርምሮ የሚገልጽ ነው። በዚህም መንስኤዎቹም ሆኑ ምክንያቶቹ እንዲሁም ውጤቶቹ በዘላለምና በኃይለየሱስ ጥናቶች ከተገለጹት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ልዩነት ቢኖር የቦታ ጉዳይ ብቻ ነው። ስለዚህ የመሐመድም ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚገናኝ አይደለም።

በሌላ በኩል የሃይማኖት ግጭቶችን ከሕግ አንፃር የመረመሩ ጥናቶችም አሉ። ለዚህ ማሳያ የተካልኝ ፋንታ ጥናት ለአብነት ይጠቀሳል። የተካልኝ ጥናት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ለሕግ ትምህርት ቤት የቀረበ ሲሆን፤ "Managing Religious Conflicts: A Study of the Legal Framework with Particular Reference to the 2006 Muslim-Christian Conflict in Oromya." የሚል ርዕስ አለው።

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ቀደም ሲል የነበሩ የሀገሪቱን ሕገ መንግሥቶች ከሃይማኖት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ዳራ በማድረግ፤ በአሁኑ ሕገ መንግሥት ላይ ተመስርቶ የግጭቶቹን መንስኤ፣ ምክንያትና ውጤት ከሕገ-መንግሥቱና ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች አንቀፆች ጋር በማጣቀስ ትንተና ማድረግ ነው። በዚህም የሕግ ልዕልና፣ የሃይማኖት ነፃነትና የሰብአዊ መብት ጽንሰ ሃሳቦችን መርምሮ የሃይማኖት ነፃነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ አብራርቷል። በመሆኑም የተካልኝ ጥናት የሃይማኖት ግጭቶችን ከሕግ አንፃር የመረመረ እንጂ ከሃይማኖት መቻቻል እሴት አንፃር ያጠና ባለመሆኑ ሰፊ የጥናት ክፍተት አለ።

ከዚህ በላይ በሃይማኖት ግጭቶች ላይ ተመስርተው ከተካሄዱ ጥናቶች ውስጥ አንድ የጋራ ጉዳይ ነቅሶ ማውጣት ይቻላል። ይኸውም ጥናቶቹ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ በተከሰቱ የሃይማኖት ግጭቶች ላይ ተመስርተው ቢካሄዱም፣ በሁሉም ጥናቶች የሚታዩት የግጭት መንስኤዎች፣ ምክንያቶችና ውጤቶች ፍጹም ተመሳሳይ መሆናቸው ነው። ከዚህ ሁኔታ መረዳት የሚቻለው ቁምነገር ደግሞ በሃገሪቱ የሚከሰቱ የሃይማኖት ግጭቶች ሥረ-መሠረታቸው ከአንድ ግንድ የበቀሉ ቅርንጫፎች መሆናቸውን መረዳት መቻሉ ነው። በዚህም በተለያዩ አካባቢዎች ተመሣሣይ ጥናቶች መካሄዳቸው የአንድን ችግር ምክንያትና ውጤት መመሳሰል ወይም መለያየት ለመረዳት ያስችላል። በዚህ ላይ ተመስርቶም እንደየባህርይው የመፍትሄ ርምጃ ለመውሰድ መልካም አጋጣሚ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ምንም እንኳ ጥናቶቹ ተመሣሣይ ርዕስና ተመሳሳይ የአጠናን ዘዴ ቢከተሉም በነዚህ ጥናቶች ላይ ተመስርቶ

አንድ አገራዊ የሆነ ወጥ ጥናት ለማካሄድ ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ጠንካራ ጎናቸው የሚያመዝን ጥናቶች ናቸው።

እነዚህን ጥናቶች የሚያገናኛቸው ሁለተኛው ክር ደግሞ በሁሉም አካባቢዎች በተከሰቱት ግጭቶች የእምነቱ ተከታዮች ተዋንያን ስለመሆናቸው የጥናታቸው ግኝት አለመግለጹ ነው። በመሆኑም አሁንም ቢሆን የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት መቻቻል እሴት በእምነቶቹ ተከታዮች መካከል መኖሩን ማረጋገጫ አብነት ነው። የዚህን እሴት ሚና ማጥናትና መግለጽ ደግሞ ተገቢ ይሆናል። የዚህ ጥናት ትኩረትም ይህንን እሴት መርምሮ መግለጽ ነው።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በቀረበበት ምዕራፍ ውስጥ ሃይማኖትና የሃይማኖት ግጭቶችን የጥናታቸው መነሻ ያደረጉ የተመረጡ ቀደምት ጥናቶች ቀርበው ተመርምረዋል። በዚህም ሃይማኖቶቹን ከተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር በማገናኘት አጥንተዋል። በተለይ ሃይማኖቶቹን ከታሪክ፣ ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከማኅበራዊ ጉዳዮች፣ ከባህላዊና ከራሳቸው ከሃይማኖቶቹ ጉዳይ ጋር የተያያዙ ሁነቶች በጥናቶቹ ውስጥ በስፋትና በጥልቀት ምርምር ተካሂዶባቸዋል። በነዚህ ጥናቶች ውስጥ የተነሱት ርዕሰ ጉዳዮችም ለሌሎች ጥናቶች መነሻ መሠረት የሚሆኑበት አጋጣሚ ብዙ ነው።
ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋር በተያያዘ በነዚህ ጥናቶች ተደጋግሞ የሚነሳው ርዕሰ ጉዳይ ተቻችሎ፣ በሰላም በፍቅርና በጋራ መኖር የኢትዮጵያና ህዝቦቿ የጋራ መገለጫ መሆኑ ነው። እንዲሁም የሃይማኖቶቹ መነሻ ከውጭ ቢሆንም ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡ በኋላ ግን ፍጹም ኢትዮጵያዊ መንፈስ የተላበሱ መሆናቸውን መግለጻቸው ነው። ነገር ግን ሃይማኖቶቹም ሆኑ የሃይማኖቶቹ እሴቶች እንዴትና በምን አይነት ሁኔታ የመቻቻል፣ የሰላም፣ የፍቅር፣ የአንድነት፣ የመከባበር፣ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ምንጭ ሊሆኑ እንደቻሉ ተንትነው አይገልጹም።

በሌላ በኩል የጥናታቸውን መነሻ የሃይማኖት ግጭቶች ላይ ያደረጉ ጥናቶች በበኩላቸው የግጭቶቹን ምንጭ፣ ምክንያትና ውጤት ተንትነው ካሳዩ በኋላ ለሁለቱ እምት ተከታይ ማኅበረሰቦች ተቻችሎ መኖር መሰረት የሆኑ ነባሮቹ የጋራ እሴቶች አደጋ እንዳንጎበበባቸው ገልጸዋል። በነዚህ ጥናቶች መሠረት በአሁኑ ጊዜ የሃይማኖት ግጭት በኢትዮጵያ አሳሳቢ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። የግጭቶቹ ጠንሳሾች፣ ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎች ደግሞ ነባሮቹን የጋራ እሴቶች አጥብቀው የሚቃወሙና እነሱንም ለማጥፋት ቆርጠው የተነሱ አካላት ናቸው።

የነዚህ አካላት መርህ ከአንድነት ይልቅ ልዩነትን፣ ከመተባበር ይልቅ መለያየትን የሚሰብክ ነው። በዚህም የሁለቱ እምነት ተከታዮች የሚገናኙባቸውን ድልድዮች የሚያፈርሱ፣ የሚተሳሰሩባቸውን የጋራ ክሮች የሚበጥሱ አካላት ናቸው። የነዚህ አካላት ዓላማና ተልእኮ ከዚህ ጋር የተገናኘ በመሆኑ ብዙ መገናኛ ድልድዮች ሳይፈርሱና በርካታ የጋራ መተሳሰሪያ ክሮች ሳይበጠሱ በሃይማኖት መቻቻል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሌሎች ተግባራትን ጨምሮ፤ ምሁራን ጥናትና ምርምር ማድረግ እንዳለባቸው ማሳሰብ የነዚህ ቀደምት ጥናቶች የማጠቃለያ የይሁንታ ነጥብ ነው። ምንም እንኳን እንዚህ ጥናቶች ይህንን ይሁንታ (Recommendation) የሰነዘሩት በተለያዩ አካባቢዎች በተከሰቱ ግጭቶችና ግጭቶቹ ባስከተሉት ውጤት ላይ ተመስርተው ቢሆንም የተሰነዘሩት አስተያየቶች ወቅታዊና አገራዊ አጀንዳዎች ናቸው።

በዚህ መሠረት የሃይማኖት መቻቻል እሴቶችን በዚያው በተፈጠሩበት፣ አድገውና ጎልብተው አገልግሎት በሚሰጡበት ማኅበረሰብ ውስጥ ዘልቆ በመመርመር ፋይዳቸውን መግለጽ ወቅታዊም አስፈላጊም ጉዳይ እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም የዚህ ጥናት መነሻና መድረሻም በወሎ በሁለቱ እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች መካከል ለጋራ መግባባት መሠረት የሆኑ ወይም እነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች ለረዥም ዘመናት ይጠቀሙባቸው የነበሩና አሁንም የሚገለገሉባቸውን የጋራ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች በመመርመር ወቅቱ ከሚጠይቀው ሁኔታ ጋር አጣጥሞ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን በጥናት አስደግፎ ማቅረብ ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ትክክለኛ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ መሰረት የዚህ ጥናት መረጃ መሰበሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች ከዚህ እንደሚከተለው ተብራርተው ቀርበዋል።

ምዕራፍ ሦስት

3፦ የጽንሰ-ሃሳብ፣ የንድፈ-ሃሳብ ማብራሪያዎች እና የጥናቱ ዘዴዎች

ቀደም ሲል የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በቀረቡበት በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የተመረጡ ጥናቶች ቀርበው ተመርምረዋል፡፡ በተደረገው ክለሳም እነዚህ ቀደምት ጥናቶች የራሳቸውን ንድፈ-ሃሳብና የአጠናን ዘዴ ተጠቅመው ምን አጥንተው ምን እንዳገኙ፣ ምን አይነት ክፍተት እንዳለባቸውና ይሄኛው ጥናት የሚሞላው ክፍተት ወይም ሊያመጣ የሚችለው አዲስ ነገር ምን ሊሆን እንደሚችል በዚሁ ምእራፍ ውስጥ ተብራርቷል፡፡ በምዕራፍ ሦስት ውስጥ ደግሞ የዚህን ጥናት ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ የጽንሰ-ሃሳብና የንድፈ-ሃሳብ ማብራሪያዎች፣ እንዲሁም የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡ ዝርዝሩ የፎክሎርን የጽንሰ-ሃሳብ ማብራሪያ (conceptual framework) በማስቀደም ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

3.1፦ ፎክሎር

ፎክሎር የሰብአዊ ሣይንሶች ዘርፍ የሆነ የትምህርትና የምርምር መስክ ነው (Dundes 1999)፡፡ ይህ የትምህርት መስክ በዊልያም ጆን ቶምስ አማካይነት "ፎክሎር" የሚለውን መጠሪያ ከአገኘበት ከ1846 ጀምሮ በስያሜው፣ በብያኔው፣ በሚያጠናቸው የማኅበረሰብ ክፍሎችና በሚያጠናው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በርካታ ክርክሮችንና ውዝግቦችን አስተናግዷል፡፡ በዚህ ሂደት ለፎክሎር የተለያዩ ስያሜዎች የተሰጡትን ያህል ብያኔዎቹም የትየለሌ ናቸው፡፡

ፎክሎር አሁንም ድረስ ቁርጥ ያለ ብያኔ ባይኖረውም በርካታ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ እነዚህ ብያኔዎች አብዛኛዎቹ ዘርዛሪዎች ሲሆኑ፤ የተቀሩት ደግሞ ተግባራዊ ብያኔዎች ናቸው (Leach 1949; Dundes 1965; 1999; Jones 1994; Dorson 1972; Toelken 1996; Utley 1965; Oring 1986; Georges & Jones 1995)፡፡ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚገልጹት ለፎክሎር ቁርጥ ያለ ብያኔ መስጠት ያልተቻለው ፎክሎር የሰው ልጆችን ሁኔታ በየፊርጁ የሚነካና ከተለያዩ ሌሎች በርካታ ዘርፎች ጋር የሚገናኝ ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህም ሁሉም ዘርፎች ሊስማሙበት የሚችል አንድ የተወሰነ ብያኔ መስጠት የማይቻል መሆኑ አንዱ ምክንያት ነው (Dundes 1965)፡፡

ከብያኔ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሁለተኛው የፎክሎር ውዝግብ ደግሞ ከጽንሰ-ሃሳብ ጋር የተገናኘ ጉዳይ ነው፡፡ ይኸውም ፎክሎር "ፎክ" እና "ሎር" የተሰኙ ሁለት የተለያዩ ፍችዎች

ያሏቸው ስያሜዎች ጥምረት ውጤት መሆኑ ነው። የክርክሩና የውዝግቡ መነሻም እነዚህ ቃላት በውስጣቸው የያዙት ጽንሰ-ሃሳብ ወይም ፍች ነው። ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ቃላቱ በያዙት ጽንሰ -ሃሳብ መነሻ ዘረኝነት ተስፋፍቷል። ቃላቱ የኋላቀርነትና የስልጣኔ መለያ ምልክት ተደርገው ተወስደዋል (Dundes 1999)። በዚህ ብቻም ሳይወሰኑ የአውሮፓውያንን የስልጣኔ ብርሃን ወደ ጨለማው የዓለም ክፍል ለማዳረስ በሚል ሰበብ ለቅኝ ግዛት መስፋፋት ምክንያት ሁነዋል። እነዚህ ቃላት በያዙት ጽንሰ-ሃሳብ አማካይነት የአገሬው ነባር ባህል በቅኝ ገዥዎቹ ተለውጧል፤ ተደምስሷል። በዚህ ምክንያትም የአገሬው ማኅበረሰብ የማንነት ቀውስ ውስጥ እንዲገባ ምክንያት ሁነዋል። ምክንያቶቹ "ፎክ" ከሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ጋር እንዴት እንደተገኙ ከዚህ ቀጥሎ ባጭሩ ቀርቧል።

3.1.1፦ ‹‹ፎክ››

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በፎክሎር ጥናት ውስጥ "ፎክ" ማንን ይወክላል? የሚለው ጥያቄ ብዙዎችን እያወዛገበ ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ ዘልቋል። በተለይ የአዝማሞታውያን እና የሥርፀታዊያን ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኝ የነበሩ የዘርፉ ተመራማሪዎች ለአብነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ ምሁራን በዘመኑ "ፎክ" የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ የሚወክለው፤ ሣይንስ ያልደረሳቸውን፣ ያልተማሩና ያልሰለጠኑ፣ ባጠቃላይ ኋላቀር የሆነውን የገጠሩን ማኅበረሰብ በተለይ አፍሪካን ነው፤ የሚል አስታሳሰብ ነበራቸው (Dundes 1980; Dorson 1977)::

በነዚህ ምሁራን አስተሳሰብ እነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጥንታዊና ባዕድ አምልኮ የሚከተሉ በመሆናቸው ይህንን መለወጥና አውሮፓዊ ማድረግ የሚል ተልዕኮ ነበራቸው። ለማኅበረሰቦቹም "Savage, Barbaric, Primitive, Backward" የሚሉ የኋላቀርነት መገለጫ የሆኑ ስያሜዎችን ሰጥተዋል። ስያሜው የተሰጣቸውን ማኅበረሰቦችም ሕግና ሥርዓት የሌላቸው፣ እንደ አራዊት የሚኖሩ፣ አረቄ፣ አረመኔ፣ ኋላቀር...ወዘተ በማለት ፈርጀዋቸዋል። የነዚህ ምሁራን ቅኝት ሙሉ በሙሉ አውሮፓዊ ሁኖ (Erocentric) ፎክሎሩንም የተመለከቱት ከዚህ አንፃር ነበር (Dundes 1965; 1980; Schoemaker 1990)።

ነገር ግን ከ1960ዎቹ አጋማሽ በኋላ ይህንን አመለካከት የተቃወሙ ሌሎች የዘርፉ ምሁራን ተነስተዋል። እነዚህ ምሁራን በፎክሎር ጥናት ሪቻርድ ዶርሰን እንደሚሉት "አዲሱ ትውልድ (Young Turks)" በመባል ይታወቃሉ (Dorson 1972; 45)። ዶርሰን እንደሚሉት እነዚህ ምሁራን ያለፈውን የተዛባ አመለካከት ሙሉ በሙሉ በማረም በሌላ አዲስ አይነት አስተሳሰብ ተክተውታል (Paredes and Bauman 1972)። ሪቻርድ ቦውማን በበኩላቸው "ፎክ" ማንን

ይወክላል? የሚለው ውዝግብ መፍትሔ ማግኘቱን ገልፀው፤ ይህም የሆነው አሜሪካዊው ፎክሎሪስት አላን ዳንደስ ለዘመናት የነበረውን ጫጫታ ሁሉ መዝጋት በመቻላቸው ነው። ይህንንም "ከፎክሎር ብያኔ ጋር በተያያዘ የነበረውን ውዝግብ ዳንደስ ፈር አስይዞታል።" በማለት ቦውማን ይገልጻሉ (Bauman 1992: 35)። ቦውማን እንደሚሉት አላን ዳንደስ ለረዥም ዘመናት ቀጥሎ የነበረውን የፎክሎር ብያኔ ውዝግብ የፈቱት በመጀመሪያ "ፎክ" ማንን ይወክላል? ለሚለው ጽንሰ-ሃሳብ የሚከተለውን ብያኔ በመስጠት ነው። በዚህ መሰረት፤

> "ፎክ" ማለት በአንድ በሆነ የጋራ ክር ወይም እሴት በአንድነት የተሳሰሩ የየትኛውም አካል የሰዎች ስብስብ ወይም ቡድን የጋራ መጠሪያ ነው። ቡድኑ የተሰባሰበበት ምክንያትም ሆነ የተሳሰረበት የጋራ ክር ወይም እሴት አይነቱና አገልግሎቱ ምንም ነገር ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ቡድኑ በሥራ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በሌሎች ተመሳሳይ ክሮች ወይም እሴቶች ሊገናኝ (ሊተሳሰር) ይችላል። መሠረታዊው ቁም ነገር ግን ቡድኑን በጋራ ያስተሳሰረውን ክር ወይም እሴት የቡድኑ አባላት የኔ የራሴ ብለው የሚቀበሉት የጋራ እሴት (ትውፊት) መሆን ይኖርበታል። እንዲሁም የቡድኑ ቁጥር በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ከሁለት ሊጀምር ይችላል። በተጨባጭ ግን ብዙውን ጊዜ የተወሰኑ ቡድኖችን ወይም የማኅበረሰብ ክፍሎችን ጨምሮ፤ እስከ አንድ አገር ህዝብ ሊደርስ ይችላል። ከዚህ አንፃር የቡድኑ አባላት እርስ በርስ ላይተዋወቁ ይችላሉ፤ መተዋወቅም የግድ አይደለም። ከጋራ እሴቱ ጋር ግን የቅርብ ዝምድና ሊኖራቸው ግድ ነው።[27]

በዳንደስ ብያኔ መሰረት "ፎክ" ማለት የማንኛውም ቡድን ወይም አካል መጠሪያ ስያሜ ነው። ስያሜው የገጠር-የከተማ፣ የሃብታም-የድሃ፣ የሰለጠነ-ያልሰለጠነ፣ የአውሮፓ የአፍሪካ...ወዘተ ሳይሆን፤ የየትኛውም ቡድን መጠሪያ ስያሜ ነው። በሌላ አገላለጽ "ፎክ" ማለት በአንድ የጋራ ጉዳይ የሚገናኙ የሰው ልጆች በሙሉ ተጠቃለው የሚጠሩበት ስያሜ ነው። መሠረታዊው ቁም ነገር ግን እነዚህ አካላት እርስ በርስ የሚገናኙበት ወይም የሚተሳሰሩበትና የኔ የራሴ የሚሉት አንድ የጋራ እሴት ከመኖሩ ላይ ነው። ይህ የጋራ እሴት ደግሞ "ሎር" ተብሎ የሚጠራው ጽንሰ-ሃሳብ ነው። ጽንሰ ሃሳቡ እንደ "ፎክ" ሁሉ ምንን እና የማንን ጉዳይ ይመለከታል? የሚለው ነጥብ ግን ለረዥም ዘመናት ሲያከራክር ቆይቷል። ይህ ክርክር እንደ ‹‹ፎክ›› ሁሉ በተመሳሳይ ከ1960ዎቹ በኋላ በተነሱ የፎክሎር ምሁራን እልባት አግኝቷል።

---

[27] The term 'folk' can refer to any group of people what soever who share at least one common factor. It does not matter what the linking factor is- it could be a common occupation, language or religion-but what is important is that a group formed for what ever reason will have some traditions which it calls its own. In theory a group must consist of atleast two persons, but generally most groups consist of many individuals. A member of the group may not know all other members, but he will probably know. The common core of traditions belonging to the group, tradition which help the group have a sense of group identity (Dundes 1965:2).

3.1.2፡- ‹‹ሎር››

ከላይ እንደተጠቀሰው ቀደምት የፎክሎር ተመራማሪዎች ‹‹ፎክ›› የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ የተመለከቱት ከገጠሩ ማኅበረሰብ ጋር በማያያዝ ነበር፡፡ እነዚህ አካላት ‹‹ሎር›› ለሚለው ጽንሰ- ሃሳብም ተመሳሳይ አመለካከት ነበራቸው፡፡ በመሆኑም በነዚህ አካላት ‹‹ሎር›› ማለት የገጠር ህዝብ እሴት በመሆኑ የሚገኘውም በገጠር ነው፤ የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው፡፡ በተመራማሪዎቹ እምነት መሠረት የ‹‹ሎር›› መነሻ ገጠር በመሆኑ ግንኙነቱም ሆነ አገልግሎቱ ከገጠሩ ህዝብ ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ በመሆኑም እሴቱ ከዘመኑ ስልጣኔ ጋር አብሮ የማይሄድ፣ የጥንት ዘመን አስተሳሰብ በመሆኑ ፋይዳ የሌለውና የመሃይም ሥራ የሚል ሥያሜ ሰጥተውታል፡፡ “እረጋ ሰራሽ” በማለት ጠርተውታል፡፡

በተጨማሪም የኋላቀር ህዝብ እውቀትና የኋላቀርነት መገለጫ በማለት ፈርጀውታል፡፡ በዚህ መነሻ እሴቱን ጎጂ-ልማድ ወይም ድርጊት እንዲሁም ጎጂ-አስተሳሰብ ወይም የሕይወት መመሪያ...ወዘተ የሚል ብያኔ ሰጥተውታል፡፡ ከዚህ የተዛባ አስተሳሰብ በመነሳትም እሴቱ ወይም ሎሩ መወገድ ያለበትና በሌላ ጠቃሚ በሆነ በሰለጠነው ዓለም እሴት መተካት አለበት የሚል ጽኑ አቋም ነበራቸው፡፡ በዚህም ባህልን የበላይነትና የበታችነት መለኪያ በማድረግ ልዩነትን (Ethnocentrism) አስፋፍተውበታል፡፡ የአውሮፓውያንን የበላይነት (Eurocentrism) ሰብከውበታል (Dundes 1965, 1999; Ben -Amos 1971; Dorson 1972)::

ነገር ግን ድኅረ-1960ዎቹ የፎክሎር ምሁራን ይህንን አስተሳሰብ በመቃወም በምትኩ ከቀዳሚዎቹ የተለየ ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ የነዚህ ምሁራን መሠረታዊ ፍልስፍና ወይም መርህ የአንዱን ባህል ጎጂ፣ የሌላውን ባህል ጠቃሚ ብሎ መፈረጅ ሳይንሳዊ አለመሆኑን በጥናት አስደግፎ መግለጽ ነው፡፡ ምንም እንኳን የዚህ አይነት አስተሳሰብ በእነ ፍራንዝ ቦአዝ ዘመን የተጀመረ ቢሆንም እነዚህ ምሁራን ግን አስተሳሰቡን ይበልጥ ገፍተውበት በተግባር ሥራ ላይ አውለውታል፡፡ በዚህም አንድ ባህል ጎጂ ወይም ጠቃሚ መባል ካለበትም ከሌላው ማኅበረሰብ እሴት አንፃር እና ለእሴቱ ባእድ በሆነ አካል ሳይሆን፤ የእሴቱ ባለቤት ከሆነው ማኅበረሰብ አንፃርና በእሴቶቹ ባለቤቶች አማካይነት ነው፤ የሚል መከራከሪያ ነጥብ ነበራቸው (Ben-Amos 1976; Geertz 1973; Hobsbawm & Terence 1983)::

በዚህ መነሻ እነዚህ ምሁራን ‹‹ሎር›› ለሚለው ጽንሰ-ሃሳብ የሰጡት ብያኔ የሰው ልጅ በማኅበር ሲኖር በየትኛውም ቦታና ጊዜ የፈጠረውና ያካበተው የትኛውም አይነት አገር በቀል እውቀት ነው፡፡ ወይም “ሎር” ማለት መሳጭነት ያላቸው ህዝባዊ የሆኑ በቃልም፣ በጽሑፍም፣

በድርጊትም ሆነ በእደ ጥበብ አማካይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩና የአንድ ማኅበረሰብ የፍልስፍና፣ የገጠመኝ፣ የእምነት፣ የሃዘን፣ የደስታ...ወዘተ መገለጫ የሆነ ጥበባዊ እሴት ነው፤ በማለት በይነውታል (Ben- Amos 1971; Dorson 1972; Glassie 1999; Schoemaker 1990)::

በመሆኑም "ሎር" ማለት የሰው ልጅ በማኅበር ሲኖር የፈጠራቸውና የሚጠቀምባቸው የአሰራር፣ የአኗኗር፣ የአስተዳደር፣ የአነጋገር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣...ወዘተ ዘዴዎች፣ ብልሃቶች፣ ፍልስፍናዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ጥበቦች፣ አመለካከቶች፣ እምነቶች፣ አምልኮዎች፣ የእርስ በርስ ግንኙነቶች፣ ገጠመኞች...ወዘተ ሁሉ የሚያጠቃልል ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ እንዲሁም ‹‹ሎር›› በየጊዜው አንዳንድ ነገሩ እየተሻሻለ፣ እየተለወጠ፣ እየተተካ፣ ሃዳዲስ እየተፈጠረ፣ አንዱ ማኅበረሰብ የሌላውን በመውረስ ሲጥመው የሚጠቀምበትና ሳይጥመው ሲቀር የሚተወው፤ ባጠቃላይ በሂደት አገልግሎት እየሰጠና ጉዳትም እያደረሰ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ በገጠርም በከተማም፣ በሰለጠነም ባልሰለጠነም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኝ የወል እሴት ነው (Oring 1986; Dorson 1986; Bauman 1992; George& Jones 1995)፡፡

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ከ1960ዎቹ በፊት የነበሩ ምሁራን ‹‹ፎክ›› እና ‹‹ሎር›› ለተሰኙት ጽንሰ-ሃሳቦች የነበራቸውን አመለካከት ለማየት ተሞክሯል፡፡ ባንፃሩ ድኅረ-1960ዎቹ የፎክሎር ምሁራን የሰጡት ብያኔም ተገልጿል፡፡ በመሆኑም በድህረ-1960ዎቹ የፎክሎር ምሁራን ብያኔ መሰረት በጥቅሉ ‹‹ፎክ›› ማለት ከናሳ ሳይንቲስቶች እስከ የታክሲ ወያላዎች፣ ከሃገር መሪዎች እስከ እፅ አዘዋዋሪዎች፣ ከገበሬ እስከ ነጋዴ፣ ከወታደር እስከ መምህር፣ ወይም ባጠቃላይ የስልጣኔ ጣሪያ ከነኩ የማኅበረሰብ ክፍሎች እስከ "የአቦርጅን" የማኅበረሰብ ክፍሎችን የሚመለከት ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ ከቡድኑ ብዛት ወይም ቁጥር አንፃርም ከአንድ አገር ህዝብ እስከ ባልና ሚስት ሊደርስ ይችላል፡፡

"ሎር" የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ደግሞ በነዚህ አካላት ተፈጥሮና ዳብሮ ከነሱ ጋር የሚኖር፣ ከእለት ተለት ሕይወታቸው ጋር የተገናኘ፣ ማኅበራዊ የሆነና ማኅበሩ የሚገለገልበት አገር በቀል እውቀት ወይም እሴት ነው፡፡ ለምሳሌ የዘርፉ ምሁራን እንደሚሉት የናሳ ሳይንቲስቶች እራሳቸውን የሚገልጹበት ወይም እርስ በርስ የሚግባቡበት "ሎር" አላቸው፡፡ ሃኪሞች፣ መምህራን፣ ነጋዴዎች፣ ተማሪዎች፣ የጦር ሰራዊት፣ ፖሊሶች፣ የፋብሪካ ሰራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ ሹፌሮች፣ ሴቶች፣ ወንዶች፣ ሕፃናት፣ አዛውንቶች፣...ወዘተ "ሎር" አላቸው፤ ዘዬ አላቸው ::

ባጠቃላይ በዚህ የጽንሰ-ሃሳብ ማብራሪያ መሠረት ፎክሎር እነማንን እና ምንን ያጠናል? ወይም "ፎክ" ማንን ይወክላል "ሎር"ስ? የሚሉት ጥያቄዎች በዚህ ጥናት ውስጥ "ፎክ" ማለት የሚጠናውን ማኅበረሰብ፣ የማኅበረሰቡን መዋቅሮችና መስተጋብሮች ወይም የእርስ በርስ ግንኙነቶች ይመለከታል። "ሎር" ደግሞ የማኅበረሰቡን የጋራ እሴቶች፣ የእሴቶቹን ምንጭ፣ አሠራራቸውን፣ አተገባበራቸውን፣ ፋይዳቸውን እና ሌሎች ጉዳዮችን ሁሉ የሚመለከት ጽንሰ - ሃሳብ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ የተገለጹት ጉዳዮች በሙሉ በዚህ የጽንሰ-ሃሳብ ማዕቀፍ ውስጥ የተተነተኑ ናቸው። ፎክሎር የሚለው መጠሪያም እነዚህን ጽንሰ-ሃሳቦች ሁሉ የሚያካትት ሆኖ፤ የራሱና እሱ የሚያጠናው ሣይንስ መጠሪያም ነው (Dorson 1972)።

ከላይ እንደተመለከተው ድህረ-1960ዎቹ የፎክሎር ምሁራን ከነሱ በፊት ለፎክሎር በተሰጡ ብያኔዎችና ልዩ ልዩ አመለካከቶች ላይ የታዩ ድክመቶችን በማሳየትና በማረም የራሳቸው የሆነ አዲስ አይነት አቅጣጫ አሳይተዋል። ለፎክሎር ጥናት የነዚህ ምሁራን አስተዋጽዖ በፎክሎር ብያኔ ላይ ብቻ የተገደበ አልነበረም። ባንዳንዱ ምሁራኑ ለፎክሎር ብያኔ ማብራሪያ የሰጡትን ያህል፤ በፎክሎር ህልውና፣ በፎክሎር ባህርይ፣ በፎክሎር ንድፈ ሃሳብና የአጠናን ሥነ-ዘዴ ላይም ሃዳዲስ መርሆዎችንና ሥልቶችን በማምጣት አቅጣጫ አሳይተዋል። ለምሳሌ የፎክሎር ባህርይ ከክዋኔ ጋር የተያያዘ መሆኑን በመጠቆም የፎክሎር ህልውና አውድ መሆኑን በጥናት አረጋግጠዋል። (Ben-Amos 1976; Bauman 1983; Dundes 1980; Dorson 1972):: በዚህ መሠረት ይሄ ጥናት የሚመራበት የንድፈ ሃሳብ አቅጣጫና የተከተለው የጥናት ዘዴ ከነዚህ ምሁራን አስተሳሰብ የመነጨ ነው። የእነሱንም ሣይንሳዊ አስተሳሰብ የተከተለ ነው። አስተሳሰቡም ከዚህ ቀጥሎ ተጠቃሎ ቀርቧል።

3.2፦ የጥናቱ ንድፈ ሃሳብ

መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከ19ኛው ከፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በፎክሎር ጥናት መስክ በርካታ ምሁራን የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦችን መነሻ በማድረግ ፎክሎርን አጥንተዋል። ንድፈ ሃሳቦቹም ከብሔራዊ መነቃቃት እስከ አዝግሞተ-ለውጥ ሥርዓት፤ ከዚያም ርዕዮተ-ዓለማዊውን አመለካከት ጨምሮ የፎክሎርን መፈጠሪያ ቦታ (Ur-Form) ወይም መነሻ መንደሩን ለማወቅ የተደረገውን ጥረት ሁሉ ያጠቃልላል (Dorson 1972: 7-47)። በዚህ ሂደት በዘመኑ የአውሮፓ ብሔርተኝነት እንቅስቃሴ ወቅት የፎክሎር ንድፈ ሃሳብ የማንነት መፈለጊያ መሣሪያ በመሆን አገልግሏል። በዘመነ አዝግሞተ-ለውጥ ጊዜ ደግሞ የልዩነት መፍጠሪያ (ማበላለጫ) ቤተ-መከራ ነበር። ከርዕዮተ-ዓለማዊው አንፃር ጀርመንና ሩሲያ በተግባር ሥራ ላይ አውለውታል።

የፎክሎርን መነሻ ቦታ ወይም የተፈጠረበትን መንደር ለማወቅ ከተደረገው ጥረት አንፃርም የፊላንድ ወይም የሥርፀታውያን ንድፈ ሃሳብ አራማጅ ምሁራን ተጠቃሾች ናቸው። ከሥነ-ልቡና አንፃርም ሲግመንድ ፍሮይድ እና ካርል የንግ የየራሳቸው ድርሻ አላቸው።

በሌላ በኩል የፎክሎርን ቅርጽ ከይዘቱ ጋር አጣምሮ የመመርመሩ ሂደት የመዋቅራዊ ንድፈ ሃሳብ ተከታይ ምሁራን መገለጫ ነው። እነዚህ ምሁራን ፎክሎርን በይዘቱ፣ በመዋቅሩና በአገልግሎቱ ላይ ተመስርተው አጥንተዋል። በዚህ በኩል ስቲስ ቶምሰን፣ ቭላድሚር ፕሮፕ፣ ክሎውድ ሌቪስትራውስ እና ብሮኒስላው ማሊኖውዊስኪ ግንባር ቀደሙን ቦታ ይይዛሉ። እነዚህ ምሁራን የፎክሎርን መዋቅር በምእራፍ፣ በምእራፍ በመከፋፈል መገጣጠሚያውን ሳይቀር ተንትነው አጥንተዋል።
ምንም እንኳን እነዚህ ምሁራን ለፎክሎር ጥናት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ያበረከቱና ንድፈ ሃሳቦቹም አሁንም ድረስ እየተሰራባቸው የሚገኙ ቢሆንም፤ በንድፈ ሃሳቦቹም ሆነ በምሁራኑ ላይ የተለያዩ ትችቶች ተሰንዝረውባቸዋል። ትችቱ የተሰነዘረባቸው ደግሞ በድህረ-1960ዎቹ የፎክሎር ምሁራን አማካይነት ሲሆን፤ የትችታቸው መሠረታዊ ምክንያትም የቀዳሚዎቹ ጥናት በዋናነት የተመሰረተው በፎክሎር ቴክስት ላይ ብቻ በመሆኑ ነው (Ben-Amos 1976: 1993; Bauman 1983; Dundes 1980)::
እነዚህ ምሁራን እንደሚሉት በፎክሎር ጥናት ‹‹ቴክስት›› አንድ አካል እንጂ፤ መሠረታዊ ጉዳይ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም የፎክሎር መዋቅር ወይም ቅርጽና ይዘት አለያም አገልግሎቱን ብቻ መነሻ በማድረግ የሚካሄድ የፎክሎር ጥናት ተገቢነት ያለው ሁኖ አይገኝም። ለምሳሌ በዳን ቤን-አሞፅ አመለካከት መሰረት ለአንዱ ማኅበረሰብ ከፍተኛ ቁምነገር ወይም ጥቅም ያለው የፎክሎር ዘርፍ ለሌላው የማኅበረሰብ ክፍል ምኑም ላይሆን ይችላል (Ben- Amos 1976)። ይህንን የቤናሞፅ የመከራከሪያ ሀሳብ ወደኛ አገር አምጥተን ብናየው፣ ለአብነት የኑዌር ማኅበረሰብ የግንባር መተልተል ባህል-ወግና ልማድ ለሱርማው ማኅበረሰብ ምኑም ላይሆን ይችላል።ባንፃሩ የሱርማው የዶንጋ ባህል-ወግና ልማድ ለኑዌሩ ባእድ ሊሆን ይችላል። ለየራሳቸው ግን ከነፍሳቸው ጋር የተዋኻደ ፋይዳ አለው።
በዚህ መሠረት ቤናሞፅ እንደሚሉት አንዱ ማኅበረሰብ ለራሱ የፎክሎር ዘርፍ የሚሰጠው ትርጓሜ ወይም ፍቺ ሌላው ማኅበረሰብ ከሚሰጠው ትርጓሜ ጋር ተቃራኒ የሚሆንበት አጋጣሚም ብዙ ነው። የፎክሎር ዘርፍ አከፋፈሉም ሆነ አመዳደቡ እንደየማኅበረሰቡ ሁኔታ የሚወሰን ነው፤ በአካባቢውና በባህሉ የሚዳኝ ነው (Ben-Amos 1975; 1993):: በመሆኑም

የአንዱን ማኅበረሰብ ባህል መነሻ በማድረግ የሌላውን ማኅበረሰብ ባህል መዳኘት ወይም መፈረጅ አይቻልም።

ነገር ግን ድህረ-1960ዎቹ የፎክሎር ተመራማሪዎች እንደሚሉት አንድን ማኅበረሰብ ወይም ሰውን መረዳትና ማወቅ የሚቻለው በዚያው በአካባቢው፣ በባህሉና በኑሮው ላይ ተመስርቶ ሲጠና ብቻ ነው (Geertz 1973)። የትንታኔ ዘዴውን ብቻ ተጠቅሞ የፎክሎር ጥናት ማካሄድ ከፎክሎር ተፈጥሯዊ ባህርይ ውጭ ነው። ባንባሩ የፎክሎርን ትርጉምና ምንነት መረዳት የሚቻለው ባለቤቶቹ እንደሚረዱት፣ እንደሚከውኑትና እንደሚያውቁት ያህል ሁኖ በማጥናት ነው። የፎክሎሩን ፋይዳ፣ ተግባርና ጥቅም ለማጥናት ቢያስፈልግም ፎክሎሩ ተፈጥሮ ባደገበት፣ አድጎ በሚኖርበትና አገልግሎት በሚሰጥበት በአውዱ ላይ ተመስርቶ ማጥናት ሲቻል ነው። የማኅበረሰቡን ስሜት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ፍልስፍና፣ አመለካከት ወዘተ ማወቅና መረዳት የሚቻለውም በአውዱ ውስጥ ነው። የዚህ አይነቱ አስተሳሰብም በፎክሎር ጥናት አውዳዊ ንድፈ-ሃሳብ በመባል ይታወቃል (Bauman 1983; 1992; Ben-Amos 1975)::

3.2.1፦ አውዳዊ ንድፈ ሃሳብ (Contextual theory)

ድህረ-1960ዎቹ የፎክሎር ተመራማሪዎች የነደፉት የፎክሎር ንድፈ ሃሳብ አቅጣጫ ፎክሎርን በአውዱ ውስጥ ማጥናት የሚል አስተሳሰብ ነው። አስተሳሰቡ አውዳዊ ንድፈ ሃሳብ በመባል ይታወቃል። በዚህም ፎክሎር ሥጋ ነስቶ ደም አግብቶ ባጠቃላይ ሕልውና ዘርቶ የሚገኘው በአውድ ውስጥ በመሆኑ ጥናቱም በዚህ ንድፈ ሃሳብ መመራት እንዳለበት ተስማምተውበታል (Dundes 1980; Bauman 1992; Workman 1993; Dorson 1972; Paredes and Bauman 1972):: ከዚህ ጋር በተያያዘ ምሁራኑ እንደሚሉት በዚህ ንድፈ ሃሳብ በመመራት የፎክሎር ጥናት መነሻና መድረሻ የመሥክ ሥራ (fieldwork) ነው። የፎክሎር ጥናት ትንታኔም መመራት የሚኖርበት በዚያው ፎክሎሩ በተፈጠረበት አካባቢ፣ በአገሬው እውቀት ላይ ተመስርቶ፣ ከአካባቢው ከራሱ አመለካከትና ስሜት አንፃር መሆን ይኖርበታል። በመሆኑም በፎክሎር ጥናት ከቴክስት ይልቅ፤ በአገሬው ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ወይም ባጠቃላይ ማኅበረሰቡን ከአካባቢው ጋር አገናኝቶ ማጥናት የፎክሎር ጥናት መርህ መሆኑን አሳይተዋል (Bauman 1983; 1992)::

ምሁራኑ እንደሚሉት በፎክሎር ጥናት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የፎክሎር "ቴክስት" አንድ አካል አንጂ መሰረታዊ ጉዳይ አይደለም። በመሆኑም በፎክሎር ጥናት "ቴክስት" አንድ አካል ሆኖ መሰረታዊ ጉዳይ የሚባሉት የፎክሎር ሁነት (Event) እና ክዋኔ (performance) ናቸው (Ben-Amos & Goldstein 1975; Bauman 1992)። በባለሙያዎቹ እምነት መሠረት

የሁነቶቹ ምንነት እና የክዋኔዎቹ ፋይዳ ተለይቶ የሚታወቀው ደግሞ ድርጊቶቹን በመግለጽና (description) የክዋኔዎቹን ሂደት በመተረክ (narration) ሳይሆን፤ በአብዛኛው እንደሚጠናው ርእሰ ጉዳይ ሁኔታ ድርጊቶቹን በመተርጎም (interpretation) እና ሂደቱን በመተንተን (Analysis) ነው (Geertz 1973; Dundes 1980)::

የዚህ አይነት ጥናት የሚመራው ወይም መረጃው የሚተነተነው ደግሞ የአውዳዊ ንድፈ-ሃሳብ አካል በሆኑት በክዋኔ (performance) እና በትርጓሜ ንድፈ ሃሳብ (interpretive theory) አማካይነት ነው (Bauman 1992; Dundes 1980)። ይህን ንድፈ ሃሳብ የሌሎች የማኅበራዊ ሣይንስ ምሁራን የማኅበረሰብ አዋቃሪ (Social-Constructive Theory) ንድፈ-ሃሳብ በማለት ይጠሩታል (Creswell 2014)። እንዲሁም የፎክሎር ትርጉምና ምንነት በአውዱ ውስጥ ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት በእውቀት ንድፈ ሃሳብ (cognitive-theory) መመራት ያስፈልጋል (Geertz 1973):: ይህም ማለት የሚጠናውን የፎክሎር ሁነት ወይም ርእሰ ጉዳይ የፎክሎሩ ባለቤቶች የሚረዱትንና የሚያውቁትን ያህል እንኳ ባይሆን፤ ከእነሱ ጠይቆ በመረዳት በተቻለ መጠን ፎክሎሩን አውቆና ተረድቶ ማጥናት ሲቻል ነው።

ስለዚህ በአውዳዊ ንድፈ ሃሳብ መመራት ተመራማሪው የሚያጠናውን ማኅበረሰብ አካባቢና ባህል በትክክል እንዲረዳና እንዲያውቅ ያደርገዋል። ይህ ካልሆነ ግን የፎክሎር ትርጉም በአውዱ ውስጥ ምን ማለት እንደሆነ ሊያውቅ አይችልም። እንዲሁም ማኅበረሰቡ ፎክሎሩን በአውዱ ውስጥ እንዴት እንደሚተረጉመው፣ እንዴት እንደሚረዳው፣ እንዴት ፍቺ እንደሚሰጠው፣ እንዴት እንደሚገለገልበት ...ወዘተ በትክክል ሊያውቅ አይችልም። በፎክሎሩ ላይም ምልው የሆነ ትንታኔ አያደርግም። በዚህም ትክክለኛና ጥልቀት ያለው የፎክሎር ጥናት ሊያካሂድ አይችልም (Dundes 1980)::

የነዚህ ምሁራን ጥናቶች እንደሚገልጹት የአንድን ማኅበረሰብ ያለፈና የአሁን ተጨባጭ የማኅበራዊ ሕይወት መስተጋብር በፎክሎር አማካይነት መርምሮ ለመረዳት የሚቻለው ጥናቱ በማኅበራዊና ባህላዊ አውድ ውስጥ ሲመሠረት ነው (Bauman 1993)። የማኅበረሰቡን የሃዘንና የደስታ፣ የመተሳሰብና የመተዛዘን፣ የመረዳዳትና የመከባበር፣ የመቻቻልና በሰላም አብሮ የመኖር እሴቶቹን መርምሮ ፋይዳቸውን መግለጽ የሚቻለውም በፎክሎሩና በማኅበረሰቡ መካከል ያለውን ተፈጥሯዊ ተራክቦ (ግንኙነት) በአውዱ ውስጥ ማጥናት ሲቻል ነው (Ben-Amos 1976; 1993)።

ከዚህ በላይ የተገለፀው አውዳዊ ንድፈ ሃሳብ ከፎክሎር ጥናት ጋር ያለውን ግንኙነት ወይም የፎክሎር ጥናት በአውዳዊ ንድፈ ሃሳብ እንዴት ሊመራ እንደሚችልና ለጥናቱ ትንታኔ እንዴት እንደሚጠቅም የሚያስረዳ መሰረታዊ ሃሳብ ነው። በሌላ በኩል እነዚህ ምሁራን ለፎክሎር ጥናት አውድ ብቻውን በቂ አለመሆኑን በመጠቆም ሌላ ተጨማሪ የፎክሎር ጥናት የሚመራበትን አቅጣጫ አሳይተዋል። ይኸውም ፎክሎርን ማጥናትና መመርመር የሚቻለው በአንድ ገጽታው ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ አቅጣጫዎች (multidisciplinary approach) ጭምር በመመርመር ነው። በመሆኑም የፎክሎር ጥናት ወሰን እንደሌለው በመግለጽ፤ በፎክሎር ጥናት ይሄ የኔ አይደለም፣ አያገባኝም የሚባልበት አንዳችም ነገር እንደሌለ በጥናት አሳይተዋል (Dorson 1972; Cliford 1988; Dundes 1999)። እንዲሁም ፎክሎር በተለይ ከሌሎች የሰብአዊና የማኅበራዊ ሣይንስ የእውቀት ዘርፎች ጋር የጠበቀ ዝምድና እንዳለው እነዚህ ምሁራን የተስማሙበት ጉዳይ ነው።

ሌሎቹ የእውቀት ዘርፎችም ፎክሎርን ከማጥናት፣ ከማሳደግና ከማበልፀግ አንፃርም ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክተዋል። ፎክሎርም ለነዚህ የእውቀት ዘርፎች የራሱን ድርሻ አበርክቷል። አሁንም እያበረከተ ይገኛል። ለአብነት የሳይኮሎጂ ጉዳይ ያለው ከማኅበረሰቡ ፎክሎር ውስጥ ነው። በዚህም የሥነ-ልቡና ተመራማሪዎች ፎክሎርን ያጠናሉ፤ ይጠቀማሉ። ምክንያቱም የአንድን ማኅበረሰብ ሥነ-ልቡና ከፎክሎሩ ውጭ ማጥናት "ላም ባልዋለበት" አይነት የጥናት ሣይንስ ስለሚሆን ነው (Geertz 1973)። ፎክሎርና የታሪክ ትምህርትም የእትብት ዝምድና አላቸው። አፈታሪኩ፣ ሥነ ቃሉ፣ የሕይወት ታሪኩ...ወዘተ የዚህ ማሳያ ነው (Fekadu 1990; Gashaw 2003)።

ፎክሎር ከሥነ-ጽሑፍ፣ ከአንትሮፖሎጂ፣ ከሶሽዮሎጂ፣ ከፍልስፍና፣ ከቋንቋና ሌሎች የእውቀት ዘርፎች ጋርም የጠበቀ ቁርኝት አለው። በዚህም የየዘርፎቹ ሊቃውንት ፎክሎርን ያጠናሉ፣ ይጠቀማሉ (Clifored 1988; Hymes 1962; 1972)። በዚህ መነሻ ፎክሎር ከሌሎች የእውቀት ዘርፎች አንፃር ሲታይ ብቻውን ተነጥሎ የሚጠና የእውቀት ዘርፍ አይደለም። በመሆኑም ከሌሎች የእውቀት ዘርፎች ጋር ተገናኝቶና ተጎራብቶ መጠናት ይኖርበታል። በዚህ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ የፎክሎር ጥናት ደግሞ የአንድን ማኅበረሰብ አካባቢያዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ ግንኙነት ምን ሊሆን እንደሚችል በትክክል ሊገልጽ ይችላል። በዚህም የተጠኚውን ማኅበረሰብ ሁለንተናዊ ማንነት ለመረዳት ያስችላል። እነዚህ እሴቶች የተደራጁበትንና የሚገለጹበትን ሥልት በትክክል ለማወቅ ይረዳል። ይህም ሊሆን የሚችለው ሌሎች የእውቀት ዘርፎችን ከፎክሎር ጋር

አገናኙ መመርመር ሲቻል ነው። እንዲሁም ጥናቱ በአውዳዊ ንድፈ ሃሳብ መርህ ሲመራና መረጃዎቹም በዚሁ ንድፈ ሃሳብ ሲተነተኑ ነው (Bauman 1983; 1992; Dundes 1980; Ben-Amos 1976) ።

ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በድህረ-1960ዎቹ የፎክሎር ምሁራን አስተሳሰብ መሠረት የፎክሎር ጥናት ሥረ-መሰረቱ የመስክ ሥራ ነው። የመስክ ጥናት ዋነኛ ትኩረት ደግሞ የፎክሎሩን ቴክስት ጨምሮ በፎክሎር ሁነት እና ክዋኔ ላይ የተመሰረተ ነው። የሁነቶቹ ትርጉምና ፋይዳ እንዲሁም ክዋኔውን መረዳት የሚቻለው ደግሞ የሚጠናውን ማኅበረሰብ ቋንቋውን ጨምሮ፣ ማኅበራዊ ግንኙነቱን፣ አካባቢውንና ባህሉን ማወቅ ወይም መረዳት ሲቻል ነው። አካባቢውንና ባህሉን ከማወቅ በተጨማሪም በፎክሎር ትምህርት አማካይነት የተገኙ የእውቀት፣ የትምህርትና የምርምር ልምዶችን መጠቀም ያስፈልጋል። በዚህም እያወቁ እንዳላወቁ በመምሰል የፎክሎሩ ባለቤቶች በሚከውኑት ድርጊትና በሚሰጡት መረጃ መሠረት ጥናቱን ማካሄድ ተገቢ ይሆናል (ፈቃደ 2004 ዓ.ም.)።

በዚህ መርህ ላይ ተመስርቶ ጥናት ለማካሄድ ከላይ እንደተጠቀሰው ጥናቱ በአውዳዊ ንድፈ ሀሳብ አማካይነት መመራትና መረጃዎቹም በዚሁ ንድፈ ሃሳብ መተንተን አለባቸው። ስለዚህ ይሄ ጥናት የተመራበትና መረጃዎቹም የተተነተኑበት የንድፈ ሃሳብ መርህ ከዚህ በላይ የተለያዩ ሣይንሳዊ ነጥቦችን በማንሳት በተብራራው በዚሁ በአውዳዊ ንድፈ ሃሳብ አማካይነት ነው። እንዲሁም ለዚህ ጥናት መረጃዎች ሲሰበሰቡም ሆነ ሲተነተኑ በዚህ ንድፈ ሃሳብ ሥር የሚጠቃለሉት የክዋኔ (performance)፣ የጠቀሜታ (functional)፣ የትርጓሜ (interpretive) እና የእውቀት (cognitive) ንድፈ ሀሳብ መርሆዎችም ታሳቢ ተደርገዋል። እንዲሁም ሌሎች የእውቀት ዘርፎችን ከነዚህ ንድፈ ሃሳቦች ጋር በማጣጣም በዚህ ጥናት ውስጥ አገልግሎት ላይ ውለዋል።

ባጠቃላይ የንድፈ ሃሳቦቹ ዋና ዓላማ ጥናቱ በትክክለኛ አቅጣጫ እንዲመራና መረጃዎቹም በተገቢው መንገድ እንዲተነተኑ ለማድረግ ነው። ይህንን መርህ በተግባር ሥራ ላይ በማዋል የዚህ ጥናት የጀርባ አጥንት የሆኑት መረጃዎች በተገቢው መንገድ ተሰብስበዋል። ለዚህ ደግሞ ትክክለኛ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴ ተነድፎ ወደሥራ ተገብቷል። በዚህ መሰረት የዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢና መተንተኛ ሣይንሳዊ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው።

3.3፦ የጥናቱ ሥልት (Research Approach)

ከላይ በንዑስ ርዕስ 3.2 እንደተገለጸው ይሄ ጥናት የተመራውና መረጃዎቹም የተተነተኑት በአውዳዊ ንድፈ ሃሳብ ፍልስፍና (philosophical worldview) አማካይነት ነው። ንድፈ ሃሳቡ

የተመረጠበት መሠረታዊ ምክንያትም በዚህ ንድፈ ሃሳብ አማካይነት የሚመራ ጥናትና ምርምር መነሻና መድረሻው የመስክ ጥናት ወይም ተፈጥሯዊ አውድ (መቼት) በመሆኑ ነው። የንድፈ ሃሳቡ ተከታዮች እንደሚሉት አውድ የመረጃ መሰብሰቢያ፣ መተንተኛና መተርጎሚያ መሠረት ነው። በዚህም በጥናቱ ውስጥ የተነሱ የምርምር ጥያቄዎችን በትክክል በመመለስ የጥናቱ ዓላማ ግቡን እንዲመታ ያስችላል ተብሎ ይገመታል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ለጥናቱ በግብአትነት የሚያገለግሉት መረጃዎች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሲሰበሰቡ፣ ሲተነተኑና ሲተረጎሙ ነው። ከዚህ አንፃር ሊኖሩ ከሚችሉ በርካታ አማራጮች መካከል ለአንድ ጥናት ተስማሚ የሆነ የመረጃ መሰብሰቢያ፣ መተንተኛና መተርጎሚያ ዘዴ መምረጥ ያስፈልጋል።

ተስማሚ የጥናት ዘዴ መምረጥ የሚቻለው ደግሞ የተለያዩ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ ነው። ታሳቢ መደረግ ካለባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የሚጠናውን ርዕሰ ጉዳይ አይነትና ባህርይ፣ የተመራማሪው የትምህርትና ምርምር ቀረቤታ፣ እንዲሁም በጥናቱ ሊገለገሉ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ አካላትና ተቋማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው (Creswell 2014)። በዚህ መሠረት የዚህ ጥናት ትኩረት በሰብዓዊና ማኅበራዊ ሳይንስ የእውቀት ዘርፎች ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የሚከተለው የጥናት አቅጣጫ አይነታዊ የጥናት መንገድ (Qualitative research approach) ነው።

3.3.1፦ አይነታዊ የጥናት ዘዴ

በተለያዩ ጥናቶች ገለፃ መሰረት አንድ ጥናት አይነታዊ ወይም መጠናዊ አለያም የሁለቱን ቅልቅል መሠረት አድርጎ ሊካሄድ ይችላል (Creswell 2014)። ምርጫው የሚወሰነው ግን በሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ አይነትና ባህርይ እንዲሁም በተመራማሪው ምርጫ ላይ ተመስርቶ ነው (Jackson 1987)። ለምሳሌ የአንድን ማኅበረሰብ ባህላዊና ማኅበራዊ እሴቶችን በመመርመር የዚያን ማኅበረሰብ ማንነትና ምንነት ለመረዳት እንዲቻል ለሚደረግ ጥናትና ምርምር አይነታዊ የጥናት መንገድ መከተል ተመራጭ ነው።

ይህም የሚሆነው ማኅበረሰቡን በእሴቶቹ አማካይነት ለመረዳት የሚቻለው በዚያው በአካባቢው፣ በባህሉና በኑሮው ላይ ተመስርቶ ሲጠና በመሆኑ ነው። በዚህም የአይነታዊ የጥናት መንገድ ከመጠናዊ የጥናት ሥልት የበለጠ ተመራጭ ነው። በመሆኑም አይነታዊ የጥናት ሥልት በሰብአዊና ማኅበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች መሰረቱን ሊጥል ችሏል (Creswell 2014)። የተመራማሪዎቹ ዋና ዓላማም የተለያዩ ማኅበራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን ወይም የሰው ለሰው

ግንኙነቶችን በተለያየ መንገድና አቅጣጫ መርምሮ መግለጽ ነው። በሰዎች የእርስ በርስ ግንኙነቶች አማካይነት የሚታዩ የተለያዩ ዝርዝር ጉዳዮችን በተለያየ መንገድ መተንተንና መተርጎም ነው። አይነታዊ የጥናት መንገድ የሚከተሉ የዘርፉ ተመራማሪዎች ከአንድ ነጠላ ጉዳይ ላይ (Inductive Approach) ተነስተው ወደ አንድ ጥቅል ወደሆነ (Deductive Approach) ድምዳሜ ላይ መድረስ በጥናታቸው የሚከተሉት አቅጣጫ ነው (Miles & Huberman 1984)::

ከዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ደግሞ የጥናታቸው ትኩረት የሰዎች የእለት ተለት እንቅስቃሴዎችና ግንኙነቶች ናቸው። በዚህም የሁነቶቹን ትርጉምና የክዋኔዎቹን ሂደት ከባህሉ ባለቤቶች አንፃር መመርመር ይቻላል። የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት አይነታዊ የጥናት መንገድ መከተል ተገቢ የሚሆነውም በዚህ አይነት መንገድ ጥናት ለማካሄድ ወሳኝ በመሆኑ ነው (Marshal & Rosman 2011):: ይህም ስለሆነ አይነታዊ የጥናት ሥልት እንደ መጠናዊ የጥናት ሥልት በአንድ የተወሰነ ነገር ላይ ብቻ የታጠረ አይደለም። በቁጥር ወይም በልኬት አለያም በቤተ-ሙከራ ላይ የተመሰረተ አይደለም። ባንፃሩ አይነታዊ ጥናት በሰዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም መስተጋብር ላይ የተመሠረተ ነው። የአጠናን መንገዱም ከተለያዩ ነጠላ ጉዳዮች ላይ ተነስቶ በሂደት እየዳበረ፣ እየጎለበተና እየበለፀገ አንድ ማጠቃለያ ላይ የሚደርስ ሣይንስ ነው (Creswell 2014)።

ከላይ እንደተጠቀሰው ለዚህ አይነቱ የጥናት ሥልት ሥረ-መሠረቱ አውድ ወይም የመስክ ጥናት ነው። የመስክ ጥናት መሰረታዊ ጽንሰ-ሃሳብም መረጃዎቹ የሚሰበሰቡበትን ሁኔታ ወይም ድባብ (situation) ተገን አድርጎ ጥናቱን መተንተንና መተርጎም ነው። አይነታዊ ጥናት በመስክ ላይ ተመስርቶ በርካታ ውስብስብ ጉዳዮችን በብልሃት እየፈታ የሚጓዝ ነው። በመሆኑም በዚህ መንገድ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከተለያዩ ሌሎች ጉዳዮች ጋር እየተገናኙ፣ እየተጎራበቱና እየተዛመዱ ይተነተናሉ (Maxwell 2005; Merriam 1998)።

በአይነታዊ ጥናት ሁሉም ነገር ከባለቤቶቹ መንጭቶ እዚያው የሚቀዳ ነው። መረጃው ሲቀዳም ተመራማሪው በቦታው ተገኝቶ እዝነ ልቡናውን እና አእምሮውን አስተባብሮ በማየትና በመጠየቅ ነው (Lincoln & Guba 1985; Bauman 1983):: ከላይ እንደተገለፀው አይቶ ማስተዋል፣ አስተውሎ መገንዘብ እና ጠይቆ መረዳት የአይነታዊ ጥናት መለያ ምልክት ነው። የዚህ አይነቱ ባህርይ ደግሞ ከተመራማሪው ጋር በቀጥታ ይገናኛል። ምክንያቱም የአይነታዊ ጥናት ውጤት ትክክለኛነት የሚረጋገጠው በተመራማሪው መረጃ የመሰብሰብና

የመተንተን ብቃትና ችሎታ አማካይነት ነው። በዚህም በአይነታዊ ጥናት የተመራማሪው ድርሻ ከምንም በላይ ነው። በመሆኑም የጥናቱ ቁልፍ ሰው ተመራማሪው ነው (Jackson 1987; Goldstein 1964)።

ይህም ማለት የአይነታዊ የጥናት ውጤት የሚባለው ተመራማሪው የባህሉ ባለቤቶች ለእሴቶቻቸው በሚሰጡት ትርጉምና ፍች ላይ ተመስርቶ የሚያካሂደው ትንታኔ ነው። አይነታዊ ጥናት ሁልጊዜ በመላምት ወይም በንድፈ ሃሳብ ላይ ተመስርቶ ሊካሄድ አይችልም። ባንባሩ ከተመራማሪው ማኅበራዊ የሕይወት አስተውሎት የሚመነጭ ነው። ከተመራማሪው ልምድ፣ ትምህርትና ምርምር የሚፈልቅ ነው። በዚህም ተመራማሪው በርካታ ውስብስብ ጉዳዮችን መርምሮና ፈትሾ፣ በርካታ ጉዳዮችን አውጥቶና አውርዶ፣ የተለያዩ ትርጉሞችና ፍችዎች ሰጥቶ ወደ አንድ ማጠቃለያ ሊደርስበት የሚችል የጥናት ሂደት ነው (Miles & Huberman 1994; Merriam 1998)።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው አይነታዊ የጥናት መንገድ መከተል ውስብስብ ጉዳዮችን በሂደት መርምሮ ለመረዳት የሚያስችል ሥልት ነው። ምክንያቱም ተመራማሪው በርካታ ጉዳዮችን ቀስ በቀስ የማወቅና የመረዳት እድሉ ሰፊ ነው። እንዲሁም አይነታዊ የጥናት ሥልት በባህርይው አንድን ጉዳይ ደጋግሞ ወይም መላልሶ ለማየትና ለመጠየቅ እድል ይሰጣል።በዚህ መሰረት የጥናቱን ተአማኒነት ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመርመር ማረጋገጥ ይቻላል (Creswell 2014)። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት የሃይማኖት መቻቻል እሴቶችን መርምሮ ለመረዳት እንዲቻል አይነታዊ የጥናት ሥልት ተመርጧል። ይህንን ሥልት መሰረት በማድረግም ለዚህ ጥናት የሚያገለግሉ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል። ሂደቱ የተከናወነው ከዚህ በታች ተብራርተው በቀረቡት ዘዴዎች አማካይነት ነው።

በአይነታዊ የጥናት ሥልት መረጃ ለመሰብሰብ አምስት አይነት አማራጮች አሉ። እነዚህም "Narrative Research, Phenomenological Research, Grounded Theory, Ethnography, Case Studies." በማለት የዘርፉ ባለሙያዎች ይከፍሏቸዋል (Creswell 2014;14)። በዚህ መሠረት ከነዚህ አማራጮች መካከል የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ፣ መተንተኛና መተርጎሚያ ሥልቱ ኢትኖግራፊክ የምርምር ንድፍ (Ethnographic Research Design) ነው። ምክንያቱም ኢትኖግራፊክ የጥናት ዘዴ አንድን የተወሰነ ማኅበረሰብ ወይም ቡድን በዚያው በአካባቢውና በባህሉ ላይ ተመስርቶ በስፋትና በጥልቀት ለማጥናት የሚያስችል ዘዴ በመሆኑ ነው።

3.3.2፦ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Research Methods)

ከላይ እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡትና የተተነተኑት በኢትኖግራፊክ የመረጃ መሠብሰቢያና መተንተኛ መርህ አማካይነት ነው፡፡ ይህ መርህ የራሱ የሆኑ መገለጫዎችና ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሁም ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳሉት ጥናቶች ያሳያሉ (Hammersley & Atkinson 1991)፡፡ ለምሳሌ ከላይ እንደተገለፀው ኢትኖግራፊክ የጥናት ዘዴ አንድን የተወሰነ ማኅበረሰብ ወይም ቡድን በዚያው በአካባቢውና በባህሉ ላይ ተመስርቶ በስፋትና በጥልቀት ለማጥናት የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ጥናቱም የሚካሄደው በአንድ በተወሰነ ቦታ ረዥም ጊዜ በመቆየት ስለሆነ አንድን ጉዳይ በስፋትና በጥልቀት ለመመርመር እድል ይሰጣል፡፡ እንዲሁም በኢትኖግራፊክ የጥናት ዘዴ አጥኚው ወደፊት እና ወደኋላ በመንቀሳቀስ፣ ወደ ላይና ወደታች በመመላለስ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ ይበልጥ እንዲያውቅና እንዲረዳ ሰፊ እድል ያገኛል፡፡ በዚህም በሂደት ሃዳዲስ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ ማጎልበት፣ ማበልፀግና መተግበር ይችላል (Hammersley & Atkinson 1991)፡፡

ኢትግራፊክ የጥናት ዘዴ የአንድን ማኅበረሰብ ወይም ቡድን ማኅበራዊ ሕይወትና ተቋማቱን ለማጥናት የተሻለ አማራጭ በመሆኑ የዚያን ማኅበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማዱን ለማወቅ ያግዛል፡፡ በዚህም የማኅበረሰቡን ማንነት አመለካከት፣ አተያይ፣ እምነት፣ ፍልስፍናና የእርስ በርስ ግንኙነቱን ለመመርመር አመች ነው (Ben-Amos 1976)፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ማኅበረሰቡን በቅርበት ማጥናት ሲቻልና መረጃዎቹም ከዚያው ከማኅበረሰቡ አካባቢና የእለት ተለት ማኅበራዊ ሕይወትና የእንቅስቃሴ ምንጭ ሲቀዱ ነው፡፡ እንቅስቃሴዎቹ ከምንጫቸው የሚቀዱት ደግሞ በተለያዩ ዘዴዎች አማካይነት ነው፡፡ እነዚህም በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በቡድን ውይይት፣ በጽሑፍ፣ በድምፅና በምስል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት ነው፡፡ የኢትኖግራፊክ የጥናት ዘዴ ደካማ ጎን የሚገለፀውም ከነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች ጋር ተያይዞ ነው፡፡ እነዚህ ዘዴዎች ቀዳማይና ካልኣይ የመረጃ ምንጮች በመባልም ይታወቃሉ (Goldstein 1964; Jackson 1987)፡፡

በዚህ መሠረት የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮች የተቀዱት ጥናቱ ከተካሄደበት አካባቢና ማኅበረሰብ ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ ውስጥ ሁኖ፤ በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በጽሑፍ፣ በድምጽና በምስል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ምልከታና ቃለመጠይቅ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ሲሆኑ፤ የጽሑፍ፣ የድምፅና የምስል መረጃዎች ደግሞ ካልኣይ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡

3.3.2.1፦ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች

ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የሚባሉት የየእለት ማስታወሻዎች (diary)፤ እለታዊ ደብዳቤዎች፣ የፍርድ ቤት፣ የጦር ሜዳ፣ የግጭት አፈታትና የእርቅ ሥርአት ሪፖርቶች፣ የቴሌግራምና የፋክስ መልዕክቶችን...ወዘተ ጨምሮ፤ በምልከታና በቃለመጠይቅ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው፡፡ ቀጥታ ግንኙነታቸውም በአብዛኛው ከመስክ ሥራ ጋር ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የመረጃ ምንጮቹ በአብዛኛው በቀጥታ የባህሉ ባለቤቶች የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት በነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች እና ሌሎች ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች አማካይነት በወሎ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮችን የሃይማኖት መቻቻል እሴት ለመመርመር የሚያስችል መረጃ ለዚህ ጥናት ተሰብስቦና ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ከዚህ አንፃር መረጃዎቹ ከየት፣ እንዴትና ከነማን እንደተሰበሰቡና በምን አይነት ሁኔታ እንደተተነተኑ ከዚህ ቀጥሎ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

3.3.2.1.1፦ ምልከታ

ምልከታ በፎክሎር ጥናት ውስጥ አንድን ጉዳይ በቦታው ላይ በአካል ተገኝቶ ድርጊቱን ፊት ለፊት ማየት ወይም መመልከት ማለት ብቻ አይደለም፡፡ ባንፃሩ በፎክሎር ጥናት ምልከታ ማለት አንድን ጉዳይ (ድርጊት/ ክዋኔ/ ሁነት) በአካል ተገኝቶ በሁሉም የስሜት ሕዋሳት አማካይነት ተረድቶ መረጃ መሰብሰብ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ምልከታ አንድን ድርጊት ማየት ብቻ ሳይሆን "መቅመስ፣ መዳሰስ፣ መስማትና ማሽተትን ሁሉ ይጨምራል" በማለት የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልፁታል (Goldstein 1964: 77)፡፡

በጎልድስቴይን ገለፃ መሠረት ምልከታ አንድን ድርጊት ከመመልከት ባለፈ የድርጊቱ ባለቤቶች የሚሰማቸውን ስሜት ተመራማሪው ስሜቱን የመጋራት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በፎክሎር ጥናት በምልከታ መረጃ መሰብሰብ ማለት ተመራማሪው በማኅበረሰቡና በባህሉ ውስጥ ዘልቆና ጠልቆ የመግባት ጉዳይ ነው፡፡ የማኅበረሰቡን የእለት ተለት እንቅስቃሴ የማወቅና የራስ ለማድረግ የመሞከር ጣጣ ነው፡፡

በዚህም ተመራማሪው ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ አንፃር የሚያጠናውን ማኅበረሰብ የእለት ተለት እንቅስቃሴ በማኅበራዊና ባህላዊ አውዱ ውስጥ ከተለያየ አቅጣጫና ማዕዘን በአንክሮ ይከታተላል፤ ይጠይቃል፤ ጠይቆም ይረዳል፡፡ አንዱን ሁነት ከሌላው ሁነት ጋር እያወዳደረና እያነፃፀረ ይዘግባል፤ ይተነትናል፤ ይተረጉማል (Goldstein 1964; Hammersley & Atkinson 1991)፡፡ በዚህ መሰረት ምልከታ የራሱ የሆኑ መገለጫ ባህርያት አሉት፡፡ ከዚህም ሌላ የራሱ

የሆኑ ቅደመ ሁኔታዎችም አሉት። በዚህ መነሻ በምልከታ ዘዴ መረጃ መሰብሰብ የራሱ የሆነ ጠንካራ ጎኖች ያሉትን ያህል ውስንነቶችም አሉበት (Miles & Huberman 1994)።

ከምልከታ ዘዴ ጠንካራ ጎኖች መካከል አንዱ የሚሰበሰበው መረጃ በተፈጥሮ አውዱ ውስጥ በመሆኑ እንደወረደ የሚቀዳ ነው። በዚህም ተአማኒና የተረጋገጠ መረጃ ማግኘት ይቻላል። በርካታ ጉዳዮችንም በአንድ ጊዜ ማግኘትና መሰብሰብ ማስቻሉም ሁለተኛው ጠንካራ ጎኑ ተደርጎ ይጠቀሳል። ሦስተኛው ጠንካራ ጎኑ ደግሞ የባህሉ ባለቤቶች በቀያቸው በነፃነት የሚከውኑት ጉዳይ በመሆኑ በርካታ ያልተጠበቁ መረጃዎችን ለማግኘት አጋጣሚው ሰፊ ነው። በዚህም ከተለያዩ አቅጣጫዎች በአንድ ጊዜ የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት ያስችላል። ከዚህ በመነሳትም ስፋትና ጥልቀት ያለው ቃለመጠይቅ ለማካሄድ መንገድ ይከፍታል። በመሆኑም ከቃለ-መጠይቅ በፊት ምልከታ መቅደም እንዳለበት ይመከራል (Goldstein 1964; Hammersley & Atkinson 1991)።

በሌላ በኩል ምልከታ የሚጠይቃቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ጨምሮ፤ የጊዜ፣ የገንዘብና የተመራማሪውን ትዕግስት ይጠይቃል። የሚሰበሰቡት መረጃዎች አይነትና ብዛትም አሰልች የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ምልከታ በቦታና በጊዜ ሊወሰን ይችላል። በምልከታ መረጃ የመሰብሰብ ዘዴ ለተመራማሪው የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ ሁኔታዎችም ሊያጋጥሙ ይችላሉ (Creswell 2014)። ምልከታ ደረጃዎች አሉት። እነዚህም ፍፁም ተሳትፎ፣ ከፊል ተሳትፎና ፍፁም ተመልካች የሚሉትን ደረጃዎች ጨምሮ፣ ተሳትፎና ተሳትፎ አልባ ምልከታዎች የምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መገለጫዎች ናቸው። እነዚህ መገለጫዎች ሁሉም የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን አላቸው። ለአብነት በተሳትፎ ምልከታ ተመራማሪው የባህሉ ባለቤቶች አካል ተደርጎ ይቆጠራል። ይህም ማለት ተመራማሪው ለባህሉ ባለቤቶች ባዕድ አይደለም። በዚህም ተመራማሪው የሚፈልገውን መረጃ በአውዱ ውስጥ ተመልክቶም ሆነ ጠይቆ በነፃነት ሊያገኝ ይችላል፤ ይረዳልም (Jackson 1987)።

ባንፃሩ ሂደቱ በክዋኔ ላይ ከሆነ ግን ማስታወሻ ለመያዝም ሆነ ለመቅረጽ ሊቸገር ይችላል። በዚህም በርካታ ጉዳዮች ሊያመልጡት ይችላሉ። በሌላ በኩል ግን በተሳትፎ አልባ ምልከታ ተመራማሪው ማስታወሻ የመውሰድም ሆነ የመቅረጽ እድሉ (ክዋኔው ቀረፃ የሚፈቅድ ከሆነ) ሰፊ ነው። በዚህ መሠረት ተመራማሪው የውጭ ተመልካች ሁኖ የተለያዩ ሂደቶችን ማጤንና መረዳትም ይችላል። ነገር ግን አጥኚው በባህሉ ባለቤቶች ዘንድ እንደ ባዕድ ስለሚቆጠር የተለያዩ ተፅዕኖዎች ሊገጥሙት ይችላሉ። በዚህ መሠረት በምልከታ ዘዴ መረጃ በመሰብሰብ

ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ መሆን ወይም ሙሉ በሙሉ ታዛቢ መሆን ተገቢ አይደለም። በመሆኑም ሁለቱንም አማራጮች እንደየአስፈላጊነታቸው ተግባራዊ ማድረግ ይገባል (Hammersley & Atkinson 1991)።

በምልከታ ዘዴ መረጃ ለመሰብሰብ በአብዛኛው የተሳታፊ ተመልካች (as a participant than as an observer) እና በተቃራኒው በአብዛኛው ተመልካች ሁኖ (as an observer than as a participant) በመሳተፍ መረጃ መሰብሰብ ይቻላል። ሂደቱም መጀመሪያ በውጭ ተሳትፎ ተመልካች (participant-outsider) ዓይን ጉዳዩን መመርመር ያስፈልጋል። ቀስ በቀስ ግን የውስጥ ተሳታፊ ተመልካች (participant-insider) በመሆን አንዱን በሌለው ማካካስ እንደሚችል ጥናቶች ያሳያሉ (Creswell 2014: 191)።

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በምልከታ መረጃ የመሰብሰብ ዘዴ ፍፁም ተሳታፊ (Complete participant) እና ፍፁም ተመልካች (Complete observer) በመሆን መረጃ መሰብሰብ አይቻልም። ይልቁንም ትክክለኛና አስተማማኝ መረጃ መሰብሰብ የሚቻለው ሁለቱንም ስልቶች "ሚዛናዊ" አድርጎ መገልገል ሲቻል ነው (Jackson 1987:65)። በዚህ ሂደት ግን የተመራማሪው የግል ችሎታና ብቃት ወሳኝ ነው። ከዚህ በላይ የተለያዩ የዘረፉ ባለሙያዎች የሰጧቸውን አስተያየቶች ግምት ውስጥ በማስገባት በምልከታ ዘዴ መረጃ መሰብሰብ ያሉትን ጠንካራና ደከማ ጎኖች ለመግለጽ ተሞክሯል። በዚህ መሰረት እነዚህ አካላት የሰጧቸውን አስተያየቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ወይም በማካተት ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎች በምልከታ ዘዴ ተሰብስበዋል። በዚህም በውሎ የእስልምናና ክርስትና እምነት ተከታዮችን የእለት ተለት እንቅስቃሴ ወይም የእርስ በርስ ግንኙነት በምዕራፍ አምስትና ስድስት ውስጥ ተተንትኖ ቀርቧል። ምልከታው የተካሄደው በዋናነት በአምልኮና መዝናኛ ቦታዎች፣ በገበያና በሥራ ቦታዎች፣ እንዲሁም በተለያዩ የማኅበራዊ ሕይወት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ነው።

ለዚህ ደግሞ በወሎ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች እርስ በርስ ያላቸውን የሕይወት ግንኙነት ወይም መስተጋብር መርምሮ ለመረዳት እንዲቻል አጥኚው በተለያዩ ጊዚያት በቦታው ላይ በመገኘት የማኅበረሰቦቹን (የነዋሪዎቹን) አጠቃላይ የእለት ተለት የማኅበራዊ ሕይወት እንቅስቃሴዎች በመመልከትና በማጤን መረጃዎችን በአውዳቸው ውስጥ ሰብስቧል። ለምሳሌ የክርስትናው ትውፊቶች በሚገኙባቸው ቦታዎች በመገኘት የሙስሊሞቹንና የክርስቲያኖቹን የእርስ በርስ ግንኙነት በተሳትፎ ምልከታ አማካይነት መረጃ ሰብስቧል። ለአብነት ምዕራፍ አምስት ውስጥ የወረ-ካሎ ተክለሃይማኖትን ሁነት ይመልከቱ።

በእስልምናው በኩል ለዱዓ በተመሰረቱ ቦታዎች ላይ በመገኘት፤ ቦታዎቹ የሙስሊሞቹም የክርስቲያኖቹም የጋራ እሴቶች መሆናቸውን ተረድቷል። በሙስሊሞቹም ሆነ በክርስቲያኖቹ ዘንድ የበረከት ምንጭ እና የመልካም ነገር ተምሳሌት ተደርገው እንደሚቆጠሩ ተገንዝቧል። በተለያዩ የገበያ ቦታዎች ላይ በመገኘት ባየውና በሰማው ነገር ሁሉ በእጅጉ ተደምሟል። በተለያዩ የመዝናኛ ቦታዎች ላይ በመገኘት የወሎየዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት አስተውሎ መረጃ ሰብስቧል።

እንዲሁም በወሎየዎች የሀዘን፣ የደስታ፣ የሥራና በተለያዩ ክብረ በዓላት ላይ በመገኘት የሁለቱ ሃይማኖት እምነት ተከታዮች ያላቸውን የእርስ በርስ ግንኙነት በቅርበት ተመልክቶ መርምሯል። እንዲሁም የሁለቱን እምነት ተከታዮች የጋራ የሆኑ ገናን እሴቶች፣ ምግባሮችና የሰው ለሰው ግንኙነቶች ለአምስት ወራት ያህል በ2004፣ በ2006 እና በ2007 ዓ.ም. እዚያ በቆየባቸው ጊዜያት ውስጥ ተመልክቶ ሁነቶቹን ለመረዳት ጥረት አድርጓል። ከዚህም ሌላ የሁለቱን እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች ሀገረሰባዊ እምነቶች፣ አምልኮዎች፣ ልማዶች፣ ማኅበራዊ ተቋማትና ሌሎች ጉዳዮችንም በቅርበት ተመልክቶና ተረድቶ የጋራ የሆኑትን እሴቶች ለይቷል። ከለየም በኋላ በምልከታ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር በማሰባጠር ተንትኖና ተርጉሞ ፋይዳቸውን ገልጿል።

ከዚህም ሌላ ምልከታው የተከናወነው እንደየእሴቶቹ ባህርይ በአብዛኛው አጥኝው ተሳታፊ ተመልካች ሆኖ ነው። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ፎክሎራዊ ሁነቶች የአጥኚውን ተሳትፎ የሚገድቡ አልነበሩም። አጥኚው አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምንበት ወይም ጉዳዮቹ ተሳትፎ የማይጠይቁ ሆነው ሲገኙ ብቻ ከተሳትፎ ውጭ በመሆን መረጃዎች ተሰብስበዋል። በዚህ መሰረት አጥኚው መረጃዎቹን በምልከታ ዘዴ የሰበሰበው ተሳታፊና ከተሳትፎ ውጭ በመሆን ነው። አጥኚው ይህንን ሁሉ ሲያደርግ ግን የምርምሩ ሣይንስ የሚጠይቀውን የሥነ-ምግባር መርህና የራሱን እውቀት፣ ክህሎትና ብቃት፣ በተቻለ መጠን በተግባር ሥራ ላይ ለማዋል በመሞከር ነው።

ይህም ሆኖ አጥኚው በምልከታ ዘዴ ብቻ ሙሉ በሙሉ በቂና አስተማማኝ የሆነ መረጃ መሰብሰብ ይቻላል የሚል እምነት አልነበረውም። ወደ ሥራ ሲገባም በተግባር ያረጋገጠው ይህንኑ እውነታ ነው። በመሆኑም ለዚህ ጥናት በምልከታ ዘዴ ብቻ መረጃ አልተሰበሰበም። በዚህ መሰረት በምልከታ ዘዴ ሊሰበሰቡ ያልቻሉ መረጃዎች ወይም ሰፊና ጥልቅ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተሰብስበዋል።

3.3.2.1.2፦ ቃለመጠይቅ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በራሱ ባህርይና አውድ ላይ ተመስርቶ በምልከታ ዘዴ መረጃ መሰብሰብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ምልከታ የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳሉት ከላይ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት በምልከታ ዘዴ ብቻ የተሟላ መረጃ መሰብሰብ አልተቻለም፡፡ ስለዚህ ሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ከነዚህ ዘዴዎች መካከል አንዱ ቃለመጠይቅ ነው፡፡ ቃለመጠይቅ ተመራማሪው ለመረጃ አቀባዮቹ ጥያቄ በማቅረብ መረጃ የሰበሰበበት ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ በአብዛኛው በቃለ-መጠይቅ ዘዴ መረጃ የተሰበሰበው ከምልከታ በኋላ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አጥኚው በመጀመሪያ ሁኔታዎችን ሁሉ በምልከታ ካስተዋለና ከመረመረ በኋላ በእሴቶቹ ባለቤቶች እንዲብራሩለት የሚፈልጋቸውን ነጥቦች ለይቶ ለመረዳትና ለመጠየቅ እንዲያመቸው ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ለጉዳዮቹ በቂ እውቀትና ግንዛቤ ኖሮት መጠየቅ እንዲችል ነው፡፡

በቃለመጠይቅ መረጃ የመሰብሰብ ዘዴ የራሱ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ ከጠንካራ ጎኖቹ መካከል አንዱ ቃለመጠይቅ በምልከታ ሊገኙ የማይችሉ መረጃዎችን ማስገኘት ማስቻሉ ነው (Creswell 2014; Hammersley & Atkinson 1991)፡፡ ለምሳሌ ከጊዜ አንፃር ወደ ኋላ በመመለስ ታሪካዊ ሁነቶች ተለይተው የሚታወቁት በቃለመጠይቅ አማካኝነት በሚሰበሰቡ መረጃዎች ነው፡፡ ከቦታ አንፃርም በአካል መገኘት ሳያስፈልግ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ አንድን ድርጊት ጠይቆ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም በአይን መታየት፣ በእጅ መዳሰስ የማይችሉ ረቂቅ ጉዳዮች፣ ትዕምርታዊና ተምሳሌታዊ ሁነቶች፣ ትርጓሜያቸው ተተንትኖ ሊብራራ የሚችለው በባህሉ ባለቤቶች አማካኝነት በቃለመጠይቅ ነው (Jackson 1987)፡፡ ከዚህም ሌላ የባህሉን ባለቤቶች እውቀትና ክህሎት እንዲሁም ልምድ ጠይቆ መረዳት የሚቻለው በዚሁ የቃለ-መጠይቅ ዘዴ አማካይነት ነው፡፡ እንዲሁም በአደባባይ በግልጽ የማይከወኑና የማይነገሩ ሁነቶች በቃለመጠይቅ የሚገለጹበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ምክንያቱም ቃለመጠይቅ ለግለሰቦች አንፃራዊ ነጻነት፣ ደህንነትና ምቾት የሚሰጥ፣ ባጥኚው አማካኝነት የመረጃ አቀባዩን ስሜት፣ ፍላጎትና ተነሳሽነት የሚቀሰቅስ ዘዴ ነው (Miles & Huberman 1994)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ቃለመጠይቅ ለተመራማሪው በርካታ ነፃነቶችን ይሰጣል፡፡ በዚህም ተመራማሪው የሚፈልገውን መረጃ ዘዴው የሚጠይቀውን ብልሃት ተጠቅሞ ሊሰበስብ ይችላል፡፡

አንድን ርዕሰ ጉዳይ በስፋትና በጥልቀት ለማወቅ የተለያዩ ሥልቶችን ተጠቅሞ ጠይቆ ይረዳል። የመረጃ አሰባሰቡን ሂደት የመቆጣጠርና የመምራት እድሉም ሰፊ ነው። ከመረጃ አቀባዮቹ አንፃርም በአደባባይ ሀሳባቸውን ለመግለጽ የሚፈሩ ወይም የማይፈልጉ ግለሰቦች ቢኖሩ በቃለመጠይቅ አማካይነት የዚህ ዓይነቱን ችግር መቅረፍ ይቻላል (Goldstein 1964)።

በሌላ በኩል ግን በቃለ-መጠይቅ ዘዴ ሊሸፈኑ የማይችሉ ክፍተቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ከክፍተቶቹ አንዱ በቃለ-መጠይቅ ዘዴ መረጃ ከተፈጥሯዊ አውዱ ውጭ እንዲሰበሰብ መፍቀዱ ነው። በዚህም መረጃ አቀባዩም ሆነ ተመራማሪው መረጃዎቹን የሚረዱት ከራሳቸው ፍላጎትና ስሜት አንፃር ብቻ የሚሆንበት አጋጣሚ ይፈጠራል። በመሆኑም ሌሎች እውነተኛ መረጃዎች ተደብቀው በምትኩ የተሳሳቱ መረጃዎች ሊሰበሰቡ ይችላሉ። እንዲሁም ተመራማሪው በመረጃ አቀባዩ ላይ የራሱን ተጽዕኖ የሚያሳድርበት ሁኔታም ያጋጥማል (Creswell 2014)። ነገር ግን ቃለ መጠይቅ እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት የሚያስችሉ ዘዴዎች አሉት። ዘዴዎቹ ቅንብር (structured)፣ ያልተቀናበረ (unstructured)፣ በከፊል የተቀናበረ (semi-structured)፣ ዝግ (closed)፣ ክፍት (open-ended)፣ የአስገዳጅ ምርጫ (Yes/No) እና መሪ ጥያቄዎች (directive) በመባል ይታወቃሉ (Hammersley & Atkinson 1991)።
በዚህ መሰረት የቃለመጠይቅ ጠንካራም ሆነ ደካማ ጎን የሚመነጨው እነዚህን የአጠያየቅ ዘዴዎች በአግባቡ፣ በአስፈላጊው ቦታና ሁኔታ ተግባራዊ ባለማድረግ ነው። ለምሳሌ የዘርፉ ምሁራን እንደሚሉት የአስገዳጅ ምርጫና መሪ ጥያቄዎች ለፎክሎር ጥናት ተመራጭ አይደሉም። ምክንያቱም የአስገዳጅ ምርጫ ጥያቄ መረጃ አቀባዩ ከቀረቡለት ሁለት አማራጮች ውስጥ አንዱን እንዲመርጥ የማስገደጃ ስልት በመሆኑ ነው። መሪ ጥያቄ ደግሞ ተመራማሪው የራሱን ፍላጎት ጠይቆ ያው ጥያቄ በመረጃ አቀባዩ በኩል እንዲረጋገጥለት የሚያደርግበት ሂደት ነው (ፈቃደ 1991 ዓ.ም.)። በመሆኑም በነዚህ ዘዴዎች አማካይነት (ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ አግባብነት የላቸውም ባይባልም) የሚሰበሰብ የፎክሎር መረጃ አስተማማኝነቱ አጠራጣሪ ነው (Jackson 1987; Miles & Huberman 1984)።

በሌላ በኩል ያልተቀናበረ፣ የተቀናበረና በከፊል የተቀናበረ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ሲባል ደግሞ ግንኙነቱ ጥያቄዎቹን ቀድሞ ካለማዘጋጀት፣ ከማዘጋጀትና በከፊል ከማዘጋጀት ጋር የተገናኘ አስተሳሰብ ነው። ሐመርስሌይና አትኪንሰን እንደሚሉት በጥናትና ምርምር ሂደት ውስጥ ይቅርና የእለት ተለት ንግግርም ቢሆን የተቀናበረ ወይም ፈር የያዘ የተግባቦት ሂደት አለው።

ባንፃሩ የተቀናበረና በከፊል የተቀናበረ ሲባልም የተመራማሪውን ቅድመ ዝግጅት የሚመለከት ጉዳይ እንጂ መሰረታዊ ሃሳቡ፤ "የተቀናበረ ቃለ-መጠይቅ ማለት ተመራማሪው የሚጠይቀውን ርዕሰ ጉዳይ በሚገባ ተረድቶ፣ አቀናብሮና አደራጅቶ በቃለመጠይቁ ቦታ ላይ መገኘት ማለት ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ተመራማሪው ዝርዝር ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መረጃ አቀባዩን አንድ በአንድ ወይም ቃል በቃል እየጠየቀ መልስ ያገኛል ማለት አይደለም" የሚል ነው (1991; 113)፡፡

በጥቅሉ ፍቃደ እንደሚሉት የተቀናበረም ሆነ በከፊል የተቀናበረ የቃለ-መጠይቅ ዘዴ ማለት ተመራማሪው "በባዶ ራስ" ወደ መስክ መውጣት የሌለበት መሆኑን የሚያመለክት ጽንሰ-ሃሳብ ነው (1991፣ ዓ.ም 124) ፡፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ ጽንሰ-ሃሳቦች መነሻ በማድረግ በዚህ ጥናት ተግባራዊ የተደረጉት የቃለ-መጠይቅ ሥልቶች ክፍት እና ዝግ የጥያቄ ዘዴዎች ናቸው፡፡ በነዚህ ዘዴዎች አማካይነት ለዚህ ጥናት ግብአት የሚሆኑ የተለያዩ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

በዚህ ጥናት ክፍት የጥያቄ ሥልቶችን መጠቀም ያስፈለገው መረጃ አቀባዮች ብዙ ሳይጨነቁ፣ በነፃነትና በመዝናናት መረጃ እንዲሰጡ ታስቦ ነው፡፡ በዚህም መረጃ አቀባዮቹ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች የራሳቸውንና የሌሎች ሰዎችን አስተያየትና ስሜት እያጣቀሱ መልስ ይሰጣሉ (እንደላይኛው፤ 125)፡፡ እንዲሁም በዚህ ዘዴ ያለፈውን ያስታውሳሉ፤ ያሁኑን ያገናዝባሉ፤ መጭውን ሁኔታ ይተነብያሉ፡፡ ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን በማገናኘትና በማነፃፀርም ጉዳዮችን እየተነተኑ ያብራራሉ፡፡

በዚህ መሠረት ለዚህ ጥናት መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች በክፍት ቃለ-መጠይቅ ዘዴ አማካይነት መልስ አግኝተዋል፡፡ ለምሳሌ የሁለቱን እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች እርስ በርስ አስተሳሰረው፣ አስተባብረው፣ አግባብተውና አስማምተው በሰላምና በፍቅር ለዘመናት ያቆዩዋቸው የጋራ እሴቶች ምን ምን እንደሆኑና እንዴት እንደሚያገለግሉ በእሴቶቹ ባለቤቶች ማብራሪያ የተሰጠባቸው የተለያዩ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር በማገናኘት መልስ የተሰጠባቸው በክፍት ቃለ-መጠይቅ ዘዴ አማካይነት ነው፡፡ እንዲሁም የእሴቶቹ ምንጮች ምን እንደሆኑና እንዴት እንደሚሰሩ፣ ፎክሎራዊ የሆኑት ጉዳዮች፣ ሃይማኖታዊ የሆኑት ትውፊቶች እና የሁለቱ ቅልቅል የወሎዬዎችን የጋራ ፍላጎት በማሟላት ለሃይማኖት መቻቻል እሴት እንዴት መሰረት ሊሆኑ እንደቻሉ ለመረዳት የሚያስችል መረጃ የተሰበሰበው በአብዛኛው በክፍት ቃለ-መጠይቅ ዘዴ

ነው፡፡ ለዚህም በምእራፍ አምስትና በምእራፍ ስድስት የተጠቀሱት አብዛኛዎቹ ምሳሌዎች በዚህ ዘዴ የተሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው፡፡

ምንም እንኳን በክፍት ጥያቄ ስልት መረጃ አቀባዩ መንገድ ሲስት ወይም ፊር ሲለቅ ወደ መንገዱ መልሶ ማስገባት የሚቻል ቢሆንም፤ ቁርጥ ያለ መልስ ለማግኘት ወይም ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮችን ይበልጥ ለማብራራትና ግልጽ ለማድረግ ሲባል በዚህ ጥናት ሂደት ወቅት ዝግ ጥያቄዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በዚህም ክክፍት ጥያቄዎች ጋር በማዛመድ አስፈላጊ በሆነበት ቦታና ጊዜ በማንሳት የመረጃውን ተአማኒነት ለማረጋገጥ ጥረት ተደረጓል፡፡ ቃለመጠይቆቹ የተካሄዱት ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ እሴቶቹ በሚገኙበት አውድ ውስጥ ነው፡፡ ይህም ማለት መረጃ አቀባዮቹ ባህሉን ጠንቅቀው ያወቃሉ ተብለው የሚገመቱና መረጃውን የሰጡት በዚያው በሚያውቁት አውድ ውስጥ ሆነው ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በቃለ-መጠይቅ ዘዴ ከአውድ ውጭ መረጃ መሰብሰብ የሚቻል ቢሆንም በዚህ ጥናት ግን ይሄ አልተደረገም፡፡ ይህም ሆኖ በቃለ-መጠይቅ በተሰበሰበ መረጃ ብቻ መገልገል ጥናቱን የተሟላ ሊያደርገው ስለማይችል ለዚህ ጥናት ከካልኣይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ በረጃዎችን መጠቀም አስፈላጊ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ካልኣይ የመረጃ ምንጮች ለዚህ ጥናት በግብዓትነት አገልግለዋል፡፡

3.3.2.2፦ ካልኣይ የመረጃ ምንጮች

ከዚህ በላይ እንደተብራራው በምልከታና በቃለመጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ የተመራማሪው የመስክ ሥራ ክህሎት ወሳኝ ነው፡፡ በአርካይቭ፣ በሙዚዬምና በቤተ-መጻሕፍት የመጠቀም ክሂል ደግሞ ከጽሑፍ፣ ከድምጽና፣ ከምስል ክምችት መረጃ ለመሰብሰብ ቁልፍ ጉዳይ ነው (Dorson 1986; Jones 1994)፡፡ በሌላ አባባል ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ቀጥታ ግንኙነታቸው ከመስክ ሥራ ጋር ሲሆን፤ የካልኣይ የመረጃ ምንጮች ቁርኝት ደግሞ ከአርካይብ፣ ከሙዚዬምና ከቤተ-መጻሕፍት ጋር ነው፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ለፎክሎር ጥናት ወሳኝ እንደሆኑ ሁሉ፣ ካልኣይ የመረጃ ምንጮችም ተመሳሳይ ሚና አላቸው፡፡ ለምሳሌ በካልኣይ የመረጃ ምንጮች አማካይነት ከግለሰብ እስከ አንድ ሀገር ህዝብ ያሉ ሁለንተናዊ ጉዳዮችን ማጥናት ይቻላል፡፡ የአንድን ማኅበረሰብ መስተጋብር፣ ሀዘንና ደስታ፣ ፍቅርና ጥላቻ፣ መውደቅና መነሳት ወዘተ መረዳት ይቻላል፡፡ ማኅበረሰቡ ከአካባቢው ጋር ያለውን ትስስር ጨምሮ፤ የታሪክ፣ የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ ሕይወት፣ የባህል፣ የሃይማኖት...ወዘተ

ሁኔታዎች ሁሉ በካልኣይ የመረጃ ምንጮች አማካኝነት ሊጠኑ ይችላሉ (Hammersley & Atkinson,1991)።

በካልኣይ የመረጃ ምንጮች ሊሰበሰቡ የሚችሉ ጉዳዮች የፎክሎር ይዘት ያላቸው ሆነው፤ የትኛውም ዓይነት የዕደ ጥበብ ውጤቶች (ቁሳዊ ባህል)፣ ልዩ ልዩ ድርጊቶችና ትውን ጥበባት (social folk custom & performing arts) እና ቃላዊ ጥበቦች (oral literature) ሁሉ ሊሆኑ ይችላሉ (Dorson 1972)። እነዚህ መረጃዎች ሊገኙ የሚችሉት ደግሞ ከበራሪ ጽሑፎች አንስቶ እስከ ጥናትና ምርምር ውጤቶች ሊሆኑ ይችላሉ። በቴፕ ከተቀረጹ ድምጾች እስከ ፊልምና ቪዲዮ መረጃዎች ይደርሳሉ። የሚገኙበት አካባቢና ቦታም ከግለሰብ መኖሪያ እስከ ቤተ-መዘክር፣ ከቤ-መጻሕፍት እስከ ቤተ-እምነት ያሉትን ሁሉ ያጠቃልላል (Hammersley & Atkinson 1991)።

ካልኣይ የመረጃ ምንጮች የራሳቸው የሆነ ጠንካራ ጎን እንዳላቸው ሁሉ ደካማ ጎንም አላቸው። ጠንካራ ጎናቸው በአንጻራዊነት የመረጃ ምንጮቹን በቀላሉ ከማግኘት አንስቶ የተረጋገጠ መረጃ እስከ ማግኘት ሊደርስ ይችላል። እንዲሁም በምልከታና በቃለመጠይቅ ሊገኙ የማይችሉ መረጃዎች በካልኣይ የመረጃ ምንጮች የሚገኙበት አጋጣሚም ሰፊ ነው። ደካማ ጎናቸውም በዚሁ አንጻር የሚታይ ነው። ለምሳሌ መረጃዎቹን በቀላሉ ወይም ሙሉ ለሙሉ ማግኘት ካለመቻል ጀምሮ የያዙት መረጃ ትክክለኛነትና አስተማማኝነት አጠራጣሪ መሆን ለአብነት የሚጠቀስ ክፍተት ነው (Creswell 2014)።

ነገር ግን ይህንን ክፍተት በተለያዩ መንገዶች መድፈን ይቻላል። መሠረታዊው ጉዳይ ካልኣይ የመረጃ ምንጮችን ለመጠቀም የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎች መኖራቸውን አስቀድሞ መረዳት ነው። ከዚህ ውስጥ ‹‹መረጃዎቹ እንዴት ተፃፉ? ማን ፃፋቸው? ለምን ዓላማ ተፃፉ? ለማን ተፃፉ? በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ተፃፉ? ምልአት ቀርነታቸው ምንድን ነው? ስለትክክለኛነታቸው ምን አይነት ማረጋገጫ አላቸው?...ወዘተ›› የሚሉትን ጥያቄዎች መርምሮ መመለስ መቻል መሠረታዊው ጉዳይ ነው (Hammersley & Atkinson 1991; 143)።

የካልኣይ መረጃ ምንጮች ምንነት፣ አስፈላጊነትና ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ ከዚህ በላይ ለመግለጽ ተሞክሯል። የተገለጹትን መሠረታዊ ነጥቦች ታሳቢ በማድረግ ለዚህ ጥናት ከቀደማይ የመረጃ ምንጮች በተጨማሪ ካልኣይ የመረጃ ምንጮችም በዋናነት ተግባራዊ ተደርገዋል። በተለይ ከቤተ-መፃሕፍት የተሰባሰቡ ካልኣይ የመረጃ ምንጮች ለዚህ ጥናት ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ከተሰባሰቡ መረጃዎች የሚተናነሱ አይደሉም። ምክንያቱም

የተለያዩ የጥናትና ምርምር ውጤቶች፣ የንድፈ-ሃሳብና የጽንሰ-ሃሳብ መፃሕፍት፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች፤ ለዚህ ጥናት በግብዓትነት አገልግለዋል። ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም (IES) ቤተ-መፃሕፍትና ሰራተኞች የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ።

ከነዚህ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበው የተተነተኑት መረጃዎች የነዚህን ተጠኚ ማኅበረሰቦች ያለፈም ይሁን ያሁን ዘመን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ ይገልፃሉ። ምክንያቱም የነዚህ ማኅበረሰቦች ታሪካቸው፣ የፖለቲካ ጉዳያቸው፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሁኔታቸው፣ የባህላዊና የሃያማኖታዊ ትውፊታቸው፣ እውቀታቸው፣ ጥበባቸው፣ ፍልስፍናቸው...ወዘተ ተከትቦ የሚገኘው በነዚህ ካልኣይ የመረጃ ምንጮች ውስጥ ነው። ለምሳሌ በዚህ ጥናት በምእራፍ አራት ውስጥ የተጠቀሱት ሁነቶች የዚህ አባባል ማረጋገጫ አብነቶች ናቸው። ለበለጠ መረጃ ምዕራፍ አራትን ይመልከቱ።

ከዚህም ሌላ ማህበረሰቦቹ የሚጠኑት ከፎክሎር አንፃር በመሆኑ ካልኣይ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም ተገቢነት ያለው የምርምር ሂደት ነው። ምክንያቱም በፎክሎር ጥናት ያለፉ ልምዶችን መሰረት በማድረግ አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መመዘን ይቻላል። እንዲሁም መጪው ዘመንም ባለፈውና ባሁኑ ዘመን የፎክሎር እውቀትና ልምድ ላይ ተመስርቶ ይተነበያል፤ ይቀመራል። እነዚህ ሁሉ እሴቶች የሚገኙትና ተለይተው የሚታወቁት ደግሞ በቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ብቻ ሳይሆን በካልኣይ የመረጃ ምንጮችም ጭምር ነው። በመሆኑም በዚህ ጥናት ከካልኣይ የመረጃ ምንጮች መረጃ ተሰብስቦ በዚህ ጥናት ውስጥ መካተቱ ጥናቱን የተሟላና ተአማኒ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል።

ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት አካል የሆኑት የሁለቱ እምነት ተከታይ የማኅበረሰብ ክፍሎች የጋራ እሴቶችን ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎች ከካልኣይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበው በጥናቱ ውስጥ ተተንትነው ቀርበዋል። ለምሳሌ የሁለቱ አካላት ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ አካባቢያዊና ሌሎች ጉዳዮች አጠቃላይ ሁኔታ ምን እንደሚመስል በጥናቱ ውስጥ ተብራርተው ቀርበዋል። ባጠቃላይ ከዚህ በላይ እንደተብራራው ቀዳማይና ካልኣይ የመረጃ ምንጮች ምን ምን እንደሆኑና ለዚህ ጥናት ከነዚህ ምንጮች መረጃዎች እንዴት እንደተሰበሰቡ ዋና ዋና ነጥቦችን በመጥቀስ ባጭሩ ተመልክቷል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የመረጃ አቀባዮቹ የአመራረጥ መርሆች፣ መረጃዎቹ የተሰበሰቡባቸው መሣሪያዎችና መቼቶች እንዲሁም አንፃሮች ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል።

3.4. የመረጃ አቀባዮች ምርጫ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች፣ መቼቶች እና አንፃሮች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር መረጃ በመሰብሰብ ሂደት መረጃ አቀባዮች እነማን ናቸው? በምን መስፈርት ወይም በምን መመዘኛ ተመረጡ? መረጃዎቹስ በየትኛው አውድ ውስጥ ተሰበሰቡ? የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹና የመረጃ መሰብሰቢያው አንፃርስ? የሚሉት ነጥቦች ባጭሩ ተብራርተው ተጠቃለው ቀርበዋል።

3.4.1፦ የመረጃ አቀባዮች ምርጫ

በዚህ ጥናት ውስጥ የመረጃ አቀባዮች ምርጫ የተከናወነውና ሚናቸው ተለይቶ ወደ ሥራ የተገባው የተለያዩ መመዘኛዎችን ወይም መስፍርቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ለምሳሌ በፎክሎር ጥናት የመረጃ አቀባዮች ምርጫ የናሙና (sampling) ጉዳይ አይደለም። ባንፃሩ በፎክሎር ጥናት የመረጃ አቀባዮች ምርጫ ዓላማ ተኮር (purposive sampling) ወይም የምርጫ (selection) ጉዳይ ነው። ምርጫው የሚከናወነው ግን የተለያዩ መሠረታዊ ወይም ሣይንሳዊ የሆኑ ጉዳዮችን (መስፈርቶችን) መነሻ በማድረግ ነው። ለአብነት በፎክሎር ጥናት መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ፤ መረጃ አቀባዮቹ ለባህሉ ያላቸው ቅርበት፣ ልምድ፣ እውቀት፣ ክህሎት፣ ፍቃደኝነት፣ ተነሳሽነት፣ ወይም ፍላጎት (desirability)፣ በአስፈላጊው ቦታና ጊዜ መገኘት...ወዘተ የመምረጫ መስፈርቶች ናቸው (Goldstein 1964; Jackson 1987; Hammersley & Atkinson 1991)። እንዲሁም ከመረጃ አቀባዮቹ ሚና አንፃር የሚሰበሰበው መረጃ የተወሰኑ አካላት አስተያየትና ስሜት (dominant views) ብቻ እንዳይሆን፤ ባንፃሩ የሚጠናውን ማኅበረሰብ ድምፅ (diversity of voices) የሚወክሉ መሆናቸው ትኩረት የሚሰጠው የመረጃ አቀባዮች የመምረጫ መስፈርት ነው። በዚህ መሰረት እነዚህን ነጥቦች ታሳቢ በማድረግ ለዚህ ጥናት በሁለት ምድብ የተከፈሉ መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል።

እነዚህም አጠቃለይ እና ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው። እነዚህ መረጃ አቀባዮች ሲመረጡ ካላይ እንደተገለፀው የተለያዩ አካላትን አስተያየቶችና አመለካከቶች (diversity of voices) ያካተቱ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጓል። በዚህ መሰረት ቁጥራቸው እንደሁኔታው የሚለያይ ሆኖ የዚህ ጥናት መረጃ አቀባዮች አጠቃላይና ቁልፍ የሚለውን መስፈርት ጨምሮ፤ ከዖታ አንፃር፦ ሴት-ወንድ፤ ከእድሜ አንፃር፦ ወጣት፣ ጎልማሳና አዛውንት፤ ከሃይማኖት አንፃር፦ ክርስቲያን ሙስሊም (ቄስ/ ሼህ)፤ ከአካባቢ አንፃር፦ የከተማ የገጠር፤ ከሙያ

አንፃር፦ የባህል ባለሙያ፣ መምህር፣ ወታደር፣ ፖሊስ፣ አርሶ አደር፣ ነጋዴ፣ ተማሪ፣ ጡረታ፤ ከኃላፊነት አንፃር፦ የዞን የባህል መምሪያና የወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች፣ የቤተክርስቲያንና የመስጊድ ተጠሪዎች በዚህ ጥናት ውስጥ ተካተዋል።

ይህንን ስብጥር መሰረት ያደረጉት የዚህ ጥናት መረጃ አቃባዮች በቁጥር 41 ሲሆኑ፤ 18ቱ አጠቃላይና 23ቱ ደግሞ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው። ለበለጠ መረጃ አባሪ አንድን ይመልከቱ። ከፆታ አንፃርም አስራ አንዱ ሴቶች ሲሆኑ ሰላሳዎቹ ደግሞ ወንዶች ናቸው። የወንዶቹ ቁጥር ከሴቶቹ የበለጠው ከጥናቱ ባህርይ አንፃር ፆታን መሰረት አድርጎ የሚሰበሰብ መረጃ የግዴታ ስላልሆነ ብቻ ነው። አስፈላጊ ለሆኑት መረጃዎችም በጥናቱ ከተካተቱት ሴቶች በቂ መረጃ መሰብሰብ ተችሏል። ከሃይማኖት ስብጥር አንፃርም 16ቱ ሙስሊሞች ሲሆኑ፤ 25ቱ ክርስቲያኖች ናቸው።

ከአጠቃላይ መረጃ አቀባዮች መረጃ የተሰበሰበው በተለያዩ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች ውስጥ ርዕሰ ጉዳዩን በማንሳት አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ ነው። በዚህ ሂደት በተፈጠረ ግንኙነትም ከነዚህ አካላት ከአንድ ጊዜ በላይ መረጃ የመሰብሰብ አጋጣሚ ተፈጥሮ፤ ከብዙዎቹ ከአንድ ጊዜ በላይ መረጃ ተሰብስቧል። ከነዚህ መረጃ አቀባዮች የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ደግሞ በቁልፍ መረጃ አቀባዮችና በካልኣይ የመረጃ ምንጮች አማካይነት ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል።

ነገር ግን ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት በዋናነት በቁልፍ መረጃ አቀባዮች አማካይነት ነው። እነዚህ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች የተመረጡት ደግሞ የተለያዩ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ነው። ከነዚህ መስፈርቶች መካከል አንዱ የቁልፍ መረጃ አቀባዮች የአመራረጥ ሂደት አንዱና ዋነኛው ነው። በዚህ መሰረት እነዚህ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች የተመረጡት በዓላማ ተኮር (purposive sampling) የምርጫ ዘዴ ወይም ሥልት መሰረት ነው። ይህም ማለት እነዚህ አካላት የተመረጡት አጥኚው በዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ላይ መረጃ ለመስጠት ማን ከማን እንደሚሻል ወይም አንዱ ከሌላው በምን እንደሚሻል ለመለየት የሚያስችሉ ዘደዎችን ተጠቅሞ ምርጫ አካሂዷል።


ከተጠቀመባቸው ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ከአካባቢው የማኅበረሰብ ክፍሎች መካከል የአካባቢው ነዋሪዎች ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን እንዲጠቁሙት ማድረግ ነው። ይህም የጓዳዊ ጥቆማ ዘዴ የሚባለው ነው። ሁለተኛው ዘዴ ደግሞ እነዚህ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ራሳቸው ሌሎችን እንዲጠቁሙት የማድረግ ሥልት ተጠቅሟል። ይህም ሰው በሰው የጥቆማ ዘዴ ሊባል

ይችላል፡፡ ከዚህ ሥልት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ዘዴ ደግሞ የአካባቢው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የሰጡት ጥቆማ ነው፡፡ እንዲሁም አጥኚው በራሱ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር በተደጋጋሚ የነበረው ግንኙነትና መግባባት ቁልፍ መረጃ አቀባይ ለመምረጥ አስችሎታል፡፡ በዚህ መሰረት ከነበሩት በርካታ አማራጮች ውስጥ ከላይ የተጠቀሱትን 23 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሊመርጥ ችሏል፡፡ የሚከተሉት ፎቶግራፎች ለዚህ አብነቶች ናቸው፡፡





ፎቶግራፍ አንድ፡- ቁልፍ የወንድ መረጃ አቀባዮች ናሙና፡፡



ፎቶግራፍ ሁለት፦ ቁልፍ የሴት መረጃ አቀባዮች ናሙና፡፡

ምንም እንኳን እነዚህ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች አብዛኛዎቹ ጥናቱ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ አብረው የዘለቁ ቢሆኑም፤ ሁሉም ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በእንድ ጊዜ የተመረጡ ናቸው፤ ማለት ግን አይደለም፡፡ ባንፃሩ ቀድመው የተመረጡት እንደተጠበቀው ሆነው ሳይገኙ ሲቀሩ ሌሎች በጥቆማ እየተተኩ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በጥቆማ ከተገኙት ይልቅ ባጋጣሚ የተሻሉ እየተገኙ፣ እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ ትውውቅና ቅርርብ እየተፈጠረ ሲሄድ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት ቁልፍ መረጃ አቀባይ ተብለው ከተመረጡት ግለሰቦች መካከል ሁለቱ ከሚሰጡት መረጃ አንፃር አጥኚውን ስላላረካው ግና ከመነሻው ግንኙነቱን አቋርጧል፡፡ ሌሎች ሦስቱ መረጃ አቀባዮች ደግሞ መጀመሪያ ፍቃደኛ ሆነው በኋላ መረጃ እንዲሰጡ ሲጠየቁ ሁለቱ ሃሳባቸውን እንደቀየሩ ተናግረው መረጃ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡ አንደኛው ግን፤ ነገ-ዛሬ፣ ሳምንት፣ ጧት፣ ከሰአት፣ ማታ በማለት የአጥኚውን ጊዜና ጉልበት ስላበከኑበት ሳይጠየቁ እንዲቀሩ አድርጓል፡፡

ባጠቃላይ በዚህ ጥናት ሂደት መረጃ የተሰበሰበው ሣይንሱ ወይም ሙያው የሚጠይቀውን የጥናትና ምርምር ሥነ-ምግባር መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ለዚህ ጥናት መረጃ ሰጭዎች የጥናቱን ዓላማ በግልፅ ሳይረዱ ወይም ለሌላ ዓላማ በማስመሰል መረጃ እንዲሰጡ አልተደረገም፡፡ እንዲሁም በገንዘብ በማግባባትና በማባበል ወይም በሌላ መንገድ በማታለል መረጃ አልተሰበሰበም፡፡ ወይም ተግባራዊ እንደማያደርገው ውስጡ እያወቀ ይሄ ጥናት ሲጠናቀቅ ቅጂውን እሰጣለሁ ብሎ ለማንም ቃል አልገባም፡፡ ባንፃሩ ለዚህ ጥናት መረጃ የተሰበሰበው ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የጥናቱን ዓላማና ፋይዳ በማስረዳትና በማሳመን ነው፡፡ ለግለሰቦችም ሆነ ለመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ሕጋዊ ሆኖ በመቅረብ ብቻ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ መረጃ ሰጭዎች በዚህ ጥናት ላይ ስማቸው ቢጠቀስና ፎቶግራፋቸው ቢወጣ ፍቃደኛ መሆን አለመሆናቸው በቅድሚያ ተጠይቆ ነው። መረጃ አቀባዮቹ ጥናቱን አቋርጠው ሲወጡም ሆነ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ መብታቸው መሆኑን በመረዳት ነው። በሌላ በኩል ከነዚህ መረጃ አቀባዮች መረጃ ሲሰበሰብ የተለያዩ የፎክሎር መቼቶች ታሳቢ ተደርገዋል።

3.4.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች

መረጃዎች እንደሚያሳዩት የፎክሎር ጥናት በሦስት የመስክ መቼቶች ውስጥ ሊካሄድ ይችላል። እነዚህም ተፈጥሯዊ፣ አርቲፊሻል እና ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች በመባል ይታወቃሉ (Goldstein 1964; ፈቃደ 1991፤ ዓ.ም.)። በዚህ መሰረት ይሄ ጥናት የተካሄደው ሙሉ በሙሉ በተፈጥሯዊ መቼት ውስጥ ነው። ይህም ማለት አሁን ያሉትም ሆነ ያለፉት የሁለቱ እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች የእርስ በርስ ግንኙነቶች ወይም ሁነቶች የተጠኑት በመገኛ አውዳቸው ውስጥ ነው። በዚህ መቼት አማካይነት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው መረጃዎች ከካልኣይና ከቀዳማ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበው ተተንትነዋል። እንዲሁም መረጃዎቹ የተሰበሰቡበት አንፃር ተግባዊ የተደረገው ከዚህ ቀጥሎ በተብራራው መሠረት ነው።

3.4.3፦ የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃር

የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃር ከተጠኚዎቹ የማኅበረሰብ ክፍሎች እና ከአጥኚዎቹ አካላት ጋር የሚገናኝ ጽንሰ-ሃሳብ ነው። በዚህ ጽንሰ-ሃሳብ መሰረት አጥኚው ክፍል የተጠኚዎቹ የማኅበረሰብ ክፍሎች አካል ከሆነ፤ ተጠኚዎቹን ጨምሮ ውስጣዊ (emic/ insider) አንፃር ተብለው ይጠራሉ። ከዚህ በተቃራኒ ያለው ሁኔታ ደግሞ ውጫዊ (etic/ out-sider) አንፃር የሚል መጠሪያ አላቸው(Jackson 1987)። በዚህ መሰረት ለዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡበት አንፃር በአብዛኛው ውስጣዊ (emic/ insider) አንፃር ነው። ምክንያቱም ውስጣዊ አንፃር ለፎክሎር ጥናት በርካታ ጠንካራ ጎኖች ስላሉት ነው። ለምሳሌ ተመራማሪው የልባቸውን ወይም ትክክለኛውን መረጃ ሊነግሩት የሚችሉ መረጃ አቀባዮች እንደልብ ሊያገኝ ይችላል። በፎክሎር ጥናት ቁልፍ ጉዳይ የሆነው የቋንቋ ችግርም አይገጥመውም። በማኅበረሰቡ ውስጥ ያደገና የኖረ በመሆኑም የባህሉ አካል ስለሆነ ከባህሉ አንፃር የሚፈቀዱና የሚከለከሉ ጉዳዮችን ጠንቅቆ ሊያውቅ ይችላል (Dundes 1962) ።

በመሆኑም የባህሉን ባለቤቶች በቀላሉ አያስቀይምም። በዚህ መሰረት እነሱን ሳያስቀይም መረጃዎቹን እንዴት ማግኘት እንደሚችል ሥልት ይቀይሳል። ከዚህም ሌላ እንደወቅቱና አካባቢው ሁኔታ በእሱና በመረጃ አቀባዮቹ መካከል ብዙም የመጠራጠር ስሜት ላይኖር ይችላል። ስለሆነም ተመራማሪው ሳይፈራና ሳይሸማቀቅ እንደልቡ መንቀሳቀስ ስለሚችል የተለያዩ መረጃዎችን በቀላሉ ሊሰበስብ ይችላል (Goldstein 1964)። ለምሳሌ ቀደም ሲል ባጋጠሙ ችግሮች ንዑስ ርዕስ ውስጥ እንደተገለፀው፤ በአሁኑ ወቅት ከሃይማኖት ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተገናኘ አሁን ካለው የመጠራጠር ስሜት አንፃር፤ የዚህ ጥናት አቅራቢ የአካባቢው ተወላጅ ባይሆን ኖሮ፤ ለዚህ ጥናት መረጃ የማግኘት ጉዳይ ከዚህ የባሰ አስቸጋሪ ሁኔታ ያጋጥም እንደነበር የዚህ ጥናት አቅራቢ ይገምታል።

ባንፃሩ ውስጣዊ አንፃር የራሱ የሆኑ ውስንነቶችም አሉበት። ለምሳሌ ለባህሉ እንግዳ የሆነ ተመራማሪ በአንክሮ የሚከታተላቸውን ጉዳዮች የባህሉ ባለቤት የሆነው ተመራማሪ ትኩረት ላይሰጣቸው ይችላል። በዚህ ምክንያት በርካታ ጠቃሚ መረጃዎችን ሊስት ይችላል። ከዚህም ሌላ "የባህሉ ባለቤት ነኝ" ብሎ ስለሚገምት በይሉኝታ ምክንያት ለምን እና እንዴት ብሎ ጠይቆ የማይረዳበት አጋጣሚም ብዙ ሊሆን ስለሚችል የሚያውቃቸው የሚመስሉት፤ ነገር ግን እሱ ሊረዳቸው የማይችል ጉዳዮችን ትርጉምና ፍች ላይረዳ ይችላል (ፈቃደ ፣ 1991 ዓ.ም)።

ከመረጃ ሰጭዎቹ ወይም ከሚጠኑት የማኅበረሰብ ክፍሎች አንፃር ደግሞ አለታዊ የሆኑ ነገሮችን ወደጎን በመግፋት አወንታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሊያተኩሩ ይችላሉ። ወይም ለራሳቸው የሚሰጡት ግምትና ቦታ ሌሎች ስለነሱ ከሚሰጡት ግምትና ቦታ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ይህ ማለት ግን ሌሎች ስለነሱ የሚሰጡት ግምትና ቦታ ሁልጊዜ ትክክል ነው ማለት አይደለም። ስለሆነም ባንድ የጥናትና ምርምር ሂደት ወቅት እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት እንዳስፈላጊነቱ ሁለቱንም አንፃሮች ተጠቅሞ ጉዳዮቹን መመርመር የሚያስፈልግበት አጋጣሚ ይኖራል። በተለይ ተመራማሪው የባህሉ አካል ከሆነ የውጭ ተመልካች መሆን ባይችልም እንኳን ለመሆን በመሞከር መረጃ በመሰብሰብ ጥናቱን የተሟላና ተአማኒ ማድረግ ይችላል (Hammersley & Atkinson 1991)።

በዚህ መሰረት አነዚህን ነጥቦች ታሳቢ በማድረግ የዚህ ጥናት አቅራቢ በተቻለ መጠን ገለልተኛ ሆኖ ጥናቱን ከወገንተኝነት የፀዳ ለማድረግ ጥረት አድረጓል። ለምሳሌ የዚህ ጥናት ምሰሶዎች (pillars) ሊባሉ የሚችሉ ርዕሰ ጉዳዮች በቁጥር ስድስት ናቸው። እነዚህም ጥናቱ የሚካሄድበት

አካባቢ፣ በዚህ አካባቢ የሚገኙት የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች፣ የነዚህ ሃይማኖቶች እምነት ተከታዮች ወይም ወሎዬዎች እና ፎክሎራዊ የሆኑት ጉዳዮች ናቸው። ስለሆነም አጥኚው ራሱን ገለልተኛ መሆን አለመሆኑን የሚለካው ከነዚህ ርዕሰ-ጉዳዮች አንፃር ነው። በዚህ መነሻ አጥኚው የአካባቢው ተወላጅ በመሆኑ በአካባቢው የሌለ ወይም በመረጃ ላይ ያልተመሰረተ ትንታኔ አላደረገም። ባንፃሩ የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ በመረጃ ላይ ተመስርቶ ከአወንታዊና አሉታዊ ገጽታዎቹ አንፃር መርምሯል።

ከሃይማኖት አንፃር ደግሞ ክርስቲያን በመሆኑ ለሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የክርስትናውንና የክርስቲያኖቹን ትውፊቶች ፋይዳ አስበልጦ የእስልምናውንና የሙስሊሞቹን እሴቶች ላሳነሰም። ሁለቱንም በተሰበሰበው መረጃና የጥናቱ ሣይንስ ቢሚፈቅደው መርህ መሰረት ለመመርመር ጥረት አድርጓል። እንዲሁም የፎክሎር ተመራማሪ በመሆኑ ለፎክሎራዊ እሴቶቹ የማይገባቸውን ቦታ አልሰጠም። ለዚህም ፀበልና ዱዓን አንስቶ (ሁለቱም የፎክሎር ዘረፎች ቢሆኑም ቅሉ) ዛር፣ ወዳጃ፣ ጥንቆላና አስማትን አልዘለላቸውም። ምንም እንኳ አንድ ተመራማሪ መቶ በመቶ ከወገንተኝነት ነፃ ሆኖ ጥናትና ምርምር ሊያካሂድ ይችላል ባይባልም፤ ሣይንሱ የሚያዘውን መርህ ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሁኔታው ከወገንተኝነት "የፀዳ" (neutral) ጥናትና ምርምር ማካሄድ ይችላል። ስለዚህ የዚህ ጥናት አቅራቢ በዚህ ጥናት ውስጥ ያለው ቦታ (positionality/ reflexivity/ identity) በተቻለ መጠን ከወገንተኝነት የራቀ ነው።

3.4.4፦ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

በፎክሎር ጥናት በተለያዩ መሣሪያዎች መረጃ መሰብሰብ ይቻላል። የመሣሪያዎቹ አይነትም ሆነ አገልግሎት እንደሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ አይነትና ባህርይ፣ እንደ ጥናቱ አውድና ክዋኔ ሊለያይ ይችላል። በዋናነት ግን የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች፤ ማስታወሻ ደብተር፣ የድምጽና የምስል መቅረጫ መሣሪያዎች ናቸው። እነዚህ መሳሪያዎች የየራሳቸው የሆነ አወንታዊና አሉታዊ ገጽታዎችም አሏቸው። እንዲሁም እነዚህ መሣሪያዎች የየራሳቸው የሆነ የአጠቃቀም ሥነ-ምግባር፣ እውቀትና ክህሎት የሚጠይቁ የፎክሎር ጥናት ቁልፍ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ናቸው (Dorson 1972; Goldstein 1964; Jackson 1987)። ለምሳሌ ማስታወሻ ደብተር በምልከታም ሆነ በቃለመጠይቅ ወይም ከሳልኣይ የመረጃ ምንጮች መረጃ ለመሰብሰብ ሁለገብ ጠቀሜታ ያለው መሣሪያ ነው። በቃለመጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ ደግሞ መቅረፀ-ድምጽ የመጀመሪያውን ቦታ ይይዛል። የአንድን ድርጊት ክዋኔ

ወይም ሁነት ከነሥጋና ነፍሱ ወይም ከነመቼቱ ቀርፆ ለማስቀረት የድምፅና ምስል መቅረጫ መሣሪያ (ቪዲዮ-ካሜራ) የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የሚጠይቁት የአጠቃቀም ሥነ-ምግባር፣ እውቀትና ክህሎት በቅደም ተከተላቸው የዚያኑ ያህል የተወሳሰበ ነው፡፡ አወንታዊና አሉታዊ ጎናቸውም በዚሁ አንፃር የሚታይ ነው (Hammersley & Atkinson 1991)፡፡

በዚህ መሠረት የዚህ ጥናት የመረጃ መሠብሰቢያ መሣሪያዎች ማስታወሻ ደብተርና የድምፅ መቅረጫ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በተለይ በምልከታ ወቅት የተወሰደ ማስታወሻና በቃለመጠይቅ የተቀረፀ የድምጽ ግብአት ለዚህ ጥናት ወሳኝ የመረጃ ምንጮች ሆነው አገልግለዋል፡፡ ባጠቃላይ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዜደዎች ከኢትኖግራፊክ የጥናት ሥልት አኳያ አንድን ጉዳይ መልሶ መላልሶ ከመመልከትና ከመጠየቅ በዘለለ፤ የአንዱን ክፍተት በሌላው ዘዴ መድፈን ስለሚያስችሉ ለዚህ ጥናት ተገቢ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ዘዴዎች በበኩላቸው የመረጃዎቹን ተክክለኛለት "በትሪያንጉሌሽን" መርህ ማረጋገጥ ያስችላሉ፡፡ በዚህም ጥናቱን ተአማኒ ያደርጋሉ፡፡

3.5፡- የ"ትሪያንጉሌሽን" መርህ

በአንድ የጥናትና ምርምር ሥራ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችም ሆኑ የመተንተኛ ሥልቶች አግባብነት በቀጥታ ከመረጃዎቹ ትክክለኛነት ወይም ተአማኒነት ጋር ይገናኛል፡፡ ይህንንም በተለያዩ ዘዴዎች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከነዚህ ዘዴዎች መካከል አንዱ የትሪያንጉሌሽን ሥልት ነው፡፡ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት የትሪያነጉሌሽን ሥልት "የአንድን ርዕሰ ጉዳይ ትክክለኛነት ከተለያዩ አካላት በተሰበሰበ መረጃ አማካይነት ማረጋገጥ ማለት ነው "(Hammersley & Atkinson 1991: 198; Creswell 2014: 211)፡፡ ይህም ማለት በምልከታ ዘዴ የተሰበሰበን መረጃ፤ በቃለ-መጠይቅ ዘዴ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ በቃለ-መጠይቅ ዘዴ የተሰበሰቡ መረጃዎች በምልከታ ዘዴ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር እየተነፃፀሩ ይፈተሻሉ፡፡ እንዲሁም የሁለቱ ውጤት ከካልኣይ የመረጃ ምንጮች ጋር እየተገናዘቡ ይመረመራሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ለተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ የተለያዩ መረጃ አቀባዮችን መጠቀም፣ አንድን ጉዳይ ደጋግሞ በመመልከትና በመጠየቅ የርዕሰ ጉዳዩን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

በዚህ መሰረት ይህ ጥናት የመረጃዎቹን ተአማኒነት ለማረጋገጥ የትሪያነጉሌሽን መርህን ተግባራዊ አድረጓል፡፡ ምክንያቱም ቢያንስ፣ ቢያንስ በምልከታ ዘዴ የሰበሰባቸውን መረጃዎች

በቃለ-መጠይቅ ወቅት ለማረጋገጥ ጥረት አድርጓል። በቃለ-መጠይቅ ዘዴ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ደግሞ የተለያዩ መረጃ አቀባዩችን በመጠየቅና ለተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ የርዕሰ ጉዳዩን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል። እንዲሁም በምልከታና በቃለ-መጠይቅ ዘዴ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ክለሳ ድርሳናትን ጨምሮ ከካልኣይ መረጃ ምንጮች ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር በማነፃፀር መርምሯል። ስለዚህ የቀደምት ጥናቶች ክለሳ የተካሄደው፣ በምልከታም ሆነ በቃለ-መጠይቅ ዘዴ መረጃ የተሰበሰበው፣ ካልኣይ የመረጃ ምንጮች እንዲካተቱ የተደረገው በትሪያንጉሌሽን መርህ የመረጃዎቹን ትክክለኛነትና ተአማኒነት ለማረጋገጥ ታስቦ ነው።

መረጃዎቹ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የመረጃ ምንጮችና በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ትክክለናነታቸውም ከላይ በተጠቀሰው የተሪያንጉሌሽን መርህ ከተፈተሼ በኋላ የሚቀጥለው የሥራ ሂደት ደግሞ መረጃዎቹን የማደራጀት፣ የመተንተን፣ የመተርጎምና የመግለጽ ጉዳይ ነበር። በመሆኑም ይህ መረጃ የማደራጀትና ከትንተና ጋር የተገኛኘ ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ ቀጥሎ ባጭሩ ተብራርቶ ቀርቧል። የመረጃ ትንተና በፎክሎር በትርጎማ (interpretation) ወይም በገለፃ (description) ሥልት አለያም ሁለቱን በማቀላቀል ሊካሄድ ይችላል። የሚወስነው በርዕሰ ጉዳዩ ሁኔታና በአጥኚው ምረጫ ነው። በዚህ መሰረት ሦስቱም ሥልቶች እንዳስፈላጊነቱ በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ተደርገዋል።

3.6፦ የጥናቱ የትንተና ሥልት

በአንድ የጥናትና ምርምር የሥራ ሂደት ተዛማጅ ጥናቶች ተከልሰው የጥናት ክፍተት የሚለየው፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተመርጠው መረጃ የሚሰበሰበውና የመተንተኛ ሥልቶች ተቀይሰው መረጃዎች የሚተነተኑት አንድ ዓላማ ለማሳካት ነው። ይኸውም ጥናቱ ሊመልሰው የሚፈልገውን ጥያቄ ወይም ሊፈታው ያቀደውን ችግር አለያም የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ በተግባር ፈትሾ አንድ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ነው (Goldstein 1964)። በዚህ መሠረት በፎክሎር ጥናት መረጃ መሰብሰብ አንድ የጥናት አካል ሁኖ፤ መሠረታዊው ጉዳይ ግን ከመስክ የተሰበሰበን መረጃ መልሶ ከመንገር ያለፈ ተግባር ማከናወን ሲቻል ነው።ይህ ተግባር ከመስክ የተሰበሰበውን መረጃ በማደራጀት ከሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ጋር አያይዞ፣ አዛምዶና አጎራብቶ የመተንተንና የመተርጎም የሥራ ክፍል ነው (Dundes 1980; Bauman 1986; Dorson 1986; Hammersley & Atkinson 1991)። በዚህ መነሻ አለን ዳንደስ እንደሚሉት ትንተና ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮችን መሠረት አድርጎ ሊከናወን ይችላል። እነዚህም

"ፎክሎሩ የተገለፀበት ሥልት (texture)፣ የፎክሎሩ አይነት (text) እና ፎክሎሩ የተከናወነበት አውድ (context) ናቸው" (Dundes,1980,22)። ፊቃደ በበኩላቸው የፎክሎር ትንተናን የሚገልጹት በሚከተለው ሁኔታ ነው።

> መተንተን ማለት...የየዘውጉን የተለያዩ መረጃዎች አጥንቶ፣ በመሀከላቸው ያሉትን ገናን አስተሳሳሪ ወይም አለያይ ነጥቦች እያነሱ በመወያየት ወዳንድ፣ በመረጃው የሚደገፍ ማጠቃለያ ማምራት ማለት ነው። ይህ ሲፍታታ (1ኛ) የየዘውጉን ቅንጣቶች ዓበይት የይዘትና የቅርጽ ባህርያት አጥንቶ መለየትና በባህርያቱ ላይ ተመስርቶ ማጠቃለል ማለት ነው። (2ኛ) በዘውጎቹ ውስጥ በሙሉ የተከሰቱ የጋራ ቅርጽና ይዘት-ነክ ገናን ባህርያት (ሞዠፊሎች) ቢኖሩ እነሱን ለይቶ ለማጠቃለል የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ ማለት ነው (2004 ዓ.ም.፤ 3)

በዳንደስ ገለፃ መሠረት የፎክሎር ትንተና ማለት ፎክሎሩ የተገለፀበትን የቋንቋ ጥበብ ወይም ሥልት አለያም ቅላጼ መሠረት ማድረግ ይኖርበታል። እንዲሁም የፎክሎሩን ዘርፍ ወይም አይነት ለይቶ መረዳትና የት እና መቼ ወይም በምን ሁኔታ ውስጥ እንደተከወነ ለይቶ ማወቅ የትንተናው ሂደት የሚጠይቀው ቅድመ ሁኔታ ነው። በፊቃደ አስተያየት ደግሞ በባህሉ የፎክሎሩን ፍች በመለየትና የተገለፀበትን መንገድ በመመርመር ትንተና ሊካሄድ ይችላል። ከላይ እንደተገለጸው የሁለቱን ምሁራን አስተያየት መሠረት በማድረግ የትኛውም ከመስክ የተሰበሰበ መረጃ በዘርፉ፣ በቅርጹ፣ በይዘቱ፣ በሞብጡ፣ በፋይዳው ወይም በጥቅሙ ከዚያም አልፎ በጊዜ ቅደም_ተከተል ተለይቶና ተደራጅቶ ሊተነተን ይችላል። ነገር ግን ቤን-አምፅ እንደሚሉት ዋናው ጉዳይ መረጃው የሚደራጅበትም ሆነ የሚተነተንበት መንገድ የባህሉ ባለቤቶች በሚሰጡት ፍች እና መረጃዎቹ ከተሰበሰቡበት ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ ውስጥ የመነጨ መሆኑ ነው። ወይም አደረጃጀቱም ሆነ የትንተና ሥልቱ በባለቤቶቹ ድምጽ (voice) ላይ መመስረቱ ነው (Ben-Amos 1975; 1976; 1993)።

በቤናሞፅ አስተሳሰብ የተመራማሪው ድምጽ መሰማት የሚጀምረው መረጃዎቹ በባለቤቶቹ ድምጽና በተሰበሰቡበት አውድ መሠረት ከተደራጁ በኋላ ነው። ከዚህ በኋላ በባለቤቶቹ ፍች ላይ ተመስርቶ የተደራጀውን መረጃ የመተንተንና የመተርጎም ኃላፊነት የተመራማሪው ሥራ ነው (Ben-Amos 1976)። በዚህ መሠረት ለዚህ ጥናት በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ሙሉ በሙሉ ዕንደወረዱ ወደ ወረቀት እንዲገለበጡ ተደርጓል። ከዚያም በይዘታቸው ወይም በርዕሰ ጉዳቸው ከተደራጁ በኋላ እንዳስፈላጊነቱ ከሌሎች ጉዳዮች ጋር እየተሰናኘ ተብራርተዋል፤ ተተንትነዋል።

ይህም የተደረገው "አጥኚው መረጃዎቹን ማደራጀት፣ መተንተንና መተርጎም የሚጀምረው መረጃ መሰብሰብ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው!" የሚለውን መርህ መሰረት አድርጎ ነው። ይህም ሲባል ተመራማሪው በመስክ ቆይታው እያንዳንዱን ድርጊት መጠየቅና መረዳት

የሚኖርበት ‹‹ምን ተደረገ ወይም ምን ተባለ በማለት ሳይሆን፤ እንዴት ተደረገ ወይም እንዴት ተባለ›› ብሎ መጠየቅ ይኖርበታል (Hammersley & Atkinson 1991:15)። ይህም የትንተናው አንዱ አካል ነው። እንዲሁም ተመራማሪው መረጃዎቹን ሲሰበስብ በአውዱ ውስጥ ያሉ አጠቃላይ ሁኔታዎችን በአንክሮ ይከታተላል። አንዱን ከሌላው ያወዳድራል፤ ያነፃጽራል። አንድነታቸውንና ልዩነታቸውንም ይለያል። ጭብጥና ትርጉማቸውን ይረዳል። ቅርጽና ይዘታቸውን፣ ፋይዳና ዘርፋቸውን ይለያል (Dorson 1986; Bauman 1986, Dundes 1980)። በዚህ መሠረት የዚህ ጥናት ትንተና የተከናወነው ከመስክ ጀምሮ የመረጃ አቀባዮቹንና የአጥኚውን ፍች መሠረት በማድረግ ነው። ይህም ማለት በጥናቱ ንድፈ ሃሳብ እንደተገለፀው መረጃዎቹ የተተነተኑት አውድን መሰረት ባደረገ የአውዳዊ ትንተና (contextual analysis) ሥልት መሠረት ነው። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የቀረቡት መረጃዎች ሁሉ የተብራሩትና የተተነተኑት ቀደም ሲል እንደተብራራው በይዘታቸው፣ ወይም በርዕሰ ጉዳያቸው ተደራጅተው ነው። ሪቻርድ ቦውማን እንደሚሉት የፎክሎር ትንተና መሠረቱ ‹‹ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ›› ነው (1986:363)። በቦውማን ገለፃ መሠረት ባህላዊ አውድ የማኅበሩን ወይም የቡድኑን የጋራ እሴቶች፣ እንዲሁም በእሴቶቹና በእሴቶቹ ባለቤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ይመለከታል። በእሴቶቹ የፍች ሥርዓቶችና ትዕምርታዊ (ተምሳሌታዊ) የግንኙነት መርሆዎች ላይ የሚያተኩር ጉዳይ ነው። ማኅበራዊ አውድ ደግሞ በማኅበሩ መዋቅር እና ግንኙነት ላይ የተመሰረተ አስተሳሰብ ነው። አስተሳሰቡ ማኅበራዊ፣ ግለሰባዊና ተቋማዊ አውዶችን በውስጡ ያካትታል።

ይኸ ጥናት በዚህ መርህ ላይ ተመስርቶ በወሎ የሁለቱን እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች የአኗኗር ዘይቤ ወይም የአኗኗር ስርዓቶች፣ ባህል-ወግና ልማዶች፣ ደንብና ሥርአቶች፣ ምግባሮች፣ እምነቶች፣ የሰው ለሰው ግንኙነቶችና ሌሎች ጉዳዮች በወሎ ለሃይማኖት መቻቻል እሴት ያላቸውን ፋይዳ በምዕራፍ አምስትና በምዕራፍ ስድስት መርምሮ ገልጿል። እንዲሁም የሁለቱን እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች በጋራ አስተሳስረው፣ አግባብተውና አስማምተው ለዘመናት ያቆዩዋቸው እሴቶች ምን ምን እንደሆኑና እንዴት እንደሚሰሩ በነዚሁ ምዕራፎች ውስጥ የተለያዩ አብነቶችን በመጥቀስ አብራርቶ አቅርቧል። ከጥቅማቸው ወይም ከአገልግሎታቸው አንፃርም እሴቶቹ ለሁለቱ እምነት ተከታዮች እንዴት የእርስ በርስ ማያያዣ ክር እና መገናኛ ድልድይ በመሆን እንደሚያገለግሉ ተብራርተዋል።

ምዕራፍ አራት

4፡- የሃይማኖት መቻቻል እሴት ሥረ-መሠረት በኢትዮጵያ

በምዕራፍ ሦስት ውስጥ እንደተብራራው ይህ ጥናት የተመራውና መረጃዎቹም የተተነተኑት በዓውዳዊ ንድፈ-ሃሳብ መርህ አማካይነት ነው፡፡ ዓውድ በዚህ ጥናት ውስጥ የወሎዬዎች የጋራ እሴቶች የተፈጠሩበት፣ ተፈጥረው የሚኖሩበት፣ የሚከወኑበትና አገልግሎት የሚሰጡበት ቦታና ጊዜ ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የምዕራፍ አራት ዋና ዓላማ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ይህ ጥናት በተካሄደበት ቦታና ጊዜ ውስጥ ከወሎዬዎች አጠቃላይ፤ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር የተገናኙ በአብዛኛው ፎክሎራዊ የሆኑ እሴቶችን በመመርመር ለምዕራፍ አምስትና ለምዕራፍ ስድስት መሰረት መጣል ነው፡፡

እነዚህ ፎክሎራዊ የጋራ እሴቶች አጠቃላዩ የወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር ወይም የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም አብሮነት ምን አይነት ገጽታ እንደነበረው ገልጠው የሚያሳዩ የማኅበራዊና ባህላዊ ዓውድ (Socio-Cultural Framework) ማእቀፎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር የተሳሰሩ ርእሰ ጉዳዮች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተመርምረዋል፡፡ በዚህም በተለያዩ ዘመናት የወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር ወይም አብሮነት ምን አይነት መልክ እንደነበረው ሊያሳዩ የሚችሉ የጋራ እሴቶች ለአብነት ቀርበዋል፡፡ እነዚህም ታሪካዊ ሁነቶች፣ የጋብቻ ትሥሥር እና የዘር ሐረግ ትውፊቶች፣ የትንቢት፣ የፊረስ እና የወፋ ውጊያ ትውፊቶች፣ የርስት፣ የመብት ጥያቄና የገበያ ተውፊቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ትውፊቶች የሚወክሉት ከላይ እንደተገለጸው የዚህን ጥናት አጠቃላይ ማኅበራዊና ባህላዊ ዓውድ ወይም የጥናቱን ሥረ-መሰረት ነው፡፡ በምእራፍ አምስትና ስድስት የቀረቡት ትውፊቶች ደግሞ መረጃዎቹ ተሰብስበው የተተነተኑበትን ዓውድ የሚገልጹ ርእሰ-ጉዳዮች ናቸው፡፡ ስለዚህ በምእራፍ አራት ውስጥ የተነሱት ነጥቦች፤ በምዕራፍ አምስትና ስድስት ውስጥ ተተንትነው ለቀረቡት ርእሰ-ጉዳዮች “ያው እዚያጋም እንዲህ ነበረ፤ አሁን ያለው ሁኔታ ደግሞ ይሽን ይመስላል!” ብሎ ለመግለጽ እንዲቻልና ለነዚህ ምእራፎች መነሻና መንደርደሪያ ነጥቦች እንዲሆኑ ታስቦ ነው፡፡ ስለዚህ በምዕራፍ አራት ውስጥ የተነሱት ርእሰ-ጉዳዮች በቀጥታ የሃይማኖት መቻቻል እሴትን የሚገልጹ ነጥቦች ሳይሆኑ፤ የወሎዬዎችን ታሪካዊ፣

ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን በመመርመር የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ሥረ-መሠረቱን ወይም ምንጩን በመጠቆም ፍንጭ የሚሰጡ የመንደርደሪያ ነጥቦች ናቸው፡፡ ባንዳሩ ምእራፍ አምስትና ምእራፍ ስድስት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ምን ማለት እንደሆ፤ እንዴትና በምን እንደሚገለጽ የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ገለፃና ትንታኔ የተካሄደባቸው ምእራፎች ናቸው፡፡

ጥናቶች እንደሚያስረዱት ከሰሜን የሚዲተራንያን ጫፍ እስከ ምስራቅ የቀይ ባሕር ጠረፍ እና የግዮን፣ የኤፌሶን፣ የጢግሪስና የኤፍራጥስ ወንዞች የሚፈሱባቸው አካባቢዎች ጥንታዊ ስልጣኔዎችና ሃይማኖቶች የፈለቁባቸው ቦታዎች ናቸው (Sergew 1972: 1)፡፡ በመሆኑም እነዚህ አካባቢዎች የታሪክ፣ የንግድ፣ የፖለቲካ፣ የባህል፣ የአምልኮ፣ የሥነ-ጥበብ፣ የዕደ ጥበብ፣ የኪነ-ጥበብ፣ የፍልስፍና፣ የሥነ-ጽሑፍ፣ የሥነ-ፎክሎርና የሌሎች እሴቶች ሁሉ ማዕከላት ናቸው (Assefa 1992: 1-3):: ከሃይማኖት አንፃርም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሦስቱ ጥንታዊና ታላላቅ ሃይማኖቶች (የአይሁድ፣ የክርስትናና የእስልምና) የተፈጠሩት በነዚህ አካባቢዎች ውስጥ ነው፡፡ በዚህም ሃይማኖቶቹ ከነዚህ አካባቢዎች ጋር ከፍተኛ የሆነ ታሪካዊ ትስስር አላቸው (Sergew 1970: 1-2)፡፡

በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ የነዚህ አካባቢዎች አካል እና የግዮን (ዓባይ) ምንጭ ወይም መነሻ በመሆኗ አንዷ ተጠቃሽ ሀገር ናት (Ephraim 208: 118)፡፡ በተለይ ኢትዮጵያ ከዐረቢያ፣ ከሕንድ፣ ከቀድሞዋ ፐርሻ-ከአሁኗ ኢራን፣ ከያኔዋ ሜሶፖታሚያ-ከዛሬዋ ኢራቅ፣ ከሶሪያ፣ ከእስራኤል፣ ከአርመን፣ ከግሪክ፣ ከሮማ፣ ከምሥር (ግብፅ) እና ከኑቢያ (ሱዳን) ጋር ለዘመናት የዘለቀ ግንኙነት ነበራት (Tessore 1989: 491; Trimingham 1965: XIII-XV; Assefa 1992: 4-51):: ኢትዮጵያ በዚህ ግንኙነቷ የተነሳ የነዚህን አካባቢዎች የተለያዩ እሴቶች በስፋት ተቀብላለች (V.C Samuel 1976፡ 60; Taddesse 1988: 121; Bojoviç 2010: 33)፡፡

ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው እነዚህ እሴች ደግሞ መንፈሳዊና ዓለማዊ እሴቶች ተብለው በሁለት ምድብ ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ዓለማዊ ከሆኑት እሴቶች መካከል ቁሳዊና ቁሳዊ ያልሆኑ እሴቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ለአብነት ኢትዮጵያ የሳባውያንን አስተዳደር፣ ቋንቋና ፊደል ከደቡብ ዐረቢያ፤ የግሪካውያንን ቋንቋ፣ ፊደል፣ ሥነ-ጽሑፍና ፍልስፍና ከግሪክ፤ የሰሎሞንን ጥበብና የአስተዳደር ዘይቤ ከእስራኤል...ወዘተ ወስዳለች (Sergew 1970: 2; Sumner 1988: 146-147)፡፡

ከመንፈሳዊው እሴት አንፃር ደግሞ ከውጭ የገቡና ኢትዮጵያ የራሷ ያደረገቻቸው እሴቶች ልማዳዊ አምልኮዎችና ተቋማዊ ሃይማኖቶች ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ከልማዳዊ አምልኮዎች አንፃር ጣያታትና አማልክት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ለዚህም እንደ አልሙቃህ፣ አስታር፣ አፍሮዳይት፣ ቤኑስ፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ዜውስ፣ ኤሬስ፣ ሔርሜስ፣ ኤራክለስ፣ ማሕረምና አርቄ (ገብገቦ) ለአብነት ይጠቀሳሉ (Sergew 1970:95; Assefa 1992: 5)፡፡

እንዲሁም ዛር፣ ቡዳ፣ ጂይኒ (አጋንንት)፣ አስማት፣ (መተት)፣ ጥንቆላ፣ ኮከብ ቆጠራ፣ መጽሐፍ ገላጭ፣ ኪታብ፣ ጠልሰም፣ ውቃቢ (ከራማ)፣ አውሊያ፣ ቆሌ (አድባር)፣...ወዘተ ከነዚህ አካባቢዎች ጋር የተሳሰሩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁነቶች ደግሞ አሁንም ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉና ሁሉም ኢትዮጵያውያን በሚባል ሁኔታ በተለያየ መንገድ ይተገብሯቸዋል፤ ከማኅበራዊ ሕይወታቸው ጋርም ያቆራኟቸዋል፡፡ (Leslaw 1949; 1994; Lewis 1984; Mallery 1998; Natving 1987; Messing 1958; Young 1975; Torrey 1970; Reminick 1976; Morton 1974; Aspen 2001)::

ተቋማዊ ሃይማኖቶቹን በተመለከተ ደግሞ በምእራፍ አንድ ውስጥ እንደተጠቀሰው፤ የአይሁድ፣ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች በተለያዩ ወቅቶችና አጋጣሚዎች ከእስራኤልና ከአረቢያ ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል (Ephraim 2008: 116-117):: እነዚህ ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ የተፈጠሩበትን አካባቢና ማኅበረሰብ ባህል ወግና ልማድ አብረው ይዘው ነው (Leslaw 1958:194-196):: በሌላ በኩል ሃይማኖቶቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡ በኋላ የአገሬውን ባህል-ወግና ልማድ የራሳቸው አድርገዋል (Benzing 2000: 15)፡፡ የአገሬው ነባር ባህል-ወግና ልማድ በበኩሉ ከውጭ የመጡትን አላስገባም ሳይል "ቤት ለእንቦሳ! ወይም ቤት ለእንግዳ!" ብሎ ተቀብሏቸዋል (Last 1982: 3; Alula 1994፡ 933-953; 2000: 15; Belay 1977፡ 18)፡፡ እነሱም "እንቦሳ እሰሩ!" በማለት በሰላም ገብተዋል፡፡ በዚህ መሠረት ተቋማዊ ሃይማኖቶቹ ከነባሩ ባህል-ወግና ልማድ ጋር ተቻችለው፣ ተስማምተው፣ ተግባብተውና ተጎራብተው ከዚያም ሲያልፍ ተጋብተው በሰላም አብረው ኑረዋል፤ አሁንም በሰላም አብረው እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ ይህ የመቻቻል ባህል ደግሞ የኢትዮጵያና ህዝቦቿ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ልዩ መገለጫ ሆኖ አሁን የምንገኝበት ዘመን ላይ ደርሷል::

የሃይማኖት መቻቻል እሴት በኢትዮጵያ ሊዳብርና ሊጎለብት የቻለው በተለያዩ ምክንያቶች አማካይነት ነው፡፡ አንደኛው ምክንያት የሃይማኖቶቹ አገባብና ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡ በኋላም

የተላበሱት ኢትዮጵያዊ የሆነ ባህርይ ወይም ትውፊት መኖሩ ነው። እንዲሁም ሦስቱ ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ከውጭ በተደረገ ግፊት ወይም በኃይል ሳይሆን፣ ከራስ በመነጨ የልብ መሻትና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው። በዚህም ሃይማኖቹ የራሳቸውን መገለጫ ወይም ሃይማኖታዊ አስተምህሮ (*መርሀ*) ሳይለቁ፤ ነባሩን ባህል-ወግና ልማድ ሙሉ በሙሉ ሳይፍቁ፤ ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር እራሳቸውን አስማምተውና ተስማምተው እዚህ ደርሰዋል (Schwab 1985: 92-95; Sergew 1970: 3-6)።

ነገር ግን የሦስቱ ሃይማኖቶች መገለጫ ይህ ቢሆንም ሃይማኖቶቹ እያንዳንዳቸው ወደ ኢትዮጵያ የገቡበት አጋጣሚ የየራሳቸው የሆነ ታሪክና ምክንያት አላቸው። ከነዚህ ምክንያቶች መካከል "እንግድነት" እና የንግድ ግንኙነት ለአብነት ይጠቀሳሉ:: ይህም ለሃይማኖት መቻቻል እሴት በኢትዮጵያ አንዱ ሥረ-መሠረት ወይም ምንጭ ነው (Hussein 2001; Trimingham 1965; Ephraim 2008)።

ንግድን መነሻ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል ከአይሁድ ሃይማኖት አንፃር ነጋዴው ታምሪን ይጠቀሳል። የሰሎሞን ሀገር ነጋዴ የሆነው ታምሪን ከኢትዮጵያ ንግሥት ከማክዳ ጋር ለመተዋወቅ የበቃው በንግድ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ነው (አክሊሉ 1963 ዓ.ም፤188)። በዚህ ሰበብ የሰሎሞንን ጥበብ ለማየት በተፈጠረ ፍላጎትና ሥሜት አማካይነት የአይሁድ ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ ችሏል። (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን 2000 ዓ.ም.፤ XI):: ይህንን ሃይማኖት መነሻ በማድረግም በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የፎክሎር ዘውጎች ተፈጥረዋል። የተለያዩ ባህሎች-ወግና ልማዶች፣ አፈታሪኮችና ሚቶች የዚህ አገላለጽ ማሳያዎች ናቸው።

ለአብነት የሰሎሞናዊ ሥርዎ-መንግሥት ተፀንሶ የተወለደው በዚህ ሃይማኖት ሰበብ ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤1994 ዓ.ም.)። የሰሎሞናዊ ሥርዎ-መንግሥት በበኩሉ በኢትዮጵያ ታሪክና በኢትዮጵያውያን ማኅበራዊ ሕይወት መስተጋብር ውስጥ የራሱን አሻራ ትቶ አልፏል። ከዚህ ሃይማኖት ጋር ትስስር ያላቸው የሌዋውያን ካህናት በበኩላቸው ጽላተ ሙሴን ጨምሮ የተለያዩ ሃይማኖታዊና ልማዳዊ ብሂሎችን (ትውፊቶችን) ወደ ኢትዮጵያ አስገብተዋል። በዚህም መንፈሳዊና ዓለማዊ እሴቶች በኢትዮጵያ ምድር ሊስፋፉ ችለዋል (Abba Gorgorios 1970: 391)::

የክርስትና ሃይማኖት አገባብ ደግሞ ከሕንደኬ ጃንደረባ (በጅር ወንድ) ጋር ይገናኛል። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ጃንደረባው ባኮስ በወንጌላዊው ፊልጶስ እጅ ተጠምቆ ክርስትናን የተቀበለና የክርስትናን ዜና ለሀገሩ ህዝቦች ያበሰረ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የክርስትና እምነት ሐዋርያ ነው:: ነገር ግን ክርስትና በኢትዮጵያ መሠረቱን የጣለውና የተስፋፋው በ330 ዓ.ም. አካባቢ በፍሬምናጦስ ወይም በኢትዮጵያዊ መጠሪያ ስሙ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን አማካይነት ነው (Sergew 1970: 97)።

እንዲሁም በዘመኑ የቤተ-መንግሥቱ ሰዎች የነበሩት ኢዛና እና ሳይዛና ወይም በስመ ክርስትናቸው አብረሃ ወ አጽብሃ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ነበራቸው (እንደላይኛው፤ 97-98)። ከፍሬምናጦስ በኋላም ዘጠኙ ቅዱሳን (ተሰዐቱ ቅዱሳን) በኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት መሠረቶች ናቸው። በነዚህ ቅዱሳን አማካይነት ክርስትና ተሰብኳል፤ ተስፋፍቷል። ገዳማትና አድባራትም ተመስርተዋል፤ ተስፋፍተዋል (Norheim,Ragnar & Norheim,Ingrid 1973: 32)። የነዚህ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ዋናው ምክንያት ደግሞ በሀገራቸው ያጡትን ሰላም፣ ፍትሕና ርትዕ በኢትዮጵያ ለማግኘት ሲሉ ነው። ምክንያታቸው ደግሞ ከአርዮስና ከኒቂያ ጉባዔ ጋር ይገናኛል (Sergew 1972፡ 118-119)

በሌላ በኩል የእስልምና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባበት አንዱ ምክንያት ከዚሁ ከሰላም፣ ከፍትሕና ርትዕ ጋር ተያይዞ ነው። ሰበበ ምክንያቱ ደግሞ ከአካባቢው ቆራይሽቶች ጋር የተያያዘ ነው። የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት ኢትዮጵያ ለነብዩ መሐመድም ሆነ ለአካባቢው ሩቅ ወይም አዲስ ሀገር አልነበረችም። ምክንያቱም ነብዩን ያሳደገቻቸው ኢትዮጵያዊቷ መጉዚታቸው ባራክ ኡም አይማን ነበረች። እንዲሁም በእስልምና ሃይማኖት ታሪክ የመጀመሪያው ሙአዚን (ፀሎት ጠሪ) ኢትዮጵያዊው ቢላል ነው (እንደላይኛው፤186)። በቢላልም ምክንያት በእስልምና ትውፊት "ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮጵያዊት የሆነን እንግዳ ወደ ቤቱ የሚያስገባ ማንም ቢኖር የአላህን በረከት ወደ ቤቱ ያስገባል!" የሚል በህል አለ (ኤፍሬም 2000 ዓ.ም፤11) ።

ከሰላም፣ ከፍትሕና ርትዕ ጋር በተያያዘ ደግሞ የመጀመሪያዎቹ የነብዩ ተከታዮች (ሰሓባዎች) በሀገራቸው መከራና እንግልት በደረሰባቸው ጊዜ ነብዩ "ወደ ኢትዮጵያ ብትሄዱ በእጁ ሥር ያሉትን ማንንም የማይበድል ንጉሥ ታገኛላችሁ። ያቺ ሀገር የጽድቅ ሀገር ናት። አላህም

በዚያ ለስቃያችሁ እረፍት ይሰጣችኋል!"[28] ብለው ወደ ኢትዮጵያ ልከዋቸዋል (Ephraim 2008: 116-117; Trimingham 1965: 44):: በዚህ መሠረት የነብዩ ሴት ልጅ ሩቅያ፣ ባለቤቷ አትማን፣ መጀመሪያ የነብዩ መጉዚት የነበረችውና በኋላ ላይ ደግሞ የልጃቸው የሩቅያ መጉዚት የሆነችው ኢትዮጵያዊቷ ባራክ ኡም አይማን፣ ከኢትዮጵያ መልስ ነብዩ ያገቧት ኡም ሐቢባህ እና ሌሎች በጠቅላላው 12 ወንዶች እና አምስት ሴቶች በድምሩ 17 ሰሓባዎች ኡት ማን ማንዙን በተባለ ግለሰብ አማካይነት እየተመሩ ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል:: ይህም ክስተት በእስልምና ሊቃውንት "የመጀመሪያው ሂጅራ" በመባል ይታወቃል (Sergew 1972: 182; Trimingham 1965: 44; Ephraim 2008: 117)::

ከዚህ በኋላም የመጀመሪያዎቹን ፈለግ በመከተል በነብዩ አጎት በጃፋር-ቢ- አቡ ጣሊብ መሪነት ለሁለተኛ ጊዜ ቁጥራቸው 107 የሚደርሱ ሰሓባዎች ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል:: እንግዶቹን የተቀበሉት ኢትዮጵያዊው ንጉሥም ጥላና ከለላ በመሆን ከአሳዳጆቻቸው በመታደግ አስተናግደዋቸዋል፤ እምነታቸውንም በነፃነት እንዲያመልኩ ፈቅደውላቸዋል:: በዚህም ነብዩ "[ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን][29] ካልነኳችሁ በስተቀር አትንኳቸው::"[30] የሚለውን መመሪያ በመስጠት ለኢትዮጵያና ህዝቦቿ ያላቸውን ጥልቅ ፍቅር ገልፀዋል (Sergew 1972: 190):: ከሃይማኖት ጉዳይ ጋር በተገናኘ የኢትዮጵያ ስም የሚነሳው በታሪክ መዛግብት ውስጥ ብቻ ሳይሆን፤ በመጽሐፍ ቅዱስና በቅዱስ ቁርአን ውስጥ ጭምር ነው:: በመሆኑም በሁለቱ ቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ የኢትዮጵያ ስም ተደጋግሞ ተጠቅሶ ይገኛል (Schwab 1985: 4; Belay1997: 1; Gorgorios 1970: 391)::

በኢትዮጵያ የክርስትናም ሆነ የእስልምና ሃይማኖቶች የየራሳቸው የሆነ የአገባብ ታሪክና ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ወይም ፍልስፍናና መርህ አላቸው:: ነገር ግን ሁለቱም የሚገናኙባቸው፣ የሚተሳሰሩባቸውና የሚጎራበቱባቸው በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው::

---

[28] "If you go to Abyssinia [Ethiopia] you will find a king under who none are persecuted. It is a land of righteousness where God will give relief from what you are suffering." (S.J. Trimingham 1965:44)

[29] ከዚህ ጥቅስ ጋር በተያያዘ ሦስት አከራካሪ ነጥቦች ይነሳሉ:: እነዚህም "ነብዩ መሐመድ የተናገሩት 'Al-Habesh' ወይም 'Habesha' ብለው ነው፤" የሚለው ነጥብ አንደኛው ጉዳይ ነው:: ሁለተኛው ነጥብ "Abyssinians" የሚለው አገላለጽ ነው:: "ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን" የሚለው አገላለጽ ደግሞ ሦስተኛው አከራካሪ ጉዳይ ነው:: በዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት ግን አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ (ዓውድ) መሰረት በዚያን ዘመን ነብዩ የገለጹበት አግባብ የአሁኗን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን የሚወክል ነው:: ስለዚህ "Abyssinians" የሚለውን አገላለጽ አጥኚው የራሱ ሃሳብ መሆኑን በሚገልጽ አግባብ "[ኢትዮጵያና ህዝቦቿን]" ብሎ ተርጉሞታል::

[30] "Leave the Abyssinians in peace, so long as they do not take the offensive."(Sergew 1972:190)

ለምሳሌ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁለቱም ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ የገቡትና የተስፋፉት በአብዛኛው በኃይልና በግዳጅ ሳይሆን፤ በሰላምና በፍላጎት ነው፡፡ ከዚያም በኋላ የእምነቶቹ ተከታዮች ባላቸው መልካም ማኅበራዊ መስተጋብር አማካይነት በሰላም ኑረዋል፤ አሁንም እኖሩ ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያውያንም በራሳቸው ቋንቋ፣ በራሳቸው አለባበስ፣ በራሳቸው የአኗኗር ዘይቤና ሁኔታ ሃይማኖቶቹን ያመልካሉ፡፡ የራሳቸውን ቅርስና ትውፊት ለትውልዱ ያስተላልፋሉ፡፡ በዚህ መሠረት ሃይማኖቶቹም ሆኑ የእምነቶቹ ተከታዮች የራሳቸው ከሆነው ከሀገር በቀሉ ባህል ወግና ልማድ ጋር ተስማምተውና ተከባብረው፤ አገር በቀሉን ትውፊት ሳይጋፉና ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት ሳይሞክሩ፣ የራሳቸውንም ሳያጡ ለዘመናት ኑረዋል፤ አሁንም እየኖሩ ይገኛሉ፡፡

በዚህ መነሻ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በኢትዮጵያ ሥረ-መሠረቱ ወይም ምንጩ ሃይማኖቶቹ የሚኖሩበትና የሚከወኑበት አውድ ነው፡፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖቶቹ አስተምህሮ ወይም መርህ ቢለያዩም እንኳ በሃይማኖቶቹ ትውፊቶች አማካይነት ቋንቋ፣ ድንበርና ሃይማኖቶቹ ራሳቸው ሳይገድቧቸው በጋራ ይሰባሰባሉ፤ ይገናኛሉ፤ ይተባበራሉ (Alula 1994: 50)፡፡ በዚህም ኢትዮጵያውያን በጋራ የእኔ የሚሏቸው በሃይማኖቶቹ ትውፊቶችም ሆነ፤ በፎክሎር ብሂል የሚገለጹ የጋራ መተሳሰሪያ ክሮች አሏቸው፡፡ እነዚህ የጋራ መተሳሰሪያ ክሮች ደግሞ የኢትዮጵያውያንን በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችሉ የጋራ እሴቶች ናቸው፤ ማለት ይቻላል፡፡

በዚህ መነሻ በኢትዮጵያ የዚህ አይነት የሃይማኖት መቻቻል እሴት ከሚገለጹባቸው አካባቢዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ወሎ ነው፡፡ ሃይማኖትና የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ምንጩ ብዙ ነው፡፡ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ከሃይማኖቶቹ ይመነጫል፡፡ ከወሎዬዎች አንደበትና ተግባርም ይፈልቃል፡፡ ከማኅበራዊ መስተጋብራቸው ተፀንሶ ይወለዳል፡፡ ከወሎ ደጋጎች ከራማ፣ ዱዓና ቱፍታ ይገኛል፡፡ ከወሎ አድባር መንጭቶ ይፈሳል፡፡ የሼሆቹ ውሃ ቢሉ፤ የቄሶቹ ፀበል በወሎ ለሃይማኖት መቻቻል እሴት የፈውስ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

4.1፦ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ሥረ-መሠረት በወሎ

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ የተጠቀሱት አካባቢዎች የዓለማችን የሃይማኖታዊና የዓለማዊ እሴቶች ማዕከላት እንደሆኑ ሁሉ፤ በጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ ውስጥ እንደተብራራው የኢትዮጵያ

ሃይማኖታዊና ዓለማዊ እሴቶች ማዕከላት ከሆኑ አካባቢዎች መካከል አንዱ ወሎ ነው። ለአብነት ወሎ የኢትዮጵያውያን መንፈሳዊና ቁሳዊ እሴቶች የሚገኙበትና ለዓለም ህዝቦች ጭምር ቅርስ የሆኑበት አካባቢ ነው። በሌላ በኩል ወሎ በክርስትናው በኩል ቤተ-መንግሥቱ ለቤተ-እምነቱ መርህ ያበጀበት፣ በእስልምናው በኩል ደግሞ የእምነቱ ተከታዮች ለሚከተሉት እምነት መመሪያ ፀድቆ አዋጅ የታወጀበትና ከዚሁ ጋር በተያያዘ ብዙ ትዕይንቶች የተከናወኑበት፣ ግማደ መስቀሉን ጨምሮ ከኢትዮጵያ ልዑላን ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው አምባ ሸንጎ የሚገኝበት ስፍራ ነው።

ወሎ ለሰለሞናዊው ሥርዎ-መንግሥት መስራች ለአፄ ይኩኖ አምላክ መነሻ የሆነውን ያህል፣ ለዚሁ ሥርዎ-መንግሥት አካል ለሆነው (አፄ ተክለ ጊዮርጊስ) ፍፃሜ መንግሥት ምክንያት የሆነው ታላቁ ራስ ዓሊ የተነሳበት ቦታ ነው። ወሎ ቅኔ፣ ዜማና መንዙማ የሚፈልቅበት እና "እንዴ በዘፈኑ፤ አንዴ በመንዙማ..."እንደሚባለው ፈጣሪና የወሎ ደጋጎች የሚመሰገኑበት፤ የሚፈሩና የሚከበሩ የሃይማኖት አባቶች፣ ሊቃውንትና ሼሆች የሚወለዱበትና የሚያስተምሩበት ምድር ነው። በዚህም "የወሎ ከራማ ዝም አይልም ሰው ታሞ!..."በማለት ይመጀኑባቸዋል።

ወሎ በዓለማችን የተለያየ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ በህል፣ ወግና ልማድ ያላቸው ህዝቦች በጉርብትናም ሆነ በአንድ ጣሪያ ሥር በሰላምና በፍቅር በጋራ የሚኖሩበት አካባቢ ነው።በዚህም ወሎ፤

ካለው እንብላ ነው አርሂብ አብሽር ብሎ፤

መቼም አይታማም ስስታም ነው ተብሎ!" (Rukya 2013: 31)።

የሚል ስንኝ የተቋጠረለት መሬት ነው። ወሎ ኢትዮጵያ መሪዋ (ንጉሷ) ለህገርና ለወገን ክብር አርአያ ለመሆን ሲል ራሱን በራሱ የሰዋበት የመቅደላ አምባ የሚገኝበት ቦታ ነው። ወሎ ለአድዋ ጦርነት ምክንያት እና ውጤቱም ለጥቁር ህዝቦች ነፃነት ተምሳሌት የሆነው የውጫሌ ውል የተፈረመበት ቦታ ነው። ወሎ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የአየር ላይ ውጊያ የተካሄደበት እና ክስተቱን በማስመለከት የአገሬው ህዝብ፤

ከሰማዩ በታች ከዳመናው በላይ መንግድ አበጁብህ፤

ተጠንቀቅ እግዚአብሔር ወደ አንተ መጡብህ።

አባ ደልድል ጉግሳ ወንዱ ወዘወዘው፡

መሬት አስለቅቆ በሰማይ አስጓዘው፡፡

በማለት በወቅቱ የነበረውን ትዕይንት የገለፀበት አካባቢ ነው (Awoke 1996: 27-28)፡፡ በዚህ መሠረት ፎክሎር በወሎ የስሜት፣ የፍልስፍናና የጥበብ መግለጫ እሴት ነው፡፡ ወሎ በየጁ መሳፍንቶች እና በወረ-ሂመኖ ኢማሞች አማካይነት የሥልጣን ሽኩቻ ከልክ አልፎ ሞልቶ የፈሰሰበት፣በዚህም ለስልጣን ሲባል ወንድም ወንድሙን ገድሎ "የሞትንም እኛ ያለንም እኛ...!" (Bairu 1987: 628) በማለት አዋጅ ያስነገረበት፣ የአገሬው ህዝብም እንደተለመደው በፎክሎሩ ክስተቱን፣

እንደተያዘለት እንደ ሽማግሌ፣

ኑ ቤት[31] አለ ብሎ አስፈጀው ብርሌ፡፡

የወንድምን ነገር አለማንሳት መተው፣

በቅሎውን ለረታ አገሩን ላብተው፣

ቆሰሮ ተረዱ ዋሮ ጥለው መጥተው፡፡

ዓሊን ዓሊ ገሎት ደስ ብሎት አደረ፣

ምላሹ እንዴት ይሆን ሰርጉ እንዲህ ያማረ[32]፡፡

በማለት ትዝብቱን የገለጸበት ቦታ ነው፡፡ ከዚህ በኋላም ቢሆን አራቱ "ኃያላን" የኢትዮጵያ የጦር አበጋዞች አፄ ቴዎድሮስ፣ ዋግ ሹም ጎበዜ (አፄ ተክለ ጊዮርጊስ)፣ በዝብዝ ካሳ (አፄ ዮሐንስ አራተኛ) እና ንጉሥ ምኒልክ (አፄ ምኒልክ ዳግማዊ) አንዱ ሌላውን አስገብሮ የሀገሪቱ ንጉሠ-ነገሥት ለመሆን ፍትጊያ ያደረጉበትና በመጨረሻም አፄ ምኒልክ ራሳቸውን ንጉሠ-ነገሥት ብለው ያወጁት ወሎ ቦሩ ሜዳ ላይ ነው (Molla 1973: 55) ባጠቃላይ ወሎ ተፈጥሮ ልግስናዋንና ጭካኔዋን በተግባር የገለፀችበት ምድር ነው፡፡

እንዲሁም ወሎ በተመራማሪዎች "ሌላው መርካቶ" የሚለውን አገላለጽ ጨምሮ፣ (ጌታቸው 1984 ዓ.ም፣17)፣ "...the veritable heart of Ethiopia, physically, culturally and psychologically." የሚል ስያሜ የተሰጠው ቦታ ነው (Mesfin 1991: 18)፡፡ በተጨማሪም "a

---

[31] "ኑ ቤት" ላስታ አውራጃ ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስም ነው፡፡አንድምታው ግን ሰምና ወርቅ ያዘለ ፍቺ አለው፡፡

[32] አቶ ወዳጄ ይማም፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 6 ቀን 2007 ዓ.ም፣ ወልዲያ-መቻሬ፡፡

melting-pot of different ethnic groups [a mosaic of people]" የሚለው አገላለጽም ወሎን የተመለከተ ነው (Awoke 1996: 2)። ሌሎች ተመራማሪዎች በበኩላቸው ወሎን "a Steppingstone" በማለት ገልፀውታል (Fekadu 1973: 12)።

በዚህ መሠረት ወሎ በ"መርካቶ" የተሰየመበትም ሆነ፣ "መረማመጃ/መሸጋገሪያ" ተብሎ የተገለፀበት፣ "ልብ"ን ተክቶ የገባበትም ሆነ የ"ማሰሮ"ን ድርሻ የወሰደበት የራሱ የሆኑ በርካታ ምክንያቶች አሉት። ከነዚህ ምክንያቶች መካከል ጥቂቶቹ አካባቢው፣ ታሪኩ፣ የሃይማኖቶቹ ትውፊቶች፣ ባህሉ-ወግና ልማዱ እንዲሁም የወሎዬዎች የሕይወት ፍልስፍዎችና የአኗኗር ዘይቤዎች ናቸው።

4.1.1፡ ታሪካዊ ሁነቶች በወሎ

የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚሉት ከ16ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ጀምሮ እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ በነበሩት ዘመናት ውስጥ በወሎ እጅግ በርካታ ሁነቶች ተከስተው አልፈዋል። ከነዚህ ክስተቶች መካከል የአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) እና የኦሮሞ ህዝብ ወደነዚህ አካባቢዎች ያደረጓቸው መስፋፋቶች ለአብነት ይጠቀሳሉ። የአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) መስፋፋት ከ1520ዎቹ እስከ 1540ዎቹ በነበሩት አመታት ውስጥ የተከናወነ ሁነት ነው (Trimingham 1965: 84-92)። የኦሮሞ መስፋፋት ደግሞ ከ1590ዎቹ እስከ 1680ዎቹ የተካሄደ ክስተት ነው (Teferi 1993: 17-18; Mengistu 1997: 13)።

ለአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) መስፋፋት ምክንያቱና ውጤቱ ከእስልምናና ክርስትና ሃይማኖት ጋር የተሳሰረ ነው። ትስስሩ ወይም ክስተቱ ለእስልምናው በአወንታዊ ጎኑ የሚጠቀስ ሲሆን፣ ለክርስትናው ግን በአሉታዊ ገጽታው የሚጠቀስ ነው። ከእምነቶቹ ተከታዮች አንፃርም ውጤቱ ተመሣሣይ ነው (Hussein 2001: 13)።

የኦሮሞ መስፋፋት ደግሞ የባሬንቱማ በኩር ልጅ ከሆነው ከከረዩ ጋር ይገናኛል። እንዲሁም ከረዩ ከነበሩት ስድስት ልጆች መካከል ሁለተኛ ልጅ ከሆነው ከ"ወሎ" ጋር የእትብት ዝምድና አለው። ዝምድናውም በዚህ ጥናት አካባቢያዊ ዳራ ውስጥ እንደተጠቀሰው ከመጠሪያ ስሙ የሚጀምር ነው። ምክንያቱም "ወሎ" የያዘው አካባቢ ሁሉ በስሙ የሚጠራ "የሥሙ መጠሪያ" ሥያሜ ነው (Rukya 2013: 28)። ይህንንም አለቃ ታየ "አገሩ ጥንት ላኮመልዛ ይባል ነበር።

በኋላ የወለሞ ልጆች ከያዙት በኋላ ግን ያገሩን ስም ለውጠው ባባታቸው ስም ወለሞ አሉት" በማለት ጽፈዋል (ታየ 1958 ዓ.ም.፤ 40)።

እንዲሁም "ወለሞ" የያዘው አካባቢ "ሰባት ቤት ወለሞ" በመባል ይታወቃል። እነዚህም ጃማ፣ ለጋሂዳ፣ ለጋጎራ፣ ለጋ አምቦ፣ አሊ ቤት፣ አባይ ቤት እና ጊምባ ናቸው (Zergaw 1973: 3-4; Mengistu 1997: 4; Hussein 2001: 16)። ነገር ግን ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አካባቢው "ወለሞ" በሚለው ስያሜ ከመጠራቱ በፊት የራሱ የሆነ መጠሪያ ስም ነበረው። ይህም "ላኮመልዛ እና ቤተ አምሐራ" በመባል ይታወቃል (Bairu 1987: 616-620)።

በሌላ በኩል "የጁ"[33] የሚባለው ስያሜም ከዚህ የከረዩ ኦሮሞ እና ከአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) መስፋፋት ጋር የተሳሰረ ነው። ጥናቶች እንደሚጠቁሙት አካባቢው "የጁ" የሚለውን ሥያሜ ከማግኘቱ በፊት "አንጎት" ተብሎ ይጠራ ነበር (Fekadu 1990: 9)። መጠሪያውም የሚያጠቃልለው በዋናነት በሰሜን ከአላማጣ ተነስቶ፣ በምዕራብ ዋድላ ደላንታን ጨምሮ፣ በደቡብ ምስራቅ ከአፋር ጋር እየተዋሰነ እስከ ሐይቅ ይደርሳል (Merid 1974:619)።

በሌላ በኩል "አንጎት" "የጁ" በሚለው መጠሪያ ከተተካ በኋላ "የጁ" የሚለው መጠሪያ አሁን ሰሜን ወለሞ ተብሎ የሚጠራውን አካባቢ ሁሉ የሚያጠቃልል ሥያሜ ነበር። ይህም በአካባቢው ነዋሪዎች "ጨጨሆ በመለሰ ዋጃ በፈሰሰ" በመባል ይታወቃል[34]። በዚህ መሠረት "የጁ" የሚለው መጠሪያ እራሱን የጁን ጨምሮ፤ ዋድላ-ደላንታና ዳውንት፣ ዋሮ-ሼዴሆና መቄት፣ ኩላና ማሶ፣ ራያና ዙባል፣ ጉራወርቄና ቃሊም፣ አንጎትና ላስታ ተብለው የሚታወቁ አካባቢዎችን ሁሉ ያጠቃልላል (Molla 1994: 207)።

ከላይ በተጠቀሱት ላኮመልዛ እና ቤተ አምሐራ እንዲሁም አንጎት ተብለው ይጠሩ በነበሩ አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ደግሞ የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑ አማሮች ነበሩ (Rukya 2013: 27-28)። እነዚህ ህዝቦች በደቡብ ምስራቅ ከአፋርና ከአርጎባ፣ በምስራቅ ከአፋር፣ በሰሜን ምስራቅ ከአፋርና ከዶባ፣[35] በሰሜን ምዕራብ ከትግራይና ከአገው ህዝቦች ጋር

---

[33] የጁ የሚለው መጠሪያ ሥያሜ ከገነተ-ልዑሉ ጳጳስ ጋር እንደሚገናኝ የአካባቢው ነዋሪዎችም ሆኑ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። ለበለጠ ማብራሪያ ገጽ፣ 146 ይመልከቱ።

[34] አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 12 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ።

[35] የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት በአሁኑ ጊዜ ራያና ቆቦ በመባል ሚታወቁት አካቢዎች በ15ኛውና በ16ኛው መቶ ክፈፍለ ዘመን ውስጥ "ቄዳ" በሚል መጠሪያ ይታወቁ ነበር። በነዚህ አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ ህዝቦች ደግሞ "የዶባ ህዝቦች" የሚል መጠሪያ ነበራቸው። እነዚህ ህዝቦች ቀደምት የእስልምና እምነት ተከታዮች

ሁሉ ግንኙነትና ትስስር ነበራቸው፡፡ እንዲሁም በሰሜን ምእራብና በደቡብ ምእራብ ደግሞ ከአካባቢው አማሮችና ሌሎች የጎብረተሰብ ክፍሎች ጋር ተጎራብተው ይኖሩ ነበር (Merid 1974: 619-622; Trimingham 1965: 193-198; Taddesse 1972: 60-66)፡፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ የአህመድ ኢብራሂም (ግራኝ) እና የኦሮሞ ህዝብ ወደነዚህ አካባቢዎች መስፋፋት በአጠቃላይ በአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ሊያስከትሉ ችለዋል፡፡ በተለይ በነዚህ አካባቢዎች ይኖሩ በነበሩ ህዝቦች የማኅበራዊ ሕይወት መስተጋብር ወይም የሰው ለሰው ግንኙነት ላይ ሁሉ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ አስከትለዋል፡፡

ለምሳሌ ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ከላይ እንደተጠቀሰው "ወሎ" እና "የጁ" የተሰኙ ስያሜዎች የተገኙት በነዚህ ክስተቶች አማካይነት ነው፡፡ እነዚህ ስያሜዎች በበኩላቸው ሌሎች ክስተቶችን ወልደዋል፡፡ በዚህም በ"የጁ" የ"የየጁ ወርሴህ" ወይም "ዘመነ መሳፍንት" ሲወለድ፤ በ"ወሎ" ደግሞ "ማመዶች" ወይም "የወረሂመኖ ኢማሞች" እና "የአምባሰል ጎንጥራሮች" ተፈጥረዋል፡፡ የየጁ መሳፍንቶችም ሆኑ፤ የወርሂመኖ ኢማሞች፤ እንዲሁም የአምባሳል ጎንጥራሮች መነሻቸው የእስልምና ሃይማኖት ነው (Hussein 2001; Trimingham 1965):: የየጁ መሳፍንቶች (የየጁ ወርሴህ) የዘር ሐረጋቸው የሚመዘዘው ወደ አካባቢው አህመድ ኢብራሂምን (ግራኝን) ተከትለው እንደመጡ ከሚነገርላቸውና ትውልዳቸውም አመጣጣቸውም ከዓረቡ ዓለም ከሆኑት ከሼህ ዑመር ነው (Fekadu 1990: 18)::

በሌላ በኩል የወርሂመኖ ኢማሞችም ሆኑ የአንባሰል ጎንጥራሮች የዘር ሐረጋቸው የሚመዘዘው ከአርሲ ተነስተው ወሎ-ጋፍራ፤ "ማማድ" በሚበለው አካባቢ ከሰፈሩት ከጎዳና ባቦ ሆኖ፤ ከባሌው ሼህ ሁሴን ጋር ይገናኛል፤ በዚህም ከዓረቡ ዓለም ጋር ይተሳሰራል (M0lla 1994:197; Hussein 2001: 116; 203):: እንዲሁም ከዓረቡ ዓለም በተጨማሪ የየጁ ወርሴህዎችም ሆኑ የወረሂመኖ ኢማሞች አለያም የአንባሰል ጎንጥራሮች ከኦሮሞ መስፋፋት ጋር በቀጥታ ይተሳሰራሉ (Bairu 1987):: ከክርስትና ሃይማኖትና ከሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋርም ይዛመዳሉ፡፡ ከነባሩ እምነት፣ በህል-ወግና ልማድ ጋርም ይቆራኛሉ (Mengistu 1997: 4-7)::

የነዚህ ሁነቶች ድምር ውጤት ደግሞ የአካባቢውን ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሁኔታዎች ሁሉ በአዲስ መልክ ቀይረውታል፡፡ በምትኩ ነባሩ ከእንግዳው ትውፊት

እንደነበሩ ይነገራል፡፡ ነገር ግን በንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ (1434-1468) እና በንጉሥ በዕደ ማርያም (1468-1478) ዘመነ መንግሥታት ውስጥ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ በአሁኑ ዘመን ግን እነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች የትኞቹ እንደሆኑ በታሪክ ተለይተው አይታወቁም፡፡ ለበለጠ መረጃ፣ (Merid 1974: 618-619; Fekadu 1990: 7) ይመልከቱ፡፡

ጋር ተጋብቶ አዲስ አይነት ማኅበራዊ ግንኙነቶችና እሴቶች ተፈጥረዋል፤ ዳብረዋል። እነዚህ ትውፊቶች ደግሞ በክርስትናና እስልምና እምነት ተከታዮች አብሮነት ላይ የራሳቸውን አሻራ አሳርፈዋል። መተሳሰሪያ ክር እና መገናኛ ድልድይም ሆነዋል።

በነዚህ አዲስ አይነት የሰው ለሰው ግንኙነቶች ወይም የማኅበራዊ ሕይዎት መስተጋብሮች አማካይነት በወሎ የጋራ የሆኑ ባህሎች ወግና ልማዶች፣ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች፣ የሥነ-ምግባርና የማኅበራዊ ሕይወት ፍልስፍናዎች፣ የአኗኗር ዘይቤዎች፣ የሃይማኖት መርሆዎችና አስተምህሮዎች...ወዘተ ተፈጥረዋል፤ ዳብረዋል። እነዚህ የጋራ እሴቶች ደግሞ ራሳቸውን "ወሎዬ" ብለው የሚጠሩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን አስገኝተዋል። ከነዚህ የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ነው።

የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ሥረ-መሠረቱ (ምንጩ) ብዙ ነው። ምክንያቱ በርካታ ነው። ለአብነት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ከፖለቲካውና ከኢኮኖሚው ጉዳይ ጋር ይገናኛል። ከሃይማኖቶቹና ከባህሉ ጋር ይተሳሰራል። ከወሎዬዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም አብሮነት፣ ባህል-ወግና ልማድ ውስጥ ይፈልቃል። ከተፈጥሮና ፈጣሪ ጋር ይቆረኛል። በወሎ እነዚህ ሁሉ ትውፊቶች ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንድኖሩ የሚያስችሉ የጋራ እሴቶች ናቸው።

የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ሥረ-መሠረቱ ወይም ምንጩ የጀማው ህዝብ አኗኗር ውጤት ነው። ባጠቃላይ የአካባቢው ማኅበራዊ ተራክቦና ባህላዊ አውድ ነው። ነገር ግን ከጀማው ህዝብ ተነስቶ ወደ ሊሂቃኑ ያቀናል፤ በአንፃሩ ከሊሂቃኑ መንጭቶ ወደ ጀማው ህዝብ ይወርዳል (Ben-Amos 1976; Bauman 1983)። በመሆኑም ሂደቱ እርስ በርሱ የተሳሰረ፣ የተዋኸደና የተዋደደ ነው። በዚህም በወሎ የዚህ አይነቱ ክስተት ከሚገለጽባቸው እሴቶች መካከል አንዱ በሊሂቃኑ በኩል የነበረው የጋብቻ ትስስር እና የዘር ሐረግ ዘይቤ ነው።

የዘር ሐረግና የጋብቻ ትስስር ባህል በወሎ ክርስቲያን ሙስሊሙን እርስ በርስ የሚያስተሳስር ክር እና በጋራ የሚያገናኝ ድልድይ ነው። አንዱን የማኅበረሰብ ከፍል ከሌላው የማኅበረሰብ ክፍል ጋር የሚያገናኝ ጥርጊያ መንገድ ነው። የአንዱን አካባቢ ነዋሪ ከሌላው አካባቢ ነዋሪ ጋር እርስ በርሱ የሚያስተሳስር ድርና ማግ ነው። ይህንንም ሊሂቃኑን አብነት በማድረግ በፎክሎር ብሂል የአገሬው ሕዝብ እንዲህ ይገልፀዋል።

ሰሜንም ያንተ ነው የኃይሉ የገበሬ፤
ጎጃም የናትህ ነው የክንፉ የሮሌ፤
የጁም ያባትህ ነው ያባ ጠላው[36] ወሌ፤
የዘንድሮው ራስ፤ የወዳኛው ንጉሥ፤
ባለግንቡ አንተነህ ራስ ጉግሳ ወሌ (Awoke 1996: 82)።

እነዚህ ስንኞች የሚያሳዩት በጋብቻ ትስስር ምክንያት በተገኘ የዘር ሐረግ ማንነት ሲገለጽ ነው። በሌሎች አካባቢዎች ሊኖር እንደሚችል ቢገመትም የዚህ አይነት እሴት ግን ምንጩ ወሎ ነው። በዚህም ሊሂቃኑ ሳይቀር የጋብቻ ትስስር ትውፊት በወሎ ከፍተኛ ቦታ ያለው የወሎዬዎች የጋራ እሴት ነው።

4.1.2፦ የጋብቻ ትስስር እና የዘር ሐረግ ትውፊት በወሎ

በጋብቻ የሚመሠረት የእትብት ዝምድና በወሎ ሌሎች መመዘኛዎች ቢኖሩትም፤ በቋንቋ፣ በብሔር ወይም በሀገር ልጅነት ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም (Mesfin 1991: 18-19)። ለዚህ ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ከዓረቡ ዓለም እንደመጡ የሚነገርላቸው የየጁ ወረሴህ መስራቾችም ሆኑ፤ መነሻቸው ከአርሲ የሆኑት የወረሂመኖ ኢማሞች ወይም የአንባሰል ጥንጥራሮች ሥረ-መሰረታቸው ከአካባቢው ህዝብ ጋር ተጋብተው ከነሱ የዘር ሐረግ የሚመዘዙ ልጆቻቸው በወሎ እና በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ላይ የራሳቸውን አሻራ አኑረው አልፈዋል (Hussein 2001: 116)።

ለአብነት የየጁ ወርሴህ የዘር ሐረግ የመጀመሪያ እንደሆኑ የሚነገርላቸው ሼህ ዑመር ከየጁ የኦሮሞ ባላባት (ኢልማ ኦርማ) ጋር ተጋብተው፤ ለነ አባ ገትየና ለነ አባ ሴሩ ጓንጉል የዘር ሐረግ መነሻ ሆነዋል። የነ ጎዳና ባቦ ታሪክም ተመሳሳይ ነው (Fekakdu 1990: 18; Hssein 2001: 116-136)። በሌላ በኩል ወደ አካባቢው የተንቀሳቀሱት የኦሮሞ የጎበረተሰብ ክፍሎችም የጋብቻ ትስስራቸው ከአካባቢው ህዝብ አልፎ ጎንደር ቤተ-መንግሥት ድረስ የዘለቀ ነው። ለዚህም ኢዮአስ የኦሮሞ የአብራክ ክፋይ ነው። ምክንያቱም የኢዮአስ ወላጅ እናት ዋቢ የወሎ ባላባት የአሚጦ ልጅ ስለመሆኗ ጥናቶች ያሳያሉ (Hussein 2001፡126)።

ከዚህም አልፎ በወሎ የሃይማኖት ልዩነት ለጋብቻ መስፈርት የማይሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው። በዚህም ክርስቲያንና ሙስሊም በወሎ በእትብት ዝምድና የተሳሰሩ የማኅበረሰብ

[36] "አባ ጠላው" የራስ ወሌ ብጡል የፈረስ ስም።

ክፍሎች ናቸው። ይህም በተለያዩ ጥናቶች የተረጋገጠ እውነታ ነው። ለዚህ ደግሞ "በወሎ ክርስቲያንና ሙስሊም በአንድነት ፍጹም በሆነ ሰላምና ፍቅር በጉርብትና መኖር ብቻ ሳይሆን፤ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች እንኳ ሳይቀር ግማሹ ሙስሊም፤ ግማሹ ክርስቲያን በመሆን የሚኖሩበት አካባቢ ነው። ለዚህ መሠረቱ ደግሞ የአካባቢው ማኅበረሰብ የጋብቻ ትስስር ትውፊት ነው[37]።" የሚለው አገላለጽ ለአብነት ይጠቀሳል (Mesfin 1991: 18)። የዚህ አይነቱን እሴት ሌሎች ተመራማሪዎች የሚገልጹት "...በወሎ እስላም ከክርስቲያን፤ ክርስቲያን ከእስላም በጋብቻ መተሳሰር የተለመደ ባህል ነው። የዚህ አይነቱ ባህል ደግሞ በሌሎች አካባቢዎች ብዙም ያልተለመደ በወሎ ብቻ የሚገኝ እሴት ነው[38]።" በሚል አንድምታ ነው (Berhanu 1998: 4)።

እንዲሁም ሌሎች ተመራማሪዎች በተመሳሳይ "...በወሎ እስላምና ክርስቲያን በሰላም አብሮ መኖር ብቻ ሳይሆን፤ በሥጋ ዝምድና ጭምር የተሳሰሩ ናቸው። በባህሉም በኩል እንዲሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ነው[39]።" (Rukya 2013: 32)። ሌሎች ተመራማሪዎች በበኩላቸው በወሎ ያለውን በሰላም አብሮ የመኖሩንም ሆነ፤ በጋብቻ የመተሳሰሩን እሴት የሚገልጹት ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የእስልምና ትውፊት ወይም ባህርይ ጋር አገናኝተው ነው።ይህንንም "...እስልምና በኢትዮጵያ የተስፋፋው ለእምነቱ መስፋፋት ምክንያት የነበሩ አካላት ከአገሬው ህዝብ ጋር በነበራቸው መልካም መስተጋብር ነው። ይህ መስተጋብር ደግሞ የአካባቢውን ቋንቋ ከመልመድ ጀምሮ በጋብቻ መተሳሰርንም ይጨምራል[40]።" በማለት ይገልጹታል (Trimingham 1965: 139)። ሌሎች መረጃዎችም በወሎ ያለውን እውነታና ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አብነቶች በተጨባጭ ያጠናክራሉ። ለዚህ አባባል ማሳያ የሚከተለው የሁለት ሰዎች ታሪክ ሊጠቀስ ይችላል።

---

[37] "Not only do Christians and Muslims live next to each other in perfect harmony and absolute peace, but even within the same family half may be Christian and half Muslim. Moreover, Intermarriage between religious groups is rather common."(Mesfin1991:18.)

[38] "Intermarriage between members of Muslim and Christian is much more common in Wollo than any other parts of Ethiopia" (Berhanu1998:4.).

[39] "The Wollo community is far more than mixed since there is a strong blood ties due to intermarriage between Muslims and Christians, There is also cultural diffusion and strong sense of togetherness that has been held for generations"(Rukya 2013:32).

[40] "Arab traders, artisans, and adventurers were the chief medium of Islamic expansion; and coming as they did as individuals and not as tribes they naturally lived in close touch with the natives, adopted their language in stead of imposing Arabic, and intermarried with them" (Trimingham 1965: 39).

...በዚያው ወራት ሁለት ሰዎች ዋድላ ገረገራ ከሚባል ሀገር ተገናኙ። አንድ ከቤጌምድር፤ አንድ ከየጁ ናቸው። በጌምድሬው የጁየውን ጠየቀው፤ ሲል ምን ጎሳ ነህ ብሎ። አባቴ [ኦሮሞ] ነው፤ እናቴ ክርስቲያን ነበረች፤ ዛሬ ወደ እስላምነት ታስባለች አለው። በጌምድሬውም አለው፤ የኔ ግን አባቴ አምሓራ ነበረ፤ እናቴ ግን የየጁ [ኦሮሞ] እስላም ናት አለው። በዚህ ዘር ሲቋጠሩ ተዛምደው[41] [ተገኙ] (Bairu 1987: 635-636)::

ከዚህ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው በወሎ የሰው ለሰው ግንኙነቱ የተሳሰረው፣ የሃይማኖትና የባህል ውህደቱ የሰመረው፣ በዚህ አይነቱ ተራክቦ አማካይነት ነው። የዚህ አይነቱ ተራክቦ ደግሞ "ወሎዬ" ወይም "የወሎ ሰው" አሊያም "ወሎ ገብሱ" የሚለውን የወሎየዎች ልዩ መገለጫ ባህርይ አስገኝቷል (Teferi 1993: 20-21; Rukya 2013: 32-33; Berhanu 1998: 4-5):: በመሆኑም ለወሎ ሰው "እናቱ ዱበርቲ አባቱ ሼህ ናቸው..." የሚለውን አገላለጽ ጨምሮ፤

ባባቱ ወርሴህ በናቱ በቆቹ

አበላዋለሁኝ ፈጭቹ በእጆቹ


እያሉ በፎክሎር አማካይነት ስንኝ ይቋጥሩለታል፤ ይቀኙለታል (Molla 1994: 199):: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወሎ የእርስ በርስ ግንኙነቱም ሆነ የጋብቻ ትስስሩ በጀማው ህዝብ ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ባንፃሩ በሊሂቃኑም ጭምር የተዘወተረ ባህል ነው። የዚህ አዓይነቱ ባህል ደግሞ በዚያው በወሎ አካባቢና በወሎዬዎች ብቻ የተወሰነ አይደለም። የጋብቻ ትስስር ባህል በወሎ ከሌሎች አካባቢ ህዝቦች ጋር ሁሉ ይገናኛል (Mesfin 1991: 18-19)::

በዋናነት ግን የጋብቻ ትስስር ባህል በወሎ ከአፋር እስከ ትግራይ፤ ከላስታ እስከ ጎንደር፣ ከዚያም ከጎጃም እስከ ሸዋ ይዘልቃል። በወሎ የዚህ አይነቱን የጋብቻ ትስስር ባህል የሊሂቃኑን ሁኔት አብነት በመጥቀስ በተጨባጭ ማሳየት ይቻላል። ለዚህ ደግሞ በየጁ-የየጁ ወርሴህ፤ በወሎ የወርሂመኖ ኢማሞችና የአምባሰል ጎንጥራሮች ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። በዚህ መሠረት የጋብቻ ትስስር ትውፊት በወሎ ምን አይነት ገጽታ እንዳለው ከዚህ ቀጥለው በቀረቡት ሁለት ሥዕላዊ መግለጫዎች ተመልክቷል። እነዚህ ሥዕላዊ መግለጫዎች የጋብቻ ትስስሩን ሥረ-መሠረት ወይም ምንጭ፣ የጋብቻ ትስስሩን አካባቢና የዘር ሐረጉን ትስስር ሁኔታ በተጨባጭ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው።

ከዚህም ባለፈ ሥረ-መሠረታቸው ከየጁ ወረሴህ የሆኑ አካላት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የነበራቸውን ሚናም በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ይህ ታሪክ ደግሞ አጠቃላይ የዘመኑ ነባራዊ ሁኔታ መገለጫ መሠረት ነው። ምንም እንኳ ከሥዕላዊ መግለጫዎቹ መረዳት እንደሚቻለው የሊሂቃኑ የጋብቻ ትሥሥር የሚያያዘው በዋናነት ከፖለቲካውና ከኢኮኖሚያዊው ሁኔታ አንፃር ቢሆንም፤ ሁነቶቹ ግን የወሎዬዎች ማኅበራዊ ሕይወት አንድ አካል ናቸው። አጠቃላይ የየጁ ወረሴህን እና የወረሂመኖ ኢማሞችን የዘር ሐረግና የጋብቻ ትስስር ከሚከተሉት ሁለት ሥዕላዊ መግለጫዎች ይመልከቱ።

---

[41] ዐሐፊው ይህንን ታሪክ የተጠቀሙበት አግባብ የሃይማኖቱም ሆነ የዘር ሐረጉ አንዱ ከሌላው እንዴት እየተቀላቀለ እንደሄደ ለማሳየት ነው። የርዕሰ ጉዳዩ አንድምታ ግን የዚህ አይነቱ መቀላቀል በክርስትና ሃይማኖት ላይ አሉታዊ ገጽታ ማሳደሩን ለማሳየት የተጠቀሙበት ይመስላል።



ሥዕላዊ መግለጫ ፩፡- የየጁ ወረሴህ የዘር ሐረግና የጋብቻ ትስስር


ምንጭ፡- -አወቀ አስማረ፤ 1996፤ ገጽ፤ vii

-ሞላትኩየ፤1994፤ገጽ፣199

-ፈቃዱ ቤኛ፤1990፤ገጽ፣ 57

*ደ/= "ደጃች"

*ወ/= "ወለተ"/ "ወልደ"



ሥዕላዊ መግለጫ ፱፡- የወረሂመሞ ኢማሞች (ማማዶች) የዘር ሐረግና የጋብቻ ትስስር፡፡

ምንጭ፡- -ሁሴን አህመድ፤2001፤ገጽ፣203

-ፈቃዱቤኛ፤1973፤ገጽ፣4

-ሞላ ትኩየ፤ 1994፤ገጽ

*ገይቲ፣ ወርቂትና መስታዋት፤ እንደቅደም ተከተላቸው፤ የመሐመድ ዓሊ፣ የአመዴ ዓሊና የአመዴ ሊበን ወላጅ እናቶች ናቸው፡፡ በተለይ ወርቂትና መስታዋት በወሎ ታሪክ ውስጥ በአመራር ደረጃ ተጠቃሽ ሴቶች ነበሩ፡፡

እንዲሁም በምእረፍ ስድስት ውስጥ እንደተጠቀሰው በጀማው ህዝብ መካከል የሚደረገው የጋብቻ ትስስርም ቢሆን የራሱ የሆኑ መነሻ ምክንያቶች ያሉት ነው፡፡ መሠረታዊው ጉዳይ ግን የጋብቻ ትስስር ትውፊት በወሎ ከብዙሃኑ መንጭቶ ወደ ሊሂቃኑ፤ ከሊሂቃኑ መንጭቶ

ወደ ብዙሃኑ የሚወራረስ ባህል መሆኑ ነው። ምክንያቱም ሁለቱም አካላት የተፈጠሩትና የሚኖሩት በተመሳሳይ አውድ ወስጥ ነው። የዚህ አይነቱ አውድ በፎክሎር "environment itself acts as a mechanism in the selection of cultural traits." ከሚለው አስተሳሰብ ጋር ይገናኛል (Braukämper 1984: 439):: ይህንንም ከየጁ ወርሴህ የዘር ሐረግና የጋብቻ ትስስር መረዳት ይቻላል።በየጁ ወርሴህ የዘር ሐረግ ሥዕላዊ መግለጫ መሠረት የየጁ ወርሴህ መፈጠሪያ ቦታ ሰሜን ወለሞ መርሣ እሚባለው አካባቢ ነው። ይህ አካባቢ ደግሞ አባ ገትየ የተወለዱበትና በረከታቸው ለብዙዎች የሚተርፍበት ለዱዓ የተመሰረተ ቦታ ነው።

በዚህ መሠረት አባ ገትየ የሚታወቁት በበረከታቸው፣ የእርቅና የሥርአት አባት ወይም የትውልዱ አርአያ (Hero) በመሆናቸው ነው። በመሆኑም መርሣ አባገትየ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ የበረከት ቦታ ነው። ለምሳሌ ወለዬዎች "መርሣ አባ ገትየ መጀን!" ብለው ሳይሰምርላቸው ቢቀር፤

መርሣ አባ ገትየን ብጠራው ዝም አለኝ፤
እውነተኛው እንቅልፍ ወስዶት ነው መሰለኝ።።[42]

በማለት ቅሬታቸውን ይገልፃሉ። ስለዚህ መርሣ አባገትየ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም ሃጃ የሚሞላበት፣ ሙስሊም ክርስቲያኑ በረከት የሚያገኝበት ቦታ ነው። በዚህም የሃይማኖት መቻቻል እሴት ሥረ-መሠረት ነው። በዚህ መነሻ ከዚህ ቦታ ላይ የሼህ ዑመር እና የአካባቢው ማኅበረሰብ የጋብቻ ትስስር በሂደት እየዳበረና እየጎለበተ ሂዶ ከአባ ገትየ ልጅ ከአባ ሴሩ ጓንጉል ላይ ይደርሳል።

በአባ ሴሩ ጓንጉል አማካይነት ደግሞ ላስታ ይሻገራል። "የሴሩ ቀመስ" የሚለው የርስት ትውፊትም በጋብቻ ምክንያት ተፀንሶ ለዘመናት በላስታና አካባቢው ከማንነት ጋር የተገናኘ ባህል ሁኖ ኑሯል (wudu 1995:122)። አባ ሴሩ ጓንጉል ላስታ ከተሻገረ በኋላ ከክርስትና ሃይማኖት ጋርም ይዛመዳል።

በዚህም ከእስልምና ወደ ክርስትና፤ ከክርስትና ወደ እስልምና እምነትን መቀየር በወለሞ አንዱ የጋራ መገለጫ ትውፊት ሆኖ አሁን የምንገኝበት ዘመን ላይ ደርሷል። አባ ሴሩ ጓንጉል ከነዋሪዎቹም ሆነ ከሃይማኖቱ ጋር ያደረጉት ጋብቻ ከ"የጁ ሃዳ" ወይም ከየጁ ባህል-ወግና

[42] አያሌው ብሩ፣ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 9 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ሳንቃ።

ልማድ ውስጥ የመነጨ ነው። ሂደቱም ከዚሁ የትውፊት ምንጭ የተቀዳ ነው። የዚህ ሁነት ሥረ-መሠረቱ ወይም ምንጩ ደግሞ የጀማው ህዝብ ፎክሎር ነው። የጀማው ህዝብ በረከት ነው። የጀማው ህዝብ ትውፊት ነው። ከአባ ሴሩ ጓንጉል እስከ ራስ ወሌ ብጡል ቅርንጫፉን ያስፋፋው የየጁ ወርሴህ የዘር ሐረግና የጋብቻ ትስስር መነሻው ፎክሎር ነው። ለዚህም የሚከተለውን የአባ ሴሩ ጓንጉል ታሪክ ከፎክሎር አንፃር ለአብነት እንጠቅሳለን።

> ጓንጉል አባ ሴሩ እሚባል አንድ ሉባ ነበረ። የአባ ገትየ ልጅ ነው። ሦስት ሚስቶች ነበሩት። ራጂያ፡አትሞቱና እና ገለቡ ይባላሉ። አባ ሴሩ ጓንጉል ዱዓ ጠቃሚ መሆኑን ያውቃልና ወልዮቹን ለዱዓ ወደ ቤቱ ይዶላል። ሲያስቅም ያድራል። ኮርማ ጀባ ይላቸዋል። ድገም ሲሉት፣ ድገም ሲሉት፣ ድገም ሱሉት፤ አርባ የሞላ ጊዜ "ጓንጉል ረባሽ! ሰባሽ! እንግዲህ ከበርሽ!" አሉት ወልዮቹ። ምን ይወልዳል ጓንጉል አባ ሴሩ አርባ ልጅ። አርባ ጊዜ አደለም ዱዓ ያስደረገው፤አርባ ልጅ ወለደ።[43] አርባ ልጅ ሲወልድ፤ ሃርባዎቹ ልጅ ማን አስተዳዳሪ ይሆናል ራስ ዓሊ ጓንጉል። የራስ ዓሊ ጓንጉል እናት ገለቡ ትባላለይ። ገለቡ ወለዮቹን እየካደመይ በረካቸውን አሜን ብላ ተቀበለይ። ራጂያ ግን አልካድምም ብላ እምቢ አለይ። የዚህ ጊዜ ወልዮቹ፤
>
> ራጂያ ወልደይ አህያ
>
> ገለቡሳ ወለደይ አንበሳ።
>
> ብለው ገለቡን መርቋት። ራጂያን ግን ረገሟት። ይኸ ስለሆነ ራጂያ ለራስ ዓሊ ገባር ሁነው የቀሩትን ልጆይ ወለደይ። ራስ ዓሊ ማንን ገባር አደረገ የገዛ ወንድሞቹን[44]።

በዚህ ትውፊት መሠረት ከሥዕላዊ መግለጫ አንድ መመልከት እንደሚቻለው ከገለቡ የተወለዱት የአባ ሴሩ ጓንጉል ልጆች ሦስት ናቸው። እነሱም ራስ አሊጋዝ፣ ወይዘሮ ከፊይ እና ታላቁ ራስ ዓሊ ናቸው። እነዚህ ሦስት ግለሰቦች በየጁና አካባቢው እንደሁም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በክፉም ሆነ በደጉ ሰፊ ቦታ አላቸው። የራሳቸውን አሻራም ትተው አልፈዋል።

ባንፃሩ የአካባቢው ማኅበረሰብም ሆነ የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት ከራጂያ የተወለዱት የአባ ሴሩ ጓንጉል ልጆች አምስት ናቸው (Molla 1994: 199)። እነዚህም ወሌ፣ የሱፌ፣ ብርሌ፣ ኮርሜና አስቴር ሲሆኑ፤ እነሱም ስማቸው ከመጠቀሱ ያለፈ ሌላ ታሪክ የላቸውም። ነገር ግን ከነዚህ ልጆች መካከል ወሌ የአባ ሴሩ ጓንጉል የመጀመሪያ ልጅ ስለነበር አባቱ ሲሞት የጁን የማስተዳደር ኃላፊነት ተረክቦ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ቢሆንም አስተዳደሩ ብልሹ ከመሆኑም ባለፈ፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ ከጫካ "አንበሳ ከነሕይወቱ!" እንዲያመጣለት ግዳጅ ይጥል ነበር።

---

[43] መረጃ አቀባዩ አባ ሴሩ ጓንጉል 40 ልጆች እንደወለዱ ቢገልጹም፣ በታሪክ ምሁራ ተጠቅሰው የሚገኙት ግን ስምንት ልጆች ብቻ ናቸው። ለበለጠ መረጃ ሞላ ትኩየ፣ 1994፣ ገጽ፣ 199 ይመልከቱ።

[44] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ

በዚህ የተነሳ የአካባው ማኅበረሰብ ከራሱ ወንድም ከራስ ዓሊ ጓንጉል ጋር በመሆን ወሌን ከአስተዳዳሪነቱና ከአካባቢው አባሮታል። በዚህም ወሌ ከወልዲያ ሰሜን አቅጣጫ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደሚገኘው ሐራምባ ወደተባለ አካባቢ መሸሸ ይነገራል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የአካባቢው ማኅበረሰብ "ወሌ ዳባ-ወረደ ሐራምባ!" በማለት ወሌን ስለፈሪነቱ ተሳልቆበታል ይባላል (እንደላይኛው፤ 201-202)።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ ከቀረቡት ትውፊቶች መረዳት እንደሚቻለው፤ ለስልጣንም ሆነ ለጋብቻ፤ ለክፉም ሆነ ለበጎ ወይም ለመመረቅም ሆነ ለመረገም በወሎ ትውፊት መሠረት የጀማውን ህዝብ በረከት ከማግኘትና ከማጣት ጋር በእጅጉ የተያያዘ አስተሳሰብ ነው።"በሼሆቹ በደጎቹ ወሎ መጀን!" ከሚለው የወሎዬዎች እሴት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው። ይህ በረከት ደግሞ የሙስሊም ወይም የክርስቲያን ሳይሆን በአጠቃላይ ከወሎ መሬት የሚመነጭና የክርስቲያን ሙስሊሙ የጋራ እሴት ነው።

የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት ጓንጉል አባ ሴሩ ከእስልምና ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተቀየረ የመጀመሪያው የወርሴህ ተወላጅ ነው (Fekadu 1990: 18):: የክርስትና ሃይማኖት እምነት ተከታይ ከሆነ በኋላ ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በ1760ዎቹ አካባቢ ከወልዲያ ምእራብ አቅጣጫ 10 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ላይ አማየ ሚጫ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን አሰርቷል። ይህ ቤተ ክርስቲያን አሁንም ድረስ በፀበሉ ፈዋሽነት ይታወቃል። በፀበሉ ክርስቲያኖቹ ተጠምቀው እንደሚድኑበት ሁሉ፤ ሙስሊሞቹም ተጠምቀው ይፈወሱበታል። በዚህም እንደክርስቲያኖቹ ሁሉ ሙስሊሞቹም ስዕለት ያገቡለታል፤ ዝክር ይዘክሩለታል። በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያኑ በክርስትናና እስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ቦታ አለው። አባ ሴሩ ጓንጉል ይህንን ቤተ ክርስቲያን ያሰራው በሚስቱ ግፊት ተነሳስቶ እንደሆነ ይነገራል። ለዚህም የሚከተሉት ስንኞች የባልና ሚስቱን ፍላጎት፣ ሰሜትና አመለካከት የሚያሳዩ አብነቶች ናቸው።

ሚስት፡- ጓንጉል አባ ሴሩ እንጀራሁን እንጂ አንቱን አልወድሁም
የሚቀበሩበት በተስኪያን የለሁም።

ጓንጉል አባ ሴሩ፡- እንጀራ ነው እንጂ የሰው ቁም ነገሩ
ይቀበር የለም ወይ ሰው ሁሉ በዘሩ (እንደላይኛው፤ 19)

ከነዚህ ሁለት ግለሰቦች የሃሳብ ልውውጥ በኋላ የዘር ሐረጋቸውን ከአባሴሩ ጓንጉል የሚመዙ የየጁ ወረሴዎች እምነታቸውን ከእስልምና ወደ ክርስትና በመለወጥና በየጁ የተለያዩ አካበቢዎች ቤተክርስቲያን በማሰራት ይታወቃሉ፡፡ ለዚህም ታላቁ ራስ ዓሊ፣ ራስ አሊጋዝና ራስ ወሌ ብጡል ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በጓንጉል አባ ሴሩ የተጀመረው ከሌሎች የክርስትና እምነት ተከታይ አካባቢዎች ጋር በጋብቻ የመተሳሰር ባህልም የየጁ ወረሴዎች ልዩ መገለጫ ለመሆን በቅቷል፡፡ ለአብነት የአባሴሩ ጓንጉል የልጅ ልጅ ራስ ጉግሳ መርሶ በሬንቶ ይጠቀሳል፡፡ ባንፃሩ የክርስትና እምነት ተከታዮችም ከእስልምና እምነት ተከታዮች ጋር በጋብቻ የመተሳሰር ባህል የአካባቢው ልዩ መገለጫ ነው፡፡ ለበለጠ ማብራሪያ እዚሁ ምእራፍ ውስጥ ገጽ 121 የሚገኘውን የየጁ ወረሴህ የዘር ሐረግና የጋብቻ ትስስር የሚያሳየውን ሥዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ፡፡

4.1.3፡- የትንቢት ትውፊት በወሎ

ከላይ እንደተመለከተው ራስ ዓሊ ጓንጉል በየጁ የወልዮቹ የትንቢት ውጤት ነው፡፡ በዚህም ራስ ዓሊ ጓንጉል በዱዓ ተፀንሶ በዱዓ የተወለደ ነበርና ከየጁ እስከ ጎንደር ቤተ መንግስት ድረስ እጅግ በርካታ ታሪኮችና ትውፊቶች አሉት፡፡ የጎንደሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በየጁ ከታላቁ ራስ ዓሊ ጋር የተገናኙ ትውፊቶች በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ "በጓንጉል ሳሩ፤ በዓሊ ምሳሩ!"[45] የሚባለውን የአካባቢውን ብሂል ጨምሮ፤ ራስ ዓሊ ጓንጉል ለየጁ ወርሴህ መፈጠር ምክንያት የሆነ፣ ወልዲያ ገበያን እና ወልዲያ ከተማን የቆረቆረ፣ ለመጠሪያ ስያሜያቸውም ምክንያት የሆነ፣ በወልዲያ እና አካባቢዋ ሰባት ደብሮችን የተከለ፣ በየጁና አካባቢው በርካታ መጠሪያ ስያሜ ለነበረውና ለዘመናት ባህል ሆኖ ለኖረው የርስት ሥርአት ምክንያት የሆነና የየጁ ወርሴህ መስራችና የመጀመሪያው መሪ ነው (Trimingham 1965: 111; Awoke 1996: 5; Wudu 1995: 102):: በወልዲያና አካባቢው በታላቁ ራስ ዓሊ እንደተመሰረቱ የሚነገርላቸው አብያተ ክርስቲያናት፤ ወልዲያ ገብርኤል፣ ጉባርጃ ማርያም (ገነተ-ልዑል)፣ ጃርሳ መድኃኔዓለም፣ ዛሚል ጊዮርጊስ፣ ኪቢ ቃለ ሚካኤል፣ ሸዋና ማርያም እና ጉባላፍቶ ተክለሃይማኖት ናቸው (Fekadu 1990: 25; Molla 1994: 203; ታየ 1958 ዓ.ም. 50)::

---

[45] "በጓንጉል ሳሩ በዓሊ ምሳሩ!" የተባለበት ምክንያት በአባ ሴሩ ጓንጉል ጊዜ በየጁ ከግብርና ሥራ ይልቅ የከብት ርባታ የተዘወተረ የግብርና ሥራ ነበር ይባላል፡፡ ባንፃሩ በታላቁ ራስ ዓሊ ጊዜ ደግሞ የእርሻ ሥራ ከፍተኛ ቦታ እንደነበረው ይነገራል፡፡ ለዚህም የራስ ዓሊ ጓንጉል የርስት ስሪት በየጁ ለአብነት ይጠቀሳል፡፡ ለበለጠ መረጃ ገጽ 137-138 ይመልከቱ፡፡

እነዚህ ቤተክርስቲያናት በሚከበሩበት ጊዜ ደግሞ መንፈሳዊው ጉዳይ የክርስትና እምነት ተከታዮችን የሚመለከት ሆኖ፤ ከዚያ ውጪ ያሉት ዓለማዊ ጭፈራዎችና ከበራዎች ግን የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴቶች ናቸው። የፀበላቸው፣ የእምነታቸውና የመስቀላቸው ትውፊትም ለክርስቲያኑም ለሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው። በመሆኑም በአካባቢው የሁለቱን ሃይማኖት እምነት ተከታዮች በማገናኘትና በማቀራረብ በኩል ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። በዚህም ለሃይማኖት መቻቻል እሴት ምንጮች ናቸው። ለበለጠ ማብራሪያ ምዕራፍ አምስትን ይመልከቱ። የወልዲያ ከተማና የወልዲያ ገበያ ስያሜዎች ደግሞ ከታላቁ ራስ ዓሊ ጓንጉል ጋር የሚተሳሰሩት በሚከተለው ትውፊት አማካይነት ነው።

> ...ራስ ዓሊ ከጎንደር ከተመለሰ በኋላ ምን ላይ ተቀመጠ ወልድያ ገብርኤል "ማንም ይምጣ" ላይ። ቦታው ዙሪያውን ገደል ሁኖ መሀሉ ሜዳ ነው። በሯም አንዲት ብቻ ናት፤ አላህ ሲኸልቅ። "የፈለገው ይምጣ እንግድህ ይችን በር ይዤ እሚመጣውን ጠላት አወድመዋለሁ!" ማለቱ ነው። "ደጃማይም ይምጣ፣ አጤም ይምጣ እንግደድህ ኸይች ኸሆንኩኝ እሚነካኝ የለም!" ማለቱ ነው። የፈለገው ይምጣ ማለቱ ነው። ኸይህ የተነሳ ያ ቦታ አሁንም መጠሪያው "ማንም ይምጣ" ነው። ኸይህ በኋላ ፍጣሜ ተ/ጊዮርጊስም ሳይመጣበት ቀረ። ዓሊም ኸይህ ላይ እንዳለ ኸለታት አንድ ቀን ሰጋና በአፋፉ ብቅ ሲል፤ በወልዲያ በላይ ብቅ ብሎ ሲያይ ወልዲያ ገበያው ወይዱ ላይ ቆየ ሲያይ አሁን ገበያው ሃለበት ቦታ የጨርቅ ምልክት አየ። ኸይህ ኸገበያው ግርጌ ላይ ውሃ ይፈልቃል። ዛሬም ድረስ አለ፤ምንጭ ነው። "ምንድ ነው!? ጦር መጣ መሰለኝ፤ ምልክት አየሁ፤እርችት ነው፤ ጨርቅ ተሰጥቷል!" ብሎ አሸከር ላከ። አሸከሮቹ እቦታው ላይ ሲደርሱ ሴቶች ልብስ አጥበው አስጥተው ቁጭ ብለዋል። "ምንድን ናችሁ!?" "እረ-እኛ ምንም አደለን አራስ ሴት ወልዳብኝ፣ የሷን የደም ጨርቅ አጥበን ነውይ ሌላ ምንም አደለን፤" "አሃ! ወልዳ ነው እንዴ? ሴት ወልዳ ነው?" "አዎ!" እየበረሩ ሂደው "እራስ፤ ሰላም ነው! ሴት ወልዳ አድራ ነው። የሴት የደም ጨርቅ አጥበው ነውይ ሰላም ነው!" "አሃ! ሴት ወልዳ ነው እንዴ?" "አዎ!" "በሉ ያነን የወይዱውን ገበያ ኸይህ አንጡት" አለና ያነን ገበያ ነቅሎ አሁን ሃለበት ስፍራ ላይ አረገው። መጠሪያውም በያው ወልድያ[46] ሁኖ ቀረ ይባላል[47]።

በዚህ መሠረት ወልዲያ ገበያ ለወሎዬዎች ብቻ ሳይሆን፤ ለአጎራባች አካባቢዎች ሁሉ፤ የንግድ ብቻ ሳይሆን የመገናኛ፣ የመተሳሰሪያና የባህል መለዋወጫ መድረክ ሆኖ አሁን የምንገኝበት ዘመን ላይ ደርሷል። በመሆኑም ወልዲያ ገበያ ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችል የጋራ እሴት ነው። (ለበለጠ ማብራሪያ ከገጽ 146-151ይመልከቱ።)

---

[46] ስለ ወልዲያ መጠሪያ ሌላኛው መረጃ አቀባይ የነገሩኝ ታሪክ ደግሞ የሚከተለውን ነው። የኸውም፣ "ዱሮ እዚህ ገበያ አልነበረም ይባላል። ገበያው ወይዱ እሚባል አካባቢ ላይ ነበረ። አሁን ገበያው ያለበት ቦታ ግን የቀረጥ ማስከፈያ በር (ኬላ) ነበር ይባላል። ቦታው ዋና መመላለሻ መጋቢ መንገድ ነበር ይባላል። እዚህ ቦታ ላይ ቀረጥ የሚያስከፍለው ሰው ሥሙ "ወልዴ" ይባል ነበር አሉ። በዚያው ወልዲያ ተብሎ ቀረ ይባላል።" በማለት አብራርተውልኛል። (ውዳድስ ምህረቱ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም. ሐብሩ- ስሪንቃ።)

[47] አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ መጠይቅ፤ ሐምሌ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ።

በሌላ በኩል ታላቁ ራስ ዓሊ በወልዮቹ ዱዓ ታላቅ እንደሚሆን ትንቢት የተነገረለትን ያህል፤ በወይዘሮ ከፊይና በራስ አሊጋዝ መካከልም እንዲሁ የተነገረ ትንቢት ነበር። ይህንን ትንቢት የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልፁት እንደሚከተለው ነው።

> የራስ አሊጋዝ ሥልጣን ከወይዘሮ ከፊይ በሚወለድ ልጅ እንደሚወሰድ በወልዮቹ ትንቢት ተነግሮ ነበር። ትንቢቱን የሰማው ራስ አሊጋዝ በወቅቱ ወይዘሮ ከፊይ ሁለቱን ልጆቿን እንድታስረክበው አስጮት ነበር። ወይዘሮ ከፊይም በሃሳቡ ተስማምታ ልጆቿን ለማምጣት ከእስር ተፈታ ወደ ቤቷ ተመለሰች። ነገር ግን ሳትመለስ ልጆቿን ይዛ በዚያው ተሰወረች። በመሃል ግን ራስ አሊጋዝ ታመመ። ወንድሟ መታመሙን የሰማችው ወይዘሮ ከፊይ፤ ግን የእህት አንጀቷ አላስችል ቢላት ልትጠይቀው ድጋሚ ወደ ራስ አሊጋዝ ቤት መጣች። ራስ አሊጋዝ ግን በድጋሚ ልጆቿን እንድታመጣ አሰራት። ወይዘሮ ከፊይም በእስር ላይ እንዳለች ልጆቿ እንዲመጡ መልዕክተኛ ላከች። ልጆቿ ከራስ አሊጋዝ ቤት ከመድረሳቸው በፊት ግን በመሐል ራስ አሊጋዝ ቀድሞ ሞተ። በትንቢቱ መሠረትም የራስ አሊጋዝን ሥልጣን የወይዘሮ ከፊይ ልጅ ጉግሳ መርሶ ወረሰ። ሃያ አምስት አመትም ገዛ። ለራስ አሊጋዝ ግን፤
>
> ከራስ አሊጋዝ ቤት አለች ትንሽ ልግም
>
> ያለዚያ ክርስቶስ እንዲህ አያደርግም፤ ተብሎ ተገጥሞለታል[48]።

የራስ ጉግሳ መርሶ የዘር ሐረግና የጋብቻ ትስስርም ከሥዕላዊ መግለጫ አንድ ላይ እንደሚታየው ከየጁ አልፎ ለሌሎች አካባቢዎች ሁሉ ተርፏል። ለምሳሌ ከትግራይ ከራስ ገብሬ ልጅ ከደጃዝማች ኃይለማርያም፣ ከላስታ ዋግ ሹም ክንፉ፣ ከሚጫ ወልደ ሩፋኤል፣ ከደንቢያ ደጃች ማሩ፣ ከወርሂመኖ ከሊበን አባ ጅሩ ልጅ ሐሊማ (ኢቴጌ መነን)፣ ከዚያም በኋላ የነዚህ ልጆችና የልጅ ልጆች ከኢትዮጵያውያን ሁሉ በሚባል ሁኔታ በጋብቻ ተሳሰሩ፤ ተዛመዱ። የዚህ አይነቱ የጋብቻ ትስስር ወሎዬዎች አንዱ ከሌላው ጋር በእትብት ዝምድና የሚተሳሰሩበት የጋራ እሴት ነው። ለበለጠ ማብራሪያ ምእራፍ ስድስትን ይመልከቱ።

የወሎ ባህል ወይም የየጁ “ሃዳ” የዚህ አይነት ባህርይ ያለው ነው። ምክንያቱም ሰው ከሰው የሚለያይበት ሳይሆን፤ የሚተሳሰርበት፤ ሰው ከሰው የሚለያይበት ሳይሆን በእትብት ዝምድና የሚዛመድበት፤ ሰው ከሰው በሃይማኖቱ ወይም በብሔሩ የሚቧደንበት ሳይሆን ሰው በሰውነቱ ብቻ አንድ የሚሆንበት መሬት ነው። በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ሥረ-መሠረቱ የዚህ አይነቱ ትውፊት ነው።

---

[48] ፱ አለቃ መኮንን የሺጥላ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 6 ቀን 2004 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ።

በሌላ በኩል ከሥዕላዊ መግለጫ አንድ ላይ እንደሚታየው የራስ አሊጋዝ ልጆች የዘር ሐረግ በዚያው ባለበት ቁሞ ቀርቷል። ነገር ግን ከራስ አሊጋዝ ልጆች አንዱ የሆነው የደጃች ጎጂ ታሪክ ግን አሁንም ድረስ በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ይተረካል። ይኸውም ጎጂ በአካባቢው ማኅበረሰብ የሚጠራው "ዓይን አውጣው ጎጂ" በሚል ቅጽል ነው። ይህ የቅጽል መጠሪያ የጎጂን የጭካኔ ተግባር የሚገልጽ ምልክት ነው። ጎጂ ይህንን ተግባር የሚፈፅመው ሌሎች ተቀናቃኞቹ እጅግ እንዲፈሩት በነበረው ፅኑ ምኞት መሠረት ነው። ለዚህም ጎጅ የሚቃወሙትንና በጦርነት የሚማርካቸውን ግለሰቦች ዓይን እያወጣ በእንቅብ (ቁና) ይሰፍር እንደነበር ይነገራል።

ከዚህም ሌላ የራስ ቅላቸውን በአፍንጫቸው ትክክል እኩል ከሁለት እየከፈለ ወደ ገደል በመጣል ለአንበሳ ይሰጥ ነበር ይባላል። የራስ ቅል የመክፈሉን ሂደት የሚያከናውነው ግለሰብ ትንሽ ቢላሳት ወይም ቢዛነፍ እንኳ፤ በምትኩ የሱ የራሱ የራስ ቅል በሌላ ግለሰብ አማካይነት እኩል እንዲከፈል ይደረጋል (Molla 1994: 204)። ይህ ድርጊት ሲከናወንበት የነበረው አካባቢ ደግሞ ራስ አሊጋዝ የተወለደበትና የሚኖርበት፤ ከዚያም የዓይን አውጣው ጎጂ መኖሪያ የነበረ አካባቢ ነው። ይህ አካባቢ ሻሪያ መድኃኒዓለም በመባል ይታወቃል። ሻሪያ መድኃኒዓለም ከወልዲያ ሰሜን ምዕራብ[49] አቅጣጫ 20 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ላይ ይገኛል። በዚህ አካባቢ አሁንም ድረስ "ዓይን አውጣው ጎጂ ገደል" የሚባል ቦታ አለ። ይህንን ቦታ ለዚህ ጥናት አቅራቢ ወላጅ አባቱ በትክክል አሳይቶታል፤ ታሪኩንም ተርኮለታል። ሌሎች መረጃዎች በበኩላቸው ዓይን አውጣው ጎጂ ተቀናቃኞቹን ለማስፈራራት በእንቅብ (ቁና) የሚሰፍረው ዓይን፤ የሰው ዓይን ሳይሆን የበግ ዓይን እንደነበር ጽፈዋል። ድርጊቱም ጎጂ እንዳሰበው ሳይሆን፤ እንዲያውም ይበልጥ ጠላት እንዳፈራበት ይተርካሉ (Molla 1994: 204)።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ታሪካዊ ትውፊት የየጁ ወርሴህዎችን የተመለከተ ነው። በአንፃሩ የወርሂመኖ ኢማሞች ትውፊትም ተመሳሳይ ታሪክ አለው። ለአብነት የአባ ቡላ ዓለ ሊበን ትውፊት በአገሬው ህዝብ የሚተረከው እንደሚከተለው ነው።

> ዓለ አባ ቡላ ሚስቱ ብትመክንበት ወሎ ላይ ማንን ይዶላል ወዳጃ ውሴን ጅብሪልን። ውሴን ጅብሪል የወሬው ጠጅ ጠጥቶ ነው አለ፤ የዓለ አባ ቡላ ሚስት ወይዘሮ ባፋና ትባላለይ። ገረዲቱ ደሞ ገይቲ ናት። ሚስቱ እንድትወልድለት ነው ዱዓ ሊያስደርግ።

[49] ሞላ ትኩየ 1994፤ ገጽ፣ 204፤ ላይ ሻሪያ መድኃኔዓለም የሚባለው አካባቢ የሚገኘው ከወልዲያ ከተማ ምስራቅ አቅጣጫ 15 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ እንደሆነ ጽፈዋል። ነገር ግን ይህ አገላለጽ ትክክል አይደለም። ትክክለኛው ከላይ የተገለፀው የምዕራብ አቅጣጫና አካባቢ ነው።

ወሎ መቼም የዱዓ አገር በመሆኗ። ወይዘሮ ባፈና ቡን ኸተጠጣ በኋላ ሃልጋዋ ላይ ህዳ ተኛይ። ገረዲቱ (ባሪያይቱ) ገይቲ ግን ቡን እያፈላይ ውሴን ጅብሪልን ስትካድም አደረይ። ያቺ አልጋዋ ላይ ተኛይ ወይዘሮ ባፋና። ኸዚያ ውሴን ጅብሪል ምን አለ ሲፈርድ፤

ወይዘሮ ባፋና ኸደይ ተሸፍና፤

ልጅስ አየነ ኸገረድ፤

ስሙን ማን እንበለው መሐመድ፤

ያውም የነቢን ዲን እሚንድ።

ብሎ ይኸነን ቂስፋ አወጣ። ኸዚያ መሐመድ ዓሊ ኸገረዲቱ ኸገይቲ ተወለደ። ደሞ ለመሐመድ ዓሊ ሲፈርድ ውሴን ጅብሪል ምን አለ፤

ባዳራሽ ገብተህ በየልፍኙ ውጣ፤

የቀኘህን ትተህ የግራህን ጠጣ፤

የተከለከልክ እንደሁ እኔ በጉድ ልውጣ፤

ጊደር ትሰጣለህ ጥለህ እንዳትመጣ።

ብሎ ፈርዶለታል። ሸዋረጋሸን እንዲያገባ፤ የአፄ ምኒልክን ልጅ። ኸዚያ ኸምኒልክ ዘንዳ ማን ትሰጠዋለች ሸዋረጋሸ ምኒልክ። ማን ይወለዳል ሥኒን ሚካኤልና እያሱ ሚካኤል። እያሱም ያው ባክኖ ሞተ ነው የሚባለው። ሥኅን ሚካኤልም አስፋው ዓሊን አግብታ እትየ መነን አስፋውን ወለደይ፤ የኃይለሥላሴን ሚስት። ሁሴን ጅብሪል ሃዳ ምን አለ በኋላ ትንቢት ሲናገር፤

ኮርማው ተሐረርጌ ጊደሪቱ ተኛ

ወደፊት ይሆናል የሐባሻ ዳኛ፤ አለና፣

ሰባ አመቱ አልቆ ሰማኒያው ቲባ፤

የራስ መኮንን ልጅ አለበት መከራ፤ አለና፣

ግባ በቀላጤ-ውጣ-በቀላጤ፤

ከተፈሪ ወዳ አይባልም አጤ፤ አለና፣

እራሰ ከርዳዳ ከንፈረ-ዘርባባ

ኸቤተ መንግሥቱ ሰተት ብሎ ገባ፤

ብሎ ተነበየ ሁሴን ጅብሪል። ዝርዝሩ ብዙ ነው። እንግድህ አመጣጡ ወሎ የዱዓ አገር ናት እሚባለው፤ በዱዓ እንዲህ እያደረጉ እነ እራስንም፣ እነ ደጃማይንም ያራቧቸው በይህ ነው[50]።

[50] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ሚያዚያ 6 ቀን 2006 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ።

ባጠቃላይ ወሎ የሃይማኖት እምብርት የመሆኑን ያህል፤ በሌላ በኩል መተትም ቢሉ ጥንቆላ፤ ትንቢትም ቢሉ ንግርት፤ የተፈጥሮም ቢሉ የሰው ርኅራሄም ሆነ ጭካኔ ሞልቶ የተትረፈረፈበት መሬት ነው። ይህንንም እውነታ ከላይ ከተጠቀሱት አብነቶች መረዳት ይቻላል። ወሎ ውጥንቅጡ ብዙ ነው። ያም ሆኖ ወሎ "ገብስ" ነው። "ገብስ የእህል ንጉሥ!" እንዲሉ፤ የወሎ ሰውም እንዳደረጉት ይሆናል።

ለምሳሌ የወሎ ሰው የተረዱትን ያህል ይተረጎማል፤ ያጠኑትን ያህል ይተነተናል። የቀረቡትን ያህል ይታወቃል፤ የቀረቡትን ያህል ይዛመዳል። የቀረቡትን ያህል ይፈቀራል፤ የቀረቡትን ያህል "አርሂብ እንጂ!" ብሎ አብሮ ይበላል፤ አብሮ ይጠጣል። የቀረቡትን ያህል "ቤት ለእንግዳ!" ብሎ ያስተናግዳል። ልብን ከፍቶው የሰጡትን ያህል ሃጃ ይሞላል።[51]

ባንፃሩ የወሎ ሰው የተጣሉትን ያህል ይጣላል። የጠሉትን ያህልም እሱም ይጠላል። የጠላውን አካል ደግሞ "ዓይኑን አያሳየኝ!" እስከማለት ይደርሳል። የበደሉትን ያህል ቂም ይቋጥራል። ለዚህም "በጥቁር ደም" ብሂል ጠላቱን እስከመበቀል ይደርሳል።[52] የዚህ አይነቱ ትውፊት በወሎ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም መገለጫ የጋራ እሴት ነው።

ባጠቃላይ ከላይ እንደተገለጸው የጋብቻም ሆነ የሥልጣን ምንጩ የጀማው ባህል-ወግና ልማድ ወይም ትውፊት ነው። በዚህ መሠረት የጋብቻ ትስስርም ቢሉ የስልጣን፤ የሃይማኖት መቻቻልም ቢሉ የእትብት ዝምድና ምንጩ የወሎዬዎቹ ትንቢት፣ ዱዓና በረካ ነው። የወሎ ደጋጎች ከራማና ቱፍታ ነው። እንዲሁም አልፎ አልፎ ጥንቆላና መተት ቢጤም አለበት። ድግምትና ንግርትም አያጣውም። የፍቅርና የውበት ጉዳይም ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው (Mesfin 1991: 19)። እነዚህ እሴቶች በወሎ፤ የሙስሊሙ ወይም የክርስቲያኑ ብቻ ሳይሆኑ ባጠቃላይ የወሎዬዎች የጋራ እሴቶች ናቸው።

ከዚህም ሌላ ወሎዬዎች በዘመኑ ለጋብቻ ትስስር የሚመረጡባቸውም ሆነ፤ ለሥልጣን የሚበቁባቸው እንዲሁም ለአብሮነት ምክንያት የሆኗቸው ሌሎች የጋራ ትውፊቶችም ነበሯቸው። ከነዚህ ትውፊቶች መካከል አንዱ ከውኂ ጋር የተያያዘ የወሎዬዎች ትውፊት ነው። በዚህ ረገድ የየጁ መሳፍንቶች በ "ዋፋ" ውኂ ትውፊት ሲገለፁ፤ የወረሂመኖ ኢማሞች ደግሞ በፈረስ ላይ የውኂ ትውፊት ይታወቃሉ (Hussein 2001: 133–134; Fekadu 1973: 12; 1990: 33; Awoke 1996: 2)።

---

[51] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 15 ቀን 2006 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።
[52] አድኖ ተካየ፤ ቃለመጠይቅ፤ ሚያዚያ 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 02 ቀበሌ።

4.1.4፦ የፈረስና የዋፋ ውጊያ ትውፊቶች በወለኔ

የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚያስረዱት የወረሂመኖ ኢማሞች በፈረስ ላይ ውጊያ የተካኑ ነበሩ (Hussein 2001: 133)። ለአብነት የዚህ አይነቱ የውጊያ ብቃት ባህል ከወረሂመኖ ኢማሞች አንዱ ከነበሩት ከመሐመድ አባ ጅቦ[53] ይጀምራል። የመሐመድ አባ ጅቦ የተዋጊነት ብቃት "ይበላሃል፣ይበላሃል-ጅቦ፤ ይቆራርጥሃል!" በሚል ብሂል ይገለፃል (Fekadu 1973: 4)። የዚህ አይነቱ ብሂል አሁንም ድረስ በወለኔ ከጀግንነት ወይም ከጦርነት ጋር የተያያዘ ጭፈራ መከወኛ ስንኝ ሆኖ ያገለግላል። እንዲሁም የወለኔ ተዋጊዎች የሚጠሩት በፈረሶቻቸው ስም ነበር። ለአብነት አባ ጅቦ፣ አባ ጅሩ፣ አባ ሜጃ፣አባ ቡላ፣ አባ ዋጠው፣ አባ ጀበል...ወዘተ የሚሉት መጠሪያዎች ከፈረሶች ጋር የተገናኙ ናቸው (Hussein 2001፡119)።

የዚህ አይነቱ በፈረስ ስም የመጠራቱ ባህል የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች መጠሪያም እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። ነገር ግን ልማዱን ማን ከማን እንደወሰደና ከየትኛው አካባቢ እንደተቀዳ በግልጽ የሚታወቅ ነገር ያለ አይመስልም። ምናልባት ከወለኔ ቢሆንስ? ጥያቄው አጠቃላይ ትውፊቱን ጨምሮ አንድ የፎክሎር የጥናት ርዕስ ሊሆን እንደሚችል የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል፡

ከወረሂመኖ የተዋጊነት ባህል ጋር በተገናኘ ጥናቶች እንደሚያስረዱት አፄ ቴዎድሮስ ከተቀናቃኞቻቸው ጋር ባደረጓቸው የተለያዩ ጦርነቶች ሙሉ በሙሉ ሳያስገብሯቸው ለህልፈተ ሞት ከበቁባቸው አጋጣሚዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ከወረሂመኖ ኢማሞች ጋር ያደረጓቸው ውጊያዎች ናቸው። በተለይ የወርቂትና የመስታዋት ጉዳይ ለአብነት የሚጠቀስ ክስተት ነው። እነዚህ ሁለት ሴቶች አፄ ቴዎድሮስን መቅደላ አፋፍ ላይ እንደወጡ እግራቸው መሬት ሳይረግጥ ተራራ ላይ ተንጠልጥለው እዚያው እንዲቀሩ አድርገዋቸዋል።

አፄ ቴዎድሮስ በታሪካቸው "ተደፈሩ" ሊባል የሚችለው በሦስት ሴቶች አማካይነት ነው። ይህም አንድ በሚስታቸው፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በወርቂትና በመስታዋት ነው። ከሚስታቸው ጉዳይ ጋር በተገናኘ አፄ ቴዎድሮስ ለሚወዱት ለገብርየ ሲናገሩ "ገብርየ! አንተ የምታውቀኝ ታጥቄ! እሷ የምታውቀኝ አውልቄ !" አሉት ይባላል።

የወርቂትና የመስታዋት ጉዳይ ግን "ታጥቀውም" ሳይሳካላቸው ቀርቷል። ለምሳሌ አፄ ቴዎድሮስ ባካሄዷቸው ጦርነቶች ከተቀናቃኞቻቸው ጋር ለመደራደር ሽማግሌ የላኩበት

[53] "አባ ጅቦ" የግለሰቡ ፈረስ መጠሪያ ስም ነው (Hussien 2001: 119)።

አጋጣሚ ስለመኖሩ በታሪክ ድርሳናት እስካሁን ተጠቅሶ አይገኝም። ነገር ግን ከወርቂት ጋር ለመደራደር (ባይሳካላቸውም) ከሁለት ጊዜ በላይ ሙከራ አድርገዋል (Fekadu 1973: 20-23)። አፄ ምኒልክም ቢሆኑ የመስታዋት ጭዳ ሊሆኑ በመሸሻ ሰይፉ አማካይነት ከጭንቅ የተረፉት ለጥቂት ነው (እንዳላይኛው። 33)። ባጠቃላይ የወርሂመኖ ኢማሞች የፈረስ ላይ የውጊያ ባህል በዚያው አካባቢ ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፤ ከመተማ እስከ አድዋ የዘለቀ ነበር። ለዚህ ደግሞ የመሐመድ ዓሊ (ንጉሥ ሚካኤል) ተሳትፎ ለአብነት ይጠቀሳል። ይህም ለወሎዬዎች ኢትዮጵያ የጋራ መተሳሰሪያ ክር እና መገናኛ ድልድያቸው መሆኗን የሚያሳይ ምሳሌ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ የወሎዬዎች የአብሮነት መገለጫ ምልክታቸው ናት። የማንነት መለያ ምልክት ሰንደቃቸው ናት። የዚህ አይነቱ የአብሮነት ስሜት ደግሞ የወሎዬዎች የእርስ በርስ መተሳሰሪያ ክር እና መገናኛ ድልድይ ነው።

የየጁ መሳፍንቶች መገለጫ ደግሞ "ዋፋ ውጊያ" የሚባለው ትውፊት ነው። ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የዋፋ ውጊያ ትውፊት በየጁ ከገነተ-ልዑሉ ጳጳስ ርግማን ጋር የተያያዘ ነው። ምክንያቱም በየጁ ጣአታትን የሚያመልኩና በአስማታቸው የሚመኩ አስማተኞችና መተተኞች እንደነበሩ ይነገራል። በመሆኑም አለቃ ታየ እንደፃፉት እነዚህ አስማተኞች በጳጳሱ ላይ በሰሩት ተንኮል ምክንያት ጳጳሱ "የዚህ አገር ሰውም ለእኔ ስም ማክፋት ብሎ፤ ሰውን ገድሎ፣ እጁን ቆርጦ፣ አናቱን ፈጥፍጦ በሰው እንደተጫወተ የእጁን ይስጠው፤ ሁል ጊዜ ደም ይፍሰስበት፤ እርስ በርሱ ይተላለቅበት፤ ጳጳስም አይቀመጥበት፤" ብለው ረገሙት (ታየ፡1958 ዓ.ም. 50)። በዚህም "ቀድሞ የነበረው የየጁ መጠሪያ ‹ግነቴ› መባሉ ቀርቶ አገሩ የጁ ተባለ። ከዚህ በኋላም በየጁ እርስ በርሱ በዋፋ ውጊያ [ሰበብ] ሁልጊዜ የሰው ደም የሚፈስበትና በከንቱ ነፍስ የሚወድቅበት የተረገመ አገር ሆነ"። በማለት አለቃ ታየ ጽፈዋል (እንደላይኛው፤ 51)።

የዋፋ ውጊያ ትውፊት በየጁ ከመነሻው ለሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ሲባል የሚከወን ተግባር ነበር (Fekadu 1990:33-36)። አንደኛው ምክንያት የየጁ አድባር ናት። ምክንያቱም በየጁ አድባር አማካይነት አዝመራው ያፈራል፤ ከብቱ ይወልዳል፤ የአካባቢው ሰላምና ደህንነት ይረጋገጣል ተብሎ ይታመናል። እናም ይህ በረከት እንዲረጋገጥ በዋፋ ውጊያ አማካይነት ለየጁ አድባር የሰው ደም ማፍሰስ ግድ ይላል። ለዚህ ግብር ሲባልም የአካባቢው ማኅበረሰብ ወቅት ጠብቆ ጎራ ለይቶ ውጊያ ያካሂዳል። በዚህም ቀኑ የደረሰበት ግለሰብ ደም ፈስሶ ለየጁ አድባር መስዋዕት ይቀርባል። ሟቹ ለማኅበረሰቡ ትውፊት ሲባል መስዋዕት (ጭዳ) እንደሆነ ሁሉ፤ ገዳዩም ግለሰብ ለዚሁ ዓላማ መሳካት የፈፀመው ተግባር በመሆኑ በሚች ወገን በኩል

ቂም አይቋጠርበትም፡፡ ክስም ሆነ ወቀሳ አይሰነዘርበትም፡፡ ከገዳይ የሚጠበቀው ግደታ መግደሉን ሳይደብቅ ለሚች ቤተሰብ መግለፅ ብቻ ነው፡፡ የዋፋ ውጊያ በየጁ በዘመኑ ምን አይነት ገጽታ እንደነበረው አለቃ ታየ የገለፁት እንደሚከተለው ነው፡፡

> የየጁ ሰዎች ይህ መርገም ስለፀናባቸው አገር ላትገዙበት ጠጅ ላትጠጡበት ቀሚስ ላትለብሱበት ስም ላታወጡበት ስለምን እርስ በርሳችሁ በከንቱ ትጋደላላችሁና ወገን ከወገኑ ይጋባል? ቢልዋቸው ቆሌይቱ ደም ትወዳለችና ዋፋ ውጊያ ሲቀር ካፋፍ ላይ ዘልቃ እሪ ትላለች፡፡ የዚያን ጊዜ ሰው ሁሉ ጋሻ ጦሩን እየያዘ ከያገሩ ይወጣልና በየመልካው ይወርዳል፡፡ በያላ ወንዝ፣ በጥቁር ውኃ፣ በሸሊ፣ በሚሌ እየወረደ ዋፋ ይዋጋል ይላሉ፡፡...ያገሩ ቆሌ የሰው ደም የለመደች ናትና ዋፋ ውጊያ ሲቋረጥ ከሰማይ ዝናብ ያንስብናል፣ ብናርስም እህሉ ይጠፋብናል፣ አገራችንም ይራብብናል፣ በሽታም ይነሳብናል፤ ዋፋ በተዋጋን ጊዜ ግን ዝናብ በበረከት ይወርዳልና፣ እህልም ይወጣል አገራችንም ጥጋብ፣ ጤናማም፣ ይሆናል ይላሉ (ታየ፣ 1958 ዓ.ም.፤ 52)

ሁለተኛው የዋፋ ውጊያ ምክንያት ደግሞ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፋይዳው ነው፡፡[54] በዚህም የየጁ ሰው ከአፋሮች ጋር ወቅት ጠብቆ፣ ቀን ቆርጦ፣ የጎበዝ አለቃ ወይም አለንጋ ጣይ መርጦ፣ አስማተኛ ወይም ጠጠር ጣይ አስከትሎ ውጊያ ያካሂድ ነበር (Fekadu 1990: 35)፡፡ በዚህ ትውፊት መሠረት ከማኅበራዊ ፋይዳው አንፃር ሃዳል [አፋር] የገደለ ማኅበራዊ ደረጃው እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ክብር ደግሞ የተለያዩ መገለጫዎች ነበሩት፡፡ ለምሳሌ የገዳዩ ክብር ከራሱ አልፎ በረከቱ ለሚስቱ፣ ለቀሪ ቤተሰቦቹና ለቅርብ ጎረቤቶቹ ጭምር ሁሉ ይተርፍ ነበር፡፡

ከኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ አንፃር ደግሞ በውጊያ ወቅት የሚገኘው የከብትና የቁሳቁስ ምርኮ ነው፡፡ ባንፃሩ ለአፋሩም እንዲሁ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይፋው ተመሳሳይ ነው (እንደላይኛው፤ 33-41)፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ለየጁ አድባርም ሆነ ለአፋር ዘመቻ ዋፋ ውጊያ የሚካሄደው አዝማች ተመርጦ፣ ቀን ተቆርጦ፣ ለውጊያ የሚያነሳሳ "አረሆ" ተዘጋጅቶ ነው፡፡ በዘመኑ የነበረውን የዚህ አይነቱን ባህል አሁንም ድረስ የአካባቢው ማኅበረሰብ ያስታውሰዋል፡፡ ለአብነት የአበጋር ማዱን ትውስታ እንደሚከተለው እንጠቅሳለን፡፡

> በዋፋ ውጊያ የሚጠቀሱ ብዙ ጀግኖች ነበሩ፡፡ እነ መሸሻ ወንዴ፣ እነ አፍራሳ ወንዴ፣ እነ ጃሌ ጎበና፣ እነ ዮሱፍ ዮዶሪ፣ እነ ዓሊ ነጎደ፣ እነ ቄድ ያየ በሬ፣ እነ አለነ አጉረው፣ እነ ፈቴፋ አለፊ፣ እነ ደበላ አባ ጫጉ፣ እሚባሉ ነበሩ ይባላል፡፡ አነይህ እንግድህ ዋኖቹ አንጋፋ ጀግና የተባሉቱ ናቸው፡፡ አረሆይቱ ምን ትል ነበረ ይባላል፤

---

[54] ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ እንደሚሉት የዋፋ ውጊያ በህል ትክክለኛው ምክንያት የየጁ ሰው ወቅት እየጠበቀ ከአፋሮች ጋር ሲያካሂደው የነበረው ውጊያ ነው፡፡ ከዚያ ውጭ አለቃ ታየ የገፉትም ሆነ በአፈታሪክ እንደሚነገረው በየጁ ለቆሌ ተብሎ ውጊያ የሚካሄድበት ባህል አልነበረም (ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፤ ቃለ-መጠይቃ፤ ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲ- 04 ቀበሌ)፡፡

የተዋጋም አይሞት የሸሸም አይድን፤

ዙረህ ተመልከተው አለነ አጉረውን፤ ጭድ ያየ በሬን።

እነ አብደላ ካፊ ሞታቸው ይወራል፤

እንግድህ አገሩ በዘንግ ይወረራል[55]።

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚተርኩትም ሆነ ጥናቶች እንደሚያስረዱት የዋፋ ውጊያ ባህል በየጁ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ መገለጫ እሴት ነው (Fekadu 1990: 36)። ለምሳሌ ከሃይማኖት አባቶች አንፃር በከንቱ የሚፈሰውን የሰው ደም ለማስቀረት የወልዮቹ ድርሻ ከፍተኛ ነበር (Hussein 2001: 135)። እንዲሁም ትውፊቱ የወንድነት ወይም የጀግንነት መስፈርት እና የዝናና ክብር መጎናፀፊያ ብሂል ስለነበር ባህሉ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ መገለጫ እሴት ነው። በምርኮ የሚገኘው ነገርም ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ የጋራ ነው። በዚህ መሰረት የዋፋ ውጊያ ከሃይማኖት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ስላልነበረው ሙሉ በሙሉ ሙስሊም የሆነውን አፋሩን ለመውጋት ወደ አካባቢው የሚሄደው ሙስሊሙም ክርስቲያኑም በጋራ ነው። በዚህ ወቅት የጎበዝ አለቃ ሆኖ የሚያዋጋው ደግሞ ሙስሊሙ ወይ ክርስቲያኑ ሊሆን ይችላል።

በሌላ በኩል የዋፋ ውጊያ ትውፊት የአካባቢው ማኅበረሰብ ለዘመናት የዳበረ የውጊያ ባህል ወይም ስልት ለማካበት እንዳስቻለው ይነገራል። በዚህም "የጁ ደረቱን ለጦር እግሩን ለጠጠር!" እየተባለ ይነገርለታል (Fekadu 1990: 51)። ጥናቶች እንደሚያስረዱት ይህ የውጊያ ባህል ለየጁ መሳፍንቶች የስልጣን ምንጭ እና የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት ተደርጎ ይጠቀሳል።[56] ለምሳሌ ራስ ዓሊ ጓንጉልም ሆነ ሌሎቹ የየጁ ወረሴህዎች ወደ ጎንደር ቤተ-መንግሥት በመዝለቅ ራስ ቢት ወደድ ወይም ርዕሰ መኳንንት የሚለውን ማዕረግ ያጎናፀፋቸው ይኸው የየጁ የዋፋ ውጊያ ትውፊት ነው (ታየ፤ 1958 ዓ.ም.)።

በዚህ የውጊያ ትውፊታቸው የየጁ ወረሴህዎች በጎንደር ነገሥታት ዘንድ ከሌሎች በተለየ የተወደዱ፣ የተከበሩ፣ በቤተ መንግሥቱ ዘንድ ግርማ ሞገስን ያገኙ እንደነበሩ ጥናቶች

---

[55] አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 4 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ።

[56] የታሪክ መፃሕፍት እንደሚያስረዱት የዘመነ መሳፍንት ታሪክ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ሁኔታ በጦርነት ተጀምሮ በጦረነት የተደመደመ ታሪክ ነው። የወረሂመኖ ኢማሞች ታሪክም ቢሆን ከዘመነ መሳፍንቶች ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ነው። ከዘመኑ ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው በወቅቱ ውጊያ በየጁ ባህል ነው፤ ውጊያ በየጁ ሱስ ነው፤ ውጊያ በየጁ ሥራ ነው፤ ባጠቃላይ በዚያን ዘመን በየጁ በሆነ ባልሆነው መዋጋት ነው፤ የዚህ ሁሉ ዓላማ ደግሞ ሞትን ለመጥራት ነው። በዚህ የተነሳ በዘመኑ የፈሰሰው የሰው ደም "የውሻ ደም" የሚባል አይነት ነው።

ይገልፃሉ (Awoke 1996: 4-5):: ይህም ከአባ ሴሩ ጓንጉል ይጀምራል፡፡ አለቃ ታየ፤ "አባ ሴሩ ጓንጉል መልኩ እጅግ ያማረ፣ የተዋበ ነበር:: ኃይለኛ ጀግና ፈረሰኛም ሆነ፡፡ ጀግንነቱና ኃይሉም በቤተ-መንግሥት የታወቀ ሆነ" በማለት ይገልጹታል (ታየ፣ 1958 ዓ.ም.፤ 49)፡፡ በመጨረሻ ግን "አያያዙን አይቶ..." እንዲሉ የጓንጉል አባ ሴሩ ልጅ ታላቁ ራስ ዓሊ ለጎንደር ፍፃሜ መንግስት ምክንያት ሆነ፡፡ በዚህም ራስ ዓሊ ጓንጉል አፄ ተክለጊዮርጊስን በጌምድር ድረስ ዘምቶ አፈረ-ዋናት፤ መደብ በሚባል ቦታ ላይ ድል በመምታት የየጁ መሳፍንቶች የአስተዳደር ዘይቤ አሀዱ ብሎ እንዲጀምር ምክንያት ሆነ (Bairu 1987: 628; Wudu 1995: 102)::

በዋፋ ውጊያ የጦር ልምድ መነሻነት ጎንደር ዘልቆ የሥልጣን ባለቤት የሆነው የየጁ ወርሴህ ታሪክ በበኩሉ ሌላ ትውፊት ይወልዳል፡፡ ይህ ትውፊት የየጁ ወረሴህ የርሥት ስሪት ትውፊት ወይም ዓሊ ዘማች የመሬት ስሪት ትውፊት በመባል ይታወቃል (Fekakdu 1990: Molla 1984; Daniel 2009; Mengistu 1997)፡፡ ይህ ትውፊት በበኩሉ በወሎ "በርስትና በሚስት የለም ዋዛ!" የሚለውን የወሎዬዎች አባባል ጨምሮ፤ ከወሎዬዎች ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ሕይወት መስተጋብር ወይም የእርስ በርስ ግንኙነት እና ባጠቃላይ ከወሎዬዎች ባህላዊና ማኅበራዊ አውድ ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው፡፡ ይህም በወሎ የክርስቲያን ሙስሊሙ የጋራ መገለጫ ትውፊት ነው፡፡

4.1.5 ፦የርስት ትውፊት በወሎ

የርስት ትውፊት ጠንሳሽ በየጁ በዋናነት ታላቁ ራስ ዓሊ ጓንጉል እንደሆነ ጥናቶች ይገልፃሉ (Fekadu 1990: 71)፡፡ የወረሂመኖ ኢማሞችም በወሎ የበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል (Mengistu 1997: 40)፡፡ እነዚህ ጥናቶች እንደሚገልጹት በተለይ በየጁ ርስት ለተሰኘው ባህል ምክንያቱ ራስ ዓሊ ጓንጉል ከአፄ ተክለጊዮርጊስ ጋር ያካሄደው ጦርነት ነው፡፡ በዚህ መነሻ ከዚህ ዘመቻ በኋላ ራስ ዓሊ ጓንጉል በወቅቱ አብረውት ለተዋጉትም ሆነ በተለያየ ምክንያት ከመንገድ ለተመለሱት (በተለይ በዋድላ ደላንታ ብርድ ምክንያት) ዘማቾች የመሬት ጉርሻና አጠቃላይ የመሬት ስሪት እንዳደረገ ጥናቶች ይጠቁማሉ (Molla 1984:2)::

ይህ የመሬት ጉርሻ ወይም ስሪት ዓሊ ዘማች መሬት ወይም አፅመ ርስት በመባል ይታወቃል፡፡ እነዚህ የራስ ዓሊ ወታደሮች የሚመለመሉት ደግሞ በዋናነት ከየጁ ሆኖ፤ ከጉባላፍቶና ከሐብሩ ወረዳ ነዋሪዎች መካከል እንደነበር ይነገራል፡፡ በተለይ ሙሬ ሶዶማ፣

መንዩ እና ጋፍራ የሚባሉት አካባቢዎች ለአብነት ይጠቀሳሉ (Molla 1973: 3):: የዓለ ዘማች የመሬት ስሪት ሃይማኖትን ወይም ብሔርን መሠረት ያደረገ አልነበረም:: ባንፃሩ ዋናው መመዘኛ ለዘመቻ በተጠሩ ጊዜ ዝግጁ ሆኖ መገኘት ብቻ ነው:: ይህ ሂደት ከታላቁ ራስ ዓለ በኋላም ቀጥሎ በራስ አሊጋዝ፣ በራስ ጉግሳ፣ በራስ ዶሪ፣ በራስ ማርየ፣ በራስ ይማም፣ በታናሹ ራስ ዓለ እና ከዚያ በኋላም እስከ 1970ዎቹ መጀመሪያ ድረስ በነበሩት የአካባቢው አስተዳዳሪዎች መጠሪያ ስሙን እየቀያየረ የቀጠለ ክስተት ነበር (Fekadu 1990; Molla 1984; Daniel 2009)::

በዚህ የመሬት ስሪት ትውፊት መሰረት ከወሎዬዎች ማኅበራዊ ሕይወት ጋር የተያያዙ በርካታ ሁነቶች ተከስተው አልፈዋል:: ለምሳሌ ቀጥለው የተዘረዘሩት ከወሎ መሬትና ከወሎዬዎች ጋር የተያያዙ ትውፊቶች በወሎ በተለይ በየጁ በተግባር የተፈፀሙ ሁነቶች ናቸው:: እነዚህ ሁነቶች ደግሞ የወሎዬዎች የጋራ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ አሻራ የታተመባቸው ጉዳዮች ናቸው:: በዚህም ከፎክሎር ሣይንስ አንፃር የጀማው ህዝብ አጠቃላይ ሥረ-መሠረት ወይም አውድ እነዚህ ሁነቶች ስለሆኑ ማንነቱም መንጭቶ የሚቀዳው ከነዚህ ሁነቶች ውስጥ ነው::

በሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ቢገመትም ነገር ግን በወሎ በተለይ በየጁ ከመሬት ጋር የተያያዙ ሁነቶች እጅግ በርካታ ነበሩ:: ለምሳሌ በወሎ፤ ዓለ ዘማች መሬት፣ ዓለ ገባር መሬት፣ አለንጋ መሬት፣ የፈረሰኛ መሬት፣ ቃጨ ዘማች መሬት፣ ማደሪያ መሬት፣ የግብር ፍራሽ መሬት፣ የግብር መሬት፣ ግብረ-ጠል መሬት፣ የሞፈር ማጋደሚያ መሬት፣ የጭቅነት መሬት፣ የወለድ አገድ መሬት፣ የገና መምቻ መሬት፣ የነጭ ለባሽ መሬት፣ የጡር መሬት፣ የሴሩ ቀመስ መሬት፣ ያፈላማ መሬት፣ የክርክር መሬት፣ የባኒ መሬት፣ የእኩል አራሽ መሬት፣ የእርቦ አራሽ መሬት፣ የሲሶ አራሽ መሬት፣ የመጋዞ መሬት፣ የቀለብ ተመላሽ መሬት፣ የቀለብ ለውጥ መሬት፣ የጠፍ መሬት እና ሌሎች፤ ርስት፣ አፅመ-ርስት፣ ቤተ-ርስት፣ ርስተ-ጉልት፣ ሲሶ ጉልት፣ ጉልት፣ ዓለ ሁዳድ፣ የሻለቃ ሁዳድ፣ የፈረንጅ ሁዳድ፣ የመንግሥት ሁዳድ፣...ወዘተ የተሰኙት የመሬት ስሪቶች ከጀማው ህዝብና ከሊሂቃኑ ጋር እጅግ የተሳሰረ ታሪክ ነበራቸው::

ከሃይማኖቶቹ አንፃር ደግሞ፤ በክርስትናው በኩል:-የሰሞን መሬት፣ የሰሞን ገባር መሬት፣ የቅስና መሬት፣ የድቁና መሬት፣ የድብትርና መሬት፣ የግብዝና መሬት እና ሌሎች የሚጠቀሱ ሲሆን፤ በእስልምናው በኩል ደግሞ፤ የሼህ መሬት፣ የአበጋር መሬት፣ የናኢባ መሬት፣ የቃዲ

መሬት፣ የዋቅፍ መሬት እና ፍርቅ የተሰኙት የይዞታ ስያሜዎች ተጠቃሽ አብነቶች ናቸው። ከነዚህ ይዞታዎች ጋር ተያይዞ ለሚከፈል ግብር ደግሞ፤ የደም ግብር፣ የማር ግብር፣ የጨው ግብር፣ የቆሎ ግብር፣ የሞፈር ማጋደሚያ (የማባበያ) ግብር፣ አስራት፣ መጋዘ፣ የሼማ እና የኩታ ግብር የሚል ስያሜ ነበራቸው። ከጀማው ህዝብ አንፃርም እኩል አራሽ፣ ርቦ አራሽ፣ ሲሶ አራሽ፣ የቀንጃ መሬት አራሽ፣ የሞፈር ዘመት አራሽ፣ ጠሰኛና ጤሰኛነት የሚሉት ስያሜዎች ይገኙባቸዋል። በሊሂቃኑ በኩል ደግሞ፤ በየዘመኑ የነበረውን የመንግሥት ሥያሜ ጨምሮ፤ እንደራሴዎች፣ ምስለኔዎች፣ ጭቃ ሹሞች፣ ነጭ ለባሾች፣ መልከኞች፣ አንጋቾች፣ የጎበዝ አለቆች፣ የቤተ-ርስት ሹም፣ የርስት አለቃ፣ ትክለኛ፣ጉልተኛ፣ አቅኝ፣ አቅኝ አባት፣ ባላባት፣ ገበዝ፣ አጥቢያ ዳኛ፣ ሹም፣ ወኪል፣ እና የትክለኛ ሹም በሚል ስያሜ ይጠሩ ነበር[57]

ከላይ እንደተጠቀሰው የወሎ ሰው ታሪካዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረቱ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ ሕይወቱና ባህላዊ ሥርአቱ ከነዚህ የርስት ትውፊቶች ጋር የተሳሰረ ነበር። በዚህ ሂደት ውስጥ ወሎዬዎች ክርስቲያን ሙስሊም ሳይሉ በጋራ ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፈዋል። በጋራ ሀዘንና ደስታ ተካፍለዋል። በዚያ ምስቅልቅሉ በበዛበት የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ የሁለቱም ሃይማኖቶች እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦች፤

አይዞህ አብሽር ብሎ ወሎ ከመቀረኝ፤
ክፉም አያገኘኝ መልካምም አይርቀኝ።

በሚለው ብሂላቸው እየተመሩ በክፉም ሆነ በደጉ ሳይነጣጠሉ በአንድነት ዛሬ እሚገኙበት ዘመን ላይ ደርሰዋል። ለምሳሌ የሁለቱ ሃይማኖቶች እምነት ተከታዮች በየጁ ከላይ ከተጠቀሱት የርስት ትውፊቶች ጋር በተያያዘ በጋራ ያሳለፏቸው የማኅበራዊ ሕይወት ውጣ ውረዶች ምን አይነት ገጽታ እንደነበራቸው ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሱት ነትቦች ማሳያ አብነቶች ናቸው።

4.1.6፦ የመብት ጥያቄ ትውፊት በወሎ

በየጁ ከመሬት ወይም ከርስት ጋር በተያያዘ ወሎዬዎች ከሊሂቃኑና ከቤተ-እምነቶቹ ጋር የተገናኙ በርካታ ትውፊቶች አሏቸው። ከነዚህ ትውፊቶች መካከል አንዱ ከሰሞን መሬት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው። ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በየጁ ከቤተክርስቲያን ጋር በተገናኘ

---

[57] የገርገሮቹን አጠቃላይ ሁኔታና ትርጉም ወይም ፍች የበለጠ ለመረዳት፤
i፦ Fekadu Begna; 1990: 225-235፤
ii፦ Daniel Dejene; 2009: xii፤ ይመልከቱ።

ከጓንጉል አባ ሴሩ እና ከልጃቸው ከታላቁ ራስ ዓሊ በመቀጠል አፄ ዮሐንስ አራተኛን ጨምሮ፤ የሚጠቀሱ ሌሎች ሁለት ሊሂቃን፤ ራስ አሊጋዝ እና ራስ ወሌ ብጡል ናቸው (Molla 1973: 4)። ራስ ወሌ ብጡል በየጁ ከብዙሃኑ ላይ (በተለይ ከሙስሊሙ) መሬት ቆርሰው ለወልዲያ ገብርኤል፣ ለመርጠ ኢየሱስ እና ለመርጠ ሚካኤል የሰሞን መሬት እንደሰሩ ይነገራል (እንደላይኛው፤ 4-5)። በዚህም የአካባቢው ማኅበረሰብ ቅር በመሰኘቱ ራስ ወሌ ብጡል በ1910 ሸዋ-አንኮበር ተወስደው በታሰሩ ጊዜ፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ፤

የመርጠው ኢየሱስ፣
የመርጠው ሚካኤል፣
የወልዲያው ገብርኤል፣
እንደ መኳንንቱ ሹም ሽር ተቃዳችሁ፣
እንደ ወታደሩ ቀለብ ተሰፍራችሁ፣
እስኪ ወሌን አምጡ ይታይ ጉልበታችሁ (Fekadu 1990: 58)።

በማለት ተሳልቆባቸዋል። ስላቁ "ወሌ ከኛ መሬት ቀምቶ ለናንተ ሰጥቷችሁ ሳለ፤ እናንተ ግን ከእስር አላዳናችሁትም!" ማለት ይሆናል። ይህም ሆኖ ራስ ወሌ ብጡል ከላይ ለተጠቀሱት ቤተ-ክርስቲያናት አድልተው ሙስሊሞቹን ቅር ከማሰኘታቸው በስተቀር በየጁ በጣም ተወዳጅ አስተዳዳሪ እንነደበሩ ይነገራል። በመሆኑም ከእስር ተፈተው ወደ አካባቢው እንዲመለሱ ብዙዎች ይመኙ እንደነበር ይነገራል። በዚህም ራስ ወሌ ብጡል አንኮበር ተወስደው በታሰሩ ጊዜ የአካባቢው ህዝብ፤

በእየሌ[58] ሸምቼ በላሁኝ ሦስት ወር
በሞንሚናው ጌታ በወሌ ብጡል

በብር ሸምቼ ባነሳው ቀለለኝ
ወሌ ወሌ እንዳልኩኝ ልሞት ነው መሰለኝ

ኢያችሁት ብያ ወሌ ቅንነቱ
ተመልሶ ገባ በሰባት አመቱ

[58] "እየሌ" ማለት በዘመኑ አጠራር "ስሙኒ ወይም ሃያ አምስት ሳንቲም" ማለት ነው። (Molla Tikuye 1984: 6).

በማለት ስሜቱን በፎክሎር አማካይነት ይገልጽ እንደነበር ይነገራል (Molla 1984: 6-7)። ከላይ ከተገለጹት ከነዚህ ሁለት ተቃራኒ ሃሳቦች መረዳት የሚቻለው መሰረታዊ ነጥብ የዎሎዬዎች ማኅበራዊ ሕይዎትና የፖለቲካ ሊሂቃኑ ግንኙነት ምንአይነት ገጽታ ወይም ግንኙነት እንደነበራቸው ነው። ግንኙነቱ ደግሞ ከዎሎዬዎች ጋር ብቻም ሳይሆን ሃይማኖቶቹንም ይጨምራል። በተለይ የሰሞን መሬት ትውፊት ከክርስቲያኖቹ በዘለለ ከሙስሊሞቹ ጋር ሳይቀር የጠበቀ ቁርኝት ነበረው። ለዚህም የወሎ ሙስሊም ለቤተ ክርስቲያን "ማስቀደሻ ስንዴ" ከመገበር አንስቶ "ገበዝ" እስከመሆን የደረሰበት አጋጣሚ ብዙ ነው (Hussein 2001: 170)። ይህንን እውነታ ውዱ ጣፈጠ፤ ታደሰ ታምራትን ጠቅሰው እንደሚከተለው ገልፀውታል።

> በ1950ዎቹ መጨረሻ አካባቢ፣ ፕሮፌሰር ታደሰ ለዶክትሬት ጥናታቸው ከለንደን ወደ ኢትዮጵያ ይመጡና ለመስክ ጥናት ወሎ ክፍለ ሀገር ይሄዳሉ። በዚህ ምክንያት ስሙን አሁን የማላስታውሰውን ትልቅ ደብር ይጎበኛሉ። ይህንን ደብር ለመጎብኘት እንደሄዱ ደብሩ ያለውን መጻሕፍት ለማየት አልቻሉም። ምክንያቱም የዚህን ደብር የእቃ ቤት ቁልፍ የሚይዘው ሰው በአካባቢው አልነበረም። ስለዚህም ለመጠበቅ ይገደዳሉ። ቁልፍ ያዡ ተፈልጎ ሲመጣ ቁልፉን ከፈተና ቁጭ ብለው ሲጠብቁ ለነበሩት ቄስ ይግቡ ይላቸዋል። ፕሮፌሰር ታደሰም አንተ ግባና መጻሕፍቱን አሳየን እንጂ ብለው ይጠይቁታል። ጌታዬ እኔ መግባት አልችልም። ሙስሊም ነኝ ይላቸዋል። በጉዳዩ የዚያ ጊዜ ታደሰ ግራ ይጋባሉ። ምክንያቱም ከዚህ ቀደም የቤተ ክርስቲያን እቃ ግምጃ ቤት ቁልፍ ያዥና የንብረት ጠባቂ የሆነ ሙስሊም ሰው አጋጥሟቸው አያውቅምና። በኋላ እንደተረዱትም፣ ቁልፍ ያዡ ሙስሊም ለደብሩ የመጀመሪያው አገልጋይ እንዳልሆነና ከእሱ በፊት አባቱ ቁልፍ ያዥ እንደበሩና የአባቱን ሥራ በመውረስ ለብዙ ጊዜ በሥራው ላይ እንደነበር ይገልጽላቸዋል። ይህ የሆነበትም በጃቸው ያለው መሬት በጊዜው የሰሞን መሬት የነበረና ያንንም መሬት የሚጠቀም ሰው ቤተ ክርስቲያንን የማገልገል ግዴታ ስላለበት ነው። ወይ ራሱ ያገለግላል ወይ ቀጥሮ ሌላ ሰው (ቶፋ) እንዲያገለግል ያደርጋል (ውዱ፤ 2004 ዓ.ም፤ 203-204)።

በወሎ በተለይ በየጁ ከርስት ጋር በተያያዘ የሚጠቀሰው ሌላው ትውፊት ደግሞ የርስት ክርክር ወይም እሰጥ አገባ አለያም በልሃ-ልበልሃ በመባል የሚታወቀው ትውፊት ነው። መግት ወይም ክርክር በወሎ ሰፊ ሥረ-መሠረት ያለው ትውፊት ነው። ጥናቶች እንደሚገልጹት የመግቱ ሂደት "ግብር ለገበረ፤ ጦር ለወረወረ!" የሚለውን ብሂል ጨምሮ "ወፍ ጭጭ፤ ሰማይ ብልጭ ሲል የያዝኩት፤ ከጥንት ከአባቶቼ ያገኘሁት መሬት ነው!" በሚል የመከራከሪያ ነጥብ ተጀምሮ መሬቱ የዓሊ ዘማች መሬቴ ነው። በዓሊ፣ በአሊጋዝ፣ በጉግሳ፣ በማርየ፣ በይማም፣ በዶሪ፣ በቴዎድሮስ፣ በዮሐንስ፣ በምኒልክ፤ የገበርኩበት፣ የዘመትኩበት መሬቴ ነው። ለዚህም ማስረጃ እቆጥራለሁ። ለኔ ይገባኛል ባይ ካለም በቅሎ እሰጥ፣ ወይም ማር እሰጥ፣ ወይም ፈረስ እሰጥ...ወዘተ! እያሉ ይሟገቱ ነበር (Molla 1984: 14)።

ነገር ግን የወሎ ሰው እየተሟገተ አደባባይ የመዋሉን ያህል እውነተኛ ፍትሕ የማግኘት እድሉ ከመርፌ ቀዳዳ የጠበበ እንደነበር ይነገራል። ምክንያቱም የፖለቲካ ሊሂቃኑ የፍርድ ሚዛን ለብዙሃኑ ወይም እውነትን ለያዘ ሳይሆን ለሊሂቃኑ ወይም "መተያያ" አለያም "የእጅ መንሻ" ወደያዘ ያጋደለ ስለነበር ነው። ባንፃሩ የወሎ ሰው ፍትሕ ለማግኘት ከፖለቲካ ሊሂቃኑ ጋር የሚታገልባቸው በርካታሥልቶች ነበሩት። ከነዚህ ሥልቶች መካከል አንዱ ፎክሎር ነው። ፎክሎር በወሎ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የሃዘን፣ የደስታ፣ የፍቅርና ጥላቻ መግለጫ ጥበብ ነው። የመታገያ መሣሪያም ነው። ከመታገያ መሣሪያነቱ አንፃር የሚከተሉት ነጥቦች ለአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በየጁ በተለይ በጉባላፍቶና በሐብሩ ወረዳዎች ውስጥ ከወሎዬዎች ባህል፣ ወግና-ልማድ በማፈንገጥ በሰፊው ህዝብ ስማቸው ከሚጠቀሱ የፖለቲካ ሊሂቃን መካከል ራስ ኃብተማርያም አንዱ ናቸው። ከእሳቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው ፊታውራሪ አመጠኛና ባሕሩ የተባሉ ግለሰቦችም ሌሎች ተጠቃሽ አካላት ነበሩ። እነዚህ ሦስት ግለሰቦች በጉባላፍቶ ወረዳ ነዋሪዎች ዘንድ "ክፉ መካሪ ነገር ቆፋሪ" ተብለው ይገለፃሉ። እነዚህ ሦስት ግለሰቦች እንደ ብዙሃኑ ባህል ከተጎዱት ጎን የሚቆሙ፣ የተጨነቁትን የሚያጽናኑ፣ የወደቁትን የሚያነሱ፣ ባጠቃላይ ህዝቡን የሚያስተዳድሩና የሚመሩ ሳይሆኑ በነዚህ እሴቶች ተቃራኒ የቆሙ ግለሰቦች ነበሩ (Fekadu 1990: 59)::

የአካባቢው ማኅበረሰብ በባህሉ-በወጉና በልማዱ መሠረት የሚመራውና የሚያስተዳድረው የመንግሥት ኃላፊ እዲመደብለት በጨዋ ደንብ ለራስ ኃብተማርያም አመልክቶ የተመደቡለት ግለሰቦች ግን ከእሱ ፍላጎት በተቃራኒ የቆሙ ስለነበሩ፤ ተቃውሞን በፎክሎር እንዲህ ገልጿል።

ሰዋሜዳን ለባሕሩ ጀርሳን ላመጠኛ፤
ታይቶም አይታወቅ እንዲህ ያለ ዳኛ።

ነገር ግን ቅሬታውን በዚህ መልክ ቢገልጽም፤ በምትኩ የራስ ኃብተማርያም መልስ "እንዲህ በፊት ጥርሴ ስይዘው የተንቀጠቀጠ፤ በመንጋጋየ ስይዘው ምን ሊሆን ነው!?" የሚል ስላቅ እንደነበር ይነገራል (Molla 1984፡18)። ይህ ስላቅ ያንገበገበው የአካባቢው ማኅበረሰብ ደግሞ የዋፋ ውጊያ ትውፊቱን ተጠቅሞ በእነ አበጋዝ ጓንጉል የጎበዝ አለቅነት እየተመራ ራስ ኃብተማርያምን ውጊያ ገጥሟቸው ነበር። ነገር ግን በለስ ሳይቀናው ቀርቷል። በምትኩ ራስ

ኃምተማርያም ንብረቱን ዘርፈው፣ ቤቱን አቃጥለው መመለሳቸው ይነግራል።[59] በዚህ ክስተት ድል አድራጊው አካል፤

አበጋዝ ባያምጥ ማሬ ባይቆጣ፤
ማን ያበላን ነበር በበርበሬ ቂጣ።
አባ ማሬ[60] ኃብቴ አይደለህም ወይ፤
ውድመን ተነስተህ መቻሬ ገዳይ፤
በዚያ በነዳዳ በዚያ በፀሐይ።

በማለት እርካታውን ሲገልጽ፤ ድል የተመታው ክፍል በበኩሉ፤

ራስ ኃብተማርያም ጫማቸው ሰፋፊ
ውድመን ተነስተው መቻሬ ዘራፊ።

በማለት ቅሬታውን ገልጿ (Fekadu 1990: 59)። በዚህ ክስተት ተስፋ ያልቆረጡት ወሎዬዎች ግን ለሁለተኛ ጊዜ በእነ መላኩ ታየ እና በእነ አንዳ መሐመድ እየተመሩ ሌላ የመብት ማስከበር መከራ አድርገው ነበር። ይህም መከራ ሳይሳካ ቀርቶ በምትኩ፤ ሊሂቃኑ ከላይ የተጠቀሱትን የጀማውን የጎበዝ አለቆች ወልዲያ ገበያ ላይ እያንዳንዳቸው አርባ ጅራፍ እንዲገረፉ በማድረግ መቀጣጫ አደረገ (Molla 1984: 75)። ነገር ግን ከነዚህ ከከሸፉ ሁለት ሽንፈቶች ትምህርት የቀሰመው የአካባቢው ማኅበረሰብ አሸናፊነቱን በነደጃች ያረጋል ረታ ላይ አሀዱ ብሎ ጀመረ። ከዚያም በእነ ቀኛዝማች አባተ ኃይሉና በእነ ደጃች ጎበና አመዴ ላይ አስመሰከረ። በተለይ ከአባተ ኃይሉ ጋር የተፈጠረውን የወቅቱን ክስተት የአካባቢው ማኅበረሰብ አሁንም ድረስ ያስታውሱታል። አበጋር ማዱ በላይ ክስተቱን የሚገልፁት በሚከተለው ሁኔታ ነው።

> ...የአባተ ኃይሉ አሽከር ትራክተር ወስዶ የጠመደ ጊዜ፤ እነ እራስ ጀበና ወይተባህንስ ብለው ሹፌሩን አባረው መኪናይቱን አገዱት፤ እንዳታርስ። አባተ የሰማ ጊዜ እየበረረ ሲሄድ አላ ውሃ፣ ኸብቱ በዚ በሜዳው ዘግ እንዳለ። አባተ ሰዎቹን ያጣ ጊዜ፣ ኸብቶቹን ግፍግ አርጎ ዶሮ ግብር ሦስት ቀን አደረ። ጥጆቹና ላሞቹ እየተንጫጫ። የላሞቹ ጡት እሚጠባው ያጣ ጊዜ ፈንድቶ ወተታቸው መሬቱን አርሶታል ይባላል። ሂደው ለሼሆቹ ነገሩ እነ እራስ ጀበና። ሼሆቹም አባተን "አትተውሞይ!" ቢሉት፤ "ኧረ-አበዙት አሁንስ፤ ታረቅ ብለው አስታርቀው ደሞ..."ያለ ጊዜ፤ "እንግዳስ ጥይትህን ውኃ አርገነዋል!" አሉት፤ አሙስ ቀን ነው። እንግዲህ ያው ድሉ ያናንተ ነው አሉ ሼሆቹ፤ ገበሬው ተሸክሮ ጥቂት ሲቀረው እሸንቁሩ ሊዘልቅ ሲል እዚያው እፍን አርገው ገደሉት። የላስቴ ገበሬ እነ እራስ

[59] አብርሃም ሽፈራው፣ ቀለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አፏፊ።
[60] "ማሬ" የራስ ኃብተማርያም የፈረስ ስም ነው።

ጀበና፣ እነ አባ ምቴ ለገሰ፣ እነ ሲሳይ ገላኔ፣ እነ አሊ ገላኔ፣ አንቱ፣ አንቱ የተባሉቱ ከበው በድንጋ ላይ ያፍዝ ያደንግዝ አድርገው፤ ሊያመልጥ ሲል፡፡ ሽንቁሯንማ አለፍ ቢል አይነኩትም ቆየ፡፡ ያች አፍዝ አደንግዝ ስላለች፤ ያገሬው ባህል ደሞ ይቺ አንድ ችግር አለቻት፤ ጅኒዩን ሃዘዙት፤ ደብተሮቹ ያዙታል፤ ጠንቋዮቹ ያዙታል፤ ጢበኞቹ ያዙታል፤ ከዞረብህ ምን ዋጋ አለው፡፡ የጁን ይሰጣል፡፡ እንድህ ያለች አገር ናት፡፡ ኸዚያ ሞተ ገደሉት[61]፡፡

ከጥቅሱ እንደምንረዳው "ላስቴ" ማለት ከወልዲያ ምስራቅ አቅጣጫ 15 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ላይ ዶሮ ግብር የሚባለው አካባቢ እሚገኝ ቦታ ነው፡፡ "ራስ ጀበና" የሚለው መጠሪያ ደግሞ "ለአስፋው ፈንታቢል" ጀማው የሰጠው የማዕረግ መጠሪያ ሥም ነው፡፡ መረጃ አቀባዩ እንደሚሉት አስፋው ፈንታቢል መልኩ በጣም ጥቁር ስለነበር "ጀበና" የሚል ቅፅል ሲሰጠው፤ ለጀግንነቱ ደግሞ "ራስ" የሚል ማዕረግ በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ተሰጥቶታል፡፡ አባቱ ኃይሉ ያገታቸው የአካባቢው ማኅበረሰብ ከብቶች ብዛት ቁጥራቸው ሦስት ሺህ ገደማ ይደርስ እንደነበር ይገመታል፡፡ ላሞቹም ለአራት ቀናት ያህል ከጥጆቻቸው ተለይተው እንደነበር ይነገራል፡፡ በመሆኑም አባቱ ኃይሉ በራስ ጀበና አማካይነት ሲገደል የአካባቢው ማኅበረሰብ፤

ጥጆቹ ተርበው እርሾ ሲግቷቸው፤

ወንዱ ራስ ጀበና ወርዶ አገናኛቸው፡፡[17]

በማለት ለራስ ጀበና ያለውን አድናቆት ገልጿል፡፡ ከዚህም ሌላ የደጃች ኅበና አመዴ ታሪክም ተመሳሳይ ነው፡፡ ልዩነቱ ደጃች ኅበና አመዴ የተገደሉት ያለምንም ጦርነት መሆኑ ነው፡፡ በወቅቱ የነበረውን ሁኔታም የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው፡፡

...ደጃይ ኅበና ጥሬ ይወዳል፡፡ ጥሬ ጋር ነው የሞተው፡፡ እሱ ሂዶ እዚያ ዋጃ ላይ አልጠቅመው ብሎ፤ በይህ ስንት አለንጋ መሬት አለው መስሎሃል? እንደው መሬት የተባለን እየመረጠ ደጃይ ኅበና ነው የያዘው፡፡ ደጃይ ኅበና "እኔ ጣሊያን ጋር ተዋግቻለሁ!" ብሎ ኃይለሥላሴ የሰጠው መሬት ህልቆ መሳፍርት የለለው ነው፡፡ ታዲያ ደጃይ ኅበና ይኸ ሁሉ መሬት እያለው እዚያ ኸዋጃ በላይ ፈሰሱን ያን እንደው ኸይህ ወዲህ ብሎ አረሰው፡፡ የአገሬው ሰው የኸብት ምሳጋቸው ቆየ፡፡ 60 ጉድጓድ እኮ ነው አንደየ አመረተ የተባለው፤ ደጃይ ኅበና፡፡ኸይህ ያለ ገበሬ ሂዶ ነው፤ እህሉን የወቃው፤ 60 ጉድጓድ፡፡ "እንግዲህ ይኸ አይበቃህም ወይ? እኛን እየገፋህ!" አለው የአገሬው ሰው፤ ዋጃዎቹ፤ የዋጃ ሰው፡፡ ያው በድንጋይ ላይ፤ ድንጋ ላይ ያው የጅይኒ ሥራ ነው፡፡ ጅኒይ ይች መድሃኒት የምን መሆኗን የአፍዝ የአደንግዝ ያውቃል፡፡ ድንጋ ላዩ ይኸንን ያውቃል፡፡ እነሱም ከድንጋ ላይ ሂደው በነጭ ፈረስ አዙረው እሱ አንድ ሰው ሳይገል እሱን ገደሉት፡፡ መጥቶ ሞላ ጊዮርጊስ ተቀበረ፡፡[62]

---

[61] ፱ አለቃ መኮንን የሽጥላ፤ ቃለመጠይቅ፤ ሐምሌ 4 ቀን 2004 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ፡፡

[62] አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 4 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ፡፡

ጎበና ሲገደሉ ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቁ አሽከሮቻቸው አጅበዋቸው እንደነበር ይነገራል። ነገር ግን አሽከሮቻቸው በወቅቱ ምንም ነገር ስላልፈየዱ፤ ምንም እንኳን አባቱ ኃይሉ የጀማው ህዝብ ጠላት ቢሆንም፤ ጀግና የሚያከብረውና ጀግና የሚያደንቀው የአካባቢው ህዝብ፤

ከደጃች ጎበና ይሻላል አባቱ፤
ሦስት ቀን ተዋግቶ በአራተኛው ሞቱ።

በማለት አባቱ ኃይሉን በማወደስ፤ ደጃች ጎበናን ተሳልቆባቸዋል። ነገሩ የጊዜ ጉዳይ ሆኖ እንጂ፤ በጣሊያን ወረራ ጊዜ ጎበና አመዴ ለፊፀሙት የጀግንነት ተግባር፤

ካልተቆሰቆሰ አይፈላም ጀበና፤
ከኃይለሥላሴ ይሻላል ጎበና።

በማለት አወድሷቸው፤አሞግሷቸውም ነበር። የየጁ ህዝብ ሽንፈቱንም ሆነ አሸናፊነቱን በፎክሎሩ እየገለፀ ረዥም ዘመናት ተጉዟል። የሚገለገልባቸው የፎክሎር ዘርፎችም አይነታቸው ብዙ፤ መልዕክታቸው ደግሞ እንዳይነታቸው ጥልቅና ሰፊ ነው። ለምሳሌ የየጁ ሰው በሰላማዊ መንገድ በደሉን ለማሳየትና ብሶቱን ለመግለጽ "ቅርፊቱ ሙሉ በሙሉ የተላጠ አጠና" ይዞ በዚያን ዘመን ሰልፍ የወጣበት ጊዜ ነበር። ይህንንም የታሪክ ተመራማሪዎች ጽፈዋል (Molla 1984:33):: በዚህ ሰልፍ ለማስተላለፍ የተፈለገው ዋና መልእክት፤ ልክ ቅርፊቱ ተልጦ እንደደረቀው አጠና፤ እሱም በሥርአቱ ንቅዘት ምክንያት ሃብትና ንብረቱን ጨምሮ፤ ስብዕናው መንጠፉን (dehumanization) ወይም ከሰውነት ጎዳና መውጣቱን ለማሳየት ነው። በዚህም የፎክሎሩ ትዕምርት ወይም ተምሳሌታዊ ውክልና ሰፊ ነው፤ ጥልቅ ነው። ተምሳሌታዊ ውክልናው ደግሞ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ መገለጫ ነው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንደተብራራው በወሎ ከ1780ዎቹ እስከ 1970ዎቹ በነበሩ ዘመናት ለሁለት ክፍለ ዘመናት ያህል ከርስት ጋር በተያያዘ በርካታ ክስተቶች ተከናውነው አልፈዋል። ወሎዬዎችም በነዚህ ክስተቶች ምክንያት ከሊሂቃኑ ጋር ባደረጉት ግብ ግብ የተለያዩ የማኅበራዊ ሕይወት ውጣውረዶችን አሳልፈዋል። ለምሳሌ ወልዲያ ገበያ ላይ ለመቀጣጫ አርባ ጅራፍ ተገርፈዋል፤ ተሰቅለዋል። ርስታቸውን ተቀምተው ተሰደዋል። በዚህ ወቅት ወሎዬዎች ሙስሊም ክርስቲያን ሳይሉ ልሂቃኑን በጋራ እየታገሉ እነሱ ግን በሃይማኖት ልዩነት ሳይከፋፈሉ በሰላምና በፍቅር በጋራ አብረው ኑረዋል። ከዚህም ሌላ የወሎዬዎች አብሮነት የሚገለፀው ከሊሂቃኑ ጋር ባደረጉት ትግልና ባጋጠማቸው የሕይወት ውጣ ውረድ ብቻ አይደለም። በተመሳሳይ ወሎዬዎች ከተፈጥሮ ጋር ታግለዋል። በዚህ ትግል ሂደትም

በርካታ የማኅበራዊ ሕይወት ውጣውረዶችን አሳልፈዋል። የሕይወት መስዋዕትነትም ከፍለዋ። ለምሳሌ በዚህ የርስት ባህል ማክተሚያ ወቅት ላይ ወሎዬዎችን ከምንጊዜውም በላይ የፈተነ ከሰማይና ከመሬት ጋር የተያያዘ ክስተት ተፈጥሮ ነበር።

ከላይ እንደተገለጸው ወሎዬዎች ክርስቲያን ሙስሊም ሳይሉ በነዚህ ዘመናት ውስጥ ለተፈጠሩባቸው የሥርአቱ ቁንጮዎች እጃቸውን አልሰጡም፤ አልተንበረከኩም ነበር። ነገር ግን ለተፈጥሮ ጭካኔ ወሎዬዎች እጃቸውን ሰጥተዋል፤ ተንበርክከዋል። ያም ሆኖ ወሎዬዎች ከነፍቅራቸው፣ ኩራትና ክብራቸው ከዚያም አልፎ ከነውበታቸው ከሚወዱት ከወሎ ምድርና አድባር በድርቅ ምክንያት ተሰደዋል፤ በሞት ተለይተዋል። ወሎዬዎች በሕይወት እያሉ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ግማሹ ሙስሊም ግማሹ ደግሞ ክርስቲያን በመሆን በፍቅርና በሰላም መኖር እንደሚችሉ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። የወሎ ድርቅ በተከሰተ ጊዜ ደግሞ ትስስራቸውና ፍቅራቸው እጅግ ፀንቶ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ በጋራ እስከመቀበር ደርሰዋል (Endris 1986: 24)::

የወሎ ድርቅ ለወሎ ሰው ስደትና ሞት ቢያስከትልም ወትሮውንም ያላቸውን ተካፍሎ መብላት ባህላቸው የሆኑት ወሎዬዎች በዚህ ጭንቅ ጊዜ ደግሞ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ፤ ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ፤ ገጠሩ ከከተማው እየተረዳዳ ያለውን ተካፍሎ በልቷል (እንደላይኛው፤ 38)። ያለው ሲያልቅ ደግሞ በጋራ ተሰዷል፤ በጋራ ሙቷል፤ በጋራ ተቀብሯል። በዚህ መሠረት የወሎዬዎች የእርስ በርስ ትስስር የተመሠረተው ከሰላምና ደስታ ጋር ከተያያዙ ጉዳዮች ጋር ብቻ ሳይሆን፤ ጭንቅ፣ መከራና ሰቆቃ ከዚያም አልፎ ሞት ጭምር ከፈጠሯቸው ጉዳዮች ጋር ነው።

ምንም እንኳ ወሎዬዎች ጭንቅ፣ መከራና ሰቆቃ ከመከሰታቸው በፊት ዝናብ እምቢ ቢል፤ ሰማይና መሬትን የሚያስታርቁ፤ ሰውን ከሰው፣ ሰውን ከፈጣሪና ሰውን ከወሎ አድባር ጋር ጭምር የሚያስማሙ፤ በሽታና መጥፎ ነገር ቢመጣ እሱን የሚያርቁ፣ ሁለት ቃል የማይናገሩ፣ ከሐሜት፣ ከፌዝና ትችት የራቁ፣ ወረትና ቧልት የሌለባቸው፣ ሰላምን፣ ፍቅርን፣ ፀጋንና ሞገስን ለሌሎች ሁሉ የሚቸሩ የወሎ ደጋጎች ቢኖሯቸውም በሊሂቃኑም ሆነ በተፈጥሮ አማካይነት ከላይ የተጠቀሱትን ክስተቶች ማስተናገድ ግን ግድ ሆኖባቸዋል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በወሎ በረካ እንዳለ ሁሉ እርግማን መኖሩ ነው። ነገር ግን በወሎ የአንዱ እርግማን በሌላው በረካ፣ ዱዓና ቱፍታ ይካካሳል። ለዚህ አባባል ማሳያ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት የግኑተ-ለዑሉ ጳጳስና የሰባቱ ወልዮች ታሪኮች አብነቶች ናቸው።ታሪኮቹ በታሪክ ድርሳናት የተፃፉና

በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ አሁንም ድረስ የሚተረኩ ሁነቶች ናቸው። ሁለቱም ታሪኮች በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል።

> የገነተ-ልዑለ ጳጳስ፡- የጁ ጥንት ስሟ "ገነቴ" ትባል ነበር። እንደ ጀነት አርጎ የኸለቃት ይችን መሐሏን አገር ነው ይባላል። የጁ የተባለችበት ምክንያት እንድህ ነው፤ "የጁ የጅህን አትጣው!" ያሉት ጳጳስ ናቸው ይባላል። ገነተ-ልዑል ማርያም በገነቴ ምድር የከበረች ደብር ነበረች። በእርስዋም ሰባት ጳጳሳት ይኖሩባት ነበር ይባላል።ሰባቱ ጳጳሳትም ተቀብረውባታል፤ ይላሉ። ነገር ግን በገነቴ ምድር ጣያታትን የሚያመልኩና በአስማታቸ ውም የሚመኩ አስማተኛ ሰዎች ነበሩ። አስማተኞቹም በጳጳሱ ምክንያት ክብራቸው እንደተገፈፈና በሥራቸውም እንደተነቀፉ ባዩ ጊዜ አንድ ሕፃን ሰርቀው በስውር አርደው ለጳጳሱ ወጥ ሰሪ፤ "ይህንን ወጥ ሰርተህ ጳጳሱ ግብር በሚያበሉበት ጊዜ ከጳጳሱ ፊት ይህንን አቅርብልን። ይህ ምንድር ነው? ቢሉህ የወትሮ ግብርዎ ነው፤ ብለህ በሰው ሁሉ ፊት አሳፍርልን" ብለው ለጳጳሱ አገልጋይ ብዙ ገንዘብ ሰጡት። እሱም እንዳሉት አደረገ። የወጡ ሰታቴ ድስት በተከፈተ ጊዜ የዚያ ሕፃን ሁለቱ እጆቹ ከሌላው ሥጋው ጋር ወጥ ተሰርቶ ታየ። ጳጳሱም አብረዋቸው የተቀመጡትም ሰዎች እጅግ ደነገጡ። "አንተ! ዛሬ ያደረግኸው ነገር ምንድር ነው!? ቢሉት፤ እንደተመከረው "ጌታዬ እኔ ዛሬ አዲስ ነገር አላመጣሁም፤ ያው የወትሮ ግብረዎ ነው!" አላቸው። ሰው ሁሉ ደነገጠና ፈራ። ጳጳሱም እጅግ አዘኑና፤ "እኔ የሰው ሥጋ ከአሁን በፊት ስበላ ታውቀኛለህን!? የሰው ሥጋ ከነእጁ ሰርተህ ያቀረብክልኝ!? አንተ ከጠላቶቼ በገንዘብ ተገዝተህ ይህን ታላቅ ድፍረትና ክፋት በገንዘብ መውደድ ልብህ ጠፍቶ አድርገሃልና ለዘላለም ርጉም ሁን! ንበዝ ልብ ሁን!" ብለው ረገሙት ይባላል። ያን ጊዜውን ልብሱን ጥሎ ሱሪውን ቀዶ ራቁቱን ሆኖ በሰዎች ፊት አብዶ በረረ፤ ገደል ገብቶም ሞተ።[63] ጳጳሱ አገሩንም የጁን ይስጠው ሲሉ ረገሙት። "የጁ የጅህን አትጣው!" ሲሉ ረገለሙት። ይኸው አሁን ከፍ አንል ዝቅ አንል፤ይኸው እንዲህ ሁነን፣ ደካማ ጎን ሁነን፣ ኸድሪቶ አንወጣ፣ የጣመ አንበላ፣ ይኸው እንድህ ሁነን አለን[64] (ታየ 1958 ዓ.ም.፤ 50-51)።

የሰባቱ ወልዮች ትውፊትም ከዚሁ መተትና አስማት ጋር የተያያዘ ነው። በዚህም የወልዮቹ ተልዕኮ በወሎ የነበረውን የጣያት አምልኮና የመተት ክፋ ሥራ ወደ ተቀደሰና ወደ መልካም ሥራ መቀየር ነው። ተልዕኮው ደግሞ ለሙስሊሙም ለክርስቲያኑም የጋራ ነው። ታሪኩ ከዚህ ቀጥሎ ተጠቃሎ የቀረበው ነው።

> ሰባቱ ወልዮች፡- ሰባቱ ወልዮች፤ አመጣጣቸው አገሩን ሊያቀኑት ነው። ሐላልና ሐራመ እንዲለይ ነው። ወልዮቹ ኸባሕር ገማ ነው የመጡት። እንግድህ ሰባት ሁነው ነው

---

[63]ይህንን ታሪክ የተረኩልኝ ግለሰቦች ሦስት ናቸው። በነዚህ ግለሰቦች ትረካ መሰረት ሌላው ታሪክ ሁሉ ተመሳሳይ ሁኖ፣ ፍፃሜው ግን ይለያያል። የአንድኛው አቀባይ መደምደሚያ በጥቅሱ ውስጥ እንደተገለፀው "ምግብ አብሳዩ አብዶ ልብሱን አውልቆ ወዲያው ገደል ገብቶ ሞተ፤ የሚል ነው። የሁለተኛው መረጃ አቀባይ ትረካ ደግሞ "ተንኮሉን የጠነሰሱት ግለሰቦችም ጭምር እስከ ሰባት ትውልዳቸው ድረስ አበዱ" የሚል ሲሆን፣ የሦስተኛው መረጃ አቀባይ ትረካ ግን "ጳጳሱ እንደተራገሙ እሱ ወዲያው ገደል ገብቶ ሞተ፣ እሳቸውም ግን ወዲያው ተነስተው አገሩን እረግመው ወደጠሐይ መግቢያ ሲሄዱ አንቺም እምትባል አገር ላይ ሲደርሱ ጨለመባቸው፣ "አዬ! አንችም ትከጅኝ?' ያሉ ጊዜ ጠሐይ ለሳቸው ወዲያ እያበራይ ወዲህ ጨለማ እየሆነ ሄደ። "አንቺም" የቦታ መጠሪያ ሁና አሁንም ድረስ አለች።" እሚል ነው።

[64] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 4 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ።

የመጡት፡፡ሽሰባቱ የአባ ገትየው ጌታው ሼህ ዑመር መርማ ላይ፣ የለገጋዲው ጌታው ሼህ ኢብራሂም፣ የኛ የየጁ አደም ካሊሳ፣ ጌታው ሼህ አይፈራ፣ ጌታው ሼህ ዳውድ (ደሴ ዳውዶ)፣ ጌታው ሼህ ሷቢር፣ ጌታው ሼህ ፈቂ መሳ፣ እነይህ ናቸው፡፡ የተለያየ ቦታ ይሁኑ እንጂ በቀልብ እርስ በርሳቸው ይገናኛሉ፡፡ ወልዮቹ ልጅ ስትድሩ እኛን ጥሩነ አለ፣ ወንድ እንደሁ እሚዳረው ጫጉላ ይሠራለታል፡፡ መ·ሽራይቱን አምጥቶ እቤት እይዶልም፡፡ የብቻው አስር ቀንም ተጨጎለ፣ አስራ አምስት ቀንም ተጨጎለ ወይም እንደ አቅሙ እነሱ ይሂዳሉ፤ ጨፌ ይጎዘጎዛል፣ ቁጭ ይላሉ፡፡ ቁርስ ይቀርብላቸዋል፡፡ ቡና ይጠጣሉ፡፡ ሽዚያ ወዲያ ወደ ዱዓው፡፡ እርቅ አላህ ያርገው፡፡ እንግድህ አይነናስህ ይነሳ፣ ይሽ ሁሉ እሚያይህ አይነ ናስ እንዳይጣበቅብህ፣ ስትሂድ ደሞ መ·ሽራ ይዘህ ልትመጣ ስትል እንቅፋት እንዳያጋጥምህ፣ እሾህ እንደያጋጥምህ፣ ተሸልመህ ወደ ቤትህ መ·ሽራህን ይዘህ እምትገባ አላህ ያርግህ፣ ተብሎ ሱሪህን ፍታ ተብሎ አውረቱ ላይ ጠላውን ይጠጡና "እሱሱሱሱ...!"ይሉበታል፡፡ መ·ሽራይቱንም እንድሁ ብልቷ ላይ ያደርጋሉ፡፡ ይሽንን የሚያደርጉቱ እሚወለደው ልጅ ሰላም የሆነ፣ ብልህ የሆነ፣ ሃይማኖተኛ የሆነ፣ መሪ የሆነ ልጅ፣ እንዲወለድ ለማድረግና ጓላቀሩን፣ መተቱን አስማቱን፣ ጥንቆላውን፣ የጣያት አምልኮውን እየተው እንድሄዱ ለማድረግ ነው፡፡ በዱዓ የተወለደ ልጅ፤ የተማረ ይሆናል፡፡ አገርንም የሚረከብ፤ እሚመራ ይሆናል፡፡ እውቀት ያለው ይሆናል፡፡ እንደተባለው በዱዓ ከመጣይ መ·ሽራና በዱዓ ከመጣ መ·ሽራ እሚወለደው ልጅ ንፍጥ የለው ልጋግ የለው፤ ያው ሃብታም ነው፤ በዱዓ ተወልዷልና[65]፡፡

ከላይ ከተተረኩት ሁለት ታሪኮች መረዳት እንደሚቻለው የዎሎዬዎች ማኅበራዊ ሕይወት ውጣ ውረድ ግንኙነቱ ከፖለቲካ ሊሂቃኑና ከተፈጥሮ አንፃር ብቻ ሳይሆን፤ ከሃይማኖቶቹ ሊሂቃን፣ ከአካባቢው ጠንቋዮች፣ መተተኞችና አስማተኞች ጋር ጭምር ነው፡፡ በዚህ የማኅበራዊ መስተጋብር ሂደት ወቅት በጎም ሆነ መጥፎ ነገር በክርስቲያኑ የመጣ ለመ·ስሊመ፤ በመ·ስሊመ· የመጣ ለክርስቲያኑ ይተርፋል፡፡

ለምሳሌ ከላይ በቀረቡት ሁለት ትረካዎች መሰረት በጳጳሱ ላይ የተሰራው ክፉ ነገር ክርስቲያኑን አስከፍቶ መ·ስሊመን አያስደስትም፡፡ የወልዮቹ መምጣትም መ·ስሊመን አስደስቶ ክርስቲያኑን አያስከፋም፡፡ በመሆኑም እርግማኑም ሆነ በረካው በወሎ ለመ·ስሊመም ሆነ ለክርስቲያኑ እኩል ነው፡፡ ለአብነት ከአበጋር ማዱ በላይ ትረካ እንደምንረዳው የገነቱ- ልዑሉ ጳጳስ እርግማን ያስከተለው ውጤት ደረሰ ተብሎ የሚታመነው በሁለቱም እምነት ተከታዮች ዘንድ ነው፡፡ በመሆኑም በጳጳሱ ላይ የተሰራውን መጥፎ ነገር ሁለቱም አካላት እኩል ይቃወሙታል፡፡ በተመሳሳይ የወልዮቹም በረካ ለመ·ስሊመም ለክርስቲያኑም ነው፡፡ መ·ስሊሞቹ በወልዮቹ ዱዓና ቱፍታ ሐሴት እንደሚያደርጉ ሁሉ፤ ክርስቲያኖቹም የወልዮቹን በረካ ይሻሉ፡፡

ባጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱት የወሎዬዎች ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሁነቶች ቀደም ሲል እንደተገለፀው የወሎዬወች ማኅበራዊና

---

[65] ሼህ ዑመር እሸቱ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 20 ቀን 2006 ዓ.ም. መርሳ- 02 ቀበሌ፡፡

ባህላዊ ዓውድ (socio-cultural framework) ማእቀፎች ናቸው። እነዚህ ማእቀፎች ደግሞ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ምንጩ ወይም ሥረ- መሰረቱ ምን እንደሆነ፣ በምን እና እንዴት እንደሚገለጽ ለመመርመር የሚያስችሉ መነሻ መሰረቶች ናቸው።

የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ምንጩ፣ መገለጫ መንገዶቹና አይነቱ ብዙ ነው። ለምሳሌ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ከዎሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር መገለጫ ምልክት ከሆኑት አብሮ ከመብላትና አብሮ ከመጠጣት ትውፊቶች ውስጥ ይመነጫል። እንዲሁም ከወሎዬዎች አብሮ ከመሥራትና ከመረዳዳት፣ ከመተዛዘንና ከመተሳሰብ፣ ከመከባበርና ከመደጋገፍ፣ ከመጋባትና አበልጅ ከመናሳት...ወዘተ ብሂሎች ሁሉ ይፈልቃል። ከዚህም ሌላ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ በአንድ ቤት ውስጥ አብሮ ከመኖር ጀምሮ፣ የወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት መለኪያ ከሆኑት ከሃዘንና ደስታ እንዲሁም ከሞትም ጭምር ይመነጫል። የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ከክርስትናና እስልምና ሃይማኖት ትውፊቶችና ከወሎ ደጋጎች ዱዓ፣ በረካ፣ ከራማና ቱፍታ እንደሚመነጭ ሁሉ ከገበያም "ይሸመታል"። ገበያ በወሎ የቁሳቁስ መገበያያ ቦታ ብቻ አይደለም። ገበያ በወሎ የባህል፣ የውበት፣ የፍቅር፣ የሃቅ፣ የእምነት፣ የመገናኛና የእርስ በርስ መተሳሰሪያ ቦታ ጭምር ነው። ገበያ በወሎ የመቅጫ፣ የመቀጣጫና የአዋጅ መንገሪያ መድረክ ሆኖ አገልግሏል።

4.1.7፦ የገበያ ትውፊት በወሎ

ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ወሎ ተለይቶ ከሚታወቅባቸው በርካታ መገለጫዎች መካከል አንዱ የመገበያያ ቦታና ዋነኛ የንግድ መተላለፊያ መስመር መሆኑ ነው። (Hussein 2001፡ 143-159):: የወሎ ሲራራ ነጋዴም ከዚሁ የገበያ ትውፊት ጋር የተያያዘ ነው። በወሎ በታሪክ ተለይተው የሚታወቁ ትላልቅ የመገበያያ ቦታዎችና ረጎኛም የንግድ መተላለፊያ መስመሮች አሉ። ከነዚህ መካከል መነሻው ከታጁራ ወደብ ሆኖ ደቡብ ወሎ በሚገኙት በቃሉና ዳዋይ አቋርጦ ወደ ሀገሪቱ ደቡብ ክፍል የሚዘልቀው የንግድ መተላለፊያ መስመር አንዱ ነው (እንደላይኛው፤ 143):: በሰሜን በኩል ደግሞ ከምፅዋ ወደብ ተነስቶ በመቀሌ፤ ኮረም፣ ወልዲያና ደሴ፤ ከዚያም ከወልዲያ ተነስቶ ወረታና ይፋግ፣ ቡሬ-ወለጋ የሚደርሰው የንግድ መስመር ሁለተኛው ነው (Tsegaye 2009: 195):: ከመገበያያ ቦታዎች አንፃር ደግሞ፤ በደቡብ ወሎ አንቻሮና ባቲ፤ በሰሜን ወሎ ደግሞ የወልዲያና የጊራና ገበያዎች ለአብነት ይጠቀሳሉ (Fekadu 1990: 193-197)::

እነዚህ የመገበያያ ቦታዎችና የንግድ መስመሮች ከፖለቲካውና ከኢኮኖሚው ጉዳይ ጋር ያላቸው ግንኙነትና ትስስር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሃይማኖት፣ የባህልና የማኅበራዊ ሕይወት መስተጋብር መንሸራሸሪያ፣ መፍለቂያ ምንጮችና መከወኛ መድረኮች ነበሩ፡፡ የሰው ለሰው መገናኛ ድልድዮች እና መተሳሰሪያ ድርና ማግ በመሆንም አገልግለዋል፡፡ ከክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች ጋር ያላቸው ግንኙነትም ጥንተ-ሥረ-መሰረት ያለው ነው፡፡ በተለይ የእስልምና ሃይማኖት ከንግድ ጋር ታሪካዊ ትስስር እንዳለው ጥናቶች ይጠቁማሉ (Trimingham1965: 60-65)፡፡ በጥናቶቹ መሰረት እስልምና በንግድ ምክንያት ተስፋፍቷል፡፡ እስልምና በንግድ ምክንያት ከአካባቢው ባህል፣ ቋንቋና ከማኅበረሰቡ ሥነ-ልቡና ጋር ተዛምዷል፤ ተላምዷል (Hussein 2001: 30-58)፡፡ በዚህ ምክንያት ከንግድ ጋር ተያይዞ ሙስሊምና እስልምና በወሎ የወሎዬዎች የጋራ እሴት ነው፤ የሙስሊም ክርስቲያኑ የጋራ ትዝታ ነው፡፡ የሚከተሉት ስንኞች ለዚህ አባባል አብነቶች ናቸው፡፡

ወረ ኢሉ-ጃማ፣ አማራና ሳይንት፣ እንዴት ነው ከላላ፤
ወረ ባቦ-ጢሳ፣ አምባሰል ውርጌሣ-ላስታ ላሊበላ፤
ደሴ ዙሪያ ዳውንት-ተንታና መቅደላ፤
ግሼን ደብረ ከርቤ-አቡነ አሮን ገዳም፤
መስቀለ ክርስቶስ-ደሓና ዝቋላ፤
ቆቦ ራማ ዞብል-ኮረም ጋራ ካሦ አላማጣ ባላ፤
ስሪንቃ በሆሮ-ቡርቃ ጨፌ መርሳ፤
መቻሬ ማሸላ፤
ሻሂው የአዚዚ ነው፤ ፓስቲኒው የሼሁ፤ ቁርሱ ግን የአብደላ፤
ጀነቶ በር ቲንፋዝ-ጎንደር በር ሃዳጎ-ወይ ደብረ-ገሊላ፤
ሁሉም ይሰባሰብ፤ በፍቅር በሰላም ተካፍሎ እንዲበላ፡፡[66]

በሌላ በኩል በየጁ አለ ከሚባሉ በርካታ የመገበያያ ቦታዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ወልዲያ ገበያ ነው፡፡ ወልዲያ ገበያ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በታላቁ ራስ ዓሊ ጓንጉል አማካይነት ወይዱ ከሚባለው አካባቢ ተነስቶ አሁን ወዳለበት ቦታ ተዛውሮ የተመሠረተና በየሳምንቱ እለተ ማክሰኞ የሚውል ገበያ ነው (Fekadu 1990: 94-95):: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ወልዲያ ገበያ፤ የመገበያያ ቦታ ብቻ ሳይሆን፤

---

[66] መሐመድ ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ራያና ቆቦ- ሮቢት፡፡

ልሂድ በወልዲያ በአዋጅ መንገሪያው፤

ሰው ጠራኝ መሰለኝ አቤት ልበለው፤

እንዴት የጁን ትቶ ይሰደዳል ሰው

እንደሚባለው፤ ወልዲያ ገበያ እንደሌሎቹ ወሎ ውስጥ እንደሚገኙ ትላልቅ የገበያ ቦታዎች ሁሉ፤ ለሊሂቃኑ የአዋጅ መንገሪያ አደባባይ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው መቅጫና መቀጣጫ መድረክ በመሆንም የበኩሉን ድርሻ ተወጥቷል (Molla 1984: 25)::

ከጀማው ህዝብ አንፃር ደግሞ ወልዲያ ገበያ ተፈልጎ የማይገኝ እቃ እንደሌለ ሁሉ፤ በወልዲያ ገበያ የማይታደም የጎብረተሰብ ክፍል አይገኝም፡፡ በወልዲያ ገበያ ከአፋር፣ ከትግራይ፣ ከላስታ፣ ከጎንደር፣ ከዋድላ ደላንታ፣ ከአምባሰልና ከሌሎች አካባቢዎች የሚመጡ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሁሉ ይገበያዩበታል (Fekadu 1990: 94):: ከነዚህ አካባቢዎች የሚመጡ የማኅበረሰብ ክፍሎች ደግሞ ወልዲያ ገበያ ሲመጡ ይዘውት የሚመጡት ቁሳዊ ሸቀጥ ብቻ አይደለም፡፡ ባንፃሩ ከቁሳዊ ሸቀጥ ያለፉ በገንዘብ ሊገዙ የማይችሉ በርካታ እሴቶችን ጭምር ይዘው ይመጣሉ፡፡ እነዚህ እሴቶች ደግሞ ወልድያ ገበያ ላይ ገንዘብ ሳይከፈልባቸው በነፃ ይሸመታሉ፡፡ የነዚህን ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ የማኅበረሰብ ክፍሎች አለባበስና አጊያጊጥ ጨምሮ፤ ቋንቋ፣ ፍቅርና ውበት፣ እምነትና እውነት (ሃቅ)፣ ቸርነትና ሩኅሩኅነት...ወዘተ ለዚህ አባባል አብነቶች ናቸው፡፡

እንዲሁም የክርስቲያንና የሙስሊም የእርስ በርስ ግንኙነት የሰምና የፈትል ያህል መሆኑን አይቶ ለማመን፤ ሰምቶ ለመረዳት ወልዲያ ገበያ በፎክሎር ሳይንስ ተፈጥሯዊ መቸት ነው፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ በዚህ መቼት ላይ ተገኝቶ የሚከተሉትን ሁነቶች አይቷል፤ ሰምቷል፡፡ ምንጊዜም ወልዲያ ገበያ ላይ ክርስቲያንና ሙስሊም መሳ ለመሳ ናቸው፤ ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ዓውድ ውስጥ ታዲያ ሻጭ ሙስሊም፤ ገዥ ደግሞ ክርስቲያን፤ ወይም ሻጭ ክርስቲያን፤ ገዥ ሙስሊም ናቸው፡፡ ለመሳሌ ሻጭ ሙስሊም ገዥ ደግሞ ክርስቲያን ብትሆን፤ ክርስቲያኗ ሙስሊሟን ዋጋ ትጠይቃለች፡፡ ሻጭ ዋጋ ትናገራለች፡፡ ክርስቲያኗ "ማርያምን?" በማለት የዋጋውን ትክክለኛነት ታረጋግጣለች፡፡ ሻጭ በበኩሏ "ወላሂ!" በማለት ጥሪው እውነት መሆኑን ታስረዳለች፡፡ ከዚህ በኋላ በቃ! ይገበያያሉ፡፡ ለምን ቢሉ፤ ለክርስቲያኗ ሙስሊሟ "ወላሂ!" ካለቻት የተረጋገጠ እውነት ስለመሆኑ አታመነታም፡፡

የዚህ አይነቱ ማኅበራዊ ግንኙነት በወሎ የሚያረጋግጠው መሰረታዊ ቁም ነገር ደግሞ የሙስሊሟ እምነት ከልብ እንደሆነ በክርስቲያኗ ዘንድ ጥርጣሬ አለመኖሩን ነው፡፡ ይህም

አንዱ ለሌላው እምነት ያለውን ክብርና ቦታ በተግባር የሚያረጋግጥ ምሳሌ ነው። በተመሳሳይ ክርስቲያን ሻጭ፤ ሙስሊም ደግሞ ገዥ ከሆኑም ትውፊቱ አንድ ነው። ልዩነቱ ገዥ፤ "ወላሂ!" ብላ ጥሪው ሃቅ መሆኑን ታረጋግጣለች ፤ ሻጭ በበኩሏ፤ "ማርያምን!" በማለት እውነት መሆኑን ትናገራለች።

በሌላ በኩል ግን ሂደቱ የመተዛዘንና የመተሳሰብ ብሂልም አለበት ። ይህም ማለት ሻጭ፤ "ወላሂ መሸጫው ይሄው ነው!" ትላለች። ገዥ በበኩሏ "እረ!- በማርያም ትንሽ ቀንሱ!" በማለት "እንተዛዘን" የሚል ቃና ባለው አንደበት ትጠይቃለች። ሻጭም "ወላሂ! አሁን ካንቺ በፊት የሸጥኩት እኮ በዚሁ ዋጋ ነበር" በማለት "መቸስ ምን አደርጋለሁ!" በሚል ስሜት አስተያየት አርጋ ትሸጥላታለች።

ሌላው የሃቅ ማረጋገጫ ጉዳይ ደግሞ ከእቃው ጥራት ጋር የተያያዘ ነው። ለምሳሌ ገዥ፤ "ይሽ ጤፍ፣ ይሽ ቡና፤ ይሽ ሽክላ...ወዘተ የዚህ አካባቢ ነው? ብላ ትጠይቃለች። ሻጭ "አዎ!" ብላ ተመልሳለች። ገዥ በበኩሏ "ወለሂ!?" በሚል ጥያቄ ሃቅ መሆኑን ታረጋግጣለች። ባንፃሩ ሻጭ "ድንግልን!" የሚል መልስ ትሰጣለች። ገዥ በዚህ አይነት ተውፊት እውነቱን አረጋግጣ የምትፈልገውን ነገር ገዝታ ትሄዳለች። ለምን ቢሉ፤ ከላይ እንደተገለፀው የአንዱ ሃይማኖት ለሌላኛዋ የእውነት ማረጋገጫ ሰነድ ስለሆነ። ነገር ግን የዚህ ጥናት አቅራቢ በቦታው ላይ ተገኝቶ ያየው ነገር በትግባር ምንያህል እውነት ነው? የሚል ጥያቄ አቅርቦ ነበር። ከክርስቲያኖቹ በኩ ያገኘው መልስ "እረገኝ! ‹ወላሂ› ብላ አደለ የሸጠችልኝ! እንዴት ትዋሸኛለይ!"[67] የሚል ነው። በሙስሊሞቹ በኩል ያለው አስተሳሰብና አመለካከትም ከክርስቲያኖቹ ጋር ተመሳሳይ ነው። ለዚህም ከላይ የቀረበውን ጥያቄ የመለሱት "እስቲ ወላሂ በይ ስላት እኮ ‹ማርያምን› ብላለይ፤ ስለዚህ እንተማመናለን"[68] በማለት ነው። ከዚህም ሌላ አሰፋ አበጋዝ ትውፊቱን የሚያብራሩት ከነምክንያቱ እንደሚከተለው ነው።

> ለምሳሌ ላሚቱን ሲሸጥለት "የምትወልደው ባመት-ባመት ነው። ዘጠኝ ወር ደሞ ትታለባለይ፤ ወተታም ናት። እኔ እምሸጣት ቸግሮኝ ነው።" ሊለው ይችላል። "ይቺ ፍየል መንታ-መንታ ነው እምትወልደው፤ ይሽ በሬ ስቦ አይጠግብም...ወዘተ" ይለዋል። ገዥው እስላም ከሆነ "እስቲ ወላሂ በል!" ይለዋል። የሚሸጠው ክርስቲያን ከሆነ "ጊዮርጊስን!" ሊለው ይችላል። እንዲህ ስላለ ብቻ ያምነዋል፤[69] ምንም ተያዥ፣ ምንም ሌላ ነገር ሳያሰፈልግ።

---

[67] ዓለም አራጋው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ዶሮ ግብር።

[68] ዘሐራ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ራያና ቆቦ- ሮቢት።

[69] መረጃ አቀባዩ እንደሚሉት ባሁኑ ጊዜ ግን በተለይ በወጣቱ ክፍል "ወላሂ! ማርያምን! አርሴማን! ሰመአቱን!...ወዘተ ማለት ለሃቅ ማረጋገጫ ሳይሆን እንዴ ፋሽን ነው። ለውሸት ነው። እንደ ልምድ ነው። ወይም ደግሞ አማኝ መስሎ ለመታየት ነው። የዱሮዎቹ ግን ይተማመናሉ። በሌላ ጊዜ አይ እንዲህ ብሎ አበያ በሬ

> በዚህ ብቻ ይተማመናሉ። ምክንያቱም የሚገናኙበት አይታወቅምኮ! በሌላ ጊዜ "አይ! እንዲህ ብሎ ዋሽቶ ሸጠልኝ!" ብሎ ይወቅሰዋል። ለምን የሚገናኙበት ነገር ስላለ! ወይ በሃዘን ወይ በደስታ ወይ በሌላ ነገር ይገናኛሉ። ወይም እነዚህ ሰዎች በሆነ ዘመድ ይገናኛሉ። ከዚያ ደሞ "ዘመዴን እንዲህ አረከው" ብሎ ያኛው ይወቅሰዋል። ሊጣሉም ይችላሉ። በዚህ ምክንያት ማኅበራዊ ግንኙነታቸው ሊበላሽ ይችላል። በተለይ ቀደም ያሉት ከውነት የራቀ ነገር ይናገራሉ ብዬ አላምንም። ሲጠሉም እውነት ነው። የዚያኑ ያህል ይጠሉሃልኮ! ቂምም ሊመጣ ይችላል፤ ዘመዴን በደልከው ብሎ። አይ! እንደዚህ በድሎኛል እሚል ነገር ይመጣል።[70]

ከዚህ ጥቅስ ሁለት መሰረታዊ ነጥቦችን መረዳት ይቻላል። አንደኛው ነጥብ ሃይማኖቶቹ የመተማመኛና የመግባቢያ የጋራ እሴቶች መሆናቸውን ነው። የሥነ-ምግባርና የግብረ-ገብነት መሰረቶች መሆናቸውን ነው። ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ የወሎዬዎች የእርስ በርስ ግንኙነት በእንዴት አይነት ጠንካራ መሰረት ላይ የተገነባ እንደሆነ በዚህ ትውፊት ሳይቀር የሚገለጽ መሆኑ ነው።

ሌላኛው የወልዲያ ገበያ ትውፊት "መመረቅ" የሚባለው ብሂል ነው። መመረቅ አንድ ሰው አንድ ነገር ከገዛ በኋላ በሻጭ በኩል ከመለኪያውና ከዋጋው ውጭ የሚሰጠው ተጨማሪ "ችሮታ" ማለት ነው። በወልዲያ ገበያ ከልብስና ከተወሰኑ ሸቀጦች በስተቀር፤ ከእህል እስከ ቅመማ ቅመም፣ ከሸንኮራ አገዳ እስከ ከረሚላ ለገሸ ይመረቃል። በዚህ ሂደት ሙስሊሟ ከክርስቲያኗ ከገዛች፤ ክርስቲያኗን፤ "ኧረ-ላላህ ብለው መረቅረቅ አርጉት!" በማለት ያግባባሉ። በተመሳሳይ ክርስቲያኗ ከሙስሊሟ ከገዛች፤ ሙስሊሟን፤ "ኧረ! በማርያም በደንብ መርቁት እንጂ!" በማለት ይጠይቃሉ። በሁለታቸውም በኩል እምቢ ማለት የለም፤ ባንዳሩ በተጠየቁት መሰረት ለአመልም ያህል እንኳ ቢሆን የልባቸው እንዲደርስ ያደርጋሉ። የዚህ አይነቱን ትውፊት ፋዳ የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> አሁን እኔ በቅርብ የማስታውሰውን አንድ ገጠመኝ ልንገርህ። ሕፃን ልጅ ናት። ተልካ ልኳንዳ ቤት ሥጋ ልትገዛ ነው። እኔም ሥጋ ልገዛ እዚያ ነበርኩ። ታዲያ ያቺ ሕፃን ምን አለች መሰለህ "በደንብ መረቅረቅ አርግበት!" ስትል ሰማኋት። እሱም የሆነ የሆነ ነገር ቆርጦ መረቃት። መመረቅ በመሰረቱ ምስክርነት ነው። እምነት ወይም ሃቅ ነው። እጅህ ይታሰራል ትሞታለህ፤ ይኸ እጅህ ትክክል ለክቷል ወይ!? ተብለህ በፈጣሪ እንዳትጠየቅ ነው። እና እምነት ነው። ለምሳሌ መስፈሪያው አለ ግን በሆነ አጋጣሚ ሊጎል ይችላል። ስለዚህ ለዚያ ማሚያ ምስክርነት ነው። ማካካሻ ነው። ጎደሎነት እንዳይኖር ነው። ግን ደሞ እንደበረከትም ይቆጠራል።[71]

ሸጠልኛል ብሎ ይወቅሰዋል። የማትታለብ ላም ሸጠልኛል ብሎ ይወቅሰዋል። ስለዚህ አያስመስልም።" (አሰፋ አበጋዝ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ።

[70] እንደላይኛው።

[71] ዓሊ መሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አንጦ- 04 ቀበሌ።

“አይታሰር እጂህ፤ አይዘጋ ደጅህ” ብለው እንዲመርቁ ወሎዬዎች፤ ከላይ በቀረበው ጥቅስ እንደተገለጸው የመመረቅ ትውፊት እጅ ከታሰረ ሁሉም ነገር ከንቱ ነው፤ የሚል አንዲምታ ቢኖረውም በብዙ መልኩ ግን ከመተዛዘን፣ ከመተሳሰብና ከለጋስነት ጋር ይገናኛል። ለምሳሌ የነጋዴና የገበሬ ምርቃት ይለያያል። ገበሬ ሲመርቅ አፈስ፣ አፈስ አርሳ ነው። አስተፋፈሱ ራሱ ልዩነት አለው። የራሱ የሆነ መገለጫ አለው። በዚህ ሂደት ገዥውም ሆነ ሻፊዒ ሙስሊምም ይሁን ክርስቲያን ትውፊቱ አንድ ነው (ጌታዋ 2004 ዓ.ም.)። የትውፊቱ አንድምታ ደግሞ፤ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የመተዛዘን፣ የመረዳዳት፣ የመደጋገፍ፣ ከዚያም አልፎ የሃቅ ማረጋገጫ ሰነድ ነው። በዚህም አንዱ ሌላውን ከልብ አመኖ ይቀበላል። ከዚህ ካለፈ ግን በወሎ፤ “እስላም አበለ፤ ቀን ዘነበለ!” ይሉት ፈሊጥ ይሆናል። በክርስቲያኑም እንዲሁ “የተናገሩት ከሚጠፋ፤ የወለዱት ይጥፋ!” እንደማለት ነው። በሌላ በኩል ወልዲያ ገበያ ላይ ሻጭም ሆነ ገዥ ሁሉም እንደየ እምነቱና እንደየ እድሜው አንዱ ሌላውን በቃል የሚገለጠውን ምረቃ ይመርቃል። በረካ እንዲደርሰውም ይመኛል። በረካ ተቀባዩ በበኩሉ “አሜን!” ብሎ ከልቡ ይቀበላል።

በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት ማለት በውሎ፤ የወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር ወይም የእርስ በርስ ግንኙነት የሚገለጽበት ሁነት ማለት ነው። የሃይማኖት መቻቻል እሴቱ የሚገልፀው ወይም የሚያሳየው መሰረታዊ ነጥብ ደግሞ የወሎዬዎችን መተማመንና መከባበር፣ መተዛዘንና መተሳሳብ፣ መዋደድና መፋቀር፣ አመለካከትና አስተሳሰብ፣ ሥነ-ምግባርና ግብረ-ገብነት...ወዘተ ሁሉ ነው። ይህ ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው በገበያ ቦታ ላይ ሳይቀር ይገለፃል። ይህም ማለት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለፀው በወሎየዎች ባህላዊና ማህበራዊ አውድ ውስጥ ነው። ነገር ግን የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ መገለጫ መንገዱ የወሎዬዎችን ማኅበራዊና ባህላዊ ዓውድ ያህል የሰፋ ነው።

ለምሳሌ በወሎ ክርስትናውም ሆነ እስልምናው የየራሳቸው መገለጫ የሆኑ የተለያዩ ትውፊቶች አሏቸው። እነዚህ ትውፊቶች ደግሞ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ መገለጫ አብነቶች ናቸው። ለዚህም በክርስትናው በኩል ፀበል እንዳለ ሁሉ፤ በእስልምናውም በኩል እንዲሁ የሼሆቹ “ውኃ” አለ። አገልግሎታቸው ደግሞ ለክርስቲያኑም ለሙስሊሙም ነው። በሌላ በኩል የገናና የጥምቀት በዓላት ሃይማኖታዊና ባህላዊ የሆኑ እሴቶች አሏቸው። ሃይማኖታዊ እሴቶቹ የክርስቲያኖቹ ሲሆኑ፤ ባህላዊ እሴቶቹ ግን የክርስቲያኖቹም የሙስሊሞቹም የጋራ ሃብቶች ናቸው። በእስልምናውም እንዲሁ ለዱዓ የተመሰረቱ ቅዱስ ቦታዎች አሉ። የበረከት

ምንጭነታቸው ግን ለሙስሊሙም ለክርስቲያኑም ነው። በዚህም ሙስሊሞቹም ክርስቲያኖቹም ይዘይሯቸዋል፤ ከራሳቸው የማኅበራዊ ሕይዎት ፍልሥፍና ጋር ያገናኟቸዋል። ለምን ቢሉ ከራማቸው እንዲጠብቃቸው፤ በረካቸው እንዲደርሳቸው (Hussein 2001:85; Fekadu 1990:15)። በመሆኑም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለፀው በነዚህ እሴቶች አማካይነት ነው። በዚህ መሰረት እነዚህ እሴቶች በቀጣዩ ምዕራፍ አምስት ውስጥ ተመርምረው ቀርበዋል።

"ከሩቅ ዘመዴ የቅርብ ጎረቤቴ!" እንዲለ ወሎዬዎች፤ ጉርብትና በወሎ በርካታ ትውፊቶች አሉት። ወልዶ መታረስ ቢሉ ታሞ መተኛት፤ ለቅሶ ቢሉ ሠርግ፤ ማኅበር ቢሉ ወንፊል/ጂጊ፤ ተርቲብ ቢሉ ፋጢማ ቆሪ፤ ክርስትና ቢሉ መታቀፍ፤ አርባ ቢሉ ሰደቃ፤ ወዳጃ ቢሉ አድባር፤ ዛር ቢሉ ዓይነ-ጥላ፤ ጥንቆላ ቢሉ ኮከብ ቆጠራ፤...ወዘተ በወሎ፤ የወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊቶች መገለጫ አብነቶች ናቸው። የወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊቶች መስረታቸው ደግሞ የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ነው። በመሆኑም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚገለጽ፣ እንዲሁም ምንን እንደሚያሳይ ወይም ምንን እንደሚገልጽ መርምሮ ለመረዳት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ የወሎዬዎቹ የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ትውፊት ነው። የምዕራፍ ስድስት ዋና ዓላማም በዚህ ትውፊት ላይ የተመሰረተ ነው።

ምዕራፍ አምስት

5፡- የሃይማኖት መቻቻል እሴት እና ሃይማኖታዊ ትውፊቶች በወለኖ

ቀደም ሲል የቀረበው የምዕራፍ አራት ዋና ዓላማ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ይህ ጥናት በተካሄደበት ቦታና ጊዜ ውስጥ ከወለኖዎች አጠቃላይ፤ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር የተገናኙ በአብዛኛው ፎክሎራዊ የሆኑ እሴቶችን በመመርመር ለምዕራፍ አምስትና ለምዕራፍ ስድስት መሰረት መጣል ነው፡፡ በተደረገው ምርምርም እነዚህ ጉዳዮች የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለኖ፤ ሥረ-መሠረቱ ወይም ምንጩ ምን እንደሆነ ፍንጭ የሚሰጡና አጠቃላዩ የወለኖዎች ማኅበራዊ መስተጋብር ወይም የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም አብሮነት ምን አይነት ገጽታ እንደነበረው ገልጠው የሚያሳዩ የማኅበራዊና ባህላዊ ዓውድ (Socio-Cultural Framework) ማእቀፎች መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በዚህ መነሻ የምእራፍ አምስት ዋና ዓላማ ደግሞ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለኖ፤ በሃይማኖታዊ ተቋማቱ ትውፊቶች አመካይነት እንዴት ይገለጻል? ምንንስ ይገልፃል? የሚሉትን ዓበይት ጥያቄዎች መመለስ ነው፡፡

5.1፡- የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለኖ፤ በእምነቶቹ ተከታዮች አብነት

በዓለም ላይ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች የሚለያዩባቸው በርካታ ሃይማኖታዊ መርሆዎች እንዳሏቸው ሁሉ፤ የሚመሳሰሉባቸው ጉዳዮችም አሏቸው፡፡ በተለይ በአንድ ፈጣሪ ማመናቸው (Monotheism) ለአብነት ይጠቀሳል፡፡ ይህ ፈጣሪ ደግሞ ሃዳም ያመለከው፣ አብርሃም ያስተናገደው፣ ሙሴ የታዘዘውና ዳዊት ያመሰገነው እንደሆነ ይታመናል (Yonas 2011: 89)፡፡

እንዲሁም የሁለቱ ሃይማኖቶች እምነት ተከታዮች የሚያምኑበት ፈጣሪ የፍጥረታት ሁሉ ምንጭና በመጨረሻው ዘመንም ወደዚህ ዓለም ለፍርድ የሚመጣ ኃይል ነው፡፡ በዚህም የአይሁድ ሃይማኖትን ጨምሮ፤ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች "Abrehamic faiths" በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ሃይማኖቶች የዚህ ፈጣሪ ትእዛዛት የተደነገጉባቸው ቅዱሳት መፃሕፍትም አሏቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስና ቅዱስ ቁርዓን ለምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በነዚህ ቅዱሳን መፃሕፍት የተደነገጉት ትእዛዛትና አስተምህሮዎች ደግሞ በበርካታ ጉዳዮች

ይገናኛሉ፤ ይዛመዳሉ። ለዚህም "ከክፉት ደግነት" የሚለው አጠቃላይ መርህቸው ይጠቀሳል (እንደላይ ኛው፤ 89-90)።

ነገር ግን የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ግንኙነት በወሎ፤ ከላይ ከተጠቀሱት የሁለቱ ሃይማኖቶች አጠቃላይ የግንኙነት መርሆዎች የዘለለ ሌሎች መገለጫዎች ወይም መስተጋብሮች አሏቸው። የነዚህ መስተጋብሮች መሰረታዊ መነሻ ደግሞ የእምነቶቹ ተከታዮች ናቸው። ምክንያቱም የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት እምነት ተከታዮች በወሎ፤ አብሮ በመኖር ሂደት ለዘመናት የገነቧቸውና ያዳበሯቸው በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው። ይህንን እውነታ የአካባቢው ነዋሪዎች የሚያረጋግጡት እንደሚከተለው ነው።

> እስላምና ክርስቲያን በወሎ በስግነታችን ተሁለት ቤት፣ ተሦስት ቤት አንሆንም። የቁሱ ልጅ የቃልቻውን ልጅ አግብታ እስላም ሁና ነው ያለች። የቃልቻው ልጅ የቁሱን ልጅ አግብታ ክርስቲያን ሁና ነው ያለችው። ስለዚህ ማንና ማን ይለያያሉ። በስግነትም ያልተለያየን ነን። አብረን እየበላን አብረን እየጠጣን። ይቺው "በስመ አብ ወወልድ ወ መንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ" እና "ቢስሚላሂ" እምትባል እርድ ናት የምትለያየን እንጂ፤ በዚህ ባለንበት አካባቢ በዚህ በውስጣችን ሌላ እሚለየን ነገር የለም።[72]

በዚህ ጥቅስ ውስጥ የቀረበውን አስተያየት ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ "እኛ የምንለያየው በሃይማኖት እምነቶች በእርድና በሰገዳ ነው። ከዚህ ውጪ በእስላምና በክርስቲያን መካከል ልዩነት የለንም!"[73] በማለት በጥቅሱ የተነሳውን ሃሳብ ቅቡልነት ይስማሙበታል። በዚህ መሰረት በወሎ የክርስትና ሃይማኖት እምነት ተከታዮች ከእስልምና ሃይማኖቶች ትውፊቶች፤ የእስልምና ሃይማኖት እምነት ተከታዮች ከክርስትና እምነት ትውፊቶች ጋር የእትብት ያህል ዝምድና አላቸው። በመሆኑም የክርስትናና የእስልምና ሃይኖቶች በወሎ፤ ለክርስቲያን ሙስሊሙ የመገናኛ ድልድይ እና የእርስ በርስ መተሳሰሪያ ክር የሚሆኑበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ከዚህ በታች ተተንትነው የቀረቡት ነጥቦች ይህንን አባባል የሚያረጋግጡ አብነቶች ናቸው።

በሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን በጉባላፍቶ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅህፈት ቤት መረጃ መሰረት በጉባላፍቶ ወረዳ ካሉት 34 ቀበሌዎች ውስጥ የቂሌ-ሃዳሚ ቀበሌ አንዷ ናት። ቂሌ-ሃዳሚ ቀበሌ ከወልዲያ ከተማ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ የገጠር ቀበሌ ናት። በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ፅህፈት ቤት መረጃ መሰረት የቂሌ-ሃዳሚ

---

[72] መሪጌታ ቀለሙ ዳኛው፤ ቃለመጠይቅ፤ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሣ- 01 ቀበሌ።
[73] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለመጠይቅ፤ ነሐሴ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።

ቀበሌ ነዋሪዎች 4195 ገደማ ናቸው፡፡ ከዚህ ቁጥር ውሰጥ 99.7 በመቶ የሚሆኑት ነዋሪዎች ሙስሊሞች ሲሆኑ፤ 0.3 በመቶ የሚሆኑት ብቻ የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው[74]፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የክርስቲያኖቹ ቁጥር እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም፤ ከ1818 ዓ.ም. አካባቢ ጀምሮ እንደተመሰረተ የሚነገርለት የቂሌ-ሃዳሜ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን በዚች ቀበሌ ውስጥ ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን ቤተ-ክርስቲያኑ ሲመሰረት በወቅቱ በአካባቢው የነበሩት የክርስትና እምነት ተከታዮች ቁጥር በውል ባይታወቅም፤ ባሁኑ ጊዜ በቀበሌው ውስጥ ያሉት የክርስትና እምነት ተከታዮች ቁጥር ግን አንድ ቄስና አንድ አርሶ አደር ከነቤተሰቦቻቸው ብቻ ናቸው[75]

ለቂሌ-ሃዳሜ ቅዱስ ጊዮርጊስ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡት ቄሶች የሚመጡት ደግሞ ከጉባርጃ ማርያም፣ ከምልምል ተክለ ሃይማኖትና ከዶሮ ግብር ጊዮርጊስ ነው፡፡ ቄሶቹም እሁድ-እሁድ ወደቦታው ሄደው ማጠንት አጥነውና ኪዳን አድርሰው ወደመጡበት ይመለሳሉ፡፡ ይህም ሆኖ የቂሌ-ሃዳሜ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ሊቀጥል አልቻለም፡፡ በዚህ መሰረት በ1998 ዓ.ም. ክርስቲያኖቹ ቁጥራቸው በጣም ትንሽ ስለሆነና ቤተ-ክርስቲያኑ አገልጋይ ስለሌለው፤ ቤተ-ክርስቲያኑ ፈርሶ ፅላቱ አገልጋይ ወዳለበት አካባቢ እንዲዛወር በሰሜን ወሎ ሀገረ-ስብከት ተወሰነ፡፡ ይህንን ውሳኔ ከዞኑና ከወረዳው ቤተክህነት የተውጣጣ ኮሚቴ ወደ ቂሌ-ሃዳሜ በመሄድ የቀበሌውን ነዋሪዎች ወይም ሙስሊሞቹን ሰብስቦ ውሳኔውን አስረዳ፡፡

ነገር ግን የቂሌ-ሃዳሜ የእስልምና ሃይማኖት እምነት ተከታዮች አሥር ከማይሞሉት የቀበሌው ክርስቲያን ነዋሪዎች ጎን በመቆም "እኛ እያለን ታቦቱ የትም አይሄድም!" በማለት የሀገረ-ስብከቱን ውሳኔ ተቃወሙ፡፡ ከዞኑና ከወረዳው ወደ ቂሌ-ሃዳሜ የሄዱት ተወካዮችም እንዳሰቡት ፅላቱን ሳያነሱ ወደ ወልዲያ ተመለሱ[76]፡፡

ባንፃሩ የቂሌ-ሃዳሜ ሙስሊም ነዋሪዎች በጣት ከሚቆጠሩት ክርስቲያኖች ጋር በመሆን በችግሩ ዙሪያ መምከር ጀመሩ፡፡ ከምክክራቸው በኋላም የቤተ-ክርስቲያኑ መሰረታዊ ችግር አገልጋይ ካህናት የሌሉት መሆኑን ተረዱ፡፡ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ቤተ-ክርስቲያኑ የራሱ የሆነ የገቢ ምንጭ በማጣቱ የተፈጠረ ችግር መሆኑን አረጋገጡ፡፡

---

[74] ጉባላፍቶ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት፤ የቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ልማት የሥራ ሂደት፤ ሚያዚያ 23 ቀን 2006 ዓ.ም፡፡
[75] ተስፋው መርሻ፤ ቃለመጠይቅ፤ ነሐሴ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ::
[76] ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፤ ቃለመጠይቅ፤ ነሐሴ 21 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ፡፡

ምንም እንኳን የቀበሌው ሙስሊም ነዋሪዎች ቀደም ሲል ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ለቤተ-ክርስቲያኑ አገልግሎት የሚውል ገቢ፤ ጢስ በጤሰ በያመቱ አንድ-አንድ ጣሳ እህል የሚሰፍሩ ቢሆንም፤ ይህ መጠን ግን ለካህናቱ በቂ አለመሆኑን በማመን ተጨማሪ አንድ-አንድ ጣሳ እህል ለማዋጣት ወሰኑ። በዚህ ውሳኔ መሰረት እያንዳንዱ አርሶ አደር በነፍስ ወከፍ በአመት ሁለት-ሁለት ጣሳ እህል ለማዋጣት ተስማማ። ከዚህም ሌላ የቤተ-ክርስቲያኑ አገልግሎት አስተማማኝ ሆኖ እንዲቀጥል ተጨማሪ 12 ጥማድ መሬት በቋሚነት ለካህናቱ ሰጡ።

ከዚህ በኋላ ደግሞ ነዋሪዎቹ ለረዥም ዘመናት አገልግሎት የሰጠውን የቂሌ-ሃዳሜ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን በአዲስ መልክ ለመስራት እንቅስቃሴ ጀመሩ። ገንዘብና ጉልበታቸውን በማስተባበርም በአጭር ጊዜ ውስጥ አዲስ ቤተ-ክርስቲያን ሰርተው ሚያዚያ 23 ቀን 2005 ዓ.ም. አስመረቁ። ጽላቱንም አጅበው፣ አመቀውና አድምቀው አዲስ ወደሰሩት ማደሪያው አስገቡ። በዚህ ወቅት የቂሌ-ሃዳሜ ቀበሌ ሙስሊም ነዋሪዎችን በጎ ተግባር በቦታው ላይ ተገኝተው ለማየትና በሥነ-ስርአቱ ላይ ለመታደም ከተለያዩ አካባቢዎች ወደ ቂሌ-ሃዳሜ ጊዮርጊስ ብዛት ያላቸው እንግዶች ተጓዙ።





ፎቶ ግራፍ ሦስት፦ በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች ትብብር የተሰራው የቂሌ-ሃዳሜ ቅ/ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን።

የቂሌ-ሃዳሜ ጊዮርጊስ ሙስሊሞችም እንግዶችን ተቀብለው ዳስ ሰርተው፣ ድንኳን ጥለው፣ አብልተው አጠጥተው አስተናገዱ። በወቅቱ የነበረውን ሁነት የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ባለሙያ፤ "እኛን የሚያስተሳስረን ባህሉ ብቻ ሳይሆን፣ ማኅበራዊ ግንኙነቱ ብቻ ሳይሆን፣ በሥጋ ዝምድና መተሳሰራችን ብቻ ሳይሆን ሃይማኖቶቹ እራሳቸው ያስተሳስሩናል።


ለምሳሌ ሙስሊሙ የክርስቲያኑን ቤተ-ክርስቲያን ይሰራል፤ ይጠብቃል፤ ይንከባከባል፡፡ ክርስቲያኑም በተመሳሳይ እንደዚሁ ያደርጋል፡፡" በማለት እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

ለምሳሌ ቂሊ-ሃዳሜ ጊዮርጊስ እሚባል ቦታ አለ፡፡ እዚያ አካባቢ የሚኖሩት ክርስቲያኖች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ በዚህም ዕላቱን ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር አስፈለገ፡፡ ነገር ግን ሙስሊሙ አናስነሳም አለ፡፡ እንዲያውም "ጊዮርጊስ ለራሳችንስ በረከት አደለሞይ! ለምንድን ነው የማናሰራው!?" ብለው ኮሚቴ ሆነው፤ የገንዘብ መዋጮ አዋጥተው፤ ጉልበታቸውን አስተባብረው እነሱ ናቸው የሰሩት፡፡ እነዚያ አሥር የማይሞሉ ክርስቲያኖች አደሉም የሰሩት፡፡ 75 በመቶ የሚሆነው የሙስሊሙ ገንዘብና ጉልበት ነው፡፡ ቤተ-ክርስቲያኑ በ2005 ዓ.ም. ተጠናቆ ሲመረቅ ልክ የራሳቸው በዓል አስመስለው ነው ያስመረቁት፡፡ እነሱ ናቸው ያን ሁሉ እንግዳ አስተናግደው የሸኙት፡፡ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ስዕለት ያስገቡ ነበር፡፡ "ሼህ ያሲን፤ ሼህ ሲራጅ፤ ሼህ እንትና ...ወዘተ ስዕለት አምጥቶ! ስዕለት ልኮ!" እየተባለ ፍየል ብቻ ከ15 በላይ ስዕለት አስገብተዋል፡፡ እና ሲጠየቁ ምንድን ነው ያሉት "ይሄ እኮ የአባቶቻችን ቅርስ ነው! የኛም ቅርስ ነው! እነዚህ ወንድሞቻችንስ ቢሆኑ የት ሊሄዱ ነው ቤተክርስቲያኑ ተነስቶ!?" ነበር መልሳቸው[77]፡፡





ፎቶግራፍ አራት፡- በቤተ-ክርስቲያኑ የምረቃ ሥነ-ስርዓት ወቅት የአካባቢው ሙስሊም ወጣቶችና ሕፃናት፡፡





ፎቶግራፍ አምስት፡- በበዓሉ ዕለት ከአካባቢው ሙስሊም ነዋሪዎች በስዕለት መልክ ከተሰጡ ፍየሎች በከፊል፡፡

ምንጭ፡- የጉባላፍቶ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ልማት የሥራ ሂደት፡፡

---

[77] ሞላልኝ ወርቁ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- መሀል መቻሬ፡፡

ባጠቃላይ የቂሌ-ሃዳሜ ቀበሌ ሙስሊሞች የአባቶቻቸው ቅርስ የሆነውን የጊዮርጊስ ፅላት ከቦታው ተነስቶ ወደሌላ ቦታ እንዳይሄድ አደረጉ። ማደሪያውን ሰርተው ፅላቱን አስገቡ። ለአገልጋዮቹ ቀሳውስት አስራት ለመስፈር ተስማሙ። ቀሳውስቱ በቋሚነት የሚገለገሉበትን መሬት ከግል ይዞታቸው ላይ ቆርሰው ሰጡ። ይህም ሆኖ የቂሌሃዳሜ ቀበሌ ሙስሊሞች በቁጥር እጅግ አነስተኛ ለሆኑት ክርስቲያኖች የቤተክርስቲያኑ አገለልግሎት ሳይስተጓጎል እንዲቀጥልላቸው በማሰብ ሌላ ስልት ቀየሱ።የቀየሱትን ስልት የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት፤ "...ለምሳሌ በገጠርም ሆነ በከተማ ክርስቲያኑ ለቤተ-ክርስቲያን የሚከፍለው መዋጮ አለ። እነዚህ ግን ሁሉም ገበሬ ምርቱን በሚሰበስብበት ወቅት ከሙስሊሙ አንድ ተወካይ ከክርስቲያኑ አንድ ተወካይ ሆነው ከገበሬው ላይ እህል ይሰበስባሉ። ከዚያ በኋላ ለቤተ-ክርስቲያኑ ገቢ ያደርጋሉ። ቤተ-ክርስቲያኑም በዚህ አይነት መንገድ ይተዳደራል"[78] በማለት ነው።

ስለዚህ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለጸው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች ትውፊት አማካይነት ነው። ትውፊቱ ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ወይም ከአብሮነት ጉዳይ አልፎ ከእኔነት ስሜት ጋር የተዋሀደ ነው። ለዚህ ደግሞ የቂሌ-ሃዳሜ ጊዮርጊስ ለአብነት የሚጠቀስ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ተምሳሌት ነው።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የቂሌ-ሃዳሜ ጊዮርጊስ ገጠመኝ ለአብነት ተጠቀሰ እንጂ፤ በወሎ ከጥንት ጀምሮ "ታቦቱ የቅድመ አያቶቻችን፣ የአያቶቻችንና የአባቶቻችን ቅርስ የነበረ፤ አሁን ደግሞ የእኛ ቅርስ ስለሆነ ከቀያችን አይነሳም!" ብሎ መከራከር የወሎ ሙስሊሞች ባህል፣ ወግና ልማድ ነው። ከአባቶቻችው የተረከቡት መልካም እሴት ነው። በዚህም በወሎ በሙስሊሞች ገንዘብና ጉልበት የተሰሩና አሁንም የሚሰሩ አብያተ-ክርስቲያናት በርካታ ናቸው።ለምሳሌ ደሴ የሚገኘውን የገብርኤል ቤተ-ክርስቲያን ጨምሮ፤ ሐብሩ ወረዳ ውስጥ የሚገኙት የአድርሶ ጅሮ ሚካኤልና የወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት አብያተ-ክርስቲያናት ለአብነት ይጠቀሳሉ። አድርሶ ጅሮ ሚካኤል የሚገኘው መርሣ ከተማ አካባቢ በሚገኝ የገጠር ቀበሌ ውስጥ ነው። በዚህ ቀበሌ ውስጥ የሚገኙት ነዋሪዎች እንደ ቂሌ-ሃዳሜ ቀበሌ ነዋሪዎች ሁሉ ክርስቲያኖቹ በጣት የሚቆጠሩ ሲሆኑ፤ አብዛኞቹ ሙስሊሞች ናቸው።

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚገልጹት በክርስቲያኖቹ ቁጥር ማነስ ምክንያት በአንድ ወቅት ፅላቱ ከቦታው ተነስቶ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወር የሚል ውሳኔ በዞኑ ሀገረ-ስብከት ተወሰነ።

[78] ተስፋው መርሻ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ።

ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የሀገረ-ስብከቱ ሊቀ-ጳጳስ የሆኑት አቡነ ቄርሎስ ወደቦታው አመሩ፡፡ ነገር ግን ጳጳሱን ያልጠበቁት ሁኔታ ከቀበሌው ሙስሊም ነዋሪዎች ገጠማቸው፡፡ ይኸውም "እንዴ! ይሄ ታቦት ከተነሳ የኛም ጤንነት ስለሚታወክ ባይሆን ቤተ-ክርስቲያኑን ካሉት ክርስቲያኖች ጋር በጋራ በመሆን እናስቀድሳለን እንሰራለን እንጂ !" በማለት ለጳጳሱ ተናገሩ፡፡ ጳጳሱም ፅላቱን ሳያነሱ ወደ ወልዲያ ተመለሱ፡፡ በዚህ መሰረት በአሁኑ ጊዜ የአድርሶ ጅሮ ሚካኤል የሚቀደሰውና የሚወደሰው በአካባቢው ባሉት ክርስቲያኖች ድጋፍ ብቻ ሳይሆን፤ በአካባቢው በሚገኙት ሙስሊሞች ትብብር ጭምር ነው፡፡[79]

በሌላ በኩል ወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት ከውርጌሣ ከተማ ሰሜን አቅጣጫ ቁጥር 14 የገጠር ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ጥንታዊ ቤተ-ክርስቲያን ነው፡፡ በሪሁን ይመር የዚህ ቤተ-ክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ናቸው፡፡ የቤተ-ክርስቲያኑንና የአካባቢውን ሙስሊም ነዋሪዎች ትስስር የሚገልጹት በሚከተለው ሁኔታ ነው፡፡

> ክርስቲያኖቹ ውስን ስለሆኑ አንድ ወቅት ላይ ቤተ-ክርስቲያኑ ይነሳ ተባለ፡፡ ሙስሊሙ አናስነሳም ብሎ ሆ! ብሎ ተነሳ፡፡ አሁን እንሰራለን ብለን ስናስብ በቀጥታ ከ20ሺህ ብር በላይና ባሕር ዛፍ የቻለው በሙሉ ሙስሊሙ ነው፡፡ ካሁን በፊትም ሙስሊሙ እንዳለ ወረ-ካሎ እምትባለው አገር ለቤተ-ክርስቲያኑ አንድ-አንድ ጣሳ እህል ያዋጣል፤ ለማስቀደሻ ማለት ነው፡፡ ሙስሊሙ በሙሉ፡፡ ቃዲው አይቀርም፡፡ ደረሳው አይቀርም፡፡ ክርስቲያኖቹ ኬሻ ይዘው ይዞራሉ፡፡ ከዚያ ከሁሉም ተሰብስቦ ለቤተ-ክርስቲያኑ ገቢ ይደረጋል፡፡ ገቢ ከተደረገ በኋላ የሚሸጠው ተሸጦ፣ የሚጠመቀው ተጠምቆ፣ የቀረው ማስቀደሻ ይሆናል፡፡[80]

ከዚህ በላይ በጥቅሱ ውስጥ የተገለጸውን ሃሳብ የአካባቢው ነዋሪ የሆኑት እንድሪስ ይመር የሚያረጋግጡት "ክርስቲያኑ አናሳ ነው ብሎ ቤተ-ክርስቲያኑን ሊያነሳው ነው ቢል፤ አገሩ ‹ቅርሳችን ነው! ንብረታችን ነው!› ብሎ አስቀረው፡፡ አንድ-አንድ ጣሳ እህል ለቅዳሴ ብሎ ፈቀደ፡፡ ያንን እያስተባበረ አሁን ዛሬ ድረስ እያዋጣ ቤተ-ክርስቲያኑን አስቀምጦታል"[81] በማለት ነው፡፡ በራያና ቆቦ ወረዳ ወርቄ አካባቢ የምትገኘው የኢሉ- ኪዳነ ምህረት እና የአካባቢው ሙስሊሞች ትስስርም ተመሳሳይ ታሪክ አለው፡፡ ትስስሩን የአካባቢው ነዋሪዎች "በቁጥር በዚያ አካባቢ ሙስሊሙ ይበዛል፡፡ እንደዚህም ሆኖ ግን የኪዳነ ምህረት በዓል ሲከበር በጋራ ነው ::ማንኛው ነው ክርስቲያኑ፤ ማንኛው ነው ሙስሊሙ ብለህ መለየት አትችልም፡፡" በማለት ይገልጹታል[82]፡፡

---

[79] ዓሊ መሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አንጦ 04 ቀበሌ፡፡
[80] በሪሁን ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 23 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ፡፡
[81] እንድሪስ ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 22 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ፡፡
[82] ደሳለ ፈንታው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 9 ቀን 2007 ዓ.ም. ራያና ቆቦ- አራዶም፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡት አብነቶች መሰረት ወሎዬዎች በሃይማኖታዊ ተቋማቶቹ ሳይቀር ይገናኛሉ፤ ይተሳሰራሉ፡፡ መገናኘታቸውና መተሳሰራቸው ብቻም ሳይሆን፤ ሃይማኖታዊ ተቋማቱን "የቅድመ አያቶቻችን፣ የአያቶቻችን፣ የአባቶቻችንና እኛም ከነሱ የወረስናቸው ቅርሶቻችንና ንብረቶቻችን ናቸው!" የሚል ከልብ የመነጨ አስተሳሰብ አላቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ቅርሶቹን ይጠብቋቸዋል፤ ይንከባከቧቸዋል፡፡ እነሱም በተራቸው ለልጆቻቸው ያወርሷቸዋል፡፡

በዚህ መሰረት የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ ዘይቤ፤ ልዩነትን ሳይሆን አንድነትን፤ ጥላቻን ሳይሆን ፍቅርና ሠላምን፤ መናናቅን ሳይሆን መከባበርን ያጸናል፡፡ መደጋገፍን፣ መረዳዳትን፣ መተዛዘንን፣ ፍቅርና ሠላምን ባህሉ፣ ወግና ልማዱ፤ እንዲሁም ደንብና መመሪያው ያደርጋል፡፡ ይህንን እውነታ በደወይ ነዋሪዎች ምሣሌነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ እንድሪስ አህመድ እንደሚሉት የደወይ ነዋሪዎች አብዛኛዎቹ ሙስሊሞች ናቸው፡፡ ባንፃሩ የክርስቲያኖች ቁጥር ከሙስሊሞቹ ቁጥር እጅግ ያነሰ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ቤተ-ክርስቲያናቸው የሚገኝበት ርቀት እነሱ ከሚገኙበት አካባቢ የውሎ ገብ የሚባል ነው፡፡ በተለይ ሰው ሲሞት አስከሬን ተሸክሞ ለመቅበር ከደወይ ነዋሪዎች ፊት ቀድሞ ድቅን የሚለው የቤተ-ክርስቲያኑ ርቀት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ከእለታት አንድ ቀን ለዚህ ችግር መፍትሄ ለማበጀት ሙስሊሞቹ ከጎረቤቶቻቸው ጥቂት ክርስቲያኖች ጋር በመሆን ተሰበሰቡ፡፡ ተሰብስበው ቤተ-ክርስቲያኑ በሚገኝበት ርቀት ዙሪያ መከሩ ዘከሩ፡፡ ነዋሪዎቹ መክረው ዘክረው አንድ የመፍትሄ ሃሳብ ላይ ደረሱ፡፡ በዚህም ካላቸው የወል ይዞታ መሬት ላይ ቀንሰው በመስጠት በአካባቢያቸው ለክርስቲያኖቹ ቤተ-ክርስቲያን ለመስራት ተስማሙ፡፡ በስምምነታቸው መሰረት ገንዘብ አዋጥተው፤ ጉልበታቸውን አስተባብረው ቤተ-ክርስቲያን ሰርተው ለክርስቲያኖቹ ጎረቤቶቻቸውና ቤተሰቦቻቸው አስረከቡ፡፡ ይህንን በማድረጋቸው የነሱንም ሆነ (ለቀብር ቤተክርስቲያን ይሄዱ ስለነበር) የክርስቲያኖቹን ችግር ቀረፉ፡፡[83]

ከላይ እንደተጠቀሰው በወሎ የክርስቲያኑን ቤተ-ክርስቲያን ሙስሊሙ ከክርስቲያኖቹ ጋር በመሆን አብሮ ይሰራል፤ ይጠብቃል፤ ይንከባከባል፡፡ በመሆኑም የወሎዬዎች በሠላምና በፍቅር አብሮ የመኖር ባህል ወይም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በዚህ ይገለጻል፡፡ እሴቱ በገጠርም ሆነ በከተማ ተመሳሳይ ነው፡፡ ለገጠሩ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች አብነቶች

[83] እንድሪስ አህመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 4 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 03 ቀበሌ፡፡

ናቸው። ለከተማው ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ምሳሌዎች የነዋሪዎቹን በሃይማኖት ተቻችሎ የመኖር እሴት የሚገልጹ አብነቶች ናቸው።

መሪጌታ ቀለመ ዳኛው የውርጌሣ ገነተ-ማርያም ቤተ-ክርስቲያን አሰሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት ባካባቢያቸው መስጊድ ሲሰራም ሆነ ቤተ-ክርስቲያን ሲሰራ በትብብር ነው። አንዱ ለሌላው መሬቱን ፈቅዶ ነው። ገንዘቡንና ጉልበቱን አስተባብሮ ነው። የዚህ አይነቱ ባህል ደግሞ ጥንተ ሥረ- መሰረት ያለው የጋራ እሴት ነው። እሴቱ አሁን ባለው ትውልድም የቀጠለ ትውፊት ነው። መሪጌታ ቀለመ እሴቱን የሚገልፁት እንደሚከተለው ነው።

> እዚህ እኛ አካባቢ ትልቅ ግዙፍ መስጊድ አለ። ይህንን መስጊድ ገንዘብ አዋጥተን፣ በጉልበታችንም እነ መምሬ ወርቁ መንግሥቱ፤ እነ መምሬ ለገሰ፤ እኛ-እኛ ሁሉ ስራው ላይ እየገባን የሰራነው መስጊድ ነው። እኛም ቀደም ሲልም ሆነ አሁን ቤተ-ክርስቲያን ስንሰራ ሙስሊሞቹ ረድተውን ነው። ለምሳሌ አሁን ገነተ ማርያም የምትባል አዲስ ቤተክርስቲያን እየሰራን ነው። የምንሰራውም መዋጮውን ከዘጠኙ ቅሬ በሙሉ ጢስ በጤሰ ሰብስበን ነው። ቃልቻው አልቀረ፤ ዱበርቲው አልቀረ። ሁሉም ተባብሮ ነው። ውጪ አገር ያሉት የእስላም ልጆች ለቤቶቻቸው 5ሺህ ብር ልከው እንደሆነ፤ 1ሺህ ብር፤ 2ሺ.ብር፤ 3ሺ.ብር ለማርያም ስጡልን እያሉ እየሰጡን ነው። ሕፃናቱ ልጆች እንኳ! የትልልቆቹን፣ የእናቶቻቸውንና የአባቶቻቸውን ፊለግ እያዩ። ስለዚህ አሁንም ቤተ-ክርስቲያኑ የሚሰራው በከፊል በእስላሞቹ ገንዘብ ነው።[84]

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው በወሎ፤ በሙስሊሙ ትብብር ቤተ-ክርስቲያን ይታነጻል። በክርስቲያኑ ትብብር ደግሞ መስጊድ ይገነባል። የዚህ አይነቱ የትብብር መንፈስ በወሎ በአንድ አካባቢ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ባንፃሩ መተባበሩ፣ መረዳዳቱና መደጋገፉ ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከደጋ እስከ ቆላ የሚዘልቅ ባህል ነው። ወንዝ የሚሻገር እሴት ነው። ዓለሙ ኃይሉ የዚህ አይነቱን የጋራ እሴት የሚገልጹት የመርሣ ከተማ ነዋሪዎችን እንደሚከተለው ምሳሌ በመጥቀስ ነው።

> ዱሮ ሚካኤል እዚያ ላይ ሳለ፤ እዚህ ከሜዳው ወርዶ እንዲሰራ ያደረጉት ሙስሊሞቹ ናቸው። አመልክቱና ሜዳ ላይ ይውረድልን አሉ። አዲስ አበባ ሂደን አመለከትነ፤ ይውረድላቸው ተባልን። አቡነ ገብርኤል መጥተው ባርከው እዚህ ቦታ ላይ ወረደልን። ማን ሰራው? ሙስሊሙ። ድንጋይ ተሸክሞ፤ እንጨቱን፣ ሚስማሩን አቅርቦ ነው የሰራው። የኛ ከተሰራ በኋላ፤ እኛ ደሞ የመስጊድ ቦታ ጠይቁና መስጊድ እንስራ አልናቸው። የዚያን ጊዜ ከተማው በጭቃ ሸም ነበረ እሚመራው፤ አባ በላቸው፤ የከቤ በላቸው አባት። እሳቸው ነበሩ ጭቃ ሸመ። ጠየቋቸው፤ ይኸን ላይኛውን መስጊድ ከመንገዱ ዳር ያለውን ቦታ ሰጧቸው። ሲሰጧቸው እኛ ድንጋዩን ተሸክመን፣ የምስማር መግጫውን አቅርበን፣ እንጨቱን ተሸክመን መስጊዱን ሰራን። አሁንም መስጊድ ይሰራል፤ አብረን ነው። አሁንም

---

[84] መሪጌታ ቀለመ ዳኛው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሣ- 01 ቀበሌ።

> ቤተ-ክርስቲያን እንሰራለን፤ አብረን ነው። ልዩነት የለንም። አኗኗራችን በዚህ መልኩ ነው። በሃይማኖታችን እንዳለን አንድ መሆናችን የማይካድ ነው ይሽ አገር።[85]

በጥቅሱ እንደተገለጸው የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ተግባራዊ የሚደረገው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች ባህል፣ ወግና ልማድ አማካይነት ነው። በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የመረዳዳት፣ የመደጋገፍ፣ የመተዛዘን፣ የመከባበርና እርስ በርስ የመተሳሰር ትውፊት ነው። በዚህ አይነቱ የወለዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ ዘይቤ ነው። በወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ ዘይቤ መሰረት የክርስቲያኑ ደስታ ለሙስሊሙ ደስታው ነው። ሃዘኑም ሃዘኑ ነው። ይህም ከላይ እንደተጠቀሰው በሃይማኖት ተቋማቱ ጭምር የሚገለጽ የአብሮነት እሴት ነው። በተጨማሪም ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሁነቶች ይህንን እውነታ ያረጋግጣሉ። ለምሳሌ በወልዲያ ከተማ ያለውን የትብብር፣ የመረዳዳት፣ የመደጋገፍና የመከባበር መንፈስ ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ እንደሚከተለው ያብራሩታል።

> ይሽ የሃዳጎው ትልቁ መስጊድ ሲሰራ ክርስቲያኑ ነው፤ በሙሉ ተባብሮ የሰራው። መስጊዱ ተጠናቆ ሲመረቅ ደሞ ሁለት ፍሪዳ ገዝተን ሰጥተናል። እንደገና እኛ ይሽን የመድኃኔዓለምን ቤተ-ክርስቲያን ስንሰራ እስላሙ በገንዘቡና በጉልበቱ ብዙ ተባብሯል። ተጠናቆ ሲመረቅ ደሞ በድግሱ ጊዜ እንዲሁ እኛ ሁለት ፍሪዳ ነበር የሰጠናቸው፤ እነሱ ሦስት አራት ፍሪዳ አድርገው ሰጥተውናል። በሌላም-በሌላም ሁሉ እንደዚሁ እንረዳዳለን። በዚህ በአካባቢያችን እንዲህ ያለ ጥሩ ባህልና በጎ አመለካከት አለ[86]

በጥቅሱ የተገለጸውን በአንተ-ትብስ፤ በአንቺ-ትብሽ መንፈስ የተቃኘውን የወሎዬዎች የጋራ እሴት አሰፋ አበጋዝ የሚገልጹት በወሎ ሙስሊሙ መስጊድ ሲሰራም ሆነ፤ ክርስቲያኑ ቤተ-ክርስቲያን ሲሰራ አንዱ ሌላውን በገንዘቡና በጉልበቱ ከማገዝ ጀምሮ፤ የአሰሪ ኮሚቴ አባል በመሆን ጭምር መስራቱ "ጥንተ ሥረ- መሰረት ያለው፤ ያለና የነበረ ባህል ነው!" በማለት የወልዲያ መድኃኔዓለም ገጠመኛቸውን እንደሚከተለው ለአብነት ይጠቅሳሉ። "እኔ አሁን መድኃኔዓለም ቤተ-ክርስቲያን ሲሰራ ሙስሊሞቹ ያደረጉት ነገር ቀላል አልነበረም። እንደው ለምሳሌ ቢያንስ የመጨረሻውን ብነግርህ ቤተ-ክርስቲያኑ ተመርቆ ታቦቱ ሲገባ ድግስ ነበር። ለዚያ ድግስ ከበሬ፣ በሬ፤ ከበሬ በሬ ተመርጦ ሦስት በሬ ገዝተው በክብር ያስረከቡት የከተማው ሙስሊሞች ናቸው"።[87]


ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ የሚኖሩት መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ ነው። እሳቸው እንድሚሉት "አላህ እድሜ ነይቶላቸው!" የ121 ዓመት የእድሜ ባለፀጋ አዛውንት ናቸው።

---

[85] ዓለሙ ኃይሉ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 02 ቀበሌ።
[86] ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 17 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ።
[87] አሰፋ አበጋዝ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 14 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ።

ሼህ በአካባቢያቸው የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ የአገር አባት ናቸው። ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ ይህን ያህል ዘመን የኖሩበትን የወሎዬዎች የአብሮነት ባህል የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> በዚህ በእኛ አካባቢ መስጊድም ሆነ ቤተ-ክርስቲያን ሲሰራ በገንዘብና በጉልበት መረዳዳቱ ባህላችን ነው። ከዚያም አልፎ እኛ የክርስቲያኖቹ ቤተ-ክርስቲያን ሲሰራ፤ ተጠናቆ ከመመረቁ በፊት እዛው እቦታው ድረስ ሂደን ውስጥ ገብተን ቤተ-ክርስቲያኑን እንጎበኛለን። ቤተ-ክርስቲያኑ ሲመረቅ ደሞ እኛ እንጠራለን። ኸዚያ እነሱ በጎን ተቀመጠው፤ እኛም በጎን ተቀምጠን የመመራረቅ ባህል አለን። እኛም መስጊድ በምንሰራበት ጊዜ የተጀመረው እምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ መጥተው ያያሉ። ሲመረቅም መጥተው የድንኳኑንም፣ የዳሱንም፣ ማንኛውንም እገዛ አድርገው ተገባብዘን በደስታ የምለያይበት ባህል ነው ያለን። ይኸ ከመሰረቱ ጀምሮ ተያይዞ የመጣ ነው። አሁንም እንዳለ ነው። ለቀጣዩም ቢሆን ፈጣሪ ነው የሚያውቀው።[88]



ፎቶግራፍ ስድስት፦ የ121 ዓመት የእድሜ በለፀጋ እንደሆኑ የሚናገሩት ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ።

ከላይ በቀረበው ጥቅስ መሰረት ወሎዬዎች ክርስቲያን እና ሙስሊም ተብለው የሚለዩት ሃይማኖታዊ በሆነው መርህ ወይም በአምልኮ ቦታና የአምልኮ ሥርአታቸው ነው። ባንዳኑ ግን በወሎ ክርስቲያን መሆን ወይም ሙስሊም መሆን፤ ለወሎዬዎች ማኅበራዊ ኑሮ ወይም የእርስ በርስ ግንኙነት የልዩነት መስፈርት አይደለም። ለምሳሌ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ማኅበራዊና ባህላዊ ጉዳይ ከሆነው የእርስ በርስ ግንኙነት ባለፈ፤ ወሎዬዎች ሃይማኖታዊ በሆኑት ጉዳዮች ጭምር ሳይቀር በጋራ ይወያያሉ፤ ይመካከራሉ። እርስ በርስ ይተጋገዛሉ፤ ይደጋገፋሉ። ለዚህ አባባል የሚከተለውን የከልክላቸው ዓሊ ሁለት ገጠመኞች ተጨማሪ አብነት መጥቀስ ይቻላል።

---

[88] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።

ከልክላቸው ዓለ. በ1997 ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ወሎ ውስጥ ያለውን የሃይማኖት መቻቻል እሴት የሚያሳዩ ገጠመኞችን ጠቅሰው ጽፈዋል። ከነዚህ ገጠመኞች መካከል፤ ደሴ አካባቢ የሚገኙት የአርቤሮ ሚካኤልና የጀሚል አል አዛር መስጊድ ይጠቀሳሉ።

በከልክላቸው ጥናት መሰረት አርቤሮ ሚካኤል የሚገኘው ከደሴ ከተማ ሰሜን ምእራብ አቅጣጫ 12 ኪሎሜትር ርቀት ላይ፤ ሩጋ ተብሎ በሚጠራው የገጠር ቀበሌ ውስጥ ነው። በ1967 ዓ.ም. የመሬት አዋጅ ምክንያት የአርቤሮ ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያን የሚተዳደርበት መሬት በመወረሱ አገልግሎቱ ተቋርጦ ነበር። በዚህ ሰበብ ፅላቱ ከቦታው ተወስዶ ወደ ደሴ እንዲዛወር በደሴ ሀገረ-ስብከት ተወሰነ። ነገር ግን ከ95 በመቶ በላይ ሙስሊም የሆኑት የሩጋ ቀበሌ ነዋሪዎች "ታቦቱ የክርስቲያኖቹ ብቻ ሳይሆን፤ የኛም ቅርስ ስለሆነ ተነስቶ ወደ ደሴ አይመለስም!" በማለት ውሳኔውን ተቃወሙ። ባንፃሩ ነዋሪዎቹ ከየግል ይዞታቸው ላይ ለቤተ-ክርስቲያኑ አገልጋዮች መተዳደሪያ የሚሆን፤ የአንድ አባወራ ይዞታ መጠን ያለው መሬት ቆርሰው ለመስጠት ተስማሙ። የገንዘብ ድጋፍም እንደሚያደርጉ ቃል ገቡ። በዚህም የአርቤሮ ሚካአልና የሩጋ ቀበሌ ሙስሊም ነዋሪዎች ትስስር ሳይቋረጥ እንደነበረ እንዲቀጥል አደረጉ (kalklachew 1997: 83)።

በሌላ በኩል ካቤ ውስጥ ሚገኘው የጀሚል አል አዛር መስጊድም ተመሳሳይ ታሪክ አለው። ከልክላቸው ዓለ እንደጻፉት ምንም እንኳን የካቤ ነዋሪዎች አብዛኛዎቹ ሙስሊሞች ቢሆኑም፤ እስከ 1978 ድረስ ካቤ ውስጥ መስጊድ አልነበረም። ነገር ግን በ1978 የካቤ ነዋሪ ሙስሊሞች ንብረትነቱ የቀበሌ ይዞታ የሆነ ቤት ለመስጊድነት ለመጠቀም እድል አገኙ። ይህ አጋጣሚ ሊቆይ የቻለው ግን ለሁለት አመታት ያህል ብቻ ነው። ከሁለት አመት በኋላ ግን አዲስ የተሾሙት የካቤ ቀበሌ ሊቀ መንበር ሙስሊሞቹ ለመስጊድነት የሚገለገሉበትን የቀበሌ ቤት እንዲያስረክቡ መመሪያ አስተላለፉ። ሊቀመንበሩ በዚህ ብቻም ሳይወሰኑ የካቤን ነዋሪዎች ሰብስበው የተፈፀመው ድርጊት ሕገወጥ መሆኑን ገለጹላቸው። በእለቱ ነዋሪዎቹ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡም አደረጉ።

በዚህ ወቅት ከተሰብሳቢዎቹ መካከል አንዱ የሆኑት የካቤ ሚካኤል የደብር አለቃ መምሬ መኮንን ኃይሌ አስተያየት ለመስጠት የመጀመሪያ እድል አገኙ። ቄሱ ያገኙትን አጋጣሚ በመጠቀም የሊቀመንበሩን ድርጊት አጥብቀው ተቃወሙ። ሌሎች ተሰብሳቢዎችም የእሳቸውን ፈለግ ተከተሉ። በዚህ መነሻ ሙስሊሞቹ ለመስጊድነት የሚገለገሉበት ቤት ለቀበሌው

ሳይመለስ ጉዳዩ ለበላይ አካል ቀረበ። ከሁለት አመታት ክርክር በኋላም ጉዳዩ የቀረበለት የበላይ አካል ቤቱንና ቦታውን ለካቤ መ·ስሊሞች ወሰነ (እንደላይኛው፤ 86)።

ከዚህ በኋላ የነበረው ቀጣይ ሥራ ደግሞ ቦታውን አጥሮ ደረጃውን የጠበቀ መስጊድ መስራት ነበር። በዚህ መሰረት ለመስጊዱ ሥራ የሚያግዙ ስድስት አባላት ያሉት የመስጊድ አሰሪ ኮሚቴ ተቋቋመ። በከልክላቸው ጥናት መሰረት ከተቋቋመው የመስጊድ አሰሪ ኮሚቴ አባላት ውስጥ አቶ ብርሃኔ ገ/ጊዮርጊስ፤ አቶ አያሌው ደመቀና መምሬ መኮንን ኃይሌ የተባሉት ግለሰቦች ክርስቲያኖች ነበሩ። እነዚህ ግለሰቦች ክርስቲያኖች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፤ የኮሚቴው ሰብሳቢ ሆነው የተመረጡት የካቤ ሚካኤል የደብር አለቃ የሆኑት መምሬ መኮንን ኃይሌ ነበሩ። በመሆኑም በእሳቸው ሰብሳቢነትና በካቤ ነዋሪዎች ትብብር አማካኝነት የካቤ ጀሚል አል አዛር መስጊድ እውን ሆነ (እንደላይኛው፤ 86)። በተመራማሪዎች ዘንድም ወሎ ውስጥ ስላለው የሃይማኖት መቻቻል እሴት ተምሳሌት ተደርጎ መጠቀስ ጀመረ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ነጥቦች በወሎ በገጠርም ሆነ በከተማ ውስጥ መ·ስሊመ· ለክርስቲያኑ፤ ክርስቲያኑ ለመ·ስሊመ· ያለውን አመለካከት የሚገልጹ ምሳሌዎች ናቸው። በነዚህ ምሳሌዎች መሰረት ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቋማቱ ሳይቀር እርስ በርስ ይረዳዳሉ፣ ይደጋገፋሉ፣ ይተጋገዛሉ፣ ይተዛዘናሉ፣ አንተ-ትብስ አንቺ-ትብሽ ይባባላሉ። እርስ በርስ በመተሳሰርም አንድነታቸውን ያጠናክራራሉ። በሃይማኖት ሰበብ የሚፈጠሩ ልዩነቶችን ያጠባሉ። በምትኩ እርስ በርስ በመከባበር፣ በሠላምና በፍቅር አብረው ይኖራሉ። በዚህም የሃይማኖት መቻቻል እሴት ፋይዳ ምን እንደሆነ ለሌሎች በተግባር ያሳያሉ።

ከዚህ አልፈው ወሎዬዎች አንዱ የሌላውን ሃይማኖታዊ ተቋም የመልካም ነገር ሰበብና የበረከት ምንጭ አድርገው ያስባሉ። በዚህ የተነሳ አንዱ የሌላውን ሃይማኖታዊ ትውፊት "የኔ የራሴ!" የሚል አዎንታዊ አስተሳሰብ ያዳብራሉ። አስተሳሰቡን ከቅድመ አያቶቻቸው፣ ከአያቶቻቸውና ከአባቶቻቸው ይወርሳሉ። እነሱም በተራቸው ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው ያስተላልፋሉ። የዚህ ሁሉ ሥረ-መሰረቱ ደግሞ የሃይማኖቶቹ ትውፊቶችና የወሎዬዎች የአኗኗር ዘይቤ ነው።

የወሎዬዎች የአኗኗር ዘይቤ "ክርስቲያን-መ·ስሊም!" በሚል አስተሳሰብ ጎራ ለይቶ ሳይሆን፤ አንዱ ከሌላው ጋር በጉርብትና ተሰባጥሮ ነው። በቤተሰብ አማካይነት ተቀላቅሎና ተዋህዶ ነው። በዚህም ክርስቲያኑ የመ·ስሊመን ባህል፣ ወግና ልማድ ይወርሳል። ወርሶም የራሱ ያደርጋል። በተመሳሳይ መ·ስሊመ· የክርስቲያኑን ባህል፣ ወግና ልማድ ይወርሳል። ወርሶም የራሱ ያደርጋል። ይህ የመወራረስ ባህል ደግሞ ማኅበራዊና ባህላዊ ከሆኑት ጉዳዮች አልፎ

የሃይማኖቶቹን ትውፊቶች ሁሉ ያጠቃልላል። በዚህ መሰረት አንዱ የሌላውን ሃይማኖታዊ ትውፊት ከራሱ ማኅበራዊ ሕይወት ጋር በተለያዩ መንገዶች ያስተሳስራል፣ ያገናኛል፣ ያዛምዳል። የዚህ አይነቱ ባህል፣ ወግና-ልማድ በበኩሉ ወሎየዎች በሃይማኖት ተቻችለው የሚኖሩባቸውን እሴቶች ይወልዳል። ሂደቶቹ ከዚህ በታች ተተንትነው በቀረቡት የሁለቱ ሃይማኖት ትውፊቶች አማካይነት ተብራርተው ቀርበዋል።

5.2፡- የክርስትና ሃይማኖት ትውፊቶች በወሎ

በክርስትና ሃይማኖት ትውፊት መሰረት የተለያዩ መላዕክት፣ ፃድቃን፣ ነቢያትና ሰማዕታት አለ። ለነሱም በስማቸው ጽላት ተቀርፆ፣ ቤተክርስቲያን ይሰራላቸዋል። በስማቸው ፀበል ይፈልቅላቸዋል። በስማቸው ተአምራት ይሰራባቸዋል። በስማቸው የታመመ ይድንባቸዋል። የተለከፈ ይሻርባቸዋል። በሌላ አገላለጽ በወሎ የታመመ በፀበላቸው ተጠምቆ ይድናል። እምነታቸውን ተቀብቶ ይፈወሳል። በመስቀላቸው ታሽቶ ከደዌ ይነፃል። እነሱንም በመማጸን ልጅ ያጣ ልጅ ያገኛል።

የወሎ ሰው በነዚህ ቅዱሳን ቦታዎች (መካናት) ተገኝቶ ቅጠላቸውን በጥሶ፣ አፈራቸውን ቆንጥሮ፣ አጥራቸውን ስሞ፣ ግድግዳቸውን ዳብሶ መልካም ነገር ሊያገኝ እንደሚችል ያምናል። በነሱ አማካኝነት ፀጋን፣ ፍቅርና ሠላምን ለራሱ፤ ለቤተሰቦቹና ለጎረቤቶቹ እእዲቸሩት ይመኛል። ከክፉ ስሪ፣ ከነገር ቆፋሪ እንዲጠብቁትም ይማፀናል።

ከድርቅና ከረሃብ፣ ከበሽታና ከቸነፈር እንዲታደጉት ኃላፊነቱን ለነዚህ መላዕክት፣ ጻድቃን፣ ነቢያትና ሰማዕታት አደራ ይሰጣል። የሚሻውን ለማግኘት ደግሞ በስማቸው ስዕለት ይሳላል። ሃጃው ሲሞላለትም ስዕለታቸውን ያገባል። የጠየቀውን ሰለፈጸመለት፤ አንዳንድ ጊዜም ቁጣቸው እንዳይደርስበት በዓላታቸውን ያከብራል። እነሱን ለማስታወስና ለመዘከርም በስማቸው ማኅበር ይመሰርታል። በመሰረተው ማኅበር ስም ደግሞ ጠላ ጠምቆ ፀበል ያጠጣል። ዳቦ ጋግሮ ፃዲቅ ይዘክራል። ምጽዋት ይመጸውታል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወሎ መሰሊመ ሞምር ከክርስቲያኑ ጋር በመሆን የጽላታቸውን ማደሪያ ይሰራል፤ ይጠብቃል፤ ይንከባከባል። በክብረ-በዓላቸው እለትም ታቦታቸውን አጅቦ፤ አመቆና አድምቆ ወደ መንበራቸው ይመልሳል።

ይህም ማለት የክርስትና ሃይማኖት ትውፊት በወሎ፤ የክርስቲያኑ ብቻ ሳይሆን የመሰሊመም የጋራ እሴት ነው። ለምሳሌ ፀበል መጠመቅ በክርስትናው በኩል የሚገኝ ትውፊት ነው። ነገር

ግን በወለ፡ ሙስሊሞችም ጤንነትን ለማግኘት ሲሉ ፀበል ይጠመቃለ፡፡ እምነት ይቀባለ፤ መስቀል ይታሻለ፡፡ በዚህ የተነሳ ሙስለሞቹ እንደ ክርስቲያኖቹ ሁለ በዓላት ያከብራለ ዝክርም ይዘክራለ፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚለት የዚህ አይነቱ ትውፊት የወለዬዎች የጋራ ባህል፣ ወግና ልማድ ነው፡፡ በዚህ ባህል፣ ወግና ልማድ መሰረት በወለ ሙስሊሞች በቁስ አስባርከው ዝክር ይዘክራለ፤ የበረከቱም ተካፋይ ይሆናለ፡፡[89]

5.2.1፡-ዝክር

ዓለሙ ኃይለ በመርሣ ከተማ የ02 ቀበሌ ነዋሪ ናቸው፡፡ የዚህ አይነቱን የጋራ እሴት የሚገልጹት "ድሮ ሚካኤል እዚህ ሳይወርድ እዚያ ላይ ሳለ ሙስሊሙ ይዘክር ነበረ፡፡ የጥር ሚካኤል ታቦቱን አስገብተን ስንመለስ በየሙስሊሙ ቤት እየዞርነ እንጠጣ ነበረ፡፡"[90] በማለት እሳቸው በተግባር ያለፉበትን የወለዬዎች የእርስ በርስ የግንኙነት ሁኔታ ምሳሌ በመጥቀስ ነው፡፡ በተመሳሳይ መላኩ ተገኘ እንደሚለት በታቦት ስም ድግስ ደግሶ ዝክር መዘከር በወለ፤ የክርሰቲያኑ ብቻ ሳይሆን የወለ ሙስሊሞችም የጋራ ትውፊት ነው፡፡ ለዚህም የዋሂለ ተክለሃይማኖት ሙስሊሞችን እሴት ለአብነት ይጠቅሳለ፡፡ እሳቸው እንደሚለት "በዚያ አካባቢ ያለ እስላም በጠቅላላ ቁስ ጠርቶ አስባርኮ፣ አዘክሮ፣ የታጎማስ ተክለሃይማኖትና የነሐሴ ተክለሃይማኖት ሲያበላ-ሲያጠጣ ይውላል!" በማለት በተግባር ያዩትን ትውፊት ለምሳሌ ይጠቅሳለ[91]

የዚህ ጥናት አቅራቢ በበኩሉ በጉባላፍቶ ወረዳ አማየ ሚጫ ገጠር ቀበሌ በሚገኙ ሙስሊሞች የሚያዚያ ጊዮርጊስ ዝክር ተጋብዞ ያውቃል፡፡ አጥኚው እንደሚያስታውሰው የአማየ ሚጫ የገጠር ቀበሌ ነዋሪዎች እንደ ክርስቲያን ጎረቤቶቻቸው ሁለ፤ ሚያዚያ ጊዮርጊስን እየዘከሩ እንግዳ ያስተናግዳለ፡፡ ጠላ ጠምቀው በአካባቢያቸው የሚያልፉ መንገደኞችን ሳይቀር የጊዮርጊስን ፀበል ቅመሱ ይላለ፡፡ በጊዮርጊስ ስምም "አመት ከአመት በሠላምና በጤና ያድርሳችሁ! ጊዮርጊስ የከርሞ ሰው ይበላችሁ!" ተብለው ባስተናገዷቸው እንግዶች ይመረቃለ፡፡ እነሱ የሚፈልጉትም ይህንን ትውፊት ነውና የእንግዶቻቸውን በረከት "አሜን!" ብለው ከልብ ይቀበላለ፡፡ በዚህም ውስጣዊ እርካታን ያገኛለ፡፡

---

[89] አሰፋ አበጋዝ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ፡፡
[90] ዓለሙ ኃይለ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 02 ቀበሌ፡፡
[91] ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 17 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ፡፡

ከዚህም ሌላ የዚህ ጥናት አቅራቢ ጥናቱን በሚያካሂድበት ወቅት በሐብሩ ወረዳ በቁጥር 14 ቀበሌ ነሐሴ 24 ቀን 2007 አ.ም. የወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት ክብረ በዓል ላይ ተገኝቶ ነበር። በዚያን ወቅት እለቱን በማስመልከት "በጌታው ቀዬ" ሙስሊሞች የተክለሃይማኖትን ዝክር ተካፍሏል።

በዚህ ሂደት አጥኚው ሁለት መሰረታዊ ቁምነገሮችን ለመረዳት ችሏል። አንደኛው መሰረታዊ ነጥብ "አውድን መሰረት በማድረግ የአንድን ማኅበረሰብ በፎክሎሩ አማካይነት ማጥናት፤ የዚያን ማኅበረሰብ አስተሳሰቡንና አመለካከቱን፣ እምነቱን፣ ፍልስፍናውንና ባጠቃላይ ማንነቱን ማወቅ ይቻላል" የሚለውን የፎክሎር አስተሳሰብ በተግባር መረዳት መቻሉ ነው። በዚህ መሰረት ሙስሊሞች በወሎ ዝክር የሚዘክሩት ለሃይማኖታዊ መርህ ብለው ሳይሆን፤ ለኑሯቸው፣ ለጤናቸው፣ ለአካባቢያቸው፣ ለአዝመራቸው፣ ለከብቶቻቸው..ወዘተ ብለው ነው። እንድንበታለን፣ በረከትም እናገኝበታለን፣ በሠላምና በፍቅር እንኖርበታለን በሚል እምነት ነው። ይህም ሃይማታዊ ጉዳይ ሳይሆን ፎክሎራዊ ብሂል ነው።

አጥኚው የተረዳው ሁለተኛው ቁምነገር ደግሞ ሙስሊሞቹ ዝክር የሚዘክሩት ለሃይማኖታዊ ጉዳይ ወይም ሃይማኖታዊ ለሆነው ዶግማና ቀኖና ብለው ሳይሆን፤ ለአካባቢው ባህል፣ ወግና ልማድ ሲሉ ነው። ይህም ከአኗኗራቸው፣ ከማኅበራዊ መስተጋብር ዘይቤያቸው የሚመነጭ ነው። ምክንያቱም በወሎ ክርስቲያንና ሙስሊም የሚኖረው በጉርብትና ተሳስሮ ነው። በዚህም ሚስቱ ቢሉ ልጆቹ፣ እርሻው ቢሉ ከብቶቹ በአንድ ላይ ያሉና በአንድ ላይ የሚኖሩ ናቸው። በዚህ መሰረት የአንዱ በረከት ለሌላው ይተርፋል። መርገምቱ ወይም ጥፋቱ ለአንዱ መጥቶ ለሌላው አይቀርም። ለምሳሌ ድርቅ ይሁን በሽታ፣ አንበጣ ይሁን ተምች፣ በረዶ ይሁን ንፋስ...ወዘተ ለክርስቲያኑ መጥቶ ሙስሊሙን አይለይም፤ ለሙስሊሙ መጥቶ ክርስቲያኑ አያመልጥም።

ስለዚህ ይህ እንዳይሆን አንዱ የሚያደርገውን ሌላውም አብሮ ያደርጋል። የዚህ አይነቱ ትውፊት ደግሞ ወሎዬዎች እርስ በርስ ተሳስረው፣ ተግባብተውና ተስማምተው በሠላምና በፍቅር በጋራ እንዲኖሩ የሚያደርግ እሴት ነው። በመሆኑም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለፀው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ መስተጋብር አማካይነት ነው። የእሴቶቹ አይነትና ብዛት ደግሞ እንደየ አውዳቸው በአይነት የተለያዩ፣ በቁጥርም በርካታ ናቸው። ክዋኔያቸውና ፋይዳቸውም በዚሁ አንፃር የሚታይ ነው። ከነዚህ መካከል የጥምቀት በዓል አንዱ ነው።

5.2.2፦ ጥምቀት

የገናና የጥምቀት ክብረ-በዓላት ሃይማኖታዊ እሴቶች እንዳሏቸው ሁሉ፤ ባህላዊ እሴቶችም አሏቸው፡፡ ሃይማኖታዊ እሴቶቹ የክርስቲያኖቹ መገለጫዎች ሲሆኑ፤ ባህላዊ እሴቶቹ በበኩላቸው የክርስቲያኖቹና የሙስሊሞቹ የጋራ መገለጫ እሴቶች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት በወሎ በጥምቀት ክብረ-በዓል ላይ ሙስሊሞቹ ከክርስቲያኖቹ ጋር እኩል "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ!" እንዲሉ፤ አምረው፣ ተውበውና ደምቀው ሆ! እያሉ፣ እየጨፈሩና እየዘፈኑ ታቦት አጅበው ያስገባሉ፡፡ በወሎ ያለውን የክርስቲያኖችና የሙስሊሞች ሠላም፣ ፍቅርና መከባበር የዚህ ጥናት መረጃ አቀባዮች በጥምቀት አብነት እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> አሁን ሐራ ማርያም ብትሂድ "ሠይዴ! ዛሬኮ ማርያም ናት! እንሂድና ሆ! ብለን ጨፍረን እናስገባት እንጂ አቦ!" ብለው ጨፍረው፣ አንድ ቦታ ላይ ቆመው ሳይሆን ከክርስቲያኖቹ ጋር ሦስተ ጊዜ ዞረው "ወላሂ! ዛሬ ማርያም እንዴት ደምቃለች አቦ!" ብለው፤ እየጨፈሩና እያስጨፈሩ ውለው፤ አድምቀው፣ አክብረው ነው፤ የሚመለሱት፡፡ ሲመለሱም ከድግሱ አብረው በልተው፤ ጠጥተው ነው፡፡[92]

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወሎ ክርስቲያኑ ባነሰበት አካባቢ አብዛኛውን የቤተ-ክርስቲያን ወጪ መስለሞቹ እንደሚሸፍኑ ሁሉ፤ ጥምቀትን የሚያነግሱትም ብዙዎቹ መስለሞች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በራያና ቆቦ ወረዳ ኢሉ ኪዳነ ምህረት፣ በጉባ ላፍቶ ወረዳ ሐራ ማርያምና ቂሌ-ሃዳሚ ጊዮርጊስ፤ በሐብሩ ወረዳ አድርሶ ጅሮ ሚካኤል፣ ወረ-ካሎ ተክለሃይማኖትና ጊራና ጊዮርጊስ ለዚህ አባባል የሚጠቀሱ አብነቶች ናቸው፡፡ በጥምቀት መስለሞቹ መዝፈንና መጨፈር ብቻ ሳይሆን፤ ታቦቱን የሚያወድሱ የዘፈንና የጭፈራ ግጥሞች እያወጡ ጭምር ይዘፍናሉ፤ ያስጨፍራሉ፤ ያቀነቅናሉ፡፡ መላኩ ተገኘ ይህንን እሴት የሚገልጹት እንደሚከ ተለው ነው፡፡

> አሁን እዚህ ወልዲያ መሐመድ አዲስ እሚባል ሰው አለ፡፡ ዱሮም እነ የሱፍ ዓሊ የሚባሉ ነበሩ፡፡ አሁን እነሱ እንደው በዚህ ላበታቸው እስቲወርድ ድረስ እየጨፈሩ ታቦቱን አዙረው ያስገቡ ነበር፡፡ በጥምቀት የክርስቲያን ሆታ፣ የሙስሊም ሆታ የሚባል ነገር የለም፡፡ የጭፈራውንና የዘፈኑን ግጥም ከቻለና ጥሩ ድምጽ አለው ከተባለ እከሌ ከእከሌ የለም፡፡ መስለሙም ክርስቲያኑም ይጨፍራል፤ ያስጨፍራል፡፡ ይኸ ባህላችን ነው፡፡ አሁንም አለ፡፡[93]

እንድሪስ አህመድ በበኩላቸው "አሁን አብዱ ሱረር እሚባል የኔ ጓደኛ ነበረ፡፡ አሁን እሱ መስለም ነው፡፡ ግን የጥር ሚካኤል እለት እሱ ነው የሚያስጨፍረው፡፡ ወጣቱን እያስጨፈረ

---

[92] ሞላልኝ ወርቁ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- መሀል መቻሬ፡፡

[93] ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 6 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ፡፡

ታቦቱን አጅቦ ይዞ እሚገባው እሱ ነው።"[94] በማለት የጥምቀት ጭፈራ በወሎ የሙስሊም-ክርስቲያኑ የጋራ እሴት መሆኑን ይገልጻለ። በዚህ መሰረት የጥምቀት ክብረ-በዓል ባህላዊ ገጽታው ወይም የጭፈራና የዘፈን ትውፊቱ ወንዶቹም ሆኑ ሴቶቹ የሙስሊም ልጆች እንደ ክርስቲያኖቹ ልጆች እኩል የሚሳተፉበት የጋራ እሴ ነው። በዚህም እንደ ክርስቲያኖቹ ሁሉ ሙስሊሞቹም ተደስተውና ተዝናንተው ታቦቱን አጅበው አስገብተው ወደቤታቸው ይመለሳሉ። በቤት ውስጥ በሚዘጋጀው ምግብና መጠጥም ተካፋይ ይሆናሉ።

በጥምቀት ለሃይማኖታዊው ጉዳይ ከሚወጡት ምእመናን በስተቀር፤ ወጣቱ እንደየ አድሜ ክልሉ የክርስቲያኑም ሆነ የሙስሊሙ አለባበስ ተመሳሳይ ነው። የፀጉር አሰራሩም ሆነ አጊያጊያጡ ሃይማኖቱን መሰረት ያደረገ አይደለም። በዋናነት ባህሉን መሰረት ያደረገ ነው። በመሆኑም በጥምቀት ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ ባለባበሱ አንድ አካል አንድ አምሳል ነው። የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት በገጠር ሁሉም እንደየአቅሙ ለጥምቀት ክርስስያኑም ሆነ ሙስሊሙ ለልጆቹ አዲስ ልብስ ይገዛል። አቅም እንኳን ባይኖረው፤ አቅም ያለው ሙስሊም ጎረቤት ለክርስቲያኑ ልጅ ለገናና ለጥምቀት ብሎ ልብስ ሊገዛለት ይችላል። በተመሳሳይ አቅም ያለው ክርስቲያን ጎረቤት አቅም ለሌለው የሙስሊም ልጅ ከክርስቲያን ጓደኞቹ ተለይቶ እንዳይውል ለጥምቀት አዲስ ልብስ የመግዛት ጎረቤታዊ ግዴታ አለበት።[95]

በገጠር ሙስሊሙ የጥምቀት እለት ልጁ ከብት እንዲጠብቅ አያስገድድም። በምትኩ ከብቶቹን እሱ እራሱ እየጠበቀ፤ ልጁ ጥምቀት ሄዶ ጨዋታ እንዲጫወት ይፈቅዳል። ልጁም ጥምቀት ሄዶ ታቦት አጅቦ ሲዘፍንና ሲጨፍር ውሎ፤ ከክርስቲያን ጓደኞቹ ቤት አግልሎ በልቶ ጠጥቶ ማታ ወደ ቤቱ ይመለሳል። ሙስሊም እናት በበኩሏ፤ ሴት ልጇ ትፍትፏን ለብሳ፤ ጸጉሯን ጋሜና ቃሪሳ ተሰርታ ጥምቀት ሄዳ እንድትጫወት ትፈቅዳለች።[96] ምክንያቱም እሴቱን አባትም እናትም ያለፉበት የማኅበራዊ ሕይወታቸው አንዱ አካል ስለሆነ ልጆቻቸውም በዚህ ሂደት ማለፍ እንዳለባቸው ያስባሉ፤ ያምናሉ፤ ይፈቅዳሉ።[97]

በዚህ መሰረት ጥምቀት በወሎ፤ ሃይማኖታዊ እሴትነቱ ለክርስቲያኖቹ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከዚሁ ጎን ለጎን የሚከወነው ፎክሎራዊ የሆነው ጉዳይ ግን የክርስቲያኑም የሙስሊሙም ልጆች በጋራ የሚደሰቱበትና የሚዝናኑበት ህዝባዊ በዓል ነው፤ማለት ይቻላል። ለክርስቲያኑም

---

[94] እንድሪስ አህመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 03 ቀበሌ።
[95] መለሰ ድንቁ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሣ- 01 ቀበሌ።
[96] ሶፍያ መሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 18 ቀን 20006 ዓ.ም. ራያና ቆቦ- ሮቢት።
[97] ከዲጃ ከድር፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 16 ቀን 2006 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ሐራ።

ለሙስሊሙም የመገናኛ፣ የመተያያና የመተዋወቂያ መድረክ ነው። በመሆኑም ሙስሊም ወጣቶች እንደ ክርስቲያን ወጣቶች ሁሉ፤ በጥምቀት በዓል ላይ ለሚ ወርውረው እሮኛም ቢሉ ፍቅረኛ ያገኛሉ። በዚህም ሙስሊሙ እንደ ክርስቲያኑ ለጥምቀት በዓል ፍቅር አለው፤ ጉጉት አለው፤ ትዝታ አለው። እንድሪስ አህመድ ያደጉበትን የደንካ ሚካኤል ትዝታ እንደሚከተለው ያስታውሱታል።

> ጥምቀት ውሎ ሌሎቹ ታቦቶች ከገቡ በኋላ፤ በበነጋው ሚካኤል ሲገባ፤ ክርስቲያን እስላም አይልም። በአብዛኛው እንዲያውም ሙስሊም ነው ሆ! እያለ ታቦቱን አጅቦ እዚያው ቤተ-ክርስቲያኑ አስገብቶ ነው እሚለያየው። ከዚያ ዘፈን አለ "ሆለሌ!" እሚባል። እዚያ "ሆለሌ!" እሚሉት ሴቶች በአብዛኛው የሙስሊም ልጆች ናቸው። ወንዱም ይጨፍራል። የከንፈር ወዳጅ እሚባል ነገር አለ። ያም እዚያ ላይ ይፈጸማል። ስለዚህ ጥምቀት ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ከከንፈር ወዳጅ ጀምሮ እስከ እሮኛ ድረስ የሚተጫጨበት በዓላቸው ነው። በኛ አገር በጥምቀት በዓል ላይ ክርስቲያን ሙስሊም እሚባ ልዩነት የለም።[98]

ባጠቃላይ የጥምቀት በዓል በወሎ ክርስቲያንና ሙስሊሙን በጋራ የሚያገናኝ ድልድይ ነው።እርስ በርስ የሚያስተሳስር የጋራ እሴት ነው። በመሆኑም ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው አንዲኖሩ ካስቻሏቸው የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ የጥምቀት በዓል ነው። ይህንን አባባል የአካባቢው ነዋሪዎች "እኛ ይዘን የምናድገው በጎረቤት የምናየውን ነገር ነው። በኛ አገር ደግሞ ጉርብትና ‹እስላም-ክርስቲያን› በሚል አጥር የታጠረ አይደለም። በዚህ መሰረት በአብዛኛው ባህላዊ በሆነው ጉዳይ ይኸኛው የሙስሊም በዓል ነው። ይኸኛው የክርስቲያን በዓል ነው፤ የሚል ልዩነት የለም። ስለዚህ የጥምቀት በዓል የሁሉም ነው። ገና ጨዋታውም የሁሉም ነው።"[99] በማለት ያረጋግጣሉ። በተለይ የገና ጨዋታ በወሎ ከሙስሊሙ ጋር የሚገናኝበት ሂደት አለው። ሂደቱን አበጋር ማዱ በላይ በሚከተለው ሁኔታ ይገልጹታል።

> በገና ጊዜ እስላም ክርስቲያኑ ገናውን ከርክሞ ይጫወታል። ማታ ስንለያይ አበጋሩ ይመጣል፤ ሊመርቅ። "እንግዲህ ከርሞ እህነየ ሳትለዩ ሳትጎነጠሉ በሠላም ያድርሳችሁ!" ብሎ ይመርቃል። በመጨረሻ ያ ሁሉ ገና አንድ ሳይቀር ተሰብስቦ ለአበጋሩ ይሰጠዋል። አበጋሩም ያንን ሁላ ገና አሸክሞ ወደ ቤቱ ይሄዳል። (ለምን?) አሃ! ኸፊት የተገኘ ባህል ነዋ! ቡን ሊያፈላበት! ማገዶ ሊያደርገው ነዋ! እምሬ እኮ ነው! ገና ደሞ ግጥም አለው። ያሸነፈው ቡድን ተሸናፊውን አካል የሚነካ ግጥም እየገጠመ ሆ! ይላል! ስድብም አለ። ምንም አለ። ለምሳሌ "የውርሴ ደበሎ!" እሚባል ግጥም አለ። እንዲህ ይላል፤
>
> የወርሴ ደበሎ-የደበሎ-አሃሃ! የደበሎ-የወርሴ ደበሎ
>
> እገሌ አባባሉን አሃሃ! የደበሎ-የወርሴ ደበሎ
>
> አገሩን ማን አውቆ አሃሃ! የደበሎ-የወርሴ ደበሎ

---

[98] እንድሪስ አህመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 10 ቀን 2997 ዓ.ም. ወልዲያ- 03 ቀበሌ።

[99] ደሳለ ፈንታው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 20 ቀን 2007 ዓ.ም. ራያና ቆቦ- አራዶም።

ጎርፍ አመጣው እንጂ አሃሃ! የደበሎ-የወርሴ ደበሎ

ከገደሉ ፍቆ አሃሃ! የደበሎ-የወርሴ ደበሎ

ይኸ እንግዲህ መጨውን ሲሰድብ ነው፡፡ ቆለኛው ደገኛውን ሲሰድብ ነው፡፡ ግን ቀየሜታ እሚባል ነገር በገና ጨዋታ የለም፡፡ በመጨረሻ ሁሉም ሆ! እያለ ወደቤቱ ይመለሳል፡፡ ይኸ ባህሉ፣ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ ነው፡፡ ዛሬ ግን ቀርቷል[100]

5.2.3፡- ፀበል

ይኸ ጥናት በተካሄደባቸው ወረዳዎች በርካታ የፀበል ሥፍራዎች ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በጉባላፍቶ ወረዳ ሻል መድኃኔዓለም፣ እማየ ሚጫ ጊዮርጊስ፣ ዶሮ ግብር ጊዮርጊስና ዋሌ ኢየሱስ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በሐብሩ ወረዳ ጋቲራ ጊዮርጊስ የታወቀ የፀበል ሥፍራ ነው፡፡ በራያና ቆቦ ወረዳ ደግሞ አራዶም አካባቢ የሚገኙት የጎሊና ፀበሎች ይጠቀሳሉ፡፡

የጤና እክል የገጠመው ወይም እርኩስ መንፈስ የተጠናወተው፣ አጋንንት የለከፈው፣ ቡዳ የበላው፣ እጁ-ሰብ ያስቸገረው...ወዘተ ክርስቲያንም ሆነ ሙስሊም በወሎ፤ በልቡ አምኖ ካልሆነም እጣ ጥሎ ወይም በቃልቻ አስጠንቁሎ አለያም በደብተራ አስነግሮ እንደየ እጣ ክፈፍሉ፤ ጤንነቱን ለማግኘት ወደነዚህ የፀበል ቦታዎች ይሄዳል፡፡ ከፀበላቸው አልፎ እምነታቸውን ይቀባል፡፡ መስቀላቸውን ይታሻል፡፡

የዚህ አይነት ትውፊት በወሎ፤ በክርስትናው በኩል የሚገኝ እሴት ነው፡፡ ነገር ግን አገልግሎቱ ለሙስሊሙ ጭምር ነው፡፡ ሙስሊሙ ለጤንነቱ ፈውስ ማስገኛ ሲል የሚገለገልበት ትውፊቱ ነው፡፡[101] ትውፊቱ ለሙስሊሞቹ ወደ ሃኪም ቤት የመሄድ ያህል የሚቆጠር የዘውትር ተግባር ነው፡፡ በወሎ የፀበል ቁምነገሩ ፀበሉን የሚፀበለው አካል ክርስቲያን ወይም ሙስሊም የመሆኑ ጉዳይ ሳይሆን፤ በፀበሉ ተጠምቆ ለመፈወስ ያለው ልባዊ ፍላጎት ነው፡፡

የፀበል ትውፊት በወሎ በዚህ አስተሳሰብ ወይም ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ምክንያቱም ሙስሊሞቹ ይህንን የሚያደርጉት ቅድመ አያቶቻቸው፣ አያቶቻቸውና አባቶቻቸው በዚህ እሴት ተጠቅመው መፈወሳቸውን ስለሚያውቁ ነው፡፡ ስለዚህ ፀበል መጠመቅ ለወሎ ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ ጉዳይ ሳይሆን ባህል፣ ወግና ልማድ ነው፡፡[102] በዚህ መሰረት ፀበል መጠመቅ

---

[100] አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ፡፡

[101] በወሎ እንደ ክርስቲያኑ ፀበል ሁሉ፤ "የሼሆች ውኃ" የሚባል ትውፊት አለ፡፡ ለምሳሌ ደሴ-ገራዶ ቢለን ጊዮርጊስ አጠገብ የሚገኘው የሼህ ዓሊ ጅሩ "ፀበል" ለአብነት ይጠቀሳል፡፡ በዚህ "ፀበል" ሙስሊሙም ክርስቲያኑም በጋራ ይፀበላል፡፡ ለበለጠ መረጃ ሩቅያ ሀሰን 2013፣ ገፅ 193 ይመልከቱ፡፡

[102] ምንጩ እንኳ ሃይማኖት መቀየር በወሎ ለክርስቲያኑም ሆነ ለሙስሊሙ በተለያዩ ምክንያቶች የተለመደ ሁነት ቢሆንም፣ ከፀበል ጋር በተያያዘ አልፎ-አልፎ ከእስልምና ወደ ክርስትና ሃይማኖት የመለወጥ አጋጣሚ ይከሰታል፡፡

በወለኖ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው። ይንን እሴት በተመለከተ የዚህ ጥናት አቅራቢ በአንድ ወቅት ጓደኛው የነገረውን አጋጣሚ እንደሚከተለው ያስታውሳል። ገጠመኙን ከግለሰቦቹ አንደበት ሲወጣ በቅርብ ጊዜ ጓደኛዬ እራሱ በትክክል ያደመጠው እውነት ነው።

ሙስሊም ባልና ሚስት ዘመድ ለመጠየቅ ከወለኖ ወደ ጎንደር ይሄዳሉ። ጎንደር እንደደረሱ ባል አግብታ ሌላ ቦታ የምትገኘው ሙስሊም ልጃቸው መታመሟን የልጃቸው ባል በስልክ ጎንደር ለሚገኙት እናት ነገሯቸው። እናትም ልጃቸው ምን እንዳገኛት፣ መቼ እንደጀመራትና የተደረገላትን የህክምና እርዳታ ሁሉ ጠየቁ። የልጅ ባል በበኩላቸው ያደረጉትን ጥረት ሁሉ በዝርዝር ለእናት በስልክ አስረዱ። በመጨረሻ የእናት ጥያቄ የነበረው "የሆነስ ሆነና ወደፀበል ወስዳችኋታል ወይ?!" የሚል ነበር። ባንፃሩ የልጅ ባል"አይ! ፀበልስ እስካሁን አልወሰድናትም!" የሚል ምላሽ ሰጡ። የልጅቱ እናት በበኩላቸው "በሉ አሁን ሳትውሉ ሳታድሩ ወደ ጊዮርጊስ ፀበል ውሰዷት!" የሚል ትእዛዝ አዘል መልእክት ለልጃቸው ባል አስተላለፉ።[103]

መሪጌታ ቀለሙ ዳኛው የውርጌሣ ከተማ 01 ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት የጋቲራ ጊዮርጊስ ፀበል የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው። ፀበሉ ለክርስቲያኑም ለሙስሊሙም፣ የፈውስ ተምሳሌት ወይም ምንጭ ነው። እንደ መረጃ አቀባዩ ገለጻ በጋቲራ ጊዮርጊስ ፀበል የሃይማት ልዩነት እሚባል ነገር የለም። ይህንንም የሚገልጹት "ያንን ፀበል ያቋቋሙት ከክርስቲያኑ ጋር በመሆን የዚያው አካባቢ ሙስሊሞች ናቸው። እነሱ ተንከባክበው፣ አክብረው ያስከበሩት ፀበል ነው። ለታቦቱም አሳቢም ተቆርቋሪም እነሱ እራሳቸው ናቸው።" በማለት የአካባቢውን ሙሰሊሞች ምሳሌ በመጥቀስ ነው። እሳቸው እንደሚሉት እንኳንስ ፈጣሪ ያፈለቀው ፀበል ቀርቶ ከዚህ በታች በቀረበው ጥቅስ የተገለፀው ትውፊትም ቢሆን የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው።

> አሁን እዚህ በኛ በሰፈራችን አንድ ሙስሊም ቢታመም ቄሶቹ ድርሳነ ሚካኤላችንን ይዘን ሄደን ደግመን ፀብለን፤ ፈዋሹ ፈጣሪ ነው፤ እኛ ለሰበብ ነው፤ ያን ሰው ከደዌው እየፈወስነው አለን በድርሳናችን፤ ሰዎቹ እኛ እንኳ! እኔም ከዚ"ህ አንድ ሰው ከታመመብኝ ሙስሊሞቹ መጥተው ዱዓ አርገው ከህመሙ እንዲፈወሱልኝ አደርጋለሁ። እና ልዩነት የለም በአካባቢያችን ከመሰረቱ ጀምሮ[104]

ይህንንም መሪጌታ ቀለሙ "ሙስሊሞቹ ሃይማኖታቸውን ድረስ እየለወጡ የተቀመጡ አሉ" በማለት የጋቲራ ጊዮርጊስን ፀበል ለአብነት ይጠቀሳሉ።

[103] ለዚህ ጥናት ግብአት ሊሆን እንደሚችል አሰቦ፣ ይሽን ገጠመኝ በቁም ነገር አስታውሶ፣ ታሪኩን የተረከልኝ ጓደኛዬ አብዩ አስማማውን ከልብ አመሰግናለሁ።

[104] መሪ ጌታ ቀለሙ ዳኛው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሣ- 01 ቀበሌ።

ውዱ ጣፊጠ (2004 ዓ.ም.፤ 204) በበኩላቸው ቀሲስ ሃዲስ የተባለ ጓደኛቸውን ጠቅሰው ስለ ጋቲራ ጊዮርጊስ የሚከተለውን ገጠመኝ ፅፈዋል፡፡

> ...[ጓደኛዬ] ኢትዮጵያ የመጣው በ2000 ዓ.ም. ነበር፡፡ ዘመዶቹን ለመጠየቅ ወደ ውርጌጣ (ወሎ) በሄደበት ጊዜ ያጋጠመው ነው፡፡ ውርጌጣ ከተማ አጠገብ በከተማው በስተምእራብ በኩል ካለው ተራራማ ጥግ በደርግ ዘመን የወጣ ጋቲራ ጊዮርጊስ የተባለ የፀበል ቦታ አለ፡፡ ቤተ-ክርስቲያኑና ፀበሉ የሚገኘው ሙስሊሙ ጎብረተሰብ በሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡ ካህናቱ የሚያገኙት ቀለብ አነስተኛ ሆኖባቸውና መሬትም ስለሌላቸው በየጊዜው እየለቀቁ ይሄዳሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ቤተክርስቲያኑ እንዳይዘጋ የአካባቢው ሙስሊሞች ገንዘብ እያዋጡ ለካህናቱ ይከፍሉ ነበር፡፡

ከዚህም ሌላ ክርሰቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ በወሎ፤ እድሜና ጤና ለማግኘት ወይም በረከት በመመኘት፤ በያመቱ በነሐሴ ወር መጨረሻ አካባቢ በእለተ ሩፋኤል ዝናብ ከዘነበ ዝናቡ እንደፀበል ስለሚቆጠር በፀበል መልክ ይፀበላል፡፡ እንዲሁም በያመቱ በእለተ-ጳጉሜ በሌሊት ተነስቶ ወንዝ ወርዶ እየዘፈነና እየተጫወተ "ውኃውን ወፍ ሳይቀምሰው!" በሚል ብሂል ገላውን ይታጠባል ወይም ይፀበላል፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች የጳጉሜን ትውፊት የሚገልጹት "በጳጉሜ በሚደረገው የገላ መታጠብ ሥርአት በተለይ በገጠሩ አካባቢ እስላም-ክርስቲያን አይልም፡፡ ሁሉም ይታጠባል፡፡"[105] በማለት ትውፊቱ ያለና የነበረ የጋራ እሴት መሆኑን በማብራራት ጭምር ነው፡፡ከዚህ በላይ እንደተብራራው ባጠቃላይ ፀበል መጠመቅ በወሎ፤ ለክርስቲያኑም ሆነ ለሙስሊሙ የፊውስ ሰበብና የመልካም ነገር ተምሳሌት ነው፡፡ የክፋ ነገር መከላከያ መሣሪያ ነው፡፡በዚህ መሰረት የፀበል ትውፊት በወሎ ክርስቲያኖቹና ሙስሊሞቹ እርስ በርስ የሚተሳሰሩበት፣ የሚገናኙበት፣ የሚተዛዘኑበት፣ የሚረዳዱበት፣ የሚደጋገፉበት፣ በመቻቻልና በመከባበር በሠላምና በፍቅር አብረው የሚኖሩበት የጋራ እሴት ነው፡፡

ለምሳሌ ፀበል ባለበት አካባቢ በጎን የቤተ-ክርስቲያን ድምጽ ይሰማል፣ በጎን ደግሞ የፀሎት መፅሐፍ ይነበባል፡፡ በጎን የመዝሙር ድምፅ ይሰማል፡፡ በጎን ታቦታቱ የሰሩት ተአምራት ይነገራል፡፡ በጎን ደግሞ ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ ጋር አብሮ ይፀበላል፡፡ በዚህ ሂደት ክርስቲያኑ ሙስሊም ለምን ከክርስቲያኑ የፀበል ቦታ ይገባል? የሚል "ሰይጣናዊ" ጥያቄ አይጠይቅም፡፡ ሙስሊሙ በበኩሉ ከክርስቲያቹ የፀበል ቦታ ለምን እሄዳለሁ? ብሎ አያመነታም፡፡ ምክንያቱም ዋና ዓላማው መዳን፣ መፈወስና በረከት ወይም መልካም ነገር ማግኘት ነው፡፡ ለዚህም ነው፤ ሙስሊሙ "ፅላቱ የክርስቲያኖቹ ብቻ ሳይሆን፤ የኛም ቅርስና ንብረት ነው!" የሚለው፡፡ ሙስሊሙ ይህንን የሚለው ፀበሉ ከላይ የተጠቀሰው አይነት የጋራ የሆነ ፎክሎራዊ እሴት ስላለው ነው፡፡ ለምሳሌ ከዚህ በታች የቀረቡት የወረ- ካሎ ተክለሃይማኖት ሃይማኖታዊና

[105] ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፣ ቃለመጠይቅ፣ ነሐሴ 21 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ፡፡

ፎክሎራዊ ክዋኔዎች በክርስትናው በኩል ከዚህ በላይ ለተገለፁት የጋራ እሴቶች ማረጋገጫ አብነቶች ናቸው።

5.2.4፡- ወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት

ወቅቱ ነሐሴ 24 ቀን 2007 ዓ.ም. ነው። እለቱ የነሐሴ ተክለሃይማኖት አመታዊ ንግሥ ነው። በዚህ እለት "በያመቱ ነሐሴ 24 ቀን በሚከበረው የወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት ንግሥ ላይ የሚገኙት ክርስቲያኖቹ ብቻ ሳይሆኑ፤ ከተለያዩ አካባቢዎች ተሰባስበው የሚመጡ ሙስሊሞችም ጭምር ናቸው!" የሚለውን አባባል ለማረጋገጥ የዚህ ጥናት አቅራቢ በእለቱ በቦታው ላይ ተገኝቶ ነበር። አጥኚው ከውርጌሣ ከተማ ተነስቶ ከቦታው የደረሰው ከጧቱ 12 ሠዓት ላይ ነበር። በጉዞው ወቅት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ወደ ንግሥ ቦተው የሚሄዱ ክርስቲያንና ሙስሊም ተጓገሮችን አስተውሏል። ሁለቱም በአንድነት ወደ ወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት ዓመታዊ የንግሥ በዓል የሚጓዙ ናቸው።




ፎቶግራፍ ሰባት፡- የወረ ካሎ ተክለሃይማኖት አካባቢያዊ ገጽታና ቤተ-ክርስቲያን።

ክርስቲያኖቹ ሃይማኖታዊ አምልኳቸውን አድርሰው የተክለሃይማትን ፀጋ ለማግኘት የሚጓዙ ምእመናን ናቸው። ሙስሊሞቹ ደግሞ "የተክልየን" ፀበል ጠጥተው፣ እምነታቸውን ተቀብተው፣ መስቀላቸውን ታሽተው፣ በልባቸው የሚሹትን በረከት ለማግኘት ወደ ቦታው የሚሄዱ ተጓገሮች ናቸው። ከነዚህ ሙስሊም ተጓገሮች መካከል ሙሉ ደሳለኝ አንዱ ነበሩ። እሳቸው ሙስሊም ሆነው ሳለ፤ ወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት የንግሥ በዓል ላይ የተገኙት ግን ከክርስቲያኖቹ ጋር

እኩል ገና በማለዳ ነው። ለዚህ ደግሞ ምክንያት አላቸው።።ምክንያታቸውን እንደሚከተለው ያብራሩታል።

> መጀመሪያ ከልቤ ላይ እበጥ ወጣብኝ። በኃኪም ብል፣ ብል እምቢ አለኝ። እምቢ ስላለኝ እጣ ጥዬ ለተክለሃይማኖት ወጣልኝ። ተክለሃይማኖትዋ አድኑኝ ብዬ አሻሸቹ እምነቱን ቅብት ሳረገው ዳንኩኝ። ሚሚልኝ። የሚሚልኝ ግዜ እንግዲህ አላህዋየ! ተክለሃይማትዋ! አድነውኛል አሁን በዚኽው እቀጥላለሁኝ፤ መቀጫም አልወቅጥ፣ ቅጠልም አልበጥስ፣ ባንቱ ግዜ፤ ኩብር ብዬ በቃ! ደስተኛ ሆኜ ነው የምቀመጠው፤ ብዬ ያው በዓመቱና በስድስት ወሩ እየመጣሁ አከብራለሁኝ። ልጄም እንደኔ እበጥ ወጥቶበት ቆየ፤ የተክለሃይማኖትዋየን እምነት ቅብት ሳረገው ዳነ። (ስዕለት ያገባሉ?) ስዕለት ደግሞ ያው በዓመትና በስድስት ወሩ አገባለሁ። ዛሬ እንኳ ለተክልዬ ጥላ ገዝቶ እንዲያመጣልኝ የላኩት ሰው ነበረ እስካሁን ጥላውን ይዞ አልመጣልኝም። በጣም ነው የተናደድኩት። አሁንም ታቦቱ እስቲገባ ድረስ ይመጣል ብዬ እየጠበቅኩት ነው[106] (ብስጭታቸውና ቅሬታቸው ከንግግራቸውና ከፊታቸው ላይ ይነበባል)።



ፎቶግራፍ ስምንት፡- ወ/ሮ መ.ሉ ደሳለኝ፤ የወረ-ካሎ ተ/ሃይማኖት ዓመታዊ ንግሥ ላይ። ነሐሴ 24ቀን 2007 ዓ.ም.።

ፀሐይነሽ አማረ አንዱን አዝለው፤ ሌላውን አስከትለው ከሁለት ሕጻናት ልጆቻቸው ጋር እንደ መ.ሉ ደሳለኝ ሁሉ በተክለሃይማኖት ንግሥ ላይ በጥዋት ተገኝተዋል። የተገኙበት ምክንያት በራሳቸው አንደበት "አኔ መ.ስሊም ነኝ። ግን ለልጆቼ ጠበልም ልወስድ፣ እምነትም ልወስድ ነው፤ የመጣሁት። መቼም ተክለሃይማኖት የጋራችን ነው። ትናንት እኛ ስንጋገር ዋልነ፤ እንጀራውን። እኛ ተባብረን ነው የምንሰራው። አንድ ላይ ነን። የሚለያየን ካራ [ቢልዋ] ብቻ

[106] መ.ሉ ደሳለኝ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 24 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ።

ነው።።"[107] በማለት ይገልጹታል። የሐዋ በድሪ ጉዳይም ከፀሐይነሽ አማረ ጋር ተመሳሳይ ነው። አመጣጣቸው ለታመመ ልጆቻቸው ፈውስ ለማግኘት በመሻት ነው።

> የመጣሁት ተክለሃይማኖት በዓመት የሚውል ስለሆነ ነው። እምነቱን ወስጄ ልጆቼ እንዲድኑልኝ ነው፤ የመጣሁት። ልጆቼን ሲያምብኝ ግዜ ተክለሃይማኖት ውሰጃቸው ሲሉኝ ይጎቸው መጣሁ። እና ያው ባህሉ የክርስቲያን ባህል መሆኑን አውቃለሁ። ግን ዙሮ ዙሮ መቼም እምነት ካለ ይድኑልኛል በሚል ተስፋ ይጎቸው መጥቻለሁ። ከቤትም ቢሆን እነሱ ሲዘክሩ ሲጠሩን እኛ እስላም ነን ብለን አንቀርም። ጎረቤቶች ስለሆነ እንሄዳለን።[108]





ፎቶግራፍ ዘጠኝ፦ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አማረ፤ የወረ-ካሎ ተ/ሃይማኖት ዓመታዊ ንግሥ ላይ።።ነሐሴ 24ቀን 2007 ዓ.ም (ከመጀመሪያው ፎቶ ሕፃናት ይዘው የተቀመጡት። ከሁለተኛው ፎቶ ደግሞ ሕፃን አዝለው ፀበል የያዙት)

ሰሚራ ሁሴን፣ ራቢያና ሐያት የመጡት ከመርሣ ከተማ በሌሊት ተነስተው ነው። ሦስቱ ጓደኛሞች ከ22 እስከ 25 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ናቸው። ሦስቱም ወጣቶች ለሥራ ጉዳይ ሳዑዲ አረቢያ ቆይተው ወደ ሀገራቸው የተመለሱት በቅርብ ነው። ራቢያና ሐያት የተክሃይማኖት ንግሥ ላይ የተገኙት ሰሚራ በመታመሟ ምክንያት ነው። የሰሚራ አመጣጥ ግን እግሯ ላይ ቁስል ስለወጣባት እናቷ በመከሯት መሰረት እንደ ሌሎቹ ሙስሊሞች ሁሉ፤ ፀበል ጠጥታ ፣ እምነት ተቀብታና መስቀል ታሽታ ከህመሟ ለመዳን ነው። ሰሚራ በውጭም በሀገር ውስጥም በህክምና ሞክራ ልትድን ባለመቻሏ በመጨረሻ

---

[107] ፀሐይነሽ አማረ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 24 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ።።


[108] ሐዋ በድሪ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 24 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ።።

ተክለሃይማኖት ይፈውሱኛል ብላ በቦታው ላይ ተገኝታለች።[109] ቀጥለው የቀረቡትን ፎቶግራፎች ይመልከቱ።









<u>ፎቶግራፍ አሥር</u>፦ ሰሚራ ከህመሟ ለመፈወስ በተክለ ሃይማኖት የንግሥ ዕለት፣ መስቀል ታሽታ፣ እምነት ተቀብታና ዐበል ይዛ። (ሰሚራ ከመጀመሪያው ፎቶ ዐበል ይዛ፣ ከሁለተኛው ፎቶ ከጓደኞቿ ጋር)።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አራት ናሙናዎች በወረ-ካለሎ ተክለሃይማኖት ንግሥ እለት የተገኙ ሙስሊሞች ዋና ዓላማ ምን እንደሆነ ሊገልጹ የሚችሉ አብነቶች ናቸው። በመሆኑም የሙስሊሞቹ ዋና ዓላማ ካጋጠማቸው የጤና ችግር መፈወስ ነው። ወይም የተክለሃይማትን በረከት ማግኘት ነው።ይህንንም በዚያው በዓውዱ ላይ በትክክል መረዳት ይቻላል። በዚህም በእለቱ በዚያው በቦታው ላይ የነበረው አጠቃላይ ድባብ (አውድ) ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ይመስል ነበር።

[109] ሰሚራ ሁሴን፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 24 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 01 ቀበሌ።

በተክለ ሃይማኖት ንግሥ ላይ የተገኙት ሙስሊሞች ከወንዶቹ ይልቅ ሴቶቹ ይበዛሉ። ከእድሜ አንፃር ደግሞ ሕፃናትን ጨምሮ፤ ከአስራዎቹ አንስቶ እስከ ሰባዎቹ የእድሜ ክልል ሊደርሱ ይችላሉ። ወጣቶቹ ፀበልና እምነት ለመውሰድ ከቤተሰቦቻቸው ተልከው የመጡ ናቸው። አልፎ አልፎ ግን እምነት ለመቀባትና መስቀል ለመታሸት የመጡ ሕፃናትና ወጣቶችም አሉ።

በቦታው ላይ የተገኙት አብዛኛዎቹ ሙስሊም ሴቶች ልጅ ያዘሉ ወይም ሕፃናት ያስከተሉ እናቶች ናቸው። ምክንያታቸው ደግሞ ሕፃናቱ እምነት እንዲቀቡና መስቀል እንዲታሸ በማለት ነው። በቦታው ላይ የተገኙት ሙስሊም ሴቶች አለባበሳቸው ንጹህ ልብስ ከመልበስ የዘለለ ከዘወትር አለባበሳቸው የተለየ አይደለም። ይህም ማለት ለተክለሃይማኖት ንግሥ ብለው የክርስቲያኖቹን አይነት አለባበስ አለበሱም።



ፎቶግራፍ 11፦ በወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት ዓመታዊ ንግሥ ላይ የሙስሊሞቹና የክርስቲያኖቹ አለባበስ።

ሙስሊሞቹ ሴቶቹም ሆኑ ወንዶቹ ወደ ቤተ-ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ሲገቡ ለቤተ-ክርስቲያኑ ያላቸው ክብርና ጥንቃቄ፤ ከክርስቲያኖቹ ቢበልጥ እንጂ፤ የሚያንስ አይደለም። በተለይ በእድሜ ገፋ ያሉት ከወጣቶቹ በተለየ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ጫማቸውን የሚያወልቁት ገና ከቤተ-ክርስቲያኑ ከመግባታቸው በፊት ነው። ካጠቃላይ ሁኔታቸው መረዳት የሚቻለው ደግሞ ቤተ-ክርስቲያኑን የመፍራት ሳይሆን፤ የማክበርና የማፍቀር ስሜት ነው። የእኔነት መንፈስ ነው። ምክንያቱም ሙስሊሞቹ ለተክለሃይማኖት ያላቸውን ክብርና ፍቅር ከፊታቸውና ከሁኔታቸው አንብቦ መረዳት ይቻላል። ሙስሊሞቹ ጫማቸውን አውልቀው ከቤተ-ክርስቲያኑ በር ላይ እንደደረሱ ሁለት ተግባራትን ያከናውናሉ። አንደኛው ተግባር ፀበል የሞሉትን እቃ

ክዳኑን አንስተው ከቤተ-ክርስቲያኑ በር ላይ ማስቀመጥ ነው፡፡ ሁለተኛው ተግባር ደግሞ ፀበሉን ካስቀመጡ በኋላ ያመጡትን ስዕለት ከተዘረጋው ምንጣፍ ላይ ማስቀመጥ ነው፡፡ የሚያመጡት ስዕለት ጧፍ፣ እጣን፣ ብር፣ የተለያዩ የጥራጥሬና የእህል አይነቶች ናቸው፡፡ ስዕለታቸውን ካስቀመጡ በኋላ በእድሜ ገፋ፣ ገፋ ያሉት ሙስሊሞች ከክርስቲያኖቹ ጋር ተቀላቅለው ይቆማሉ ወይም ይቀመጣሉ፡፡

ወጣቶቹ ግን በቡድን በቡድን ሆነው ለብቻቸው መቀመጥን ይመርጣሉ፡፡ ነገር ግን የቤተ-ክርስቲያኑን ሥርአተ-አምልኮ የሚያውክ ምንም አይነት እንቅስቃሴ አያደርጉም፡፡ አያወሩም ወይም ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አይታዩም፡፡ ሌሎች ወጣት ሙስሊሞች ደግሞ ፀበሉን የአምልኮ ሥርአት ከሚፈፀምበት ቦታ ላይ ካስቀመጡ በኋላ ራቅ ብለው ይቀመጣሉ፡፡ ይህንን ያሚያደርጉት ፀበል እንዲያመጡ ከቤተሰብ የተላኩት ወይም ጓደኞቻቸውን ተከትለው የመጡ ሙስሊም ወጣቶች ናቸው፡፡



ፎቶግራፍ12፡- ሙስሊሞቹ ያመጡትን ስዕለት ሲሰጡና የወጣቶቹ ሙስሊሞች አቀማመጥ፡፡ (ከመጀመሪያው ፎቶ ሙስሊሟ ወይዘሮ ስዕለት ሲያገቡ፣ ከሁለተኛው ፎቶ ከምትሰግደው ክርስቲያን ጎን የተቀመጡት ሦስቱ ወጣቶች ሙስሊሞች ናቸው)፡፡

ከዚህም ሌላ በእድሜ የገፉትም ሆኑ ወጣት ሙስሊሞች የቤተ-ክርስቲያኑ ሥርአተ-አምልኮ ተካፋዮች አይደሉም፡፡ ሙስሊሞቹ ክርስቲያኖቹ የሚያደርጉትን የአካል እንቅስቃሴ በፍፁም አያደ ርጉም፡፡ ነገር ግን አልፎ፣ አልፎ ክርስቲያኖቹ ከተቀመጡበት ሲነሱ እነሱም አብረው ይነሳሉ፡፡ በእልልታና በጭብጨባም ስሜታቸውን ከክርስቲያኖቹ ጋር አብረው ይገልጻሉ፡፡ ይህንን የሚያደርጉት ግን በእድሜ የገፉት ሙስሊሞች ብቻ ናቸው፡፡

በዚህ ሂደት የሙስሊሞቹን የልብ መሻት ወይም ለተክለሃይማኖት ያላቸውን ክብርና ፍቅር መረዳት የሚቻለው በሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች አማካይነት ነው። አንደኛው ምክንያት አመጣጣቸው ከግል ፍላጎታቸው ጋር የተያያዘ ቢሆንም፤ ከጎሕ እስከ ቀትር ድረስ የሚዘልቀውን ዓመታዊ የንግሥ ሥርአት ልጅ አዝለው፤ ሕፃናትን አስከትለው ያላንዳች መሰልቸት ከክርስቲያኖቹ ጋር እኩል መዝለቃቸው ነው። ለምሳሌ ከቤት ትተዋቸው የመጡት ሕፃናት እጅግ ያሳሰባቸው ወይዘሮ ሥኑ-ሥርአቱ በመርዘሙ ምክንያት አቋርጠው ሊሄዱ ሲነሱ፤ አብረዋቸው የመጡት ጎረቤታቸው "ልጆቹ ምንም አይሆኑም! ትንሽ ይቆዩና እምነቱን ተቀብተው፣ መስቀሉን ታሽተው፣ ፀበሉንም ይዘው ሂዱ! አሁን ይጠናቀቃል ምንም ያህል አልቀረው!" በማለት አበረታትተው አቆይተዋቸዋል። ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ፀበል፣ እምነትና መስቀል ለማግኘት ያለው ግብ ግብ ነው።

ከፀበል፣ እምነትና መስቀል ጋር በተያያዘ በዚህ የንግሥ ሥርአት ወቅት ጥናት አቅራቢው ካስተዋላቸው በርካታ ሁነቶች መካከል ሁለት "አሳዛኝ" ክስተቶች የሚጠቀሱ ጉዳዮች ናቸው። አንደኛው ክስተት የፀበል ጉዳይ ነው። ከፀበል ጋር በተያያዘ ከቤተሰቦቻቸው ፀበል እንዲያመጡ የተላኩ ሕፃናት ፀበል ተደፍቶባቸው ሲያለቅሱ አጥኚው ተመልክቷል። አንዱን አዝለው ሌላውን አስከትለው ግማሽ ቀን ሙሉ ቆመው የዋሉ እናቶች ፀበላቸው ተደፍቶ አዝነውና ተክዘው ግራ ሲጋቡ አይቷል።

የዚህ ሁሉ ምክንያት ደግሞ የእለቱ እለት የተክለሃይማኖት ፀበል የሚባለው ሰዎቹ ከወንዝ ቀድተው ያመጡት ፀበል የንግሥ ሥርአቱ ሲከናወንበት ቆይቶ በመጨረሻ ተባርኮ የሚሰጥ ፀበል መሆኑ ነው። ፀበሉም በአመት አንድ ጊዜ የሚገኝ የተክለሃይማኖት በረከት ነው። በዚህ ምክንያት የዚያን እለት ፀበል ብርቱ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው።

ሁለተኛው በቦታው የተገኙ ግለሰቦችን የሚያሳዝናቸው ክስተት ደግሞ የእምነት ጉዳይ ነው። የዚህ ጥናት አቅራቢ እንዳስተዋለው በእለቱ እምነት ለማግኘት ሁለት ነገሮች ያስፈልጋሉ። እነዚህም እድልና ጉልበት ናቸው። ምክንያቱም እነዚህ ሁለት ነገሮች ከሌሉ "እምነት አልቋል!" ሊባል ይችላል። በዚህ ሂደት የዚህ ጥናት አቅራቢ የተረዳው መሰረታዊ ቁምነገር የተክለሃይማኖትን እምነት ተቀብተው የልባቸውን መሻት ለማሳካት ከተለያዩ አካባቢዎች ለመጡ ሰዎች የ"እምነት አልቋል!" መርዶ የሚነገረውን ያህል ቀላል ጉዳይ አለመሆኑን ነው። ለጉዳዩ ባለቤቶች ግን መርዶው ግራ ያጋባል፤ ቅስም ይሰብራል። ነገር ግን ያለውን መካፈል

ባህሉ የሆነው የአካባቢው ማኅበረሰብ፤ ቀድሞ እምነት ያገኘው ላላገኘው ያካፍላል፡፡ ከዚህም ሲያልፍ አንዳንድ ጊዜ የኔ ይቅርብኝ ብሎ ለባሰበት ሊሰጥ ይችላል፡፡



ፎቶግራፍ13፡-በወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት የንግሥ እለት ሙስሊሞቹ ፀበል ለመውሰድ ሲጠባበቁና እምነት ሲቀበሉ

ሌላኛው የተክለሃይማኖት በረከት ከንግሥ ሥርአቱ በኋላ የሚታደለው ፀበል ፃዲቅ ነው፡፡ ፀበል-ፃዲቅ የንግሥ ሥርአቱ ማሳረጊያ ነው፡፡ ይህም ሁለት ቦታ ላይ ይከናወናል፡፡ አንደኛው ታቦቱ ዙሮ ከገባ በኋላ እዚያው ቤተ-ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚታደለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከቤተ-ክርስቲያኑ ውጪ "ጌታው ቀየ" ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ ያለው የግብጣ ሥነ-ሥርአት ነው፡፡

ፀበል-ፃዲቅ አንደ ፀበሉ፣ እምነቱና መስቀሉ ሁሉ፤ በረከትነቱ ለክርስቲያኑም ለሙስሊሙም ነው፡፡ ልዩነቱ ፀበል-ፃዲቁ በአብዛኛው እህሉ ከሙስሊሞቹ ተዋጥቶና በሙስሊሞቹ ትብብር የተዘጋጀ መሆኑ ነው፡፡ የፕሮግራሙ አስተባባሪዎችም ለዚህ ጥናት አቅራቢ እንደገለጹት ፀበል-ፃዲቁ የተዘጋጀው ከእያንዳንዱ ቤት ጢስ በጤሰ አንድ-አንድ ጣሳ እህል ተዋጥቶ ነው፡፡ ምክንያቱም የክርስቲያኖቹ ቁጥር እጅግ ትንሽ ስለሆነ አብዛኛውን መዋጮ የሚያዋጡት ሙስሊሞቹ ስለሆኑ ነው፡፡ [110]

"የጌታው ቀዬ" ዝግጅት በቤተ-ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከነበረው ዝግጅት በአይነትም በመጠንም ይለያል፡፡ ዝግጅቱ ሙሉ ዝግጅት ነው፡፡ እንጀራ በወጥ፣ ጠላና ቡቅሪ የዝግጅቱ ዋና አካል ናቸው፡፡ ከመብልና መጠጡ በዘለለ በ "ጌታው ቀየ"፤ ምርቃት የዝግጅቱ ዋና አካል

[110] በሪሁን ይመር፣ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 24 ቀን 2007 ዓ.ም.፤ ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ፡፡

ነው፡፡ በዚህ ሥነ-ሥርዓት ላይ ቄሶች ይመርቃሉ፣ ሼሆች ይመርቃሉ፣ አበጋሮችና የአካባቢው ሽማግሌዎች ይመርቃሉ፡፡ እንድሁም በዚህ የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ላይ አገር ይመረቃል፤ አካባቢ ይመረቃል፤ የአካባቢው ማኅበረሰብና ግለሰቦች ጭምር ይመረቃሉ፡፡

በዚህ እለት ትኩረት የተሰጠው የምርቃት ሥነ-ሥርአት የ2007 ዓ.ም. ክረምት ዝናብ አልዘንብ ብሎ ስለነበር ሰማይና መሬት እንዲታረቁ በተክልዬ ስም መማፀን ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ሌሊቱን እጅግ የሚገርም ነገር ተፈጥሮ አደረ፡፡ ይኸውም በጋ ሁኖ የከረመው ክረምት በዚያን እለት ሌሊት ያለማጋነን ሌሊቱ ወደ ክረምትነት ተቀይሮ አደረ፡፡ በዚህ እለት ሌሊት ከምሽቱ ሁለት ሠዓት አካባቢ መዝነብ የጀመረ ለሊቱን በሙሉ ሲዘንብ አደረ፡፡ ሰውም፣ መሬቱም፣ እፅዋቱም፣ እንስሳቱም ባጠቃላይ ሁሉም ነገር በዚያን ሌሊት ወዙ ተመልሶ አደረ፡፡ ሕይወት ተረጋጋች፡፡ የወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት ነዋሪዎች ፀሎትም እንዲህ ሰመረ፡፡ ሙስሊም-ክርስቲያኑ ጧት ላይ ሲገናኙ እርስ በርስ "ተክልዬ! ረዝቀውን አደሩ አቦ!" እየተባባሉ ተዘያየሩ፡፡ በዚህ መሰረት የክርስትናው ትውፊት ለሙሰሊሙም ትውፊቱ መሆኑን በዚህ አብነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡



ፎቶግራፍ14፡- በእለተ ተክለሃያማኖት ሌሊት ሲዘንብ በማደሩ የአካባቢው ገጽታ ተለውጦ እንዳደረ፡፡

በመጨረሻም ሌላኛው የዚህ ጥናት አቅራቢ ትዝብት በእለቱ የተከናወነው የመንፈሳዊ ትምህርት (ስብከተ ወንጌል) ጉዳይ ነው፡፡ በእለቱ መንፈሳዊ ትምህርቱን የሰጡት ከአዲስ አበባ የመጡ "ወጣት" ሰባኪያን (አስተማሪ) ነበሩ፡፡ ስብከቱ የፈጀው የጊዜ እርዝመት እንዳለ ሆኖ፤ የስብከቱ ሥልት ግን ሙሉ በሙሉ የአዲስ አበባውን የስብከት አውድ (ሥልት) መሰረት

ያደረገ ነበር። የዚህ አይነቱ ስልት ደግሞ ለወረ-ካሎ ሙስሊም የገጠር ነዋሪዎች ብዙም የተስማማቸው አይመስልም።

ምክንያቱም በቤተ-ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚገኙት ምእመናን መካከል ግማሽ የሚሆኑት ሙስሊሞች መሆናቸው እየታወቀ፤ በወቅቱ የተደረገው ስብከት ሙስሊሞቹን ግምት ውስጥ ያስገባ አልነበረም። ለምሳሌ "አዎን! ወይም አይደለም በሉ!" የሚለውን የአስገዳጅ ምርጫ ጨምሮ፤ "እስኪ ማርያምን በሉ! እስኪ ተክልዬን በሉ!...ወዘተ" የሚሉት ኃይለ ቃላት በአብዛኛው ሙስሊሞቹን የሚያገለሉ ነበሩ። ከዚህም ሌላ ድህነት የሚገኘው በክርስትናው ብቻ እንደሆነ የሚያስመስል ይዘት የበራቸው የስብከት ስልቶች ይንፀባረቁ ነበር። በእለቱ የተከናወነው "የልመና" (ምፅዋት) ሂደትም አቅምና ፍላጎትን መሰረት አድርጎ የተከናወነ አይመስልም።

በዚህ ጥናት አቅራቢ እምነትም ሆነ በወረ-ካሎ የገጠር ቀበሌ ነዋሪዎች ባህል፣ ወግና ልማድ መሰረት ተክለሃይማኖት ሙስሊሞቹም ከቅድመ አያቶቻቸው ጀምሮ የወረሱት "ቅርስ፣ ሃብትና ንብረት" ነው። የአካባቢው ባህል ይሄ ስለሆነ መንፈሳዊ ትምህርቱም ይሄንን የጋራ እሴት አጉልቶ በሚያሳይ መልኩ መከናወን ነበረበት። እዚህ ቦታ ላይ ለሚታየው የመቻቻል፣ የመከባበር፣ የመደጋገፍ፣ የመረዳዳት...ወዘተ ጉዳይ ላይ ትኩረት መደረግ ነበረበት። ምክንያቱም የወረ-ካሎ ነዋሪዎችን አስተሳሰስሮ፣ አስተባብሮ፣ አግባብቶና አስማምቶ፣ በሠላምና በፍቅር ይዟቸው የሚጓዘው በስብከቱ የተገለፀው መንፈሳዊ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፤ በዋናነት ትውፊቱ ወይም ፎክሎሩ ነው።

በወቅቱ ጥናት አቅራቢው እንደተረዳው የዚህ ሁሉ ችግር ምንጩ ደግሞ ከአዲ አበባ የመጡት ሰባኪያን (መንፈሳዊ አስተማሪዎች) የወረ-ካሎን ማኅበረሰብ፤ ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ በመጠኑም ቢሆን ቀድመው አለመረዳታቸው ነው። የአዲስአበባው የስብከተ-ወንጌል ሥልት ለወረ-ካሎ ነዋሪዎች እንግዳ ሊሆን እንደሚችል ግምት ውስጥ አለማስገባታቸው ነው። ይህም በፎክሎር ሣይንስ የአውድ ጉዳይ ነው።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ ተብራርተው የቀረቡት ዋና ዋና ነጥቦች የሚያስረዱት መሰረታዊ ቁምነገር የክርስትና ሃይማኖት ትውፊቶች በወሎ፤ ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችሉ የጋራ እሴቶች መሆናቸውን ነው። ምክንያቱም በተጠቀሱት ትውፊቶች እንደተብራራው በነዚህ እሴቶች አማካይነት ክርስቲያን-ሙስሊሙ በወሎ፤ ተግባብቶና ተስማምቶ፤ ተዛዝኖና ተደጋግፎ፤ ተከባብሮና ተቻችሎ፤ በዚህም ማኅበራዊ ትስስሩን አጠንክሮ፣

አንድነቱን አደርጅቶ በሠላምና በፍቅር በጋራ ይኖራል። ለምሳሌ የወሎ ሰው በትውፊቶቹ በጋራ ተፀብሎ፣ በጋራ እምነት ተቀብቶ፣ በጋራ መስቀል ታሽቶ፣ በጋራ ዘክሮና በጋራ ተመራርቆ ሃጃውን ይሞላል። በክብረ-በዓላቸው እለትም በጋራ ዘፍኖና ጨፍሮ ነፍሱን ያስደስታል። በዚህም አንድነቱንና የእርስ በርስ ትስስሩን ያጎለብታል።

ከላይ በወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት አብነት እንደታየው በወሎ፤ ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ ጋር እኩል በአውደ ምህረት ይገኛል። በጥምቀተ-ባህሩ ይታደማል። በዚህም ሙስሊሙ የታቦቱ በረከት የክርስቲያኑ ብቻ ሳይሆን የእኔም ጭምር ነው ይላል። ለዚህም እውነት አለው። ምክንያቱም ተክሃይማኖት ለወረ-ካሎ ነዋሪዎች የእለቱ እለት "ሲረዝቃቸው" ያደረውን ዝናብ ብቻ አብነት መጥቀስ ይቻላል።

በዚህ አይነቱ ትውፊት የተነሳ "አልሃምዲሊላሂ! ታቦታችን በሠላም ገባ!" አሉ የወሎ ሼህ እንዲሉ፤ የአካባቢው ነዋሪዎች የታቦቱንና የሙስሊሞቹን ትስስር የሚገልፁት፤ "አንዳንድ አካባቢ ሙስሊሞቹ ታቦቱ በረከት አለው ብለው ስለሚያምኑ የጥምቀት ለታ በእኔ እርሻ ላይ ነው መሄድ ያለበት፤ በእኔ እርሻ ላይ ነው! እየተባባሉ ይጣላሉ።" በማለት የወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት ነዋሪዎችን ምሳሌ ይጠቅሳሉ።[111] በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ በወሎ የዚህ አይነቱ የጋራ እሴት ነው። እሴቱም በሃይማኖታዊ ገፅታው ሳይሆን በፎክሎራዊ ትውፊቱ የሚገለፅ ነው።

ከላይ እንደተገለፀው ወሎዬዎችን የክርስትናው ትውፊት እርስ በርስ እንደሚያስተሳስራቸው ሁሉ፤ በተመሳሳይ የእስልማናው ትውፊትም በጋራ ያስተሳስራቸዋል። ለምሳሌ ሙስሊሙ ከክርስትናው ቦታ እንደሚሄድ ሁሉ፤ ክርስቲያኑም ከሙስሊሙ ቦታ ይሄዳል። ትውፊቱ መሳ ለመሳ ነው። ቀደም ሲል ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ የፀበል ቦታ እንደሚሄድ አይተናል። በተመሳሳይ ክርስቲያኑ ጥሩ ሼህ አለ ወደተባለበት ቦታ ዱዓ ሊያስደርግ ይሄዳል። ስዕለትም ይሳላል፤ ሲደርሰለትም ጀባታ ይሰጣል። ቀደም ሲል ሙስሊሙ ድርሳነ ሚካኤል አስደግሞ ከህመሙ እንደሚፈወስ አይተናል። በተመሳሳይ ክርስቲያኑ ትልቅ ወልይ ወዳለበት ለቱፍታ (ለመመረቅ) ይሄዳል። ተመርቆ (ተባርኮ) ይመለሳል።

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት የወሎ ደጋጎች ምረቃ መሬት ጠብ አይልምና ምረቃው ሊሳካለት ይችላል። በመሆኑም ወሎዬዎች በዚህ ሁሉ ክር እርስ በርስ የተሳሰሩ ናቸው። በዚህ

[111] አሰፋ አበጋዝ፣ ቃለ-መጠይ፣ ነሐሴ 13 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ።

ትስስራቸው ሙስሊሙ የክርስትናው በረከት ይደርስልኛል፤ ይፈውሰኛል ይላል። ክርስቲየኑም የእስልምናው በረከት አያልፈኝም፤ ከራማቸውም አይዘነጋኝም ይላል። በዚህም ሙስሊሙ ፀበል ይጠመቃል፣ እምነትና መስቀል ይታሻል። ክርስቲያኑም ዱዓ ያስደርጋል፤ ቱፍታ ይቀበላል። ትውፊቱ የጋራ ነው። ወሎዬዎችን ያስተሳሰራቸውም ይኸው የጋራ ትውፊት ነው። አሰፋ አበጋዝ ይህንን የጋራ ትውፊት የሚገልፁት በሚከተለው ሁኔታ ነው።

> ክርስቲያኖቹ፤ ሙስሊሞቹ ዱዓ አድርገው ዝናብ እንዲዘንብ ያደርጋሉ ብለው ያምናሉ። ለነሱም እሚታረደውን ይወስዳሉ። ጫቱን ይዘው ይሄዳሉ። ቡናውን ያፈላሉ። ይከድማሉ። መከደም በወሎ እስላም ክርስቲያን አይልም። ሙስሊሙ ይከድማል፤ ክርስቲያኑም ይከድማል። ባህሉ እስላም ክርስቲያን አይልም። ሁሉም ለዱዓ የሚያሰ ፈልገውን ነገር ያዋጣሉ። ምክንያቱም ሙስለሙም ሆነ ክርስቲያኑም ሆነ ሁለቱም መጥፎ ነገር ይጠፋል፤ በምትኩ መልካም ነገር ይገኛል ብለው ስለሚያስቡ የሚደረገውን ነገር ሁሉ በጋራ ያደርጋሉ.[112]

5.3፡- የእስልምና ሃይማኖት ትውፊቶች በወሎ

ቀደም ሲል በክርስትናው በኩል የፈጣሪ በረከቶች ይገኝባቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ቦታዎች ተገልፀዋል። አጋንንትን የሚያርቁ፣ ከደዌ የሚፈውሱ፣ ጤንነትን የሚመልሱ ትውፊቶች ተብራርተዋል። በእስልመናው በኩልም ትውፊቱ ተመሳሳይ ነው። ይሄ ጥናት በተካሄደባቸው ቦታዎች ብቻ እንኳን በሐብሩ ወረዳ ካሎ-ሼሆላ፣ መርሳ አባገትዬ፣ ዳናና አስከንትር ሚሌ-ሃጂ አቡየ ለዚህ ትውፊት ተጠቃሽ ቦታዎች ናቸው። በጉባላፍቶ ወረዳ ደግሞ ሼህ ለጋ ይጠቀሳሉ። በራያና ቆቦ ከረም በእስልምናው የበረከት ተምሳሌት ቦታ ነው። እነዚህ ቦታዎች የወልይ፣ የአራት ዓይናዎች ፣ የአበጋሮችና የወሎ ደጋጎች መፍለቂያ መካናት ናቸው። የእስልምና ሊቃውንት መወለጃ፣ መኖሪያና ማስተማሪያ ማዕከላት ናቸው። የወሎ ከራማ ከነዚህ ቦታዎች ይመነጫል። ከነዚህ ቦታዎች የሚመነጨው ከራማ ደግሞ ለሙስሊሙም ለክርስቲያኑም እንደ የበረከት ምንጭ ተደርጎ ይቆጠራል። በነዚህ ቦታዎች ሰው ሲጣላ ይታረቅባቸዋል፤ ደም ይደርቅባቸዋል። ድርቅ ሲከሰት በነዚህ ቦታዎች ላይ ተፀልዮ ሰማይና መሬት ይታረቁባቸዋል። በሽታና ቸነፈር ሲከሰትም በነዚህ ቦታዎች ላይ ዱዓ ተደርጎ ሠላምና ጤና ወደነበሩበት ይመለሱባቸዋል።

---

[112] እንደላይኛው።

የዚህ አይነቱ እሴት መሰረቶቹ ደግሞ የእነሱንና እነሱ የሚኖሩበትን ማኅበረሰብ ዓለማዊና መንፈሳዊ የሕይወት ትልሞች የሚተልሙ አንደክርስትናው ሁሉ የእስልምናው ቅዱሳን ናቸው። እነዚህ ቅዱሳን ሰውን በሃይማኖቱ፣ በዘሩ፣ በቀለሙ በሀብቱ፣ በዖታው፣ በከተሜና በገጠሬነቱ ለያይተው የሚመለከቱ ሳይሆኑ፤ ሰውን በሰውነቱ ብቻ የሚመለከቱ የጀማው ጠባቂ አባቶችና እናቶች ናቸው። ይህንን እውነታ ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> በወሎ ደጋጎች ዘንዳ እስላም ክርስቲያን እሚባል ልዩነት የለም። እኛ ሼህ ሞሐመድ ሚአዋ እሚባሉ ትልቅ ሰው ነበሩን። እዚህ መርሣ አባ ገትዬ። ክርስቲያኑም ለሚፈልገው ነገር ዱዓ እንዲያደርጉለት ሂዶ ይዘይራል። እስላሙም እንደዚሁ ነው። ሴቱም እንደዚሁ ነው። ወንዱም እንደዚሁ ነው። ልዩነት እንዳይፈጥር አደራ ሰጥተውናል። በዚያን ጊዜ ለእሳቸው እኔ ነበርኩ ወኪላቸው። "አደራ ልጄ! በሁለቱ ሃይማኖቶች መካከል አንድ ሰው ጣልቃ ገብቶ ልዩነት እንዳይፈጥርባችሁ!" እያሉ ይመክሩ ነበር። በዳና በኩል ደግሞ ሃጂ ሞሃመድ ዘይን እሚባሉ ትልቅ ሰው ነበሩ፤ የተባረኩ። ከመሰረቱ ካያቶቻቸው ጀምሮ የመጣ ነው። ከመሰረታቸው እስላምና ክርስቲያን የሚባል ልዩነት አያውቁም። የዓመት መውሊድ በሚመጣበት ጊዜ እስላሙና ክርስቲያኑ ሁሉ የሚቀርብበትና የሚባረክበት ባህል ነው የነበረው።[113]

በጥቅሱ እንደተገለፀው በወሎ ደጋጎች አማካይነት ወሎዬዎች በሠላም፣ በደስታ፣ በጤና፣ በፍቅርና በመዋደድ፣ አብረው እየበሉና እየጠጡ አብረው ይኖራሉ። በዚህ መሰረት እነዚህ ደጋጎች የተወለዱበት፣ የኖሩበት፣ ተአምራት የሰሩበት፣ በዓጸደ ሥጋ የሌሉ ቢሆኑም እነኳን አጽማቸው ያረፈበት ቦታ ጭምር በወሎዬዎች ዘንዳ እንደ የበረከት ምንጭ ተደርጎ ይቆጠራል። በመሆኑም ወሎዬዎች ቀን ቆጥረው፣ ወቅት ጠብቀው፣ ይጎበኟቸዋል፤ ይዘይሯቸዋል። ዝየራው የሙስሊሙ ብቻ ሳይሆን የክርስቲያኑም ትውፊት ነው። የሚከተለው ጥቅስ ለዚህ አባባል ማስረጃ ነው።

> አሁን የመውሊድ ጊዜ ዳና የሚያከብረው እስላሙ ብቻ ሳይሆን ክርስቲያኑም አብሮ ነው። ሁሉም ነው በጋራ የሚያከብረው። ቦታው ላይ ለመዘየር ለሄደ ሰው የሚያስተናግደውም ሙስሊሙም ክርስቲያኑም በጋራ ነው። ሁሉም ከየቤቱ ያለውን ነገር እያወጣ ከሩቅ አገር የሄደውን ሰው ያስተናግዳል። ለምሳሌ ሼህ ለጋ ያለውን እንደ ዳናው ሄጄ አይቻለሁ። እሳቸው ጋር አሁን ሙስሊሙም ከክርስቲያኑም ነው የሚሄደው። እና እዚያ ቦታ ላይ ያየሁት ክርስቲያኑም ሙስሊሙም በሠላም ስለኖርኩ እያለ ስዕለት መአት ነገር ነው የሚመጣላቸው። ሌላውን ተወውና ከ15 እስከ 20 በሬ ሊመጣ ይችላል። ታዲያ ምንድን ነው የሚያደርጉት? ለክርስቲያኑና ለሙስሊሙ አከፋፍለው አርደው ነው የሚያበሉት። ለእሳቸው ገቢ የሚሆን ነገር የለም። የዚያ አካባቢ ሰው ሴቷ እንጀራ እየያዘች ተመጣለች። እዚያ የሄደ እንግዳ ሁሉ ያነን ይበላል። ክርስቲያኑም ይሄን እንደራሱ አድርጎ ነው የሚያየው። ይሄ የእኔ ያኛው የእከሌ ነው ብለው የሚለዩት ነገር የላቸውም። ሁሉም አብሮ ነው። እንደነገርኩህ እርድ ብቻ ነው እሚለያቸው። እነሱ በሃይማኖታቸው

[40] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 01 ቀበሌ።

> የሚያውቁት ይኸን ብቻ ነው። ሌላው ነገር ሁሉ እንዳለ በጋራ ነው። ትስስራቸውም የማይላላው በዚህ ነው።[114]

ከላይ በጥቅሶቹ ውስጥ እንደተብራራው በእስልምናው በኩል የሚገኙት ቅዱሳን ቦታዎችና አባቶች እንደ ክርስትናው ሁሉ፤ ለሁለቱም የጋራ ናቸው። የጋራ የሚሆኑበት ምክንያትም በግለሰብም በማኅበረሰብም ደረጃም ነው። በግለሰብ ደረጃ የሰው ልጅ እንደፍላጎቱ ሁሉ ችግሩም የተለያየ ነው። ፍላጎቱም እንዲሟላለት፤ ችግሩም እንዲቀረፍለት ወደነዚህ ቦታዎች ይሄዳል፤ ይዘይራል። ስዕለትም ይሳላል፤ ስዕለቱ ሲሰምርለትም ጀባታ ያገባል። ጀባታው አቅም እንደፈቀደ፣ ልብ እንዳፈተተ የሚፈፀም ነው። ይህም የወረ-ካሎ ተክለሃይማኖት ገጠር ቀበሌ ሙስሊሞች ለተክሃይማኖት ከሚያገቡት ስዕለት ጋር መርሁ ተመሳሳይ ነው። በሁለቱም ወሳኙ አካል ተቀባዩ ሳይሆን ሰጪው ክፍል ነው። የተቀባዩ ድርሻ የተጠየቀውን መፈፀም ብቻ ነው። ይህም የትውፊቱን ተመሳሳይነት የሚያሳይ አብነት ነው። ስዕለት በእስልምናው ከዱዓ ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ነው። በዕስልምናው በኩል የስዕለት መሰረቱ ዱዓ ነው። ዱዓ የሚደረገው ደግሞ እንዲሁ በተራ ሰው አማካይነት ሳይሆን ተሰጥዎ፣ ብቃቱና የፈጣሪ ፀጋ በተሰጣቸው የወሎ ደጋጎች አማካይነት ነው። ከነዚህ ደጋጎች መካከል የወሎ ወልዮች ለአብነት ይጠቀሳሉ።

በምዕራፍ አንድ ውስጥ እንደተጠቀሰው በረኸርም ታሪኩ እንደሚታወቀው ወሎ፤ የወልይ አገር ነው። የጀማ ንጉሥ ሼህ፣ የዳናው ሼህ፣ የከረሙ ሼህ፣ የአጋምሳው ሼህ፣ የአባ በድሩ ሼህ፣ የአባ ገትየው ሼህ፣ የጫሌው ሼህ፣ የገራዶው ሼህ፣ የአልቡኮው ሼህ፣ የተንታው ሼህ፣ የቃሉው ሼህ እና ሌሎችም መፍለቂያቸውም መኖሪያቸውም ወሎ ነው። የነሱ ከራማም ሆነ በረከት ከሁለቱ እምነት ተከታዮች ጋር እጅግ የተሳሰሩ ናቸው። ለአብነት በነሱ አማካይነት የተጣላው ይታረቃል፤ ቂም የቋጠረው ቂሙን ይሸራል። በዱዓቸውና በቱፍታቸው የታመመው ይድናል፤ የተለከፈው ይፈወሳል። ወልዮቹ ከመንፈሳዊው ተልእኳቸው በተጨማሪ የባህላዊ እሴቶች መሰረቶች ናቸው።

5.3.1:- ወልይ በወሎ

ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ እንደሚሉት በወሎ በእስልምናውም ሆነ በክርስትናው ፈጣሪ ስጦታ የቸራቸው ቅዋ (ብቃት) ያጎናጸፋቸው ወይም እሱ የመረጣቸው የወሎ ደጋጎች ነበሩ። አሁንም አለ። ወደፊትም ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች የመረቁት ይለመልማል፣ የረገሙት ደግሞ

---

[114] አሰፋ አበጋዝ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ።

ይጠወልጋል፣ ይደርቃል። እነዚህን የወሎ ደጋጎች ወይም አራት ዓይናዎች ወሎዬዎች "ደጎቹ መጀን! ሼሆቹ መጀን!" እያለ ይመጀኑባቸዋል። ምክንያቱም ዓራት አይናዎቹ ያለፈውን እያስታወሱ ለትውልዱ ይተርካሉ። ያሁኑን እያስተዋሉ ለትውልዱ ያስረዳሉ። መጪውን በሩቅ እየተመለከቱ ለትውልዱ ይተነብያሉ።

እናም እነዚህን ደጋጎች በግልም ሆነ በቡድን ሃድያ ይዞ የዘየረ አለቃም ሆነ ምንዝር፤ "ብሩክ አላህ ያርግህ! በረካ አላህ ያርግ! እስከ ልጅ ልጅህ ብሩክ ሁን! የተናገርከውም ደሞ መቅቡል ይሁን! የረገምከው ርጉም ይሁን! የመረቅኸው ምሩቅ ይሁን! እስከ ልጅ ልጅህ ደሞ እንጀራ አግኝ!" ተብሎ ዱዓ (ቱፍታ) ይደረግለታል"[115]። ሃጃው ሲሞላለትም "አንቱ መጀን!" ብሎ ጀባታ (ስጦታ) ይዞ ወልዮቹን ይዘይራል።

ጀባታው ከኮርማ እስከ ሰንጋ፣ ከጠቦት እስከ ጫት፣ ከቡና እስከ ጎንጥላ ወዘተ... ሊሆን ይችላል። ከዚህም ሲያልፍ ያሰቡት እስከሚሳካ ጠቀልሎ ገብቶ ከዳም ሊሆን ይችላል። ትውፊቱ ደግሞ ክርስቲያን ሙስሊም ብሎ አይለይም "የከደሙ ተጠቀሙ!" እንዲሉ ወሎዬዎች፤ መከደም በወሎ የበረከት ሁሉ ምንጭ ነው። ግራዝማች ብሩ ይማም እንደሚሉት የወሎ ታላላቆች እዚህ ደረጃ ላይ የደረሱት አንዱ ሌላውን በመከደም ነው።

> የጥንቶቹ ትላልቅ የሚባሉት የወሎ ሼሆች ለዚህ የበቁት፤ ሰባት ዓመትም፣ ስምንት አመትም፣ እንደሁኔታው እዚህ መርማ አባገትየ እየመጡ ከድመው ነው። ኸዚያ "ቱቱቱ...!" ተብሎ መሐባው ተሰጥቷቸው ነው፤ ተባርኮላቸው ነው። ኸዚያ በኋላ እነሱ ሰውን ነጣጥሎ የዚህ ዘር ነው፣ የዚያ ዘር ነው፣ አይሉም። በሃይማኖት ደሞ እዲህ ያለ ሃይማኖት፤ እንዲያ ያለ ሃይማኖት እሚባል በነሱ በኩል የለም። ስለዚህ እስላምና ክርስቲያን የሃይማኖት ልዩነት ይኑራቸው እንጂ፤ በማኅበራዊ ኑሮ በኩል እንዳይለያዩ ብዙ ጥረት እሚያደርጉ ነበሩ። ከህዘ ውጪ የሆነ አስተሳሰብ የላቸውም፤ አይገኝም በታሪክም በምንም።[116]

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው በወሎ፤ ለካደመም ዱዓ ይደረግለታል። ለዘየረም ዱዓ ይደረግለታል። ሃጃውም እንደ ልቡ መሻት መጠን ይሞላለታል።በዚህም ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ ወደነዚህ ቦታዎች ይሄዳል። ሼህ ዑመር እሼቱ እንደሚሉት እነዚህ ቦታዎች የዱዓ ቦታዎች ናቸው። የበረካ ቦታዎች ናቸው። ጥንት ትላልቆቹ እነዚህን ቦታዎች ለዱዓ ደልድለ ዋቸዋል። ለዱዓ አቅንተዋቸዋል። እነሱ ዱዓ አርገውባቸዋል። ፈጣሪን ተገዝተውባቸዋል። በረካ አርገውባቸዋል። በነዚህ ቦታዎች የተደረገ ዱዓ አይቀርም።[117]

---

[115] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመደ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 01 ቀበሌ።
[116] ግራዝማች ብሩ ይማም፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 15 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ።
[117] ሼህ ዑመር እሼቱ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 20 ቀን 2006 ዓ.ም. መርሣ- 02 ቀበሌ።

በዚህ መሰረት በነዚህ ቦታዎች ሙስሊሙም ክርስቲያኑም እየመጣ ዱዓ ያስደርጋል። ሃጃው ሲሞላለት ደግሞ እየሄደ ይዘይራል። ስዕለት ያገባል። በነዚህ ቦታዎች ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ ትዳር የሌለው ትዳር እንዲያገኝ ዱዓ ያስደርጋል፤ ትዳር ያገኛል። ሃብት ለማግኘት ዱዓ ያስደርጋል፤ ሃብት ያገኛል። ስለጤናው ዱዓ ያስደርጋል፤ ጤናው ይመለስለታል። ወደውጪ [ሥደትም እንኳ ቢሆን] ለመሄድ አስቦ እንዲቀናው ዱዓ ያስደርጋል፤ አገሩን ለቆ ለመሄድም ይቀናዋል።[118] ይህ እንግዲህ በግለሰብ አንፃር ነው።

ከማኅበረሰብ አንፃር ደግሞ ዝናብ በሚቀርበት ሠዓት፣ ወረርሽኝ በሚገባበት ወቅት፣ አንበጣ፣ ተምችና ሌላም ለአዝመራ የማይሆን ተባይ በሚከሰትበት ወቅት ጀማው ዱዓ ለማስደረግ ወደነዚህ ቦታዎች ይሄዳል፤ ዱዓ ያስደርጋል። ዝናቡም ይዘንባል፤ ተባዩም ይጠፋል። አውሊያ ያለባቸው ሰዎች ደግሞ ለዱዓ ወደነዚህ ቦታዎች ይሄዳሉ፤ ዱዓ ይደረግላቸዋል፤ አውሊያቸው ይስተካከልላቸዋል።

እነዚህ ቦታዎች የሃቅ ቦታዎች ናቸው። "ከሃቅ ቦታ እወስድሃለሁ!" እንዲሉ ወሎዬዎች፤ የተካካዱና ለሽማግሌ እውነቱን አላወጣም ያሉ ሰዎች ወደነዚህ ቦታዎች ይመጣሉ፤ እውነቱን ያወጣሉ። በዚህም ፍትሕ ይረጋገጣል፤ ሠላም ይወርዳል። ባጠቃላይ ከዚህ በላይ ከቀረቡት አብነቶች መረዳት እንደሚቻለው የወሎ ደጋጎች ለክርስቲያኑም ለሙስሊሙም የሚያስቡ፣ ለሀገርና ለወገን የሚጨነቁ፣ ከአካባቢያቸው አልፈው ለዓለም ሁሉ የሚበቁ አራት ዓይናዎች ነበሩ። ለምሳሌ ሼህ አሰን አሊ ሞሐመድ የዚህ አይነት ብቃት ያላቸውን ሰዎች የሚገልጧቸው፤ "ሃጂ ሳኒ ምን ነበሩ!? ወሎ አደሉም እንዴ!? እሳቸው እንኳን ለወሎ የዓለም ሊቃውንት መፍቲ ነበሩ!" የሚል ምሳሌ በመጥቀስ ነው። እሳቸው እንደሚሉት እነዚህ ደጋጎች በሃይማኖት መካከል ልዩነት የማይፈጥሩ፣ ሰውን ከሰው የማይለዩ፣ ለተቸገሩና ለተጨነቁ የሚደርሱ፣ የፈጣሪን ሥራ ብቻ የሚሰሩ ብዑዓን ነበሩ።[119] ግራዝማች ብሩ ይማም በበኩላቸው እነዚህ ደጋጎች ለፈጣሪ ያደሩ መሆናቸውን የሚያብራሩት እነሱ የጠየቁት ነገር በፈጣሪያቸው እንዴት እንደሚፈጸም የሚያስረዳ ምሳሌ እንደሚከተለው በመጥቀስ ነው።

> የነሱ በረካ ለክርስቲያኖቹም፣ ለሙስሊሞቹም ለሁሉም ነው። አሁን እኔ ክርስቲያኑ እነሱ ዘንዳ እሄዳለሁ። ስሄድ "ምን ሆንክ?" ይሉኛል። እንደዚህ ሆኜ፤ እያመመኝ፤ እላቸዋለሁ። "በል ፈጣሪ ይማርህ፤ ይምርሃል፤" ብለው እጃቸውን እንዲህ አርገው ዳበስ፣ ዳበስ

---

[118] እንደላይኛው።

[119] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም.መርሣ- 01 ቀበሌ።

ያረጉሃል፡፡ በዚህ ብቻ ከበሽታህ ይፈውሱሃል እንጂ፤ እንደዚህ አርግ፤ እንትን እረድ፤ ደም አፍስ፤ እንደዚህ የለም፡፡ እነዚህ ከሥረ-መሠረታቸው የአምልኮ ሥራ አይሰሩም፡፡[120]

5.3.2፡- የመርሣው ጌታ

ትክክለኛ መጠሪያ ሥማቸው ሼህ ሞሐመድ ሚአዋ ይባላሉ፡፡ ወሎዬዎች የሚያውቋቸው ግን የመርሣው ጌታ ወይም መርሣ አባገትዬ በሚለው ሥማቸው ነው፡፡ የአንድ ሰው እድሜ በእናትና በአባት፣ ይህ ካልሆነ ደግሞ በቅርብ ዘመድና ጎረቤት ተቆጥሮ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ የመርሣው ጌታን እድሜ ለማረጋገጥ ግን ከእሳቸው የቀረበ ሰው በወሎ ምድር እንዳልተገኘ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ እድሜያቸውን የሚናገርና ትውልዳቸውን የሚቆጥር እንኳንስ እናትና አባት፣ እንኳንስ የቅርብ ዘመድና ጎረቤት ቀርቶ የእርሳቸውን የእድሜ ዘመን ግማሽ ያህል የኖረ ባልንጀራ የላቸውም፡፡ መረጃዎች እንደሚሉት የመርሣው ጌታ 207 ዓመት በወሎ ምድር ላይ ኖረው፤ በ1983 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡[121]

የመርሣው ጌታ በአገር አባትነታቸውና በፈጣሪ አገልጋይነታቸው የተወደዱና የተከበሩ ነበሩ፡፡ በህዝብና በአገር ላይ የሚመጣን በላ ቀድሞ የማየትና የመዳኛን መንገድ ለህዝብ ጠቁሞ የማሳወቅ ተሰጥዖ ነበራቸው፡፡ በፀሎትና በዱዓ አገር አማን ውሎ እንዲያድር፤ በህዝብ ላይ የመጣ የመከራ ደመና እንዲገፈፍ በማድረግ ታላቅ ሥራ ሰርተዋል፡፡ ክቡር ስምም አትርፈዋል፡፡ በአካል የሚያውቋቸው የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ፈጣሪን ጠይቀው ዝናብ ያዘንባሉ፡፡ በሽታ አባረው የአካባቢውን ጤና ይመልሳሉ፡፡ እንኳን ሰው አውሬ ሳይቀር ይታዘዝዝላቸው ነበር፡፡ ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ የመርሳው ጌታ ይህንን የማድረግ አቅም ወይም ተሰጥዖ አንደነበራቸው የሚመሰክሩት የሚከተሉትን ነጥቦች ምሳሌ በመጥቀስ ነው፡፡

> ገበሬው አዝመራችንን ከርከሮ በላብን፣ አንበጣ በላብን፣ ወፍ በላብን፣ ከብቶቻችንን ከውረኔ ጅብ በላብን፣ ደሞ በይህ በደጋው በጥጉ አገር ዝንጀሮ አስቸገረን፣ ጦጣ አስቸገረን፣ እያሉ መጥተው ለሳቸው ይናገሩ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ "አባባ አዝመራው የኔ ነው ብለዋል! እኛ

---

[120] ግራዝማች ብሩ ይማም፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 13 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ፡፡

[121] ዜና ቱሪዝም ጋዜጣ በቁጥር 14፤ በነሐሴ ወር 1973 ዓ.ም. እትሙ እንደዓፈው፤ በሐምሌ ወር 1973 ዓ.ም. ደሴ ላይ በተዘጋጀው "ወሎ ትግላችን ኤክስፖ፤" የመርሣው ጌታ ፎቶግራፍና 197 ዓመት እድሜ እንዳላቸው የሚገልጽ ታሪክ ተዕፎ ለጎብኝዎች ቀርቦ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መነሻ ባለታሪኩ ካሉበት ቦታ መርሣ ከተማ ድረስ በመሄድ የመርሣውን ጌታ ቃለ መጠይቅ አድርጎላቸው ነበር፡፡ በቃለ-መጠይቁ መሰረት የመርሣው ጌታ ታላቁ ራስ ዓሊ ሲሞቱ የአምስት ዓመት ልጅ ነበሩ፡፡ ጋዜጣው እንደዓፈው የታላቁ ራስ ዓሊ እረፍት በ1781 ዓ.ም. ነው፡፡ የመርሣው ጌታ በዚያን ወቅት የአምስት ዓመት ልጅ ከነበሩ፣ ልደታቸው በ1776 ዓ.ም. እንደሆነ ጋዜጣው ዕፏል፡፡ በዚህ መሰረት የመርሣው ጌታ በነሐሴ ወር 1973 ዓ.ም. 197 ዓመት ሞልቷቸው ነበር፡፡ በሐምሌ ወር 1983 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ደግሞ የ207 ዓመት የእድሜ ባለፀጋ ነበሩ፣ ማለት ነው፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ግን የመርሣው ጌታ የእድሜ ባለፀጋ ሊሆኑ እንደሚችሉ ባይጠራጠርም፣ የዚህን ያህል ዘመን በአፀደ ሥጋ ሊቆዩ ይችላሉ ብሎ አይገምትም፡፡ ነገር ግን የመርሣው ጌታ የቅርብ ተጠሪና የዚህ ጥናት አንዱ የመረጃ አቀባይ የሆኑት ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ የ121 ዓመት የእድሜ ባለጸጋ እንደሆኑ ነግረውታል፡፡

> መውሊድ የምናወጣበት፣ ጎብረተሰቡን የምናስተዳድርበት ስለሆነ አልፈቀድንልህም ብለዋል! ብላችሁ ንገሯቸው!" ብለው የሚናገሩበት ወቅት ነበር። ይኸም ብቻ ሳይሆን፤ "ይኸን ከተናገራችሁ በኋላ ለሊት ከርከሮ እንዳትጠብቁ ከቤታችሁ ሂዳችሁ እደሩ!" ይሉ ነበር። ከዚህ በኋላ በጌታ ይሁንብኝ አንድ ከርከሮ አንዲት ነገር አዝመራ አይነካም ነበር። በዚህ አካባቢ ብቻም ሳይሆን፤ ከጅማ ድረስ አንበሳ ከብቶቻችንን እየበላ አስቸገረን ብለው ይመጡ ነበር። እሳቸውም "አባባ አልፈቀድንልህም ብለዋል ብላችሁ ንገሩት!" በማለት አንበሳውን ያስቆሙላቸው ነበር። በአካባቢያችን የዚህ አይነት ብቃት የነበራቸው ሰዎች ነበሩ።[122]

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው የመርሣው ጌታ ሁለት ቃል የማይናገሩ፣ ከሃሜት፣ ከፌዝና ከቧልት፣ ከትችትና ከንዋየ ፍቅር የራቁ፣ ያለፈውን በጥንቃቄ የሚመረምሩ፣ ያሁኑን በአንክሮ የሚከታተሉ፣ መጭውን በእርቀት የሚያዩ፣ የህዝባቸውን ጭንቅና መከራ የሚገፉ፣ ለሚኖሩበት ማኅበረሰብ ፍቅርና ሠላምን የሚሰብኩና የሚያረጋግጡ፣ የትውልዱ አርአያ ነበሩ። የክርስቲያን ሙስሊሙ የጋራ አባት ነበሩ። ባጠቃላይ የመርሳውን ጌታ በረካ ያገኘ ደጅ ጠኚ ፈጣሪ የወደደው ነው፤ ይባላል።

ሼህ ዑመር እሼቱ እንደሚሉት የመርሣውን ጌታ የዘየረ ሹምም ይሁን፤ ተርታ ሰው የእድሉ ጥሪ ከመነሻ እስከ መድረሻ ይነገረዋል። ሰውየው ጨካኝ፣ ተንኮለኛና መሰሪ ሆኖ ካገኙት ገልጠው ይነግሩታል። በጎ ሰው እንዲሆንም ይመክሩታል። ልቡ የጠዳ ቡልሃ ሆኖ ካገኙት ደግሞ እንዲያ መሆኑን ነግረውት፣ መርቀውትና ቱፍታ ሰጥተውት ይሸኙታል።[123]

ለምሳሌ ኢትዮጵያን ለ17 አመታት ያስተዳደሩት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የመርሣውን ጌታ ሁለት ጊዜ እንደዘየሯቸው ይነገራል።[124] ኮሎኔሉ በ1974 ዓ.ም. መቅደላን ጎብኝተው ሲመለሱ ለመጀመሪያ ጊዜ እኒህ አራት ዓይና አባት ወደሚኖሩበት ወደ መርሣ ከተማ ሂደው ዘይረዋቸዋል።[125] በዚህ ወቅት የመርሣው ጌታ፤ "መቼም ወሎን ንጉሥ መጥቶ ውሎ አድሮባታል መባልን አልሰማንም! ላንተ ግን ሦስት ቀን ውለህ እንድታድርባት ከአላህ ተፈቅዶልሃል!!" ስላሏቸው በደሴ መርሆ ቤተ-መንግሥት ለሦስት ቀናት ሊቆዩ መቻላቸውን ሼህ ዑመር እሼቱ ይገልፃሉ።

---

[122] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 17 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 01 ቀበሌ።

[123] ሼህ ዑመር እሸቱ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 01 ቀበሌ።

[124] እንደላይኛው።

[125] ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ወደ መርሣ በሄዱ ጊዜ፤ መርሣ ከተማ አጠገብ የማስታወሻ ሣጥ ተክለው እንደነበር የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ። በ1982 ዓ.ም. ኢህአዴግ አካባቢውን ሲቆጣጠር አንድ ታጋይ ሣጡን ለመቁረጥ ሲሞክር የአካባቢው ነዋሪዎች ድርጊቱን ተቃውመው እንዳስቆሙት ይነገራል። ነገር ግን በቅርብ ጊዜ በመንገድ ሥራ ምክንያት (መንገዱና ዘጩ ግንኙነት ባይኖራቸውም ቅሉ) ዛጩ እንድትቆረጥ መደረጉን የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ። የዚህ ጥናት አቅራቢ ግን "ዘጩ ቅረስ ስለነበረች መቆረጥ አልነበረባትም!" የሚል ጽኑ እምነት አለው።

ሼህ ዑመር እንደሚሉት ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ በ1980 ዓ.ም. ፕሬዝዳንት መንግሥቱ የመርሣውን ጌታ እንደዘየሩና በዚህ ወቅት ፕሬዝዳንቱ "ምን ይሻላል!?" የሚል መሪ ጥያቄ ለመረሣው ጌታ አቅርበውላቸው፤ እንደሚከተለው ቁርጥ ያለ መልስ ሰጥተዋቸው እንደነበር ይነገራል፡፡

> ግንቦት የሚሉት ወር ባንተ ላይ ሊጠመጠምብህ አቆብቁቦብሃልሳ በል! የምትመጣዋ ግንቦት እንኳን [1981 ዓ.ም.] መላም የላት፤ በራሷ ገመድ ተጠልፋ ትወድቃለች፡፡ እዚያው ተንፍሳ ትሟሸሻለች፡፡ ላንተ የምታስፈራው የወዳኛዋ ግንቦት ናት በል!! [1983 ዓ.ም.] ባልንጀሮችህ እንደ ክብት በበረት ታጉረው ይማቅቃሉ! አንተ ግን አገርና ወገን እንደናፈቀህ ትቀራለህ! መቼም ሃቲማ የላችሁ! የምትሆነው ነገር የለም! አብሸር! እሩህያህን ለአላህ ነግረን እናስመልሳታለን በል![126]

በሌላ በኩል ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ እንደሚሉት ከሁሉም ነገር በላይ አስደናቂ ሆኖ የሚጠቀሰው የመርሣው ጌታ ትንቢት ይህንን የኮሎኔል መንግሥቱን ፍርድ በሰጡ ሰሞን ስለራሳቸው የመጨረሻ ዘመን ቀድመው የሰጡት ትንቢት ነው፡፡ የመርሣው ጌታ በ1983 ዓ.ም. ግንቦት ወር ላይ ሆነው፤ "አሆሆ! ዘመናችን የሚያከትመው ነሐሴ 1 ቀን ነው በል!" በማለት ተንብየው ነበር፡፡ በትንቢታቸው መሰረት የመርሣው ጌታ በዚያው እለት ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለዩ ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ ይናገራሉ፡፡[127]

ከዚህ በላይ በመርሣው ጌታ አብነት እንደተገለፀው ወሎ የዚህ አይነት አራት ዓይናዎችና ደጋጎች መፍለቂያ ምድር ነው፡፡ እነዚህ ደጋጎች ደግሞ ለክርስቲያኑም ለሙስሊሙም የጋራ የአገር አባቶችና እናቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ደጋጎች ለክርስቲያኑም ለሙስሊሙም የበረከትና የመልካም ነገር ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ የወሎዬዎች ተስፋ፣ ጥላና ከለላ ናቸው፡፡ የሠላምና የፍቅር ምንጮች ናቸው፡፡ እነሱ የተወለዱባቸው፣ የኖሩባቸውና አፅማቸው ያረፈባቸው ቦታዎች ሁሉ ለወሎዬዎች የበረከት ምንጮች ናቸው፡፡ በዚህም ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ በጋራ ይዘይሯቸዋል፡፡ የሚፈልገውን ነገር እንዲያደርጉለት ይለምናቸዋል፤ ይሳልላቸዋል፡፡ የጠየቀው ሲፈፀም ደግሞ ስዕለት ያገባላቸዋል፡፡ በዚህ መሰረት የእስልምናው ሃይማኖት ትውፊቶች እንደ ክርስትናው ትውፊቶች ሁሉ፤ ክርስቲያን-ሙስሊሙን እርሰ በርስ ያስተሳስራሉ፤ ያገናኛሉ፡፡ ክርስቲያን-ሙስሊሙ እርስ በርስ ተባብሮና ተስማምቶ በፍቅርና በሰላም በጋራ እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም የሃይማት መቻቻል አሴት በወሎ የሚገለፀው በነዚህ ትውፊቶች አማካኝነት ነው፡፡ የትውፊቶቹ አይነትና ብዛት ግን በዚህ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፤ እጅግ በርካታ ነው፡፡ ከነዚህ እሴቶች አንዱ የአበጋር ትውፊት ነው

---

[126] ሼህ ዑመር እሸቱ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 20 ቀን 2006 ዓ.ም. መርሣ- 02 ቀበሌ፡፡
[127] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 01 ቀበሌ፡፡

5.3.3፡-አበጋር በወሎ

አበጋር በወሎ ከእስልምናው ትውፊት ጋር የተያያዘ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ እሴት ነው፡፡ ትውፊቱ እንደ ወሎ ደጋጎች ሁሉ የመልካም አጋጣሚ ሰበብ ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የመጥፎ ነገር ሰበብ የሚሆንበት አጋጣሚም አለ፡፡ ለምሳሌ በወሎ አበጋር የመረቀው በረካ ይገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ባንፃሩ አበጋር የረገመው እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ብኩን ሆኖ ይቀራል ተብሎ ይታመናል፡፡ አበጋር ማዱ በላይ እንደሚሉት ወሎ የአበጋር አገር ነው፡፡ ወሎ፤ "ጨጨሆ በመለሰ፣ ዋጃ በፈሰሰ፣ ሞፈር ውኃ በመለሰ" ግዛቱ የአበጋር ነው፡፡

በመረጃ አቀባዩ ማብራርያ መሰረት አበጋር በወሎ፤ አይኑ መድኃኒት ኩቴው እርጥበ ነው፡፡ አንደበቱ ገራም ነው፡፡ አበጋር በወሎ ዲና ያለው ነው፡፡ የተጣላ ለማስታረቅ የተሰጠ አበጋር አለ፣ ለመውለድ የተሰጠ አበጋር አለ፡፡ ለመክበር የተሰጠ አበጋር አለ፣ የታመመ ለማሻር የተሰጠ አበጋር አለ፡፡ አዝመራው እንዲይዝ፣ ከብቱ እንዲወልድ ለማዲረግ የተሰጠ አበጋር አለ፡፡ በመረጃ አቀባዩ እምነት አበጋር በወሎ የአገር አባት ነው፡፡ አበጋር በወሎ ላገሩ በሞላ፤ ለቆላ ለደጋው የቆመ ነው፡፡[128]

በዚህ መሰረት አበጋር በወሎ የሙስሊሙም የክርስቲያም የጋራ አባት ነው፡፡ በእሱ አማካይነት የሚከናወኑ ትውፊቶች ሁሉ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ እሴቶች ናቸው፡፡ ሁለቱም አካላት ለነዚህ የጋራ እሴቶች ይገዛሉ፤ በእሴቶቹም እኩል ይገለገላሉ፡፡ ለምሳሌ የወሎዬዎች ሠላም ተጠብቆ፣ ማኅበራዊ ሥርአታቸው ሳይናጋ እንዲቀጠል ለማድረግ ሲባል፤ የአበጋር "ቆቲ"[129] እና "መሥዋሃ"[130] ከቄስ ቤት ይገባል፡፡ ትውፊቱም የአገር ሃዳ ነውና የወሎ ቄስ የአበጋርን ደንብና ሥርአት ያከብራል፡፡ ደንብና ሥርዓቱም በቄሱ ቤት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

የአበጋር ቆቲና መሥዋሃ በወሎ ከዘመኑ የፍርድ ቤት መጥሪያ ጋር ይነፃፀራል፡፡ ነገር ግን የፍርድ ቤት መጥሪያ ተግባራዊ የሚደረገው ሕጉ ባሰፈረው አንቀጽ አግባብ ነው፡፡ የአበጋሩ ግን ከሥነ-ልቡና፣ ከሃይማኖታዊ፣ ከማኅበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር የተሳሰረ አንድምታ አለው፡፡ ተቀባይነቱና ተፈፃሚነቱም ከነዚህ ጉዳዮች ጋር የተገናኘ ነው፡፡ በመሆኑም ክርስቲያን-ሙስሊሙ በወሎ በአበጋር ትውፊት እርስ በርስ ይገናኛል፤ ይተሳሰራል፤ ይተዳደራል፡፡ እንድሪስ አህመድ ትስስሩን የሚገልጹት በሚከተለው ሁኔታ ነው፡፡

---

[128] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 10 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ-ባዶ፡፡

[129] "ቆቲ" አበጋሮች እሚይዙት ተዕምርታዊ ወይም ተምሳሌታዊ አንድምታ ያለው ከተመረጠ እንጨት የተዘጋጀ (የተባረከ/የተመረቀ) በትር (ዓለ. መሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም.ሐብሩ-አንጦ- 04 ቀበሌ)፡፡

[130] "መሥዋሃ" አበጋሮች እሚይዙት መቁጠሪያ (እንደላይኛው)፡፡

> በፊት ጀምሮ በጎብረተሰቡ ዘንድ የሃይማኖት ልዩነት አለመኖሩን የምታየው፤ በጣም እሚገርምህ ነገር በዚህ በወሎ አበጋር እሚባል አለ። እነዚህ አበጋሮች ሙስሊሞች ናቸው። ግን ቂሱ ሳይቀር ክርስቲያኖቹን የሚያስታርቁት እነሱ ናቸው። ለምሣሌ በወሎ ደም እሚደርቀው በአበጋር ነው።አንድ ሰው ነፍስ አጠፍቶ፣ ወይም ቤት አቃጥሎ ወይም ከምር አቃጥሎ ወይም ሰርቆ ወይም አንድ ነገር አድርጎ ከሆነ፤ አበጋሮቹ ጋር ሂዶ ሽገባ አይነካም። እና የተበደለው ክርስቲያን ቢሆን እንኳን፤ የአበጋር ቆቲ ከመጣበት አያጥፍም፤ እሺ ነው እሚለው። እታረቃለሁ ይላል። ይሽ ምንን ያሳያል በሃይማኖት ምክንያት ልዩነት አለመኖሩን ነው።[131]

ከላይ መረጃ አቀባዩ በጥቅሱ ውስጥ እንደገለጹት ክርስቲያንም ሆነ ሙስሊም በሰራው ጥፋት ተፀፅቶ ለመታረቅ ወይም ከጥቃት ለማምለጥ አበጋርን ጥላና ከለላ ወይም መጠጊያ ያደርጋል። ትውፊቱ ከክርስትናው አንፃር ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ ደውሎ እንደመጠለል ማለት ነው። በዚህ መሰረት ያገሩ ባህል፣ ወግና ልማድ ስለሆነ ይህንን ደንብና ሥርአት ጥሶ በደለኛውን የሚበቀል አካል የለም። ባንፃሩ የተበደለው ወገን ለጥፋተኛው ይቅርታ ማድረግ እንዳለበት በአበጋር ትውፊት ይገደዳል። ይህንን ትውፊት ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ ያከብራል፤ ያስከብራል፤ በእሱም ይተዳደራል።

በወሎ በአበጋር ትውፊት ደም ይደርቃል። የተጣላ ይታረቃል። የተሰረቀ ይመለሳል። የጠፋ ይገኛል፤ የተሰወረ ይገለጣል። በልብ ያለም ሳይቀር ይፋ ይወጣል። የወሎዬዎች ሠላምና ፍቅርም በዚህ ትውፊት አማካይነት ይጠበቃል። እርስ በርስ ተደጋግፎና ተቃቅፎ የመኖር ባህላቸውም በአበጋር ትውፊት ይበልጥ ይሰምራል። ይህም በመሆኑ፤ ወሎዬዎች በጋራ መክረውና ዘክረው፣ የዘር ሐረጉን ቆጥረው፣ ዲናውን መርምረው፣ አበጋር ይሾማሉ። ከዚህ በኋላ ሥራውን በጋራ ይሰራሉ። ለማኅበራዊ ኑሮው የሚያስፈልጉትን ጉዳዮች በጋራ ያሟላሉ። አበጋሩ በበኩሉ ወሎዬዎች እርስ በርስ የሚገናኙባቸውና የሚተሳሰሩባቸው እሴቶች ሳይናጉ እንዲቀጥሉ ያደርጋል። ፍቅርና ሠላምን ያሰፍናል። ወሎዬዎች በሃይማኖት ሳይለያዩ ተረዳድተውና ተደጋግፈው በአንድነት እንዲኖሩ ያደርጋል።

ምክንያቱም አበጋሩ በሃይማኖቱ ከእስልምናው ወገን ቢሆንም፤ ኃላፊነቱና አገልግሎቱ ግን ለሙስሊሙም ለክርስቲያኑም ነው። የአገር አባትነቱ ለሁለቱም ወገን ነው። አባትነቱ ደግሞ በሁለም የወሎዬዎች የማኅበራዊ ሕይወት ዘርፍ ሁሉ ነው። ለምሳሌ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አበጋር በወሎ ተሰጦው የተለያየ ነው። አገልግሎቱም በዚያው ልክ ነው። በአገልግሎቱ በኩል የሚገኘው በረከትም ከዚሁ ተሰጦው ጋር የተሳሳረ ነው። ወሎዬዎች በአበጋር ተሰጥኦ በረከት ከሚያጭዱባቸው ትውፊቶች መካከል አንዱ ወዳጃ ነው። ወዳጃ በወሎ

---

[131] እንድሪስ አህመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 03 ቀበሌ።

አይነቱ ሦስት አራት ነው። ዓላማውም የተለያየ ነው። ፋይዳው ግን አንድ ነው። ይኸውም ክፉ ነገር እንዲርቅ፤ ባንፃሩ መልካም ነገር እንዲቀርብ ማድረግ ነው።

5.3.4፡-ወዳጃ በወሎ

ቀደም ሲል እንደተብራራው ወሎዬዎች እንቅፋቶቻቸውን የሚያስወግዱባቸው፤ ባንፃሩ በረካ የሚያገኙባቸው በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው። ከነዚህ የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ የወዳጃ ትውፊት ነው። የወዳጃን ትውፊት እንድሪስ ይመር የሚገልጹት "ወዳጃ! እንደው የወዳጃውን ልንገረህ ደስተኝነት ነው፤ ሌላም ነገር የለው። እንግዲህ እኔ አንተ ስትመርቀኝ ጥሩ ነገር የማገኝ ይመስለኛል! ወሎ እንግዲህ ይኸው ነው!"[132] በማለት የበረከት ምንጭነቱን በማረጋገጥ ነው። በተመሳሳይ መላኩ ተገኘ የወዳጃን ትውፊት "ወዳጃ ምን መሰለህ! አንድ ሰው ያጣል ይነጣል፣ ይቸገራል። ጤናው ይስተጓጎላል፣ የዚያን ጊዜ ሃጃዬን ይሞላልኛል ብሎ የሚያስበውን በአብዛኛው ሙስሊም ሰው የተለያዩ ዝገጅቶችን አዘጋጅቶ ከቤቱ ይጠራና ሃጃውን ተናግሮ እንዲመረቁት ያደርጋል። ወዳጃ ይሄ ነው!"[133] በማለት ይገልጹታል። በዚህ መሰረት በወሎ ሰው የጤና እክል ሲገጠመው ጤናው እንዲስተካከልለት ለማድረግ ወዳጃ ያስገባል። በወሎ ሰው በማኅበራዊ ሕይወቱ የተሻለ ስኬት እንዲገጥመው በማሰብ ወዳጅ ያስገባል። መጥፎ ነገር ሊገጥመኝ ይችላል ብሎ ካሰበም፤ ሊደርስበት ከሚችለው መጥፎ ነገር ለመዳን ወዳጃ ያስገባል። በወሎ አንድ ሰው የራሱን፣ የቤተሰቡን፣ የጎረቤቱንና ያገሩን ሠላም በመመኘት ወዳጃ ያስገባል። ፈጣሪ የሰው መውደድ (ፍቅር) እንዲሰጠው በመሻት ወዳጃ ያስገባል። በወሎ አንድ ሰው አዝመራው እንዲይዝለት፣ ከብቶቹ አንዲረቡለት፣ ግጦሽ እንዲለመልምለት፣ ባጠቃላይ ማጀቱ እንዲሞላለት ወር መርጠ፤ ቀን ቆርጦ ወዳጃ ያስገባል። የወደዳጃን ትውፊት ፋይዳ በወሎ አበጋር ማዱ በላይ በበኩላቸው የሚገልጹት በሚከተለው ሁኔታ ነው።

> ለታመመ እንዲድን ወደጃ ነው። ደህይቶ እንደሆነ እንዲከብር ወዳጃ ነው። ሸመት ፈልጎ እንደሆነ፤ ሸመት እንዲያገኝ ወዳጃ ነው። አዲስ ቤት ሰርቶ ያቤት በሠላም እንድኖርበት፣ እንግዳ ተቀብሎ እንድያስተናግድበት፣ ልጆቹን እንዲድርበትና እንዲኩልበት፣ የሚያበላበትና የሚያጠጣበት እንዲሆን ወዳጃ ነው። ሚስቱ ወይም ላሞቹ መሆን ከሆኑበት፤ እንዲወልዱለት ወዳጃ ነው። በወሎ ሁሉም ነገር በወዳጃ ነው። በጉልበት እሚሆን ነገር የለም። ሃብትን፣ ስልጣንንና ጉልበትን ተመክቶ እሚሆን ነገር የለም። አገራቱ የጉልበተኛ አገር አይደለችም። ለምሳሌ አንድ ጉልበተኛ መጥቶ ጉልበት የሌለውን ቢበድል፤ ወደ ክርክር አይገባም። ወደ ፍርድ ቤት አይሄድም። ቀጥታ ወደ አበጋር ነው፤ እሚሄደው።እዚያ ሂዶ

[132] እንድሪስ ይመር፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 22 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ ወረዳ- ቁጥር 14 ቀበሌ።
[133] ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 21 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ።

> ለአበጋሮቹ "ጉልበተኛ ጣለብኝ ገላግሉኝ!" ማለት ብቻ ነው፡፡ እነሱም "ገላግለኝ ያን እርጉም፤ ሱሪ ሳይታጠቅ ፈረሱን ሳይለጉም!" ይሉታል፡፡ ከዚ ያ የተመካበት ጉልበቱ፣ ሃብትና ንብረቱ፣ ስልጣኑ፣ በዋለ ይቀራል፡፡ከንቱ ይሆናል![134]

ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ እንደሚሉት በወዳጃ ትውፊት አማካይነት ክፉ ነገር የሚርቀውም ሆነ የሚቀርበው ርዚቅ፤ የሚገኘው በሰዎች ኃይል ሳይሆን፤ በፈጣሪ ፀጋ ነው፡፡ ወይም ፈጣሪ መሃላውን በነየተላቸው የወሎ ደጋጎች አማካይነት ነው፡፡ ሼሁ ይህንን ሁነት የሚገልጹት "እኛ እምናደርግላቸው ምንም ነገር የለም! እኛ እምናደርገው ምንድን ነው የጠየቁት ነገር እንዲፈጸምላቸው ለፈጣሪ ነግረን መውጣት ብቻ ነው!"[135] በማለት የነሱ ድርሻ ምን እንደሆነ በማብራራት ነው፡፡ በዚ መሰረት ይሄ ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች የወዳጃ ትውፊት ውጤት፤ በወዳጃ ገቢው ማንነትና ወዳጃው በሚከወንበት ወራት ይወሰናል፡፡ የክዋኔ ሥርአቱም የራሱ ድርሻ አለው፡፡ በዚህም ከወዳጃ ገቢዎቹ ግለሰቦች አንፃር የአበጋር፣ የዱበርቲ፣ የጢነኛ፣ የሼነቻና የቃልቻ ወዳጃ የሚሉ ስያሜዎች አሏቸው፡፡ ወዳጃ ከሚከወንበት ወራት አንፃር ደግሞ የሚያዚያ፣ የግንቦት፣ የጥቅምትና የታኅሳስ ወዳጃ በመበል ይታወቃል፡፡ አልፎ፣ አልፎ የጳጉሜ ወዳጃ የሚባልበት አጋጣሚም አለ፡፡[136]

አበጋር ማዱ በላይ እንደሚሉት የአበጋር ወዳጃ በወሎ እንደስሙ በአበጋር ብቻ የሚከወን አይደለም፡፡ በዋናነት በአበጋር የሚከወን ቢሆንም ግለሰቡ "እከሌ ሃጃዬን ያወጣዋል! ወይም ምኞቴን ያሳካዋል!" ብሎ የሚወስነው ጉዳይ ነው፡፡ይህንን ሲያደርግ ግን የግለሰቡን ብቀቃት፣ የግለሰቡን ተሰጥኦ፣ የግለሰቡን ከራማ፣ የግለሰቡን ስብእናና ልምድ መሰረት አድርጎ ነው፡፡ ፈጣሪን ለምኖ ሊያስፈፅምለት እንደሚችል ተማምኖ ነው፡፡ ነገር ግን ለአበጋር ወዳጃ የሚገባ ሰው ሁሉም ሳይሆን፤ ከሰው፣ ሰው ተመርጦ ነው፡፡ ከሃይማኖት አንፃርም የአበጋር ወዳጃ የሚገባው ሰው ሙስሊም ነው፡፡ አልፎ አልፎ ግን ብቃቱና ተሰጥኦው ያላቸው ክርስቲያኖችም በአበጋር ወዳጃ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ የአበጋር ወዳጃ የሚያስገቡት የማኅበረሰብ ክፍሎች ደግሞ ሙስሊሞቹም ክርስቲያኖቹም ናቸው፡፡[137]

እንድሪስ ይመር እንደሚሉት የአበጋር ወዳጃ ከግንቦትና ከጥቅምት ወራት በስተቀር፤ በሌሎቹ ወራት ሊገባ ይችላል፡፡ የግንቦትና የጥቅምት ወራት ግን የቃልቻ ወዳጃ የሚገባባቸው ወራት

---

[134] አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ-ገዶ፡፡
[135] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 01 ቀበሌ፡፡
[136] አማኑኤል ሰማው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ፡፡
[137] አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ፡፡

ናቸው። ለአበጋር ወዳጃ በአብዛኛው የሚያዚያና የታኅሳስ ወራት ከሌሎቹ ወራት በተለየ ተመራጭ ወቅቶች ናቸው።[138]

ይህም የሆነበት ምክንያት "ሚያዚው እንዲገጥመኝ!" እንዲሉ ወለዬዎች፤ ወቅቱ እጣ ክፍላቸው እንዲሆን በሚያዚያ ወዳጀ ያስገባሉ። ይህም የሚያዚያ ወዳጃ በመባል ይተወቃል። አሰፋ አበጋዝ እንደሚሉት የሚያዚያ ወር በየጁ የዓመት አዝመራ የሚዘራበት ወቅት ነው። ወለዬዎች ድግስ ደግሰው ልጅ የሚድሩበት፣ ማኅበርና ሰደቃ የሚያወጡበት፣ ወዳጃ አስገብተው የሚመራረቁበት፣ በዓመት በዓል ደግሰው በጋራ የሚጨፍሩበትና የሚዘፍኑበት የማሽላ (ደጋሌት) ምርት የሚዘራው በሚያዚያ ወር ነው።[139] በዚህ መሰረት ሚያዚያው እንዲገጥማቸው ወለዬዎች የበሬ እቃቸውን ሰብስበው ወዳጃ ያስገቡታል። ቱፍታ ያስደርጉበታል። ባመቱም "የጫኝ ያለህ!" የሚያስብል ምርት ያፍሱበታል። በዚህ ወቅት ሃጃውን ለሞሉለት የወለ ደጋጎች ኮርማ ወይም ሙክት ጀባታ አቅርቦ የበለጠ እንዲያገኝ ይመረቅበታል።[140]

በሌላ በኩል የሚመረተውና ተመርቶ ወደቤት የገባው ምርት በረከትና ረድዔት ያለው፣ የሠላምና የደስታ ቀለብ እንዲሆን ደግሞ የታኅሳስ ወዳጃ ይገባለታል።"ወለ መጀን!" ይባልለታል። እንዲሁም የወለ ሰው ያልታሰበ የጤናም ይሁን የሌላ ጉዳይ እክል ቢያጋጥመው በየትኛውም ጊዜ "የቀንና የሌሊት" የአበጋር ወዳጃ በማስገባት ጤናውንና ሠላሙን ያረጋግጣል። የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት በአበጋር ወዳጃ ወቅት ግዳጅ የሚፈፀምባቸው የተለያዩ መሳሪያዎች አሉ። ከነዚህ መሳሪያዎች መካከል የልብ፣ የአካልና የአከባቢ ንጽህና፣ ጫት[141]፣ ቡና፣ ጠላ፣ ትባሆ (አጥያ)፣ የተለያዩ ጢሳ ጢሶች፣ እርጥብ ነገር እና የተለያዩ ቁሳቁሶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።[142]

አበጋር ማዱ በላይ እንደሚሉት ጫት፤ አንድ ሰው ታሞ እንደሆነ እንዲድን፣ አጥቶም እንደሆነ እንዲያገኝ፣ ታርዞም እንደሆነ እንዲለብስ የማድረጊያ መሳሪያ ናት። በመሆኑም በአበጋር ማዱ ማብራሪያ መሰረት ጫት፤ "መፍለጫም ናት ምሳር፣ መጋጠጫም ናት ማጭድ፣ መቆጥቆጫም ናት ጥልቆ፣ እሷን ቅሞ ዱዓ ኻደረገ የመረቀውን የተባረከ ማድረግ ነው። የረገመውን ደግሞ

---

[138] አንድሪስ ይመር፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 22 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ ወረዳ- ቁጥር 14 ቀበሌ።

[139] አሰፋ አበጋዝ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ።

[140] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 01 ቀበሌ።

[141] በአካባቢው በፊት የነበረውንና አሁን ያለውን የጫት ሥርአት እና ጫት የሚቃምበትን መሰረታዊ ምክንያት የአካባቢው ነዋሪዎች የሚያነፃጽሩት "የዱባና የቅል ያህል ነው!" በማለት፤ የድሮው በትክክል ሥራ ላይ የሚውልና የተሟላ ደንብና ሥርአት የነበረው ባህል እንደነበር ይገልፃሉ። የአሁኑ ግን ሰው የሚድንበት ሳይሆን ትውልድ የሚጠፋበት "ጫት የመብላት" አባዜ ነው። (እንደላይኛው)።

[142] ዓለሙ ኃይሉ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 02 ቀበሌ።

ወደ ገደል መልቀቅ ነው፤ ወይ መግደል ነው። ወይ አገር ማስለቀቅ ነው። "ሽሷ ቅማችሁ ሽኔ ጋር ተገናኙ ስላለ አላህ ሽቅጠሉ ሁሉ አልቆ ፈጥሯታል!"[143] በሚል አስተሳሰብ የተቃኘ በወዳጃ ትውፊት ውሰጥ ከፍተኛ ቦታ አላት። ሌሎቹም ጉዳዮች የየራሳቸው የሆነ መገለጫ አላቸው።

ይሄ ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች የዱበርቲ ወዳጃ ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው በሴቶች ብቻ የሚከወን የወዳጃ ዓይነት ነው። በዚህ የወዳጃ ትውፊት መሰረት ከዋኞቹ ሴቶች ብቻ ናቸው። ወዳጃውን የሚያስገቡትም በተመሳሳይ ሴቶች ብቻ ናቸው። ሥርአቱ የሚከወነው ብዙውን ጊዜ ቀን ላይ ነው። በዚህ ሠዓት የቤቱ አባወራ በሥነ-ሥርአቱ ላይ የመገኘት ግዴታ የለበትም። ለመገኘት ከፈለገ ግን የሚከለክለው ነገር የለም። ትውፊቱ በአካባቢው አጠራር መሰረት "እርፎ መረበባ" በመባል ይጠራል፡[144]

የዱበርቲ ወዳጃ በፀብ ጊዜ እርቅ እንዲወርድ፣ በእርቅ ጊዜ ደግሞ እርቅ እንዲሰምር፣ በድርቅ ጊዜ ዝናብ እንዲዘንብ፣ እርጉዝ ሴት በሠላም እንድትገላገል፣ በፀና ታሞ በሕይወትና በሞት መካከል የሚገኝ ህመምተኛ ምህረት እንዲያገኝ... ወዘተ በማሰብ ተግባራዊ የሚደረግ ትውፊት ነው።

ባጠቃላይ የዱበርቲ ወዳጃ ዋና ዓላማ ግለሰብም ሆነ የአካባቢው ማኅበረሰብ ጤና፣ ሠላምና ፍቅር አግኝቶ እንዲኖር ማደረግ ነው። መሬቱ አንዲያፈራ፣ ከብቱ እንዲረባ፣ ምንፅዩ እንዲፈልቅ፣ ወንዙ እንዳይደርቅ፣ የአካባቢው ርዚቅ እንዳይርቅ መለማመን ነው።[145] ዱበርቲዎች በእድሜ የገፉ፣ ከክፉ ነገር የራቁ፣ ፈጠሪንና ሰውን የሚያስታርቁ፣ በሥነ-ምግባር የተመረጡ፣ ተሰጥውና ልምዱ ያላቸው ሊሆኑ እንደሚገባ ይታመናል። ከሃይማኖት አንፃር ከዋኞቹ ሙስሊሞች ሲሆኑ፤ ወዳጃውን የሚያስገቡትና ተሳታፊዎቹ ግን ሙስሊሞቹም ክርስቲያኖቹም ናቸው።[146] በዚህ መሰረት ትውፊቱም በረከቱም የጋራ ነው። ለዱበርቲ ወዳጃ የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ከአበጋር ወዳጃ ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

የጢነኛ ወዳጃ በአፍላ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ተሰባስበው በጋራ የሚከውኑት ትውፊት ነው። ትውፊቱ አንድን መጥፎ ነገር ከሸንኮፉ ነቅሎ የማውጣት ኃይል እንዳለው ይታመናል። ይህም ከወጣቶቹ አፍላነት ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ትውፊት ሃይማኖት

---

[143] አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠየቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላላቶ- ገዶ።
[144] አበራ አምበዬ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 19 ቀን 2007 ዓ.ም. ቆቦ ከተማ- 02 ቀበሌ።
[145] ደሳለ ፈንታው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 20 ቀን 2007 ዓ.ም. ራያና ቆቦ ወረዳ- አራዶም።
[146] ከድጃ ከድር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 16 ቀን 2006 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ሐራ።

መስፈርት አይደለም። መስፈርቱ እድሜ ብቻ ነው። ለወዳጃው የሚያስፈልገው ግብአት ግን ከአበጋር ወዳጃ የተለየ አይደለም።[147]

ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ እንደሚሉት የቃልቻ ወዳጃ የሚደረገው በአብዛኛው ግንቦት ወር ላይ ሆኖ፤ ትውፊቱ ከሌሎች የወዳጃ ትውፊቶች ሁሉ ይለያል። ምክንያቱም የቃልቻ ወዳጃ ግንኙነቱ ከዛር መንፈስ ጋር የተቆራኘ ነው። ይህም ትስስሩ ከቅዱስ መንፈስ ጋር ሳይሆን፤ ከእርኩስ መንፈስ ጋር የተያያዘ ነው። ከባለ ዛርና ከጥንቆላ ባህል ጋር የተዛመደ ነው።[148] ከድጃ ከድር በበኩላቸው የቃልቻ ወዳጃ ከአበጋር ወዳጃ በምን እንደሚለይ፣ መቼና ለምን እንደሚገባ የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> የቃልቻ ወዳጃ እሚገቡቱ በጥቅምት ወር፣ በታሳስ ወር፣ በግንቦት ወር በነይህ በሶስቱ ነው። ከአስራ ሁለቱ ወር ለቃልቾቹ ይኸ ተፈቅዷል። ለምን? በግንቦት ወር ለወዳጃ ጠላ አይጠመቅም። ጥቅምትም እንደዚያው፤ ታሳስም እንደዚያው። ለምንድን ነው ሲባል የቃልቻ ወዳጃ ነው። ወራቱ ጠላ ተጠጥቶ ዱዓ እሚደረግበት ወዳጃ እሚገባበት ወቅት አደለም። አበጋሮቹ ደሞ ጠላ ስለሚጠጡ የተቀሩት ዘጠኙ ወራት የአበጋሮቹ ናቸው። ለምን? ዋናው ታርጌቱ ያለው ጧቱን ወሎ ስትቀና በትንባሆና በጠላ ስለሆነ ያለ ጠላ አበጋር ወዳጃ አይገባም። ለምን? ጠላ ሳትጠምቅ አበጋሩን ና ብትለው ወንዘኛ የተባለ፣ ጅኒይ የተባለ ሚስጢር አዋቂ ስለሆነ ጅኒይ፤ እገሌ አባበሉ ቤት ወዳጃ አለ ሲባል፤ አድሩሱ የሚጨሰውን ለማሽተት፣ ጨፌውን ለማሽተት፣ ቡኑን ለማሽተት፣ ሰውቱን አላህ መሶሌ ሲባል ለማዳመጥ ክብብ ይላል፤ ይኸ ተጠራርቶ። ኸይህ ኸደጃፉ ሁኖ ይኸን ሁላ ቡኑ ሲጠጣ ሽታውን፣ ጫቱ ሲቃም ሺታውን፣ የጠላውን ሽታ፣ ይኸን ሁላ ሲቃመስ አድሮ፤ የለሊት ወዳጃ እንደሆነ መዳ ታድሎ ውሌውን ይዞ ሲወጣ ጅኒውም አብሮ አበጋሩ ጋር ይወጣል። ኸዚያ ያ ቤት መነቃነቂያ የለውም። እስተ መጨረሻው፤ እስተ ልጅ ልጅ ድረስ። ቃልቻው ግን ይኸን ይኸን አያደርግም። በዚህም የቃልቻ ወዳጃ እርባና የለውም ይባላል።[149]

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ እንደተብብራው በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ትውፊቶች አማካይነት ወሎዬዎች እድሜና ጤና፣ ሠላምና ፍቅር ሊያገኙ እንደሚችሉ ያምናሉ። ለዚህም የተለያዩ ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ክዋኔዎችን ይከውናሉ። ወሎዬዎች በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ትውፊቶች አማካኝነት በተሰማሩበት የሥራ መስክ ስኬትን፣ በሚናገሩበት አደባባይ ተደማጭነትን፣ በሚሄዱበት ቦታ ተቀባይነትን፣ በሚታዩበት መድረክ ክብርና ሞገስን እንዲያጎናጽፏቸው ይፈልጋሉ። ለዚህም ስዕለት ይሳላሉ፣ ዝክር የይዘክራሉ፣ በዓላት ያከብራሉ፣ ጀባታ (ሃዲያ) ይሰጣሉ።

---

[147] መሐመድ ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ራያና ቆቦ- ሮቢት።
[148] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።
[149] ከድጃ ከድር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 16 ቀን 2006 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ሐራ።

ወለዬዎች በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ትውፊቶች አማካይነት የዘሩት እንዲያፈራ፣ ያመረቱት እንዲበረክት፣ የተከሉት እንዲለመልም፣ የወለዱት እንዲያድግ፣ የሞቱት እንዲፀድቁ...ወዘተ ይሻሉ፡፡ ለዚህም አስራት ይከፍላሉ፣ ሰደቃ ያወጣሉ፣ በጋራ ቤተ-እምነት ይሰራሉ፣ የሰሩትን ቤተ-እምነት በጋራ ይጠብቃሉ፡፡ በጋራ ይንከባከባሉ፡፡ ወለዬዎች በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ትውፊቶች አማካይነት እርኩስ መንፈስ እንዲርቅላቸው፣ በምትኩ ቅዱስ መንፈስ እንዲቀርባቸውና ሊመጣባቸው ከሚችል መጥፎ ነገር እንዲጠብቃቸው ይማጸናሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ ፀበል ይፀበላሉ፣ ወዳጃ ያስገባሉ፣ መስቀል ይታሻሉ፣ እምነት ይቀባሉ፡፡

ይህ ሁሉ የወለዬዎች የልብ መሻት የሚፈጸመው ደግሞ በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ተሰጠውና ብቃቱ ባላቸው የወለ ደጋጎች ወይም አራት ዓይናዎች አማካይነት ነው፡፡በወለ ሼሆች፣ በወለ ወልዮች፣ አማካይነት ነው፡፡ ወለዬዎች ወዳጆቻችንና ጠባቂዎቻችን በሚሏቸው መላዕክት፣ ፃድቃን፣ ነቢያትና ሰማታት ተራዳዒነት ነው፡፡ በወለ አድባርና ከራማ አጋዥነት ጭምር ነው፡፡

እነዚህ አካላት ፈጣሪን ለምነው ወይም ፀልየው አልያም በራሳቸው መልካም ፍቃድ የወለዬዎችን ሃጃ ይሞላሉ፡፡ ክፉውን አግልለው፣ የራቀውን አቅርበው፣ ለወለዬዎች እንካችሁ በረከት ይላሉ፡፡ በዚህ ሂደት ወለዬዎች ሃጃቸው እንዲሞላ ክርስቲያኖቹ ወደ አስልምናው፤ ሙስሊሞቹ ወደ ክርስትናው ትውፊቶች ይሄዳሉ፡፡ ትውፊቶቹም የወለዬዎች የጋራ እሴቶች ናቸውና ክርስቲያን ሙስሊም ሳይሉ፤ ሁሉንም በጋራ ያስተናግዳሉ፡፡

5.4፡- የክርስትናና የእስልምና ትውፊቶች ተራክቦ በወለ

ከዚህ በላይ በቀረቡት ንዑስ አርእስት እንደተብራራው፤ በወለ በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ትውፊት መሰረት ወለዬዎችን የሚያገናኙና የሚያስተሳስሩ በርካታ የጋራ እሴቶች አሉ፡፡ በዚህም በወለ ክርስቲያኖቹ ለእሰልምናው፤ ሙስሊሞቹ ለክርስትናው ትውፊቶች ከፍተኛ ክብርና ፍቅር ወይም የእኔነት ስሜት አላቸው፡፡ ለምሳሌ የወረ-ካሎ ገጠር ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት ሙስሊም ወይዘሮ ሙሉ ደሳለኝ፤ ቀደም ሲል እንደተገለፀው የወረ-ካሎ ተክለሃይማኖትን እምነት ተቀብተው፣ መስቀላቸውን ታሽተው፣ ፀበላቸውን ጠጥተው፣ ፃድቃቸውን ቀምሰው ሃጃቸው ስለሞላ፤ ለተክለሃይማኖት ያላቸውን ፍቅር የገለጹት "ተክለሃይማኖትዋዬ! አላህዋዬ! የቀልብያየን ስላደረሱልኝ የተክልዬ ለታ ምንም ሥራ

አልሰራም፤ ኩብር ብዬ በየስድስት ወሩና በያመቱ እየመጣሁ ተክልዬን አከብራለሁ!"[150] በማለት ነው።።

ባንዳሩ የወሎ ክርስቲያን ለወሎ ደጋጎች ወይም ሼሆችና ወልዮች ያለውን ክብርና የእኔነት ስሜት የሚገልፀው ስማቸውን ጠርቶ በመማል (አውነትን ለማረጋገጥ) ወይም "የሼሆቹ አሽከር!" ብሎ የወንድነት ስሜቱን በመግለፅ ጭምር ነው።። አለያም "ሼሃችን! እነ ሼህ!" ብሎ በመጥራት ነው።። ከዚህም ሲያልፍ "በሼሆቹ በደጎቹ ወሎ መጀን! ሼሆቹ መጀን! በሠላም ያዋለኝ በሠላም ያሳድረኝ፤ በሠላም ያሳደረኝ በሠላም ያውለኝ! በቀኝ ያውለኝ! ከክፉ ነገር ይሰውረኝ!.. ወዘተ" ብሎ ኸይር አንዲያውለትና ኸይር እንዲያሳድሩት ይመኛል።። በዚህም ክብሩንና ፍቅሩን ይገልፃል።።

ፈቃዱ ቤኛ የተባሉ የታሪክ ተመራማሪ የወሎ ክርስቲያን ለወሎ ደጋጎች ያለውን ክብርና የተለየ ቦታ የገለፁት ደሴ አካባቢ የሚኖሩ የአንዲት ክርስቲያን ወይዘሮ ገጠመኛቸውን ምሳሌ በመጥቀስ ነው።። ወይዘሮዋ እመት ወርቂት ወዳጆ ይባላሉ።። ተመራማሪው እመት ወርቂትን ስለ ወሎው ጌታው ሼህ ሰይድ እንዲያጫውቷቸው ጠየቋቸው።። ነገር ግን ወይዘሮዋ ፊጠን ብለው "ኧረ! እጣን ሳይጤስ ስማቸው አይነሳም! አይበጅም!"[151] በማለት ለጌታው ሼህ ሰይድ ክብር እጣን ካጤሱ በኋላ ስለእሳቸው እንዳጫወቷቸው ተመራማሪው ፅፈዋል (Faqadu 1972: 36)። ፈቃደ አዘዘ በበኩላቸው ከረኸቦም ዓመት በፊት ወሎ-ደሴ በነበሩበት ወቅት፤ ሐይቅ አካባቢ የሚገኙ መስሊሞች በአካባቢያቸው የሚገኝ ታቦት አገልጋይ ስላልነበረው እነሱ አገልጋይ ቀጥረው ያስቀደሱ እንደነበር ያስታውሳሉ።። ፈቃደ እንደሚሉት በወቅቱ መስሊሞቹ ይህንን ለምን እንደሚያደርጉ ጠይቀው ያገኙት መልስ፤ "ታቦቱ ካልተቀደሰ በስተቀር ተቀይሞ ድርቅ ያመጣብናል!" የሚል ነበር።።[152] በዚህ መሰረት የእመት ወርቂት ወዳጆም ሆነ፤ በዚያን ወቅት ሐይቅ አካባቢ የሚገኙ መስሊሞች አስተሳሰብ ወይም አመለካከት መሳ ለመሳ ነው።። ምክንያቱም እመት ወርቂት በእስልምናው በኩል ያለውን ትውፊት ካላከበሩ ምን ሊመጣ

---

[150] መ/ሊ ደሳለኝ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 24 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ።።

[151] The writer of the paper can never forget an incident when, in the course of interviewing a christian Wollo lady, the name of Sheikh Sayid came up. The lady told him to shut up and only began to talk after some incense was burnt as a mark of respect to the sheikh. This was in the course of a serious of interview at dessie in 1970 with Imet Werqit Wodajo (Faqadu 1972: 36).

[152] ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ እንደሚሉት ወሎ ውስጥ ያለው የሃይማኖት መቻቻል እሴት የሚለካው፤ በወሎም ሆነ፤ ባጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ በሃይማኖት ሰበብ በተካሄዱ ጦርነቶች ሳይሆን፤ "በህዝቡ አኗኗር ውስጥ ባሉ ትረኮች ነው!" የሚል አቋም አላቸው።። ከላይ የተጠቀሰውን ገጠመኝ የተናገሩት ደግሞ ጥር 14 ቀን 2007 ዓ.ም.፤ ለዚህ ትልመ ጥናት የውስጥ ፈታኝ ሆነው በተገኙበት ወቅት አስተያየት ሲሰጡ ነው።።

እንደሚችል ልባቸው ያውቃል። ፈቃደ የጠየቋቸው የሐይቅ አካባቢ ሙስሊሞችም ታቦቱን ካላስቀደሱ ምን ሊከሰት እንደሚችል መተንበይ አላቃታቸውም።

በዚህ መሰረት ከነዚህ ጥቅሶች መረዳት የሚቻለው መሰረታዊ ነጥብ የሁለቱ ሃይማኖቶች ትውፊቶች ምን ያህል አርስ በርስ የተሳሰሩና በወሎዬዎች ልብ ውስጥ ሰርፀው የገቡ መሆናቸውን ነው። ምክንያቱም ክርስቲየኑ የእስልምናውን፤ ሙስሊሙ የክርስትናውን ትውፊቶች የሚያከብረውና የሚተገብረው በተፃፈ ሕግ ወይም የአንደኛው የሃይማኖት ተከታይ በሌላኛው የሃይማኖት ተከታይ ላይ በፈጠረው ጫና ሳይሆን፤ በራሱ የልብ መሻት አማካይነት ነው። ይህ ደግሞ ከፎክሎር ተፈጥሯዊ ባህርይ የሚመነጭ እሴት ነው።

በዚህ ጥናት የፅንሰ ሃሳብ ማብራርያ ላይ እንደተጠቀሰው፤ ፎክሎር ሰዎች ከልባቸው አምነውና ፈቅደው፤ የእኔ የራሴ ብለው የሚፈጽሙት ተግባር ነው። አስገዳጅ ነገር አለ ከተባለም፤ የራሳቸው ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ ነው። የራሳቸው ባህል፣ ወግና ልማድ ነው። ይህ ደግሞ ከእነሱ፣ ለእነሱ፣ በእነሱ የሆኑ የፎክሎር እሴቶች ተግባራዊ የሚደረጉበት መድረክ ነው።

ከላይ የተለያዩ አብነቶችን በመጥቀስ እንደተብራራው በወሎ ክርስቲያኖቹ እስልምናውን፤ ሙስሊሞቹ የክርስትናውን ትውፊቶች የሚጋሩባቸው መንገዶች እጅግ በርካታ ናቸው። የሚገለፁትም በተለያዩ መንገዶች አማካኝት ነው። ከነዚህ መገለጫዎች መካከል ወሎዬዎች ለቆሎ ተመሪና ለደረሳ ያላቸው አመለካከት ለአብነት ይጠቀሳል።

5.4.1:- የቆሎ ተማሪና ደረሳ በወሎ

በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ትውፊቶች መሰረት ለቆሎ ተማሪም ይሁን ለደረሳ ደመወዝ አይቋረጥም፤ ቀለብ አይሰፈርም። በምትኩ ክርስቲያን ሙስሊም ሳይል አባወራ ተቆጥሮ፣ ድንበር ተለይቶ፣ የቆሎ ተማሪም ሆነ ደረሳ ለወሎዬዎች ይከፋፈላል። ክፍፍሉ ደግሞ በቋንቋ፣ በዘር፣ በሃይማኖት በሃብትና በፆታ ላይ የተመሰረተ አይደለም። ክፍፍሉ ቆላ-ደጋ፣ ገጠር-ከተማ፣ ሳይል "ጢስ በጢሰ" በሚለው መርህ ላይ የተመሰረተ ነው። ትውፊቱን የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> ለምሳሌ አሁን እዚህ ቁጥር 14 ቀበሌ ውስጥ ሊብሶ እሚባል ቦታ አለ፤ አንድም ክርስቲያን የሌለበት። የቆሎ ተማሪዎች ግን "ስለ እመ-ብርሃን!" ብለው ምግባቸውን እዚያ ሰብስበው ይመጣሉ። ወረ-ካሎም እንደዚያው። በዚህ በከተማውም ውስጥ አሁን የቆሎ ተማሪ መጥቶ የእስላሙን ቤት አያልፍም። እንደገና ደሞ ደረሶች መጥተው ይኸን የክርስቲያኑን ቤት

> አልፈው አይሂዱም፡፡ ከሁሉም ቤት ይጠይቃሉ፤ ከሁሉም ቤት ይሰጣሉ፡፡ ይኸ የእስላም-ክርስቲያን ለዩነት የለውም፡፡[153]

በዚህ ጥቅስ መሰረት በወሎ አንድ የቆሎ ተማሪ ከአንድ ሼህ ቤት በር ላይ ቆሞ "ስለ እመ-ቤቴ ስሚ ለማርያም፤ ስለ እመ-ብርሃን!" የሚለውን ስም ጠርቶ የእለት እንጀራውን ይጠይቃል፡፡ በዚህ ጊዜ "እነ እመት ፋጡማ" "እንዳይነካካ" ተጠንቅቀው ቤት ያፈራውን ይዘክሩታል፡፡ እሱም "እመ ብርሃን ትስጥልኝ!" በሚለው የምርቃት ትውፊት ምሥጋና ያቀርባል፡፡ "አሜን!" የእነ እመት ፋጡማ መልስ ይሆንና ይሰነባበታሉ፡፡

በተመሳሳይ አንድ ደረሳ በወሎ ከቄስ ቤት በር ላይ ቆሞ "አሰላም ወ አሊኩም!" በማለት ምግቡን ይጠይቃል፡፡ እናም እነ እመት "የቄስ ሚሰት" እንደተለመደው "እንዳይነካካ" እጅግ ተጠንቅቀው ማጀት ያፈራውን ለዚያ ሽርጥ ላገለደመ፣ የጡሃራ እቃ ጡሌ ላንጠለጠለና እስከ ግንባሩ ጉፍታ ለጠመጠመ ደረሳ እራቱን የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡ የዚህ አይነቱን ትውፊት እንድሪስ አህመድ የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው፡፡

> አሁን ምናልባት ሥጋ ነባር እቤት ውስጥ ተዘጋጅቶ ከሆነ "ኧረ-ተማሪ ተነካክቷል!" ብሎ ይመልሳል እንጂ፤ እህል በእህል ከሆነ፣ ወይ በበርብሬ ድቁስ ከሆነ ይሰጣል፡፡ እንጀራ ብቻ ከሆነ፣ ወይ ዳቦ ከሆነ፣ ወይ ቂጣ ከሆነ፣ ይሰጣል፤ ሙስሊሙ ለክርስቲያኑ ተማሪ ማለት ነው፡፡ ክርስቲያኑ ደሞ ለሙስሊሙ ደረሳ ምናልባት ከተነካካ "አየ! ቤታችን ዛሬ እንደው ለእናንተ አይሆንም!" ብሎ ይመልሳል እንጂ፤ ሙስሊም ስለሆነ የለም ብሎ አይመለስም፡፡ ሁለቱም ቢሆን በጋራ ነው እንጂ፤ የክርስቲያን ተማሪ፤ የሙስሊም ተማሪ ተብሎ አይለይም፡፡ ባህሉ አይፈቅድም፡፡[154]

በአካባቢው ትውፊት መሰረት ለተማሪ መስጠት ብቻ ሳይሆን፤ ትህትናና አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ተማሪ መስተናገድ አለበት፡፡ ለዚህም ደጅ ሳይጠና በፍጥነት አስተናግዶ መሸኘት አንዱ የክብሩ መገለጫ አካል ነው፡፡ ትውፊቱ የሚጠይቀው ሥነ-ምግባር ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ክርስቲያን አባወራ ደረሳም ይሁን የቆሎ ተማሪ ምላሽ ሳያገኝ ከደጃቸው ቆሞ ቢያዩ "ተዘከሩ እንጂ! ተማሪ ቆሟል እኮ!" በማለት ለቤቶቻቸው ቁጣ አዘል ትእዛዝ ያስተላልፋሉ፡፡ በተመሳሳይ ሙስሊም አባወራም ለቤቶቹ "ነይቱላቸው እንጂ!" በማለት ቁመው ደጅ መጥናት እንደሌለባቸው ይገልጻሉ፡፡

የዚህ ሁሉ መሰረቱ ደግሞ የትውፊቶቹ ተራክቦ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ከቀረቡት ነጥቦች መረዳት እንደሚቻለው የክርሰትናውም ሆነ የእስልምናው ትውፊት አኗኗሩ ጎራ ለይቶ ሳይሆን አንዱ ከሌላው ጋር በመቀናጀት ነው፡፡ ተጎራብቶ ነው፡፡ ለምሳሌ ከትውፊቶቹ አንፃር በሁለቱ

---

[153] በሪሁን ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ፡፡
[154] እንድሪስ አህመድ፤ ቃለመጠይቅ፤ ሐምሌ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 03 ቀበሌ፡፡

ተማሪዎች መካከል ያለው ልዩነት እንዱ የክርስትና ሌላው የእስልምና ተማሪዎች በመሆናቸው፣ በአለባበሳቸውና በሚይዟቸው አንዳንድ ቁሳቁሶች ብቻ ነው። በዚህም የቁሱ ተማሪ በጎኑ ዳዊት ሊይዝ ይችላል። የመድረሳው ደግሞ ጡሌ ሊያንጠለጥል ይችላል። ነገር ግን የአካባቢው ነዋሪዎች ለሁለቱም ተማሪዎች ያላቸው አመለካከት፣ ደንብና ሥርአት ተመሳሳይ ነው። ባህሉ፣ ወግና ልማዱ አንድ ነው። በዚህም ክርስቲያኑ፤ ለክርስቲያኑ ተማሪ አያዳላም፤ መስሊመም ለመስሊመ ተማሪ አያዳላም። ከተማሪው አንፃርም ከርስቲያኑ የመስሊሙን ቤት የመስሊም ቤት ነው፤ ብሎ አያልፍም። መስሊመም የክርስቲያኑን ቤት የክርስቲያን ነው፤ ብሎ አይተውም።

በወሎ፤ ወሎዬዎች የሚገዙበት አንድ ፎክሎራዊ ሕግ፣ ደንብና ሥርአት አለ። ይኸውም "እንዳይነካካ!" ወይም "ተነካክቷል!" የሚለው ብሂል ነው። ብሂሉ በወሎዬዎች ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ሁሉ አለ። እንዳይነካካ በሠርግ አለ። እንዳይነካካ በዝክር አለ። እንዳይነካካ በሰደቃ አለ። እንዳይነካካ በልቅሶ አለ። እንዳይነካካ በተማሪዎቹም ትውፊት ውስጥ አለ። አንድ ተማሪ ከክርስቲያኑም ይሁን ከመስሊመ ቤት "ዛሬ ስለተነካካ በሌላ ጊዜ ተመለስ ተሚ!" ተብሎ ሲነገረው የንፍገት ሳይሆን፤ የነፍስ መሆኑን ከልብ አምኖ ይቀበላል። በተሰጠው ጊዜም "ተነካክቶ ይሆን!?" ብሎ አይጠራጠርም። ምክንያቱም ባህሉ፣ ወግና ልማዱ፤ ደንብና ሥርአቱ ይህን እንደማይፈቅድ ጠንቅቆ ያውቃልና። ከእሱ በፊት በርካታ አራት ዓይናዎች ወይም ሊቃውንት በዚህ ትውፊት ማለፋቸውን ሰምቷል፤ ተረድቷልና። እነዚያን ሊቃውንት ያፈራቸው ቀየ አሁን እሱ የቆመበት ቀየ ስለመሆኑ ልቡ አይጠራጠርምና።

በዚህ ትውፊት የሁለቱ ተማሪዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት ሊጠቀስ ይችላል። በመሆኑም የሁለቱ ተማሪዎች ግንኙነት ወንድማዊ ነው። በመከባበርና በመተሳሰብ መርህ ላይ የተመሰረተ ነው። ለምሳሌ ሁለቱም ምግባቸውን ለመጠየቅ ባጋጣሚ ከአንድ አባወራ በር ላይ እኩል ቢደርሱ "አንተ ቅደም! አንተ ቅደም!" በመባባል ረጅም ጊዜ ሊፈጁ ይችላሉ። አንዱ "ወላሂ አንተ ቅደም!" ሲል፤ ሌላው በበኩሉ "ኧረ ባዛኒቱ አንተ ቅደም!" ይላል። በመጨረሻ ግን አንዱ ተሸንፎ ይቀድማል። እሱ ሲመለስ ያኛው ይከተላል። በሌላ በኩል በመንገድ ላይ አብረው የሚሄዱበት አጋጣሚ ሲፈጠር ደግሞ አንዱ ከሌላው ትምህርት ይቀስማል። በዚህ ሂደት አንዱ ለሌላው ሃዘኑንም ሆነ ደስታውን የሚያካፍለው የልብ ባለንጀራው እስከመሆን ይደርሳል። በዚህ መልክ የተጀመረው ጓደኝነትም ከጉልምስና እስከ እርጅና ሊዘልቅ ይችላል።

ጓደኝነት በወሎ እስከምን ድረስ እንደሆነ ከልክላቸው አለ በሌላ ምሳሌ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

> ከሌላ የወሎ አካባቢ ለሥራ ጉዳይ ካቤ መጥተው የሚኖሩ ክርስቲያንና ሙስሊም ሴት መምህራን ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁለት ሴት መምህራን የሚኖሩት በአንድ ቤተ ውስጥ ነበር፡፡ በአኗኗራቸው ማንንም አጅግ የሚያስቀና ፍቅር ነበራቸው፡፡ የሚለያዩበት ነገር ቢኖር ሥጋ ብቻ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ሁለቱም ለየብቻ የሚመገቡትን የሥጋ ቋንጣ በአንድ ገመድ ላይ ይሰቅላሉ፡፡ ቋንጣቸው በየት በኩል እንደተሰቀለ ለመለየት ግን በገመዱ መካከል ለምልክት ጨርቅ ያስሩበታል፡፡ (Kalklachew 1997: 200-2)::

ከዚህ በላይ በቀረቡት የተለያዩ አብነቶች መሰረት በወሎ ክርስቲያኖቹ በእስልምናው በኩል የሚገኙ ትውፊቶችን ይጋራሉ፡፡ በተመሳሳይ ሙስሊሞቹም በክርስትናው በኩል የሚገኙ ትውፊቶችን ተጋሪዎች ናቸው፡፡ ሁለቱም ትውፊቶቹን መጋራታቸው ብቻ ሳይሆን፤ አንዱ ለሌላው የእኔነት (የባለቤትነት) ስሜትና አመለካከት አላቸው፡፡ የዚህ አይነቱ ስሜትና አመለካከት ደግሞ የወሎዬዎች ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ ውጤት ነው፡፡

በዚህ አውድ መሰረት የእስልምናውም ሆነ የክርስትናው ትውፊቶች ወሎዬዎች እርስበርስ የሚገናኙባቸው መድረኮችና የሚተሳሰሩባቸው ክሮች ናቸው፡፡ ወሎዬዎች የሚከባበሩባቸውና የሚተማመኑባቸው የሥነ-ምግባር መርሆዎች ናቸው፡፡ የሚረዳዱባቸውና የሚደጋገፉባቸው መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ወሎዬዎች በሠላምና በፍቅር አብረው እንዲኖሩ የሚያስችሏቸው ደንብና ሥርአቶቻቸው...ወዘተ ናቸው፡፡ ባጠቃላይ ወሎዬዎች በሃይማኖት ሳይለያዩ፤ ባንፃሩ በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያደርጉ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ተመሳሌቶች ናቸው፡፡

ይሄ ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው "የተፈቀዱ" ትውፊቶች እንዳሉ ሁሉ፤ "ያልተፈቀዱ" የሚባሉ ተውፊቶችም አሉ፡፡ የተፈቀዱት የቅዱስ ተግባር ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ ያልተፈቀዱት ደግሞ "እርኩስ" ተግባርን ይወክላሉ፡፡ ነገር ግን የሃይማኖቶቹ ትውፊቶችም ሆኑ የእምነቶቹ ተከታዮች ሁለቱንም ተግባራት በተለያዩ መንገዶች ይጋሯቸዋል፡፡ ያስተናግዷቸዋል፡፡ በዚህ መሰረት ትውፊቶቹ የወሎዬዎች የጋራ እሴቶች ናቸው፡፡

ለምሣሌ ከዚህ በላይ ለአብነት የቀረቡት ትውፊቶች በሃይማኖቶቹም ሆነ በእምነቶቹ ተከታዮች "የተፈቀዱ" ተብለው የሚታመንባቸው ተውፊቶች ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ምሳሌዎች ደግሞ "የተከለከሉ" ተብለው የሚታመንባቸው ትውፊቶች ናቸው፡፡ ትውፊቶቹ

የተፈቀዱ እንደሚባሉት ትውፊቶች ሁሉ፤ የራሳቸው የሆኑ መገለጫዎችና ማኅበራዊ ፋይዳዎች አሏቸው፡፡ የተፈጠሩትና የሚኖሩትም በወሎዬዎች ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ ውስጥ ነው፡፡ አገልግሎታቸው ደግሞ ለፈጠራቸውና በዚሁ አውድ ውስጥ ለሚኖሩት የማኅበረሰብ ክፍሎች ነው፡፡ በዚህ መሰረት የወሎዬዎች ሃጃ የተፈቀዱ በሚባሉት ትውፊቶችና የትውፊቶቹ አስፈፃሚ አካላት ተራዳዒነት እንደሚሞላ ሁሉ፤ ባንፃሩ ወሎዬዎች ከነዚህ አካላት ተቃራኒ ጎራ በቆሙ ትውፊቶችና የትውፊቶቹ አስፈፃሚ ወገኖች ሃጃቸው ይሞላል፡፡ ለዚህም ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የተለያዩ ትውፊቶችም አሏቸው፡፡ በነዚህ ትውፊቶቻቸው መሰረት፤ ኮከብ ቆጥረው- ጠጠር ጥለው፣ መጠሐፍ ገልጠው- መዳፍ አንብበው፣ ሥኒ ዘቅዝቀው፣ ሞራ ዘርግተው፣ ጋኒን ስበው- ጥቁር ዶሮ አርደው፣ ቆሎ በትነው- ደንቃራ ጥለው...ወዘተ ሃጃቸውን የሚሞሉሏቸው አካላት አሏቸው፡፡

እነዚህ አካላት በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው በኩል የሚገኙ ወገኖች ናቸው፡፡ ከነዚህ ወገኖች መካከል ባለዛር፣ ጠንቋይ፣ አስማተኛ፣ መተተኛ፣ ቃልቻና ደብተራ ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡ በሁለቱም ጎራ የተጠቀሱት እነዚህ ትውፊቶች የወሎዬዎች የጋራ እሴቶች ናቸው፡፡ ወሎዬዎች እሴቶቹን በጋራ ይተገብሯቸዋል፤ በጋራ ይገለገሉባቸዋል፡፡ በዚህም ወሎዬዎች በነዚህ እሴቶች አማካይነት እርስ በርስ ይገናኛሉ፤ ይተሳሰራሉ፡፡ እርቅ ያወርዳሉ፤ ሠላም ይፈጥራሉ፡፡ የልጆቻቸውን፣ የቤተሰቦቻቸውን፣ የጎረቤቶቻቸውንና የአካባቢያቸውን ደህንነት በነዚህ እሴቶች አማካይነት ይጠብቃሉ፡፡

በሌላ በኩል ወሎዬዎች በነዚህ እሴቶች አማካይነት አንዱን ጤንኛ ሌላውን የአልጋ ቁራኛ የደርጋሉ፡፡ አንዱን ያደኸያሉ፣ ሌላውን ሃብታም ያደርጋሉ፡፡ አንዱን ሽባ ያደርጋሉ፣ ሌላውን ጠንካራና ኃይለኛ ያደርጋሉ፡፡ የአንዱን አንደበት ይዘጋሉ፣ የሌላውን የተባና የሰላ ያደርጋሉ፡፡ የአንዱን ሲሳይ ያስወጣሉ፣ ለሌላው ርዚቅ ያስገባሉ፡፡ የአንዷን ማሕፀን ይዘጋሉ፣ የሌላዋን ይከፍታሉ፡፡ አንዱን ስኬታማ ያደርጋሉ፣ ሌላውን በዋል-ፈሰስ ሆኖ እንዲቀር ያደርጋሉ... ወዘተ፡፡

ይህንን ለማድረግ ደግሞ ቀደም ሲል መልካም በሚባል ገፅታው እንዳየነው ሁሉ፤ ክርሰቲያኑ ወደ ሙስሊሙ ይሄዳል፡፡ በተመሳሳይ ሙስሊሙም ወደ ክርስቲያኑ ይመጣል፡፡ በዚህ መሰረት ወሎዬዎች "አዎንታዊ" በሚባሉትም ሆነ "አሉታዊ" ገጽታ ባላቸው ትውፊቶች አማካይነት እርስ በርስ የተሳሰሩ ናቸው፡፡ የሃይማኖቶቹ ትውፊቶችም አንዱ ከሌላው ጋር የተጋቡ፣ የተዋሃዱ፣ የተቀላቀሉና የተዛመዱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በወሎ የሃይማኖት ትውፊቶች ተራክቦ

ሥረ-መሰረት ያለው የወሎዬዎች የጋራ እሴት ነው። ይህንን አባባል ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት አብነቶች ማረጋገጥ ይቻላል።

5.4.2:- ጠንቋይና ጥንቆላ በወሎ

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወሎ በክርስትናውም ሆነ በአስልምናው ባላቸው ስጦታና ብቃት ፈጣሪን ጠይቀው የወሎዬዎችን ሃጃ የሚሞሉ አካላት አሉ። በአንፃሩ ደግሞ በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ጠንቋዮች፣ አስማተኞች፣ መተተኞች፣ ባለዛሮች፣ ቃልቾችና ደብተሮች አሉ። ወሎዬዎች የሚፈልጉት ነገር እንዲሳካላቸው ወደመጀመሪያዎቹ አካላት እንደሚሄዱ ሁሉ፤ በተቃራኒው ወደ ሁለተኛዎቹ አካላት የሚሄዱ ወሎዬዎችም አሉ። ከነዚህ አካላት መካከል ጠንቋይና አስጠንቋይ ለአብነት ይጠቀሳሉ።

አበጋር ማዱ በላይ እንደሚያብራሩት ጠንቋይ ማለት መጠሐፍ በመግለጥ፣ ጠጠር በመወርወር፣ ሥኒ ዘቅዝቆ በማንበብ፣ ጋኒን በመሳብ፣ መጋረጃ ጋርዶ እጣን በማጤስ (ይታየኛል!) የሚል አካል ነው። አውቅልሃለሁ የሚል ክፍል ነው። ወደዚህ ጠንቋይ የሚሄዱት የማጎበረሰብ ክፍሎችም ሃብት ለማግኘት፣ ከህመም ለመፈወስ፣ እጣፈንታን ለማወቅ፣ ሳይሰሩ ለመክበር፣ ጠላትን ወይም ተቃዋሚን ለማጥፋት፣ የተደበቀ ምስጢርን ለማወቅ... ወዘተ የሚፈልጉ አካላት ናቸው።[155] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ የዚህ አይነቱን ድርጊት የሚገልፁት "ደብተሮቹ ሰውን የሚያፈዝ ብዙ ድግምት ያውቃሉ። በእስልምናው በኩል ደሞ ጠንቋይ እሚባል አለ። የሰይጣን አምልኮ ነው። ሰውን ይጎዳል። ሰውን ሽባ ያደርጋል። ሰውን ሞኝ ያደርጋል። ሰውን ያደኸያል። የእስላሞች ተንኮለኞች ጠንቋዮች አሉ፤ በክርስቲያኑም እንደዚህ ያሉ ተንኮለኞች አሉ"[156] በማለት ነው።

በመረጃ አቀባዩ ማብራሪያ መሰረት ጥንቆላ ከደብተራና ከቃልቻ ተግባር ጋር የተሳሰረ ነው። ቃልቻና ደብተራ ይህንን ተግባር የሚያከናውኑት፤ ደብተራው ክርስትናውን፤ ቃልቻው እስልምናውን መነሻ በማድረግ ነው። ሁለቱም መነሻቸው ሃይማኖቶቹ ይሁኑ እንጂ፤ ግንኙነታቸው ግን ከሰይጣን (ጂኒ) ሥራ ጋር ነው። ለዚህ አባባል አበጋር ማዱ በላይ የሚያቀርቡት ምክንያት "ጀኒ አበጋሮቹ ጋር አይስማማም። ቃልቾቹና ደብተሮች ጋር ግን ይስማማል። ለምን? እነሱ ምሱን ይሰጡታል። እነሱ መቋደሻውን ይይዙለታል!" የሚል ነው።

---

[155] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ-ገዶ።
[156] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 01 ቀበሌ።

በሌላ በኩል አበጋር ማዱ ጂኒ ከአበጋሩ ጋር ለምን እንደማይስማማ የሚከተለውን ምክንያት ያቀርባሉ፡፡

> ጂኒ አበጋሩ ጋር የገባው ውለታ አለ፡፡ ይኸውም አበጋሩ ልቀቅ ሲለው ሲለቅ፣ ተው ሲለው ሊተው ነው፡፡ ከዚያ ውጭ እብድ ሁነህ እንድትሄድ፣ እንድትደኸይ፣ በዋል-ፈሰስ ሁነህ እንድትቀር ለማድረግ አበጋሩ ጋኒን አይስብም፡፡ በፈጣሪም ደሞ ነገ ስትሞት ትጠየቃለህ፡፡ በሰማይ ትጠየቃላችሁ ብሏል መጠሐፉ፡፡ በክርስትያኑም ይኸ አለ፡፡ በዚህም አበጋሩ ይፈራል፡፡ ቃልቻውና ደብተራው ግን የእለቱን እንጂ መጪውን አያስቡም፡፡[157]

በዚህ መሰረት በወሎ ክርስቲያኑ ወደ ቃልቻው፤ ሙስሊሙ ወደ ደብተራው ይሄዳል፡፡ ትውፊቱ ለወሎየዎች በዓላማው ይለያያል እንጂ፤ በግብሩ ግን ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ወደ ፀበል ቦታዎችና ወደ ወልዮቹ የመሄድ ያህል ነው፡፡ ለምሳሌ አንዲት ወሎዬ ክርስቲያን ወይም ሙስሊም እናት እንደ እጣ ክፍሏ ወይም የአካባቢዋ ጠንቋይ እንደነገራት ልጇን ቡዳ እንዳይበላባት በቃልቻ ወይም በደብተራ የተደገመ የቡዳ መድኃኒት ከልጇ አንገት ላይ ልታስር ትችላለች፡፡ ወይም እራሷ አለያም ላሚ "የሾተላይ" ካስቸገራቸው በደብተራ ወይም በቃልቻ የተጠለሰመ ጠልስም ወይም ኪታብ ልታስር ወይም ልታሳስር ትችላለች፡፡

በተመሳሳይ ጠላቱን በአንደርቢ መግቢያ መውጪያ አሳጥቶ በመጨረሻ ቤቱን እንዲያቃ ጥልለት የተመኘ የወሎ ሙስሊም ደብተራውን ጋኔን ስበህ "እጄን ሁነኝ!" ሊለው ይችላል፡፡ ሳይሰራ መከበር የተመኘ የወሎ ክርስቲያንም ቃልቻውን ደጅ ከመጥናት የተሻለ አማራጭ አይኖረውም፡፡ እጣ ክፍላቸው የሚወስነው ደግሞ በክርሰቲያን ወይም በሙስሊም ጠንቋዮች አማካይነት ነው፡፡ ስለዚህ ትውፊቱ ግብሩ የተለያየ ቢሆንም አንዱ ከሌላው ጋር ጡት የተጣባ ነው፡፡ይኸኛው የክርስቲያኑ፤ ያኛው የሙስሊሙ ተብሎ የሚፈረጅበት መስፈርቱ ከመርፌ ቀዳዳ የጠበበ ነው፡፡

በዚህ መሰረት ወሎዬዎች የሚገናኙትና እርስ በርስ የሚተሳሰሩት በተፈቀዱት ትውፊቶች ብቻ ሳይሆን የተከለከሉ ተብለው በሚታሰቡት ትውፊቶችም ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም በተፈቀዱት ትውፊቶች ወሎዬዎች ፍላጎታችንን ለማሳካት እጣ ክፍላችን ናቸው ወይም ተሰጠውና ብቃቱ አላቸው ብለው ወደሚገምቷቸው ትውፊቶች፤ "ይሄኛው የክርስቲያኑ ነው፤ ያኛው የሙስሊሙ ነው፤" ሳይሉ ልባቸው ወደፈቀደው ይሄዳሉ፡፡ ወይም እነሱ እንዲመጡ ያደርጋሉ፡፡ ትውፊቱ የተከለከሉ በሚባሉትም በመጠን ካልሆነ በስተቀር ሂደቱ ተመሳሳይ ነው፡፡

---

[157] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ. ም. ጉባላፍቶ-ገዶ፡፡

በዚህ መሰረት በወሎ ሃይማኖቶቹም ሆኑ የእምነቶቹ ተከታዮች የሚጋሯቸው ትውፊቶች አንድ፣ ሁለት ተብለው የሚቆጠሩ አይደሉም፡፡ በአይነትም፤ በመጠንም፣ በግብርም በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ጠንቋይና አስጠቂይ ከክርስትናውም ሆነ ከእስልምናው፤ እንዲሁም ከእምነቶቹ ተከታዮች ጋር በተለያዩ መንገዶች እንደሚገናኙ ሁሉ፤ ዛርና ባለዛርም ተመሳሳይ ባህርይ አላቸው፡፡

5.4.3፡- ዛርና ባለዛር በወሎ

ይሄ ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች የዛር አፈ-ታሪክ እንዲህ ይላል፡፡

> ሄዋን ሰላሳ ልጆች ነበሯት፡፡ ከእለታት አንድ ቀን እግዚአብሄር ሄዋንን[158] "ልጆችሽን አሳይኝ" ብሎ ጠየቃት፡፡ በእለቱ ሄዋን፤ ጥያቄ ያቀረበላት እግዚአብሄር መሆኑን አታውቅም ነበር "ለምን ይሆን የጠየቀኝ?" በማለት እግዚአብሄርን ተጠራጠረች፡፡ በመጠራጠሯ ምክንያትም እጅግ ውብ የሆኑትን ልጆቿን ደብቃ አስቀያሚ መልክ ያላቸውን ብቻ አሳየችው፡፡ እግዚአብሄርም በመለኮታዊ ኃይሉ የሄዋንን ድርጊት ያውቅ ነበርና "ሄዋን! ከእኔ የደበቅሻቸው ልጆችሽ ዘላለም ከሰው ልጆች ሁሉ ተሰውረው የሚኖሩ መንፈሶች ይሁኑ፡፡ እሚኖሩበት ቤት፣ የሚገለገሉበት ንብረት ለዘላለም አይኑራቸው፡፡ እንዲሁ በዓለም ላይ ሁሉ እንደተንከራተቱ ይኑሩ!" በማለት ረገማቸው፡፡ በዚህም እነዚያ የተረገሙት የሄዋን ልጆች የሚኖሩበት ቤት፣ የሚመገቡት ምግብ ስለሌላቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች በሰዎች ውስጥ በማደር የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ ሰዎች እንዲያሟሉላቸው ያስገድዳሉ፡፡[159]

ዛር በወሎ አይነቱ ብዙ ነው፡፡ መጠሪያ ስያሜውም በርካታ ነው፡፡ ዛር በወሎ አውካል፣ የላይትላይ፣ አውሊያ፣ ከራማና ውቃቢ የሚባሉ መጠሪያ ስያሜዎች አሉት፡፡ ጨንገር፣ አንበሶ፣ ራሄሎ፣ ጥቁረ-በላ፣ ነፌ-በላ... ወዘተ ደግሞ የዛር አይነቶች ናቸው፡፡ የመርሣ አባገትየ ግቢ ኃላፊ የሆኑት ሼህ ዑመር እሸቱ እንደሚገልጹት አውሊያ፣ ውቃቢና ከራማ የተለያዩ ነገሮች ሳይሆኑ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ነገር ግን ከዛር ይለያሉ፡፡ አወሊያ ያለባቸው ሰዎች ባለውቃቢ ይባላሉ፡፡ ወይም ባለ ከራማ ይባላሉ፡፡ አውሊያ ወይም ከራማ ጠባቂ ወይም ጥሩ መንፈስ ማለት ነው፡፡[160] ለምሳሌ እነ አባገትየ በአፀደ-ሥጋ ባይኖሩም እንኳን፤ አሁንም ድረስ እሳቸው ለዱዓ በመሰረቱት በመርሣ አባገትዬ ላይ ከራማቸው አለ ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህም በአባገትየ ከራማ ተራዳዒነት መልካም ነገር ለማግኘት የተለያዩ ሰዎች መርሣ አባገትዬን ይዘይራሉ፤ ይጎበኛሉ፡፡

---

[158] ቱሬ ፉለር 1970፤ ገጽ 53 ላይ ሄዋንን ልጆቿን እንድታሳያት የጠየቀቻት ማርያም እንደሆነች ይገልጻል፡፡ አፈ-ታሪኩ ግን በዚህ ጥቅስ ውስጥ ከተገለፀው አፈ-ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ እርግማኑም እንዲህ ይላል፡ "Let all the children who are hidden by you be sprits, unseen by human beings, to wander throughout the world without home or property. (E.Fuller Torrey 1970: 53).

[159] ሃምሳ አለቃ መኮንን የሺጥላ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም. ወልዲያ- 02 ቀበሌ፡፡

[160] ሌዊስ ኸርበርት ውቃቢን እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል፡ "...such a guardian spirit may protect an individual or a family,lineage a community (Herbert S. Lewis 1984: 419-427).

በሼህ ዑመር ገለፃ መሰረት አንድ ሰው አወሊያው አልስተካከል ብሎ ቢያስቸግረው የሚሄደው ወደባለዛር ሳይሆን ዱዓ ወደሚደረግባቸው ቦታዎች ነው። በመሆኑም "አውሊያ ያለባቸው ሰዎች እዚህ መጥተው ዱዓ ካስደረጉ በኋላ አወሊያቸው ይስተካከላል።" በማለት አውሊያ ያለባቸው ሰዎች መርሣ አባገትየን እንደሚዘይሩ ሼህ ዑመር ይገልፃሉ።[161]

በወሎ አወሊያ ወይም ከራማ አላቸው ተብሎ የሚታመንባቸው ሰዎች አብዛኛዎቹ ወንዶች ናቸው። ነገር ግን ቁጥራቸው የወንዶቹን ያህል አይብዛ እንጂ፤ አውሊያ ወይም በረካ ያላቸው ሴቶች በወሎ ይገኛሉ። ለምሳሌ የሳንቃዋ እመቤት ለአብነት የሚጠቀሱ በረካ ያላቸው እንስት ናቸው። ከዚህም ሌላ የአርሲዋ አመቤት (አዩ ሞሚና) ሥረ- መሰረታቸው ወሎ-የጁ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች ይገልፃሉ[162]

በሌላ በኩል ዛር የሚሰፍረው በአብዛኛው በሴቶች ላይ ነው። አልፎ አልፎ ግን ዛር በወንዶች ላይም ይሰፍራል። ዛር የሰፈረባቸው ወንዶችም ሆኑ ሴቶች "ባለዛር" በመባል ይጠራሉ። የዛር ማንነት ወይም የዛር አይነት ተለይቶ የሚታወቀው በጉሪ ነው። በመሆኑም በዛር ብሂል አጉሪና አስጎሪ አለ። አጉሪ ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ሁሉም ሴቶች ናቸው። አስጎሪ ደግሞ ወንድ ነው። አጉሪዎቹ ባለዛር ወይም የዛር ፈረስ የሚል መጠሪያ አላቸው። የላይት ላይ ያለባቸው ሰዎችም ይባላሉ። አስጎሪዎቹ ደግሞ የዛር አባት ይባላሉ። አስጎሪ ሁልጊዜ ከመጋረጃ ጀርባ ነው። ወይም በመጋረጃ የተከለለ ነው። አጉሪ ግን ከመጋረጃ ውጪ ነው።

በዚህ መሰረት የዛር አባት ከመጋረጃ ጀርባ ሆኖ የተለያዩ ነገሮችን በድምፅና በድርጊት እየከወነ ከመጋረጃው ውጪ ያሉ ሴቶች እንዲያጎሩ ያደርጋል። ከዚያም የዛሩን ማንነት ጠይቆ ይረዳል። ዛሩ የሚፈልገው ነገር ምን እንደሆነ ይጠይቃል። ፍላጎቱን ከተረዳ በኋላም የጠየቀው ነገር "በፈረሱ" በኩል እንደሚፈፀምለት ማረጋገጫ ይሰጣል። ባንዳሩ "በፈረሱ" ወይም በሴትዮዋ፣ በልጆቿ፣ በባሏ፣ በሀብትና ንብረቷ ላይ ዛር የሚፈጽመውን መጥፎ ድርጊት ማቆም እንዳለበት ቃል ያስገባል።

በዛር ተግባር መሰረት የዚህ አይነቱ የሰጥቶ መቀበል መርህ ተግባራዊ የሚሆነው ዛር የጠየቀው ቅድመ ሁኔታ "በፈረሱ" አማካይነት እስከተፈፀመለት ጊዜ ብቻ ነው። ዛር የሚጠይቀው ቅድመ ሁኔታ ደግሞ፤ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ መንፈቃዊና አመታዊ የተሰጉትን የዛር ፍላጎት

---

[161] ሼህ ዑመር እሸቱ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 02 ቀበሌ።

[162] ግራዝማች ብሩ ይማም፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 15 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ።

መሰረት አድርጎ ነው። በነዚህ ጊዜያት ከኮርማ እስከ ዶሮ፣ ከቆሎ እስከ ሽልም ዳቦ፣ ከቡና እስከ ካቲካላ፣...ወዘተ ዛር "በፈረሱ" አንድም ሳይቀር ግብር እንዲቀረብለት ይጠይቃ።

እንዲሁም በእጅ ተፈትሎ ከተሠራ ነጠላ እስከ በጥልፍና በጥበብ እስከተንቆጠቆጠ ቀሚስ፤ በእሱ ምርጫ ከተገዛ ጉፍታ እስከ ማንም ሰው የማይጠቀምበት ምንጣፍና መኝታ እንዲሚላለት ዛር" ፈረሱን" ያስገድዳል። የከበረ ጌጣጌጥ እንድታደርግ፣ መልካም መዓዛ ያለው ሽቶ እንድትቀባ ዛር "ፈረሱን" ያዛል። ከዚህ ውስጥ አንዱ ሳይፈፀም ቢቀር ግን በአለቃው በኩል የገባውን ስምምነት ዛር ያፈርሳል። በዚህም ሳይውል ሳያድር ዛር "በፈረሱ" ላይ ጦርነት ይከፍታል።

ከዚህ በኋላ ድርጊቱ ለዛር አባት እንደገና ይነገራል። የዛር አባትም በሰውና በንብረት ላይ ዛር ብዙ ጥፋት ሳያደርስ መፍትሄ ይፈልጋል። የዛር አባት እንደ ልማዱ "ፈረሷን" አስጎርቶ፣ ዛር አስነስቶ፣ ስምምነቱ ለምን እንደፈረሰ ዛርን ይጠይቃል። "ጅራፍ እራሱ ገርፎ..." እንዲሉ፤ ዛርም "በፈረሱ" የተፈፀመበትን በደል ይዘረዝራል። ከዚያም የዛር አባት፤ ዛር እንዲካስ "በዛር ፈረስ" ላይ ይፈርዳል።

በዚህም እንደገና ሠላም ይወርዳል። የወረደው ሠላም ግን ዘላቂ አይሆንም። አፍታም ሳይቆይ ተመልሶ ይደፈርሳል። አሁንም ጉዳዩ ለዛር አባት እንደገና ይቀርባል። የዛር አባት አሁንም ተመሳሳይ ፍርድ ይፈርዳል። በመሆኑም የዛር፣ የባለዘርና የዛር አባት ቁርኝት በወሎ አንድ የማኅበራዊና ባህላዊ እሴት አካል ሆኖ ይኖራል። እሴቱም የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ መገለጫ ትውፊት ነው። ትውፊቱን አንዳንዶቹ "ለበጎ ነገር" ነው፤ ሲሉት አንዳንዶቹ ደግሞ "ለኩነኔ" ነው፤ ይሉታል።

ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ ባለዛርን የሚገልጹት "ባለዛር እሚባል አለ። ሴቶችን ሰብስቦ፣ ለሃይማኖት ደንታ የሌላቸውን ሰብስቦ የሚያስጨበጭብ፤ የሚያስጎራ። ይሽ ሰውን የሚጎዳ ባህል ነው። ከሃይማኖት ውጪ ነው!" በማለት ውጉዝ መሆኑን አፅንኦት በመስጠት ነው።[163] ሞላልኝ ወርቁ ግን በሼህ አሰን ሃሳብ አይስማሙም። ምክንያቱም ባለዛር ባይኖር ኖሮ፤ ዛር የሰፈረባት ሴት የተረጋጋ ማኅበራዊ ሕይወት አይኖራትም ነበር፤ የሚል መከራከሪያ ሃሳብ ያቀርባሉ። ባንፃሩ የባለዛር ተግባር "የኩነኔ" ሳይሆን፤ "የፅድቅ" መሆኑን የሚገልፁት የሚከተሉትን የዛር አባት ተግባራት ለአብነት በመዘርዘር ነው።

---

[163] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሣ- 01 ቀበሌ።

> የዛር አባት አንዲት ሴት የሰፈረባት ዛር ተረጋግቶ እሷ ሕይወቷን በሰከነ ሁኔታ እንድትመራ የሚያደርግ ሰው ነው፤ ዛሩ አሳብዶ፣ ጨርቋን አስወልቆ ገደል እንዳይከታት የሚያደርግ ነው፡፡ ልጆቿን እንዳያምባት፣ ልጆቿን እንደይገድልባት፣ ከብቶቿን-ንብረቶቿን እንዳይጨርስባት፣ መቅኖ እንዳያሳጣት ያደርጋል የዛር አባት፡፡ ስለዚህ ዛሩ እንዲሰክን የሚለማመነው እሱ ነው፡፡ ጊዜውን፣ ቀኑን፣ ወሩን፣ አመቱን፣ ጠብቃ ምሱን እንድታደርግ ለት መመሪያውን እሚሰጠው እሱ ነው፡፡ ስለዚህ የሱም ስራ ሌሎቹ እንደሚያደርጉት ክፉ ነገር እንዲርቅ፤ በጎ ነገር እንዲመጣ ወይም መልካም ነገር እንዲገኝ፣ እንዲቀርብ፣ የሚያደርግ ነው፤ የዛር አባት፡፡[164]

መረጃ አቀባዩ በጥቅሱ ውስጥ ያነሷቸውን ነጥቦች በአምንታዊ ጎናቸው ይጠቀሱ እንጂ፤ የደብተራና የቃልቻ ተግባር ግን ከመተትና ከጥንቆላ ጋር የተያያዘ ስለሆነ አሉታዊ ጎን አለው ይላሉ፡፡ ለምሣሌ እሳቸው እንደሚሉት የጥንቆላና የመተት ተግባር አንዱን ጠቅሞ ሌላውን ለመጉዳት ነው፡፡ አንዱን ሃብታም አድርጎ ሌላውን ለማደህየት ነው፡፡ አንዱን ጤነኛ አድርጎ ሌላውን በሽተኛ ለማድረግ ነው፡፡ ተግባሩም የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ እሴት ነው፡፡[165]

ዛር ለባለዛሮቹ አሉታዊ ጎን እንዳለው ሁሉ፤ አወንታዊ ጎንም አለው፡፡ ለምሳሌ ሰዎች በዛር ምክንያት ጤናቸውን፣ ሃብትና ንብረታቸውን እንደሚያጡ ሁሉ፤ ባንፃሩ በዛር ምክንያት በሰዎች ዘንድ ይፈራሉ፤ ይከበራሉ፡፡ በዛር ምክንያት የገቢ ምንጭ ያፈራሉ፡፡ በዛር ምክንያት ስምና ዝና ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ሌሎቹን በእነሱ ቁጥጥር ሥር ለማድረግ አጋጣሚ ያገኛሉ፡፡ ነገር ግን አንዳንዶቹ ጨርቃቸውን ጥለው ሊያብዱ ይችላሉ፡፡ አንዳንቹም "ባለዛረ!" እየተባሉ ሊሰደቡ ይችላሉ፡፡ በዛር ትውፊት መሰረት ይሄ ሁሉ በወሎ አለ፡፡ ትውፊቱ ግን የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ እሴት ነው፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ዛር ባገኘው ሰው ላይ ሁሉ አይሰፍርም፡፡ ዛር ውበት ይመርጣል፡፡ ዛር በቁንጅና ይማረካል፡፡ "እሽትና ቆንጆ አይታለፍም!" እንዲሉ፤ ዛር በወሎ፤ ቆንጆ አይቶ አያልፍም፡፡ በመሆኑም ዛር በቆንጆ ሴት ላይ ይሰፍራል፡፡ የደም ገንቦ ከሆነችው ወሎዬ ጋር ጋብቻ ይመሰርታል፡፡[166]

ዛር ሰዎችን ለማጥመድ ቦታና ጊዜ ይመርጣል፡፡ ወንዝ ዳር፣ የመቃብር ቦታ አካባቢና አውራ መንገድ (ፋጅ መንገድ) ዛር የሚያደፍጥባቸው አሳቻ ቦታዎች ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በነዚህ ቦታዎች በቀትር (በጠራራ ፀሐይ)፣ በውድቅትና (በእኩለ ሌሊት) ንጋት አካባቢ (ጎሕ

---

[164] ሞላልኝ ወርቁ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- መሐል መቻሬ፡፡
[165] እንደላይኛው፡፡
[166] አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ..ም ጉባላፍቶ-ገዶ፡፡

ሲቀድ/ በፈጅር) መንቀሳቀስ ለዛር ሠርግና ምላሽ እንደሆነ ይነገራል። ነገር ግን "ያልጠረጠረ...!" እንዲሉ፤ ወሎዬዎች በነዚህ ቦታዎችና ጊዜያት ልዩ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ለዚህም በደብተራ ወይም በቃልቻ የተደገመ ወይም የተሰራ መከላከያ ይዘው ይንቀሳቀሳሉ። አለያም በየእምነታቸው ፀሎት ያደረሳሉ።

በሌላ በኩል ዛር እንደ ሃብትና ንብረት ከቤተሰብ ይወረሳል። ከእናት ወደ ልጅ ይተላለፋል። የሽግግሩ መርኅ ደግሞ ለወንድ ሳይሆን፤ ለሴት ቅድሚያ ይሰጣል። አስጎሪ ወይም የዛር አባት ከሆነ ግን ቅድሚያው ለወንድ ነው። በዚህ መሰረት አስጎሪ ወንድ (የዛር አባት) በወሎ አባወራነቱ ወይም አለቅነቱ ለሚስቱና ለልጆቹ ብቻ ሳይሆን፤ ለዛርና ለዛር ጭፍራ ጭምር ነው።

ባለዛሮችም ሆኑ የዛር አባት በወሎ ባለባበሱ፤ በፀጉሩና በሚይዛቸው ቁሳቁሶች ጭምር ከአካባቢው የወንዶች ባህል፣ ወግና ልማድ ይለያል። ከአካባቢው ወንዶች ደንብና ሥርአትም ያፈነግጣል። የሴቶቹም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። በዚህም ባለዛርና የዛር አባት በወሎ ወይ ይፈራል፤ ወይም ደግሞ ይከበራል። አንዳንድ ጊዜም ይናቃል፤ ይሰደባል። የዚህ አይነቱ ብሂል በወሎ፤ በክርስቲያኑም በሙስሊሙም የሚታይ የጋራ መገለጫ ነው። በዚህ መሰረት ባህሉ የጋራ ነው። ለምሳሌ በክርስትናው አጉሪና አስጎሪ እንዳለ ሁሉ፤ በእስልምናውም አጉሪና አስጎሪ አለ። ነገር ግን በመላኩ ተገኘ ማብራሪያ መሰረት፤ ከአጉሪ አንፃር ሚዛኑ ወደ ክርስትናው የሚያጋድል ሲሆን፤ ከአስጎሪ አንፃር ደግሞ ወደ እስልምናው ሚዛኑ ይደፋል፡[167]

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት በመጠን ይለያያል እንጂ፤ በወሎ ሙስሊም ባለዛር አለ፤ ክርስቲያ ባለዛር አለ። ወይም የሚያጎራውም ሆነ፤ የሚያስጎራው ሙስሊሙም ክርስቲያኑም ነው። ከዚህም አልፎ እስላም ዛር አለ። ክርስቲያን ዛር አለ (አጽንያት የኔ)። ለምሳሌ ፈጨንገር ክርስቲያን ዛር ነው። አንበሶ ግን እስላም ነው። ጥቁረ-በላ ክርስተቲያን ነው። ነጨ-በላ በበኩሉ እስላም ነው። በሌላ በኩል ራሂሎ ክርስቲያንም ሙስሊምም ናት። ስለዚህ ዛር ክርስቲያኑንም ይይዛል፤ ሙስሊሙንም ይይዛል።[168]

አበጋር ማዱ በላይ እንደሚሉት በወሎ አንበሶና ፈጨንገር ነባር የዛር አይነቶች ናቸው። ራሂሎም ከነሱ ተርታ ትመደባለች። ሌላው ሁሉ የዛር አይነቱ ግን "መጤ" ነው። በአበጋር ማዱ በላይ መብራሪያ መሰረት የፈጨንገር ግንኙነት ከክርስትናው ጋር ነው። ባንፃሩ በእስል

---

167 ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 21 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ-04 ቀበሌ።
168 በሪሁን ይመር፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ።

ምናው በኩል አንበሶ ይጠቀሳል፡፡ የሚከተሉት ቃል ግጥሞች ለዚህ አባባል ማረጋገጫ አብነቶች ናቸው፡፡

ጨንገር

የዚህ አገር አድባር ቁጥቡ አንደምነው
የጤና ጠባቂው ጨንገር በረኛው
እበር ላይ ቆሞ እቤት እሚለው
ያገሩ ጠባቂ ጨንገር እንዴነው
እስቲ አሜሞሱና አርሂብ እንበለው
አርብ እሮብን ጂሚ፤ ሰንበትን አክባሪ
አይደለም ወይ ጨንገር ጉድ የልቡን ሰሪ
ላሊበላ ውሎ ግሸን ሃዳሪው
ባለወርቅ መስቀል ባለ ቃሎል ነው
እቤተስኪያን ገብቶ ቅኔ እሚያወራው
የአርባ አራቶች ወዳጅ ጨንገር በረኛው

አንበሶ

አሱ ኪታብ ቀሪ ባለ ጠሃራው
ባለ ቀይ ቆቲ ባለ ቄጤማው
የሼሆቹ ወዳጅ ተነጋጋሪው
ግራ ቀኝ ትካሻ የሚራገጠው
ባለ ቀይ ኮርማ ባለ ጅብማው
እንክትክት ስብርብር አርጎ እሚገዛው
እሱ ደም አስቀማሎ ጀርባ ቆማሎ ነው
ማርልኝ ነው እንጂ ሌላ ምን አለው[169]

ከዚህ በላይ የቀረቡት ሁለት የዛር ግጥሞች ጨንገርንና አንበሶን በማሞገስና በማወደስ፤ ኃያልነታቸውንና የበላይነታቸውን አጉልተው የሚያሳዩ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ግጥሞቹ ከዚህ ያለፈ ፋይዳ አላቸው፡፡ ምክንያቱም አገር በቀል የሆኑት ልማዶች (ትውፊቶች)

[169] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ-ገዶ፡፡

ከሃይማኖቶቹ ጋር እንዴት እንደተጋቡ የተገለፀው በነዚህ የዛር ግጥሞች አማካይነት ነው፡፡ በነዚህ ግጥሞች አማካይነት የጨንገር ልዕለ ኃያልነት የሚገለፀው በክርስትናው ትውፊቶች በኩል ነው፡፡ በዚህ መሰርት አንደታቦቶቹ ሁሉ ጨንገርም በወሎ ተከብሮና ተፈርቶ ይኖራል፡፡ አስራት በኩራት ይወጣለታል፡፡

በተመሳሳይ የአንበሶ ማንነት በእስልምናው ትውፊቶች በኩል ይገለፃል፡፡ እንደ ጨንገር ሁሉ በእነዚህ ትውፊቶች አማካይነት አንበሶ የእስልምናው አንድ አካል፤ አንድ አምሳል ይሆናል፡፡ ስለዚህ በክርስትናው በኩል ጨንገር አለ፡፡ በእስልምናው በኩል ደግሞ አንበሶ አለ፡፡ በነዚህ ግጥሞቹ ውስጥ ያልተጠቀሰችው "መጣፈጥ ወርቁ አንቺን ስጠብቅ አለቀ ጨርቄ!" የሚባልላት ራሄሎ ደግሞ የጋራቸው ናት፡፡

በሌላ በኩል ሁለቱ ሃይማኖቶች የሚጋሯቸው ትውፊቶች በግጥሞቹ ውስጥ ተወክለው ቀርበዋል፡፡ ለምሳሌ ጨንገርም ሆነ አንበሶ ተወክለው የቀረቡት በሃይማኖቶቹ ትዕምርቶች አማካይነት ነው፡፡ በዚህም ጨንገር ባለወርቅ መስቀልና ባለቃጭል ነው፡፡ አንበሶ ደግሞ ባለቀይ ቆቲና ባለቁጠማ ነው፡፡ ቁሶቹ የሁለቱ ልዕልና የሚገለጽባቸው ትዕምርቶች ናቸው፡፡ የሚያዙትም በእጅ ነው፡፡ ጨንገር የአርባ አራቶቹ ወዳጅ ነው፡፡ አንበሶም የሼሆቹ ወዳጅ ነው፡፡ ሁለቱም የነዚህ አካላት ወዳጆች ብቻ ሳይሆኑ፤ ሌላ ተግባርም አሏቸው፡፡ ለምሣሌ ጨንገር በረኛ ነው፡፡ አንበሶ ደግሞ ተነጋጋሪ ነው፡፡ በሌላ ቋንቋ የህዝብ ግንኙነት እንደማለት ነው፡፡ ጨንገርን ደግሞ በሀገር መከላከያ መመሰል ይቻላል፡፡

ጨንገርም ለክርስትናው፤ አንበሶም ለእስልምናው ፍፁም ታማኝ ናቸው፡፡ ጨንገር አርብ እሮብን ይያማል፤ ሰንበትን ያከብራል፤ ልሊበላንና ግሼንን ይሳለማል፡፡ አንበሶ በበኩሉ ጦሃራና ኪታብ ቀሪ ነው፡፡ እነዚህ ተግባራት ከሃይማኖቶቹ አንፃር ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ይህንን ሁሉ የሚያደርጉት ግን ሁለቱም "ሰማይ አይታረስ-ንጉሥ አይከሰስ!" እንዲሉ ፍፁም ፊላጭ ቆራጭ ለመሆን ነው፡፡ የሰይጣን ወይም የዛር መለያ ባህርይ ደግሞ ይኸው ነው፡፡ቀደም ሲል በዛርና በዛር ፈረስ ግንኙነት አንደተብረራው ዛር ግብር ይጠይቃል፡፡ ምስ አመምጡ ይላል፡፡ ይህንን ማድረግ ካልተቻለ ደግሞ ስብርብር፣ እንክትክት አድርጎ ሽባ ያደርጋል፡፡ ጀርባ ይቆምጣል፡፡ ቁርጭምጭሚት ያደቃል፡፡ አንጀት ቆራርጠ ደም ያስቀምጣል፡፡ ይህ እንዳይሆን ደግሞ ሁለቱም እንደፍላጎታቸውና እንደምርጫቸው የሚጠይቁትን ምስ ማቅረብ ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም ለሁለቱም ምስ ይቀርባል፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚያብራሩት በወሎ የዛር ብዛቱ ለቁጥር የሚታክት ነው። ይህም ሆኖ ሁሉም ዛሮች የየራሳቸው ምስ አላቸው። "ሳይደግስ አይጣላም!" እንዲሉ፤ ከዛር ብዛቱና እንዲቀርብለት የሚጠይቀው ምስ አይነቱና መልኩ የተለያየ ከመሆኑ አንፃር፤ ደግነቱ በዚያው ልክ ዛር የሚፈልገው ነገር ሁሉ፤ በወሎ መሬት ላይ ይገኛል። ለዛር ምስ ለሚበላም ቢሉ ለሚጠጣ፣ ለሚጤስም ቢሉ ለሚለበስ፣ ለሚቀባም ቢሉ ለሚደማ፣ የወሎ መሬት ሳይሰለች ሁሉን ነገር ይለግሳል። በወሎ ዛር እንዲደማለት የሚፈልገው የበግ፣ የፍየልና የዶሮ አይነትና መልክ ከራሱ የዛር ብዛት ጋር መሳ ለመሳ ነው። ለምሳሌ የአንበሶ ለጨንገር አይሆንም። የጥቁረ-በላ ለነጨ-በላ አይስማማም። የተረጨ ለአባ ዱሪ አይገጥምም። የሻንቆ ለራሄሎ ከዛር ደንብና ሥርአት ውጪ ነው። የሌሎቹም ተመሳሳይ ነው።

የሚጠጡትም ነገር እንደ በግ፣ ፍየልና ዶሮው አይነትና መልክ ሁሉ ምርጫቸው ይለያያል። ለምሳሌ አንበሶና ጨንገር ቡቅሬ በዞረበት አይዞሩም። ምሳቸው (ግብራቸው) ጠላ ወይም ካቲካላ ነው። ጠጅና ውስኪም ካገኙ አይጠሉም። ለዛር የማይስማማው የማያሰክር ነገር ነው እንጂ፤ ከተገኘ የሚያሰክር ነገር ለዛር እጣ ፈንታው ነው።

ለራሄሎ ግን ሁሉም ነገር ይስማማታል። ራሄሎ በወንድ ዖታ ከሚጠሩት ዛሮች የምትለየው በሴት ዖታ መጠራቷ ብቻ ሳይሆን፤ በገራምነቷ ጭምር ነው። በዚህም ወሎዬዎች የወሎ አድባር (ቆሌ) በማለት ይጠሯታል። ወሎዬዎች ለወሎ አድባር እንዳይርባት ቆሎ ይበትኑላታል። ንፍሮ ያነፍሩላታል። እንዳትታረዝ እራፊ ጨርቅ ያለብሷታል። እንዳትነጣና እንዳትገረጣ ቅቤ ይቀቧታል። ከዚህም ሲያልፍ አርደው፣ ጋርደው፣ ጎዝጉዘው፣ ይሞሽሯታል።[170]

5.4.4፡- አድባር (ቆሌ) በወሎ

ከላይ እንደተጠቀሰው ዛር ግለሰባዊ ጉዳይ ነው። ፍቅሩም ሆነ ጠቡ ከሰፈረበት ግለሰብና ቢበዛ ከቤተሰቡ ጋር ነው። የሚጠራውም በወንዴ ዖታ ነው። ግብሩ ደግሞ በአብዛኛው አሉታዊ ነው። ወይም ሰይጣናዊ ነው። ባንፃሩ አድባር የምትጠራው በሴቴ ዖታ ነው። ትስስሯም ከግለሰብ እስከ ማኅበረሰብ ድረስ ነው። ግብሯም በአብዛኛው አዎንታዊ ነው። አልፎ-አልፎ ግን አሉታዊ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። በዚህ መሰረት አድባር የግለሰብም ሆነ የማኅበረሰብ

[170] ወዳጇ ይማም፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- አማየ ሚኤጌ።

ጠባቂ፣ ተጠሪና የበላይ ተቆጣጣሪ ናት[171]። በመሆኑም የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት በወሎ አካባቢው፣ ሰው፣ ከብቱ፣ እጽዋቱ፣ አራዊቱ፣ መሬቱ፣ ወንዙ፣ ጋራውና ሸንተረሩ ሳይቀር በአድባር ይጠበቃል። ቁጥጥሩም፣ ተጠሪነቱም ለወሎ አድባር ነው።[172] ስለሆነም ክርስቲያን መ·ስሊ·ሙ· የወሎ አድባር እንዳትቀየማቸው፣ እንዳትቆጣባቸው፣ እንዳታኮርፋቸው ግብር ይገብሩላታል። አድባር አኩርፋ መአት እንዳታወርድባቸው ወሎዬዎች ይጎዘጉዙላታል፣ ያርዱላታል፣ ያጨሱላታል፣ ቡና ያፈሉላታል፣ ቆሎ ይቆለላታል፣ ንፍሮ ያነፍሩላታል። ባጠቃላይ የለመደችውንና የምትፈልገውን ምስ (ግብር) ቀን ቆርጠው፣ ሠአት ወስነው ያቀርቡላታል።

ወሎዬዎች ልጆቻቸው እንዲያድጉ፣ ከብቶቻቸው እንዲረቡ፣ ማሳቸው እንዲያፈራ፣ ወንዞቻቸው እንዲሞሉ፣ ምንሥኦቻቸው እንዲፈልቁ፣ የወሎን አድባር ይማፀናሉ። ስዕለት ይሳላሉ። የጠየቁት ሲፈጸምላቸው ደግሞ ለወሎ አድባር ስዕለት ያገባሉ፣ ምሥጋና ያቀርባሉ። ወሎዬዎች የወሎ አድባር ከድርቅና ከበሽታ እንዲትጠብቃቸው ኃላፊነቱን ለወሎ አድባር አደራ ይሰጣሉ። ይሄ ሳይሆን ቀርቶ ድርቅና በሽታ ቢከሰት የወሎ አድባር ተቀይማባቸው ነውና፤ ግብሯን ገብረው፣ ከእግሯ ሥር ተንበርክከው፣ ከጭንቅ እንድትሰውራቸው ይማፀናሉ።

ይህ ሁሉ ተግባር የሚፈፀምበት ደግሞ ቦታና ጊዜ አለው። "ከእንጨት መርጦ ለታቦት" እንዲሉ፤ ከዛፍ መርጦ ለወሎ አድባር መሰየም በወሎ የተለመደ ባህል ነው። ደንብና ሥርአት ነው። የአድባር ዛፍ በወሎ ከቤተ-ክርስቲያንና ከመስጊድ ተርታ ይሰለፋል። የአድባር ዛፍ በወሎ ይፈረል፣ ይከበራል፣ ይመለካል። ከዚህም ሌላ ደም ይፈስለታል። ዳቦ ይቆረስለታል። ቆሎና ንፍሮ ይበተንለታል። ለቃል ኪዳኑም ክርና እራፊ ጨርቅ ይታሰርለታል። ለክብሩ ቄጠማ ይጎዘንዝለታል። አድሩስና ከርቤ ይጨስለታል። የባዲገዘ ፍየል አካባቢውን ዞሮ ይደማለታል።[173]

---

[171] አስቴን ሃሮልድ አድባርን አስመልክተው የሚከተለውን ረዕሰ ጉዳይ ጽፈዋል። The Adbar is a female, protective spirit, and she protects a certain neighbourhood, its inhabitants and their land, animals, and children from all sorts of ailments, if properly treated (Aspen 2001: 102).

[172] አድኖ ተካየ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 02 ቀበሌ።

[173] በዚህ ክፍል ውስጥ ከአድባር ጋር ተያይዞ የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ በአሁኑ ጊዜ መ·ሉ· በመ·ሉ· ተግባራዊ ይደረጋል ማለት አይደለም። በሌላ በኩል መ·ሉ· በመ·ሉ· ቀርቷል ማለትም አይደለም። የአድባር ትውፊት በወሎ የዚህ አይነት ሥረ-መሰረት ያለው ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ ግን "ባእድ አምልኮ!" ተብሎ ከጎጂ ባህል ተርታ ስለተሰለፈ ልማዱ ቀንሷል። ነገር ግን በገጠሩ አካባቢ አሁንም ድረስ ተግባራዊ እንደሚደረግ የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ።

አብርሃም ሽፈራው እንደሚሉት የአድባር ዛፍ ታሪካዊና ሰብአዊ የሆነ መነሻ ምክንያት አለው።[174] ይኸውም አብርሃም "አባቶች የነገሩኝ!" ብለው እንደሚተርኩት ከረዥም ጊዜ በፊት የጁ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ወረርሽኝ በሚባል በሽታ ይጠቃ ነበር። በዚያን ዘመን የአካባቢው ማኅበረሰብ ወረርሽኝ ከገባበት ቤት ገብቶ የታመመ መጠየቅ ቀርቶ በሩቅ ሆኖ አካባቢውን መመልከት እንኳ ይፈራ ነበር። ምክንያቱም በሩቅ በማየት ጭምር ወረረሽኝ ይተላለፋል ብሎ ይሰጋ ነበር። በዚህ ምክንያት በወረርሽኝ ያልተጠቃው አካባቢ፤ በወረርሽኝ ለተጠቃው አካባቢ የሚሆን ምግብና መጠጥ የሚያቀርብበት ዘዴ ነበረው። ይኸውም ወረርሽኙ ከገባበት አካባቢ የቻለ ሰው መጥቶ እንዲወስድ ማሩን፣ ቅቤውን፣ ወተቱን፣ እንጀራውን፣ ሥጋውን፣ ዳቦውን፣ ቂጣውን፣ ቆሎውን ...ወዘተ ትልልቅ ዛፍ ላይ አስረው ያስቀምጡላቸው ነበር። ከዛፉ ላይ አስረው የሚያስቀምጡትም ምግቡን አውሬ እንዳያበላሸው በማሰብ ነው።

አብርሃም እንደሚሉት በሂደት ግን፤ ሰዎች እምታድናቸው ዛፏ እየመሰለቻቸው መጡ። በዚህም ዛፏ አንድ ኃይል አላት ብለው ማሰብ ጀመሩ። ለዚህ ኃይል "አድባር" ወይም "ቆሌ" የሚል መጠሪያ ስያሜ ሰጡ። ቀደም ሲል በወረርሽኝ ለተጠቁት ሰዎች ይቀርቡ የነበሩ የምግብና የመጠጥ አይነቶችም መልካቸውን ቀይረው ለአድባሯ መቅረብ ጀመሩ። ምግቦቹ ታስረው ይቀመጡባቸው የነበሩት እንደ ልጥ፣ ገመድና የመሳሰሉት ነገሮች ደግሞ በክርና በእራፊ ጨርቅ ተቀይረው የአድባሯ የቃልኪዳን ምልክት ሆነው ይገኛሉ። በዚህም የአካባቢው ማኅበረሰብ ከሌላው ዛፍ ሁሉ የተለየ ትልቅ ዛፍ ሲያይ የአድባር ወይም የቆሌ ዛፍ እያለ መሰየም ጀመረ። በአካባቢው ትልቅ ዛፍ ከሌለ ደግሞ ቁጥቋጦችንና ሌሎች ነገሮቹን መገልገል ጀመረ። በዚህ መሰረት ለአድባር እየደገሰ፣ ስጦታ እያዘጋጀ ስዕለት እየተሳለ ለአድባሯ መገበር ለመደ። ስለዚህ ለአድባር ቅቤ መቀባቱም፣ ክርና እራፊ ጨርቅ ማሰሩም፣ ምግብና መጠጥ መውሰዱም ከዚህ ታሪክ ጋር ተያይዞ የመጣ ብሂል ነው።[175]

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ለወሎ አድባር ግብር የሚቀርበው በግንቦት ወር ነው። በአካባቢው ትውፊት መሰረት ግንቦት ጎዶሎ ወር ነው። በመሆኑም እህል ከጎተራ፣ ገንዘብ

---

[174] አብርሃም ሽፈራው "ከአባቶች የሰማሁት!" በማለት የነገሩኝ ሌላ ታሪክ ከቁጥር ጋር የተያያዘ ባህል ነው። በዘመኑ የየጁ መሳፍንቶች ቁጥር አይችሉም ነበር ይባላል። በዚህም ወደ ዘመቻ የሚጓዝ ወታደራቸውን ብዛት ለማወቅ ወታደሩ በሚያልፍበት መንገድ አንድ አካባቢ ላይ እያንዳንዱ ወታደር አንድ-አንድ ድንጋይ እያስቀመጠ እንዲያልፍ ያደርጉ ነበር። በዚህም የወታደሩን ብዛት በተከማቸው ድንጋይ መጠን ይገምቱ ነበር። በተመሳሳይ ከጦርነት መልስ የሞተውን ወታደር ለመገመት ደግሞ ሲሄዱ ድንጋይ ካስቀመጡበት ቦታ ጎን ተመላሽ ወታደር ሌላ አንድ-አንድ ድንጋይ እያስቀመጠ እንዲያልፍ ያደርጋሉ። በዚህም የሁለቱን የድንጋይ ክምሮች በማነፃፀር ከወጪ ቀሪያቸውን ይገምቱ ነበር። በዚህ ምክንያት በየጁ አውንም ድረስ በተለያዩ አካባቢዎች ጎን ለጎን የተከማቹ የተለያየ መጠን ያላቸው የድንጋይ ክምሮች እንደሚገኙ መረጃ አቀባዩ ይናገራሉ

[175] አብርሃም ሽፈራው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ሐምሌ 16 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- አዲራ።

ከተቀመጠበት እቃ አይወጣም። የመንገድ ጉዞም በግንቦት ወር ተመራጭ አይደለም። የንግድ ልውውጥም ብዙ አይመከርም። አዲስ ቤት መስራትም ሆነ ሦስት ጉልቻ መመስረት በግንቦት ወር ሄይር አይሆንም።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የአበጋር ወዳጃ ማስገባት እንኳን በግንቦት ወር አይሰምርም። ባነፃሩ ባህሉ፣ ወግና ልማዱ የለመደው፣ ደንብና ሥርአቱ የሚፈቅደው በወሎ አድባር ጥላ ስር ተሰባስቦ በአንድ ልብ "አንቺ መጀን!" ብሎ መማፀንን ነው። በዚህም ሁሉም በየአድባሩ ጥላ ሥር በመሰባሰብ፣ ዳቦና ቂጣ በመጋገር፣ ንፍሮ በማንፈር፣ ቆሎ በመቁላት፣ ቡና በማፍላት፣ እጣን በማጤስ፣ ዶሮ፣ በግና ፍየል፣ የቻለውም ኮርማ ወይም መሲና በማረድ ለወሎ አድባር ግብር ያቀርባል። አረቄና ጠላ ይዘክራል። ዝክሩን በአንድ ላይ በአድባር ዛፍ ጥላ ሥር ተሰብስቦ ይበላል፤ ይጠጣል። የጠየቀው ሁሉ ከተፈፀመለት ደግሞ ለከርሞ ከዚህ የበለጠ ግብር እንደሚያቀርብ ቃል ገብቶ ወይም ስዕለት ተስሎ ይለያያል።[176]

ግራዝማች ብሩ ይማም እንደሚገልፁት ከዚህ ልማድ ጋር የእትብት ዝምድና ያለው ትውፊት የግንቦት ልደታ ባህል ነው። ባህሉ የተጋባው ከክርስትናው የሃይማኖት ትውፊት ጋር ነው። መረጃ አቀባዩ እንደሚሉት የክርስትናው ትውፊት ከማርያም የልደት ቀን ጋር አገናኝቶ ግንቦት ልደታን ያከብራል። ለዚህም በያመቱ ግንቦት አንድ ቀን ሁሉም በየደጁ ንፍሮ ይቀቅላል፣ ቡና ያፈላል፣ ዶሮ፣ በግም ሆነ ፍየል ያርዳል። ነገር ግን አድባሯ ሳትቀምስ ቀደሞ ማንም አይቀምስም። ስለዚህ ለአድባሯ የግንቦት ልደታ እለት የሚረጨው ነገር ይረጫል፤ የሚበተነው ነገር ይበተናል። ለሙስሊሙ "ነባር ባህሉ" ስለሆነ ከክርስቲያን ጎረቤቱ ጋር የግንቦት ልደታ እለት አብሮ ንፍሮ ይቀቅላል። ቡና ያፈላል። ካለው እንዳቅሙ ያርዳል። በዚህም ግንቦት ልደታ በወሎ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ ባህል ነው።[177]

ነገር ግን ክርስቲያኖቹንና ሙስሊሞቹን ከምንም በላይ እርስ በርስ የሚያስተሳስራቸው የአድባር ትውፊት የ"ባዲገዝ" ሥርአት ነው። ባዲገዝ በወሎ፤ ለወሎ አድባር መስዋእት የማቅረብ ልማድ ነው። መስዋእት የሚቀርበው እንስሳ ደግሞ "የባዲገዝ ፍየል" በመባል ይታወቃል። በዚህ ትውፊት መሰረት የአካባቢው ማኅበረሰብ በያመቱ በግንቦት ወር ለባዲገዝ ፍየል መግዣ የሚሆን ገንዘብ ያዋጣል። በተዋጣው ገንዘብ ዳልቻ ፍየል ይገዛል። የተገዛው ዳልቻ ፍየል በተራ እየዘረ በእያንዳንዱ ሰው ቤት ይታሰራል። የሚያዞረውም ሆነ ከቤቱ ወስዶ

---

[176] ግራዝማች ብሩ ይማም፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 15 ቀን 2006 ዓ..ም ወልዲያ- 01 ቀበሌ።
[177] እንደላይኛው።

የሚያስረው ሰው ግን ለባዲገዝ ፍየል መግዣ የሚሆን ገንዘብ ያዋጣ ወይም አጣሁ ነጣሁ ብሎ ያስፈቀደ ሰው ብቻ ነው።

በዚህ የተነሳ ፍየሉን ያላዞረ ወይም ከቤቱ ወስዶ ያላሰረ ክርስቲያንም ሆነ ሙስሊም ሰው ይደኸያል፣ በሽታ ይወርድበታል፣ ሞትም ሊመጣበት ይችላል ተብሎ ይታሰባል። ስለዚህ ማኅበረሰቡ ለባዲገዝ ፍየል ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። ፍየሉን ሁሉም በየቤቱ አስገብቶ ካስወጣና አከባቢውን ዙሮ ከጨረሰ በኋላ ለአድባሯ ይደማል ወይም ይታረዳል። ወጥ ሳይሰራ ተጠብሶ ይበላል። አጥንቱና ሌሎች ቀሪ አካላቶቹ ተቃጥለው ለአካባቢው ሠላምና ጤና ይጨሳሉ። በመጨረሻ ወሎዬዎች ተመራርቀው ይለያያሉ።[178]

በዚህ የባዲገዝ ሥርአት ላይ የወለዬዎች የልዩነት ምልክት ተደርጎ የሚታሰበው "ካራ" (ቢልዋ) አለ። ነገር ግን ልዩነቱ በሁለት መንገድ ይፈታል። አንደኛው መንገድ ዓሊ ሞሐመድ እንደሚያብራሩት "እዚያው አድባሩ ላይ ሁለት ፍየል ለየብቻ አርደው እዚያው ላይ በልተው ይለያያሉ"።[179] በሚለው ሥርአት የሚከናወን ነው። ሁለተኛው መፍትሄ ደግሞ በሪሁን ይመር "አሁን እኛ ጋር እዚህ ካሎ-ሼሆላ እሚባል ቦታ አለ። ክርስቲያኑም ሙስሊሙም በአንድ ላይ ይቀመጣል። በአንድ ላይ ያመልካል። ግን ለክርስቲያኑ ተብሎ እሚታረድ ነገር የለም። እዚያ ላይ እርጎ አለ፤ እርጎ ለክርስቲያኑ ይዘረገፋል። ክርስቲያኖቹ በእርጎ ይስተናገዳሉ። ሥጋውን ሙስሊሞቹ ይበላሉ።"[180] በማለት የሚገልፁት ሥርአት ነው።የዚህ ሁሉ ፎክሎራዊ ክዋኔ ዋና ዓላማ የሙስሊም ክርስቲያን ሳይል አዝመራው እንዲይዝ፣ የሰው፣ የከብቱ ጤንነት እንዲጠበቅ፣ በአካባቢው ደስታ፣ ሠላምና ፍቀር እንዲሰፍን፣ ልጆች እንዲያድጉ፣ አረጋውያን እንዲጠወሩ፣ የታመሙ እንዲድኑ፣ የተለከፉ እንዲፈወሱ፣ የተጣሉ እንዲታረቁ... ወዘተ ለማድረግ ነው። ይህም በወሎ አድባር በኩል እንዲፈፀም ታስቦ የሚደረግ ፎክሎራዊ ክዋኔ ነው።

በዚህ መሰረት ፎክሎሩ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው። ለምሳሌ በወሎ አድባር አማካይነት የሚገኘው በረከትም ሆነ፤ የሚመጣው ቁጣ በክርስቲያኑ ላይ ተፈፃሚ ሆኖ በሙስሊሙ ላይ አይቀርም። ወይም በሙስሊሙ ላይ ተፈፃሚ ሆኖ ክርስቲያኑን አያልፈውም። በመሆኑም ወሎዬዎች በጋራ ለወሎ አድባር የሚደረገውን ነገር ሁሉ

---

[178] አድኖ ተካየ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 02 ቀበሌ።
[179] ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አንጦ 04 ቀበሌ።
[180] በሪሁን ይመር፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ።

ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መሰረት በወሎ የክርስቲያን የሙስሊም አድባር የሚባል ነገር የለም፡፡ የወሎ አድባር የጋራ ናት፡፡ በዚህም ወሎዬዎች በወሎ አድባር አማካይነት ይገናኛሉ፣ ይተሳሰራሉ፡፡

ባጠቃላይ ወሎዬዎች ክፉ ነገር እንዲርቅ፤ በምትኩ መልካም ነገር እንዲቀርብ ለዱዓ ወደተመሰረቱ ቦታዎች በረከት ለማግኘት በጋራ ይሄዳሉ፡፡ በታቦት ስም ወደተመሰረቱ ቦታዎች ሂደው በጋራ ፀበል ይጠመቃሉ፡፡ እምነት ይቀባሉ፤ መስቀል ይታሻሉ፡፡ ለወሎ አድባር መስዋእት ያቀርባሉ፡፡ ወደ ቃልቻ፣ ጠንቋይና ደብተራ ሂደው የቡዳ መድኃኒት ያሰራሉ፡፡ የሰላቢ መከላከያ ይቀበላሉ፡፡ ደንቀራ ያስወጣሉ፡፡ መስተፋቅር ያስደግማሉ፡፡ የዓይነ-ናስ ያስወጣሉ፤ መተት ያሰራሉ፡፡ የአንደርቢ ያስደግማሉ፤ የሾተላይ ይቀበላሉ፡፡

ወሎዬዎች ለዚህ ሁሉ መነሻ ምክንያታቸው ደግሞ እንድሜና ጤና፣ ክብርና ዝና፣ ሃብትና ንብረት፣ ሠላምና ፍቅር... ወዘተ ለማግኘት ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ወደፈጣሪ ፀልየው ወይም ዱዓ አድርገው ሃጃቸውን የሚሞሉላቸው የወሎ ደጋጎች አሏቸው፡፡ ወሎዬዎች በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው፤ በእጃቸው ዳብሰው፣ በዓይናቸው አይተው፣ በምራቃቸው እንትፍ እንትፍ ብለው፣ በቃላቸው ፈጣሪ ይማርህ ብለው፣ በፈጣሪ ለሰው ልጅ መድኃኒት እንዲሆኑ የታዘዙ እጽዋቶችን ቆርጠው፣ በፀበል አጥምቀው፣ በመስቀል አሽተው...ወዘተ ከበሽታ የሚያድኑ፣ ከደዌ የሚያነጹ፣ ከልክፍት የሚፈውሱ፣ ተሰጥኦውና ብቃቱ ያላቸው አራት ዓይናዎች አሏቸው፡፡ እንዲሁም በመላዕክት፣ በዓድቃን፣ በነብያትና በሰማዕታት ተራዳዒነት ወሎዬዎች የሚፈልጉት ይቀርባል፤ የሚጠሉት ይርቃል፡፡

ባንፃሩ ጠንቁለውም ሆነ ድግምት ደግመው፣ መጠሐፍ ገልጠውም ሆነ መዳፍ አንብበው፣ ኮከብ ቆጥረውም ሆነ ጠጠር ጥለው፣ ሥር ምሰውም ሆነ ቅጠል በጥሰው፣ እጣ ጥለውም ሆነ አስጎርተው...ወዘተ ለወሎዬዎች ጥያቄ መልስ የሚሰጡ ባለዛሮች፣ ጠንቋዮች፣ መተተኞች፣ ቃልቾችና፣ ደበተራዎች አሉ፡፡ የወሎ አድባር ደግሞ የአካባቢው በሞላ ጠባቂና ተጠሪ ናት፡፡ ተጠሪነቷም ከግለሰብ እስከ ማኅበረሰብ ድረስ ነው፡፡ከላይ በሁለት ጎራ የተጠቀሱት አካላት ከነግብራቸው፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከክርስትናውም ሆነ ከእስልምናው ትውፊቶች ጋር ይገናኛሉ፤ ይተሳሰራሉ፡፡ ግንኙነታቸውም አንድም ከትውፊቶቹ ከራሳቸው የፈለቀ ነው፡፡ አንድም በተለያየ ምክንያት ከትውፊቶቹ ጋር በመጋባት የተፈጠረ ዝምድና ነው፡፡ በዚህም አንዱ ከሌላው የዘር ሐረግ ይስባል፡፡ እሴቱን ይጋራል፡፡ አንዱ የሌላውን ይወርሳል፡፡ ወርሶም የራሱ፣ የግሉ ንብረት ያደርጋል፡፡ በዚህ ሂደት የክርስትናው ከእስልምናው ትውፊት፤ የእስልምናው ከክርስትናው ትውፊት ጋር ይወራረሳል፤ ይዛመዳል፡፡

የዚህ አይነቱ የእርስ በርስ መስተጋብር ደግሞ የወለዬዎች መገናኛ ድልድይ እና የእርስ በርስ መተሳሰሪያ ክር በመሆን ያገለግላል። የወለዬዎች የእኔነት ስሜት የተፈጠረውም በዚህ አይነቱ የትውፊቶች የእርስ በርስ ግንኙነት አማካይነት ነው። በዚም በወለ ክርስቲያኑ ወደ እስልምናው ትውፊቶች ይሄዳል፤ በተመሳሳይ መ.ስ.ሊ.መ ወደ ክርስቲያኑ ትውፊቶች ይሄዳል። ፀበል ይጠመቃል፣ እምነት ይቀባል፣ መስቀል ይታሻል። ባንዳኑ የክርስቲያኑ ምርጫ ቃልቻ ሊሆን ይችላል። መ.ስ.ሊ.መ ደግሞ እጣ ጥለ ወይ አስጠንቁለ ከቃልቻ ይልቅ እጣ ክፍሌ ደብተራ ነው፤ የማለት አማራጩ ሰፊ ነው። በዚህም ወደ ደብተራ ሄዶ ለሚፈልገው ነገር ድግምት አሰርቶ ይመለሳል። ይህ እንግዲህ የግለሰቡ ምርጫ ነው። ባህሉ ግን ለሁለቱም እኩል ይፈቅዳል። ሁለቱንም እኩል ያስተናግዳል።

ጉዳዩ የጀማው ሲሆን ደግሞ መ.ስ.ሊ.መም ክርስቲየኑም በወለ አድባር ጥላ ሥር ይሰበሰባል። ለወለ አድባር የሚያስፈልጋትን ነገር ሁሉ በጋራ ያሟላል። በጋራ ይገብራል። በረከቷንም በጋራ ይቀበላል። ቁጣዋንም በጋራ ይሸከማል። ለዱዓ በተመሰረቱ ቦታዎችም ትውፊቱ ተመሳሳይ ነው። ልዩነቱ ልሂቃኑ "የተፈቀደ" "የተከለከለ" ወይም "ቅዱስ" "እርኩስ" ብለው አጥር ባበጁለት ቦታ ላይ ጀማው መገኘቱ ነው። ለጀማው ግን ልዩነቱ የቀኝና የግራ እጅ ያህል ነው። በዚህ መሰረት ወለዬዎች እርስ በርስ ከሚገናኙባቸውና ከሚተሳሰሩባቸው የጋራ እሴቶች መካከል የሃይማኖቱ ትውፊቶች የሚጠቀሱ አብነቶች ናቸው። እነዚህ ትውፊቶች ግንኙነታቸው በዋናነት ከሃይማኖቶቹ መርሆዎች ጋር ሳይሆን ከፎክሎር መርህ ጋር ነው። ስለዚህ ፎክሎር የወለዬዎች የጋራ እሴት ነው። ይህ የጋራ እሴት ለክርስቲያኑ አይበልጥም፤ ለመ.ስ.ሊ.መም አያንስም። በተመሳሳይ ለፎክሎሩ መ.ስ.ሊ.መ ባለቤት፤ ክርስቲያኑ ጎረቤት አይደሉም። ፎክሎሩ ለክርስቲያኑ ሃብቱ ነው። ለመ.ስ.ሊ.መም ንብረቱ ነው። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አብነቶች የሚያረጋግጡት ይህንን ሃቅ ነው። ስለዚህ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ማለት በወለ፤ በዚህ የእኩልነት መርህ ላይ የተመሰረተ ጉዳይ ነው።

በመሆኑም የሃይማት መቻቻል እሴት በወለ፤ የሚገለፀው በክርስትናውና በእስልምናው ትውፊቶች አማካኝነት ነው። ይህም ማለት በወለዬዎች ፎክሎር አማካኝነት ነው። ፎክሎሩ ደግሞ የወለዬዎች የጋራ እሴት ነው። የፎክሎር ተፈጥሯዊ ባህርይ ሰዎችን መለያየት ሳይሆን፤ ማገናኘት ነው። አንዱን ከሌላው መነጣጠል ሳይሆን፤ ማሰበሰብ ነው። ማራራቅ ሳይሆን፤ ማስተሳሰር ነው። የወረ-ላሎ ተክለሃይማኖት ትውፊት ለዚህ አባባል ማረጋገጫ ምሳሌ ነው። ጋቲራ ጊዮርጊስ አሰረጅ ነው።የቂሌ- ሃዳሚ ጊዮርጊስ ለአብነት የሚጠቀስ ነው።

የመርሣ አባገትየ፣ የዳናና የሼህ ለጋ ትእይንት ለሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ዋቢ ነው፡፡ ጠንቋዩ፣ ባለዛሩ፣ ቃልቻውና ደብተራውም ለሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ የራሱ ድርሻ አለው፡፡ በዚህ መሰረት ኬሚስትሪ የሚባለው የተፈጥሮ ሣይንስ ዘርፍ አተሞች እርስ በርስ የሚያያዙበት ወይም የሚሳሳቡበት ክር "bond" በመባል ይታወቃል፡፡ ሣይንሱ እንደሚለው የዚህ ቦንድ ቁጥር እየጨመረ በሄደ መጠን የአተሞቹ የእርስ በርስ የመሳሳብ ኃይል ይጨምራል፡፡ ጥንካሬያቸውም የዚያኑ ያህል ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ የኬሚስትሪው ተፈጥሯዊ ቀመር ለፎክሎሩም ይሰራል፡፡ ይህም ማለት ፎክሎር ሰዎች እርስ በርስ የሚገናኙበት ክር (common bond) ነው፡፡ ሰለሆነም እንደ ኬሚስትሪው ሁሉ፤ የፎክሎር ቦንድ (ክር) በጨመረ ቁጥር ወይም አንድ ማኅበረሰብ የበርካታ አሴቶች (ትውፊቶች) ባለቤት እየሆነ በሄደ ቁጥር አንድነቱ ይጠነክራል፤ ሃይሉም ይጨምራል፡፡ ይበረታል፤ ፍቅርና ሠላሙም አስተማማኝ ይሆናል፡፡

ይህ የሚሆነው ግን በዚህ ጥናት በፎክሎር ፅንሰ-ሃሳብ ማብራሪያ ውስጥ እንደተገለፀው አንዱ የሌላውን ተውፊት የኔ የራሴ ብሎ እስከተቀበለ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን መሳሳቡ ይቀርና መገፋፋቱ ያይላል፡፡ መጠጋጋቱ ይቀርና መለያየት ይፈጠራል፡፡ መስማማቱ ይቀርና መበጣበጡ የዘወትር ተግባር ይሆናል፡፡ ለወሎዬዎች ግን ኬሚስትሪው (የአቶሞቹ) ቀመር ተምሣሌትነት ይሰራል፡፡ ምክንያቱም ወሎዬዎች በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ትውፊቶች አማካይነት እርስ በርስ ይሳሳባሉ፤ ይጠጋጋሉ፡፡ እርስ በርስ ይገናኛሉ፤ ይተሳሰራሉ፡፡ ይረዳዳሉ፤ ይደጋገፋሉ፡፡ ይተሳሰባሉ፡ ይተዛዘናሉ፡፡ ይከባበራሉ፤ ይተባበራሉ፡፡ አብረው ይበላሉ፤ አብረው ይጠጣሉ፡፡ አብረው ይደሰታሉ፡ አብረው ያዝናሉ፡፡ ባጠቃላይ በዚህ ምእራፍ ውስጥ ለአብነት በተጠቀሱት እሴቶች አማካይነት ወሎዬዎች በሠላምና በፍቅር አብረው ይኖራሉ፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው የአብሮነታቸው ምስጢር ደግሞ የሃይማኖቶቹ ትውፊቶችና ወሎዬዎች የፈጠሯቸው የጋራ እሴቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን የወሎዬዎች አብሮነት የሚገለፀው በነዚህ እሴቶች ብቻ አይደለም፡፡ ባንፃሩ የወሎዬዎች አብሮነት በተለያዩ መንገዶች ይገለፃል፡፡ ከነዚህ መንገዶች መካከል የወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር (social interaction) አንዱ ነው፡፡ የምእራፍ ስድስት ዋና አላማም የወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር፣ ክርስቲያን ሙስሊሙ በሃይማኖት ተቻችሎ የሚኖርበት የጋራ እሴት መሆኑን በተለያዩ አብነቶች አማካይነት ተንትኖ መግለፅ ነው፡፡

ምእራፍ ስድስት

6፡- የሃይማኖት መቻቻል እሴት እና ማኅበራዊ መስተጋብር በወለኖ

(Social Interaction)

የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለኖ፤ በክርስትናውና በእስልምናው ትውፊቶች አማካይነት እንዴት እንደሚገለጽ በምዕራፍ አምስት ውስጥ የተለያዩ አብነቶች ቀርበው ተመርምረዋል፡፡ በዚህም የሃይማኖቶቹን ትውፊቶች የእርስ በርስ ተራክቦ ጨምሮ፤ በወለኖ ክርስቲያኖቹ ከእስልምናው፤ ሙስሊሞቹ ከክርስትናው ትውፊቶች ጋር በተለያዩ መንገዶች ይገናኛሉ፤ እርስ በርስ ይተሳሰራሉ፡፡ እነዚህ የእርስ በርስ ግንኙነቶችና ትስስሮች በበኩላቸው ወለኔዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችሉ የጋራ እሴቶቹ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ትውፊቶቹ በወለኖ የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

ነገር ግን የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ በወለኖ፤ በምዕራፍ አምስት ውስጥ የተጠቀሱት ትውፊቶች ብቻ አይደሉም፡፡ ባንፃሩ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለኖ በተለያዩ ትውፊቶች አማካይነት ይገለፃል፡፡ ከነዚህ ትውፊቶች መካከል አንዱ የወለኔዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ብሂል ነው፡፡ በዚህ የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ብሂል አማካይነት ወለኔዎቹ በሰላምና በፍቅር በጋራ የመኖር ባህል አላቸው፡፡ በጋራ የመስራት ባህል አላችው፡፡ በጋራ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ባህል አላቸው፡፡ በጋራ የመብላትና በጋራ የመጠጣት ባህል አላቸው፡፡ በጋራ የመደሰትና በጋራ የማዘን ባህል አላቸው፡፡ የዚህ አይነቱ የጋራ ባህል ሥረ-መሰረቱ ደግሞ የወለኔዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር መገለጫ የሆነው የጉርብትና (Neighbourhood) ትውፊት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የምእራፍ ስድስት ዋና ዓላማ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለኖ፤ በወለኔዎች የጉርብትና ትውፊቶች አማካይነት እንዴት እንደሚገለጽ መመርመር ነው፡፡

6.1፡- የሃይማኖት መቻቻል እሴት እና የጉርብትና ትውፊቶች በወለኖ

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ከቀረቡት ዋና ዋና ነጥቦች መረዳት እደሚቻለው ወለኔዎች የተለያዩ የጉርብትና ሥልቶችና ከሥልቶቹ የሚመነጩ በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው፡፡ "ከሩቅ ዘመዴ የቅርብ ጎረቤቴ!" እንዲሉ ወለኔዎች፤ ጉርብትና ለእነሱ መገናኛ መንገዳቸው፤

መተሳሰሪያ ጅማታቸው ነው። በዚህም የውለዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ዘይቤ የተዋቀረው ሃይማኖትን መሰረት በማድረግ ጎራ ለይቶ ሳይሆን፤ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ፣ ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ ጋራ በጉርብትና ተሰባጥሮ ነው። በጋብቻ፣ በአበልጅ፣ በማኅበር፣...ወዘተ እርስ በርሱ ተሳስሮ ነው። ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ እንደሚሉት የጉርብትና ትውፊት በወለዬ፤ ባህል ብቻ ሳይሆን፤ ከሃይማኖታዊው መርህ ጋር የተገናኜ ትውፊት ነው። በዚህ መነሻ ሼህ ዓሊ ሞሐመድ የጉርብትናን ትውፊት የሚገልፁት በሚከተለው ሁኔታ ነው።

> የጉርብትና መነሻችን ከነቢያቶች ያገኘነው ነው። ነብዩ መሐመድ አሉ "የጎረቤትህን ነገር አደራ! ማነም ቢሆን የጎረቤትህን ነገር አደራ!" ይሽነን ቃል መሰረት አደርገን፤ ይሽ ጎረቤት የክርስቲያን ነው፤ ይሽኛው ጎረቤት የእስላም ነው፤ የሚል አድሏዊነት የለም። የጎረቤት ልጆችን እንደባህርያቸው፣ ሚስትን እንደ ባህርይዋ፣ እናት አባትን እንደ ባህር ያቸው አድርጎ በሰላምና በፍቅር የመተዳደር ሃይማኖታዊ ግዴታ አለብን። ጉርብትና ባህል ብቻ አደለም። አብረን ስንኖር ይሽነን መሰረት አድርገን ነው። በዚህ መሰረት እኔ እደቤተሰቦቼ፣ እንደ ልጆቼ አድርጌ ነው፤ ጎረቤቶቼን የምጠብቃቸው። ማንም ይናገር። በዓል በሚመጣበት ጊዜ፣ የዓመት ግብጥ በሚመጣበት ጊዜ መጀመሪያ አካባቢዎቼን እንዲጋበዙ አድርጌ ነው። ይሽ ተያይዞ የመጣ ነው። አሁንም አለ።[181]

ከዚህ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው ውለዬዎች የሃይማኖታዊ፣ የማኅበራዊና የባህላዊ ኑሮ መሰረታቸው ሳይናጋ፣ መከባበራቸውና መተዛዘናቸው ሳይሸረሸር፣ ፍቅራቸውና መተማመናቸው ሳይደበዝዝ ከራማቸውና በረካቸው ሳይርቅ በሰላምና በደስታ በጉርብትና አብረው ይኖራሉ። ወለዬዎች በማኅበራዊ መስተጋብር ብሂላቸው በተለያዩ የጋራ እሴቶች የተሳሰሩ፣ የተገናኙና የተዋሃዱ ናቸው። ለምሳሌ የወለዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር በጉርብትናው፣ በሥጋ ዝምድናው፣ በሃይማኖትና በመጠሪያ ስም ጭምር ሳይቀር የተወራረሰ ነው። በታሪኩ፣ በባህሉ፣ በሃይማኖት ትውፊቱ፣ የተገናኘ፣ የተዋሃደና የተዛመደ ነው። የዚህ ሁሉ መሰረቱ ደግሞ የወለዬዎች የጉርብትና ትውፊት ነው።

በወለዬዎች የጉርብትና ትውፊት መሰረት በር ዘግቶ ጉርብትና የለም። በዚህ ምክንያት በራቸው ለክርስቲያኑም፣ ለሙስሊሙም፣ ለዘመዱም፣ ለባዕዳውም ክፍት ነው። በዚህ መሰረት የራበው "አርሂቡ!" ተብሎ ይገባና ተጋብዞ ይበላል፤ የጠማውም ይጠጣል። የመሸበት እንግዳ ደግሞ ‹‹ቤት ለእንግዳ!›› ተብሎ ይስተናገዳል። በዚህ የተነሳ ራስን ብቻ አለመውደድ ወይም ሌላውን እንደራስ አድርጎ መውደድ የወለዬዎች የጉርብትና ተግባር ነው።

በዚህ መርህ መሰረት ወለዬዎች እንደሚበርደኝ ሌላውንም ይበርደዋል፤ እንደሚቸግረኝ ይቸግረዋል፤ እንደሚርበኝና እንደሚጠማኝ ሌላውንም ይርበዋል፤ ይጠማዋል፤ እንደሚከፋኝ

---

[181] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ግንቦት 8 ቅን 2006 ዓ.ም.መርሳ- 01 ቀበሌ።

ይከፋዋል፤ወዘተ. ብሎ የመፍረድና የህሊና ማስተንተን ባህል አላቸው።[182] ይህም ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ውስጥ መንጭቶ የሚቀዳ የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ደንብና ሥርአት ነው። የዚህ አይነቱ ደንብና ሥርአት በወሎ፤ የማኅበረሰቡ አቋም የሚጠነክርበት፣ የማኅበራዊ ኑሮ መሰረት የሚስፋፋበትና የሃይማኖት መቻቻል እሴት በተግባር የሚገለጽበት ባህል፣ ወግና ልማድ ነው።

ለምሳሌ በወሎ የተጣላ የሚታረቀው፤ በልቡ ቂም የቋጠረ ቂሙ የሚሽረውና ደም የተቃባ ደሙ የሚደርቀው በቅጣት ወይም ብዙ ካሳ በመክፈል ሳይሆን፤ በአንድ ገበታ አብሮ በመብላትና በመጠጣት ነው። ምክንያቱም አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት በወሎ፤ ቦታ አይለው ጠውም፤ ጊዜ አይሽረውም። ወሎዬዎች በዚህ ትውፊታቸው እየተመሩ ልጅ አዋቂ፣ ዘመድ ባዕድ፤ ክርስቲያን-ሙስሊም ሳይሉ ለሁሉም የእንጀራ ሌማታቸውን ይዘረጋለ፤ የመጠጥ ዋንጫቸውን ሞልተው ያቀርባሉ፤ ብሉ እንብላ ጠጡ እንጠጣ ይላሉ። የዚህ አይነቱ ባህል በወሎ የክርስቲያን ሙስሊሙ የጋራ መገለጫ እሴት ነው። ይህም የወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ውጤት ነው።

በዚህ መሰረት የጉርብትና ትውፊት በወሎ፤ የክርስቲያን-ሙስሊሙ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር መሰረት ነው። በመሆኑም ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ፍቅር ይመነጫል። መተባበር፣ መረዳዳት፣ መተዛዘን፣ መተሳሰብና መከባበር ይፈልቃል። በሌላ አገላለፅ ጉርብትና በወሎ፤ የፍቅር ምንጭ ነው። የሰላም አድባር ነው። የቤተሰብና የማኅበረሰብ መሰረት ነው። ጉርብትና በወሎ የመረዳጃ ማዕከል ነው። የትብብር ተምሳሌት ነው። የመግናኛ ድልድይ ነው። የእርስ በርስ መተሳሰሪያ ክር ነው።

ጉርብትና በወሎ የክርስቲያንና የሙስሊም ሕፃናት በጋራ አፈር ፈጭተው፣ ጭቃ አቡክተው፣ ውኃ ተራጭተው፣ የክርስቲያንና-የሙስሊም አዛውንቶችን ተረት-ተረት በጋራ ሰምተው የሚያድጉበት ቀዬ ነው። አበውና እመው የሕይወት ልምዳቸውን፣ ታሪካቸውንና ባህላቸውን ለተተኪው ትውልድ የሚያስተላልፉበት መድረክ ነው። እነሱም በተራቸው በትውልዱ የሚጠወሩበት ቦታ ነው። እንዲሁም "የጎረቤቴ ልጅ-ባልወለደውም ልጄ ነው! ባልወለዳትም ልጄ ናት!" በተመሳሳይ "የእኔ ልጅ ጎረቤቴ የሆነ ሰው ባይወልደውም ልጁ ነው! ባይወልዳትም ልጁ ናት!" በሚለው የወሎዬዎች መርህ መሰረት ሕፃናት በሥነ -ምግባር ተኮትኩተው

[182] The Wollo people are also known to be kind and innocent. This is also indicated by the popular saying "Wollo the barely" (Rukya 2013:31).

የሚያድጉበት፤ ካደጉም በኋላ በሙስሊሙ አባቶችና እናቶች ተመርቀው፣ በተመሳሳይ በክርስቲያኑ አባቶችና እናቶች ተባርከው የሚዳሩበትና የሚኳለሉበት ወይም ለወግ ለማዕረግ የሚበቁበት ሰፊር ነው።

አጋጣሚው የዚህ ተቃራኒ ከሆነም በወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት መሰረት በጋራ ይለቀስላቸዋል፤ በጋራ ይታዘንላቸዋል። በዚህም ወሎዬዎች በጋራ ደግሰው በጋራ ድረዋል፤ በጋራ ለወግ ለማዕረግ አብቅተዋል። በጋራ አልቅሰው በጋራ ቀብረዋል[183]። በዚህ መሰረት የወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት በደስታ ይገለፃል። በሃዘንም ይገለፃል። በሥራ ይገለፃል። በግጭት ወይም በፀብ ይገለፃል። በእለት ተእለት የወሎየዎች የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቶች ይገለፃል። በቅሬ ወይም በእድር ይገለፃል። እነዚህ ሁሉ የእርስ በእርስ ግኙነቶችና የማህበራዊ ኑሮ ትስስሮች በበኩላቸው ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችሏቸው የጋራ እሴቶች ናቸው። በዚህ መሰረት ከዚህ ቀጥለው የቀረቡት አጫጭር ዋና ዋና ነጥቦች የሚያረጋግጡት ይህንኑ ሐቅ ነው።

6.1.1፡- ጉርብትና በደስታ

የደስታ እና የጋራ የሆኑ እሴቶች በወሎ በብዙ አጋጣሚዎች ይገለፃሉ። መጠሪያ ሥያሜያቸው በርካታ ነው። ለምሳሌ ደስታ በሠርግ አማካይነት ይገለፃል። ደስታ በልደት ይገለፃል። ደስታ በዓለማዊና በሃይማኖታዊ ክብረ-በዓላት ሰበብ ይገለፃል። በወሎ ደስታ የሚገለፅባቸው መንገዶች ወይም ምክንያቶች የተለያዩ ቢሆኑም፤ ሁሉም የደስታ መገለጫ እሴቶች ግን በአንድ ነገር ይመሳሰላሉ። ይኸውም ሁሉም የደስታ መገለጫ እሴቶች ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊቶች ጋር የእትብት ያህል ዝምድና ያላቸው መሆኑ ነው። ከወሎዬዎች የጉርብትና ደንብና ሥርአት፤ ከወሎዬዎች ባህል፣ ወግና-ልማድ ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ያህል መሆናቸው ነው። ከነዚህ እሴቶች መካከል አንዱ የወሎዬዎች የሠርግ ትውፊት ነው። የሠርግ ትውፊት በወሎ፤ ከወሎዬዎች ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር በተለያዩ ክሮች የተሳሰረ ነው። ከወሎዬዎችዎ የጉርብትናና ማኅበራዊ መስተጋብር ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው በሰላምና በፍቅር እንድኖሩ የሚያስችል የጋራ እሴት ነው።

---

[183] ዓለሙ ኃይሉ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ግንቦት 10 ቀን 2006 ዓ.ም. መርሳ- 02 ቀበሌ።

6.1.1.1፡- የሠርግ ትውፊት በየጁ ሃዳ[184]

ከላይ እንደተጠቀሰው በወሎ፤ ጉርብትና በደስታ ከሚገለፅባቸው ማኅበራዊና ባህላዊ የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ የሠርግ ትውፊት ነው፡፡ የሠርግ ትውፊት ደግሞ መሰረቱ ጋብቻ ነው፡፡ ጋብቻ በወሎ በክርስቲያኑም ሆነ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ ያለው ማኅበራዊ ተቋም ነው፡፡ ጋብቻ በወሎ እንደሌሎቹ የኢትዮጵያ ክፍሎች ሁሉ የተቀደሰና የተከበረ ቦታ ያለው የወሎዬዎች የማኅበራዊና የባህላዊ እሴት መሰረት ነው፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት የጋብቻ መስፈርት በወሎ የወንዱም ሆነ የሴቷ ቤተሰቦች መልካም ሰውነት፤ ጨዋነት፤ ሚዛናዊነትና ባጠቃላይ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት ወይም ማኅበራዊ ደረጃ (social status) ነው፡፡ ባንፃሩ በወሎ የክርስትና ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆን ግን የጋብቻ መስፈርት የማይሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ለምሳሌ በወሎ የሙስሊም ልጅ የክርስቲያን ልጅ፤ የክርስቲያን ልጅ የሙስሊም ልጅ ታገባለች፤ ያገባል፡፡ በዚህ ሂደት ሙስሊሙ ወደ ክርስትናው ወይም ክርስቲያኑ ወደ እስልምናው ይሄዳል፡፡ አልያም ሁለቱም የየግል እምነታቸውን እንደያዙ በጋብቻ ተጣምረው ሦስት ጉልቻ ይመሰርታሉ፡፡ ወይም ይጋባሉ፡፡ ይህም ማለት በወሎ ባል ወይም ሚስት አንዱ የቄስ ሌላው የሼህ ልጅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በወሎ ለጋብቻ መስፈርት ሃይማኖት የራሱ የሆነ ድርሻ ቢኖረውም፤ የተለያዩ ጥናቶችና የዚህ ጥናት መረጃ አቀባዮች እንደሚገልጹት በወሎ የጋብቻ መስፈርቱ ፍቅር ነው፤ መተማመን ነው፡፡[185] የዚህ አይነቱን እሴት ሞላልኝ ወርቁ የሚገልፁት፤ “በጋብቻ መንገድ ብትሄድ አሁን የኔ ግማሽ ቤተሰቦች ሙስሊሞች ናቸው፡፡ በጎን ደሞ የቀሳውስት ዘሮች ነን፡፡ እኔ አሁን ክርስቲያን ነኝ፡፡ የኔ እህት ግን ሙስሊም አግብታ ሰልማ ልጆቿ በሙሉ ሙስሊሞች ናቸው[186]፡፡” በማለት የራሳቸውን ቤተሰቦች የዘር ሐረግ ጭምር ምሳሌ በመጥቀስ ነው፡፡ አሰፋ አበጋዝ በበኩላቸው በወሎ ያለውን የጋብቻ መስፈርት የሚገልጹት በሚከተለው ሁኔታ ነው፡፡

> በጋብቻ በኩል ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ፤ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጋር ይጋባል፡፡ ይኸ በወሎ ያለና የነበረ የጋብቻ ባህል ነው፡፡ ምናልባት ዘር ይቆጥሩ ይሆናል፡፡ ዘር የሚቆጠሩበት ደሞ ምክንያት አላቸው፡፡ አንዱ ለአጥንት ጉዳይ ሲሉ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በሥጋ ዝምድና የማይገናኙ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ከአጥንት ጉዳይ ጋር ተያይዞ እከሌ ወይ ቡዳ ነው ወይ ድሃ ነው ሊሉ ይችላሉ፡፡ ባጠቃላይ በማኅበረሰቡ መስፈርት የሚባሉ ጉዳዮችን ብቻ

---

184 “የየጁ ሃዳ” አገሩ በሞላ የተስማማበት፤ የሚተዳደርበት፤ የሚገዛበት፤ የወሎዬዎች ደንብና ሥርአት ወይም ባህል፤ ወግና- ልማድ (ዓለ. መሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 4ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አንጦ- 04 ቀበሌ)፡፡

185 It is generalized that the men & women of Wollo are love addicts (Rukya 2013: 31).

186 ሞላልኝ ወረቁ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ግንቦት 9 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- መሐል መቻሬ፡፡

ሊያስቡ ይችላሉ። ከዚህ ውጪ በአጥንቱም በሃብቱም ይመጥናል ለሚለው እስላሙ ለክርስቲያኑ ክርስቲያኑ ለእስላሙ ልጁን ይሰጣል። ይጋባል፤ ይዋለዳል። ይኸ ልዩነት የለውም። የዚህ አይነቱን ባህል ከስማችን መረዳት ትችላለህ።[187]

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው ክርስቲያኑ ለእስልምናው፤ ሙስሊሙ ለክርስትናው ባዕድ ወይም ሩቅ አይደሉም። ምክንያቱም ሙስሊሙ ክርስቲያኗን ያገባል፤ ሙስሊም ትሆናለች። በተመሳሳይ ክርስቲያኑ ሙስሊሟን ያገባል፤ ክርስቲያን ትሆናለች። በዚህ የጋብቻ ትውፊት ወይም የጋብቻ ትስስር መሰረት በወሎ ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ፤ ክርስቲኑ ከሙስሊሙ ጋር በሥጋ ዝምድና ተሳስረው አንድ ሆነው በሠላምና በፍቅር በጋራ ይኖራሉ። ግራዝማች ብሩ ይማም እንደሚሉት በዚህ አይነቱ የጋብቻ ትስስር የተነሳ በወሎ፤ "እስላሙም ክርስቲያኑም ዘሩ አንድ ነው! ከሃይማኖት አንፃርም ከእርድና ከአምልኮ ሥርአታቸው ውጪ የሚለያዩበት ነገር የላቸውም!"[188]

ዮሴፍ ወርቁ የውርጌሳ ከተማ 01 ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት ሙስሊም ወይም ክርስቲያን ሆኖ አንዱ ከሌላው ጋር መጋባት በወሎ፤ ከሁለቱ ተጋቢዎች አልፎ ማኅበረሰቡ አምኖ የተቀበለው የጋራ እሴት ነው። ለዚህም መረጃ አቀባዩ፤ "ይኸ በቤተሰብ ጭምር የታመነ የጋብቻ ባህል ነው፤ በአገራችን በዚህ ውርጌሳ ላይ። ምንም ይነት የእምነት ተቃውሞ የለም። ተጋቢዎቹ የፈለጉትን እምነት መርጠው ጋብቻ ይፈፅማሉ[189]።" በማለት በቅርብ የሚያውቁትን የአካባቢያቸውን ትውፊት ምሳሌ ይጠቅሳሉ። አማኑኤል ሰማው በበኩላቸው በወሎ ያለውን የጋብቻ ትውፊት የሚያብራሩት የራሳቸውን ቤተሰቦችና በቅርብ የሚያውቋትን የጓደኛቸውን የጋብቻ ሁኔታ እንደሚከተለው አብነት በመጥቀስ ነው።

> አሁን የእኔ ጓደኛ አለ። እናቱና ወንድሞቹ ክርስቲያኖች ናቸው። ከክርስቲያን ቤተሰብ ነው የመጡት። የእናቱ ወንድሞች አጎቶቹ በሙሉ ቄሶች ናቸው። የአባቱ ቤተሰቦች ደሞ ሼሆች ናቸው። የእሱን ተወውና የራሴን ምሳሌ አድርጌ ልንገርህ፤ ጉዳዩን ተጨባጭ ለማድረግ። አጎቴ ክርስቲያን ነው። የአጎቴ ልጅ ግን በእናቷ የሙስሊም ዘር ስለሆነች ሙስሊም ናት፤ እናቷን ተከትላ። እኔ ግን ክርስቲያ ነኝ። የእኔን ምሳሌ አድርጌ ነገርኩህ እንጂ፤ ሁሉም የአንድ ቤተሰብ ልጅ ግማሽ ሙስሊም ይሆናል፤ ግማሽ ክርስቲያን ይሆናል። ባልና ሚስቱ አንዱ ከቄስ ሌላው ከሼህ ቤተሰብ የሚሆኑበት አጋጣሚ ብዙ ነው[190]።

መረጃ አቀባዩ በጠቀሱት ምሳሌ መሰረት በወሎ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ግማሽ ሙስሊም ግማሽ ክርስቲያን ሆኖ ይኖራል። ወይም በወሎ ባል ወይም ሚስት አንዱ የቄስ ሌላው የሼህ

---

187 አሰፋ አበጋዝ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ግንቦት 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ።
188 ግራዝማች ብሩ ይማም፤ ቃለ- መጠይቅ፤ ግንቦት 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 01ቀበሌ
189 ዮሴፍ ወርቁ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሳ- 01 ቀበሌ።
190 አማኑኤ ሰማው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ግንቦት 15 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ።

ልጅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህንን አባባል የዚህ ጥናት መረጃ አቀባይ የሆኑት እንድሪስ አህመድ የራሳቸውን ቤተሰብ ምሳሌ በመጥቀስ በተጨባጭ እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

> በአብዛኛው በወሎ ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ ጋር ይጋባል፡፡ ክርስቲያኑም ከሙስሊሙ ጋር ይጋባል፡፡ ከዚያ አንፃር ስትወስድ አሁን እኔ ሙስሊም ነኝ፡፡ ግን የውብዳርና ፍሬሕይወት እሚባሉ ሁለት ሴት ልጆች አሉኝ፡፡ ሁለቱም የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡ ምክንያቱም እኔ ክርስቲያን ስላገባሁ፡፡ እናታቸው ክርስቲያን ስለሆነች፡፡ የባለቤቴ ቤተሰቦች በሙሉ ክርስቲያን የቄስ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ እኔና የእኔ ቤተሰቦች ደሞ በሙሉ ሙስሊሞች ናቸው፡፡ አሁን ልጆቼ ክርስቲያን እናገባለን አሉ፤ ተፈቀደላቸው አገቡ፡፡ እና ይኸ ልዩነት የለውም በዚ በኛ አገር በወሎ፡፡[191]

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው በወሎ በሙስሊሙ በኩል ክርስቲያን ሆኜ ክርስቲያን አገባለሁ ለሚል የሙስሊም ልጅ፤ ምርጫው በቤተሰብ በኩል ይጠበቅለታል፡፡ በተመሳሳይ በክርስቲያኑ በኩል ሙስሊም ሆኜ የሙስሊም ልጅ፤ አገባለሁ ለሚል የክርስቲያን ልጅ ከቤተሰብ ይሁንታ ይቸረዋል፡፡ በዚህ መሰረት በወሎ፤ “ሙስሊም” “ክርስቲያን” ማለት ድንበር አልባ ነው፡፡ አድኖ ተካየ ይህንን ድንበር አልባነቱን የሚገልጹት “ክርስቲያን ሙስሊም ማለት እኮ በዚህ አገር በሆነ አጋጣሚ ክርስቲያን የነበረ ሰው ሙስሊም ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሙስሊም የነበረው በሆነ አጋጣሚ ክርስቲያን ይሆናል፡፡ አጋጣሚው አንደኛ በጋብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በኮከብ ቆጣሪዎች ተነግሯቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ሦስተኛው ከጤና ጋር ተያይዞ ሊሆን ይችላል፡፡”[192] በማለት ወሎ በሥጋ ዝምድና ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት ጭምር የተቀላቀለ ማኅበረሰብ በሰላምና በፍቅር የሚኖርበት አካባቢ መሆኑን በማብራራት ነው፡፡

ድርቤ ካሰው በበኩላቸው ሙስሊምና ክርስቲያን በወሎ በአንድ ቤት ውስጥ እንዴት መኖር እንደሚችል በተጨባጭ ማረጋገጥ ካስፈለገ እኔን ምሳሌ መጥቀስ በቂ ነው፤ ይላሉ፡፡ ለዚህ የሚያቀርቡት ምክንያት ደግሞ፤ “ከእኔ ቤት፤ ከራሴ ብትወስድ እናቴ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ናት፤ ወላጅ እናቴ፡፡ እኔ ግን ሙስሊም ነኝ፡፡ እምንኖረው ግን በአንድ ቤት ውስጥ ነው፡፡ አሁን እናቴን ሲያምብኝ ጊዜ የነፍስአባት ያዥላት አሉኝ፡፡ ቄስ ፈልጌ ያዝኩላት፡፡ ችግር የለም፤ በሰላምና በፍቅር ነው የምኖረው፡፡”[193] የሚል ነው፡፡

ሙስሊም አግብታ ሙስሊም በሆነችው ልጃቸው የሚጠወሩትን የእኒህን መረጃ አቀባይ ወላጅ እናት የዚህ ጥናት አቅራቢ የማየት እድል ገጥሞት ነበር፡፡ ምንም እንኳን አጥኚው አዛውንቷ በእድሜ መግፋትና በህመም ምክንያት አልጋ ላይ ስለዋሉ ቃለ-መጠይቅ ማድረግ ባይችልም፤

---

[191] እንድሪስ አህመድ፣ ቃለ-መጪቅ፣ ሚያዚያ 28 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 03 ቀበሌ፡፡
[192] አድኖ ተካየ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልድያ- 02 ቀበሌ፡፡
[193] ድርቤ ካሳው፣ ቀለ-መጠይቅ፣ ግንቦት 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 05 ቀበሌ፡፡

የእናትና ልጁን ግንኙነት በአንክሮ አስተውሏል። በዚህ መሰረት ሙስሊም ልጅ ለክርስቲያን እናታቸው፤ በተኙበት መኝታ ክፍል ውስጥ የተለያዩ መላዕክት፣ ፃድቃንና ሰማዕታት ምስሎችን ሰቅለውላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ መዝሙረ ዳዊትና የዘውትር ፀሎት መጻሕፍታቸውን በራስጌያቸው አስቀምጠውላቸዋል። መቁጠሪያቸውን በእጃቸውና በአንገታቸው ላይ አስረውላቸዋል። እንዲሁም ዘወትር ጧት፣ ጧት የእናታቸውን የንሥሃ አባት ቄስ በመጥራት ፀበል እያስደገሙ መኝታ ክፍላቸውን ፀበል ያስረጩላቸዋል። ፀሎት ያስደርሱላቸዋል።

ባጠቃላይ በሙስሊም ልጅ እና በክርስቲያን ወላጅ እናት መኖሪያ ቤት ውስጥ ያለው ማኅበራዊ ሕይወት፤ ወሎ ውስጥ ያለውን የሃይማኖት መቻቻል እሴት ወይም የክርስቲያንና የሙስሊም ማኅበረሰብን የእርስ በርስ ግንኙነት በወሎ እንዴት እንደሚገለፅ የሚያስረዳ ምሳሌ ነው። በዚህ መሰረት በወሎ ሙሉ በሙሉ እኔ የክርስትና ሃይማኖት እምነት ተከታይ ቤተሰብ ነኝ ማለት አይቻልም። በተመሳሳይ የእስልምና እምነት ተከታይ ቤተሰብ ነኝ ማለት አይቻልም። ምክንያቱም ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች እንደተገለጸው ወሎዬዎች የሃይማኖት ልዩነት ሳይገድባቸው በጋብቻ የተሳሰሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ናቸው። ዓለሙ ኃይሉ ይህንን እውነታ የሚያረጋግጡት፤ "ለምሳሌ እኔ አጥባቂ ክርስቲያኖች ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ነኝ። ነገር ግን የእኔ የአያቴ እናት የትልቅ ሼህ ልጅ ናት። እዚህ ጉኒ እሚባለው አካባቢ። ሼህ ወለላ ይባላሉ። የእሳቸው ልጅ ናት። በዚህ በወሎ ከእስላም የማይወለድ የለም። ከክርስቲያን የማይወለድም እንዲሁ የለም። ግን በያዝነው እንገፋለን። የያዝነውን ይዘን ግን አንድ ቀንም እንከን የለንም።[194] በማለት ነው።

ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ በበኩላቸው፤ "ይኸ ወሎ፤ የጁ ሲባል የአንድ አባት የአንድ እናት ልጅ ነው። አባቱ ክርስቲያን ሆኖ በእናቱ ወገን እስላም ነው። ስለዚህ በወሎ እስላምና ክርስቲያን በሥጋ፤ በደም፤ በአጥንት፤ በጅማት የተያያዘ ነው።"[195] በማለት የዓለሙ ኃይሉን አስተያየት ይጋራሉ። ዓሊ መሐመድ በሐብሩ ወረዳ ቀበሌ 04 አንጦ ገጠር ቀበሌ ውስጥ የሚኖሩ የ80 አመት አዛውንት ናቸው። አዛውንቱ በመጠሪያ ስማቸው ሙስሊም ይምሰሉ እንጂ፤ በሃይማኖታቸው ግን የክርስትና እምነት ተከታይ ናቸው። መረጃ አቀባዩ ክርስቲያንና ሙስሊም በወሎ በጋብቻ ትስስሩ ምክንያት አንድ አካል አንድ አምሳል መሆናቸውን የሚገልፁት የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን የጋብቻ ሀኔታ እንደሚከተለው ምሳሌ በመግለፅ ነው። "በዚህ አገር እስላም ተክርስቲያኑ ጋር ተጋብቶ ተዋልዶ ነው። ክርስቲያን ሆኖ፣ እስላም

---

[194] ዓለሙ ኃይሉ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ.ም.መርሳ- 02 ቀበሌ።

[195] ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ግንቦት 6 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ።

ዘመዶች አሉት፡፡ እስላም ሆኖ፤ ቄስ ዘመዶች አሉት፡፡ አሁን እኔ ዘመዶቼ ሙስሊሞች ናቸው፡፡ እኔ ግን ክርስቲያን ነኝ፡፡ አሁን ለጆቼ ደሞ እስላም አግብተው ወልደዋል፡፡"[196]

ሌላው የዚህ ጥናት መረጃ አቀባይ በበኩላቸው በወሎ ያለውን የክርስቲያኑንና የሙስሊሙን አማኞች የጋብቻ ትውፊት የሚያብራሩት ሁለቱ አካላት በጋብቻ ከተጣመሩ በኋላ ያለውን የአካባቢውን የጋራ እሴት እንደሚከተለው አብነት በመጥቀስ ነው፡፡

> ወደታች ወደ ሐራ ብትሄድ አሁን ብዙው እስላሙና ክርስቲያኑ ተጋብቶ ነው፤ እምታገኘው፡፡ ለምሳሌ ሚሰቲቱ የሺ የምትባል ክርስቲያን ልትሆን ትችላለች፡፡ ባልዮው ደሞ እንድሪስ የሚባል እስላም፡፡ ታዲያ እስላም ባል የክርስቲያን ሚስቱ ታቦት በምትነግስበት ጊዜ ከሚስቱ ጋር ሄዶ አንግሶ ነው፡፡ ለምሳሌ ሐራ ማርያም እምትባል ቤተክርስቲያን አለች፡፡ እና ሐራ ማርያም በምትነግስበት ጊዜ እስላም ባል ጓደኞቹን "ሰይዲ! ዛሬኮ የነየሺ ታቦት ማርያም ትነግሳለይ! ሆ! ብለን ጨፍረን እናስገባት እንጂ!" ተባብለው፤ ተጠራርተው ነው፡፡ ደስየሚል፡፡ ተጠራርተው ሄደው "እንዴት ነው እንድሪስ ዛሬ!? አዬ! ሄይር ሆኗል! ማርያም በሄይር ገባይ!" እያሉ ነው፤ በፍቅር እሚመለሱት፡፡ ደስ ብሏቸው፡፡ እንደዚህ አይነት ትልቅ እሴት ያለበት አካባቢ ነው፤ ወሎ፡፡ የዚህ ሁሉ መሰረቱ ደሞ ክርስቲያኑና እስላሙ በጋብቻ ቁርኝት በመተሳሰሩ ነው፡፡[197]

ከዚህ በላይ የቀረቡት ርእሰ ጉዳዮች የጋብቻ መስፈርት በወሎ ምን አይነት መመዘኛዎች እንዳሉት የሚገልፁ አብነቶች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት በወሎ ክርስቲያን ወይም ሙስሊም መሆን የጋብቻ መስፈርት የማይሆንበት አጋጣሚ መኖሩን እነዚህ አብነቶች ያረጋግጣሉ፡፡ በመሆኑም የጋብቻ መስፈርት በወሎ፤ የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ ተምሳሌት ነው፡፡ ምክንያቱም በወሎዬዎች የጋብቻ መስፈርት መሰረት ሃይማኖቶቹም ሆኑ የሃይማቶቹ አባቶችና የእምነቶቹ ተከታዮች የልዩነት ምንጭ ሳይሆኑ፤ የመተሳሰሪያና የመገናኛ ምክንያቶች ናቸው፡፡ የአንድነት፣ የመተባበር፣ የመከባበር፣ የመተሳሰብ፣ የመሰባሰብ፣ እንዲሁም የሰላምና የፍቅር ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ የእትብት ዝምድና የሚመሰረትባቸው አብነቶች ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ በወሎዬዎች የጋብቻ መስፈርት አማካይነት ይገለፃል፡፡

ከዚህም ሌላ የወሎዬዎች የሠርግ ሥርአት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ተመሳሳይ ሚና አለው፡፡ በወሎ የሠርግ ሥርአት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ አማካይነት ክርስቲያን-ሙስሊሙ እርስ በርስ ይገናኛል፤ ይረዳዳል፤ ይደጋገፋል፡፡ በወሎ የሠርግ ሥርአት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ አማካይነት ክርስቲያን-ሙስሊሙ አብሮ ይበላል፤ አብሮ ይጠጣል፡፡ በወሎ የሠርግ ሥርአት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ አማካይነት ክርስቲያን-ሙስሊሙ አብሮ ይዝናናል፤ አብሮ ይደሰታል፡፡ በመሆኑም የሠርግ ትውፊት በወሎ የወሎዬዎች የሃይማኖት መቻቻል እሴት በተግባር

---

[196] ዓሊ መሐመድ፤ ቃለ- መጠይቅ፤ ሚያዚያ 7 ቀን 2006 ዓ.ም. ሐብሩ- አንጦ- 04 ቀበሌ፡፡
[197] ሞላንኝ ወርቁ፤ ቃለ- መጠይቅ፤ ሚያዚያ 14 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- መሐል መቻሬ፡፡

የሚገለፅበት ዋነኛ የማኅበራዊ ተቋም መሰረት ነው። ትውፊቱ ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ከዚህ በታች በቀረቡ የሠርግ ትውፍቶች አማካይነት ተተንትኖ ቀርቧል።

6.1.1.1.1፡- የሠርግ ሥርአት በየጁ ሃዳ

ሠርግ በየጁ ሃዳ በክርስቲያኑም ሆነ በሙስሊሙ በኩል ከአራት የማያንሱ ሂደቶች አሉት። መተጫጨት አንደኛው የሠርግ ሂደት ሲሆን፤ ሁለተኛው ሂደት ደግሞ ቀን ቆረጣ ነው። ሦስተኛው ሂደት ዝግጅቱን ጨምሮ፤ የሠርጉን ሥነ-ሥርአት ያካትታል። አራተኛው ሂደት የጫጉላ ጊዜ ነው። በነዚህ ሁሉ ሂደቶች የሁለቱ ሃይማኖት እምነት ተከታዮች እርስ በርስ ይረዳዳሉ፣ ይተጋገዛሉ፣ ይደጋገፋሉ፣ ይተዛዘናሉ፣ ይተሳሰባሉ። ባጠቃላይ የክርስቲያኑ ሠርግ በወሎ ለሙስሊሙም ሠርጉ ነው። በተመሳሳይ የሙስሊሙ ሠርግ በወሎ ለክርስቲያኑም ሠርጉ ነው። ይህንን እውነታ ዮሴፍ ወርቁ የሚገልፁት "በወሎ አንድ ክርስቲያን ወይም አንድ ሙስሊም ሠርግ ሊያሠርግ ሲያስብ ሃምሳ ፐርሰንት ለክርስቲያኑ፣ ሃምሳ ፐርሰንት ለሙስሊሙ ያስባል። ሙስሊም ስለሆነ ለሙስሊሙ ብቻ፤ ክርስቲያን ስለሆነ ለክርስቲያኑ ብቻ አያስብም።"[198] በማለት ነው።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሠርግ በየጁ ሃዳ በተለያዩ መመዘኛዎች የእከሌ-ልጅ ከእከሌ ልጅ ትሻላለች ተብሎ በወንድ ወገን በኩል ከተወሰነ በኋላ፤ ቀጣዩ ሂደት የሚሆነው የመተጫጨት ሥርአት ነው። የመተጫጨት ሥርአት በወሎ፤ "ልጅህን ለልጄ" የሚለውን የወሎዬዎች ነባሩን ባህል ጨምሮ፤ የራሱ የሆነ ባህል፣ ወግና ልማድ፣ ወይም ደንብና ሥርአት አለው። የዚህ ባህል፣ ወግና ልማድ ዋነኛ መገለጫ ደግሞ የሽማግሌ አላላክ ሥርአት ነው።

6.1.1.1.2፡- የሽማግሌ አላላክ ትውፊት በየጁ ሃዳ

ለመሆኑ በየጁ ሃዳ ሽማግሌ ማን ነው? መስፈርቱስ? ለሚሉት ጥያቄዎች የሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ መልስ "በሠርግ ጊዜ እስላሙ ከክርስቲያኑ ቤት ሽማግሌ ሆኖ ይሄዳል። ክርስቲያኖቹ ከእስላሞቹ ቤት ሽማግሌች ሆነው ይሄዳሉ። ደረጃው፣ ማእረጉና ሁኔታው እኩል ነው"[199] የሚል ነው።

---

[198] ዮሴፍ ወርቁ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሳ- 01 ቀበሌ።
[199] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።

በወለዬዎች የሠርግ ሽማግሌ አላላክ መስፈርት መሰረት ወደ ሴት ቤት ሽማግሌ ሆነው የሚላኩት ግለሰቦች ከያታ አንፃር ወንዶች ናቸው። ከሃይማኖት አንፃር ግን ክርስቲያን ወይም ሙስሊም አልያም የሁለቱ ቅልቅል ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ መሰረት በወለዮ የእርኛ ሽማግሌ አላላክ መስፈርት "እነእከሌ-እነእከሌን ሊያሳምኑ ይችላሉ ወይም ጥያቄው ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው እነእከሌ ቢላኩ ነው!" ተብለው የሚገመቱ ሰዎች መሆናቸው ብቻ ነው። በሌላ አገላለፅ የእርኛ ሽማግሌ አላላክ መስፈርት በወለ፤ ሽማግሌ ሆነው የሚላኩት ሰዎች ክርስቲያን ወይም ሙስሊም መሆናቸው ሳይሆን፤ በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ያላቸው ማኅበራዊ ቦታ፣ ደረጃ፣ ተቀባይነትና ተደማጭነት ነው። የእድሜ፣ የሃብትና የሃይማኖት ሁኔታቸው ነው። ይህንን እውነታ ተበጀ መኮንን የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> ወደ ሴቷ ቤተሰቦች የሚላኩ ሽማግሌዎች ጠይቀው እሺ የሚያሰኙ፣ የሚያሳምኑ፣ እነሱ ያመጡት እርኛ በሴቷ ቤተሰቦች ዘንድ እኛን እሚጎዳ አይሆንም ብለው የሚገምቷቸው ሽማግሌዎች መሆን አለባቸው። እነዚህ ሽማግሌዎች በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ የተመሰገኑ፣ በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ተደማጭነት ያላቸው፣ በቤታቸው፣ በሃብትና ንብረታቸው፣ በሥራቸው በሥነ-ምግባራቸውና በሃይማኖታቸው ሁሉ የተሟላ ስብዕና ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል። እነዚህ ሽማግሌዎች እንግዲህ ሙስሊም ወይም ክርስቲያን አልያም የሁለቱ ቅልቅል ሊሆኑ ይችላሉ። ዋናው ነገር ሽማግሌዎቹ የሽማግሌ መስፈርት አሟልተው መገኘታቸው ነው።[200]

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው የሽማግሌ አላላክ ባህል፣ ወግና ልማድ፣ ደንብና ሥርአት በወለ፤ ቀጥታ ግንኙነቱ ከፎክሎር ጋር ነው። ምክንያቱም ትውፊቱ ከማኅበረሰቡ የእለት ተእለት ማኅበራዊ ኑሮና ሥነ-ልቡና ጋር በቀጥታ የተገናኘ ነው። ለምሳሌ የእርኛ የሽምግልና ትውፊት በወለ፤ የያታ ጉዳይ ይወስነዋል። የእድሜ ጉዳይ ይወስነዋል። የሃብት፣ የስልጣንና የዝና ጉዳይ ይወስነዋል። የሃይማኖት ጉዳይም ይወስነዋል። ይህም በፎክሎር ሳይንስ የማኅበራዊ ደረጃ (social status) ጉዳይ ነው። ይህም ማለት ማኅበረሰቡ ለቄስና ለሼህ የሚሰጠው ክብርና ቦታ ለተራው ሰው ከሚሰጠው ክብርና ቦታ ይለያል። ማኅበረሰቡ ለአዛውንቶች ወይም በእድሜ ለገፉ ሰዎች የሚሰጡት ክብርና ቦታ ለወጣቶችና ለጎልማሶች ከሚሰጠው ክብርና ቦታ ይለያል። ማኅበረሰቡ ሃብት፣ ስልጣንና ዝና ላላቸው ሰዎች የሚሰጠው ክብርና ቦታ ለዝቅተኛው የማኅበረሰብ ክፍል ከሚሰጠው ክብርና ቦታ ይለያል።

በዚህ መሰረት የወለዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ ብሂል ወይም ፍልስፍና የተመሰረተው የዚህ አይነቱን ባህል፣ ወግና ልማድ ወይም ደንብና ሥርአት መሰረት አድርጎ ነው። የወለዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ ፍልስፍና በዚህ አይነቱ እሴት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፤ ማኅበራዊ ደንብና

---

[200] ተበጀ መኮንን፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አዲራ።

ሥርአቱ፣ ባህሉ፣ ወግና ልማዱ ሳይናጋ በሰላምና በፍቅር እንዲቀጥል ያደርጋል። አንዱ ለሌላው ባለው አመለካከትና በሚሰጠው ቦታ አማካይነትም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ ተግባራዊ ይደደረጋል። የፎክሎር ማኅበራዊ ፋይዳ ወይም ጥቅሙ የሚለካውም ከዚህ አንፃር ነው። ይህም በወሎዬዎች የሠርግ ሥርአት ወይም የሠርግ ዝግጅት ሂደት የሚገለፅ የጋራ እሴት ነው።

6.1.1.1.3፦ የሠርግ ዝግጅት በየጁ ሃዳ

ሠርግ በየጁ ሃዳ "ሰጠሀ! ተቀበልኩ!" ወይም "ቀን ቆረጣ" የሚባለውን ሥርአት ተከትሎ የሠርግ ዝግጅት ይጀመራል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የሠርግ ዝግጅት በወሎ፤ በግለሰቡ የኢኮኖሚ አቅምና የአካባቢ ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ፤ እንደ ሽምግልናው ሁሉ ክርስቲያኑንና ሙስሊሙን የሚያካትት ትውፊት ነው። ከሠርግ የሥራ ክንውን አንፃር ሙስሊምና ክርስቲያኑ ወንዱ በወንድ፤ ሴቱ በሴት የሚሳተፍበት ሂደት አለ። በዚህ ሂደት የሠርግ ዝግጅቱ የክርስቲያንም ይሁን የሙስሊም፤ ሙስሊም-ክርስቲያኑ በጋራ ይረዳዳል፣ ይተጋገዛል፣ ይተባበራል፣ ይደጋገፋል። ትብብሩም በሃሳብ፣ በጉልበት፣ በገንዘብና በዓይነት ሊሆን ይችላል።

ከጉልበት አንፃር በተለይ በገጠሩ አካባቢ ወንዶች በጋራ ለሠርጉ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ያቀርባሉ፤ የተለያዩ ሥራዎችን ይሰራሉ። ለምሳሌ እንጨት ይፈልጣሉ። የእርድ ሰንጋ ይገዛሉ፤ ያርዳሉ። ዳስ ይሰራሉ። አሳላፊ (አስተናጋጅ) ይሆናሉ። በተመሳሳይ ሴቶቹ ብቅል ይሰብራሉ፣ የጠላ ቂጣ ይጋግራሉ፣ ከምንጭ ወይም ከወንዝ ውኃ በመቅዳት ጠላ ይዘልላሉ፤ ጠጅ ይጥላሉ፤ ቡቅሬ ይጠምቃሉ። እንጀራ ይጋግራሉ፤ ወጥ ይሰራሉ።

የሠርግ ዝግጅት በወሎ፤ በክርስቲያኑም ሆነ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ ያለው የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር መሰረት ነው። ምክንያቱም የሠርግ ዝግጅት በወሎ ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ጋር በእጅጉ ይገናኛል። ከወሎዬዎች የወዳጅ ዘመድ ብሂል ጋር በጥብቅ ይተሳሰራል። በሠርግ ዝግጅት ትውፊት አማካይነት የወሎዬዎች የአብሮነት ባህል የሚፀናውን ያህል፤ የሚላላበት አጋጣሚም ብዙ ነው። በመሆኑም የወሎዬዎች የማኅበራዊ መስተጋብር መሰረት እንዳይላላ፤ በምትኩ የማኅበራዊ መስተጋብራቸው መሰረት እንዲፀና ወሎዬዎች ለሠርግ ዝግጅት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። ይህንንም መርጌታ ቀለመ ዳኛው የራሳቸውን የሠርግ ዝግጅት ምሳሌ በመጥቀስ እንደሚከተለው ያብራሩታል።

> እኔ በራሴ በእድሜዬ ሁለት ልጆች ድሬያለሁ። ስድር እኔ አንዱን በሬ ለሙስሊም ጎረቤቶቼ እንኩ፤ አዘጋጁና የሙስሊም እንግዳ አስተናግዳችሁ እንድትሸኙ ብዬ ሰጥቻለሁ።

> የክርስቲያኑን ለክርስቲያኖች ሰጥቻለሁ፡፡ ሙስሊሞቹ ያነን ራሳቸው ከዚኽው ከእኔ ቦታ በራሳቸው መሳሪያ አርደው፤ ራሳቸው ቀንም ሌሊትም ቆመው ራሳቸው የሙስሊም እንግዳን ከገጠርም የመጣውን ከከተማም የመጣውን የሸኙልኝ እነሱ ናቸው፡፡[201]

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው በክርስቲያን ሠርግ ወቅት ሙስሊም ጎረቤት፤ ክርስቲያን ጎረቤቱን ወክሎ ሁለት ኃላፊነቶችን ይረከባል፡፡ እነዚህም ለሙስሊሙ የሚሆን ምግብ ማዘጋጀትና የተዘጋጀውን ምግብ ለሙስሊም እንግዶች በአግባቡ የማስተናገድ ኃላፊነቶች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት በሠርግ ወቅት ሙስሊም ጎረቤት የክርስቲያን ጎረቤቱን ኃላፊነት መቶ በመቶ ይወስዳል፡፡ ከክርስቲያን ጎረቤቱ የተረከበውን ኃላፊነትም በተገቢው መንገድ ይወጣል፡፡ በክርስቲያኑም በኩል ኃላፊነቱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ምክንያቱም በሙስሊም ሠርግ ወቅት ክርስቲያን ጎረቤት የሙስሊሙን ኃላፊነት ወስዶ ምግብ ያዘጋጃል፤ ክርስቲያን እንግዶችን ያስተናግዳል፡፡ አደራውንም በተገቢው መንገድ ይወጣል፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ምሳሌ በወንዶች በኩል ያለውን ኃላፊነት የሚገልጽ ነው፡፡ በሴቶች በኩል ያለው ኃላፊነትም ተመሳሳይ ነው፡፡ በሴቱ በኩል ያለውን ኃላፊነት ደግሞ አስካለ አበበ የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው፡፡

> በሠርግ ጊዜ ክርስቲያኑም ዳረ፤ እስላሙም ዳረ ያው ካለው ከበርበሬው፣ ከቅቤው፣ ከዘይቱ፣ ከቅመማ ቅመሙና ከሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ተከፍሎ ይሰጣል፡፡ ሥጋው ይታረዳል፡፡ ከዚያ የሥራውን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ወስደን ምግቡን እናዘጋጃለን፡፡ ይኸ በሙስሊሙም ሆነ፤ በክርስቲያኑ ልዩነት የለውም፡፡ ኃላፊነቱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ያነ ልጅ ተድሮ፤ ወይም ያቺ ልጅ ተድራ ሠርጉ እስከሚወጣ እቃው እስቲመለስ ድረስ ያው እንደባለቤት ሁነን ነው የምንሰራው፡፡ እናም በክርስቲያኑም ሆነ በሙስሊሙ በኩል ያለ ጎረቤት እኔ እንደዚህ ነኝ በልቼ ልውጣ ሳይል፤ እንግዳ ይሸኛል፡፡ ኃላፊነት አለበት፡፡ ኃላፊነቱን ተቀብሎ ኃላፊነቱን መወጣት ግዴታ አለበት፡፡[202]

በጥቅሱ የተነሱ የጋራ እሴቶችን ድርቤ ካሳው በተመሳሳይ እንደሚከተለው ያብራሯቸዋል፡፡

> የክርስቲያኑ ሠርግ ሲሆን፤ እኛ ሙስሊሞቹ የሙስሊሙን ምግብ እንሰራለን፡፡ ሠርጉ የኛ ከሆነም እነሱ ይሰራሉ፡፡ እርዱ ለየራሳችን ይሰጣል፡፡ ከዚያ እቃችንን አዘጋጅተን እንሰራለን፡፡ ምንም ችግር የለውም፡፡ ሌላው ቢቀር ሙስሊሙ እንኳን ቀረት ቢልብን ክርስቲያኖቹ አብረው ሽንኩርት ያካትፋናል፡፡ እኛ ካነስን ማለት ነው፡፡ የነሱንም ሥራ እኛ ገብተን እንሰራለን፤ እነሱ ካነሱ ማለት ነው፡፡ እና ያለምንም ችግር ተረዳድተን እንግዶቻችንን እንሸኛለን፡፡[203]

ከላይ በቀረቡት ጥቅሶች እንደተብራራው የወሎዬዎች የጉርብትና ባህል የሚገለፀው በዚህ አይነቱ የመረዳትና የመደጋገፍ፣ የመተዛዘንና የመተሳሰብ፣ አንተ-ትብስ፣ አንቺ-ትብሽ የመባባል እሴት ነው፡፡ የመከባበር፣ የመቀራረብና እርስ በርስ የመተሳሰር ባህል ነው፡፡ ከላይ በቀረቡት

---

201 መሪጌታ ቀለሙ ዳኛው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሳ- 01 ቀበሌ፡፡
202 አስካለ አበበ፣ ቃለመጠይቅ፣ ነሐሴ 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ፡፡
203 ድርቤ ካሳው፣ ቃለ- መጠይቅ፣ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ፡፡

ሁለት ጥቅሶች ውስጥ ከተገለፁት የመረዳዳት እሴቶች በተጨማሪ በሠርግ ወቅት በወሎ፤ ክርስቲያኑ ሲያሠርግ ለሙስሊሙ የሚያስፈልገውን ነገር አሟልቶ ማቅረብ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ ሙስሊሙ ሲድር ለክርስቲያኑ የሚያስፈልገውን ነገር አሟልቶ ማቅረብ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ባንፃሩ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት "ሙስሊም ከሆነ እሚድረው ለክርስቲያኑ ቆባ ያለ ነገር (ተለቅ ያለ፤ በዛ ያለ ነገር) ይሰጣል፡፡ ክርስቲያንም ከሆነ እሚድረው ደግሞ ለሙስሊሙ ቆባ ያለ የእርድ እንስሳ ይሰጣል፡፡"[204] በማለት ነው፡፡ ይህ እንግዲህ በወሎ ያለውን የመከባበርና የመተዛዘን እሴት የሚገልጽ አብነት ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወሎ ክርስቲያንና ሙስሊሙ በጉርብትና ተሰባጥሮ የሚኖር ማኅበረሰብ ነው፡፡ ነገር ግን የወሎዬዎች የአኗኗር ዘይቤ በጉርብትና ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ባንፃሩ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በቤተሰብ ወይም በዝምድና ጭምር የተሳሰረ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከክርስቲያኑ ሠርግ ሙስሊሙ፤ ከሙስሊሙ ሠርግ ክርስቲያኑ ሊገኝ ግድ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የሠርግ ሥርአት በወሎ፤ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የማኅበራዊ መስተጋብር መሰረት የሆነ የጋራ እሴት ነው፡፡ ልዩነቱ በእርድ፤ እርዱ በሚዘጋጅበት እቃና በአመጋገቡ ብቻ ነው፡፡ ከአመጋገብ አንፃር በሠርግ ጊዜ በአንድ ዳስ ውስጥ ሆኖ፤ ነገር ግን ቦታ ተለያይቶ የክርስቲያን ለብቻ፣ የሙስሊሙ የብቻ ነው፡፡ በዚህ ሂደት "አንዳይነካካ!" የሚለው የወሎዬዎች የጥንቃቄ ብሂል አለ፡፡ ከዚህ ባለፈ ከምግብ በኋላ ያለው የሠርግ ሥነ-ስርአት ግን በጋራ የሚከወን ነው፡፡

በእርድና በአመጋገብ ሥርአት ብቻ የክርስቲያንና የሙስሊም ሠርግ ተብሎ የሚለየው የወሎዬዎች የሠርግ ሥርአት ከምግብ በኋላ የጋራ የሆኑ በርካታ ትውፊቶች አሉት፡፡ ከነዚህ ትውፊቶች መካከል አንዱ እየጠጡ የመጫወት፣ የመዝፈንና የመጨፈር ሂደት ነው፡፡ የመሸለልና የመፎከር ትዕይንት ነው፡፡ ትዕይንቱን የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው፡፡

> በሠርግ ጊዜ የየራሳቸውን ምግብ ከበሉ በኋላ ወደ ዳስ ነው የሚገቡት፡፡ ከዚያ እየተጠጣ ዘፈን ይጀመራል፡፡ ሠርጉ የክርስቲያንም ሆነ የእስላም ጨዋታው፣ ጭፈራው፣ ዘፈኑ ተመሳሳይ ነው፡፡ የዘፈኑ ግጥም ተመሳሳይ ነው፡፡ የእስክስታው አይነት ተመሳሳይ ነው፡፡ የሽለላና የፉከራው አይነትና ግጥም ተመሳሳይ ነው፡፡ ለእስላም ሠርግ የሚዘፈን፤ ለክርስቲያን ሠርግ ተብሎ እሚዘፈን ዘፈን እሚባል ነገር የለም፡፡ ባህሉ ተመሳሳይ ስለሆነ ሁሉም ዳስ ውስጥ ገብቶ ይዘፍናል፤ ይጨፍራል፤ ይሸልላል፤ ይፎክራል፤ ይጫወታል፤ ይዝናናል፡፡ በሠርግ ላይ ጥሩ ድምፅ አለው ከተባለ ክርስቲያኑም ሆነ እስላሙ ይዘፍናል፤ ይሸልላል፡፡ ችሎታ ያለው ማንም ሰው ተነስቶ እስክስ ይላል፡፡ ማንም ሰው ተነስቶ

[204] በሪሁን ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ ቁጥር 14 ቀበሌ፡፡

ደስታውን ይገልጻል፤ እዚያ ዳስ ላይ። ባጠቃላይ ሁሉም ይጫወታል። ይዝናናል። የዳረውንም ግለሰብ ያስደስታል።[205]

ከላይ እንደተጠቀሰው በወሎ በሠርግ ጊዜ ለሙስሊሙ ለብቻ ይታረዳል። ለክርስቲያኑም ለብቻ ይታረዳል። የክርስቲያኑና የሙስሊሙ የመመገቢያ እቃም የተለየ ነው። ዝግጅቱንም ሁለቱም የየራሳቸውን ወይም በጋራ ያዘጋጁታል። ነገር ግን ለምግቡም ሆነ ለመጠጡ ዳሱ አንድ ነው። ልዩነቱ የሚመገቡበት ቦታ የክርስቲያኑ ለብቻ፣ የሙስሙ የብቻ መሆኑ ነው። መጠጡ፣ ዘፈንና ጭፈራው ግን የጋራ ነው።

የሠርግ ትውፊት በወሎ የሠርጉን ባለቤትና የሠርጉን ታዳሚዎች ማስደሰቱና ማዝናናቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ካሉት በርካታ ማኅበራዊ ፋይዳዎች መካከል አንዱ፤ በተለይ ለባለቤት፣ ለዘመድ አዝማድና ለጎረቤት ጭምር ዝና በማጎናጸፍ የኩራት ምንጭ መሆኑ ነው። ከዚህ አንፃር በወሎ "ድል ባለ ሠርግ!" ስምና ዝና ማትረፍ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም ምኞት ነው። ባህልም ነው። የሚከተለውን ጥቅስ ከሙስሊሙ የሠርግ ትውፊት አንፃር ለአብነት እንመልከት።

አሁን በዚህ በቆላው አካባቢ ስትሄድ ጠላ ጠምቆ ሠርግ የማያሠርግ ሙስሊም አታገኝም። ሙስሊሙ ልጁን ሲድር "እኔማ ጠላዬን ጠምቄ፣ ዘመድ አዝማዴን ቀላቅዬ እንደው ዘፍኜ ካልዳርኩ ምኑን ዳርኩት!" ነው እሚሉት። በሠርጉ እለትም ሙስሊሙ ጠላውን ጠጥቶ "ወላሂ! በጣም ቆንጆ ጠላ!" እያለ ነው፤ እሚመለሰው። ምክንያቱም ባህሉ ከጥንት ጀምሮ የኖረ ባህል ነው። ከሃይማኖቱ አንፃር ተሸማቆ ወይም እንትና ይከለክለኛል ብሎ ሳይሆን፤ ባህሌ ነው፤ ወጌ ነው፤ ያኖረኝ ነው፤ ያደግኩበት ነው። ከክርስቲያኑ ጋር ያኖረኝ ባህል፣ ወግና ልማድ ነው፤ በፍቅርና በሰላም እንድኖር ያደረገኝ ደንብና ሥርአት ይሄ ነው፤ ብሎ ነው ቀጥሎበት የሚኖረው።[206]

በዚህ ጥቅስ መሰረት በወሎ ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ ጠላ ጠምቆ፣ ጠጅ ጥሎ፣ ቡቅሬ አዘጋጅቶ፣ ሠርግ ማስረግ ባህሉ ነው። ወግና ልማዱ ነው። መላኩ ተገኘ እንደሚሉት ከሠርግ ድግስ ጋር በተገናኘ አንድ ገጠመኝ አላቸው። ገጠመኛቸውን፤ "እዚህ ወልዲያ ሙ.ጋድ አካባቢ ሃጂ ወርቁ እሚባል ሰው ነበረ። እስላም ነው። ጠጅ ጠምቆ ልጅ ድሮ፤ እስላም ክርስቲያኑ ጠጅ ከመጠጣቱ ብዛት የተነሳ ተሳከረ፤ ተሰካከረ። ብዙ ሰው ሰክሮ በየቦታው ወደቀ። እስላም የለ፤ ክርስቲያን የለ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በእስላሙ በኩል በዚህ በወልዲያ ቡቅሬ እንጂ፤ ጠላ እንዳይጠመቅ፣ ጠጅ እንዳይጠመቅ ተባለ።"[207] በማለት ያስታውሱታል። አስካለ አበበ

---

[205] ደሳለ ፈንታው፤ ቃለ-መጠቅ፣ ሚያዚያ 28 ቀን 2006 ዓ.ም. ራያና ቆቦ ወረዳ- አራዶም።
[206] ሞላልኝ ወርቁ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ሚያዚያ 14 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- መሐል መቻሬ።
[207] ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፣ ቀለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 6 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ 04 ቀበሌ።

በበኩላቸው ያለፈውን ዘመን የሚያስታውሱት "የዛሬን አያድርገውና በሠርግ ጊዜ ብርዙን እምንጠጣው ከእስላሞቹ ቤት ነበረ!"[208] በማለት በትዝታ ወደኋላ ተጉዘው ነው።

ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ በወሎ ለሠርግ ዝግጅት ጠላ የሚጠምቀው፣ ጠጅ የሚጥለው፣ ቡቅሬ የሚያዘጋጀው በአካባቢው ትውፊት መሰረት ጠጥቶ ለመዝናናት፣ ለመዝፈንና ለመጨፈር ብቻ ሳይሆን፤ ለወሎዬዎች የሠርግ "አደጌር" ትውፊት ሲባል ጭምር ነው። ወይም ብድር ለመመለስ ነው። አንዳንድ ጊዜም ስምና ዝና ለማትረፍ ከመሻት ጭምር የሚመነጭ ነው። ከለጋስነትና ከእንግዳ ተቀባይነት የወሎዬዎች ባህል ጋር የሚገናኝ ትውፊት ነው። ከመረዳዳት፣ ከመደጋገፍና ከመከባበር ስሜት ጋር የተሳሰረ ነው። የዚህ አይነቱን እሴት ዓለሙ ኃይሉ የሚገልጹት የራሳቸውን ገጠመኝ ምሳሌ በመጥቀስ ነው።

መረጃ አቀባዩ እንደሚሉት እሳቸው ልጃቸውን ሲድሩ የጠመቁት ስድስት ጋን ጠላ ብቻ ነው። ባንፃሩ አስራ ሁለቱን ጋን ጠላ የጠመቁት ሙስሊም ጎረቤቶቻቸው ናቸው።[209] መረዳዳቱና መደጋገፉ ከቤተሰብ አንፃር ሲሆን ደግሞ፤ ክርስቲያኑ ለሙስሊም ዘመዱ ወይም ሙስሊሙ ለክርስቲያን ዘመዱ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። የዚህ አይነቱን የመረዳዳትና የመደጋገፍ፣ የመተዛዘንና የመተሳሰብ እሴት የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት "እኔ ልድር ከሆነ ሙስሊሟ እህቴ ሁለት ጋን ጠላ እኔ ችያለሁ! ከመቶ እንጀራ ጋር ትላለች። ከባሏ ጋር ደሞ ‹አንድ በግ ይበቃው ይሆን አሊዋ !› ተባብለው ያነን አሰናድተው ነው፤ ይዘው የሚመጡት እንጂ፤ የተዳረው ክርስቲያን ነው፤ የተዳረው ሙስሊም ነው፤ እኔ ምን አገባኝ አይሉም።"[210] በማለት ነው።

በሌላ በኩል በወሎ በሠርግ ጊዜ ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ በልቶ ጠጥቶ የሚዘፍነው፣ የሚጨፍረውና እስክታ የሚወርደው ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የሠርጉን ባለቤት ለማስደሰት፣ ለማሞገስ፣ ዳሱን ለማሞቅና ለማድመቅ ነው። በዚህ መሰረት በወሎ ከክርስቲያኑም ሆነ ከሙስሊሙ ዳስ ወይም ሠርግ ይዘፈናል፣ ይጨፈራል፣ ይሸለላል፣ ይፎከራል። በዚህ ሂደት ክርስቲያኑም-ሙስሊሙም ዘፈን፣ ጭፈራ፣ ሽለላና ፉከራ እስከቻለ ድረስ ይዘፍናል፣ ይጨፍራል፣ እስክስታ ይወርዳል፣ ይሸልላል፣ ይፎክራል።

---

208 አስካለ አበበ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ።
209 ዓለሙ ኃይሉ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 02 ቀበሌ።
210 ሞላልኝ ወርቁ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 14 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልድያ-መሐል መቻሬ።

ከዚህ አንፃር የሠርግ ዘፈን በወሎ፤ በሥራ እንደ መረዳዳቱና መተጋገዙ፣ አብሮ እንደ መብላትና አብሮ እንደመጠጣቱ ሁሉ፤ የባለ ሠርጉን ዳስ የማሞቅና የማድመቅ ኃላፊነቱም የጋራ ነው፡፡ የሠርግ ዳስ ማሞቅና ማድመቅ ደግሞ የደስታ መገለጫው የመጨረሻ ደረጃ ነው፡፡ ይህም ስለሆነ "ሠርጌን እነእከሌ አሞቁልኝ! አደመቁልኝ!" በማለት ባለቤት ስሜቱን ይገልፃል፡፡ ከዚህ አንፃር የሠርግ ደስታ ወይም የሠርግ ዘፈንና ጭፈራ በወሎ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ እሴት ነው፡፡ ያሲን ፍሬው ይህንን የጋራ እሴት እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> በሠርግ ጊዜ ኃብቻው በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው፤ ሃይማኖታዊ ኃብቻ ካልሆነ በስተቀር፤ ባህላዊ ኃብቻዎች ላይ ዘፈን ይዘፈናል፡፡ ቀረርቶዎች፣ ሽለላዎች፣ ፉከራዎች አለ፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በሙስሊሙም፣ በክርስቲያኑም ማኅበረሰብ ዘንድ እሚዘፈኑ የሠርግ ዘፈኖች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በወንዱም በሴቱም እሚዘፈኑ የሠርግ ዘፈኖች ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የዘፈኖቹ፣ የሽለላዎቹና የፉከራዎቹ ግጥሞች ከሙሽራው አንፃር ሊገጠሙ ይችላሉ፡፡ ከሙሽራይቱ አንፃር ሊገጠሙ ይችላሉ፡፡ ከሙሽሮቹ ቤተሰቦች አንፃር ሊገጠሙ ይችላሉ፡፡ ባጠቃላይ ከሠርጉ ሁኔታ አንፃር ሊገጠሙ ይችላሉ፡፡ ታዳሚው ደስ ሲለው እየተነሳ የሚፎክርበትና የሚሸልልበት፣ የሚዘፍንበትና እስክስታ የሚወርድበት አጋጣሚ አለ፡፡ ይኸ ባህሉ የወሎ ባህል ነው፡፡ የወሎ ባህል ደግሞ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ ባህል ነው፡፡ ስለዚህ የሠርግ ዘፈን የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው፡፡[211]

አበጋር ማዱ በላይ በያሲን ፍሬው አስተያየት ሙሉ በሙሉ ይስማማሉ፡፡ ለዚህም ከዛሬ 64 አመት በፊት እሳቸው ተኩለው ሲዳሩ በእናትና በአባታቸው ዳስ ውስጥ የነበረውን የሠርግ ትእይንት አሁንም ድረስ አይዘነጉትም፡፡ ለምሳሌ በወቅቱ ከተገጠሙ የዘፈን፣ የቀረርቶና የሽለላ ግጥሞች መካከል እናትና አባታቸውን ለማሞገስ ተብለው የተገጠሙ ግጥሞችን እንደሚከተለው ያስታውሷቸዋል፡፡

አባባየ-ኧረ-አባባ በላይ ከፍ በል ቸፍ በል
አሳላፊው ቅዳ ግንቦኛው ለግስ
አባባ ከፍ በል እንደ ጊዮርጊስ

ትድሩ እንደሆነ እንደ በላይ ዳሩ
ባንዳንድ ጋን ጠላ ሰው አታስቸግሩ

ኧረ-አባባየ-ያ በላይ አድማሱ ያነን ቀይ በሬ ንጥር ቅቤ አውጠው

---

[211] ያሲን ፍሬው፣ ቃለ-መጠቅ፣ ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- 03 ቀበሌ፡፡

እሱ ቢያርሰው አደል እሚያቅበጠብጠው

ያ በላይ አድማሱ እየው ቅንነቱ
ትናንት ሲዘንብ ውሎ ዛሬ ማባራቱ
የመሸራው አባት ቅዳበት በቦይ
ዓባይና ጣና አይደለህሞይ

በወዳድል በሬ ወትውቶ ወትውቶ
ይቀዳው ጀመረ በርሚሉን ጎልቶ

ሽልሙነ፣ ሽልሙነ ሽልማት ደግ ነው
ሽልማቱ ለኛ ሥሙ ለናንተ ነው

ስጠው ብረት የተወለወለ፤ ስጠው ብረት የተወለወለ
ልጁም የኮራ ነው የተንጠበለለ

የመሸራው እናት ቁማ ተጠየቂ
የጠመቅሽው ጠላ ጠጅ ነው አረቂ

የመሸራው እናት ይሽነን ጠላሽን ማን ነው ማር ያላሰው
ድውይ ይፈውሳል ለደጋግመው ሰው
አበድነ ሰከርነ በገዛ ጠላችን
የመሸራው እናት ጠምቃው እናታችን

ሴቶች ተሰባስበው ሙያ ሲቋጠሩ
የመሸራው እናት በላይ ትሁን አለ.[212]

---

[212] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ።።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የሽለላ ስንኞች መረዳት እንደሚቻለው የግጥሞቹ ፋይዳ የድግሱን ማማር፣ የድግሱን ስፋት፣ የደጋሾቹን ለጋስነት፣ የደጋሾቹን ክብርና ሞገስ የሚያንፀባርቁ ግጥሞች ናቸው። ለዚህም ነው ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የወሎ ሰው ልጁን ሲድር "እኔማ ጠላዬን ጠምቄ ዘመድ አዝማዴን ቀላቅዬ እንደው ዘፍኜ ልጄን ካልዳርኩ ምኑን ዳርኩት!" የሚለው። እንዲሁም ባለ ሠርጉ ሙስሊም ሆነው ሳለ ሙግሳ የሚቀርብላቸው፤ "አባባ ከፍ በል እንደጊዮርጊስ!" ተብሎ ነው። ይህም ክርስትናው ለሙስሊሙ ያለውን ቅርበት የሚገልፅ ነው። ጠጅና ጠላ መጥመቁም ቢሆን የሙስሊሙም የጋራ እሴት በሆኑን ከሽለላ ግጥሞቹ መረዳት ይቻላል።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ በቀረቡት የወሎዬዎች የሠርግ ትውፊት አብነቶች መሰረት የሁለቱ ሃይማኖት እምነት ተከታዮች በወሎ፤ ከሚለያዩባቸው ጉዳዮች ይልቅ፣ የሚተሳሰሩባቸው ክሮችና የሚገናኙባቸው መንገዶች እጅግ በርካታ ናቸው። በዚህም ወሎዬዎች የራሳቸውን እምነት ጠብቀው፤ የሌሎቹንም አክብረው፣ የጋራ በሚያደርጓቸው የማኅበራዊ ኑሮ መሰረቶች ላይ ግን የሰምና የፊትል ያህል ናቸው።

በዚህ አይነት የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር አማካይነት ወሎዬዎች ክርስቲያን ሙስሊም ሳይሉ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸውና ከጎረቤቶቻቸው ጋር በመተዛዘን፣ በመተሳሰብ፣ በመረዳዳት፣ በመደጋገፍ፣ በመከባበር፣ በሰላምና በፍቅር አብረው ይኖራሉ። አብረው ይሰራሉ፣ አብረው ይበላሉ፣ አብረው ይጠጣሉ። አብረው ይዝናናሉ፣ አብረው ይደሰታሉ። የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ የሚገለፀውና የሚሰራው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር አማካይነት ነው። በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ በወሎዬዎች የሠርግ ሥርአት (ትውፊት) ይገለፃል።

ከወሎዬዎች የሠርግ ትውፊት ጋር በተገናኘ ሌላኛው የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ በወሎ፤ የሚዜ ትውፊት ነው። የሚዜ ባህል፣ ወግና ልማድ በወሎ፤ በርካታ መመዘኛዎችና ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ፋይዳዎች አሉት። እነዚህ መመዘኛዎችና ማኅበራዊ ፋይዳዎች በበኩላቸው ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋር ጥብቅ ትስስር አላቸው። የዚህ ንዑስ ርዕስ ዋና ዓላማም የሚዜ ትውፊት በወሎ፤ ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋር በወሎ ያለውን ግንኙነትና ማኅበራዊ ፋይዳ መርምሮ መግለፅ ነው።

6.1.1.1.4፡- የሚዜ (የጫጉላ) ትውፊት በየጁ ሃዳ

የጋብቻ መስፈርት፤ የሠርግ ሥርአት ወይም ባህል፣ ወግና ልማድ በወሎ፤ ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት እና ማኅበራዊ መስተጋብር ጋር ያለው ትስስር ከዚህ በላይ በቀረቡት ዋና ዋና ነጥቦች አማካይነት ተገልጿል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ደግሞ የሚዜ ትውፊት በወሎ፤ ከወሎዬዎች የጉርብትና ብሂልና የማኅበራዊ ኑሮ ዘይቤ አንፃር ያለው ቁርኝት ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት በወሎ ሚዜ የሚመሰረተው በዋናነት በአንድ አካባቢ አብሮ በማደግ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በአንድ አካባቢ ተወልደው ያደጉና እርስ በርስ የሚግባቡ፣ በተመሳሳይ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙና ቁጥራቸው ከ10-15 ወይም ከ20-30 ሊደርስ የሚችል ወጣቶች ተሰባስበው ሚዜ ይመሰርታሉ፡፡[213] እነዚህ ወጣቶች በአንድ አካባቢ አፈር ፈጭተው፣ ውኃ ተራጭተው፣ ልዩ ልዩ የልጅነት ጨዋታዎችን በጋራ ተጫውተው፣ የማይረሳ የልጅነት ጊዜ ትዝታ በጋራ አሳልፈው ለአቅመ ሃዳም ሲደርሱ ወይም ለመዳር-ለመኳል ወይም ለወግ-ለማዕረግ ሲደርሱ ሚዜ ይመሰርታሉ፡፡

በወሎ የጉርብትና ትውፊት መሰረት የክርስቲያኑም ሆነ፤ የሙስሊሙ ልጅ የሚያድገው አብሮ ነው፡፡ አጠቃላይ ማንነቱ የሚቀረፀው በክርስቲያኑና በሙስሊሙ የጋራ በሆነው የወሎዬዎች ቀየ (መንደር) ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ የሙስሊሙ ልጅ ለክርስቲያኑ ልጅ፤ የክርስቲያኑ ልጅ ለሙስሊሙ ልጅ አብሮ አደግ ጓደኛው ወይም የልብ ባልንጀራው ነው፡፡ ይህም ማለት የሙስሊሙ ልጅ ባልንጀራ የክርስቲያኑ ልጅ ነው፡፡ በተመሳሳይ የክርስቲያኑ ልጅ ባልንጀራ የሙስሊሙ ልጅ ነው፡፡ በመሆኑም በወሎ የክርስቲያኑ ልጅ ሚዜ ሙስሊሙ ነው፡፡ የሙስሊሙ ልጅ ሚዜ ክርስቲያኑ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ሚዜ በወሎ የሚመሰረተው አብሮ አደግ ወይም የልብ ባልንጀራ በሆኑ የክርስቲያንና ሙስሊም ወጣቶች ነው፡፡ ይህንን እውነታ ሞላልኝ ወርቁ የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው፡፡

> በዚህ አገር ሚዜ የሚመሰረተው በዙሪያዬ አብረን ያደግነው ሙስሊሙም ክርስቲያኑም ነው፡፡ ምክንያቱም ከሕፃንነት ጀምሮ አብሮ አደግ ጓደኞቼ እነሱ ናቸው፡፡ በኋላ ሚዜ የሚሆኑኝም እነሱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ሙስሊሙም ክርስቲያኑም ናቸው እንጂ ሚዜ የሚሆኑኝ፤ ሙስሊም ነው እሱ ከክርስቲያን ሚዜ አናስገባውም፤ ክርስቲያን ነው እሱ ከሙስሊም ሚዜ አናስገባውም አይባልም፡፡ ባህሉም አይፈቅድም፡፡ እንዲያውም ሌላውን ተወውና ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ፤ ሙስሊሙ ለክርስቲያኑ ሥር-ሚዜ ሁሉ ይሆናል፤ አይደለም አጃቢ ሚዜ፡፡ እንደ አስተዳደጉ፣ እንደ ቀረቤታው፣ እንደ ፍቅሩ ነው፡፡ በሴቷም

---

[213] ደሳለ ፈንታው፣ ቃለ- መጠይቅ፤ ሚያዚያ 28 ቀን 2006 ዓ.ም. ራያና ቆቦ ወረዳ- አራዶም፡፡

> በኩል ባህሉ፣ ወግና ልማዱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህም ማለት የወንዶቹ ሚዜ ትውፊት መመዘኛዎች ለሴቶቹም ተመሳሳይ ናቸው፡፡[214]

በዚህ ጥቅስ መሰረት በወሎ ዓለማዊ ለሆነው የጋብቻ ባህል፣ ወግና ልማድ ለሚከናወን የጋብቻ ሥርአት ሚዜ ሃይማኖትን መሰረት አድርጎ አይመሰረትም፡፡ ባንፃሩ ሙሽራው ሙስሊም ሆኖ፣ ክርስቲያን ሚዜዎች ይኖሩታል፡፡ በተመሳሳይ ሙሽራው ክርስቲያን ሆኖ፣ ሙስሊም ሚዜዎች ይኖሩታል፡፡ የዚህ አይነቱን ትውፊት በሪሁን ይመር የሚገልጹት "ለምሳሌ እኔ ሳገባ አስራ ስምንት ሚዜዎች ነበሩኝ፡፡ ከአስራ ስምንቱ ሚዜዎች ውስጥ አስሩ ሙስሊሞች ነበሩ[215]፡፡›› በማለት በተግባር የሚያውቁትን እውነታ በመጥቀስ ነው፡፡ ከቁጥር አንፃር ደግሞ ለክርስቲያኑ ሙስሊሙ፣ ለሙስሊሙ ክርስቲያኑ ሊበዛ ወይም ሊያንስ ይችላል፣ አለያም መሳ ለመሳ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም የሚያሳየው ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ የቁጥር መስፈርት በወሎ የሚዜ ትውፊት ውስጥ አለመኖሩን ነው፡፡ ባንፃሩ በወሎ የሚዜ መስፈርት አብሮ አደግነት፣ ባልንጀርነትና የእድሜ እኩያነት መሆኑን የሚገልጽ ምሳሌ ነው፡፡

የሚዜ ትውፊት በወሎ ከባለንጀርነት ወይም ከአብሮ አደግነት ባለፈም፣ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ በሥጋ ዝምድና የተሳሰረ ስለሆነ አንዱ በሌላው እየተሳበ ሙስሊሙ ለክርስቲያኑ፣ ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ ሚዜ ይሆናል፡፡ ይህንን አባባል መሪጌታ ቀለሙ ዳኛው የሚገልፁት "ሃይማኖት በልብወለድ ይሄዳል፡፡ እንደ ፍላጎቱ የእናቱን ሃይማኖት፣ የአባቱን ሃይማኖት ትቶ የፈለገውን ሃይማኖት ሊይዝ ይችላል፡፡ እኔ ለምሳሌ ቄስ ነኝ፡፡ የእኔ ልጅ ሄዶ ሊሰልም ይችላል፡፡ ልትሰልም ትችላለች፡፡ ሚዜ ግን ከዘር ይወርዳል ይላሉ፡፡ የሚዜ ልጅ ሚዜ ይሆናል፣ እንኳን ዘመዱ፡፡ እና ሙስሊሙንና ክርስቲያኑን እሚለየው ነገር የለም፡፡ ከጥንት ያገኘነው ነው፡፡"[216] በማለት የሚዜን ትውፊት ከሃይማኖት ጋር በማነጻጸር ነው፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡት አብነቶች መሰረት የሚዜ አመሰራረት በወሎ አብሮ በማደግም ሆነ በሥጋ ዝምድና ሙስሊሙ ለክርስቲያኑ፣ ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ ሚዜ ሆኖ ይድራል፣ ይሞሸራል፡፡ በወሎ የሚዜ ትውፊት መሰረት ዋናው ጉዳይ ይሄ አይደለም፡፡ ዋናውና መሰረታዊው ጉዳይ ግን በወሎ የክርስቲያንና የሙስሊም ድንበር የሆነው የእርድ ወይም የካራ (ቢላዋ) ጉዳይ በየጁ ሃዳ ለሚዜ ትውፊት የማይሰራ ድንበር መሆኑ ነው፡፡

---

[214] ሞላልኝ ወርኩ፣ ቃለ- መጠይቅ፣ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ-መሐል መቻሬ፡፡
[215] በሪሁን ይመር፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ፡፡
[216] መሪጌታ ቀለሙ ዳኛው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 5 ቀን 2006 ዓ.ም. ውርጌሳ- 01 ቀበሌ፡፡

6.1.1.1.4.1፡- ሚዜና እርድ በየጁ ሃዳ

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ሚዜ በወሎ “መ·ሽራ ስለሆነ!” ወይም “ኒካ ስላላሰረ!”[217] ክርስቲያን ያረደውንም ሆነ መ·ስሊም ያረደውን ሥጋ እንዲበላ ባህሉ ይፈቀድለታል፡፡ ፈቃጁ አካልም ከቤተሰብ እስከ ጎረቤት፣ ከጎረቤት እስከ ቤተ-እምነት ይደርሳል፡፡ ትውፊቱ በቤተሰብ ተቀባይነት ያገኘበት፣ በጎረቤት የታመነበትና በሃይማኖቶቹ የተፈቀደበት መሰረታዊ ምክንያት፤ የወሎ ሚዜ ከመ·ሽራ ልብስ አጠባ (የጫጉላ ፍጻሜ) በኋላ እምነቱን የሚያድስበት ዘዴውና ብልሃቱ ስላለው ነው፡፡ የቤተ-እምነቶቹም ሆነ የማኅበረሰቡ ፎክሎራዊ ደንብና ሥርአት ስለሚፈቅድለት ነው፡፡ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ነጥቦች ለዚህ አባባል ማረጋገጫ አብነቶች ናቸው፡፡

> በጫጉላ ቤት ውስጥ ክርስቲያን ወይም እስላም ያረደው ሳይባል ሚዜዎች አንድ ላይ በመብላትና በመደሰት አብረው ይሞሸራሉ፡፡ አብሮ አደግ ናቸውና በሃይማኖት አይደለም ሚዜ እሚመረጠው፡፡ አብሮ ማደጉ ነው ሚዜ አርጎ እሚያስተሳስራቸው፡፡ እና ይሞሸራሉ አብረው፡፡ በዚህ ጊዜ ይሄ ክርስቲያን ያረደው ሥጋ ነው፤ ያኔ መ·ስሊም ያረደው ሥጋ ነው፤ እሚባል ነገር የለም፡፡ ሁሉም ሚዜዎች መ·ሽራውን መስለው አብረው ሲበሉ፣ አብረው ሲጠጡ ይከርማሉ፡፡ ሁሉም መ·ሽሮች ናቸውና፡፡ እንግዲህ ያን ጊዜ ክርስቲያኑ አስላም፤ እስላሙ ክርስቲያን ሆነ ማት ነው፡፡ መጨረሻ ላይ ምንድን ነው የሚያደርጉት፣ የመ·ሽራ ልብስ አጠባ እሚሉት ባህል አላቸው፡፡ ወይም መለያያቸው ጊዜ አለ፡፡ ያን ጊዜ ጨርሰው ወደየቤተሰቦቻቸው ሲመለሱ፤ ወደየሃይማኖታቸው ሂደው ክርስቲያኑ “ቄዴር” እሚባል ባህል አለ፤ እሱን ይጠመቃል፤ መ·ስሊም ያረደውን ሥጋ በልቷልና፡፡ ያኑን በማድረጉም የሃይማኖት መሪውም ያኑን እሚቃወም አደለም፡፡ እስላም ያረደውን በልተሃል ብሎ አያወግዝም፡፡ መ·ስሊሙ ምናልባትም “ማሼደ” እሚባል አለ፤ ዶሮ አርዶ ወደ እስልምናው ይመለሳል፡፡ “አሼዴ” ነው እሚሉት[218]፡፡ ከዚያ ውጪ ሕይወታቸው አብሮ እሚቀጥል ስለሆነ ምንም አደለም፡፡ በኋላም የነሱ ልጆች የሚከተሉት ይህንኑ ፈለግ ነው፡፡ ባህሉ ያው ነው፡፡ በዚሁ አይነት ነው እሚቀጥለው፡፡[219]

በዚህ ጥቅስ የተነሱትን የወሎ የሚዜ ትውፊቶች የክርስትና የሃይማኖት አባት የሆኑት መርጌታ ቀለሙ ዳኛው “ባህሉ የአባት አደር ነው!” በማለት ሃሳቡን ይስማሙበታል፡፡ ለዚህም “በሚዜነት አይለያይም ‹ቄዴር› ይፀበላል እንጂ፤ ተሞሽረው እስቲወጡ ድረስ አይለያዩም፡፡ አብረው እየበሉ፣ አብረው እየጠጡ ባንድ ላይ ይሞሸራሉ፡፡ እና ይኸ ያለ ነው፡፡ እንኳን ሚዜ ልጆቹ ቀርቶ ትልልቆቹ እኛ እንኳን አብረን ነው፡፡ እና ይኸ ከጥንት ጀምሮ የቆየ ባህል ነው፡፡››[220]

---

[217] እንድሪስ ይመር የሚዜን ትውፊት የሚገልፁት “አሁን እኔ የክርስቲያኑ ሚዜ ሁኜ፣ ተክርስቲያኑ ቤት ተተሞሽርኩኝ፣ ልጅ ስለሆንኩኝ፣ ኒካ ስላላረፈብኝ ክርስቲያን ያረደውን ሥጋ እበላለሁኝ” በማለት ነው፡፡ነገር ግን ያገባው ሚዜ ላላገባው ሚዜ ሆኖ ስለሚድር “ኒካ ስላላረፈብኝ!” የሚለው ምክንያት ትክክል አይመስልም፡፡

[218] ዓሊ መሐመድ በመ·ስሊሙ በኩል ያለውን ከጫጉላ በኋላ ወደ ሃይማኖቱ የመመለስ ሥርዓት የሚገልፁት “በቁርቁሃ ያጥቡታል!” ኸዚያ በኋላ እስላም ይሆናል፡፡

[219] አሰፋ አበጋዝ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 5 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ-ጎላ መቻሬ፡፡

[220] መሪጌታ ቀለሙ ዳኛው፣ ቃለ-መጠቅ፣ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሳ-01 ቀበሌ፡፡

በማለት ምክንያታቸውን ያቀርባሉ፡፡ ትውፊቱ እንደሚቀጥልም ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ እንድሪስ አህመድ በበኩላቸው ከዚህ በላይ በወሎ የሚዜ ትውፊትን አስመልክቶ በተነሱት ነጥቦች ይስማማሉ፡፡ ለዚህም በወሎ የሚዜ ደንብና ሥርአት መሰረት ባህሉ፣ ወግና ልማዱ ይሄው መሆኑን የሚከተሉትን ነጥቦች ምሳሌ ይጠቅሳሉ፡፡

> በወሎ ሚዜ ክርስቲያኖችም ሙስሊሞችም ናቸው፡፡ ምክንያቱም የሚዳረው ሙሽራ የሙስሊምም ጓደኛ አለው፤ የክርስቲያንም ጓደኛ አለው፡፡ ክርስቲያን ከሆነ ልጁን የዳረው የሙስሊሙ ሚዜ ክርስቲያኑ ያረደውን ሥጋ አብሮ ይበላል፡፡ አይለይም፡፡ "ብላ እንግዲህ የግድ ነው! ምንም አይደለም!" ይባላል፡፡ በተመሳሳይ ክርስቲያን ሆኖ የሙስሊም ሙሽራ ሚዜ ከሆነ አብሮ ይሞሸራል፤ ሙስሊም ያረደውን ይበላል፡፡ ከዚያ ከሠርጉ በኋላ ይጠመቃል፡፡ ቤተሰቦቹ ያውቃሉ፡፡ መከልከል ስለማይችሉ እንዲጠመቅ ያደርጉታል፡፡ በሙስሊሙም ያው ነው፤ ልዩነት የለውም፡፡ "እኔ እንግዲህ በልቼ ነበር!" ይላል፤ ‹‹ስቴክ ጋር አድርግ!" ይባላል፤ ያው ጌታውን ይቅርታ መጠየቅ ነው፤ ጌታውን ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ ከዚያ በኋላ ከዘመዶቹ ጋር ይቀላቀላል፡፡ ችግር የለውም፡፡ ዘመዶቹም ክርስቲያን ያረደውን ሥጋ በልተሃል ብለው አይቀየሙትም፤ አያገሉትም፡፡ ያ የተለመደ ባህል ስለሆነ፤ ከጥንት ከአባቶቻችን የመጣ ስለሆነ፡፡ ለጓደኛው ተሞሽሯል ነው እሚባለው፡፡ ተሞሽሮ ሥጋ በልቷል ነው፤ እሚባለው ችግር የለውም፡፡[221]

ከላይ እስካሁን በቀረቡት ጥቅሶች ውስጥ በተነሱ መሰረታዊ ነጥቦች መሰረት ወይም በወሎ የሚዜ ትውፊት መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት መሰረቶችና መገለጫዎች በወሎ፤ ባህሉ፣ የባህሉ ባለቤቶችና የሃይማኖቶቹ ትውፊቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ የሚዜ ትውፊት በወሎ ክርስቲያን ሙስሊሙ የተስማማበት ባህል፣ ወግና ልማድ ነው፡፡ ከሃይማኖቶቹ አንፃር ደግሞ ይህንን ባህል፣ ወግና ልማድ የሃይማኖቶቹ አባቶች (መሪዎች) አይነቅፉትም፤ አያወግዙትም፤ አይከለክሉትም፡፡

ባንፃሩ የባህሉ ባለቤቶች ከባህሉ ወደ ሃይማኖቶቹ፣ ከሃይማኖቶቹ ወደ ባህሉ በነፃነት፣ በፍቅርና በሰላም እንዲመላለሱ መንገድ ያመቻቻሉ፡፡ ለዚህም በጥቅሶቹ ውስጥ በተነሱት ዋና ዋና ነጥቦች መሰረት በክርስትናው በኩል "ቁዴር"፤ በእስልምናው በኩል ደግሞ "ማሼድ" ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡ የሚዜ ትውፊት በወሎ በሚዜዎች ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቆም አይደለም፡፡ ባንፃሩ የሚዜ ባህል፣ ወግና ልማድ በወሎ እንደሠርግ ሥርአቱ ሁሉ ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ጋር በተለያዩ ክሮች ይተሳሰራል፡፡

6.1.1.1.4.2፡- ሚዜና የጉርብትና ትውፊት በየጁ ሃዳ

የወሎዬዎች የጫጉላ ባህል፣ ወግና ልማድ ክርስቲያን ሙስሊሙ የሚገናኝበት፣ የሚተሳሰርበት፣ የሚተባበርበትና የሚከባበርበት፣ የሚተዛዘንበትና የሚተሳሰብበት፣ የሚዝናናበትና የሚደሰትበት

---

[221] እንድሪስ አህመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 28 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ-03 ቀበሌ፡፡

ትውፊት ነው። የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት በግለሰቡ አቅም የሚወሰን ሆኖ፤ የጫጉላ ጊዜ በወሎ፤ ከአስር እስከ አስራ አምስት ቀን፤ ከዚያም ሲያልፍ እስከ አንድ ወር ድረስ ሊዘልቅ ይችላል።በነዚህ ቀናት ውስጥ ደግሞ በሚዜዎችና በማኅበረሰቡ መካከል የተለያዩ የእርስ በእርስ ግንኙነቶች ይደረጋሉ፤ የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎች ይፈፀማሉ። እነዚህ ግንኙነቶችና ክዋኔዎች ደግሞ ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ጋር በእጅጉ የተሳሰሩ ናቸው።

ይህም ማለት የጫጉላ ጊዜ በወሎ ከጉርብትና ጋር ይቆራኛል። ከገበያ ጋር ይገናኛል። በወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት መሰረት በጫጉላ ጊዜ ክርስቲያን ሙስሊም ሳይል ለተጨነቀ ሚዜ ከበግ እስከ ገንፎ ፣ከፍርፍር እስከ አነባብሮ፣ ከጠጅ እስከ ጠላ፣ ከቡቅሬ እስከ እርጎ እንደአቅሙና እንደ ቀረቤታው ሊያመጣ ይችላል። አበጋር ማዱ በላይ የዚህ አይነቱን ትውፊት የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> ማታ ሚዜ እዛፍ ላይ ይወጣና አዋጅ ስማ! አዋጅ ስማ! ይላል። ነገ ጧት፣ ነገ ሱቢህ፣ ነገ ሌሊት በንጥር ቅቤ ገንፎ ይዘሽ ያልመጣሽ ለአጤ እገሌ አባበሉ (ሙሽራው አጤ ይባላል) በትኋን አጋሰስ፣ በቁንጫ ፈረስ ትወረሪያለሽ! ነገ ይዘሽ ግቢ! አዋጅ ስማ! ይላል። ይኸ መንደሩ ይሰማል። እንዳይሰድቡኑ ይላል። ያው የጎረቤት ሴት ሌሊት ተነስታ እንዳይሰድቧት ንጥሩን ጎልጉላ ከዚያ ገንፎ ላይ አርጋ ይዛ ትሄዳለይ። እልል! እልል! እልል! ይላል ሚዜ፤ ይቀበላል። መቼም ሚዜ የአበላል ቅጥም የለው፤ በይህም ዘርፎ፣ በይህም ዘርፎ አንዱ ሲቀማ፣ ሌላው ሲቀማ በቅጥ እንኳን አይበሉትም[222]።

ከላይ ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው በወሎ ሚዜ የሚሞሸረው በቤተሰቦቹ ብቻ ሳይሆን፤ በጎረቤት ጭምር ነው። ምክንያቱም የጎረቤት ልጅ በወሎ፤ የወላጆቹ ብቻ ሳይሆን፤ የጎረቤትም ልጅ ነው። ስለዚህ ወግ-ማዕረጉ፣ ደስታውና ፌሽታው ለቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ለጎረቤት ጭምር ነው። በመሆኑም ጎረቤት ለዚያ ልጅ ፍቅሩንና መውደዱን የሚገልጽበት አጋጣሚ ይህ የጫጉላ ጊዜ ነው።

ከዚህም ሌላ ሚዜ በራሱ በአካባቢው እየተዘዋወረ ከክርስቲያኑም ሆነ፤ ከሙስሊሙ ቤት አንድም "በልመና" አንድም "በጉልበት" የሚያስፈልገውን ነገር አሰባስቦ ይዞ ይመለሳል። እንዲሁም ሙሽራ ለማየት ወደ ጫጉላ እሚመጡ የጎረቤት ሴቶችን መቀነት አስፈትቶ ብር ይቀበላል። በተጨማሪም ለሙሽሮቹ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ከቤታቸው ይዘው እንዲመጡ ቃል ያስገባል። የዚህ አይነቱን ትውፊት የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚከተለው ይገልፁታል።

---

[222] አበጋር ማዱ በላይ ፣ ቃለ-መጠይቅ ፣ ነሐሴ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ።

> ለምሳሌ ያንተ ሚስት ወይ የእኔ ሚስት ሙሽራ ልታይ መጥታ ከጫጉላው ደጃፍ ላይ ትቀመጣለይ። ሚዜ ጎትቶ ያስገባታል። ካስገባት በኋላ ዳቦ ጋግራ፣ ገንፎ አገንፍታ እንድታመጣ ቃል ያስገቧታል። ይህንን ቃል ገብታ ሙሽራ አይታ ትሄዳለይ። አመጣጧም ለዚሁ ነው። ከዚያ እንደ አቅሟ ሙሬራ፣ አነባብሮ፣ ዶሮ፣ ገንፎ፣ እርጎ ወይ ሌላ ነገር ልታመጣ ትችላለይ። ቃል ገብታ ስለሄዴይ ግዴታ ይዛ ትመጣለይ፤ ባህልም ፍቅርም (አጽንዖት የኔ) ስለሆነ። እዚህ ላይ እከሌ ከእከሌ አይባልም። ባህሉ የእስላሙም የክርስቲያኑም ነው። እስላሟ ሰርታ ካመጣይ ሥጋም ቢሆን ሁሉም ሚዜ ይበላል። ክርስቲያኗም ሥጋ ሰርታ ካመጣይ ሁሉም ሚዜ ይበላል። ግድ ነው። ሚዜ ሃይማኖት አይለያየውም ይባላል[223]።

በወሎ ሚዜ በሃይማኖት አለመለያየቱ ብቻም ሳይሆን፤ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት መሰረት የጎረቤት ልጅ ከወለዱት ልጅ ተነጥሎ አይታይም። ለምሳሌ በወሎ የክርስቲያኑ ልጅ በጥሩ ሥነ-ምግባር ታንፆ የሚያድገው በክርስቲያን ወላጅ ቤተሰቦቹ ብቻ ሳይሆን፤ በሙስሊም ጎረቤቶቹ ጭምር ነው። ክርስቲያኑም ለሙስሊሙ ልጅ ተመሳሳይ ሚና አለው። ሙስሊሙም ክርስቲያኑም አብሮ አንዱ የሌላውን ልጅ እንደራሱ ልጅ አርጎ ያሳድጋል። በዚህ መሰረት ሲዳሩም ደስታው የሁለቱም ነው። ልዩነት ነገር የላቸውም። ለነሱ አብረው መኖራቸው፣ አብረው ማሳደጋቸው በቂ ነው። በዚህ መሰረት በጫጉላ ጊዜ ለሚደረግ ነገር ሁሉ አድሎ የለም። አይታሰብምም። በመሆኑም ለሚዜ የሚደረገው ነገር ሁሉ ከዚሁ ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ጋር የተያያዘ ነው።

በሌላ በኩል በወሎ የሚዜ ባህል፣ ወግና ልማድ መሰረት ሚዜ ከጎረቤት አልፎ ራቅ ወዳለ በግና ፍየል ወደተሰማራበት ቦታ ሂዶ እረኛ የሌላቸው የሙስሊምም ሆኑ የክርስቲያን በጎች ወይም ፍየሎች ካገኘ "ዘርፎ" ያመጣል፤ አርዶ ይበላል። ይህንን በማድረጉም ሚዜ በወሎ አይከሰስም፤ አይወቀስም። የአካባቢው ነዋሪዎች ይህንን ትውፊት የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> ሚዜዎች ዱር ሂደው የሙስሊምም ይሁን፣ የክርስቲያንም ይሁን፣ እረኛ የሌላቸው በጎች ካገኙ፣ ፍየሎች ካገኙ፣ ዘርፈው ይዘው ይሄዳሉ። ስለዚህ ክስ የለም፤ ወቀሳም የለም። የሚባል ነገር ቢኖር "ሚዜ እንዳይወስዳቸው ተጠንቀቁ!" ብቻ ነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ሚዜ ቢወስዳቸው "አዬ! የእከሌ ሚዜዎች ዛሬ በይህ መጥተው ነበር! በጌን ወሰዱብኝ! ፍየሌን ወሰዱብኝ! ነው። ከዚህ ውጪ ክስ የለም፤ ወቀሳ የለም። ለምን? ይኼ የባህሉ ሕግ ለሚዜዎቹ የፈቀደላቸው ስለሆነ[224]።

እንዲሁም የሚዜ ትውፊት በወሎ ከጎረቤትና ከአካባቢ አልፎ ገበያ ውስጥ ይገባል። "ገበያ የሚሰጠውን እናት አትሰጥም!" እንዲለ ወሎዬዎች፤ ምሳሌያዊ አነጋገሩ ለሚዜም ይሰራል።

---

[223] በሪሁን ይመር፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ።

[224] አድኖ ተካየ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 02 ቀበሌ።

ሚዜ በቤቱና በአካባቢው የማያገኘውን ነገር ገበያ ወጥቶ ያገኛል። ሚዜ በወሎ ኩል ተኩለ፣ ጎፈሬውን ነቅሶና ቅቤ ተቀብቶ፤ ሚዶ፣ አደስ፣ አሽኩቲ፣ አሩቲና ናትራ ከጎፈሬው፤ መፋቂያውን ከጥርሱ ሰክቶ ገበያ ይዞራል። ዋና ዓላማውም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ዘፍኖም ሆነ ለምኖ፤ ቀምቶም ሆነ ገዝቶ ለሙሽሮቹ መውሰድ ነው። በዚህ ሂደት ገበያተኛ ለገበያ ያመጣውን ቁሳቁስ በሚዜ እንዳይቀማ ብርቱ ጥንቃቄ ያደርጋል። የነቃው ላልነቃው "ሚዜ! ሚዜ!" በማለት ያስጠነቅቃል። ይህም ሆኖ ትንሽ የተዘናጋ ገበያተኛ በሚዜ ይቀማል። "አዬ! ሚዜ ወሰደው!" በማለት ወደ መጣበት ይመለሳል። በለስ የቀናው ሚዜ በበኩሉ፤ እየዘፈነና እየጨፈረ የያዘውን ይዞ ወደ ጫጉላው ይመለሳል።

በዚህ አይነት ትውፊት የታጀበው የጫጉላ ሥርዓት በወሎ፤ ወንዝ ወርዶ የሙሽራ ልብስ በማጠብ ፍፃሜውን ያገኛል። ወይም ይጠናቀቃል። በዚህ ፍፃሜ ሂደት ሦስት መሰረታዊ ሁነቶች ይከወናሉ። ጎረቤት እንደለጋስነቱ የሚሞካሸበትና የሚሞገስበት፤ ንፉግም የሚወቀስበት ሥርአት አንዱ ሲሆን፤ ሙሽራውን ወደ ወንዝ በመውሰድ "እንዲረክስ" ማድረግ ሁለተኛው ትውፊት ነው። ሦስተኛው ሥርዓት ደግሞ ሙሽራውን ገበያ ውስጥ እንዲዞር በማድረግ "ዓይነ-ናስ" ወይም የሰው ዓይን እንዲላመድ ማድረግ ነው። የሚዜን መግሳና ወቀሳ አበጋር ማዱ በላይ የሚገልጹት "የጫጉላው ፍፃሜ እለት ሌሊት ላይ ሚዜ ይነሳና እዛፍ ላይ ወጥቶ ‹አዋጅ ስማ! አዋጅ ስማ !› ይላል። ተዚያማ ሙክት የመጣበትን ቤት፣ ንጥሩ በብዛት የመጣበትን ቤት፣ እርጎው በብዛት የመጣበትን ቤት፣ የባለቤቱን ስም ይጠራና ‹ለእገሌ አባበሉ የሙክቱን አገር! የላሙን አገር! የጤፉን አገር! የገብሱን አገር...ወዘተ ሰጥተናል!› ይላል። እንደየደረጃው አገር ይሰጣሉ። ላላመጣም በተቃራኒው ነው[225]።" በማለት ነው። ወንዝ የመውረዱ ብሂል ደግሞ በወሎዬዎች የሚዜ ትውፊት መሰረት የራሱ የሆነ ዓላማ አለው። ትርጉም አለው። ለምሳሌ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት።

> የሙሽራውን ልብስ ሰብስቦ "ዋርዳው ሸቦ!" እያለ ሚዜ ሙሽራውን ወንዝ ይዞ ይወርዳል። እንግዲህ ሙሽርነቱን ሊለቅ ነው። ወረደ ሸወንዙ ገላውን ያጥባል፤ ልብሱን ያጥባል ሚዜ። እንግዲህ ውኃ ሸነካው እረከሰ ማለት ነው። ይሸ ቁጥቡ (ጂኒው) አወቀው ማለት ነው። ነገም አይጣላውም። ለመደው ማለት ነው። ሃለበለዚያ በሙሽርነቱ ወይ በሙሽርነቷ ጥለዋት ከሄዱ ብዙው እብድ እሚሆነው፤ ብዙው በሽተኛ እሚሆነው ሸያ ቁጥቡ እየተጠጋቸው ነው። አራስም እንዳይሸው ናት። አራስ አርባ ቀን እስቲሆናት ድረስ እየተጠበቀች ነው። አርባ ቀን አስቲሆናት እመጫት ሰው አይነጠላትም። ሰው ከተነጠላት

[225] እንደላይኛው።

ያው በሽተኛ ነው እምትሆነው፡፡ የሚጠጋት አለ ይኸ ወንዘኛው ይጠጋታል፤ ጂኒው፡፡ መ·ሽራውንም፣ መ·ሽራይቱንም ሰው ኸተነጠላቸው እንዲያ ነው·[226]፡፡

ከላይ በጥቅሱ እንደተገለጸው መ·ሽራው ወንዝ የመውረዱ ፋይዳ ከክፉ መንፈስ ለመከላከል ነው፡፡ ከዚህም ሲያልፍ ከቁጥቡ ጋር ለማስተዋወቅና ለማላመድ ነው፡፡ መ·ሽራውን ገበያ ወስዶ የማዞር ፋይዳ ደግሞ ዓሊ መሀመድ እንደሚሉት "ገበያውን ያ ሁሉ ሰው እያየው ይዞራል፡፡ ይኸም ከሰው ዓይን ጋር ተላመደ ማለት ነው፡፡ ገበያውን ዙረው ኸጨረሱ በኋላ ደሞ ሂደው ወይ ጠጅ ቤት ወይ ቡና ቤት ይገባሉ፡፡ ጠጅ ይቀዳል፡፡ መጠጥ ይወርዳል፡፡ ዘፈን አርሽ ይቀልጣል፡፡ እዚያ ያለው ሰው እንደ አቅሙ ኸልማት ይሸልማል፡፡ በዚህ ብር ደሞ እዚያው ጠጅም ሆነ ሌላ መጠጥ ይወርዳል፡፡ ኸዚያ አቅሙ እስከቻለ መጠጣት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የጫጉላ ሥርአቱ ይጠናቀቃል[227]፡፡"

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወለዬዎች የጉርብትና ትውፊት መሰረት የሙስሊሙም ሆነ የክርስቲያኑ ልጅ ተወልዶ የሚያድገው በወለዬዎች የጋራ ቀየ ውስጥ ነው፡፡ በዚህ ቀየ ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም የማኅበራዊ መስተጋብር ደንብና ሥርአት ተኮትኩቶ ያደገ ልጅ ለዚህ ወግና ማዕረግ በመብቃት ወደ ቀጣዩ የማኅበራዊ መስተጋብር እርከን ይሸጋገራል፡፡ ይህም ማለት ሦስት ጉልቻ ይመሰርታል፡፡ ሦስት ጉልቻ ሲመሰርት ግን፤ ከላይ እንደተጠቀሰው የተለያዩ ትውፊቶች ተከናውነውበትና ተስተናግደውበት ፍፃሜውን ያገኘው የወለዬዎች የጫጉላ ሥርአት የሚፈፀመው መ·ሽሮቹን ከሦስት ጉልቻ ጋር ለተገናኘው ትውፊት አስረክቦ ነው፡፡ ይህ ትውፊት በወለዬ የሼነቻ ወይም "የተወፈሌ ወደጃ" አለያም የዱዓ ሥርዓት በመባል ይታወቃል፡፡

6.1.1.1.5፦ የሼነቻ (የተወፈሌ) ወዳጃ በየጁ ሃዳ

አበጋር ማዱ በላይ እንደሚሉት የሼነቻ ወዳጃ መ·ሽሮቹ ጫጉላቸውን ጨርሰው ከቤተሰብ ጋር ሲደባለቁ የሚደረግ የዱዓ ሥርዓት ነው፡፡ ወዳጃ የሚገቡትም የዘር ሐረጋቸው ከዚሁ ሥርዓት ጋር የተያያዘ ሼነታዎች ብቻ ናቸው፡፡ ወይም ለዚህ የዱዓ ትውፊት ከፈጣሪ ተሰጥኦው የተቸራቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ ከሃይማኖት አንፃርም ሙሉ በሙሉ መስሊሞች ናቸው፡፡ ለምሳሌ መ·ሽራው መ·ሽራይቱን ሊያመጣ ሲሄድ ዱዓ የሚደረገው በአበጋሩ አማካይነት ነው፡፡ ፀጉሩንም የሚላጨው በአበጋሩ ነው፡፡ ዳስ ላይም የምረቃ ሥነ- ሥርዓት

---

[226] ሃምሳ አለቃ መኮንን የሺጥላ፣ቃለ-መጠይቅ፣ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም ወልዲያ-02 ቀበሌ፡፡

[227] ዓሊ መሐመድ፣ቃለ-መጠይቅ፣ነሐሴ 4 ቀን 2007 ዓ.ም ሐብሩ-02 ቀበሌ አንጦ፡፡

የሚከናወነው በአበጋሩ ነው። ነገር ግን ይኸኛው የዱዓ ሥርአት የሚፈፀመው በሼነቻዎች ብቻ ነው። ሥርዓቱን አበጋር ማዱ እንደሚከተለው ይገልጹታል[228]።

> ሙሽሮቹ ጫጉላቸውን ጨርሰው ወደ ቤተሰብ ሲደበላለቁ ደሞ ሼነቻዎቹ ይመጣሉ። ሙሽራው ኮርማውን አዘጋጅቶ፣ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ አዘጋጅቶ፣ ጨፌውን ጎዝጉዞ ይጠብቃቸዋል። ተዚያ ተሚስቱ ጋር እየከደሙ ሼነቻዎቹ ገብተው አጎልፍፎውን ይጠርጋሉ። ሼነቻዎቹ ሲመጡ ቆቴያቸው ማቶት ተሰርቶለት እዚያ ይቀመጣል። ሁሉን ነገር የሚከድሙት ሙሽራውና ሙሽራይቱ ብቻ ናቸው። ሌላ ጎረቤትና ቤተሰብ ወደነሱ አይቀርብም። ጨፌውን ከሁለቱ ሙሽሮች ውጪ ሌላ ማንም ሰው አይረግጠውም። ተዚያ ሼናቻዎቹ ዱዓ አድርገው ሙሽራዎቹን ሙዳ ቅቤ ይቀቧቸዋል[229]።

በዚህ ጥቅስ መሰረት በወሎዬዎቹ የጋብቻ ባህል፣ ወግና ልማድ፣ እንዲሁም ደንብና ሥርአት ዱዓ አንዱ የሠርግ ወይም የጋብቻ አካል ነው። በምዕራፍ አምስት ውስጥ እንደተጠቀሰው የዱዓ ትውፊት ዋና ዓላማ በወሎ፤ በረካ ለማግኘት ነው። በወሎ ደጋጎች ተራዳኢነት መልካም ነገር ለማግኘት ነው። በመሆኑም የሠርግ ዱዓ በወሎ የሙሽሮቹ ጋብቻ የሰመረ እንዲሆን ለማድረግ ነው። የሙሽሮቹ ማኅበራዊ ሕይወት የተሟላና የተቃና እንዲሆን በመመኘት ነው። ሙሽሮቹ ሲሳይ፣ ሰላምና ፍቅር፣ ሃብትና ጤና ያለው ልጅ እንዲወልዱ ለማድረግ ነው። እነሱም እድሜ፣ ሃብትና ጤና እንዲያገኙ ለማስቻል ነው። ቀጣዩ ማሕበራዊ ሕይወታቸው ከየጁ አድባር ጋር እንዲሰምር በመመኘት ነው። ወይም ሃጃዎች እንዲሞላ በማሰብ ነው። ስለዚህ ዱዓ በወሎ የሥልጣን ምንጭ ነው። ዱዓ በወሎ የእድሜ፣ የሃብትና ጤና፣ የሰላምና የፍቅር ተምሳሌት ነው። ለሙሽሮቹም ዱዓ የሚደረገው ይሄ ሁሉ በረካ እንዲደርሳቸው ታስቦ ነው።

በዚህም መሰረት በወሎ ሙሽራው የክርስቲያን ልጅም ሆነ የሙስሊም ልጅ የጫጉላ ሥርአቱን ጨርሶ ወደቤት ሲገባ የሼነቻ ወዳጃ ወይም ዱዓ ይደረግለታል። በዚህ ባህል መሰረት የሼነቻ ወዳጃ በወሎ ከቁሱም ቤት ሆነ፤ ከሼሁ ቤት ሊደረግ ይችላል። በዚህ ፎክሎራዊ ክዋኔ ዱዓ አድራጊው ሙስሊሙ ሲሆን፤ ዱዓ አስደራጊው ደግሞ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ነው። በዚህ መነሻ ዱዓ በወሎ ለክርስቲያኑም ሆነ፤ ለሙስሊሙ የበረከት ምንጭ የሆነ የጋራ እሴት ነው። የመልካም ነገር ስበብ ወይም ተምሳሌት ነው።

---

[228] አበጋር ማዱ በላይ እንደሚሉት፣ ኢማን ኦርማ፣ በቆጂ፣ ካሎኒ፣ ዲሮኒ፣ ቆሬው ከሚባሉት ትውልዶች የዘር ሐረጋቸው የሚመዘገ ግለሰቦች፣ ከሼነቻ ወዳጃ እሚገቡ አካላት ናቸው። ከነሱ ውጭ ከሼነቻ ወዳጃ ሌላ ግለሰብ አይገባም።

[229] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ

ነገር ግን ከላይ እንደተጠቀሰው ለክርስቲያኑም ሆነ ለሙስሊሙ የጋራ እሴት የሆነው የዱዓ ትውፊት በወሎ፤ ምንጩ እስልምናው ነው። አገልግሎቱ ወይም ፋይዳው ግን ለሙስሊሙም ለክርስቲያኑም የጋራ ነው። በዚህ መነሻ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለፀውና የሚሰራው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የጋራ ትውፊት አማካይነት ነው። ይህ የጋራ ትውፊት ደግሞ ወሎዬዎች እርስ በርስ የሚገናኙበት ድልድይና እርስ በርስ የሚተሳሰሩበት ክር ነው። የወሎዬዎች የማኅበራዊ መስተጋብር ውጤት ነው። ይህም ማለት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ የሚገለፀው በዋናነት በወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር አማካይነት ነው። ማኅበራዊ መስተጋብሩ በሚፈጥራቸው ሁነቶች አማካይነት ነው።

ከላይ እንደተገለጸው የወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር መገለጫ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ የጉርብትና ትውፊት ነው። በዚህ ትውፊት ላይ በመመስረት "ጉርብትና በደስታ" ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ለመግለጽ የወሎዬዎች የጋብቻ፣ የሠርግ ሥርዓትና የሚዜ ትውፊቶች ከላይ በቀረቡት ንዑስ አርዕስት አማካይነት ተመርምረዋል። በነዚህ ዋና ዋና ነጥቦች መሰረት ወሎዬዎች እርስ በርስ የሚሳሰሩባቸው፣ የሚገናኙባቸው፣ የሚተዛዘኑባቸው፣ የሚተሳሰቡባቸው፣ የሚረዳዱባቸው፣ የሚደጋገፉባቸው፣ በሰላምና በፍቅር አብረው የሚኖሩባቸው በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው። በመሆኑም ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ ከሚያስችሏቸው በርካታ የጋራ እሴቶች መካከል እነዚህ ከማኅበራዊ መስተጋብሮቻቸው ውስጥ የሚመነጩ የጋራ ሃብቶቻቸው ናቸው።

ለወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር መሰረቶቹ ደግሞ የጉርብትና ትውፊቶቻቸው ናቸው። የጉርብትና ትውፊቶቻቸው ደግሞ የሃይማኖት መቻቻል እሴታቸው መገለጫ ትዕምርቶች ወይም ተምሳሌቶች ናቸው። ለምሳሌ በወሎዬዎች የሠርግ ባህል፣ ወግና ልማድ ወይም ደንብና ሥርዓት መሰረት በክርስቲያኑ የፆም ወቅት የወሎ ሙስሊም ሠርግ አስርጎ ልጁን አይድርም። በተመሳሳይ በሙስሊሞች የፆም ወቅት የወሎ ክርስቲያን ሠርግ አያሰርግም። ክርስቲያኑ ይህንን የሚያደርገው የሙስሊም ፆም እርድ ስለሚከለክል ሳይሆን፤ የሠርጉ ሥርዓት ሙስሊሞቹ ፆም ከሚያሰሩበትና ከሚያፈጥሩበት ሠአት ጋር ስለማይሰምር ነው። ከዘፈን፣ ጨዋታና ፌሽታው ጋር ስለማይገጥም ነው። ሃይማኖታዊ ከሆነው ጉዳይ ጋር ስለማይመቻች

ነው። ባንፃሩ በክርስቲያኑ የፆም ወቅት ሙስሊሙ ልጁን የማይድረው፤ አርዶና ጋርዶ ክርስቲያኑን ማስተናገድ ስለማይችል ነው[230]።

የዚህ አይነቱን የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ የወሎዬዎች ትውፊት የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት "አንደኛ ጎረቤቶች ነን፤ ሁለተኛ ዘመዳሞች ነን። ለምሳሌ ሙስሊሙ ሲድር ለክርስቲያኑ አርዶ ነው። እሱ ባይጠጣ ለሚጠጣው ጠምቆ ነው። ምክንያቱም አባት ክርስቲያን ቢሆን ልጁ እስላም ናት። አባቷ እስላም ቢሆን እናቷ ክርስቲያን ናት። ስለዚህ ሰው ከልጁ ይለያል? አይለይም። ጉርብትናውም ከዚህ አይለይም። በዝምድናውም በጉርብትናውም የተሳሰርነ ሥለሆነ፤ በሠርግ ስለማንነጣጠል በተለይ በዱሮው ዘመን በፆም ወቅት ሙስሊሙም ክርስቲያኑም አይድሩም!"[231] በማለት ነው።

ከዚህ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለፀው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የመተሳሰብና የመተዛዘን፣ የመከባበርና አንተ-ትብስ፣ አንቺ-ትብሽ የመባባል ትውፊት አማካይነት ነው። በሥጋ ዝምድና የመተሳሰር ብሂል ነው። በመሆኑም ሠርግና ጉርብትና፣ ሠርግና የሥጋ ዝምድና በወሎ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ከሃይማኖት መቻቻል እሴት ጋርም የሰምና የፈትል ያህል ይዛመዳሉ።

ባጠቃላይ በቁስ ተባርኮ፤ የሼህ፣ የአበጋርና የሼነቻ ወይም የወሎ ታላላቆች ዱዓና ቱፍታ ተደርጎበት፣ በአበውና በእመው ምርቃት ታጅቦ፣ ቤተሰብን ከቤተሰብ፣ ጎረቤትን ከጎረቤት አገናኝቶ የሚከናወነው የወሎዬዎች የሠርግ ሥርዓት ዋና ዓላማ ሙሽሮቹ የትውልዱን ቀጣይነት እንዲያረጋግጡ ማስቻል ነው። የትውልዱ ቀጣይነት የሚረጋገጠው ደግሞ ሁለቱ ተጋቢዎች ሲወልዱ፣ ሲከብዱ ነው። ወይም ሁለቱ ተጋቢዎች በሚያፈሯቸው ልጆች አማካይነት ነው። በዚህ መሰረት ከወሎዬዎች የጫጉላ ሥርዓት በኋላ ቤተሰብም ሆነ ጎረቤት የሚጠብቀው የሙሽሮቹን ወልዶ መሳም ነው። ወሎዬዎች "ውለዱ! ክበዱ!" ብለው እንደሚመርቁ ሁሉ፤ ወሊድ በወሎ ሌላኛው የማኅበራዊ መስተጋብር ወይም የጉርብትና መገለጫ ትውፊት የሆነ የደስታ ምንጭ ነው።

---

[230] ዓሊ መሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 4 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ-አንጦ -04ቀበሌ።

[231] አስካለ አበበ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ -04 ቀበሌ።

6.1.1.2 :- ልደት

የወሊድ ትውፊት በወሎ ከሥጋ ዝምድና ጋር ይገኛል:: ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ጋር ይተሳሰራል:: ከወሎዬዎች የማኅበራዊ መስተጋብር ጋር ይዛመዳል:: ከፎክሎር ጋር ይቆራኛል:: በዚህም ከወሎ ዱበርቲዎች፣ ከወሎ ሼሆች፣ ከወሎ ቃልቾችና ደብተራዎች ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ነው::

6.1.1.2.1:- ፋጢማ ቆሪ[232]

ጥናቶችም ሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ፋጢማ ቆሪ በወሎ አንዲት እርጉዝ ሴት በሰላም እንድትወልድ በአካባቢዋ በሚገኙ ዱበርቲዎች (ባልቴቶች) አማካይነት የሚደረግ ዱዓ ወይም ፀሎት አለያም የመልካም ምኞት መግለጫ ትውፊት ነው:: ትውፊቱን የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልፁት እንደሚከተለው ነው::

> ፋጢማ ቆሪ ማለት አንዲት ሴት ከመውለዷ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ የሚደረግ የገንፎና የምርቃት ሥርዓት ነው:: የፋጢማ ቆሪ ክዋኔ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ክርስቲያንም ሆኑ ሙስሊም ሴቶች በአንድ ላይ ይሆኑና ወደ እርጉዟ ቤት ይሄዳሉ:: ከዚያ ገንፎ አገንፍተው ሴትዮዋ (እርጉዟ) በሰላም እንድትወልድ ይመርቃሉ ወይም ይፀልያሉ:: ይህም ማለት ለእርጉዟ ሴት መልካም ነገር እንዲሆንላት ፈጣሪያቸውን በዱዓ ይለምናሉ:: ከዚህ የዱዓ ስርዓት በኋላ ገንፎ የመብላት ሥነ-ስርዓት ይከናወናል፤ ቡና ይፈላል፤ ምርቃትም ይደረጋል:: ባህሉ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ ነው:: የክርስቲያን፣ የሙስሊም ፋጢማ ቆሪ እሚባል ባህል የለም:: ባህሉ የጋራ ነው:: ነገር ግን ዱበርቲዎቹ ሙስሊሞች ናቸው:: ዱበርቲዎቹ ፋጢማ ቆሪውን የሚያደርጉት ለሙስሊሟም ሴት፣ ለክርስቲያኗም ሴት ነው:: የፋጢማ ቆሬው ተሳታፊ ሴቶች ደግሞ ሙስሊሞቹም ክርስቲያኖቹም ናቸው[233]::

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው ፋጢማ ቆሪ በወሎ ከእርጉዝ ሴት ጋር የሚገናኝ ትውፊት ሆኖ፤ ትውፊቱ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ እሴት ነው:: ፋይዳውም በዋናነት ከእርጉዟ ሴት ምጥ እና ከሚወለደው ሕፃን ደህንነት ጋር የተያያዘ ነው:: ምርቃት፣ መለማመንና መማፀን የፋጢማ ቆሪ ፎክሎራዊ ክዋኔዎች ናቸው:: የሚከተሉትን ምሳሌዎች ለአብነት እንመልከት ::

---

[232] The objective of Fatima Kori is to eat porridge and thereby make supplication (prayer) to make the labor of the woman easy. Other women in the neighbourhood are also invited to the event (Rukya 2013:144).

[233] ድርቤ ካሳው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ግንቦት 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ -05 ቀበሌ::

እርጉዟም በኸይር ትገላገል!

እንግዲህ ሃብታም ልጅ፤

ለዘመድ እሚበጅ ልጅ ውለጅ!

አዎ! እንግዲህ በረካ ሁኚ!

ወንድ ልጅ ጀባ!

ልጁም ወንድ ይሁን

ምጡም ገር ይሁን

ቤተሰብ እሚጠቅም

እድሜ ያለው ልጅ ይሁን

በሀብት የሚያድግ ልጅ ይስጥሽ

አላሁ መሶሌ!

ማርያም ማሪያት! ማሪያም ማሪያት!

ማርያም ማሪያት! ማሪያም ማሪያት!

ግቡ-ግቡ እሜቴ አንሻ፤ ግቡ - ግቡ እሜቴ አንሻ

የዑመቱ ሁላ መሸሻ::

ግቡ-ግቡ ፋጡማ፤ ግቡ ግቡ ፋጡማ[234]

እንዲሆንልን ሀቲማ::

ግቡ-ግቡ አሚናት፤ ግቡ-ግቡ አሚናት

የሙሃመድ እናት፡፡

ግቡ-ግቡ አሚናት፤ ግቡ-ግቡ አሚናት

የነብያችን እናት[235] (Rukya 2013:145-148)፡፡

ከላይ ከቀረቡት የምርቃት ስንኞች መረዳት እንደሚቻለው በፋጢማ ቆሪ ትውፊት ውስጥ በክርስትናው ማርያም፤ በእስልምናው በኩል ደግሞ አንሻ፣ ፋጡማና አሚናት ተጠቅሰዋል፡፡

[234] "Fatima Kor" literally means the bowe of Fatima. Fatima is the name of one of the daughters of Prophet Muhammad (Rukya 2013:143).

[235] ከድጃ ከድር፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 16 ቀን 2006 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ሐራ፡፡

እነዚህ እንስቶች ደግሞ በሁለቱ ሃይማኖቶች እና በእምነቶቹ ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ክብርና ቦታ ያላቸው እንስቶች ናቸው። ከዚህ አንፃር በፋጢማ ቆሪ ትውፊት መሰረት የተጠቀሱት እንስቶች ለሙስሊሞቹም ሆነ፤ ለክርስቲያኖቹ የመልካም ነገር ሰበቦች፣ ወይም የበረከት ምንጮች፣ አለያም አማላጆችና ለጭንቅ ደራሽ ተምሳሌቶች ተደርገው ይታሰባሉ።

በዚህ መሰረት ከሙስሊም ቤት፣ ለሙስሊሟ እርጉዝ ሴት የማርያም ተራዳዒነት እንዳይለያት በማርያም ስም ይፀለይላታል። ሙስሊሟ እርጉዝ ሴትም ፋጢማ ቆሪ ያስገባቸው ይህንን በረከት ለማግኘት ነውና የማርያም ተራዳዒነት እንደማይለያት ከልቧ ተስፋ ታደርጋለች። በተመሳሳይ ከክርስቲያኑ ቤት ለክርስቲያኗ እርጉዝ ሴት፤ የእነ አንሻ፣ ፋጡማና አሚናት ተራዳዒነት እንዳይለያት በእነሱ ስም ዱዓ ይደረጋል። ዱዓ የሚደረግላት ክርስቲያን ሴትም፤ "እነሱ መጂን! ከራማቸው እንዳይለኝ!" በማለት የዱበርቲዎቹን ምርቃት "አሜን!" ብላ ትቀበላለች።

በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ የሚገለፀው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የማኅበራዊ መስተጋብር ብሂል ነው። ወይም በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የማኅበራዊ ሕይወት ፍልስፍና ውስጥ ነው። የዚህ ፍልስፍና መሰረቱ ደግሞ የወሎዬዎች ፎክሎር ነው። ፎክሎር በወሎ ከወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ነው። ከእስልምናውና ከክርስትናው ትውፊቶች ጋርም ጥርስና ከናፍር ነው። የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ መገለጫውም፣ ሥረ-መሰረቱም ይሄው የወሎዬዎች ፎክሎር ነው። ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው በወሎ ጋብቻው ፎክሎር ነው። በወሎ ሠርጉ ፎክሎር ነው። በወሎ ልደቱ ፎክሎር ነው። ከልደት ፎክሎር ውስጥ ከላይ እንደተጠቀሰው የፋጢማ ቆሪ ትውፊት አንዱ ነው። ከዚህ በኋላ ተከትሎ የሚመጣውም የወሎዬዎች "የጉማታ" ወይም አራስ የመጠየቅ ትውፊት ራሱ ፎክሎር ነው። ፎክሎር ደግሞ ወሎዬዎች የሚገናኙበትና እርስ በርስ የሚተሳሰሩበት የጋራ እሴት ነው።

6.1.1.2.2፦ ጉማታ (አራስ መጠየቅ)

ከልደት ጋር በተገናኘ የወሎዬዎች የጉርብትና መገለጫ እሴት በፋጢማ ቆሪ ሥርዓት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቆም አይደለም። ባንፃሩ ልደትና ጉርብትና በወሎ ከጉማታ ወይም ከወሎዬዎች አራስ የመጠየቅ ትውፊት ጋር በእጅጉ ይተሳሰራል። በዚህ መሰረት በፋጢማ ቆሪ ትውፊት አማካይነት በዱበርቲዎች ምርቃት፣ በማርያም፣ በፋጡማ፣ በአንሻና በአሚናት ተራዳዒነት በሰላም የወለደች እናት በወሎ፤ በባሏና በቤተሰቦቿ እንደምትታረስ ሁሉ፤

በጎረቤቶቿም ትጠየቃለች፤ ትጎበኛለች፡፡ አራሷን ወሎዬዎች በጋራ እንደዳሯት ሁሉ የሚያርሷትም በጋራ ነው፡፡[236] ለዚህም የወሎዬዎች አራስ የመጠየቅ ትውፊት የሆነው የ"ጉማታ" ትውፊት ለአብነት ይጠቀሳል፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ጉማታ በወሎ ለእመጫቷ የሚሆኑ የተለያዩ ነገሮችን በመያዝ አራስ የመጠየቅ ባህል ነው[237]፡፡ ይህ ባህል በወሎ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው፡፡ በዚህም ክርስቲያን አራስ በሙስሊም ጎረቤቶቿና በሙስሊም ዘመዶቿ ትጠየቃለች፡፡ "ይበላ እንደ ቤቱ፤ይሮጥ እንደጉልበቱ!" እንደሚባለው፤ በወሎ አራስ የሚጠየቀው እንደ ግለሰቡ አቅምና ፍላጎት የሚወሰን ሆኖ፤ ለአራሷ ተስማሚና ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ነገሮች ተይዘው ነው፡፡ ለምሳሌ ገንፎ፣ አጥሚት፣ ቅቤ፣ እርጎ፣ ዳቦ፣ አነባብሮ፣ እንጀራ በወጥ፣ ስኳር፣ የሕፃን ልብስና ተመሳሳይ አልሚ ምግብና መጠጦች ተይዘው አራስ ይጠየቃል፡፡ ከዚህም አልፎ አራሷ ክርስቲያን ከሆነች ሙስሊሙ ዶሮ በክርስቲያን አሳርዶ፤ በተመሳሳይ አራሷ ሙስሊም ከሆነች ክርስቲያኑ ዶሮ በሙስሊም አሳርዶ የወሎ ሰው አራስ ይጠይቃል፡፡ ድርቤ ካሳው ይህንን ትውፊት የሚገልጹት የራሳቸውን ገጠመኝ እንደሚከተለው አብነት በመጥቀስ ነው፡፡

> አሁን እኔ ልጆቼን ስወልድ በአብዛኛው ክርስቲያን ጎረቤቶቼ በእስላም እያሳረዱ መጥተው ይጠይቁኛል፡፡ እኔም እበላለሁ፡፡ እነሱም ቢሆኑ እንደዚያው ነው፡፡ በመሰረቱ እኔ ስወልድ ክርስቲያን ጎረቤቶቼ መጥተው መጠየቅ ብቻ ሳይሆን የሚያርሱኝ እነሱ ናቸው፡፡ ሙስሊም አደለም የሚያርሰኝ፡፡ ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ናቸው ሲያርሱኝ የኖሩት፡፡ እና ችግር የለም፡፡ እኔ በጣም የወሎ ነገር ይገርመኛል፡፡ ያገሬ ነገር፡፡ እወደዋለሁ፤ ይሽን ባህሉን ማለቴ ነው፡፡ እኛ እኮ የተለየ ባህል ነው ያለን[238]፡፡

ጉማታ በወሎ ለአራሷ የሚበላና የሚጠጣ፣ ለሕፃኑ ደግሞ ልብስ ይዞ መጠየቅ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ጉማታ በወሎ በዋናነት የሚገለፀው ከላይ ከተገለፁት ነገሮች በተጨማሪ ለአራሷ በሚሰጥ የገንዘብ ስጦታ አማካይነት ነው፡፡ ይህ የገንዘብ ስጦታ ሴትዮዋ ወልዳ የተኛች በመሆኗ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማሟላት እንዳትቸገር ታስቦ ነው፡፡ ይህም የወሎዬዎች የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴት ነው፡፡ ለምሳሌ እመጫት ለመጠየቅ ወደ አራስ ቤት የሄደች የወሎ ሴት፤" እንኳን እመቤቴ ማረችሽ!" ወይም "እንኳን አላህ ማረሽ!" በማለት አራሷን ጠይቃና እሷም ተስተናግዳ፤ "እመቤቴ በሽልም ታውጣሽ!" ወይም "አላህ በሽልም ያውጣሽ!" የሚለውን

---

[236] አበባ ደምሴ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ዶሮ ግብር፡፡
[237] አስካለ አበበ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ፡፡

[238] ድርቤ ካሳው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ግንቦት 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 05 ቀበሌ፡፡

መልካም ምኞት አስቀድማ ተሰናብታ ከቤት ከመውጣቷ በፊት፤ በመቀነቷ የቋጠረቻትን ብር[239] ፈታ ለአራሷ በእጇ አስይዛት ትወጣለች፡፡ በዚህ ሂደት ሰጭዋ ወይም ተቀባዩዋ አንዲ ክርስቲያን ሌላዋ ሙስሊም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር መሰረት የሃይማኖት ልዩነት በወሎ አብሮ ለመኖር ወይም ለማኅበራዊ ግንኙነት ድልድይ ከመሆን ያለፈ፤ አጥር የሚሆንበት አጋጣሚ የለም ማለት ይቻላል፡፡ ይህንን እውነታ በሚከተለው ምሳሌ ማብራራት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ "እንኳን አላህ ማረሽ!" ብሎ የሚገባ ወይም "አላህ በሽልም ያውጣሽ!" ብሎ የሚወጣ ሙስሊም ጠያቂ፤ "እንኳን እመቤቴ ማረችሽ!" ብሎ የሚገባ ወይም "እመቤቴ በሽልም ታውጣሽ!" ብሎ የሚወጣ ክርስቲያን ጠያቂ፤ ለአንዲት ሙስሊም አራስ ወይም ክርስቲያን የወሎ ሴት ልዩነት የለውም፡፡ መልሱ በወሎ ባህል፣ ወግና ልማድ መሰረት "አሜን!" ብቻ ነው፡፡ "ኪታቡ ያለው ከኛ ነው፤ አንቺ ያለብሽ መርሃባ ነው!" እንዲሉ ወሎዬዎች፤ የሙስሊ ሙም ሆነ የክርስቲያኑ መልካም ምኞት በአላህ ስምም ተገለፀ በማርያም ስም፤ ለወሎዬዎች መሰረታዊው ጉዳይ በምርቃት ትውፊት የሚገኘው በረከት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለፀው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር አማካይነት ነው፡፡

ከልደት ጋር በተገናኘ ሌላኛው የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ በወሎ፤"ማቃመስ" የሚባለው የወሎዬዎች ትውፊት ነው፡፡ ማቃመስ በወሎ አንድ ሕፃን ከእናቱ ማኅፀን እንደወጣ የእናቱን ጡት ሳይቀምስ ውኃ ያልነካው ቅቤ ማቅመስ ወይም የሕፃኑን አንቃር ቅቤ ማስነካት ማለት ነው[240]፡፡ የዚህ አይነቱን ልማድ ፎክሎራዊ ሂደትና ፋይዳ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚከተለው ያብራሩታል፡፡

> ለምሳሌ አንዳንድ ልጆች ጫሂ ሲሆኑ "ምን ይሄ አንቃሩን ቅቤ ያልነካው!" ምናምን ይባላል፡፡ እና ያነን ማቃመስ ይሉታል፡፡ ህፃኑን የሚያቃምሰው ግለሰብ ደግሞ በዚያ አካባቢ በሥነ-ምግባሩ የተመሰገነ ወይም ደሞ ታዋቂ የሆነ፣ ቸር ወይም ለጋስ የሆነ፣ ጀግና የሆነ፣ በፀባዩ ጥሩ የሆነ ሰው ካለ ሙስሊም ክርስቲያን ሳይል ይጠራና ሕፃኑ ወንድ ከሆነ ውኃ ያልነካውን ቅቤ አንቃሩ ላይ ያስነካለታል፡፡ በተመሳሳይ ሕፃኗ ሴት ከሆነች በሙያዋና በፀባይዋ የተመሰገነች፣ በአካባቢዋ አርአያ የሆነች ሴት ሙስሊም ክርስቲያን ሳይባል ትጠራና ቅቤ ታቃምሳታለች፡፡ ይህ እንግዲህ ለክርስቲያኑ ልጅ ሙስሊሙ፤

---

[239] በገጠሩ የወሎ አካባቢ አሁንም ድረስ ሴቶች ብር የሚይዙት በመቀነታቸው ጫፍ ቋጥረው ነው፡፡
[240] ዓሊ መሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 7 ቀን 2006 ዓ.ም. ሐብሩ-አንጦ- 04 ቀበሌ፡፡

ለሙስሊሙ ልጅ ክርስቲያኑ ሊያቃምሰው ይችላል። ዋናው ነገር ወላጆቹ የእከሌን አርአያ ይዞ እንዲያድግ ብለው የሚገምቱትን ሰው ብቻ ነው የሚጠሩት[241]።

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው የማቃመስ ዋና ዓላማ ወይም ፎክሎራዊ ፋይዳ በአካባቢው ባህል መሰረት "ሕፃኑ ጥፁመ ለዛ ያለው ድምጽ ይኖረዋል!" የሚለውን ብሂል ጨምሮ፤ የአቃ ማሹን ጥሩ ፀባይና ሥነ-ምግባር እንዲወርስ ወይም እንዲላበስ ለማስቻል ነው። ሰላም፣ ፍቅር፣ ጤና፣ ሃብትና መልካም እድል ያለው የማጎበረሰብ (የጀማው) አካል ለማድረግ ነው። ወሎዬዎች የሚግባቡባቸውና የሚተሳሰሩባቸውን ባህሎች፣ ወጎችና ልማዶች የሚረከብ፣ የሚጠ ብቅና ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፍ ዜጋ ለመፍጠር ነው።

በዚህ መሰረት በክርስቲያኑ በኩል ልጁ የሙስሊሙን መልካም ባህርይ እንዲወርስለት ይመኛል። በተመሳሳይ ሙስሊሙም ልጁ የክርስቲያኑን ሰናይ ምግባር እንዲላበስለት ይፈልጋል። ምክንያቱም በወሎ ክርስቲያኑ የሙስሊሙን በረካ አጥብቆ ይሻል። ሙስሊሙ የክርስቲያኑን ፀጋ ይፈልጋል። ይህም በወሎዬዎች የማቃመስ ትውፊት ተግባራዊ ይደረጋል። በወሎ ሙስሊሙ ለክርስቲያኑ፤ ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ የመልካም ነገር ተምሳሌትና የበረከት ምንጭ ተደርጎ ስለሚታሰብ ልጁን እንዲያቃምስለት ከማድረግ በዘለለ፤ በምዕራፍ አምስት ውስጥ እንደተብራራው ክርስቲያኑ የእስልምናው በረከት በእስልምናው ትውፊቶች በኩል እንዲ ደርሰው አጥብቆ ይመኛል። ለዚህም ዱዓ ያስደርጋል።

በተመሳሳይ ሙስሊሙ የክርስትናው በረከት በክርስትናው ትውፊቶች በኩል እንዲደርሰው ይፈልጋል። ለዚህም ፀበል ይጠመቃል፤ እምነት ይቀባል፤ መስቀል ይታሻል። ከልደት ጋር በተያያዘም ሙስሊሙ የክርስቲያኑን ልጅ ያቃምሳል። ክርስቲያኑም የሙስሊሙን ልጅ ያቃምሳል። ከዚህም ባለፈ ክርስቲያኑ ወደ ቃልቻው ሂዶ ለልጁ የቡዳ መድኃኒት አስደግሞ ከአንገቱና ከክንዱ ላይ ያሳስራል። አይነናስም ያስወጣል። ሙስሊሙም ወደ ደብተራው ሂዶ የሚፈልገውን ነገር ለልጁ ያስደግማል። እነዚህ ሁሉ ፎክሎራዊ ትውፊቶች ደግሞ ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያደርጉ የጋራ እሴቶች ናቸው። ለዚህም በፋጢማ ቆሪውም ቢሉ በጉማታው፤ በማቃመሱም ቢሉ በአበልጅ ትውፊቱ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ይገለፃል።

---

[241] አድኖ ተካየ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 02 ቀበሌ።

6.1.1.2.3፦ የአበልጅ ትውፊት በወሎ

ከዚህ በላይ በተለያዩ አብነቶች እንደተጠቀሰው ወሎዬዎች እርስ በርስ የሚተሳሰሩባቸው፣ የሚግባቡባቸውና ልዩነታቸውን የሚያጠቡባቸው በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው፡፡ እነዚህ የጋራ እሴቶች በወሎ የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ ከነዚህ የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ የወሎዬዎች "የአበልጅ" ትውፊት ነው:: የአበልጅ ትውፊት ደግሞ ምንጩ ልደት ነው፡፡

የአበልጅ ትውፊት በወሎ በክርስትናው በኩል "የክርስትና አባት እና የክርስትና እናት" ይባላሉ፡፡ ባንፃሩ በእስልምናው በኩል "ታቃፊ" ይባላል[242]፡፡ ከልጆቹ አንፃር ደግሞ በክርስትናው "የክርስትና ልጅ" የሚል መጠሪያ ስያሜ አለው፡፡ በእስልምናውም እንዲሁ "የዓይን ልጅ" በመባል ይታወቃል (Rukya 2013: 33)፡፡ እነዚህ የአበልጅ ትውፊቶች ስያሜያቸው ይለያይ እንጂ፤ ማኅበራዊ ፋይዳቸው ግን ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም በወሎዬዎች መካከል ቤተሰባዊ ትስስር መፍጠር ነው፡፡ ዝምድና መመስረት ነው፡፡ የወሎዬዎች የእርስ በርስ መገናኛ ድልድይ እና መተሳሰሪያ ክር ሆኖ ማገልገል ነው፡፡ በወሎዬዎች መካከል በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት ክፍተት እንዳይፈጠር ቀዳዳዎችን መድፈን ነው፡፡ ለዚህ አባባል ከዚህ በታች የቀረቡት የአበልጅ ትውፊቶች ማረጋገጫ አብነቶች ናቸው፡፡

ከክርስቲያኖቹ አንፃር የሚገለፀው የአበልጅ ትውፊት በወሎ፤ ከክርስትና ሃይማኖት ጋር የሚገናኝባቸው ሃይማኖታዊ መርሆዎች አሉት፡፡ ነገር ግን በትውፊቱ ውስጥ ጎልተው የሚታዩት ሁነቶች ፎክሎራዊ እሴቶቹ ናቸው፡፡ ባንፃሩ ከሙስሊሞቹ ጋር የተገናኘውና በመታቀፍ ሥርዓት የሚገለፀው የአበልጅ ትውፊት በወሎ፤ ግንኙነቱ ከእስልምና ሃይማኖት ጋር ሳይሆን፤ ሙሉ በሙሉ ከባህላዊ እሴቶቹ ጋር ነው፡፡

በዚህ መሰረት ከክርስትናው አንፃር ሙስሊም ሰው የክርስቲያኑን ልጅ ክርስትና አያነሳም፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደተገለፀው ክርስትናው በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ሃይማኖታዊ ሥርዓት የሚፈፀምበት ሂደት ስላለው ነው፡፡ ይህንንም የአካባቢው ነዋሪዎች "እኔ ክርስቲያኑ አሁን ታቃፊ የሙስሊም ልጅ አለኝ፡፡ ነገር ግን ሙስሊሙ የክርስቲያኑን ልጅ እንዳያቅፍ ቤተ-ክርስቲያን ሂዶ የሆነ የሚቀመስ ነገር አለ፡፡ ልጁ ቅባ ቅዱስ ሲቀምስ ክርስትና አባቱ አቅፎት

---

[242] አሰፋ አበጋዝ ፣ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ - ጎላ መቻሬ፡፡

ነው፡፡ ክርስቲያኑ ግን የሙስሊሙን ልጅ ሲያቅፍ መስጊድ ሂዶ የሚቀምሰው ነገር የለም፡፡ ስለዚህ ክርስቲያኑ የሙስሊም ልጅ ይታቀፋል[243]፡፡" በማለት ይገልፀታል፡፡

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው የመታቀፍ ትውፊት በመስጊድ ውስጥ የሚፈፀም ሃይማኖታዊ ሥርዓት የለውም፡፡ ይህም በመሆኑ ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ ልጅ ታቃፊ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የታቃፊ ትውፊት በወለዮ ሙስሊሙ ለሙስሊሙ እና ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ ነው፡፡ የሁለቱ አካላት መጠሪያ ስያሜ ግን ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም ታቃፊ ወይም የዓይን አባት፣ የዓይን እናት በመባል ይታወቃሉ፡፡ ልጆቹም የአይን ልጅ ተብለው ይጠራሉ፡፡ የዓይን አባት ወይም የዓይን እናት በወለዮ፤ ከላይ እንደተጠቀሰው ክርስቲያን ወይም ሙስሊም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህም መሰረት የአንድ ሙስሊም ልጅ በወለዮ የዓይን አባትህ ማን ነው? ተብሎ ቢጠየቅ "መምሬ እንትና!" ብሎ ሊመልስ ይችላል ፡፡

በሌላ በኩል ክርስትና በማንሳቱም ሆነ በመታቀፉ ትውፊት፤ በክርስትናው በኩል ከሚከናወነው ሃይማኖታዊ ሥርዓት በስተቀር፤ ሌሎቹ ባህላዊ እሴቶች ግን በሁለቱም በኩል ፍፁም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ሂደታቸው፤ ፎክሎራዊ ክዋኔያቸውና ማኅበራዊ ፋይዳቸው ሁለቱም ከወለዮዎች ማኅበራዊ መስተጋብር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከሁለቱ ትውፊቶች ክዋኔ አንፃር በክርስትናው በኩል ሕፃኑ ክርስትና ሲነሳ ክርስትና አባቱ ታቅፎት ቅብዓ ቅዱስ ይቀምሳል፡፡ ባንፃሩ በእስልምናው የመታቀፍ ሥርዓት ደግሞ የመታቀፍ ሥነ-ስርዓቱ የሚፈፀመው በሕፃኑ የግዝረት እለት ነው፡፡

በመሆኑም ክርስቲያኑ ሕፃን ክርስትና አባቱ ታቅፎት ክርስትና ሲነሳ ቅብዓ ቅዱስ እንደሚቀምስ ሁሉ፤ ሙስሊሙ ሕፃን ደግሞ ታቃፊ አባቱ ታቅፎት ይገረዛል፡፡ ሂደቱን የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልፁት "በሙስሊሙ የዓይን አባት፣ የዓይን እናት የሚባል ባህል አለ፡፡ ይህም ሲገረዝ የሚያቅፈው ነው፡፡ በክርስትናው በኩል እንዳለው እንደ ክርስትና አባት ነው የሚቆጠረው ባህሉ፡፡ የቡሄ ዳቦ ይጋገርለታል፡፡ ልብስ ይገዛለታል[244]፡፡" በማለት ነው፡፡ ስለዚህ የክርስትናውም ሆነ የመታቀፉ ትውፊት አውዱ ከመለያየቱ በስተቀር ፎክሎራዊ ክዋኔውና ሂደቱ፣ እንዲሁም ፋይዳው ተመሳሳይ ነው፡፡

---

[243] በሪሁን ይመር፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ-ቁጥር 14 ቀበሌ፡፡

[244] አበባ ደምሴ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ዶሮ ግብር፡፡፡

የዚህ አይነቱ ተመሳሳይነት ደግሞ ከሃይማኖቶቹ ወይም ከባህላዊ እሴቶቹ አልያም ከሁለቱ ቅልቅል አንዱ ከሌላው በመውረስ የተገኘ ትውፊት መሆኑን መገመት ይቻላል። የመወራረሱ መሰረታዊ ምክንያት አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን የባህል፣ ወግና ልማድ ልዩነት ለማጥበብ ከመሻት የዘለለ አይሆንም። ለምሳሌ በአበልጁ ትውፊት ቤተሰባዊ ትስስር መመስረት እንደሚቻል ሙስሊሙ ያውቃል። በዚህ መሰረት የመታቀፍ ትውፊት ከእስልምናው ጋር የሚያስተሳስረው አንዳችም ጉዳይ ባይኖርም እንኳን ሙስሊሙ ከባህሉ ጋር አስተሳስሮ ከክርስቲያኑ ጋር ይገናኝበታል፤ ይዛመድበታል። በተመሳሳይ ክርስቲያኑ የመታቀፍ ትውፊት ከክርስትናው ጋር እንደማይገናኝ ያውቃል። ነገር ግን ባህሉን ተቀብሎ ከሙስሊሙ ጋር ይገናኝበታል፤ ይዛመድበታል። ስለሆነም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ በነዚህ ሁሉ ትውፊቶች ይገለፃል።

6.1.1.2.4.- ማስመረቅ

በሌላ በኩል በአበልጅ ትውፊት የክርስትናውን እና የመታቀፉን ትውፊቶች የሚያመሳስላቸው ጉዳይ "ማስመረቅ" የተሰኘው ማኅበራዊና ባህላዊ ፋይዳ ያለው የወሎዬዎች የጋራ እሴት ነው። ማስመረቅ በወሎ ክርስትና ያነሳው ወይም ታቃፊው አካል ለክርስትና ልጁ ወይም ለዓይን ልጁ የቡሄ እለት ዳቦ ጋግሮ ወይም ሙሬራ አስደፍቶ፣ ልብስ ገዝቶ ልጁን በቤተሰብ፣ በዘመድ አዝማድና በጎረቤት ማስመረቅ ማለት ነው። ትውፊቱን ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ ከማኅበራዊ ጥቅሙና ከባህላዊ ፋይዳው አንፃር እንደሚከተለው ያብራሩታል።

> መተቃቀፍ ማለት ልጆች የተወለዱ ጊዜ ሴቱ በሴት፤ ወንዱ በወንድ ይተቃቀፋል። በክርስቲያኑም ሆነ በእስላሙ አለ። ዳቦ ይጋገራል። ዳቦውን የሚወስደው አቃፊው አካል ነው። አቃፊው ዳቦ ብቻ መቼ ነውና የሚወስደው። ልብስም አለ። ፎጣ አለ። እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮች አብረው ተዳቦው ጋራ ይሄዳሉ። እኒያ ሲመለሱ ደሞ አብልተው፤ አጠጥተው፤ እራሳቸውን ቅቤ ቀብተው፤ ምን ብለው፤ ምን ብለው ይሸኟቸዋል። እንደውም አሁን፣ አሁን ተለወጠ ወደ ትልቅ ድግስ እየመጣ፣ ደሮው፣ በጉ፣ ፍየሉ እየታረደ እየተበላ፤ እየተጠጣለ፣ እየተገባበዘ፣ ዝምድና እየተቀጣጠለ እየሄደ ነው። የዝምድና ባህል ነው ይሄ፤ ዛሬም አለ[245]።

ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ በበኩላቸው "እኔ ውርጌሳ ሳለሁ ለምሳሌ አንድ ዓሊ ይማም እሚባል እስላም ነበረ። ስለምንዋደድ ልጄን ታቀፍልኝ አለኝ። ታቀፍኩለት። የእሱን ልጅ ታቅፌ እንደዚሁ እንደሰዎቹ በያሙቱ ዳቦና ልብስ እየወሰድኩኝ ሳስመርቅ ነበረ" በማለት አጠቃላይ ባህሉን እንደሚከተለው ይገልፀታል።

---

[245] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።

አንድ ሰው አሁን ለምሳሌ፣ ክርስትና ያነሳል፤ ወይም ደሞ ይታቀፋል። ክርስትና ሲያነሳ ወይም ሲታቀፍ ዳቦ ጋግሮ፣ ልብስ ገዝቶ ክርስትና ወዳነሳው ወይም ወደታቀፈው ልጅ ቤት ይዞ ይሄዳል። ይኼ ለወንዱም ለሴቱም ነው። ያ ሰውዬ ደሞ ከዚያ ከቤቱ ጠምቆ፣ አርዶ ይጠብቃል። ያ ዳቦ ይሄዳል። ጎረቤት፣ ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ይጠራል። የሚዘጋጅ ድግስ አለ። ዶሮም የሚያርድ አለ። በአብዛኛው የሚታረደው ግን በግ ነው። ከዚያ ያ ተበልቶ ተጠጥቶ ሲያበቃ ዳቦው ይቆረሳል። ለጎረቤት ይታደላል። ከዚያ ልጁ ወይም ልጂቱ በሰላምና በጤና እንድታድግ፣ ቤተሰብነቱ ለሁልጊዜ እንዲቀጥል ይመረቃል። ዳቦ ይዞ ለሄደው ክፍል ደሞ ወደ ቤቱ ሲመለስ ራሱን ቅቤ ይቀባል። ይኼ ያለ ነገር ነው። እንደው አንዳች የሚያህል ቅቤ ይቀባል። ሰው እንኳን በመንገድ ሲያየው "ይሄ ሰውዬ ክርስትና ደርሶ የመጣ ነው!" ይላል። እንዲህ እንዲህ ያለ ጥሩ ባህል አለ፤ ይሄ አሁንም አለ [246]።

ከላይ ከቀረቡት ሁለት ጥቅሶች መረዳት የሚቻለው መሰረታዊ ቁም ነገር በወሎ፤ በአበልጅ ትውፊት አማካይነት ክርስቲያን ከክርስቲያን፣ ሙስሊም ከሙስሊም እና ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ፤ ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ ጋር እንዴት እርስ በርስ እንደሚተሳሰር ነው። ትስስራቸው ደግሞ ሃይማኖታቸውን መሰረት አድርገው ሳይሆን፤ የማኅበራዊ መስተጋብራቸውን መሰረት አድርገው ነው። በአኗኗር ዘይቤያቸው ላይ ተመስርተው ነው። የወሎዬዎች የሃይማኖት መቻቻል እሴት የሚገለፀው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የማኅበራዊ መስተጋብር ወይም የአኗኗር ዘይቤ አማካይነት ነው። በዚህ የማስመረቅ ትውፊት ዘመድ አዝማድና ጎረቤት በልቶ ጠጥቶ ልጁን ይመርቃል። የምረቃው ይዘትም በልጁና ክርስትና ባነሳው ወይም በታቀፈው አባት መካከል የሰመረ ግንኙነት እንድኖር መመኘት ነው። ለዚህ አባባል የሚከተሉት የክርስትና ምረቃ ለአብነት እንጠቅሳለን።

> በይህ ልጅ ክርስትና አንሽውም እሚደሰት ይሁን!
>
> ልጁ አድጎ ታቃፊ አባቱን አባቴ የሚለው ይሁን!
>
> በሰፊ ደረቱ፤ በአስር ጣቱ የታቀፈውን አባቱን የሚያከብር ይሁን!
>
> አድጎ ለቁም ነገር በቅቶ ሁለቱንም ጧሪ ቀባሪ ይሁን! አሜን![247]

6.1.1.2.5፦ የልጅ አስተዳደግ ትውፊት በወሎ

በወሎ ደጋጎች የዱዓና የቱፍታ ባህል ተፀንሶ፣ በወሎ ዱበርቲዎች የ"ምጡም ገር ይሁን! ልጁም ወንድ ይሁን!" የፋጢማ ቆሪ ትውፊት በሂይር ተወልዶ፤ ክርስቲያኑ በክርስቲያን ግለሰብ ክርስትና ተነስቶ፣ ሙስሊሙ በሙስሊም ወይም በክርስቲያን የመታቀፍ ሥርዓት የሚከናወን

---

246 ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 6 ቀን 2007 ዓ.ም ወልዲያ-ቀበሌ-04።

247 ተበጀ መኮንን፤ ቃለ-መተይቅ፤ ሐምሌ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አቧራ።

ለት የወለሞ ሕፃን፤ ለአቅመ ሃዳም ደርሶ ወይም ለአቅመ ሔዋን ደርሳ፣ ሚዜ ሁኖ፣ ወይም ሆና ድሮና ኩለሞ፣ እሱም በተራው ተድሮና ተኩለሞ ለሦስት ጎልቻ እስኪበቃ ድረስ በየደረጃው የተለያዩ የአስተዳደግ ትውፊቶችን ያልፋል። እነዚህ የልጅ አስተዳደግ ትውፊቶች በወለሞ የቤተሰብና የጎረቤት ወይም የክርስቲያኑና የሙስሊሙ የልጅ አስተዳደግ የጋራ እሴቶች ናቸው። እነዚህ የጋራ እሴቶች የሚገለፁት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፤ "የጎረቤቴ ልጅ ባልወልደውም ልጄ ነው! የእኔን ልጅ ጎረቤቴ ባይወልደውም ልጁ ነው!" በሚለው የወለሞዬዎች የልጅ አስተዳደግ ትውፊት አማካይነት ነው።

የልጅ አስተዳደግ ትውፊት በወለሞ፤ እናቶች ልጆቻቸውን ከራሳቸው ሳይለዩ ለረኽርም አመታት በጥንቃቄና በፍቅር ተንከባክበው ከማሳደግ ጋር ይገናኛል። የልጅ አስተዳደግ ትውፊት በወለሞ፤ እናቶች ልጆቻቸውን ከሁለት እስከ ሦስት ለሚደርሱ ዓመታት ጡት የማጥባት የወለሞ እናቶች ባህል ጋር ይዛመዳል። የልጅ አስተዳደግ ዘይቤ በወለሞ፤ ከቤተሰብና ከጎረቤት ፍቅር ጋር ይተሳሰራል። በወለሞ ልጅ ከእናቱና አባቱ፣ ከአያቱ፣ ከአክስቱና ከአጎቱ፣ እንዲሁም ከጎረቤቱ ጋር ያድጋል፤ አብሮ ይኖራል። በዚህ መሰረት የአንድ ሕፃን ማንነት (ስብዕና) የሚቀረፀው እነዚህን ሁሉ አካላት መሰረት አድርጎ ነው። እነዚህ አካላት ደግሞ ክርስቲያንም ሙስሊምም ናቸው።

በወለሞ የልጅ አስተዳደግ ባህል መሰረት፤ የክርስቲያኗ ልጅ የሙስሊም ጎረቤቷን ጡት ጠብቶ ሊያድግ ይችላል። በተመሳሳይ የሙስሊሟ ልጅ የክርስቲያን ጎረቤቷን ጡት የሚጠባበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ይህ የሚሆነው ደግሞ አንዲት ክርስቲያን ወይም ሙስሊም እናት በወለሞ ገበያም ሆነ ሌላ ቦታ ስትሄድ፤ ልጇን የምትጠብቅላትና የምትንከባከብላት ሙስሊም ጎረቤቷ ናት። ይቺ ሙስሊም ጎረቤት የክርስቲያን ጎረቤቷን ልጆች ሲርባቸውና ሲጠማቸው እናታቸውን ተክታ ታበላቸዋለች፤ ታጠጣቸዋለች። በዚህም እናታቸው ከሄደችበት እስከምትመለስ ያላትን አጉርሳና አጠጥታ እራብ ጥማታቸውን ታስታግስላቸዋለች። አንዳንድ ጊዜም ጡቷን ታጠባቸዋለች። ክርስቲያኗም ለሙስሊም ጎረቤቷ ልጆች ይህንኑ ታደርጋለች ። የዚህ አይነቱን ትውፊት የአካባቢው ነዋሪዎች የሚያረጋግጡት በሚከተለው ሁኔታ ነው።

> በጣም እሚገርምህ ነገር እንደውም በእኛ የከተማ ሰው ስለሆነ ትንሽ ልዩነት እየፈጠረ ነው እንጂ፤ በገጠሩ አካባቢ ብትሄድ ክርስቲያኗ በጎረቤት እምታጠባ እስላም ካለች ለእሷ ልጇን አስይዛ ገበያ ትሄዳለች። እስከምትመለስ ድረስም ሕፃኑ የእስላሟን ጡት እየጠባ ይቆያል። የእስላሟም ልጅ ካለ የክርስቲያኗን ይጠባል። የእስላሟም ልጅ እንደዚህ ሆኖ የክርስቲያን ነው አይባልም። የክርስቲያኗም ደሞ የእስላም ነው አይባልም። አብረው የአንድ ሰው ጡት እየጠቡ የሚያድጉበት አጋጣሚ አለ፤ በዚህ በወለሞ። እና በመረዳዳትም ደግሞ ልዩነት

> የለም። ሥጋውም የተካበደው ዛሬ ነው እንጂ፤ድሮ ያን ያህል ቦታ አንሰጠውም ነበር። አኗኗራችን የእስላም የክርስቲያን ነው ሳይሆን፤ በመረዳዳት ነው የምንኖረው። እንዲያውም ካልክ የወሎ እኔ ክርስቲያን ከሆንኩ እህቴ እስላም ናት። ልዩነት የለውም። ስለዚህ ተረዳድተን በደንብ ነው፤ የምንኖረው። እስላም ክርስቲያን የሚባል እኔ እንጃ፤ በመቃብር፣ በመስጊድ እና በቤተክርስቲያን ነው እንጂ፤ በኑሮ አንለያይም[248]።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወሎ የክርስቲያንና የሙስሊም የአኗኗር ዘይቤ በሃይማኖት ተለያይቶ ወይም ሃይማኖትን መሰረት አድርጎ ሳይሆን፤ በጉርብትና ተሰባጥሮ ነው። በዚህ መሰረት የክርስቲያኑ ጎረቤት ሙስሊሙ ነው። የሙስሊሙ ጎረቤት ክርስቲያኑ ነው። በመሆኑም ከላይ በጥቅሱ እንደተብራራው እናቶች በወሎ በተለይ በገጠሩ አካባቢ ገበያ ሲሄዱ፣ እንጨት ለቀማ ሲሄዱ፣ ውሃ ለመቅዳት ሲሄዱ ወይም ለሌላ ተግባር ከቤታቸው ርቀው ሲሄዱ ልጆቻቸውን እና ቤት ንብረታቸውን ለጎረቤት አደራ ሰጥተው ይሄዳሉ። ስለሆነም ክርስቲያኗ የሙስሊም ጎረቤቷን ልጅ ትይዛለች፤ ቤቷን ትጠብቃለች።

በተመሳሳይ ሙስሊሟ የክርስቲያኗን ልጆች ትይዛለች፤ ቤቷን ትጠብቃለች። ስለዚህ አንዱ ሲሄድ ሌላው ቤት እየጠበቀ፣ ልጆችን እየተንከባከበ ይቆያል። በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት መሰረት የልጅ አስተዳደግ ባህል በወሎ፤ ከወሎዬዎች ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው። እንዲሁም ከወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር ጋር የእትብት ያህል ዝምድና ያለው ነው። የወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር ደግሞ እስካሁን የተለያዩ ነጥቦችን በመጥቀስ እንደተብራራው፤ የፍቅርና የሰላም ተምሳሌት ነው።

ይህንን አባባል የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልፁት “እኔ ተወልጄ ሳድግ እስላሞች ናቸው ጎረቤቶቼ። አንተ ከነእከሌ ቤት እንዳትበላ፣ እንዳትጠጣ፣ ለነእከሌ እንዳትላክ ወዘተ...እየተባልኩ ሳይሆን ያደኩት፤ ለጎረቤቶቼ እየተላኩኝ፣ ከሙስሊሙ ቤት ገብቼ እንደል ጅነቴ ከሙስሊሙ ጓደኛዬ ጋር በልቼ፣ እሱ ደሞ የእኛ ሲታረድ እንደፊለገ በልቶ ይሄዳል፤ ቤተሰብ ምንም አይልም። “ልጆች አደሉ እነሱ!” ነው እሚለው[249]።” በማለት የልጅነት ትዝታ ቸውን ምሳሌ በመጥቀስ ነው። የእንድሪስ አህመድ ትዝታ ደግሞ ከአብዱዬ ወይም ከእረቡ ቁርስ ጋር ይገናኛል። መረጃ አቀባዩ እንደሚሉት የአብዱዬ ቁርስ በወሎ ለክርስቲያኑም ልጅ፤ ለሙስሊሙም ልጅ የጋራ ትዝታ ነው። የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት

---

[248] አስካለ አበበ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ።

[249] ሞላልኝ ወርቁ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- መሐል መቻሬ።

> የሮብ ወተት ማጠራቀሚያ ውስጥ አይገባም፤ እረግቶ ቅቤ እንዲሆንም አይፈለግም፡፡ የሮብ ወተት ምንድ ነው የሚደረገው፤ ይታለብና ቂጣ ተጋግሮ የጎረቤት ልጆች በወተት እያማኑ እንዲበሉ ይደረጋል፡፡ ወደ መስጊድም ይላካል፡፡ የአብዱዬ ቁርስ ይባላል፡፡ ክርስቲያኑም አልቦ ወይ ለጎረቤት ልጆች ይሰጣል ወይ ወደ መስጊድ ይልካል፡፡ ክርስቲያኑም ወደ ማጠራቀሚያ አያስገባም፡፡ በዚህ ምክንያት የክርስቲያኑም የሙስሊሙም ልጆች አብዱዬን በጉጉት ይጠብቁታል፡፡ አሁን ይሄ በይህ በቆላው አሁንም ድረስ አለ፡፡ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም በጋራ ያረገዋል፤ ባህል ነው[250]፡፡

ከላይ የተጠቀሰው የእስልምና ትውፊት የሆነው የአብዱዬ ትሩፋት ለሙስሊሙ ልጆች ብቻ ሳይሆን፤ ለክርስቲያኑም ልጆች ጭምር ነው፡፡ በተመሳሳይ በምዕራፍ አምስት ውስጥ እንደተብራራው የክርስትናው ትውፊቶች የሆኑት የገናና የጥምቀት፤ የሆያ-ሆዬ እና ሌሎች ባህላዊ ትሩፋቶች የክርስቲያኑ ልጆች ብቻ ሳይሆኑ፤ የሙስሊሙ ልጆች ጭምር ናቸው፡፡ በዚህም ሙስሊም ክርስቲያኑ እኩል ይዝናኑባቸዋል፡፡ እኩል ይደሰቱባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ባህላዊ እሴቶቹ ለሁለቱም የጋራ ሃብቶች ናቸውና፡፡



ፎቶግራፍ15፦ ሙስሊሞቹና ክርስቲያኖቹ ሕፃናት በክርስቲያኑም በሙስሊሙም ቤት እየዞሩ"ሶለል" ሲጫወቱ፡፡

ለምሳሌ የሆያ-ሆዬ ትውፊት በወሎ፤ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም ልጆች በጋራ የሚሳተፉበት የሁለቱም የጋራ እሴት ነው፡፡ በምዕራፍ አምስት እንደተገለፀው በወሎ የገና ጨዋታ፣ የጥምቀት ዘፈንና ጭፈራ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም ልጆች የጋራ ባህላዊ እሴቶች ናቸው፡፡ እሴቶቹ ከመዝናኛነት ባለፈ ሁለቱም ሎሚ ወርውረው፤ አደስ፣ አሩቲ፣ አሸኩቲና ናትራ ስጦታ ሰጥተው፣ ለልጃገረዶች ድንብል አስረው የከንፈር ወዳጅ ይይዙባቸዋል፤ እጮኛ ያጬባቸዋል፡፡

---

[250] እንድሪስ አህመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 28 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 03 ቀበሌ፡፡

በዚህ ምክንያት ሁለቱም እነዚህን ወቅቶች እኩል ይናፍቋቸዋል፤ እኩል ይዘጋጁባቸዋል። በመጨረሻም እኩል ይዝናኑባቸዋል፤ እኩል ይደሰቱባቸዋል።

እነዚህ እሴቶች በወሎ በቤተሰብ የተፈቀዱ፤ በጎረቤት የተወደዱ፤ በሃይማኖት ተቋማቱ የተባረኩ የወሎዬዎች የጋራ ሃብቶች ናቸው። በዚህ መሰረት የልጅ አስተዳደግ ዘይቤ በወሎ፤ ፈር የሚይዘው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ አማካይነት ነው። የዚህ አይነቱ የወሎዬዎች ባህላዊና ማኅበራዊ አውድ ደግሞ ከመለያየት ይልቅ አንድነትን ወይም መሰባሰብን፣ ከጥላቻ ይልቅ ፍቅርና ሰላምን የሚያፀና ነው።

በዚህ አውድ መሰረት በወሎ ልጅ የሚያደርገው ሃይማኖቱን መሰረት ያደረገ የአለባበስም ሆነ ያጊያጊያጥ ዘይቤ ሳይከተል ነው። ለምሳሌ ክርስቲያኖቹም ሆኑ ሙስሊሞቹ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ፀጉራቸውን ሲላጩ እንደየእድሜ ደረጃቸው ጋሜ፣ ቁንሮ፣ ወይም ጉዲሮ አልያም ጋሜና ቃሪሳ ይወጣላቸዋል። እንዲሁም ክርስቲያንም ይሁኑ ሙስሊም ልጃገረዶች ያላገቡ መሆናቸውን ለመግለጽ "ሳዱላ" ይከረከማሉ። ትፍትፍ ቀሚስ ይለብሳሉ። ሲያድጉም ያገቡት ሙስሊም ሴቶች ጉፍታ ጣል ከማድረጋቸው በስተቀር፤ ሹሩባ ይሰራሉ። ሹሩባ በተሰሩት ጠጉራቸው፣ በአንገታቸውና በእጃቸው ላይ ደግሞ እንደ ዛጎል፣ እንደ አምባር ያለ ልዩ ልዩ ጌጣጌጥ ያደርጋሉ። እንዲሁም እንደየ አካባቢው ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ፤ ድሩም ማጉም የቤት ፈትል የሆነና በልዩ ልዩ ጥበብ ያጌጠ ረዥም ቀሚስ ይለብሳሉ። ቀሚሱንም በልዩ ልዩ ጥለት ባጌጠ ወፍራም መቀነት ይታጠቁታል።[251] ሲታጠቁትም በጣም አጥብቀው ስለሆነ ከራባቸው እርሃባቸውን ይቆጣጠሩበታል። ከዚህም የተነሳ፤

ራበኝ እናቴ፤ ውኃ ጠማኝ እቴ

ጉዳቴን ማን ያውቃል፤ ያለ መቀነቴ

እያሉ ያንጎራጉራሉ። በሌላ በኩል ሙስሊሞቹም ሆኑ ክርስቲያኖቹ ሴቶች ልዩ ልዩ ጥበብ ኩታ ይለብሳሉ። ወለባ፣ አሸንክታብ፣ የጆሮ ጉትቻ፣ የአንገት ሃብል፣ የእጅ አምባርና የእግር አልቦ ያደርጋሉ። ጠልሰም ይታጠቃሉ። ጥርሳቸውን፣ አንገታቸውንና እጃቸውን ይነቀሳሉ (ይወቀራሉ)። ዛሬም ቢሆን ጊዜው በሚፈቅደው ሁኔታ ለውጦች ቢኖሩም አሁንም በተለይ በገጠሩ አካባቢ ባህሉ አለ።

---

[251] ዓሊ መሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 13 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አንጦ-04 ቀበሌ።

እንዲሁም ለክርስቲያኖቹም ሆነ ለሙስሊሞቹ ወንዶች ልጆች "ዓይን እንዳይገቡ" እየተባለ በአንገታቸው የቡዳ መድኃኒት ይታሰርላቸዋል። መድኃኒቱ በቃልቻው ወይም በደብተራው የተደገመ ሊሆን ይችላል። ዶቃና ዛጎል፣ ማርዳም ጭምር በአንገታቸው ይደረግላቸዋል። ይህም በፎክሎር አገላለጽ በክርስቲያኑም ሆነ በሙስሊሙ ዘንድ ለጌጥነቱ ብቻ ታስቦ ሳይሆን፤ የሚያያቸው ሰው ዓይን ከነዚህ ጌጣጌጦች ላይ እንዲያርፍ ታስቦ ነው።

በዚህ አይነት ብሂል ላይ የተመሰረተው የወሎዬዎች የልጅ አስተዳደግ ዘይቤ፣ የአንድነት፣ የፍቅርና የሰላም ተምሳሌት ነው። ትውፊቱ ከልዩነት ይልቅ ለአብሮነት ቅድሚያ የሚሰጥ ነው። ወይም ከመለያየት ይልቅ መሰባሰብን የሚያስተምር ነው። ከመናናቅ ይልቅ መከባበርን የሚሰብክ ነው። ለእኔ ብቻ ከማለት ይልቅ፤ አንተ-ትብስ፣ አንቺ-ትብሽ መባባልን የሚያስቀድም ነው። መረዳዳትን፣ መደጋገፍን፣ መተዛዘንን፣ መተሳሰብን...ወዘተ የሚሰብክ ትውፊት ነው። ታዛዥነትን፣ ትህትናን፣ እውነትን፣ ቅንነትን፣ ሰው አክባሪነትን ባጠቃላይ ሃይማኖትንና ሥነ-ምግባርን አጣምሮ የያዘ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ እሴት ነው።

በወሎዬዎች የማኅበራዊ መስተጋብር ዘይቤ መሰረት ጎረቤትን ጨምሮ፤ ወላጆችና ዘመድ አዝማድ ለልጅ አስተዳደግ የመልካም ሥነ-ምግባር አርአያ የሚሆኑበት አጋጣሚ ብዙ ነው። እነዚህ አካላት ክርስቲያን ሙስሊም ሳይሉ፤ ሕፃናት ፍቅርን፣ ሰላምን፣ መረዳዳትን፣ መከባበርን፣ ታማኝነትን ለጋስነትን፣ በጋራ መብላትና መጠጣትን፣ እውነትን፣ ሰው አክባሪነ ትን...ወዘተ ተላብሰው እንዲያድጉ የራሳቸውን አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። ተበጀ መኮንን እንደሚገልጹት ጎረቤትም ይሁን አልፎ ሂያጅ መንገደኛ አንድ ሕፃን ያልተገባ ድርጊት እየፈፀመ እያየ ዝም ብሎ አያልፍም። ገስፆ፣ ቆንጥጦና መክሮ፤ ከዚያም ሲያልፍ የማን ልጅ እንደሆነ አጠያይቆ፣ ቤተሰቦቹን ጭምር ወቅሶ፣ ሕፃኑ በጥሩ ሥነ-ምግባር ታንፆ እንዲያድግ የራሱን ድርሻ ይወጣል። ይሄ ባህል ነው። ግዴታም ነው። ልጅ መጥፎ ነገር እየፈፀመ አይቶ እንዳላየ የሚያልፍ ሰው እሱ እራሱ የሥነ-ምግባር ችግር ያለበት ሰው ሲሆን ብቻ ነው[252]።

በአካባቢው ነዋሪዎች ማብራሪያ መሰረት ሃይማኖቶቹ፣ የሃይማኖቶቹ አባቶች፣ የወሎ ታላላቆችና ደጋጎችን ጨምሮ፤ በወሎ ለልጅ አስተዳደግ ትውፊት ወሎዬዎች የመልካም ሥነ-ምግባር አርአያ ናቸው። ለምሳሌ በዚህ አይነቱ መልካም እሴት ተቀርፀው የሚያድጉ ሕፃናትም፤ በተራቸው ክርስቲያን ሙስሊም ሳይሉ ታላላቆቻቸውን አይዋ፣ እቴዋ፣ አበዋ፣

[252] ተበጀ መኮንን፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አንጦ- 04 ቀበሌ።

እመዋ፣ ወንድም ጋሼ፣ እታበባ፣... ወዘተ እያሉ በመጥራት ፍቅርና ክብር መስጠት ይጀምራሉ፡፡ ሥነ-ምግባርን የማኅበራዊ ሕይወታቸው ደንብና መመሪያ አድርገው መጓዝ ይጀምራሉ፡፡ የሚከተለውን ጥቅስ ለአብነት እንመልከት፡፡

> በዚህ በኛ አገር ጎረቤትም ሆነ ማንም ሆነ፤ እስላምም ሆነ ክርስቲያንም ሆነ አጎቴ፣ አክስቴ፣ አይዋ፣ እቴዋ፣ ወንድም ጋሼ፣ እታበባ ተብሎ ነው እሚጠራው፡፡ በዚህ አካባቢ አሁን ካንተ ትንሽ በለጥ ካለ "አይዋ!" ነው የምትለው፡፡ እቴዋ፣ አበየ፣ እነየ፣ ማንም ይሁን በእድሜ ትልቅ ሰው ከሆነ "አበየ" ነው እሚባለው፤ ወንድ ከሆነ፡፡ ትልቅ ሴትም ከሆነች "እነየ" ነው እምትለው፡፡ ደሞ ጎልማሳ ሴት ከሆነች "እቴዋ!"፡፡ ይኸ ደሞ እስላም ክርስቲያን አይልም፡፡ እስላምም ብትሆን፣ ክርስቲያንም ብትሆን "አይዋ! እንዲህ አድርግልኝማ!" ነው የሚልህ፡፡ ሽማግሌም ከሆነ "አበየ እንዴት አደራችሁ!?" ነው የሚልህ፡፡ አንድ ሰው ከየትም ይምጣ ከየት፤ ስሙንም እወቀው አትወቀው "አበየ ግባ! እነየ ግቢ! ነው እሚባለው[253]

ከዚህ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው የልጅ አስተዳደግ ትውፊት በወሎ ከቤተሰብ፤ ከዘመድ አዝማድና ከጎረቤት አልፎ ለሌሎች ሰዎች ሁሉ ፍቅርና ክብር በመስጠት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው፡፡ የልጅ አስተዳደግ በወሎ ከወሎዬዎች የእርስ በርስ ግንኙነት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ጋር የተሳሰረ መሆኑን ነው፡፡ በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ የሚገለጸው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የልጅ አስተዳደግ ትውፊት ጭምር ነው፡፡ ለምሳሌ መ·ስሊም ወላጆች በወሎ ሕፃናት ልጆቻቸውን ወደ ክርስቲያኑ የቄስ ትምህርት ቤት ሂደው ፊደል እንድቆጥሩ ይልኩ እንደነበር የአካባቢው ነዋሪዎችም ሆኑ ጥናቶች ይገልፃለ፡፡[254] ይህንንም የሚያደርጉት የቄስ ትምህርት ቤቱ ለመ·ስሊሙ ልጆች ፊደል ከማስቆጠርና የጽሑፍ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ከማድረግ የዘለለ፤ ከሃይማኖት ጋር የተገናኘ ጉዳይ እንደማያስተምራቸው በእርግጠኝነት ስለሚያምኑ ነው[255]፡፡ በመሆኑም የመ·ስሊሙ ልጆች ከክርስቲያኖቹ ጋር በመሆን ፊደል ይቆጥራሉ፤ ጽሑፍ ይለማመዳሉ፤ ሥነ-ምግባር ይቀስማሉ (Kalklachew 1997: 47)፡፡ ሲያድጉም ከመካከላቸው አንዱ ቄስ፤ አንዱ ሼህ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ዕድሜያቸው ከገፋ በኋላ ሁለቱም በሽምግልና ወይም በሌላ ምክንያት ሲገናኙ ደግሞ ፊደል የቆጠሩበትን የቄስ ትምህርት ቤት በትዝታ ወደኋላ ተመልሰው እያስታወሱ በጋራ ይጨዋወታሉ፡፡

---

[253] አማኑኤል ሰማው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 4 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ፡፡

[254] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 8 ቀን 2006 ዓ.ም. መርሳ- 02 ቀበሌ፡፡

[255] ...especially the Christian *qes timhrt bet* give priority and more emphasis to the study of the Amharic alphabet and some reading than to the religious aspect. Indeed children (some times of muslim family) are sent to *qes timhrt bet* precisely because parents want their children to know the alphabet and nothing more (Kalklachew 1997: 47).

በሌላ በኩል የልጅ አስተዳደግ ትውፊት በወሎ ማፍቀርንና መከባበርን እንዲሁም ሰላምን መርሀ አድርጎ እንደሚያድግ ሁለ፤ መታዘዝንም መርሀ ያደርጋል። በዚህ መሰረት በወሎ ልጅ ለቤተሰቡ ይታዘዛል። ልጅ ለጎረቤቱ ይታዘዛል። ትዕዛዙን ፈጽሞ ሲመለስም ከክርስቲ ያኑም ሆነ ከሙስሊሙ ቤት ዳረጎት ያገኛል። ከሙስሊሙና ከክርስቲያኑ የምርቃት በረከት ይቀበላል። በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የልጅ አስተዳደግ ትውፊት መሰረት በቂስ ጎረቤቱ ተባርኮ፣ በሽህ ጎረቤቱ ዱዓና ቱፍታ ሃጃው ሞልቶለት ያድጋል።

በትንሽ በትልቁ፣ በአላፊ አግዳሚው፣ በወንድ በሴቱ፣ በሩቅ በቅርቡ ሰው ሁሉ ተመርቆ የሚያድገው የወሎዬዎች ልጅ ፋሉ ያማረ፣ እዱኒያን የተቸረ፣ የተጣላን የሚያስታርቅ፣ የተቸገረን የሚረዳ...ወዘተ ይሆናል ተብሎ በአካባቢው ነዋሪዎች ይታመናል። በመረጃ ሰጪዎቹ ማብራሪያ መሰረት በዚህ አይነቱ ትውፊት ተመርቆ ያደገ የወሎ ሕፃን ለደካሞች ምርኩዝ የሚሆን፣ የታረዘ የሚያለብስ፣ የተራበ የሚያጎርስ፣ የተጠማ የሚያጠጣ፣ በሃይማኖቱ የፀና፣ እድሜና ጤና ከሰው መውደድ ጋራ የተቸረው ሆኖ እሱም በተራው ወደ ሽምግልናው ይሂዳል። የቤተሰብ፣ የጎረቤት፣ የአካባቢና የአገር ተምሳሌት እስከመሆንም ይደርሳል። እንዲሁም ወደ መመረቁ፣ ታሪክ ወደ መንገሩ፣ ተረት ወደ መተረቱ፣ የተጣላ ወደማስታረቁ፣ ሽማግሌ ሆኖ ወደ መላኩ...ወዘተ ይሸጋገራል[256]።

ከዚህም ሌላ ከጎረቤቱ፣ ከእናት ከአባቱ፣ ባጠቃላይ በማኅበራዊ ሕይወቱ ያየውንና የሰማውን ታሪክ፣ ባህል፣ ወግና ልማድ እሱም በተራው ለልጆቹና ለጎረቤቶቹ ያስተላልፋል፤ ያወርሳል። መከባበርን፣ መረዳዳትን፣ መተባበርን፣ መደጋገፍን፣ ባጠቃላይ ፍቅርና ሰላምን ያስተምራል፤ ይሰብካል። የወሎዬዎች የልጅ አስተዳደግ ትውፊትም፤ በዚህ አይነት ሁኔታ እድሜ ጠግቦ ከዚህ ዓለም በሞት የሚለየውን በወግ በማዕረግ እየሸኘ፤ ተተኪውን ትውልድ በሥነ-ምግባር እያነፀ፤ ከትውልድ ትውልድ፣ ከዘመን ዘመን ይሸጋገራል። ውደቱም ሳያቋርጥ በዚህ አይነት ሂደት ይቀጥላል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ ተተንትነው ከቀረቡት የወሎዬዎች የጋብቻ፣ የሠርግ፣ የሚዜና የልደት ትውፊቶች መረዳት የሚቻለው መሰረታዊ ቁምነገር፤ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለጸውና ፋይዳውም የሚመዘነው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ ወይም ማኅበራዊ መስተጋብር አማካይነት ነው። በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የተነሳው የወሎዬዎች

---

[256] አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ

ማኅበራዊና ባህላዊ መስተጋብር ደግሞ የጉርብትናን ትውፊት በደስታ አብነት መነሻ ያደረገ ነው። ነገር ግን በወሎ ጉርብትና በደስታ በሌሎች የወሎዬዎች ማኅበራዊ፤ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶችም ጭምር ይገለፃል። ከነዚህ እሴቶች መካከል ክብረ-በዓላት ለአብነት ይጠቀሳሉ። በእነዚህ የክብረ-በዓላት ትውፊቶች አማካይነት ደግሞ ክርስቲያን ሙስሊሙ በወሎ እርስ በርሱ ይገናኛል፤ ይተሳሰራል። ይተዛዘናል፣ ይተሳሰባል፤ ይከባበራል፣ ቤተሰባዊ ትስስር ይፈጥራል። በዚህም በሃይማኖት ተቻችሎ በሰላምና በፍቅር ይኖራል። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች ይህንን እውነታ የሚገልፁ አብነቶች ናቸው።

6.1.1.3፦ የክብረ-በዓላት ትውፊቶች በወሎ

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወሎ፤ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ፤ ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ ጋር ተጋብቶና ተዋልዶ በእትብት ዝምድና ተሳስሮ ይኖራል። በወሎ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ፤ ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ ጋር ሦስት ጉልቻ መስርቶም ይሁን፤ በጉርብትና ተሳስሮ በሰላምና በፍቅር አብሮ ይኖራል። የዚህ አይነቱ የአኗኗር ዘይቤ፣ ባህል፣ ወግና ልማድ የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ልዩ መገለጫ ምልክት ነው። ከነዚህ የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ልዩ መገለጫ ምልክቶች መካከል ከወሎዬዎች የክብረ-በዓላት ትውፊቶች ጋር የተገናኙ የጋራ እሴቶች ለአብነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ የጋራ እሴቶች ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችሉ የጋራ ትውፊቶች ናቸው።

ለምሳሌ በወሎ እንደሌላው የአገሪቱ ክፍሎች ሁሉ በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው ወቅት ጠብቀው፤ ቀን ቆጥረው የሚከናወኑ ሃይማኖታዊና ዓለማዊ የሆኑ በርካታ ክብረ-በዓላት አሉ። በነዚህ ክብረ-በዓላት ወቅት ሙስሊሙ ከክርስቲያኑ፤ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጋር ይገናኛል። ቀደም ሲል በምዕራፍ አምስት ውስጥ እንደተጠቀሰው ሙስሊሙ በጥምቀት በዓል ላይ ተገኝቶ አብሮ ያከብራል፤ አብሮ ይበላል፤ አብሮ ይጠጣል፤ አብሮ ይዝናናል፤ አብሮ ይደሰታል።

በወሎ በክርስቲያኑ ዝክር ወይም ማኅበር አሊያም ሰንበቴ ላይ ሙስሊሙ በክርስቲያኑ ቤት ውስጥ ተገኝቶ ከክርስቲያኑ ጋር በጋራ ፀበል-ፃዲቅ ይቀምሳል፤ የበረከቱም ተካፋይ ይሆናል። በተመሳሳይ በወሎ በኢድ፣ በአረፋና በመውሊድ ክርስቲያኑም በሙስሊሙ ቤት ውስጥ ተገኝቶ በዓሉን አብሮ ያከብራል። አብሮ ይበላል፤ አብሮ ይጠጣል። የሙስሊሙ የደስታ ተካፋይም ይሆናል። በወሎ በሙስሊሙ ሰደቃ ላይ ክርስቲያኑ ተገኝቶ አብሮ ይበላል፤ አብሮ ይጠጣል። በወሎ ክርስቲያኑ በሙስሊሙ ዱዓ ላይ ተገኝቶ ሃሴት ያደርጋል።

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ወሎዬዎች እነዚህን ትውፊቶች ከጥንት ጀምሮ ከቅደመ አያቶቻቸው የወረሷቸው ታሪካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባኅላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶች ናቸው። ይህም ሲሆን ከሃይማኖት አንፃር ሙስሊሙ ያለምንም ጫና በነፃነት የራሱን እምነት ይከተላል፤ ያፀናል። በተመሳሳይ ክርስቲያኑም የራሱን እምነት ያለምንም ጫና በነፃነት ይከተላል፤ ያፀናል። ከዚህ ባለፈ አንዱ በሌላው ላይ የግል እምነቱን አይጭንም። ለምን ቢሉ፤ የወሎ ዬዎች ባህል፤ ወግና ልማድ እንዲሁም የወሎዬዎች ማኅበራዊና ባህላዊ ደንብና ሥርዓት አይፈቅድም። የወሎ ደጋጎች ከራማና ራሷ የወሎ አድባርም ብትሆን የዚህ አይነቱን አስተሳሰብ አትቀበልም። የሃይማኖቶቹ አስተምህሮም ወይም መርህ ይህንን አያስተምርም፤ አይሰብክም።

ባንፃሩ "እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ!" ወይም "ጎረቤቶቻችሁን እንደራሳችሁ አድርጋችሁ ውደዱ!" የሚለውን መመሪያ በወሎዬዎች ልብ ውስጥ ያሰርፃል[257]። ይህንንም ወሎዬዎች በልባቸው አምነው፣ በህሊናቸው አመዛዝነው እርስ በርስ ይግባባሉ፤ ይከባበራሉ። እርስበርስ ይተሳሰባሉ፤ ይተዛዘናሉ። እርስ በርስ ይደጋገፋሉ፤ ይረዳዳሉ። እርስ በርስ ይዋደዳሉ፤ ይፋቀራሉ። በዚህም በሰላምና በአንድነት አብረው ይኖራሉ። ይህንን የእርስ በርስ ግንኙነትና ትስስር የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> በዚህ በእኛ አካባቢ የተለያዩ ክብረ-በዓላት አሉ። በተለይ ያምን ምክንያት በማድረግ የኛ አካባቢ ሰደቃ በማድረግ እጅግ የታወቀ ነው። በዚህ የሠደቃ ሥነ-ስርዓት ላይ ሙስሊሙ ሥጋ ያርዳል። ግን በጎን ደሞ ለክርስቲያኑ የሚሆን ዝግጅት ተደርጎ ክርስቲያኖቹ ሰደቃ ላይ እንዲገኙ ይደረጋል። ስለዚህ አሁን ምን ማለት ነው? እዚህ ውርጌሳ ላይ፤ የሙስሊም በዓል ላይ የሙስሊም ነው፤ ተብሎ ክርስቲያኑ አይተውም። ክርስቲያኑም የሚደሰትበት በዓል ነው። በክርስቲያን በዓል ላይ ደሞ ሙስሊሞቹ የክርስቲያን በዓል ነው፤ ብለው ዝቅ አርገው አይመለከቱም። ልጆቻቸው ጭምር በዚያ በዓል ላይ ወደ ክርስቲያን ጎረቤቶቻቸው ሂደው አብረው ይበላሉ፤ አብረው ይጠጣሉ፤ በስራም ይደጋገፋሉ[258]።

በተመሳሳይ በክርስቲያኑ በኩል ያለውን የክብረ-በዓላት ትውፊት ደግሞ መሪጌታ ቀለመ ዳኛው የሚገልፁት፤ "በእኛ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ከመስቀል ጀምሮ የተለያዩ ክብረ-በዓላትን እናከብራለን። የልደትም፤ የጥምቀትም፤ የፋሲካም እነዚህን ክብረ-በዓላት ስናከብር ግን ሙስሊም

---

[257] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 8 ቀን 2006 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።

[258] ዮሴፍ ወርቁ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሳ- 01 ቀበሌ።

ቤተሰቦቻችንን (አጽንዖት የኔ)፣ ሙስሊም ጎረቤቶቻችንን፣ ሙስሊም ጓደኞቻችንን በእኛ በዓል ላይ እንዲገኙ እናደርጋለን[259]።" በማለት ነው።

በሪሁን ይመር በበኩላቸው የእርስ በርስ ግንኙነቱን የሚያብራሩት "አሁን ዛሬ ከእኔ ቤት ተደግሶ ከሆነ እስላሙም ክርስቲያኑም ሁሉም ይጠራል" በማለት የራሳቸውን ተሞክሮ ምሳሌ በመጥቀስ የወሎዬዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት በማጎበር ትውፊት አማካይነት እንደሚከተለው ይገልጹታል። "እኔ አሁን በያመቱ የኪዳነ ምህረትን ዝክር እከፍላለሁ። ለምሳሌ ሐምሌ ኪዳነ ምህረትን አሁን ባለፈው ከፍያለሁ። እስላሙም፣ ክርስቲያኑም ቢያንስ ከ300 ያላነሰ ህዝብ ነው ያስተናገድኩት። እስላሙም ክርስቲያኑም በአንድ ሆኖ ማለት ነው። ስለዚህ እኔ የእከሌ ቤት የእስላም ቤት ነው፤ የእከሌ ቤት የክርስቲያን ቤት ነው፤ ብሎ የሚለያይበት አንድም ምክንያት የለም። በዚህ በእኛ ወረዳ ማለት ነው [260]።"

በተመሳሳይ ዓሊ መሐመድ "እስላምና ክርስቲያን ጥርስና ከናፍር ነነ! አንድ አካል አንድ አምሳል ነነ! ፊትም ከአባቶቻችን ያገኘነው ይኸው ነው፤ አሁንም ያለው ይኸው ነው!" በማለት በክብረ-በዓላት ወቅት የክርስቲያኑንና የሙስሊሙን ግንኙነት የሚያብራሩት እንደሚከተለው ነው።

> በኛ አካባቢ ሙስሊሞቹ ዖም ሲፈቱ ክርስቲያን ጎረቤቶቻቸውን እየጠሩ ቤት ያፈራውን አብረው ይበላሉ፤ አብረው ይጠጣሉ። የሚነጠል ነገር የለም። ባይሆን እንዳቅሙ ነው። እንዳቅሙ ጎረቤቱን እየጠራ ይኸ እገሌ እስላምነው፤ ይኸ እገሌ ክርስቲያን ነው አይልም። አብረን እየበላን፤ እየጠጣነ ነው ያለነው። ከጥንትም ያገኘነው ነው። አሁንም አለ። አሁን ለምሳሌ እስላሞቹን በያማቸው ጊዜ ክርስቲያን ጎረቤት ያስፈጥራል። ክርስቲያኗ የእስላም ልጅ እናቴን ላስፈጥር፣ አባቴን ላስፈጥር፣ እህቴን ላስፈጥር፣ ወንድሜን ላስፈጥር፣ ጎረቤቴን ላስፈጥር እያሉ ያስፈጥራሉ። እንዳቅሙ አንዳንዱ አሳርዶ፣ ሌላው ደሞ ቤቱ ያፈራውን፣ አቅሙ የፈቀደውን ያረጋል። እና አሁንም አለ[261]።

ከላይ በቀረቡት ጥቅሶች መሰረት የክብረ-በዓላት ትውፊቶች በወሎ እንደሌሎቹ ትውፊቶች ሁሉ፤ ወሎዬዎች እርስ በርስ የሚገናኙባቸው ድልድዮችና እርስ በርስ የሚተሳሰሩባቸው ክሮች ናቸው። ከላይ እንደተጠቀሰው በነዚህ ትውፊቶች አማካይነት ሙስሊም ክርስቲያኑ በወሎ አብሮ ይበላል፤ አብሮ ይጠጣል። አብሮ ይደሰታል፤ አብሮ ይዝናናል። አንዱ የሌላውን

---

259 መሪጌታ ቀለመ ዳኛው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሳ- 01 ቀበሌ።

260 በሪሁን ይመር፣ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ-ቁጥር 14 ቀበሌ።

261 ዓሊ መሐመድ ፣ቃለ-መጠይቅ፣ሚያዚያ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ሐብሩ-አንጠ-04 ቀበሌ

ሃይማኖት በማክበርና እርስ በርስ በመከባበር በሰላምና በፍቅር አብሮ ይኖራል። በዚህ አይነት የማኅበራዊ መስተጋብር ኑሮ አማካይነት በኅይማኖት ተቻችሎ ይኖራል።

የክብረ-በዓላት ዝግጅት በወሎ፤ ለሚዘጋጅበት ዓላማና በዝግጅቱ መጠን ካልሆነ በስተቀር፤ በብዙ መልኩ ከሠርግ ዝግጅት ጋር ይመሳሰላል። በመሆኑም የክብረ-በዓላት ዝግጅት በወሎ፤ ክርስቲያን ሙስሊሙን ታሳቢ ያደርጋል። ይህም ማለት የክብረ-በዓላት ዝግጅት በወሎ፤ በክብረ-በዓላቱ አይነትና በግለሰቡ አቅም ላይ የሚወሰን ሆኖ፤ ይነስም ይብዛም ዝግጅቱ ክርስቲያኑንና ሙስሊሙን ያካትታል። ምክንያቱም እስላምና ክርስቲያን በወሎ በሥጋ ዝምድና የተሳሰረ ነው። በጉርብትና የተዋሃደ ነው። ለምሳሌ የጉርብትናው ትውፊት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ እናትና አባት ክርስቲያን ወይም ሙስሊም ቢሆኑ፤ ክርስቲያን ወይም ሙስሊም የሆኑ ልጆቻቸውን አይነጥሉም። በተመሳሳይ ሙስሊም ወይም ክርስቲያን የሆኑ ልጆች፤ ክርስቲያን ወይም ሙስሊም እናትና አባታቸውን አይለዩም። አክስትና አጎቶቻቸውንም አይተውም።

ስለዚህ ክብረ-በዓላት ትውፊት በወሎ፤ የሁለቱን ሃይማኖት እምነት ተከታዮች ቤተሰባዊ ትስስር ይበልጥ ያጠናክራል። የእርስ በርስ ግንኙነታቸውንም ይበልጥ ያጎለብታል። የጉርብትና ትውፊቱንም የፀና ያደርጋል። ለዚህም የክርስቲያኑ ክብረ-በዓላት የሙስሊሙ፤ የሙስሊሙ ክብረ-በዓላት የክርስቲያኑ ስለመሆናቸው የአካባቢው ነዋሪዎች የሚያረጋግጡት፤ "እስላምና ክርስቲያን በወሎ፤ አላህና እግዚአብሔር ከማለታቸው ውጪ በማኅበራዊ መስተጋብራቸው የጎላ ልዩነት የላቸውም፤ በእንደዚህ አይነቱ ማኅበራዊ ግንኙነት አንዱ ከሌላው የሚነጠልበት ምክንያት የለም! ለምሳሌ የሙስሊሞቹ ፆም ሲፈታ እኛ ክርስቲያኖች እንደነሱ ነው፤ እኩል ሌሊት ተነስተን ገንፎ የምንበላው። በክርስቲያኑም በዓል ጊዜ ሙስሊም ጎረቤት ከክርስቲያን ጎረቤት የሚለይበት ምንም ምክንያት የለም።"[262] በማለት ነው።

በዚህ መሰረት የወሎ ሰው በክርስቲያኑ ክብረ-በዓላት ወቅት ክርስቲያኑ በበዛበት አካባቢ ለክርስቲያን ጎረቤት በግ ቢያርድ፤ ሙስሊሞቹ ትንሽ ከሆኑ ዶሮ በሙስሊም አሳርዶ ሙስሊሞቹን ያስተናግዳል። ጠላ የማይጠጡ ካሉ፤ ቡቅሬ ለሙስሊሞቹ ይጠመቃል። የስራ ሂደቱም ችግር የለውም። ምክንያቱም ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ ሲያርድ ሙስሊሙ እቃውን ይዞ መጥቶ ምግቡን ያዘጋጃል። ወይም በክርስቲያኑ እቃ ተዘጋጅቶ በመጨረሻ የተዘጋጀበትን እቃ

[262] አሰፋ አበጋዝ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ

እረመጥ ባለው አመድ ጎንፎ ያጥባል። ከዚህ ካለፈም እቃውን ፀበል አስረጭቶ ለራሱ ይጠቀም በታል።[263] በሙስሊሙም በኩል ትውፊቱ ተመሳሳይ ነው። በዚህ መሰረት የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ዘይቤ ሀዲዱን ሳይስት በሰላምና በፍቅር ይጓዛል።

የዚህ አይነቱ የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ዘይቤ በወሎ፤ በወሎዬዎች ማኅበራዊና ባህላዊ አውዱ ከፎክሎር ሣይንስ አንፃር ሲመረመር ያለው አጠቃላይ ገጽታ በዚህ አንፃር የሚገለፅ ነው። በዚህ መሰረት ወሎዬዎች የማኅበራዊ ሕይወት መሰረት በሆኑ ጉዳዮች ላይ አኗኗራቸው ተመሳሳይ ነው። ከላይ እንደተገለጸው ሠርግም ቢሆን፣ ፀበልም ቢሆን፣ ዝክርም ቢሆን፣ ሰደቃም ቢሆን፣ ገናም ቢሆን፣ ጥምቀትም ቢሆን፣ ዒድም ቢሆንም፣ አረፋም ቢሆን፣ መውሊድም ቢሆን፣ አንዱ ለሌላው የቻለ በሃይማኖቱ አባት ያሳርዳል፤ የሃይማኖቱ ባለቤት እራሱ ምግቡን ያዘጋጃል። ያልቻለ ደግሞ ከሥጋ ውጪ የሆነ ወጥ አዘጋጅቶ ከእሱ ሃይማኖት ውጪ የሆኑ ዘመዶቹን፣ ጎረቤቶቹን፤ ጓደኞቹንና ወዳጆቹን ያስተናግዳል።

ሙስሊሙ እሱ ባይጠጣ እንኳን ለሚጠጡት ክርስቲያኖችና ሙስሊም ዘመዶቹ ጠላ ይጠምቃል። ክርስቲያኑም ጠላ ለማይጠጡት ሙስሊም ዘመዶቹና ጎረቤቶቹ ቡቅሬ ይጠምቃል። በዚህም አብሮ ይበላል፤ አብሮ ይጠጣል። በዚህ መሰረት ወሎዬዎች ከልዩነታቸው ይልቅ አንድነታቸው ጎልቶ ይታያል። መተሳሰባቸው፣ መተዛዘናቸው፣ መከባበራ ቸው፣ ሰላምና ፍቅራቸው በእነዚህ ትውፊቶች ሁሉ ይገለፃል። እነዚህ ትውፊቶች ደግሞ ወሎዬ ዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችሉ የጋራ እሴቶች ናቸው።

6.1.2፡- ጉርብትና በወሎዬዎች የእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቶች

ወሎዬዎች እርስ በርስ እንዴት እንደሚገናኙ፣ እንዴት እንደሚተሳሰቡና እንዴት እንደሚ ተዛዘኑ፣ እንዴት እንደሚደጋገፉና እንደሚረዳዱ፣ በሰላምና በፍቅር እንዴት አብረው እንደሚኖሩ፣ እንዴት እንደሚተባበሩና አንተ-ትብስ አንቺ-ትብሽ እንደሚባባሉ ወዘተ...ከዚህ በላይ በቀረቡት የጉርብትና ትውፊቶች አማካይነት የተለያዩ ነጥቦችን በመጥቀስ ተብራርቷል። እነዚህ የጋራ የሆኑ ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶች ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው የሚኖሩባ

---

[263] የዚህ አይነቱን ባህል በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች የልዩነት መገለጫ እንደሆነ አድርገው ሲናገሩ ይደመጣሉ። መከራከሪያ ነጥባቸውም ክርስቲያኑ ለእስልምናው ያለውን ንቀት ወይም ጥላቻ የሚገልጽበት ምልክት ነው ይላሉ። ነገር ግን እውነታው በዚህ ጥናት አቅራቢና በአካባቢው ነዋሪዎች እምነት እነዚህ አካላት እንደሚሉት ሳይሆን፣ ባንፃሩ ወሎዬዎች በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት እንዳይራራቁ ልዩነታቸውን የሚያጠቡበት ዘዴ ወይም ብልሃት ነው። በሌላ አገላለጽ በሚዜ ትውፊት ከጫጉላ ፍፃሜ በኋላ ሁለቱም ወደየሃይማኖታቸው ሲመለሱ በሃይማኖቶቹ አበቶች ከሚፈፀምላቸው ሥርዓት ጋር ተመሳሳይ ነው።

ቸው የጋራ እሴቶች ናቸው። ወይም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ምሳሌዎች ናቸው። በሌላ በኩል የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ በወሎዬዎች የእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቶች ይገለፃል፤ ተግባራዊም ይደረጋል። ምክንያቱም የወሎዬዎች የእለት ተእለት ማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቶች የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ መገለጫዎችና መተግበሪያ መድረኮች ናቸው። እነዚህ የእለት ተእለት የማኅበራዊ ግንኙነቶች በበኩላቸው ከወሎዬዎች የጉርብትና ባህል፣ ወግና ልማድ፤ እንዲሁም ደንብና ሥርዓት ጋር የእትብት ያህል ዝምድና አላቸው። የዚህ ንዑስ ርዕስ ዋና ዓላማም ይህንን መሰረታዊ ጉዳይ ተንትኖ መግለጽ ነው።

የወሎዬዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ቀን ቆጥሮ፣ ወራትና አመታት ጠብቆ፤ ሠርግ ልደትና ክብረ-በዓላት ብቻ አስቦ የሚፈፀም ተግባር አይደለም። ባንፃሩ የወሎዬዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ሰርካዊ ነው። የእለት ተእለት ነው። ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ ካስቻላቸው የጋራ እሴቶች መካከልም እነዚህ የእለት ተእለት ወይም ሰርካዊ ግንኙነቶች ተጠቃሽ አብነቶች ናቸው። ግንኙነቶቹ በበኩላቸው ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ጋር የሰምና የፈትል ያህል ይዛመዳሉ። የሚከተለውን ጥቅስ ለአብነት እንመልከት

> ጨው፣ በርበሬ፣ ቡናና ሽሮም ቢሆን፤ ወላ እንጀራም ቢያልቅ ከክርስቲያን ጎረቤቶቹ ነው እኔ የማመጣው ብዙ ጊዜ። እነሱም ከእኔ ቤት ነው የሚወስዱት። የእስላም ነው ብለው አይተውኝም። ለምሳሌ እኔ እንግዳ ከመጣብኝ ድንገት በቃ! ከሥጋ ውጪ የሆነ ነገር ወጥም ቢሆን ምንም ቢሆን አምጪልኝ እንግዳ መጥቶብኛል ብዬ እጠይቃለሁ፤ ያመጡልኛል። እኔ ሀቅ ልንገርህ። እውነቴን ነው የምልህ። እና የእኛ ጉርብትና እንደዚህ ነው፤ ምንም ችግር የለብንም [264]።

ከዚህ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው ከእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነት አንፃር በወሎ ክርስቲያንና ሙስሊም በጉርብትና ተረዳድቶና ተደጋግፎ እንዴት አብሮ መኖር እንደሚችል ነው። ከዚህም ሌላ በወሎ በግለሰቦች የእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቶች ተጠንስሰው በሂደት የጀማው የጋራ እሴቶች የሚሆኑ ጉዳዮች የሚፈጠሩበት አጋጣሚም ብዙ ነው። ከዚህ በታች የተጠቀሰው የመሪጌታ ቀለሙ ዳኛው ገጠመኝ ለዚህ አገላለጽ ማረጋገጫ አብነት ነው።

> በ1999 ዓ.ም. ሮመዳን ሊገባ እንደዛሬ አንድ እዚህ እንደው የምንገናኝበት ቤት አለ፤ መጠጥ ምናምን እምንልበት። ሠዓት እምናሳልፍበት። እዚያ ተገናኝተን አንዱ ቀልደኛ እስላም "እኛ ወሩን ሙሉ ልንለቅላችሁ ነው! እስቲ የዛሬን እኛ ሰፍቶን እንጠጣ አትሻሙን!" ምናምን በማለት ቀለደ። ከዚያ ቤት በወቅቱ የማር ጠጅ አንድ ብር ነበረ። እንዲህ አግድሜ ሳይ ስምንት ሙስሊሞች አሉ። ክርስቲያኖች ሦስት አራት አለን። የእኛ የደብሩ አለቃም አለ። ለእነዚያ ሰዎች ኮማሪዋን ነይ ብዬ እስቲ አንድ አንድ ብርሌ

[264] ድርቤ ካሳው፣ ቃለ-መጠይቅ፤ ግንቦት 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 05 ቀበሌ።

> ቅጅና በፊታቸው አስቀምጪ የያም መያጣ ነው ብለሽ፤ ብዬ ተናገርኩኝ፡፡ በዚያ እንደው ብዙ ምርቃት መረቁ፡፡ እንደው አነባብረው፣ አነባብረው መርቀው ሲያበቁ፤ ኮማሪዋን ነይ ብዬ ይኸ ማንቆርቆሪያ ስንት ነው የሚይዘው አልኳት፡፡ ሃያ አምስት ብርሌ ይይዛል አለችኝ፡፡ በሉ እንግዲህ አሁን ሮመዳንን በሰላም ያስፈታችሁ! የዒድ-አልፈጥርን የፍቻችሁ በዚህ አንድ ማንቆርቆሪያ ተስየላችኋለሁ ጀባታ! ብዬ አልኳቸው፡፡ ከእኔ ጋር ያሉትም የደብሩ አለቃ አንድ ማንቆርቆሪያ አሉ፡፡ እዚያ ያለው ክርስቲያን ሁሉም አንድ-አንድ ማንቆርቆሪያ አለ፡፡ ስዕለቱ እየበዛ በሄደ ጊዜ ብሩን አሰባሰብን የ1999 ዓመተ-ምህረትን የሙስሊሞች የያም ፍቺ አርደነ ጋርደነ እንደው በሚያምር ሁኔታ በዓሉን አክብረነ ዋልነ፡፡ በዚህ አጋጣሚ እንደቀልድ የተጀመረው ግንኙነት ወደ ትልቅ ደረጃ ተሸጋግሮ አሁን የአንድነት ማኅበርን ልንመሰርት በቃነ[265]፡፡

በጥቅሱ በተተረከው ገጠመኝ እንደተብራራው ወሎዬዎች በሚያደርጓቸው የእለት ተዕለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቶች አማካይነት በርካታ ቁምነገሮች ይፈልቃሉ፡፡ በርካታ የማኅበራዊ መስተጋብር መሰረቶች ይጣላሉ፡፡ የተለያዩ የሰው ለሰው ግንኙነቶች ይዳብራሉ፡፡ የተለያዩ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ተምሳሌት የሆኑ መልካም ዘሮች በመልካም ማሳ ውስጥ ይዘራሉ፡፡ ዘሮችም በመጨረሻ መልካም ፍሬ ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የዕለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቶችን ምክንያት በማድረግ በአጋጣሚ ተጠንስሰው በአሁኑ ጊዜ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ተምሳሌት የሆኑ ጉዳዮች በወሎ በርካታ ናቸው፡፡ ለዚህም የእነ መርጌታ ቀለመ· "የአንድነት" ማኅበር ለአብነት ይጠቀሳል፡፡

የአንድነት ማኅበር የሚገኘው ሐብሩ ወረዳ ውስጥ ውርጌሳ ከተማ ነው፡፡ መነሻው የእነመርጌታ ቀለመ· ገጠመኝ ሆኖ፤ በአሁኑ ጊዜ የክርስቲያኖቹና የሙስሊሞቹ የጋራ ማኅበር ነው፡፡ የማኅበሩ ዋና ዓላማ ክርስቲያን ሙስሊመ· እርስ በርስ የሚገኛኝበት፤ አንድነቱን ይበልጥ የሚያጠናክርበት፣ ጉርብትናውን የሚያፀናበት፣ ቤተሰባዊ ትስስሩን የሚያጠብቅበት፣ ባጠቃላይ መ·ሰረሊም ክርስቲያኑ በጋራ አብረው የሚበሉበትና አብረው የሚጠጡበት፣ ችግሮቻቸውን በጋራ መክረውና ዘክረው በጋራ የሚፈቱበት፣ የተቸገረ የሚረዱበት፣ የታረዘ የሚያለብሱበት፣ የተራበና የተጠማ የሚያበለብትና የሚያጠጡበት ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ አብሮ በመብላትና አብሮ በመጠጣት፣ በመረዳዳትና በመደጋገፍ፣ በመተዛዘንና በመተሳሰብ...ወዘተ እንደሚገለጽ ሁሉ፤ አንዱ ለሌላው ሰላምና ጤና ባለው ምኞት፣ አስተሳሰብና አመለካከት ይገለፃል፡፡ የዚህ አይነቱ እሴት መሰረቱ ደግሞ የወሎዬዎች የእለት ተእለት ማኅበራዊ ግንኙነት ነው፡፡

---

[265] መሪጌታ ቀለመ· ዳኛው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሳ- 01 ቀበሌ፡፡

በነዚህ ግንኙነቶች አማካይነት ከሚፈጠሩ የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ የወሎዬዎች የሰላምታ ዘይቤ ነው። ሰላምታ በወሎ የወሎዬዎች የፍቅር፣ የሰላምና የመከባበር ስሜት መግለጫ የሆነ የጋራ እሴት ነው። ሰላምታ በወሎ የወሎዬዎች የመቀራረቢያና የእርስ በርስ መተሳሰሪያ ክር ነው። ሰላምታ በወሎ የወሎዬዎች የማኅበራዊ መስተጋብር ደንብና ሥርዓት ወይም የሥነ-ምግባር መለኪያ መሳሪያ ነው።

6.1.2.1፦ የሰላምታ ትውፊት በወሎ

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ሰላምታ በወሎ እንደቅርርቡ የሚወሰን ሆኖ፤ በተለይ በገጠሩ አካባቢ አንድ ሰው የተኮራረፈ ካልሆነ በስተቀር፤ ክርስቲያንም ይሁን ሙስሊም፣ "የሰው አገር ሰውም" ይሁን የአካባቢው ነዋሪ፣ ማንም ይሁን ማን፣ ከየትም ይምጣ ከየት፣ የትም ይግኝ የት፣ "ደህና አደራችሁ!?፣ ደህና ዋላችሁ!?፣ አማን ናችሁ!?" ተብሎ ነው የሚታለፈው። የሚተዋወቁ ሰዎች ከሆኑ ደግሞ መሳሳሙንና መዘያየሩን (መጨባበጡን) ጨምሮ፤ የግለሰቡ፣ የቤተሰቡ፣ የዘመድ አዝማዱና የጎረቤቶቹ ሰላምና ጤና ይጠየቃል። የከብቶቹ፣ የአዝመራው፣ የመሬቱና የወንዞቹ ሁሉ ሰላምና ደህንነት በወሎዬዎች የሰላምታ ብሂል ውስጥ ይካተታል። የዚህ አይነቱ የሰላምታ ልውውጥ በወሎ የክርስቲያን ሙስሊሙ የጋራ ልዩ መገለጫ ምልክት ነው። ለዚህም ማሲንቆ ተጫዋቾች ግጥም ደርድረውለታል። ዘፋኞች ስንኝ ቋጥረውለታል። ገጣሚያን ተቀኝ ተውለታል። የሚከተሉት ስንኞች ለዚህ አባባል ምሳሌዎች ናቸው።

ወሎ ለዝየራ ደሞ ለሰላምታ
እንዳንች ቁንጅና እንደእኔ ውዴታ
የትም በዘየርኩሽ ባገኘሁሽ ቦታ

የአባት የእናት ወጉ እንዳይቀየር
እስኪ እንደልምዳችን እንዘያየር

የሰላምታ ራህመት ሰጭኝ ቁልፉን
አንቺ የዘየርሽው ተከፍቶም አይውል

እንደምነህ በይኝ አሰላም አሊኩም

አሰላም ልበልሽ አሰላም አሊኩም

በደጋጎቹ አገር በአርሂቡ ስፍራ

ሰው ለሰው አይነፍግም ሰላምታ ዝየራ[266]

ቀደም ሲል እንደተብራራውም ሆነ፤ ከነዚህ የዘፈን ግጥሞች መረዳት እንደሚቻለው ሰላምታ በወሎ፤ የወሎዬዎች ባህል፣ ወግና ልማድ መገለጫ ትውፊት ነው፡፡ ሰላምታ በወሎ የወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር ፀንቶ ይኖር ዘንድ እሴቱን የሚያስቀጥል ደንብና ሥርዓት ነው፡፡ ሰላምታ በወሎ የወሎዬዎች የመከባበር፣ የሰላምና የፍቅር ሰንደቅ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ሰላምታ በወሎ ክዋኔ አለው፡፡ ለአከዋወኑም ደንብና ሥርዓት አለው፡፡ ይህም ቀጥታ ግንኙነቱ ከፎክሎር ጋር ነው፡፡ በዚህ ሰላምታ በወሎ እድሜን፣ ሃይማኖትን፣ ያታንና ማኅበራዊ ደረጃን መሰረት ያደርጋል፡፡ ሰላምታ በወሎ ማኅበራዊና ባህላዊ አውድን የነገሩ ሁሉ መካተቻ ያደርጋል፡፡

ለምሳሌ በወሎዬዎች የሰላምታ ትውፊት መሰረት አንድ ቄስና አንድ ሼህ መንገድ ላይ ቢገናኙ “ሼሁ ወይም ሼህ እከሌ እንደምን አደሩ!? እንደምን ዋሉ!? አማን ናችሁ!? መምሬ እከሌ እንደምን አደሩ!? እንደምን ዋሉ!? አማን ናችሁ!? የሚሉት የቄሱና የሼሁ የሰላምታ ልውውጦች የሁለቱን ማለሰቦች የፍቅር፣ የመዋደድና የመከባበር መጠን አይገልፁላቸውም፡፡ ወይም የመከባበር ደረጃቸውን አይመጥኑላቸውም፡፡

በዚህ መሰረት አንድ ቄስና አንድ ሼህ በወሎ መንገድ ላይ ሲገናኙ የሚለዋወጡበት የሰላምታ ዘይቤ አንዱ ለሌላው ያለውን ክብር እና ፍቅር በሚገልፁ ቃላት (Honorific terms) አማካይነት ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ቄስና አንድ ሼህ በወሎ መንገድ ላይ ሲገናኙ ሰላምታ የሚለዋወጡት ቄሱ ሼሁን፤ “ሼሃችን፣ ሼሆቹ፣ እነሼህ፣ እንደምን አደሩ!? እንደምን ዋሉ!? አማን ናችሁ ወይ አቦ!” በሚል የሰላምታ ልውውጥ ዘይቤ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሼሁ ቄሱን፤ “መምሩ!” ብለው በመጥራት ነው፡፡

የዚህ አይነቱ የሰላምታ ልውውጥ ዘይቤ በወሎ የቄሱንና የሼሁን የፍቅርና የቅርርብ መጠን፣ የመከባበር ደረጃ፣ የአስተሳሰብ ልዕልናቸውን እና የሰላም ሀዋሪነታቸውን የሚገልፁ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ቄሱ “ሼሃችን፣ እነሼህ፣ ሼሆቹ፣” ብለው ሲጠሩ “የሃይማኖት አባታችን!” ማለታቸው ነው፡፡ ሼሁም፤ “መምሩ!” ሲሉ ተመሳሳይ አንድምታ አላቸው፡፡ ይህም ከልብ የመነጨ ፍቅር፣ ከልብ የመነጨ መከባበር በመካከላቸው መኖሩን በሚገባ ይገልፃል፡፡

---

[266] አያሌው ብሩ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ጉባላፍቶ-ሳንቃ፡፡

ከዚህም ሌላ ቄሱና ሼሁ ሰላምታ ሲለዋወጡ ቄሱ "እግዚአብሔር ይመስገን!" በማለት ለሼሁ መልስ ይሰጣሉ። በአንፃሩ ሼሁ ለቄሱ "አሃምዲሊላ!" በማለት ይመልሳሉ። በዚህ መሰረት ምሥጋና የሚቀርብለት ፈጣሪ የተገለፀበት ቋንቋ መለያየቱ ለቄሱና ለሼሁ ግንኙነት አጥር አልሆነባቸውም። ከልብ ለመነጨ ፍቅር፣ ከልብ ለመነጨ መከባበር ቄሱንና ሼሁን አላገዳ ቸውም። በመሆኑም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለፀው በዚህ አይነቱ የእርስ በርስ መከባበር፣ መዋደድና መፈቃቀር አማካይነት ነው። የዚህ አይነቱን የጋራ እሴት የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልፁት እንደሚከተለው ነው።

> ሰላምታ አሁን በጣም እሚገርምህ በተለይ ቃልቾቹ፣ ሼሆዎቹና ቄሶቹ የተማሩት ሲገናኙ ትክሻ ለትክሻ ተሳስመው ነው እሚለያዩት። ቄሱ መስቀል በእጃቸው ይዘው ቃልቻው ወይም ሼሁ በትከሻ ሰላም ብሏቸው ይሄዳል። አይሳለምም እንጂ፤ ሰላምታ አይተላለፉም። "እነሼህ እንዴት ናችሁ!፣ ሼሆቹ ደህና ናችሁ!? ሼሃችን አማን ናችሁ!? ያደሞ "መምሩ እንዴት አደሩ!? ደህና አደሩ!? ነው እንጂ፤ ስም አለው ተብሎ በስሙ አይጠራም። ክብርን አይነካም። እንደዚህ የመናናቅ ሁኔታ በዝህ በኛ አገር የለም [267]።

በጥቅሱ እንደተገለፀው የሁለቱ ሃይማኖት አባቶች የሰላምታ ልውውጥ በዚህ አይነቱ የሰላምታ ልውውጥ ትውፊት ብቻ የሚወሰን አይደለም። በአንፃሩ የሰላምታ ልውውጥ በወሎ ከዚህም ያለፈ የጋራ እሴት አለው። ምክንያቱም በወሎዬዎች የሰላምታ ልውውጥ ትውፊት መሰረት ከሁለቱ አካላት ሰላምታ በኋላ እግረ መንገድ፣ የተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ተነስተው ውይይት ይደረግባቸዋል። በተለያዩ ምክንያቶች ውይይቶቹ ሳይቋጩ ቢቀሩ እንኳን በይደር በሚከተለው ሁኔታ ቀጠሮ ይያዝላቸዋል።


> ሰላምታማ ያለ ነው እንጂ። እንደውም ቢያንስ ካልቸኮለ፣ አንደኛው ወገን እሚቸኩልበት ጉዳይ ከሌለው ቢያንስ የአምስት ደቂቃ ይቅር የአስር ደቂቃ ቆመው ሳያወሩ አይለያዩም። መዘያየር ቀርቶ ብዙ ተቀላልደው፣ ብዙ ተጨዋውተው፣ ብዙ ብለው ነው። መቼ እንገናኛለን ተባብለው ነው፣ የእለት የተረፋቸውን፣ በእለት ካወጉት የሚተርፋቸውን ደሞ መቼ እንገናኛለን ተባብለው፣ቀጠሮ ይዘው ነው እሚለያዩት። እና ያለ ነው። ይሄ አንዱ ባህላችን ነው[268]።

በወሎ በጋብቻ፣ በሚዜ፣ በአበልጅ፣ በማኅበርና በሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች አማካይነት ቤተሰባዊ ትስስር መፍጠር እንደሚቻል ሁሉ፤ ሰላምታም በወሎ የመከባበር ተምሳሌት ነው። የመተሳሰቢያ፣ የመተዛዘኛ፣ የሰላምና የፍቅር መገለጫ የጋራ እሴት ነው።

---

[267] እንድሪስ አህመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 28 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 03 ቀበሌ።

[268] መሪጌታ ቀለመ ዳኛው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 5 ቀን 2006 ዓ.ም. ውርጌሳ- 01 ቀበሌ።



ፎቶግራፍ 16፦ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ በዚህ አይነት ሃሳብ ተለዋውጠው ይለያያሉ፡፡

በሌላ በኩል ወሎዬዎች እስከ ሰባት ትውልድ ዘር የመቁጠር ባህል አላቸው (ጌታዋ 2004 ዓ.ም)፡፡ በዚህም አንድ ሰው እስከ ሰባት ትውልድ ዘር መቁጠር ከቻለ "እከሌ ዘመዴ ነው!" ይላል፡፡ በዚህ መሰረት ማንም ሰው በወሎ ግለሰቡ ክርስቲያንም ይሁን ሙስሊም ሰላምታ ሲያቀርብ "አጎቴ! አክስቴ! እንደ ናችሁ!? አማን ናችሁ ወይ!? ልጆቹ፣ ከብቶቹ ደህና ናቸው ወይ!? በማለት ዝምድናውን ጠቅሶ ነው፡፡ ይህም ማለት ቄሱ ወይም ሼሁ "መጠሪያ ስም" ጠቅሶ ሰላም እንደማይል ሁሉ፤ አንድ ወሎዬ ዘመዴ ነው ብሎ የሚያስበውን ግለሰብ "መጠሪያ ስሙን ጠቅሶ" ሰላምታ አያቀርብም፡፡ ስሙን ጠርቶ ሰላምታ አቀረበ ማለት ባዕድ ሆነ ማለት ነው ፡፡ የሰው-ሰው ሆነ ማለት ነው፡፡

ወሎዬዎች ዘር ቆጥረው፣ ትውልድ አስልተው "አጎቴ፣ አክስቴ" በማለት ሰላምታ ያቀርባሉ ሲባልም፤ ከዚህ ውጭ ያሉት አካላት ለነሱ "ባዕድ" ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ባንፃሩ ወሎዬዎች እንደየ እድሜ ደረጃቸው ቀደም ሲል በቤተሰብ አስተዳደግ ትውፊት ውስጥ እንደተ ጠቀሰው "አበዋ፣ እመዋ፣ አበየ፣ እነየ፣ አይዋ፣ እቴዋ፣ ጋሽየ፣ እትየ...ወዘተ" የሚሉትን የክብርና የፍቅር መግለጫ መጠሪያዎች ተጠቅመው ሰላምታ ያቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ "አይዋ አማን ናችሁ ወይ!? አበዋ እንደምን ዋሉ!? እንዴናችሁ እነየ!?...ወዘተ" በማለት ሰላምታ ይለዋወጣሉ፡፡ የዚህ አይነቱ ትውፊት የወሎዬዎች ባህል፣ ወግና ልማድ ነው፡፡ የወሎዬዎች ደንብና ሥርዓት

ነው፡፡ የወለዬዎች የማኅበራዊ መስተጋብር መገለጫ እሴት ነው፡፡ የሃይማኖት መቻቻል ተምሳሌትም ነው፡፡

በዚህ መሰረት የዚህ ጥናት አቅራቢ መረጃ ለመሰብሰብ በተዘዋወረባቸው አካባቢዎች ሁሉ እነዚህን ቃላት መስማት የእለት ተእለት ገጠመኞቹ ነበሩ፡፡ እንዲሁም አጥኚው በእነዚህ አካባቢዎች በቆየባቸው ጊዜያት "ጋሽዬ አማን ነው!?" እየተባለ በወለዬዎች አንደበት ሰላምታ ሲቀርብለት ቆይቷል፡፡ ባጠቃላይ አጥኚው ባየውና በሰማው ነገር ሁሉ ወለዬዎች እርስ በርስ ለመከባር እና ሌላውንም ለማክበር፣ ለሰላምና ለፍቅር ያላቸውን እሴት ለመረዳት ችሏል፡፡ በዚህም ወለዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ ካደረጓቸው እሴቶች መካከል አንዱ የሰላምታ ትውፊታቸው መሆኑን ተረድቷል፡፡ ስለሆነም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለዬ፤ በወለዬዎች የሰላምታ ትውፊ እንደሚገለጽ በቦታው ላይ ተገኝቶ፤ ባየውና በሰማው ነገር ሁሉ አረጋግጧል፡፡

ጉርብትና በእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነት እንዴት የሃይማኖት መቻቻል እሴት መሰረት ሊሆን እንደሚችል በወለዬዎች የሰላምታ ትውፊት አብነት ከዚህ በላይ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ በቀረቡት አብነቶች መሰረት ሰላምታ የወለዬዎች የእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነት መገለጫ አንድ አካል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የወለዬዎች ሰርካዊ የእርስ በርስ ግንኙነት በሰላምታ ትውፊት ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ባንፃሩ ወለዬዎች እርስ በርስ የሚገናኙባቸውና የእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነት ውጤቶች የሆኑ ሌሎች የጋራ እሴቶች አሏቸው፡፡ እነዚህ የጋራ እሴቶች ደግሞ ወለዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዴት በጋራ እንደሚኖሩ በተጨባጭ የሚያሳዩ አብነቶች ናቸው፡፡ ከነዚህ አብነቶች መካከል አንዱ የወለዬዎች የቡና ሥርዓት ትውፊት ነው፡፡ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለዬ፤ በዚህ ትውፊት አማካይነት እንዴት እንደሚገለፅ ከዚህ ቀጥሎ ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

6.1.2.2፦ የቡና ሥርዓት በወለዬ

የወለዬዎች ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶች ከሚገለፁባቸው በርካታ የጋራ ጉዳዮች መካከል አንዱ የወለዬ የቡና ሥርዓት ነው፡፡ የቡና ሥርዓት በወለዬ፤ የወለዬዎች የጉርብትና መሰረት ነው፡፡ የእርስ በርስ መገናኛ ድልድይና መተሳሰሪያ ክር ነው፡፡ የቡና ሥርዓት በወለዬ የወለዬዎች የበረከት ምንጭ እና የመልካም እድል ሰበብ ነው፡፡ የቡና ሥርዓት በወለዬ የወለዬዎች የመከባበር፣ የመተዛዘን የመረዳዳት፣ የመዋደድና የመፋቀር፣ የሰላምና የፍቅር ተምሳሌት ነው፡፡ የቡና ሥርዓት በወለዬ፤ ወለዬዎች የሚመጅኑበት፣ ሃጃቸው የሚሞላበት፣ ከወለዬ አድባርና

አውጋር ጋር ልብ ለልብ የሚገናኙበት የጋራ እሴት ነው። የቡናሥርዓት በወሎ፤ ወሎዬዎች አብረው የሚበሉበትና አብረው የሚጠጡበት የጋራ ማዕድ ነው።

ባጠቃላይ የቡና ሥርዓት በወሎ የወሎዬዎች ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶች የሚገለጹበት የጋራ ሀብት ነው። በዚህ መሰረት የቡና ሥርዓት በወሎ ወሎዬዎችን እርስ በርስ የሚያቀራርብና የሚያገናኝ የጋራ እሴት በመሆኑ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለጽበት አንድ ምሳሌ ነው። ይህም ማለት ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ ካስቻሏቸው የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ የወሎ የቡና ሥርዓት ነው። የዚህ ንዑስ ርዕስ ዋና አላማም ይህንን የጋራ እሴት የተለያዩ የቡና ሥርዓት ትውፊቶችን በመጥቀስ ተንትኖ መግለጽ ነው።

የቡና ሥርዓት በወሎ በባልና በሚስት ወይም በአንድ ቤት ውስጥ በሚኖሩ የቤተሰብ አባላት ደረጃ ይፈላል። እንግዳን ታሳቢ አድርጎ ይፈላል። ጎረቤትን ታሳቢ አድርጎ ይፈላል። በወሎ የተርቲብ ትውፊት ላይ ተመስርቶ ይፈላል። የወሎ አድባርን ለማቋደስ ሲባል ይፈላል። ቡና በወሎ ሀዘንና ደስታን ለመግለጽ ታስቦ ይፈላል። ቡና በወሎ ለወዳጅና ለዛር ትውፊት ሥርዓት ማከናወኛ ግብዓት ተብሎ ይፈላል።

ባጠቃላይ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ወሎ የቀናው "በቡና፣ በጠላና በትምባሆ" ትውፊት አማካይነት ነው[269]። ይህም የሆነበት መሰረታዊው ምክንያት የቡና ትውፊት በወሎ ቡና አፍልቶ ለመጠጣት ብቻ ሳይሆን፤ ከዚህ ያለፈ ጥንተ ሥረ-መሰረት ያለው ማኅበራዊና ባህላዊ ፋይዳ ስላለው ነው። በሌላ አገላለጽ የቡና ሥርዓት በወሎ፤ ክርስቲያን ሙስሊሙ የሚሳተፍበት፣ እርስ በርስ የሚገናኝበትና የሚተሳሰብበት የጋራ እሴት በመሆኑ ነው። ይህ ማኅበራዊና ባህላዊ እሴት ፋይዳው የሚገለጸው ደግሞ በወሎዬዎች የቡና ሥርዓት አማካይነት ነው።

ለምሳሌ የቡና ሥርዓት በወሎ ከንፅህና ወይም ከጠሃራነት ጋር ይያያዛል። ይህም ማለት የአካል ብቻ ሳይሆን የልብ ንፅህናንም ይጠይቃል። በዚህም በወሎ በክርስቲያኑም ሆነ በሙስሊሙ ቤት ቡና ሲፈላ ቤት ተጠርጎ፣ አምሮበትና ንፁህ ሆኖ ነው። ቡናውን የሚያፈላው ወይም የሚከድመው አካልም ውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። ቡናው ከሚፈላበት መቼት አንፃር ደግሞ አሩቲው፣ አሸኩቲው፣ ናትራው፣ ጠጂሳሩ አደሱና ሻለ ከጨፌ ጋር ተቀላቅሎ ይጎዘጎዛል። ማጤሻው ቀርቦ አደን አዱሩሱ፣ ከርቤ ሰምቡለ፣ ቀረፋው ወገርቱ፣ ...ወዘተ ይጤሳል።

---

[269] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ

ቡና ሲፈላ በወሎ የቡና ቁርስ ተዘጋጅቶ ነው። "የቡን[270] ቁርሱ፣ የልጅ ልብሱ!" እንዲሉ ወሎዬዎች፤ ለቡና ቁርስ ማጀት ባዶ በሆነበት ወይም ቤት ደጁ ቅጠል በሚሆንበት በነሐሴና በመስከረም ወራት እንኳን ቢሆን፤ በወሎ ቡና ያለ ቁርስ ጎደሎ ነው። የቡና ቁርስ ከዳቦ እስከ አነባብሮ ከቂጣ እስከ ቆሎ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ከታጡ ደግሞ "አሹቅ" እና ንፍሮ የቡና ቁርስ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ በወሎ ቡና ካለ የቡና ቁርስ አለ። የቡና ቁርሱ ደግሞ ለሰዎቹ ብቻ ሳይሆን ለወሎ አድባርም ጭምር ነው።

የቡና ሥርዓት በወሎ ሦስት ደረጃዎች አሉት። እነዚህም አቦል (የመጀመሪያ)፣ ቶና (ሁለተኛ) እና በረካ (ሦስተኛ) በመባል ይታወቃሉ። ከነዚህ የቡና ሥርዓት ደረጃዎች ጋር በቀጥታ የሚገናኙ ሁለት አካላት ደግሞ ከዳሚና መራቂ ናቸው። ከዳሚ በወሎ የቡና ሥነ-ስርዓት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ አለው። የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ከዳሚ በወሎ በአብዛኛው ሴት ናት[271]። በዚህ መሰረት ከዳሚ ነጠል፣ ነጠል ያለች ሳይሆን፣ ከበድ ያለች፣ ደርበብ ያለች፣ ረጋ ያለች፣ ሰከን ያለች መሆን ይጠበቅባታል። ከዚህም ሌላ፤ ነጠላ ወይም የአንገት ልብሷን በደንብ ለብሳ፣ ተጣጥባ፣ በደንብ ጠሃራ ሁና በሥነ-ስርዓት ቁጭ ብላ ቡን እምትከድም መሆን አለባት [272]።

ከወሎ የቡና ሥርዓት ጋር የሚገናኘው ሌላው ፎክሎራዊ ጉዳይ ደግሞ የቡና መራቂና የቡና ምረቃ ትውፊት ነው። የቡና ምረቃ አይነት እና ደረጃ በወሎ ቡናው እንደተፈላበት አውድ ይለያያል። ለምሳሌ የወዳጃ የቡና ምረቃ ከተርቲብ የቡና ምረቃ ይለያል። የፋጢማ ቆሪ የቡና ምረቃ ለቤተሰብ ፍጆታ ከተፈላ የቡና ምረቃ ይለያል። ለዱዓ በተመሰረቱ ቦታዎች ላይ የሚከናወን የዱዓ የቡና ምረቃ ለክብረ-በዓላት በመኖሪያ ቤት ውስጥ ከተፈላ የቡና ምረቃ ይለያል። የምረቃው ክዋኔ ግን ተመሳሳይ ነው። ለምሳሌ በአንድ የቡና ሥርዓት ውስጥ የቡና ምረቃ የሚከናወነው ሁለት ጊዜ ነው። ይኸውም በአቦል ደረጃ የሚከወነው የምረቃ ሥርዓት አንደኛው ሲሆን፤ በበረካ ደረጃ የሚከወነው የቡና ምረቃ ሥርዓት ደግሞ ሁለተኛው ሂደት ነው።

---

[270] በወሎ በገጠሩ አካቢ አሁንም ድረስ "ቡና" "ቡን" ተብሎ ነው የሚጠራው።

[271] በምዕራፍ አምስት ውስጥ እንደተጠቀሰው የወሎ ደጋጎችን በረካ ለማግኘት ከሰባት እስከ ስምንት ለሚደርሱ ዓመታት ወንዶቹ ከእነሱ የቀደሙትን የወሎ ደጋጎች ይከድሙ እንደነበር ይነገራል። ይህም ቡና ማፍላት ብቻ ሳይሆን ሌሎች የአገልግሎት ተግባራትን ሁሉ ይጨምራል።

[272] ሞላልኝ ወርቁ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 14 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- መሃል መቻሬ።

የቡና ምረቃ ትውፊት በወለሞ የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው። ሥርዓቱ ከእድሜ፣ ከያታና ከሃይማኖት ጋር በእጅጉ ይገናኛል። የእድሜ መስፈርት ለሁለቱም ያታዎች እኩል ይሰራል። በዚህም በእድሜ ለገፋው አካላት ቅድሚያ ይሰጣል። ከያታና ከሃይማኖት አንፃር ግን ለወንዶች፤ ከዚያም ለሃይማኖት አባቶች ሥርዓቱ ቅድሚያ ይሰጣል። በዚህ መሰረት በወለሞ የቡና ሥርዓት ወቅት የቤቱን አባወራ ጨምሮ፤ በቡና ሥነ-ስርዓቱ ከታደሙት መካከል በእድሜ ትልቅ የሆነው አካል ይመርቃል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቅድሚያውን የሃይማኖት አባቶች ሊወስዱ ይችላሉ። ይህም ቢሆን እድሜን ታሳቢ ያደርጋል። በተመሳሳይ በቡና ሥነ-ስርዓቱ ላይ አንድ ቄስና አንድ ሼህ ቢኖሩ ቅድሚያ የሚሰጠው በእድሜ ለገፋው አካል ነው። ነገር ግን የአቦሉን የምረቃ ሥነ-ስርዓት ሼሁ ቢመርቁ፤ የበረካውን ቄሱ ሊመርቁ ይችላሉ። በአካባቢው ባህል፣ ወግና ልማድ መሰረት ግን የአቦሉን (የመጀመሪያውን) የመረቀ ሰው የበረካውን (የማክተሚያውን) ይመርቃል።

በእድሜ፣ በያታና በሃይማኖት ላይ የተመሰረተው የወለሞ የቡና የምረቃ ሥነ-ስርዓት የራሱ የሆነ የአመራረቅ ሂደት አለው። ይህም ሂደት እንደየ አካባቢው የሚወሰን ሆኖ የመጀመሪያው ቡና (አቦል) ወርዶ ትንሽ ሰከን ካለ በኋላ ሊቀዳ ሲል፤ ከዳሚዋ ጀበናውን አንስታ ወደስኒው ትንሽ ዘንበል አድርጋ ይዛ፤ "ቀሃ ጀባ!" ወይም "አቦል ጀባ!" አሊያም "ቡን ፈላ!" በማለት ቡናው ሊቀዳ ስለሆነ መርቁ የሚል ግብዣ ለመራቂው አካል ታቀርባለች። ከዚያ መራቂው፤ "አማንና ኢማን ጀባ! በረካ ጀባ! ጤና ጀባ! ሲሳይ ጀባ!...ወዘተ" በማለት፤ ወይም ምረቃውን ከተለያዩ ሁኔታዎች ጋር አያይዞ እንደሚከተለው ይመርቃል።

አማንና ኢማን ጀባ !
ጠላታችን ገደል ይግባ!
የወለድሽው ጀነት ይግባ !
ቆንዳላሽ ወራድ ይሁን!
የምትወልጅው ወንድ ይሁን !
አጃሽ አይውጣ፣ ፈትሽ አይንጣ !
ምን ልስጥ ለልጄ፣ ምን ላስጣ ከደጄ ከማለት ያድንሽ!
በእኛ የዋለ አይኑን ጨለማ፤
እግሩን ቄጤማ ያድርግልን! እሱሱሱ...!"

በማለት "በይ እንግዲህ ቅጂው!"[273] ይላል መራቂ። ይሄ እንግዲህ "ቀሃ ጀባ!" በሚል ከዳሚዋ የጋበዘች እንደሆነ ነው። "ቡን ፈላ!" በሚለው የምረቃ ግብግር ከተጀመረ ደግሞ መራቂው፤

ቡን እንደፈላ ሲሳያችን ይፍላ!
በሼሆቹ፣ በደጎቹ፣ ወሎ መጀን!
ክፉ አንከላፋ ወዲያ ገላል ይበል!
ሰንበት ይጠብቀኑ፤[274]

ብሎ መርቆ ቡናው ይቀዳል። ከዚህ በላይ የተገለጹት የቡና ምረቃ ትውፊቶች በወሎ፤ የመጀ መሪያው ቡና ወይም አቦል ቡና ሲቀዳ የሚከወኑ የቡና ምረቃ ትውፊቶች ናቸው። ሁለተኛው የቡና ምረቃ ትውፊት ደግሞ የማክተሚያ ወይም የማሰረጊያ አለያም የበረካ ምረቃ ነው። በዚህ ሂደት ከዳሚዋን ጨምሮ፤ የተለያዩ አካላት ይመርቃሉ። ለምሳሌ ምረቃው ከዳሚዋን የሚመለከት ከሆነ፤ "ቡናው እንዳለቀ ክፉ ቀንሽ ይለቅ!" ወይም ከዳሚዋ እርጉዝ ከሆነች "የሆድሽን በጀርባሽ ያዙረው!" ወይም ከዳሚዋ ገና ወጣትና ያላገባች ከሆነች "በሃብት እደጊ ተዳሪ ተኳይ! ውለጂ ክበጂ!...ወዘተ" ተብላ ልትመረቅ ትችላለች። "የሆድሽን በጀርባሽ ያዙረው!" ሲባልም በሰላም ተገላግለሽ (ወልደሽ) ልጅሽን ለማዘል ያብቃሽ ማለት ነው[275]።

ባጠቃላይ በወሎ የቡና ምረቃ ሥርዓት መሰረት ከዳሚ ይመረቃል። በቡና ሥርዓቱ ላይ የተገኙት ሰዎች ሁሉ ይመረቃሉ። አካባቢው፣ ከብቱ፣ እንስሳቱና እፅዋቱ ሁሉ ይመረቃል። እንዲሁም ህዝብና መንግሥት የሚስማሙበት ምረቃ ይደረጋል። ሰማይና መሬት የሚታ ረቁበት ምረቃ ይደረጋል። ሰውና ሰው፣ ሰውና ፈጣሪ፣ ወሎዬዎችና የወሎ አድባር ...ወዘተ የሚስማሙበት ምረቃ ሁሉ ይደረጋል። በዚህ መሰረት የቡና ምረቃ በወሎ በመልካም ምኞት የተሞላ ነው። የበረካ፣ የሰላምና የፍቅር ምንጭ ነው። የመልካም ነገር ሁሉ ሰበብ ነው። የወሎዬዎች የጋራ እሴት ነው። ይህን እሴት ወሎዬዎች የሚገልፁት "እንግዲህ ምረቃ እንደው አንተ ስትመርቀኝ፤ በረካ አላህ ያርግህ! ስትለኝ እማገኝ ይመስለኛል። ወሎ እንግዲህ ይሽ ነው![276]።" በማለት ነው። ይህም የልባቸውን መሻት፣ የፍቅርና የመዋደዳቸውን መጠን

---

[273] አቶ መሐመድ ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2004 ዓ.ም. ራያና ቆቦ- ሮቢት።

[274] አያሌው ብሩ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 9 ቀን 2004 ዓ.ም ጉባላፍቶ ሳንቃ።

[275] ዓለሙ ኃይሉ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 10 ቀን 2006 ዓ.ም. መርሳ- 02 ቀበሌ።

[276] አበጋር ማዱ በላይ ፤ቃለ-መጠይቅ፤ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም ጉባ ላፍቶ-ገዶ።

የሚገልጽ የጋራ እሴት ነው። ለዚህም ነው፤ "በረካ ሁን ብሎ ወሎ ሲመራረቅ፤ ያኔ ነው አድባሩ ሰው የሚታረቅ!" በማለት ለወሎ ስንኝ የቋጠሩለት።

ሌላኛው የቡና ሥርዓት በወሎ፤ ማክተም ወይም "በረካ መቅመስ" የተሰኘው ትውፊት ነው። ማክተም ወይም በረካ መቅመስ ማለት በወሎ በአካባቢው ነዋሪዎች ትርጉም መሰረት ማሳረግ፣ መጨረስ፣ ማጠናቀቅ ማለት ነው[277]። ማክተም የሚለውን የወሎዬዎች ባህል፣ ወግና ልማድ የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት "ወሎ ቡና ሲጠጣ ርስቱን ተቀማ!" ከሚለው አባባል ጋር አገናኝተው ነው። ለዚህ የሚያቀርቡት ምክንያት ደግሞ ከወሎዬዎች የቡና ሥርዓት ጋር የተያያዘ ነው። ወይም የቡና ሥርዓት በወሎ፤ ከወሎዬዎች ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሥነ-ልቡናዊ ጉዳዮች ጋር የተሳሰረ አስተሳሰብ ስላለው ነው። ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ጥቅስ ለዚህ አባባል ማረጋገጫ ምሳሌ ነው።

> በወሎ የቡና ሥርዓት መሰረት ቡና እየተጠጣ፤ ብድግ-ብድግ፣ ወደዚያ-ወደዚህ፣ ምናምን ማለት የለም። እንደዚህ እንኳን የሚል ካለ "አድበሽ ቁጭ በይ! ምን ይቺ ቆሌ ቢስ! ቡና እየተጠጣ ምንድን ነው መንቀዥቀዥ!" ሊባል ይችላል። በወሎ የቡና ሥርዓት መሰረት አንድ ሰው በሥነ-ስርዓቱ ቁጭ ብሎ አቦል፣ ቶናና፣ በረካ ማክተም አለበት። እንዲያው የሚያስቸኩል ነገር እንኳን ካለ "አቦ! እንግዲህ አፋ በይኝ! "ይቺ ልይ እያካለበችኝ ነው! እንዲያው ደረስ ብዬ ልምጣ!" ብላ ፍቃድ ጠይቃ፤ "ሂጂ እሺ!" ተብሎ ተመርቆላት (ተፈቅዶላት) ነው። ከዚህ ውጪ በረካ መጠጣት ወይም ማክተም ግዴታ ነው። ቢያንስ፣ ቢያንስ በረካ መቅመስ ግዴታ ነው። ምክንያቱም አይበጅም ይባላል። የምትሄድበት ነገር ሁሉ እንዲሳካ ወይም ሄይር እንዲሆን አክትመህ ሂድ! ያ ካልሆነ ደሞ በረካ ቀምሰህ ሂድ!" ነው እምትባለው በይህ በወሎ። ወደ ገበያም ሂድ፣ ወደ መንገድም ሂድ፣ ወደ ሥራም ሂድ፣ በጧት ሲወጣ ቡና ተጠጥቶና ተመራርቆ ነው። የማትጠጣ እንኳን ቢሆን "አፍልተሽ ከድመሽ ተመርቀሽ ነው መውጣት ያለብሽ! እንደው ዝም ብለሽ ነጠል፣ ነጠል እያልሽ አትውጪ!" ይባላል። እንዲህ ዝም ብለሽ ትወጫለሽ ጉዳይሽም ሳይሳካልሽ ትመለሻለሽ!" ምናምን ይባላል[278]።

ከላይ በጥቅሱ እንደተብራራው በወሎ ቡናው እራሱ እንደዚህ አይነት ሥርዓት አለው። በወሎ የቡና ከዳሚም ሆነ ታዳሚ ከቡናው ሥርዓት የሚነሳው "በረካ ሁኚ! በረካ ሁን!" ተብሎ ተመርቆ ነው። ምክንያቱም እድሚዋ ወይም እድሚው ዘለግ ያለ፣ ኋላ ቀሪ እንድትሆን ወይም እንዲሆን፣ በእድሜ ቶሎ ጠፊ እንዳትሆን ወይም እንዳይሆን በመመኘት ነው፤ "አክትም እንጂ!" እሚባለው። በወሎ የቡና ምረቃ ወቅት ከዳሚውና ታዳሚው ሁለት እጁን ዘርግቶ

---

[277] ሼህ ሐሰን አሊ መሐመድ፣ቃለ-መጠይቅ፣ሚያዚያ 18 ቀን 2006 ዓ.ም መርሳ- 01 ቀበሌ።

[278] ሼህ ዑመር እሸቱ፣ቃለ-መጠይቅ፣ሚያዚያ 20 ቀን 2007 ዓ.ም መርሳ- 02 ቀበሌ።

“አሜን! አሜን! አሜን!” ይላል። በመጨረሻም ከዳሚዋ የመራቂውን እጅ ስማ መራቂው በተራው “ቱቱቱ!” ብሎ ያሳርጋል።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የቡና አፈላል ሥርዓት በወሎ፤ የአፈላል ብሂሉ ያማረ፤ የተዋበና ሥርአቱ የተከበረ ነው። እንዲሁም የተለያዩ ፎክሎራዊ ክዋኔዎች የሚፈፀምበት የወሎዬዎች የጋራ እሴት ነው። ለምሳሌ የምረቃ ሂደቱ ብቻ እንኳን ብናይ ሁሉም መራቂ አይሆንም። ይህም ማለት ትልቅ እያለ ትንሽ አይመርቅም፣ አባት እያለ ልጅ አይመርቅም። የሃይማኖት አባት እያለ ተራ ሰው አይመርቅም። ለዚህ ደንብና ሥርዓት ሁሉ ጀማው ተገገር ነው።

በሌላ በኩል የምረቃውና የክዋኔው ፋይዳ ደግሞ ከወሎዬዎች ግላዊና ማኅበራዊ ኑሮ ጋር የተገኘ ነው። ከሥነ-ልቡናቸው ጋር የተሳሰረ ነው። የዚህ አይነቱ ትውፊት ደግሞ የክርስቲያ ኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው። የጋራ መገለጫ ልዩ ምልክት ነው። ይህ ልዩ ምልክት ደግሞ ከሌላው በተለዬ ለወሎና ለወሎዬዎች ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ያደረገ የጋራ ትውፊት ነው። ለዚህም ነው፤ ከወሎዬዎች ውጭ የሆኑ አካላት፤ “ወሎ ቶና በረካ እያለ ርስቱን ተቀማ!” በሚል የሥነ-ቃል ብሂል የሚገልጿቸው። ይህም ከወሎዬዎቹ የቡና ሥርዓት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው።

ለምሳሌ ከወሎ የቡና ትውፊት አንፃር ሌሎች አካላት ለወሎና ለወሎዬዎች ያላቸውን አመለካከት የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልፁት የግል ገጠመኞቻቸውን ማስረጃ በመጥቀስ ነው። ለአብነት በሪሁን ይመር ከዚሁ የወሎ የቡና ትውፊት ጋር በተያያዘ ያላቸውን ገጠመኝ የሚገልጹት “እኔ ወታደር ሳለሁ በነበርኩበት አካባቢ አንዲት ሴት ‹የት አገር ናችሁ?› ብላ ትጠይቀናለች። እኛም ወሎ ነን አልናት። ኸዚያ ጫት ሁሉ ገዝታ፣ ጎዝጉዛ፣ ቡና አፍልታ፣ አጫጭሳ ‹የወሎ ጀበና መጀን!› (አጽንዖት የኔ) ብላ፣ አክብራ “መርቂኝ!” አለችን። እና ወሎ ያው ባህሉ ስለሆነ በምርቃት ያምናል፤ በወዳጃና በዱዓ ያምናል፤ በቱፍታ ያምናል![279]።” በማለት ነው። በመሆኑም “አይዞህ አብሽር ብሎ ወሎ ከመረቀኝ፤ ክፉም አያገኘኝ በረካም አይርቀኝ!” እንዲሉ ወሎዬዎች፤ በእነሱ ብዙዎች ይመጀኑባቸዋል። ለዚህ ደግሞ እውነት አላቸው። ምክንያቱም የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት “ወሎ መጀን እሩቅ እንደሆነ አገስግሶ! ቅርብ እንደሆነ ለግሶ! የመከከውን የደከከውን ጀባ ብለንሃል! አደፊች እንጠባት!

---

[279] በሪሁን ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ።

ተቀደደች እንስፋት የማትባለውን ቀሚስ አለበስንህ!" ብለው መርቀው አፍታም ሳይቆይ ተግባራዊ የሚያደርጉ የወሎ ደጋጎች የሚገኙበት መሬት ወሎ በመሆኑ ነው[280]።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የቡና አፈላል ትውፊት በወሎ፤ መደበኛው ወይም ሰርካዊው የቡና አፈላል ሥርዓት ነው። ይህም ማለት ቤተሰብ ወይም ጎረቤታሞች ከሥራ ውለው ማታ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ወይም በእረፍት ቀናቸው ከአንዱ ቤት ቡና ተፈልቶ ጎረቤቶች የሚጠራሩበት ሂደት ነው። አልያም ከቅርብም ሆነ ከሩቅ እንግዳ መጥቶ እሱን ለማስተናገድ የሚፈላ የቡና ሥርዓት ማለት ነው። እንዲሁም በተለያዩ ክብረ-በዓላት፣ በሃዘንና በደስታ ወቅት የሚፈላ የቡና ሥርዓት ማለት ነው። ሥርዓቱም ከላይ እንደተጠቀሰው ወሎዬዎች የሚሰባሰቡበት፣ የሚመራረቁበት፣ ሃሳባቸውን የሚካፈሉበት፣ በጋራ ተመካክረው ችግራቸውን በጋራ የሚፈቱበት፣ አብረው የሚበሉበትና አብረው የሚጠጡበት፣ የሚዝናኑበትና የሚደሰቱበት...ወዘተ የጋራ እሴት ነው። በመሆኑም ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው ከሚኖሩባቸው በርካታ የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ ከላይ የተገለፀው የወሎዬዎች የቡና ሥርዓት ነው።

ሌላኛው የቡና ማፍላት ሥርዓት በወሎ፤ "ተርቲብ" የሚባለው የወሎዬዎች የቡና ማፍላት ትውፊት ነው። ከላይ በመደበኛው የቡና አፋላል ሥርዓት የተጠቀሱት ሂደቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የተርቲብ የቡና አፈላል ሥርዓት ግን በአንድ አካባቢ የሚኖሩ አባዎራዎች ወደ ሥራ ከተሰማሩ በኋላ፤ ሴቶቹ (ሚስቶቻቸው) ተሰባስበው የሚያፈሉት የቡና አፈላል ባህል ነው። ይህም ማለት በተራ ወይም በወረፋ ቡና ማፍላት ማለት ነው። ተርቲብ በቀን ከአንድ ወይም ከሁለት አልያም ከሦስት ሴቶች ቤት ሊፈላ ይችላል። ተርቲብ የሚወሰነው ሴቶቹ ባላቸው ጊዜና ፍላጎት መሰረት ነው። የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ተርቲብ በሌላ አባባል ወንፈል ማለት ነው[281]።

በዚህ የወሎዬዎች የተርቲብ ባህል ሁለት አከራካሪ ነጥቦች ይነሳሉ። አንደኛው ነጥብ የቡና ሥርዓቱ የሴቶቹን ጊዜ በከንቱ የሚያባክን "ጎጂ ባህል ነው!" የሚለው አስተሳሰብ ነው። በዚህ አስተሳሰብ መሰረት በተርቲብ የቡና አፈላል ባህል ሴቶቹ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በወሬና በሀሜት ነው፤ የሚል መከራከሪያ ነጥብ ይቀርባል። ለምሳሌ በተርቲብ ምክንያት የተሰባሰቡ ሴቶች የባሎቻቸውን የወሲብ ድክመትና ጥንካሬ ሳይቀር፤ የሌሎች ጎረቤቶቻቸውን ገመናና

---

280 አበጋር ማዱ በላይ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ-ገዶ።

281 አስካለ አበበ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 18 ቀን 2007 ዓ.ም ወልዲያ- 04 ቀበሌ።

ሌሎች አለቧልታዎችን ሲያነሱ-ሲጥሉ የሚውሉበት የቡና ሥርዓት ነው፤ የሚል መከራከሪያ ነጥብ ያቀርባሉ። በዚህ የተነሳም፤ "ቡና ጥሩ ነበር ለሱስ የሚበጅ፤ ቁርሱ የሰው ሥጋ መሆኑ ነው እንጂ" በማለት ለተርቲብ ስንኝ ቋጥረውለታል።

ሁለተኛው የመከራከሪያ ነጥብ ደግሞ የተርቲብን አሉታዊ ገጽታ የሚያነሱ ወገኖች የመኖራቸውን ያህል፤ አዎንታዊ ጎኑን የሚያነሱ አካላት መኖራቸው ነው። በዚህ መሰረት ተርቲብ በርካታ ማኅበራዊ ፋይዳዎች እንዳሉት ይነገራል። ለምሳሌ እነዚህ በተርቲብ ምክንያት በአንድ ላይ የሚሰባሰቡ ሴቶች ስለቤታቸው፣ ስለትዳራቸው፣ ስለልጆቻቸው፣ ስለአካባቢያቸው፤ ስለሚገጥሟቸው ችግሮቻቸውና መፍትሄዎቻቸው...ወዘተ በጋራ ይመክራሉ፤ በጋራ መፍትሄ ይፈልጋሉ። በዚህ ሂደት አንዱ ከሌላው እውቀት ይገበያል። ልምድ ይቀስማል። እንዲሁም ሴቶቹ ጉርብትናቸውን፣ አንድነታቸውን፣ የእርስ በርስ ትስስራቸውን፣ ፍቅርና ሰላማቸውን በተርቲብ ትውፊት አማካይነት ይበልጥ ያጎለብቱበታል።

ከዚህም ሌላ ተርቲብ የባልትና ሙያ የሚቀስሙበት፣ ሴቶች እርስ በርስ የሚረዳዱበት፣ የሚደጋገፉበት፣ የሚተሳሰቡበት፣ የሚተዛዘኑበት፣ የሚተባበሩበትና ክርስቲያን ሙስሊሙ ይበልጥ ቤተሰባዊ ትስስር የሚመሰርትበት የጋራ እሴት ነው። ከዚህ አንፃር የተርቲብን አዎንታዊ ገጽታ የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልፁት "አብሮ መብላቱ፣ አብሮ መጠጣቱ፣ እንደተጠቀቀ ሆኖ፤ ዱሮ ተርቲብ ልክ እንደ እቁብ ወይም ወንፈል ጥጥ ተዘጋጅቶ ይቀርብና ሴቶቹ ቡና እየጠጡ የአንድ-አንድ ጋቢ ጥጥ ይፈትሉ ነበር[282]።" በማለት ነው።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው በቡና ትውፊት ውስጥ የተገለፁት የእርስ በርስ ግንኙነቶች የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴቶች ናቸው። በሌላ አገላለጽ የቡና ሥርዓት በወሎ ከጉርብትና ጋር በእጅጉ የተሳሰረ በመሆኑ ትውፊቱ የሚከወነው ሙስሊሙና ክርስቲያኑ በአንድ ላይ ተቀላቅሎ ነው። በዚህ መሰረት የቡና ትውፊት በወሎ፤ ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው ከሚኖሩባቸው እሴቶች መካከል አንዱ ነው። ስለሆነም ትውፊቱ የክርስቲያኑና የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው። በዚህም የወሎዬዎች ማኅበራዊ ሥርዓት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ የሚለወጠው እየተለወጠ፤ የሚቀረው እየቀረ፤ የሚጨመረው እየተጨመረ፤ አሻራውን ሳይለቅ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ኖሯል። አሁንም አለ። ወደፊትም ሊቀጥል ይችላል። የወሎዬዎች የጋራ እሴት ደግሞ አይነቱ ብዙ ነው። መገለጫ ባህርይው

---

[282] ድርቤ ካሳው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ግንቦት 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 05 ቀበሌ።

በርካታ ነው። ከነዚህ የጋራ እሴቶች መካከል ሌላው የወሎዬዎች የጋራ እሴት የ"አርሂቡ!" ትውፊት ነው።

6.1.2.3፦ የአርሂቡ ትውፊት በወሎ

አርሂቡ በወሎ ከወሎዬዎች ለጋስነት ወይም እንግዳ ተቀባይነት ትውፊት ጋር በእጅጉ ይተሳሰራል። ወሎዬዎች እንግዳ በመቀበልና በማስተናገድ ወይም ያላቸውን ተካፍለው በመብላት ምን አይነት ዝንባሌ እንዳላቸው ሊገልጽ የሚችል ማስረጃ ካስፈለገ የ"አርሂቡ!" ትውፊታቸው ሊጠቀስ ይችላል። በዚህ መሰረት ወሎዬዎች "አርሂቡ!" ብለው ጋብዘው ያላቸውን ተካፍለው ከማንም ጋር አብረው ይበላሉ፤ አብረው ይጠጣሉ። ትውፊቱን የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልፁት እንደሚከተለው ነው።

> አርሂቡ! ማለት በወሎ አግሉ፣ ኑ ግቡ፣ ኑ ብሉ ጠጡ ማለት ነው። "አርሂብ እንጂ!" ከተባለ ኑ እኛን ምሰሉ እንጂ፣ ኑ ግቡ እንጂ!፣ አግሉ እንጂ ማለት ነው። ባህሉ ማንንም ሊሆን ይችላል። "ጎራ በላ!" ይላል በዘመነኛው አደል? እንደዚያው "አርሂብ!" ይልሃል ወሎ፤ "ና ግባ! ና አግል! ና ብላ! ና ጠጣ!" ማለቱ ነው። እየበላህም ቢሆን እንኳን "አርሂብ እንጂ!" ይልሃል። "ምነው? እንብላ እንጂ!" ማለቱ ነው። እንደአውዱ ነው። አሁን እየበላን ከሆነ ያለነው፤ "አርሂብ እንጂ!" ልልህ እችላለሁ። እንብላ እንጂ ማለቴ ነው። አሁን በዚህ አንድ ሰው እያለፈ ከሆነ ደሞ "አርሂብ እንጂ!" እኛን ምሰል እንጂ! አግል እንጂ! ማለት ነው። እኛ እያደረግነው ያለነውን ነገር እንዲያደርግ ወደ ቤት እንዲገባ መጋበዝ ነው[283]።

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው በአርሂቡ ትውፊት አማካይነት አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት የወሎዬዎች ልዩ መገለጫ የጋራ እሴት መሆኑ ነው። አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት ከወሎዬዎች ሥጋና ደም ጋር የተዋሃደ የማኅበራዊ መስተጋብር መገለጫ መሆኑን የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት "ምንም ባይኖረኝም እንኳን እኔም አሁን ብቅ ብትል ወደ ቤቴ ‹አርሂቡ!› ነው እምልህ። አብሮኝ ያደገ ስለሆነ[284]።" በማለት ነው። ይህ ማለት ግን "እንዳያማ ጥራው፣ እንዳይበላ ግፋው!" እንዲሉ ወሎዬዎች፤ አርሂቡ ከአንገት በላይ ሳይሆን፤ ከልብ ነው። ከአንጀት ነው። ይህንንም የአካባቢው ነዋሪዎች "አርሂቡ ማለት እንግዲህ ቅረቡ፣ ኑልን፣ ናልኝ ማለት ነው። "አርሂቡ!" ቡና ጠጡ ይባላል። ያው አሁን አንተ በዚህ ስታልፍ ቤቴ ይኸ ከሆነ አርሂቡ! ኧረ ግባ! ጎራ ብለህ፣ አረፍ ብለህ ሂድ፣ ቡና ጠጥተህ ሂድ ማለት ነው[285]።" ሲሉ ይገልፁታል። በዚህ የአርሂቡ ትውፊት መሰረት ምንም እንኳን "እግረ-

---

283 ሞላልኝ ወርቁ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- መሐል መቻሬ።

284 አሰፋ አበጋዝ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ።

285 እንድሪስ አህመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 28 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 03 ቀበሌ።

ለምለምና እግረ-ደረቅ" የሚባል ፊሊጥ ቢኖርም፤ በአብዛኛው እንግዳ በወሎ የበረከት ምንጭ ወይም የመልካም ነገር ሰበብ ተደርጎ ይቆጠራል። በዚህም ክርስቲያኑ ሙስሊሙን "አርሂቡ እነ ሼህ! አርሂብ እንጂ ሼሃችን!" ብሎ በደስታና በፍቅር ያስተናግዳል። በተመሳሳይ ሙስሊሙ ክርስቲያኑን "አርሂቡ መምሩ!" ከቤቱ ይጋብዛል። በዚህ መሰረት አንዱ ከሌላው ቤት ገብቶ በልቶ ጠጥቶ መርቆ ይወጣል።

ለምሳሌ በወሎ በቁሱ ቤት አካባቢ ቃልቻ ወይም ሼህ የሚያልፍ ከሆነ ቁሱ ሼሁን ወይም ቃልቻውን "አርሂቡ ሼሃችን" ብሎ ከቤት ገብተው ቡና ጠጥተው፣ ተጨዋውተው እንዲሄዱ ሊጋብዟቸው ይችላሉ። ሼሁ ቢያንገራግሩ እንኳን "ኧረ! በአዛኝቱ፣ ኧረ! በእመቤቴ፣ ኧረ! በሞቴ! አፈር ስሆን!" የሚሉትን ሌሎች ትውፊቶችን ጨምሮ ከቤት ጎራ ብለው እንዲሄዱ ሊጋብዟቸው ይቸላሉ። በዚህ ጊዜ ሼሁ "መርሃባ!" ብለው ከቁሱ ቤት ገብተው ቡና ጠጥተው፣ ተጨዋውተው፣ በመጨረሻም መርቀው ይሄዳሉ።

በተመሳሳይ ቁሱ በሼሁ ቤት አካባቢ የሚያልፉ ከሆነ ሼሁ ቁሱን "መምሩ አርሂብ እንጂ!" በማለት ቡና አስፈልተው ከሥጋ ውጪ ቤት ያፈራውን ሊጋብዟቸው ይችላሉ። በዚህ መሰረት የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት "አርሂብ" ተብሎ "መርሃባ!" ከተባለ መግባት ነው፤ መብላት ነው፤ መጠጣት ነው። ማንም ይሁን ማን፤ የማንም ቤት ይሁን የማን፣ የሚፈለገው አርሂብ ብቻ ነው። ስለዚህ አርሂቡ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው[286]።

አርሂቡ በወሎ በቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን አጋጣሚው በተገኘበት ቦታ ሁሉ ነው። ለምሳሌ የማሽላ ውቂያ በሚከናወንበት አካባቢ የሚያልፍ መንገደኛ ቢኖር "አርሂብ!" ይባላል። "መርሃባ!" ብሎ ጎራ ይላል። ከዚያም በአግማሱ አማካይነት ለውቂያ ከተዘጋጀው ጭብጦ ይሰጠዋል፤ ይበላል። ከጠላው ይቀዳለታል፤ ይጠጣል። አውድማው ግን የክርቲያን ወይም የሙስሊም ሊሆን ይችላል። ተጋባዡም ክርስቲያን ወይም ሙስሊም ሊሆን ይችላል። አስተናጋጁም ተስተና ጋጁም "የክርስቲያን ነው፤ የሙስሊም ነው፤" የሚለውን ጉዳይ ፊዕሞ አያስቡም፤ አያስታ ውሱም። አውድማው የሙስሊምም ይሁን የክርስቲያን ተጋባዡ በልቶ፣ ጠጥቶ "ምርቱ በሰላም ይግባ! እናንተንም በሰላም ያግባችሁ! ምርቱ ይበርክት!" ብሎ መርቆ ይሄዳል። አስተናጋጁም ክርስቲያንም ይሁን ሙሰሊም ምርቃቱን "አሜን!" ብሎ ይቀበላል[287]።

---

[286] አድኖ ተካየ፣ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 12 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 02 ቀበሌ።

[287] አሰፋ አበጋዝ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ።

በዚህ ትውፊት መሰረት ምርቱ ረድዔት ያለው፤ የጤና፣ የሰላምና የደስታ ቀለብ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። በወሎ አርሂቡ ተብሎ መግደርደር የለም" "አርሂቡ!" ሲባል ወይ "መርሃባ!" ነው፤ ወይ "አትራቡ!" ነው። ባንፃሩ አንድ እንግዳ "አርሂቡ!" ተብሎ ገብቶ በልቶ፤ ጠጥቶ በቃኝ ቢል እንኳን በወሎዬዎች ባህል፣ ወግና ልማድ መሰረት "በሞቴ! አፈር ስሆን፣ በእከሌ ሞት፣ አንድ ያጣላል!...ወዘተ" እየተባለ በተጨማሪ የጉርሻ ትውፊት ይስተናገዳል።

ይህም እሚደረገው ከዚህ በላይ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ለክርስቲያኑም፣ ለሙስሊሙም ነው። የእንግድነት መስፈርቱ በወሎ ክርስቲያን ወይም ሙስሊም መሆኑ ሳይሆን፤ እንግዳ መሆኑ ብቻ ነው። በዚህም "ከፍትፍቱ ፊቱ!" እንደሚባለው ወሎዬዎች እንግዶቻቸውን የሚያስተናግዱት ፊታቸውን ቋጥረውና ግንባራቸውን ከስክሰው ሳይሆን፣ ማንንም በሚስብ ውስጣዊ ፈገግታና ልባዊ ፍቅር ተሞልተው ነው። በዚህም ጎዝጉዘውና አንጥፈው እንግዶቻቸውን ያበላሉ፣ ያጠጣሉ። የእግር ውሃ አቅርበው የእንግዳ እግር ያጥባሉ፤ ያሳጥባሉ። በምግብ፣ በመጠጥ፣ በመልካም ፈገግታና ጨዋታ እንግዳ ያስተናግዳሉ። አልጋ አንጥፈው ያስተኛሉ።

ባጠቃላይ ወሎዬዎች ክርስቲያን ሙስሊም ሳይሉ በአርሂቡ ትውፊታቸው አማካይነት ያላቸውን ተካፍለው ይበላሉ፤ ወይም ተካፍለው መብላት ይወዳሉ። በዚህም በሃይማኖት ሳይለያዩ በአንድ ቤት ውስጥ ወይም በጉርብትና በፍቅርና በሰላም በአንድነት ይኖራሉ። ስለዚህ የአርሂቡ ትውፊት ከላይ እንደተገለፀው ክርስቲያኑንም ሆነ ሙስሊሙን፤ "ኑ እኛን ምሰሉ! ኑልን! ናልኝ! ብላልኝ! ጠጣልኝ! ከድካምህ አረፍ በልልኝ !... ወዘተ" ማለት በመሆኑ፤ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ በአርሂቡ ትውፊት ይገለፃል።

6.1.2.4፦ ግጭትና የግጭት አፈታት ሥርዓት በወሎ

ወሎዬዎች በመከባበር፣ በመተሳሰብና በመተዛዘን፣ በመረዳዳትና በመደጋገፍ፣ አንተ-ትበስ አንቺ-ትብሽ በመባባል፣ በመቻቻል፣ በሰላምና በፍቅር አብረው እንደሚኖሩ ሁሉ፤ ከእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነታቸው ጋር በተያያዘ በተለያዩ ምክንያቶች ይጋጫሉ። በዚህም መሰረት ባልና ሚስትን ጨምሮ፣ ቤተሰብ ከቤተሰብ፣ ግለሰብ ከግለሰብ፣ ጎረቤት ከጎረቤት እና ግለሰብ ከጎረቤቱ ጋር ሊጋጭ ይችላል። ከዚህም አልፎ ሰው ከራሱ፣ ሰው ከፈጣሪውና ሰው ከወሎ አድባርና ዛር ጋርም በተለያዩ ምክንያቶች ይጋጫል፤ ይቀያየማል።

የግጭቱ መጠንና ደረጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ሰው በርስቱ ወይም በእርሻ ድንበሩ፣ ሰው በሃብቱና በንብረቱ፣ ሰው በግንዘቡ፣ ሰው በሚስቱ፣ ሰው በልጆቹ፣ በከብቶቹ፣ በዶሮዎቹ፣...ወዘተ ከግለሰብ

ወይም ከጎረቤቶቹ ጋር ሊጋጭ ይችላል። እንዲሁም ኑሮውና የተለያዩ አጋጣሚዎች ለግጭት ሰበብ ይሆናሉ። በነዚህ ሰበቦች ምክንያት በወሎ፤ ቂም ወይም ጎሚ አለያም ቁርሾ ሥረ-መሰረት ያላቸው ከግጭት ጋር የተያያዙ ባህላዊ አስተሳሰቦች ናቸው።

በነዚህ አስተሳሰቦች ምክንያት በወሎ የሰው ነፍስ ይጠፋል። በዚህ ሰበብ የሚወዱትን የወሎ ቀዬ ለቆ የመሰደድ እጣ ፈንታ ይገጥማል። ገዳዩ ቢሰደድም እንኳን በወሎዬዎች ባህል መሰረት እስከ ሰባት ትውልድ ዘር ቆጥሮ ደም መመለስ ያባት ነው። ባህል፣ ወግና ልማድ ነው። ይህም በወሎ "ጥቁር ደም" በመባል ይታወቃል[288]። ጥቁር ደም ታስቦበትና ታቅዶ የሚፈፀም የግድያ ተግባር ነው[289]።

በቀሉን በጥቁር ደም ትውፊት መመለስ ያልቻለ ወሎዬ ደግሞ "ኧረ-ልጅ ማሰሪያው፣ ኧረ-ልጅ ገመዱ፤ ጎጆማ ምን ይላል ጥለውት ቢሄዱ!" የሚለውን የቁጭት መግለጫ ስንኝ በእርሻ ቦታው፣ በየመጠጥና በየሠርግ ቤቱ እያንጎራጎረ ቁጭቱን በልቡ ውስጥ ቋጥሮ ይኖራል። አንዳንድ ጊዜም እድለኛ ሆኖ ወንድ ልጅ ከወለደ ለልጁ፤ "ደምመላሽ!" የሚል መጠሪያ ስም አውጥቶ በቀሉን ልጁ እንዲመልስለት ለልጁ አደራ ይሰጣል። ተስፋም ያደርጋል። ወይም "ጠላቴ ጧት ሙቶ እኔ ልሙት ማታ፤ ዓለም አይደለሞይ የአንድ ቀን ደስታ!" የሚሉትን ስንኞች እያንጎራጎረ ተስፋውን ወይም ምኞቱን እየገለፀ፣ ከንፈሩን በጠላቱ ላይ እየነከሰ እድሜውን ይገፋል።

ምንም እንኳን ወሎዬዎች በእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነታቸው ምክንያት የተለያዩ መጠንና ደረጃ ያላቸው ግጭቶችን የሚያስተናግዱ ቢሆኑም፤ ማኅበራዊ ኑሯቸው ሳይናጋ በሰላምና በፍቅር በጋራ የሚኖሩበት፣ ለማኅበራዊ ኑሯቸው ደንብና ሥርዓት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ተገዥ የማይሆን አካል ሲያጋጥም አጥፊውን የሚገስጹበት፣ የሚቀጡበት ከዚህም ሲያልፍ ከማኅበራዊ ሥርዓቱ ውጭ የሚያደርጉበትና የተበደለን የሚክሱበት፣ ከበደሉ እንዲያገግም የሚያደርጉበትና ሞራሉን የሚገነቡበት ትውፊት አላቸው። ወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብራቸው ሳይዛባ ደንብና ስርዓቱን፣ ባህል፣ወግና ልማዱን ጠብቆ እንዲጓዝ የሚያደርጉባቸው የተለያዩ እሴቶች አሏቸው። ከነዚህም እሴቶች መካከል አንዱ የግጭት አፈታት ወይም የሽምግልና ሥርዓታቸው ነው።

---

[288] በወሎ "ቀይ ደም" የሚባል ትውፊትም አለ። በትውፊት መሰረት "ቀይ ደም" ማለት ከጥቁር ደም በተቃራኒ በድንገት፣ ወይም ሳይታሰብ በሆነ አጋጣሚ ወይም ሆነ ተብሎ ሳይታቀድ የተፈጸመ ግድያ ማለት ነው።

[289] ተበጀ መኮንን፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 26 ቀን 2006 ዓ.ም. ሐብሩ- አባሬ።

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ይሄ ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች ሦስት አይነት የግጭት አፈታት ዘዴዎች ወይም የሽምግልና ሥርዓቶች አሉ፡፡ እነዚህም የአበጋር የሽምግልና ሥርዓት አንደኛው የግጭት መፍቻ ዘዴ ሲሆን፤ ሁለተኛው የግጭት መፍቻ ዘዴ ደግሞ የዘወልድ የሽምግልና ሥርዓት ነው፡፡ በአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች ወይም በመደበኛው የሽምግልና ትውፊት አማካይነት የሚከናወነው የሽምግልና ዘዴ በሦስተኛ ደረጃ ይጠቀሳል፡፡ የአበጋር የሽምግልና ሥርዓት ተግባራዊ የሚደረገው በአብዛኛው በሐብሩና በጉባላፍቶ ወረዳዎች ውስጥ ነው፡፡ ባንፃሩ የዘወልድ የሽምግልና ሥርዓት በራያና ቆቦ ወረዳ ውስጥ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በአካባቢ ሽማግሌዎች ወይም በመደበኛው የሽምግልና ሥርዓት የሚከናወነው የግጭት አፈታት ዘዴ ደግሞ በሁሉም አካባቢዎች ተግባራዊ የሚደረግ ትውፊት ነው[290]፡፡

የአበጋር የሽምግልና ሥርዓት በወሎ ከእስልምና ሃይማኖት ጋር ይገናኛል፡፡ ከዘር ሐረግ ጋርም ይተሳሰራል፡፡ በአበጋር የሽምግልና ሥርዓት ወቅት በርካታ ፎክሎራዊ ሁነቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ እንዲሁም በውስጡ የተለያዩ ቁሳዊና መንፈሳዊ የሆኑ ጉዳዮች ይካተቱበታል፡፡ የእነዚህ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ማኅበራዊና ባህላዊ ፋይዳ ደግሞ ከወሎዬዎች ሥነ-ልቡና ጋር ይተሳሰራሉ[291]፡፡

ባንፃሩ የዘወልድ የሽምግልና ሥርዓት ከሃይማኖትም ሆነ ከዘር ሐረግ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ የዘወልድ የሽምግልና ሥርዓት በአካባቢው ነዋሪዎች አማካይነት ተመርጠው በሚሰየሙ የሀገር ሽማግሌዎች የሚዋቀር የወሎዬዎች የግጭት መፍቻ ትውፊት ነው፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት የነዚህ የሀገር ሽማግሌዎች መምረጫ መስፈርት በዋናነት በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው፤ ተደማጭነትና ተናግረው የሚያሳምኑ፤ በሥነ-ምግባራቸው የተመሰገኑ፣ በእድሜያቸው፣ በሃብታቸው...ወዘተ አንቱታን ያተረፉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሆነው መገኘታቸው ነው፡፡ ወይም አንድ የሀገር ሽማግሌ ማሟላት የሚገባውን መስፈርት ማሟላታቸው ብቻ ነው፡፡ እነዚህ አካላት በዚህ መስፈርት ከተመረጡ በኋላ ዘወልድ የሚለው ስያሜ ይሰጣቸዋል[292]፡፡

---

290 ዓሊ መሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 4 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ -አንጦ- 04 ቀበሌ፡፡

291 አሰፋ አበጋዝ ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ፡፡

292 አበራ አምባየ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 19 ቀን 2007 ዓ.ም. ቆቦ -02 ቀበሌ፡፡

ዘወልድ ማለት በአካባቢው ነዋሪዎች መረጃ መሰረት የባህላዊ ግጭት አፈታት ሥርዓትን መነሻ አድርጎ የመጣ የአንድ ግለሰብ መጠሪያ ስም ነው፡፡ የሰያሜው ዋና ዓላማም የዚህ ግለሰብ መልካም ሥራ ከመሬት በላይ እንዲቀር፣ ስሙ እንዲታወስና እንዲዘከር ለማድረግ ነው፡፡ የሚከተለውን ጥቅስ ለአብነት እንመልከት

> ዱሮ፣ ዱሮ ዘወልድ እሚባል አንድ መልካም ሰሪ ሰው ነበረ፡፡ ዘወልድ ከላስታ እስከ ዞብል ያለውን ማኅበረሰብ ግጭት በመፍታትና በማስታረቅ ሰላም ያወርድ ነበረ፡፡ ይኸ መልካም ሰሪ ሽማግሌ ማኅበረሰቡ በሰላም ውሎ እንዲገባ፤ ተስማምቶ እንዲኖር፤ ጉልበተኛው ደካማውን እንዳያጠቃው፣ በአንፃሩ እንዲረዳዳ፣ እንዲተባበር፣ እንዲከባበር፣ እንዲተዛዘን፣ እንዲዋደድና እንዲፋቀር የማድረግ ሥራ ይሰራ ነበረ፡፡ ዘወልድ ለማንም የማያዳላ፣ ከማንም ሰው ጥቅም የማይፈልግ፣ የነፍሱን ብቻ ስራ የሚሰራ ትልቅ ሰው ነበረ፡፡ ያ ሰው እንግዲህ ሲኖር፣ ሲኖር፣ ሲኖር፣ ሲሰራ፣ ሲሰራ፣ ሲሰራ ማለፍ አይቀርምና አለፈ፡፡ ካለፈ በኋላ እሱ ሲያገለግልበት የነበረውን ሂደት ተከትሎ አሁን ዘወልድ በሚል ስያሜ ሽማግሌዎች እየተመረጡ ህዝቡን ያገለግላሉ፡፡ ይህም ማለት የሱን መልካም ሥራ መነሻ በማድረግ አባቶች እየተደራጁ ወይም በህዝብ እየተመረጡ ግጭት እየፈቱ ይገኛሉ፡፡ የዘወልድ አባቶች የሁለቱም ሃይማኖቶች እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ እዚህ ራያና ቆቦ የሚገኙት የኛ ዘወልዶች ሙስሊሞችም ክርስቲያኖችም ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ባህሉ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው፡፡ ሙስሊሞቹም ይዳኙበታል፡፡ ክርስቲያኖቹም ይዳኙበታል[293]፡፡

የዘወልድም ሆነ የአበጋር ወይም መደበኛው የሽምግልና ትውፊት በወሎ፤ ወሎዬዎች እርቅ የሚፈጥሩባቸው፣ ሰላም የሚያወርዱባቸው፣ ወንጀል የሚከላከሉባቸው፣ አንድነታቸውን የሚያፀኑባቸው የጋራ እሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህ የጋራ እሴቶች ግጭት የሚያስወግዱበት ሥልትና የሚከወኑበት አውድ ቢለያይም፤ ለማኅበረሰቡ የሚያስገኙት ፋይዳ ግን ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም ሁለቱም የሽምግልና ትውፊቶች በወሎዬዎች ዘንድ ተዓማኒና ተቀባይነት ያላቸው እሴቶ በመሆናቸው ሰላም ከማስፈን አንፃር አስተማማኝ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ናቸው፡፡

ለምሳሌ በዘወልድም ሆነ በአበጋር ወይም በመደበኛው የሽምግልና ሥርዓት የተወሰኑ ውሳኔዎችን ወሎዬዎች ፈጽመው አይቃወሙም፡፡ ይግባኝም አይጠይቁም፡፡ የተሰጠውን ውሳኔ ከልባቸው አምነው ይቀበላሉ፡፡ እርቁንም “ይቅር ለፈጣሪ!” በማለት ከልባቸው አምነው ከተጣሉት ሰው ጋራ ይታረቃሉ፡፡ ይህንንም የአካባቢው ነዋሪዎች የሚያነፃፅሩት ዘመናዊ ከሚባለው የፍርድ ቤት ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጋር ነው፡፡ የሚከተለውን ጥቅስ ለአብነት እንመልከት፡፡

> አንድ ጉዳይ በፍርድ ቤት ቢያልቅ ያነን ውሳኔ ይግባኝ ብሎ ሊያሸረው፣ ወይም ሊያስመልሰው ይችላል፡፡ እንዲሁም ከደም ጋር የተያያዘን ጉዳይ ፍርድ ቤት ቢፈታው

---

293 ደሳለ ፈንታው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 26 ቀን 2006 ዓ.ም. ራያና ቆቦ- አራዶም፡፡

> በእስር ነው፤ ሊሆን እሚችለው፡፡ ግን ፍርደኛው ፍርዱን ጨርሶ ከእስር ሲወጣ፤ የዚያን ጊዜ በቀሉ ማገርሸቱ አይቀርም፡፡ ከእስር ቤት ከመውጣቱ በፊትም ቢሆን በዚያ ሰው ቤተሰቦች ላይ የሚች ቤተሰቦች በቀል ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡ የደም መመለሱ ባህል እስካለ ድረስ፡፡ ነገር ግን በዘወልድም ሆነ በአበጋር ወይም በመደበኛው የሽምግልና ሥርዓት እርቅ ከተፈፀመ ተፈፀመ ነው፤ አበቃ! ምክንያቱም የእርቅ ሂደቱ ከማኅበረሰቡ ሥነ-ልቡና ጋር የተያያዘ ባህላዊና ሃይማኖታዊ የሆነ እሴት ስላለው ነው፡፡ ማኅበረሰቡም ይሁንኝ ብሎ የተቀበለው ስለሆነ ይፈራል፡፡ አንድ ነገር ባደርግስ! እነዚህን ትልልቅ ሰዎች እንደዚህ አድርጌ ጥሼ በቀል ብፈፅም ብሎ ይፈራል፡፡ ከጊዜ አንፃርም በፍርድ ቤት ስንት አመት የሚከራከርበትንና የሚመላለስበትን ጉዳይ እነሱ ቀን ይዘው በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ይሰጡታል፡፡ በፍርድ ቤት የማይደርቀውን ደምም ቢሆን እነሱ እንዲደርቅ ያደርጉታል፡፡ ከዚህም ሌላ የእርስ በርስ መካካድ ሲኖር፣ ምስክር ስለሌለ ፍርድ ቤት ብትሄድ መፍትሄ ላታገኝ ትችላለህ፡፡ ነገር ግን እነሱ ጋ ሲደርስ ያምናል፡፡ እንደሽምግልናቸው እውነቱን እንዲያወጣ ያደርጉታል፡፡ በዚህም የተሰረቀና የተዘረፈ ወይም ሆን ተብሎ የተደበቀና የተሰወረ ንብረት ካለ በእነሱ አማካይነት ለባለቤቱ ይመለሳል[294]፡፡

በዚህ ጥቅስ መሰረት የዘወልድም ሆነ የአበጋር ወይም የመደበኛው የሽምግልና ሥርዓት የወሎዬዎች የጋራ እሴት ነው፡፡ ወይም የየጁ ሃዳ ነው፡፡ ይህም ማለት ጀማው የተስማማበት ትውፊት ነው፡፡ አለያም ክርስቲያን መስሊመ የተስማማበት የወሎዬዎች ሰላም የሚረጋገጥ ጥበት፣ አንድነታቸው የሚፀናበት፣ የጋራ እሴት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የወሎዬወች የግጭት አፈታት ትውፊት የሃይማኖት መቻቻል እሴት ተምሳሌት ነው፡፡ ለምሳሌ በአበጋር የሽምግልና ሥርዓት መሰረት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ከቁሱ ቤት የአበጋሩ "ቆቲና መስብሃ" ሊገባ ይችላል፡፡ ስለሆነም ቁሱ በየጁ ሃዳ መግባትና መስማማት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከዚህም ሌላ ከቤተ ክርስቲያን ስርዓተ-አምልኮ በኋላ ወይም ከክርስቲያኑ የሰንበቴ መጠጫ ቦታ ከአበጋሩ የተላከ መጥሪያ ሊነበብ ይችላል፡፡ የአበጋሩ መልዕክትም ሳይውል ሳያድር በክርስቲያኑ በኩል ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን "እምበዳዴ" ሊያስከትል ይችላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት መነጠልን ያስከትላል፡፡ በዚህም ተርቲብ ይቋረጣል፡፡ ሰላምታ ይቆማል፡፡ መረዳዳትና መደጋገፍ ይቀራል፡፡ ሌላው ቢቀር እሳት መጫጫር እንኳን ህልም ይሆናል፡፡

ባጠቃላይ በወሎዬዎች የእምበዳዴ ትውፊት መሰረት ከብቶችና ልጆችን ጨምሮ፤ መላው የቤተሰብ አባላት ከሚወዳቸው ዘመዶቹና ጎረቤቶቹ ተነጥሎ ባይተዋር ይሆናል፡፡ ከወሎ አድባር ሳይቀር ይቆራረጣል፡፡ ይህ እንዳይሆን ግን የወሎ ሰው ለወሎዬዎች የአኗኗር ሥርዓት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ይገዛል፡፡ ለጊዜው ከማኅበሩ ቢያፈነግጥ እንኳን በመጨረሻ "በሬየን ለጥብስ፣ ቤቴን ለማገዶ!" ብሎ ጀማውን ይቅርታ ጠይቆ ከወሎዬዎች ጋር ይቀላቀላል፡፡ የዚህ

---

[294] ያሲን ፍሬው ፤ቃለ-መጠይቅ ፤ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም ሐብሩ-03 ቀበሌ፡፡

አይነቱ ባህል፣ ወግና ልማድ በበኩሉ በወሎዬዎች መካከል የሃይማኖት ልዩነት ሳይፈጥር፤ አንዱ የሌላውን የሃይማኖት ልዩነት አክብሮ፤ ከዚያም አልፎ የእኔነት ስሜት ፈጥሮ በመከባበር፤ በመረዳዳት፤ በመደጋገፍ፤ በመተዛዘን፤ በመተሳሰብ፤ በሰላምና በፍቅር ሃዲዱን ጠብቆ ይዟቸው ይጓዛል። ለምሳሌ በአካባቢው "የሼህ ሊጋ" ባህላዊ የግጭት አፈታት አባት የሆኑት ሼህ መሐመድ ሲራጅ ይህንን እውነታ የሚያረጋግጡት በሚከተለው ሁኔታ ነው።

> እኛ በበኩላችን የሃይማኖት ልዩነት አናደርግም። ከቄሶቹም ቤት እየገባን እናስታርቃለን። ለምሳሌ ባለፈው የቄስ ልጅ ተገሎ እዚያ ሂደን አስታርቀናል። ስለዚህ እከሌ ክርስቲያን ነው፤ አከሌ ደሞ እስላም ነው አንልም" እንዲውም ይሽን አይነት ልዩነት ጨርሶ አናስታውሰውም። ከክርስቲያኑም አገር ስንሄድ በልተን እስከምናበቃ ድረስ ቁመው ነው፤ እሚያስተናግዱን። እነሱ ችግር ሲያገኛቸው እኛ እየሄድን እናስታርቃቸዋለን። እኛ ሂደን በምንሰፍርበት ጊዜ የአካባቢው ደብር ወይም ቅሬ ክርስቲያኑ ካለንበት ቦታ ድረስ መጥቶ ቦታችንን ይደላድላል፤ ይጋርዳል። ስለዚህ እኛ እምናገለግለው እስላሙንም ክርስቲያኑንም በጋራ ነው።[295]

ባጠቃላይ በዚህ ንዑስ ርዕስ እንደተብራራው ሰላምና ፍቅር የወሎዬዎች መገለጫ እንደሆነ ሁሉ፤ በመካከላቸው ግጭትም ይፈጠራል። ይህም በየትም ቦታ በሚኖር ማኅበረሰብ የእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነት ውስጥ ሊፈጠር የሚችል የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህርይ ነው። መሰረታዊው ቁም ነገር ግን ለሚከሰቱት ግጭቶች መፍትሄ ማበጀትና የማኅበረሰቡን ሰላምና ፍቅር ወደ ቦታው መመለሱ ላይ ነው።

በዚህ መሰረት ከላይ ተብራርቶ እንደቀረበው ወሎዬዎች ሰላምና ፍቅርን እንደታደሉ ሁሉ፤ ግጭቶቻቸውን የሚፈቱባቸው፣ ፍቅርና ሰላማቸውን የሚያረጋግጡባቸው ብልሃቶችም አሏቸው። ብልሃቶቹ የሙስሊሞቹም የክርስቲያኖቹም የጋራ እሴቶች ናቸው። በዚህ መሰረት ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው በሰላምና በፍቅር እንዲኖሩ ካስቻሏቸው የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ የግጭት አፈታት ሥልትና ሥርአታቸው ነው።

ይህ ሥርዓታቸው ደግሞ ከጉርብትና ብሂላቸው፣ ከእለት ተእለት የእርስ በርስ ግንኙነታቸውና ከማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብራቸው ጋር የእትብት ያህል ዝምድና ያለው ትውፊት ነው። በተለይ የመደበኛው የሽምግልና ትውፊት "ሰማይ ተቀደደ ቢለው ሽማግሌ ይሰፋዋል!" አለ እንዲሉ፤ የባልና ሚስት ግጭት በጎረቤት ሽማግሌዎች አማካይነት ይፈታል።የግለሰብና የግለሰብ ግጭት፣ የጎረቤትና የጎረቤት ግጭት...ወዘተ በሀገር ሽማግሌዎች መፍትሄ ያገኛል። በዚህ ሂደት ክርስቲያኑ በሙስሊሙ ሽማግሌዎች ይሸመገላል። በተመሳሳይ ሙስሊሙ

---

[295] ሼህ መሐመድ ሲራጅ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ሐራ።

በክርስቲያኖቹ ሽማግሌዎች ይሸመገላል። በዚህም ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጋር ተከባብሮ በሰላምና በፍቅር ይኖራል።

6.1.3፡- ጉርብትና በሥራ

የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ከሚገለጽባቸው ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶች መካከል አንዱ የወሎዬዎች የሥራ ባህል ነው። ወሎዬዎች በጉርብትና ተሳስረው በጋራ እንደሚኖሩ ሁሉ፤ በጋራ ይሰራሉ። ወሎዬዎች አብረው እንደሚበሉና አብረው እንደሚጠጡ ሁሉ፤ አብረው ይሰራሉ። በመሆኑም ወሎዬዎች በሥራ ባህላቸውም እርስ በርስ ይረዳዳሉ፤ ይደጋገፋሉ። ወሎዬዎች በሥራ እርስ በርስ ይገናኛሉ፣ ይተሳሰባሉ፣ ይተዛዘናሉ። ወሎዬዎች ባላቸው የሥራ ትውፊት አማካይነት እርስ በርስ ይከባበራሉ፣ ይዋደዳሉ፣ ይፋቀራሉ። በዚህም በሰላምና በደስታ አብረው ይኖራሉ።

የወሎዬዎች የስራ ባህል "ወንፈል እና ጂጊ/ደቦ" ተብለው በሚጠሩ የሥራ ትውፊቶች ይገለፃል።[296] በነዚህ ትውፊቶች አማካይነት ወሎዬዎች በጋራ የግብርና ሥራ ያከናውናሉ። በዚህም በጋራ ያርሳሉ፤ ያርማሉ፣ ይኮተኩታሉ። በጋራ ያጭዳሉ፣ ይቆርጣሉ፣ በጋራ ይወቃሉ፣ በጋራ ምርቱን ወደ ቤት ያስገባሉ። በጋራ ቤት ይሰራሉ፤ በጋራ የቤት መስሪያ የሚሆን ቁሳቁስ ያቀርባሉ። በጋራ አጥር ያጥራሉ። ሴቶች በጋራ ተሰባስበው ጥጥ ይፈትላሉ። የሠርግ፣ የማኅበር፣ የሠደቃ...ወዘተ የሚሆን ዝግጅት ያዘጋጃሉ። ወጣቶች በእድሜ ተደራጅተው ከእነሱ የሚጠበቅ ሥራ ያከናውናሉ። ለምሳሌ የማገዶ እንጨት ይሰበስባሉ። ከብት ይጠብቃሉ፣ ከማሳ ወደ ቤት ጭድና አገዳ ያመጣሉ።። አዛውንቶች ደግሞ በሥራ ቦታ ላይ ተገኝተው ያበረታታሉ፤ ያዝናናሉ፤ ልምዳቸውን በማካፈል ምክር ይለግሳሉ፣ ይመርቃሉ። ሥራውን፣ ምግብና መጠጡንም ይባርካሉ።

6.1.3.1፡- ወንፈል/ ጂጊ[297] በወሎ

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ወንፈል ማለት ሁለትና ከሁለት በላይ በአብዛኛው የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች የሆኑ ሰዎች ተራ ገብተው የተለያዩ ሥራዎችን የሚያከናውኑበት የወሎዬዎች የሥራ ባህል ነው። ይህም ማለት ዛሬ ያንዱን፣ ነገ የሌላውን፣ ተነገ ወዲያ ደግሞ የዚያኛ ውን...ወዘተ ሥራ ማከናወን ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ የሥራ ብድር ማለት ነው። ትውፊቱ

---

[296] ውዳድስ ምህረቱ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም. ሐብሩ- ስሪንቃ።
[297] "ጂጊ"፤ በተለያዩ አካባቢዎች "ደቦ" ወይም "ምናቦ" በመባልም ይጠራል።

ብድር ስለሆነም አንዱ የሌላውን ብድር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ክፍያውም የመጀመሪያው ግለሰብ እንደሁኔታው ያቀረበውን መስተንግዶ ጨምሮ፤ ከጉልበቱ ሌላ ይዞት የመጣውን የሥራ መሳሪያ ሁሉ ይጨምራል፡፡

ለምሳሌ የአረም ወንፈል የግለሰቡን ጉልበት ብቻ ይመለከታል፡፡ በእርሻ የወንፈል ሥራ ወቅት ግን በሬና የገበሬ እቃ ከግለሰቡ ጉልበት የበለጠ ዋጋ አላቸው፡፡ በአጨዳና በውቂያ ሥራ ጊዜ ደግሞ ከግለሰቡ ጉልበት በተጨማሪ ማጭድና የውቂያ መሳሪያ መያዝ አስፈላጊ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ ባንፃሩ ለፈትል ሥራ እንዝርትና ደጋን ከበሬ እቃ ጋር እኩል ዋጋ አላቸው[298]፡፡

በሌላ በኩል የጂጊ ዓላማ እንደ ወንፈል ሁሉ፤ አንድን ሥራ በጋራ ማከናወን ቢሆንም ሂደቱ በአንድ ቀን ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ስለሆነም በሚቀጥለው ቀን የሌላውን ግለሰብ (ጂጊ እስካል ጠራ ድረስ) የሥራ ብድር መመለስ ግዴታ ላይሆን ይችላል፡፡ ጂጊ በግለሰቡ የዝግጅት መጠን የሚወሰን ነው፡፡ በዚህ መሰረት ጂጊ የራሱ የሆነ ዝግጅትና የዝግጅት ሂደት አለው፡፡ እንዲሁም ከወንፈል በተለየ ሁኔታ በቁጥር ብዛት ያላቸው ግለሰቦች የሚሳተፉበትና በሂደቱም በርካታ ፎክሎራዊ ክዋኔዎች የሚከወኑበት የሥራ ባህል ነው፡፡ ሂደቱን የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው፡፡

> ለምሳሌ ከእርሻ ብንጀምር እርሻ ለማሳረስ የፈለገው ሰውየ ቀኑን ሌላ ሰው እንዳይዝበት አስቀድሞ ለአካባቢው ሰው ይነግራል፡፡ ከዚያ በኋላ የፈለገ ነገር ቢመጣ ያነ አካባቢ ሰው ወደ ሌላ ቦታ አይሂድም፡፡ እስላም ክርስቲያኑ በሬውን ይዞ፣ ሞፈር ቀንበሩን ተሸክሞ እርሻ ቦታ ላይ ይሄዳል፡፡ ያ ሰውየ እንግድህ እንደ አቅሙ ድግስ ይደግሳል፡፡ ከዚያ እርሻው ሲታረስ ከጂጊው ቦታ ጠላ ይሄዳል፡፡ ምግብ ይሄዳል፤ ይበላል-ይጠጣል፡፡ እርሻውን ጨርሰው ሲመለሱ ማታ ደሞ ከቤት ድግስ አለ[299]፡፡

በጥቅሱ እንደተገለጸው ጂጊ ከሥራ ጋር የተያያዘ ትውፊት መሆኑ ነው እንጂ፤ በአብዛኛው ከድግስ ጋር የተያያዘ ባህል ነው፡፡ በጂጊ በሥራ ቦታ ላይ ይበላል ይጠጣል፡፡ በጂጊ ከሥራ መልስ ደግሞ በቤት ውስጥ ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲዘፈን፣ ሲጫወት ያመሻል፡፡ በመጨረሻም የምረቃት ሥነ-ስርዓት ይከናወናል፡፡ በዚህ የምርቃት ሥነ-ስርዓት ላይ ጂጊ ያደረገው ግለሰብ በጂጊው የተካፈሉትን አካላት ይመርቃል፡፡ እነሱም በተራቸው የዋሉበት ሥራ የተባረከና

---

[298] ዓለሙ ኃይሉ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ.ም መርሳ- 02 ቀበሌ፡፡

[299] እንድሪስ ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 9 ቀን 2006 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ፡፡

የተቀደሰ እንዲሆን ይመርቃሉ። ስለዝግጅቱም ይመርቃሉ። ባህሉ ለእርሻም፣ ለአረምም፣ ለአጨዳም፣ ለውቂያም፣ ለቤት ሥራም...ወዘተ ተመሳሳይ ነው።

የዚህ አይነቱ የሥራ ባህል በወሎ፤ ክርስቲያን-ሙስሊም ተብሎ ተለይቶ ሳይሆን፤ ሥራው በጋራ ነው። በመሆኑም በወሎ በአጋማሚ ወይም አካባቢው ክርስቲያን ብቻ ካልሆነ በስተቀር የክርስቲያን ጂጊ የለም። የሙስሊም ጂጊ የለም። ባህሉ የጋራ ነው። ሥራ በወሎ ሃይማኖትን መሰረት አድርጎ ተለያይቶ አይሰራም። ይህም ማለት በወሎ የሥራ ባህል መሰረት ሃይማኖት ታሳቢ አይደረግም። ስለሆነም በጂጊ ትውፊት የክርስቲያኑን ሥራ ሙስሊሙ ይሰራል። የሙስሊሙን ሥራ ክርስቲያኑ ይሰራል። ልዩነት የለም። ስራውንም በጋራ ይሰራል፤ ድግሱንም በጋራ ይበላል፤ በጋራ ይጠጣል። ይህም ማለት በክርስቲያኑ ጂጊ ጊዜ ከሙስሊሞቹ በኩል ምናልባት ቃልቾቹና ሌሎች መጠጥ እማይጠጡ ግለሰቦች ካልሆኑ በስተቀር፤ ሌሎቹ ጠላውን አብረው ይጠጣሉ። ጠላ ለማይጠጡትም ቢሆን ቡቅሬ አለ።

ከዚህ በላይ እንደተብራራው የጂጊ ትውፊት በወሎ፤ በሥራ ከመረዳዳትና ከመደጋገፍ ያለፈ ሌሎች ማኅበራዊና ባህላዊ ፋይዳዎች አሉት። በዚህ መሰረት ጂጊ ወሎዬዎች በጋራ ተሳስበው በአንድ ማዕድ የሚበሉበትና የሚጠጡበት ገበታ ነው። ጂጊ ወሎዬዎች በሥራ ቦታ ላይም ሆነ፤ ከስራ መልስ ባለው ዝግጅት እያቅራሩ፣ እየሸለሉ፣ እየፎከሩና እየዘፈኑ የሚጫወቱበትና የሚዝናኑበት፣ መከፋት መደሰታቸውን የሚገልጹበት መድረክ ነው።

ጂጊ በወሎ ጎሚ፣ ቂምና ቁርሾ የሚሸርበት፤ በዚህም የተጣላ ታርቆ አብሮ የሚበላበትና አብሮ የሚጠጣበት የጋራ እሴት ነው። ጂጊ ወሎዬዎች እርስ በርስ የሚከባበሩበት፣ የሚተዛዘኑበትና የሚተሳሰቡበት ትውፊት ነው። ጂጊ ወሎዬዎች እርስ በርስ የሚመራረቁበትና የወሎ ደጋጎችን ቱፍታ የሚቀበሉበት የበረከት ቦታ ነው። ከምርቃት አንፃር የሚከተሉትን ስንኞች ለአብነት እንመልከት።

ጥቁሩ ቅብቅብ ነጭ መኸር ሁኖ፤
ምርቱ ተመርቶ ለጫኝ የሚያስን ይሁን!
ያ ተመርቶ በልተህ ፍጀው!
እስተ ልጅ ልጅህ የሚያልፍ ምርት ይሁን!
ያ ምርት ደሞ ተደግሶ፤
የደስታ፣ የክርስትና፣ የሰደቃ፣ የሠርግ፣ የሰንበቴ የሚሆን ይሁን

የመከራ አይሁን! የሞት አይሁን "እሱሱሱ...!

የጫኝ ያለህ፤ አሁንም እንደይኸው፤

ይኸ ምርት ተመርቶ በደስታ ተበልቶ የሚያልቅ ይሁን![300]

ከላይ እንደተጠቀሰው ጂጊ የሥራ ባህል ብቻ ሳይሆን፤ ሰዎች የሚዝናኑበትና የሚጫወቱበት ቦታ ነው። የመጫዎቻና የመዝናኛ መድረክ ብቻም ሳይሆን፤ የውስጥ ስሜትን መግለጫ መሳሪያ ነው። ለዚህም በወቅቱ በሥራ ቦታ ላይ የሚገጠሙ የዘፈንና የሽላላ ግጥሞች ለዚህ አባባል ማረጋገጫ አብነቶች ናቸው። በነዚህ ግጥሞች አማካይነትም በርካታ መልዕክቶች ይተላለፋሉ። የገበሬውን መከፋትና መደሰት፣ ፀፀት-ቁጭቱን፣ ሀዘን-ደስታውን፣ ተስፋ መሰነቁን-ተስፋ መቁረጡን፣ ማፍቀር- መጥላቱን፣ ድክመት-ጥንካሬውን፣ ብቸኝነቱን፣ እምነቱን፣ አመለካከቱን፣ ፍልስፍናውን፣ ባጠቃላይ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ተፈጥሯዊ ጉዳዮችን የተመለከቱ ሃሳቦቹን ይገልፃል፤ ያንፀባርቃል።

በተለይ በሥራው ሂደት ወቅት የሥራውን ጫና፣ ድካሙንና ውጣውረዱን ለመቀነስ፣ እንዲሁም ስራውን ለማፋጠን፣ ይገጥማል፤ ይዘፍናል፤ ይሸልላል፤ ይፎክራል። ግጥሞቹ፣ ሽለላዎቹና ዘፈኖቹ ደግሞ ማኅበረሰቦቹ እርስ በርስ የሚግባቡባቸው፣ የልብ ያንጀታቸውን የሚያወጉባቸው፣ እርስ በርስ የሚተሳሰሩባቸው፣ የሚገናኙባቸው፣ የሚፋቀሩባቸውና የሚዋደዱባቸው ከእነሱ ለእነሱ የሆኑና የጋራ ፎክሎራዊ እሴቶቻቸው ናቸው። ለዚህ አባባል የሚከተሉትን ቃል ግጥሞች ለአብነት እንጠቅሳለን።

እኔ እዘጋዋለሁ በሬን እንዳመሉ

ወይት ሄደ ሲሉ ከፍቶት ሄደ በሉ

እርሻ እረሱ ለእርሻ አትመለሱ

አቦሉ ሲፈላ ይቸግራል ቁርሱ

ምክር ጠፍቶ ምክር ተሳስቶ

ማረሻ በአንድ ብር ምንሽር በመቶ

---

[300] አበጋር ማዱ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ።

እደግ እደግ ብለን ያሳደግነው ቀጋ
ዘንበል ዘንበል አለ እኛኑ ሊወጋ

በበጋ እረስ ቢሉት ፀሐዩን ሲፈራ
በሐምሌ እረስ ቢሉት ዝናቡን ሲፈራ
ልጁ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈ

ረጅም ዛፍ አይቶ ይሰቀላል ጭላት
ሳይዘሩት ይበቅላል አረምና ጠላት

እንዴት ነው ጨለማው እንዴት ነው ሌሊቱ
ያለ ሽማግሌ የታረቅንበቱ

ኧረ-ተው አንተ ሰው ስሮጥ አታባረኝ
አንተም አበዛኸው እኔንም መረረኝ

በሮቹ ጥቋቁር ጅራታቸው ፈንዛ
አርሰን ለበላነ ምቀኛችን በዛ

ሲያርሙ አያርም ሲዘሩ አይዘራ
ይገመግማል የሰው አዝመራ

እንግድህ ደጋሌት ንፍሮም አልቀቅለው
አይደለሞይ ዝልል እሚያነጋግረው
እርሻውን አረሱት ዘቅዝቀው እንደቦ
አባትዮው ቢሞት ልጅዮው የለሞይ[301]

---

[301] ናትናዔል ደምለው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ወልዲያ- 02 ቀበሌ፡፡

በሌላ በኩል ጂጊ በወሎ ቂም ያላቸው ሰዎች የሚታረቁበት ቦታ ነው። የአካባቢው ነዋሪዎች አንደሚሉት ወሎዬዎች አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት የጋራ እሴታቸው የሆነውን ያህል፤ ባንፃሩ ሰው መጥላታቸውን የሚገልጹት ከጠሉት ሰው ጋራ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት ባለመፈለጋቸው ነው[302]። በዚህ መሰረት ሁለት የተጣሉ ሰዎች በአንድ ግለሰብ ጂጊ ላይ ቢገናኙ በአንድ ገበታም ባይሆን እንኳን በአንድ ቤት ውስጥ አንዱ ባለበት ሌላው በዚያ ቤት ውስጥ ገብቶ አይበላም፤ አይጠጣም[303]።

ነገር ግን እርሻም ከሆነ ለእርሻው ለራሱ፣ ለበሬ እቃውና ለበሮቹ ሲባል፤ አዲስ ቤት እየተሰራም ከሆነ ለቤቱ ሲባል፤ አረምም ከሆነ ለሰብሉ ሲባል፤ አጨዳና ውቂያም ከሆነ ለምርቱ ሲባል፤ የከረረ ቂም በቀል እንኳን ቢሆን፤ "አይበጅም!" በሚለው የወሎዬዎች ብዚሂል መሰረት ጂጊ ቦታ ላይ ይታረቃሉ። ሰላም ያወርዳሉ። ተበደልኩ የሚለው አካል እንኳን "መቼስ እርጥብ ላይ ሁኜ ምን አደርጋለሁ!" በማለት ይቅርታ ያወርዳል። ከዚህ በኋላ በአንድ ገበታ አብረው ይበላሉ፤ አብረው ይጠጣሉ። በዚህ አውድ ውስጥ የሚፈፀም እርቅ ደግሞ በአበጋር ወይም በዘወልድ አለያም በመደበኛው የሽምግልና የእርቅ ሥርዓት እንደሚፈጸም እርቅ ካሳ የሚከፍልም ሆነ፤ ካሳ የሚቀበል አካል የለም። በዚህ የእርቅ ሂደት "አንተም ተው! አንተም ተው!" በቂ ነው። ስለዚህ ጂጊ በወሎ፤ በሥራ ከመረዳዳትና ከመደጋገፍ ያለፈ የሰላምና የፍቅር ምንጭ በመሆን የሚያገለግል የወሎዬዎች የጋራ እሴት ነው።

በሌላ በኩል ጂጊ ታላላቆች የሚከበሩበት እነሱም የሕይወት ልምዳቸውን የሚያካፍሉበትና ለትውልዱ የሚያስተላልፉበት፣ ፍቅራቸውን የሚገልጹበት ቦታ ነው። ለምሳሌ በጂጊ የሥራ ባህል አባቶች ሥራ ባይሰሩም እንኳን በሥራ ቦታ ላይ ይገኛሉ። በግብጣው ላይ ይታደማሉ። በዚህም ጠቃሚ፣ ጠቃሚ አስተያየቶችንና ምክሮችን ለልጆቻቸው ይለግሳሉ። ለችግሮች መፍቻ ብልሃቶችን ያመነጫሉ፤ ይመርቃሉ። በወሎ የጂጊ ትውፊት አቅመ ደካሞች ይረዳሉ፤ የሃይማኖት አባቶች ይታገዛሉ። የእደ ጥበብ ባለሙያዎች የእጃቸውን ዋጋ ይከፈላሉ። ይህም ማለት በጂጊ የአቅመ ደካሞች እርሻ ታርሶ ይዘራል። አዝመራቸው ይሰበሰባል። ቤታቸው ይሰራል። በጂጊ የአበጋሮች፣ አንዳንድ ጊዜም የሼሆች እርሻ ይታረሳል። አዝመራቸው

---

302 ገዳሙ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- አማየ ሚጫ።

303 መጠጥ ቤት ከሆነ ግን አንዱ ከገባበት ቤት ሌላው ሆነ ብሎ ተከትሎት ይገባል። ይህንን የሚያደርገውም ሌላ ነገር ባያደርግ እንኳን ለአዝማሪ ግጥም በማቀበል ጠላቱን በነገር ለመሸንቆጥ ነው። ወይም ለመተረብ ነው።

ይሰበሰባል[304]። ይህም ሲሆን ወሎዬዎች እንደሌሎቹ ማኅበራዊና ባህላዊ ግንኙነቶቻቸው ሁሉ፤ በዚህ የሥራ ባህላቸውም ሃይማኖታቸውን ታሳቢ አያደርጉም። ይህንንም የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚከተለው ያብራሩታል።

> የዚህ አገር የጂጊ ባህል ከእስላም ሥራ እኔ አልሄድም፤ ከክርስቲያን ሥራ እኔ አልሄድም ብሎ ሳይሆን፤ ክርስቲያኑ ድፍት ጥልም ብሎ የእስላሙን ሥራ ሰርቶ ነው። በተመሳሳይ እስላሙ ላቡቱ ጠብ እስቲል የክርስቲያኑን ሥራ ሰርቶ ነው። ሥራውን ሊሰራ ሲሄድ የሚያስበው ሃይማኖቱን ሳይሆን፤ እሱ ጋር መተጋገዙን ነው። ነገ እኔንም የሚያግዘኝ ወንድሜ ነው፤ ብወድቅ የሚደግፈኝና የሚያነሳኝ አብሮኝ የኖረ-ጎረቤቴ ወንድሜ እሱ ነው፤ የሱን ስራ ካላገዝኩት እኔስ ማን አለኝ በሚል አስተሳሰብ ነው። በዚህ መሰረት ማኅበረሰቡ ካለው የመተጋገዝና የሥራ ባህል አንፃር ሃይማኖት እዚህ ውስጥ ምንም ጣልቃ ሳይገባ፣ በፍጹም የመረዳዳት ስሜት የሚሰሩበት የሥራ ባህል ነው[305]።

ከዚህ በላይ ከቀረቡት መሰረታዊ ነጥቦች መረዳት እንደሚቻለው ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ ካስቻሏቸው የጋራ እሴቶች መካከል አንዱ የሥራ ባህላቸው መሆኑን ነው። ወሎየዎች ባለቸው የሥራ ባህል መርህ መሰረት እርስ በርስ ይረዳዳሉ፣ ይደጋገፋሉ። ይተሳሰባሉ፣ይተዛዘናሉ። አብረው ይበላሉ፤ አብረው ይጠጣሉ። እርቅ ያወርዳሉ። በዚህም በሰላምና በፍቅር በጋራ አብረው ይኖራሉ።ለዚህም ከላይ ከቀረቡት አብነቶች በተጨማሪ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ በተጨባጭ እንዴት እንደሚገለጽ የሚያሳዩ ከወሎየዎች የሥራ ባህል ጋር የተያያዙ ሌሎች የጋራ እሴቶች አሉ። እነዚህ የጋራ እሴቶች በወሎ የቀንጃ፣ የበዓላት-ማክበርና የአግማስ ትውፊቶች ናቸው።

6.1.3.2፦ የቀንጃና የበዓላት ትውፊቶች በወሎ

ቀንጃ ማለት በወሎ አንድ በሬ ብቻ ያለው ግለሰብ፤ ሌላ አንድ በሬ ብቻ ካለው ግለሰብ ጋር አቀናጅቶ ሁለት አርጎ ማረስ ማለት ነው። ይህም መቀናጀ በመባል ይታወቃል[306]። የዚህ አይነቱን ትውፊት በተመለከተ የዚህ ጥናት አቅራቢ "ለመሆኑ ክርስቲያንና ሙስሊም በወሎ አቀናጅቶ ማረስ ይችላል?" የሚል ጥያቄ ለአንዱ መረጃ አቀባይ አቅርቦ ነበር። መረጃ አቀባዩ

---

304 የአቅመ ደካሞች፣ የአበጋሮች፣ የሼሆችና የእደጥበብ ባለሙያዎች ሥራ በጂጊ አማካይነት ሲሰራ እንደመደ በኛው የጂጊ ባህል የመብልና የመጠጥ ዝግጅት ላይኖር ይችላል።

305 እንድሪስ አህመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሚያዚያ 26 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልድያ- 03 ቀበሌ።

306 መላኩ ቢተው፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አቧራ።

የሰጡት ቁርጥ ያለ መልስ ደግሞ "ቅድም ያሳለሙኝን ቄስ አይተሃቸዋል! እሳቸው ቄስ አንድ በሬ ነው ያላቸው፤ ቀንጀኛቸው ግን ሙስሊም ነው!"[307] የሚል መልስ ነበር።

በዚህ ጥቅስ መሰረት ቁም ነገሩ ቄሱና ሙስሊሙ መቀናጀ መግጠማቸው አይደለም። ዋናውና መሰረታዊው ጉዳይ ግን የቀንጃ ትውፊት ከየግል እምነታቸው ጋር የተያያዘ የሥራ ባህል መሆኑ ነው። ይኸውም ሁለቱም በየግላቸው ሃይማኖታቸውን መሰረት አድርገው ሥራ የማይሰሩባቸው ቀናት አሉ። እነዚህ ቀናት ለሁለቱም የበዓላት ቀናት በመባል ይታወቃሉ። በዚህ መሰረት በቄሱ የበዓላት ቀናት ሙስሊሙ የቄሱን በሬ አይጠምዱም። በሙስሊሙ የበዓላት ቀናት ደግሞ ቄሱ የሙስሊሙን በሬ አይጠምዱም። ምክንያቱም በቄሱ በዓል የቄሱ በሬ በእለተ ሰንበት አረሰ ማለት ቄሱ ራሳቸው ሰንበትን እንደሻሩ ይቆጠራል። በተመሳሳይ የሙስሊሙ በሬ የአብዱየ (እለተ እረቡ) እለት አረሰ ማለት ግለሰቡ ራሳቸው አብዱየን እንደሻሩ ይቆጠራል።

በዚህ መሰረት ሁለቱም ልዩነታቸውን በዚህ መንገድ በማቻቻል፤ የአንዱን በዓል ሌላው አይሽርም፤ ባንዳሩ ያከብራል። ወይም ቄሱ በሚያከብሩት የበዓል እለት ሙስሊሙ ቀንጀኛ ቸው የቄሱን በሬ አይጠምዱም። ቄሱም በተመሳሳይ የሙስሊሙን በሬ አይጠምዱም። በዚህ አይነት መንገድ ሁለቱም ልዩነታቸውን አምነው ይቀበላሉ። ሁለቱም ልዩነታቸውን በዚህ አይነት መንገድ ያጠባሉ፤ ይደፍናሉ። በዚህ አይነት ብሂል፣ በዚህ አይነት ፍልስፍና ወሎዬዎች ፍላጎታቸውን ጠብቀው፣ ልዩነታቸውን አክብረው፣ የማኅበራዊ ሕይወት መሰረታቸው ሳይናጋ በሰላምና በፍቅር አብረው ይኖራሉ። የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የሚገለጸው በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የማኅበራዊ መስተጋብር ፍልስፍና አማካይነት ነው። ደንብና ስርዓት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ነው። የሚከተለውን ምሳሌ ለአብነት እንመልከት።

> በሙስሊሙ አሁን ጁመዓ የመስገጃ ቀን ነው። ሮብ ደግሞ አብዱየ እሚባል በዓል አለ። በጁመዓ ሙስሊሙ ሥራ አይሰራም። በአብዱየም በሬ አይጠመድም። ለምሳሌ አሁን እኔ ክርስቲያን ነኝ። የእኔ በሬ የሰንበት እለት አይጠመድም። የእስላሙ ደሞ የአብዱየ አይጠመድም። እሱም እሁድ ልጥመድ አይልም። እኔም ሮብ ልጥመድ አልልም። በዓላት መሆናቸውን ሰለምናውቅ ማለት ነው። ሮብ አብዱየ ናቸው፤ እሁድ ሰንበት ነው። እሁድ የእኔ በዓል ነው፤ ሮብ የእሱ በዓል ነው። በዚህ እንተማመናለን፤ እንተዋወቃለን[308]።

---

[307] በሪሁን ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ሐብሩ - ቁር 14 ቀበሌ

[308] ዓሊ መሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም ሐብሩ -አንጦ 04 ቀበሌ።

ከላይ በቀንጃ አብነት የተጠቀሱት ምሳሌዎች የግል ፍላጎትን በጠበቀ ሁኔታ በዓላት የማክበር ብሂል በወሎ፤ ከግለሰብ አንፃር የተጠቀሱ ምሳሌዎች ናቸው። ነገር ግን በወሎ ጀማውን የሚያጠቃልል የበዓላት ማክበር ትውፊት አለ። ይህም በወሎዬዎች ዘንድ ሥረ-መሰረት ያለውና የሃይማኖት መቻቻል እሴት ተምሳሌት የሆነ የጋራ ትውፊት ነው። ለምሳሌ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት በእስልምናው በኩል አብዱየንና ጁመዓን ጨምሮ፣ የበረዶ፣ የንፋስና የ"ላምባ"[309] የበዓላት ቀናት አለ። የበረዶ፣ የንፋስና የላምባ በዓላት ቀናት ከአዝመራ ጋር የተያያዙ የበዓላት ቀናት ናቸው። በዚህ ምክንያት እነዚህን የበዓላት ቀናት እንደ ሙስሊሙ ሁሉ፤ ክርስቲያኑ ያከብራቸዋል፤ ይጠነቀቅላቸዋል።

በተመሳሳይ በክርስትናው በኩል ሁለቱም የሚያከብሯቸው የበዓላት ቀናት አለ። ከዚህ አንፃር አንዱ የሌላውን የበዓላት ቀናት የሚያከብርበት መሰረታዊ ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እነዚህን የበዓላት ቀናት በመሻሩ የተነሳ ከማኅበራዊ ሕይወቱ ጋር የተያያዙ ችግሮች ይገጥሙኛል ብሎ ስለሚያምን ነው። ከዚህም ሌላ አንዱ ለሌላው ያለውን ክብር፣ መተሳሰብና መተዛዘን፣ ፍቅርና ሰላም ወዳድነቱን የሚገልጽበት መንገድ ነው። ተቻችሎ አብሮ ለመኖር ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ነው። ከዚህ በታች የቀረበው ጥቅስ ከላይ የተገለጹትን ነጥቦች የሚያረጋግጥ አብነት ነው።

> ልደታ፣ ባለግዚሀር፣ አቦ፣ ገብሬል፣ ስላሴ፣ ማሪያም፣ ጊዮርጊስ፣ ሚካኤል፣ እሁድ በሳምንትና ተክልዬ፣ የተቆጠሩ ባላት ናቸው። እነዚህ አይነኩም። የተለመደው ባላት እየታበለ [እየተከበረ] ነው። የጣሱ አገሮይ ነበሩ። ያበለውን እዝህ ትቶ የጣሰውን መታው። እነዛ የጣሱ ሰወይ ተቀጡ። ዳስ ሰርተው አበሉ። በባላት በኩል አደብ አለ። ባላት ጣስ ጣስ ብለህ ድህነት ዶልከን አለ ሰው። ባላቱ አንዲታበል (አንዲከበር) ያደረጉት እስላሞች ናቸው። ለግብርናው ተናንተ አናንስም ግን ዛውያው፣ ቃዲውም ቢለፈልፍ እኛ መሬቱ ስለለመደ እናብላለን አለ። ትከስብ ውየ ማታ ታስመታሁት ምን ጠቀመኝ። የጣሱት ሰወይ መቀጫ ከፍለው እዚያ ተግንጥለው እዚህ ገቡ። ለባለፈ እቀጣለሁ አለ። የቡድንና የዛውያ ልፍለፋ በክቷል። አላህን ባርክልን ብለን ታለመንን አላህስ ቢሆን አንተን አመንኩ ብለን ታላበልን በማን ቁመን ማነን እናማለን (Rukya 2013:281)::

በጥቅሱ ውስጥ ከተገለጹት መሰረታዊ ነጥቦች መረዳት የሚቻለው ዋና ቁም ነገር የአካባቢው ማኅበረሰብ በዓላት ከማክበርና በዓላት ከመሻር ጋር በተገናኘ አስተሳሰቡ፣ አመለካከቱ፣ የማኅበራዊ ሕይወት ፍልስፍናው፣ የአኗኗር ዘይቤውና ብሂሉ ምን እንደሚመስል ነው። ይህም የሚያሳየው የወሎዬዎች የማኅበራዊ መስተጋብር የተመሰረተው ጎራ ለይቶ ሳይሆን፤ ሃይማኖታዊ በሆነው አስተሳሰብ ላይ ሳይቀር እርስ በርሱ ድርና ማግ ሆኖ ነው። ይህም

---

[309] በአካባቢው ነዋሪዎች ገለፃ መሰረት "ላምባ" ማለት በጥቅምትና ህዳር ወራት አካባቢ ባለው ቅዝቃዜ ምክንያት በማሽላቸው ላይ የሚታይ ላምባ መሰል ፈሳሽ ነው።

በወሎዬዎች የሥራ ባህል ሁሉ የሚገለጽ የጋራ እሴት ነው፡፡ እሴቱም ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ ያስቻለ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ ሃብት ነው፡፡ ሌላኛው ከወሎዬዎች የሥራ ባህል፣ ወግና ልማድ ጋር የተያያዘው የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ ጉዳይ የአግማስ ትውፊት ነው፡፡፡ ይህ ትውፊት በወሎ ከማሽላ ውቂያ ጋር የተገናኘ የወሎዬዎች ባህል፣ ወግና ልማድ መገለጫ የሆነ የጋራ እሴት ነው፡፡

6.1.3.3፦ የአግማስ ትውፊ በወሎ

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት የጁ የሚታወቀው በደጋሌት (ማሽላ) ወይም በአቦላ ምርት ነው፡፡ ለዚህም፤

የየጁ ደጋሌት ታች አላ በርበሬ
የአዋኔው ጥንቅሽ ደስ ሲል አገሬ

የደጋሌቱ አገር አላ ገዶ ነው
ጥንቅሹን ወልዲያ ምን አበቀለው፤[310]

ተብሎ የዘፈን ስንኝ ተቋጥሮለታል፡፡ ለዚህ መሰረታዊው ምክንያት ደግሞ በጥቅምትና በህዳር ወራት ውስጥ የገጠሩ አርሶ አደር እሼትና አገዳውን ይዞ ከተማ ያለውን ዘመዱን የመጠየቅ ባህል ስላለው ነው፡፡ በወሎ የገጠሩ አርሶ አደር ከተማ ለገበያ ሲወጣ እቃውን ላስቀመጠባትና ጠጅና ጠላ ሲጠጣ ለተዋወቃት ኮማሪያት ሳይቀር፤ የየጁ ደጋሌት እሼትና አገዳ ከገጠሩ እኩል ለከተማው ነዋሪም ሲሳይ ነው፡፡

የደጋሌት ማሳው መንገድ ዳር ያለ ወሎዬ አርሶ አደር በጥቅምትና በህዳር፤ በማሳው አካባቢ ለሚያልፍ መንገደኛ "አርሂብ እንጂ!" ብሎ አገዳ (ጥንቅሽ) ቆርጦ ይሰጣል፡፡ ይህም ከግለሰቡ የለጋስነት ባህርይ ያለፈ የጀማው ደንብና ሥርዓት ነው፡፡ የወሎዬዎች ልዩ መገለጫ ባህል፣ ወግና ልማድ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ማኅበራዊ መስተጋብር በወሎ የክርስቲያን ሙስሊሙ የጋራ እሴት ነው[311]፡፡ የክርስቲያን ሙስሊሙ የመቀራረቢያ መንገድ ነው፡፡ የመተሳሰሪያ ብሂል ነው፡፡ ዝምድና የመመስረቻ ትውፊት ነው፡፡

---

[310] ውዳድስ ምህረቱ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 10 ቀን 2004 ዓ.ም. ሐብሩ- ስሪንቃ፡፡
[311] ወዳጄ ይማም፤ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም ጉባላፍቶ- አማየ ሚጫ፡፡

ከዚህም ሌላ የየጁ ደጋሌት የወሎዬዎች ታታሪነት፣ ጀግንነት፣ ክብርና ኩራት መገለጫ እንደነበር ይነገራል። ለዚህም ወሎዬዎች "የየጁ ገበሬ ብዙ ማምረቱን የሚያረጋግጠው ያመረተውን ምርት በምንሸር ጥይት ተኩሶ በመምታት ነው!" የሚል ትውፊት አላቸው። የአካባቢው ነዋሪዎች ትውፊቱን እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> ዱሮ ነው አሉ፣ እነ ጉሎ እጅጉ፣ እነ መኮነን ያሲን፣ እነ ተክሌ ሸንቶ፣ እነ ባይለየኝ አድማሱ እና ሌሎች ታላላቅ ሰዎች ምርት ሲያመርቱ ጠገቡና "እኔ አንዳንተ መሰልኩህ! የኔን ምርት እኮ የምንሸር ጥይት አይበሳውም!" በመባባል "የምንሸር ጥይት ይዘልቀዋል አይዘልቀውም?" ብለው፣ "እኔ በምርቱ ወዲያ ልተኛና እስቲ አንተ ተኩሰህ እኔን ምታኝ?" ተባብለው እየተወራረዱ ምርቱን ይመቱት ቆየ ይባላል። በኋላ ቢተኮስ ምንም አልመታውም። በይታይ አላ ውሃ እሚባል፤ በዶሮ ግብር በታይ። ይሽ የሆነው በጥጋብ ነው። በልተው ጠጥተው የጠገቡ ጊዜ "የኔን ምርት ጥይት ይዘልቀዋል። አይዘልቀውም?" ብለው መወራረጃ አደረጉት። ሽያም ወዲህ ይሽው አፍሮ ቀረ። ጡር ሆነ። ቀረ። የታለ? በውቂያው እሚደረገው ስርአት ሁሉ ይሽው አሁን ቀረ። በኛም በእስላሞቹ አሁን ጠላ እየጠመቃችሁ አትውቁ አለ። አስቀረው እንጂ፤ በፊት በሁሉም በክርስቲያኑም በእስላሙም እሚደረግ አንድ አይነት ባሕል ነበረ። አግማስ ምንም ቢሆን አትቀርም። አሁን ግን አስቀርተውታል። አሁን ብንወቃውም ሽቀለባችን አይዘል። በተለይ ሽ66 ወዲህ። ስልሳ ስድስት ላይ አንቱ የተባለ ደጋሌትና ጤፍ ተወቃ። ሽዚያ ወዲህ አበለ መሬቱ። ሽዚያ ወድህ ያው ደርግ ገባ ኃይለሥላሴም ለቀቀ ምርቱም በዚያው ቀረ! ቀረ!![312]

የተለያዩ ትውፊቶችን በውስጡ የያዘው የየጁ ደጋሌት አመራረቱም የራሱ የሆነ ፎክሎራዊ ክዋኔዎች አሉት። በነዚህ ክዋኔዎች አማካይነት የተለያዩ የሰው ለሰው ግንኙነቶች ይፈጠራሉ። የተለያዩ ድርጊቶች ይፈፀማሉ። ከነዚህ ድርጊቶች መካከል የአግማስ ትውፊት አንዱ ነው። የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ለማሽላ ውቂያ የተለያዩ ጥንቃቄዎች ይደረጋሉ። ለነዚህ ጥንቃቄዎች ሲባል በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ እጅግ የተመሰገነ፣ የተከበረና የተወደደ ግለሰብ ተመርጦ አግማስ ይሆናል። ይህ ግለሰብ ማሽላው ተወቅቶ፣ ተመርቶ፣ ተሰፍሮና ተጭኖ ከቤት እስከሚገባ ድረስ ከአውድማው አይንቀሳቀስም። እዚያ አካባቢ አይርቅም። እዚያው ይውላል፤ እዚያው ያድራል። እዚያው ይበላል፤ እዚያው ይጠጣል። ምክንያቱም ማሽላው ተወቅቶ ወዲያው አይጫንም። ቢያንስ፣ ቢያንስ ለአንድ ሳምንት ያህል ፀሐይ እየመታው አውድማው ላይ ይቆያል።

በማሽላ ውቂያ የአግማስ መሰረታዊ ኃላፊነት ከእለቱ እለት ጀምሮ እስከ ፍፃሜው ድረስ የሚከናወኑ ፎክሎራዊ ክዋኔዎችን መምራትና የአውድማውን አጠቃላይ ድባብ ማስጠበቅ ነው።

---

[312] አበጋር ማዴ በላይ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- ገዶ።

በዚህም ማሽላው የሚወቃበት አውድማ ጩኸት የሌለበት፤ ግር፣ ግር ያልበዛበት፤ ባጠቃላይ ጥንቃቄ የተሞላበት ሆኖ እንዲጠናቀቅ የማድረግ ኃላፊነት አለበት[313]።

የማሽላ ውቂያ በወሎ ከፎክሎራዊ ሂደቶቹ አንፃር ከሦስት ቁጥር ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ክዋኔዎች ይፈፀሙበታል። ለምሳሌ ማሽላው ለውቂያ ሲዘጋጅ ክምሩ ከመዘርገፉ በፊት ቀስተንቻና እሬት የሚባሉ ተክሎች ተቆርጠው በሦስት ድንጋዮች እየተዋቀሩ ክምሩ ባለበት አካባቢ በሚገኙ መስቀለኛ መንገዶች ላይ ይቀመጣሉ። ሦስት ጭብጦዎች ከኑግና ከማሽላ ይዘጋጃሉ። ፌጦ፣ ጤናዳምና ነጭ ሽንኩርት ምርቱ በሚመረትበት ላዳ ላይ እኩል መጠን ባላቸው ሦስት ድንጋዮች ይደቆሳሉ። ከዚያም ከጠላ ጋር ተቀላቅለው ለዚህ ተግባር በተዘጋጁ ሦስት የማሽላ ዛላዎች በአግማሱ አማካይነት ክምሩና አካባቢው ይረጫል።

ከዚህ በማስከተል የክምር መዘርገፊያ ጭብጦ ከተበላና ጠላ ከተጠጣ በኋላ ክምሩ ይዘረገፋል። ውቂያው ተከናውኖ ከተጠናቀቀ በኋላ ምርት ማምረት ይጀመራል። ምርቱ መመረት ከመጀመሩ በፊት ግን ሦስት የኑግ ልጥልጦች በብሳና ቅጠል ተጠቅልለው፤ ክምሩ ከተረጨባቸው ሦስት የማሽላ ዛላዎች ጋር በሦስት ድንጋዮች ተዋቅረው፣ ማሽላውን ከወቁት በሬዎች ማፈኛና ከቀላሹ (ከመሪው) በሬ ጭራ ጋር ተጠቅልለው ምርቱ ከሚመረትበት እምብርት (መሀል) ላይ ይቀመጣሉ።

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት የዚህ አይነቱ ፎክሎራዊ ብሂል የሚከናወነው ምርቱ በረከትና ረድኤት እንዲኖረው ነው። ወይም ምርቱን "ከሰይጣን" ወይም "ከሰላቢ/ ኢቢሊስ" ለመከላከል ነው። የዚህ ሁሉ አድራጊና ፈጣሪ ደግሞ አግማስ ተብሎ የተሰየመው ግለሰብ ነው። አግማስ በማሽላ ውቂያ ሁሉን ነገር ባርኮ የሚያስጀምረው እሱ ነው። ለምሳሌ ክምሩ ሲዘረገፍ የሚጀምረው እሱ ነው። ምርቱ ሲመረት የሚጀምረው እሱ ነው። ምርቱ ሲሰፈር ባርኮ የሚጀምረው እሱ ነው። ጭብጦ እየቆረሰ ለሚመጣ እንግዳ ሁሉ የሚሰጠው እሱ ነው[314]።

የጭብጦውን ትውፊት የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት "ይኸን፣ ይኸን የሚያህል ጭብጦ እንጨብጣለን። ሦስት ጭብጦ ይሄዳል።አግማሱ ለመጣው ሁሉ እየቆረሰ ይሰጣል። አላፊ አግዳሚው ሁሉ እያገለለ ይበላል። በልቶ ሲያበቃ "ይበርክት!" እያለ እየመረቀ ይሄዳል።

---

313 ሃምሳ አለቃ መኮንን የሺጥላ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ።

314 በሪሁን ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ።

ይኸ የጋራ ባህላችን ነው፤ የጋራ መገለጫችን ነው[315]!" በማለት ትውፊቱ ያለውን ማኅበራዊና ባህላዊ ፋይዳ በማብራራት ነው።

በአካባቢው ትውፊት መሰረት ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ፎክሎራዊ ክዋኔዎች ሁሉ፤ ሙስሊሙ ለክርስቲያኑ አውድማ፤ ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ አውድማ አግማስ ይሆናል። መሰረታዊው ጉዳይ አንድ ሰው አግማስ እንዲሆን መስፈርቱን አሟልቶ መገኘቱ ብቻ ነው። ይህንንም የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት "እንደውም አሁን እኔ ለምሳሌ ክርስቲያን ነኝ፤ እኔ እስላም አግማስ ያረኩ እንደሆነ፤ አውድማው ላይ የሚታረደውን ዶሮ ማረድ የሚችለው እሱ ነው፤ ከምርቱ ላይ ማለት ነው። "ይኸም ዲያብሎስ እንዳይመጣ ማባረሪያ ነው[316]። በማለት በወሎ በእርድ በኩል ያለው ልዩነት እንኳን አንደ ሚዜ ትውፊት ሁሉ፤ የአግማስ ትውፊት ላይ ሲደርስም ልዩነቱ እየጠበበ ይሄዳል።

የማሽላ አዝመራ በየጁ ሙስሊም ክርስቲያኑን የሚያቀራርብበትና የሚያስተሳስርበት በርካታ ትውፊቶች አሉት። ትውፊቶቹም ከወሎዬዎች የጉርብትና ብሂል ጋር የሚተሳሰሩ ናቸው። ለምሳሌ ቀደም ሲል በወሎዬዎች የወንፈል እና የጂጊ የሥራ ባህል እንደተብራራው ሥራው በጋራ የሚከወን ነው። ይህም ማለት የማሽላ አዝመራ በየጁ በጋራ ይታረሳል፤ በጋራ ይዘራል። በጋራ ይኮተኮታል፤ በጋራ ወፍ ይጠበቃል። እሼት አገዳው በጋራ ይበላል፤ ከዚያም የህዳር ሚካኤል እለት በጋራ ታጥኖ በጋራ ይቆረጣል። በመጨረሻ በጋራ ተወቅቶ በጋራ ይመረታል። ከዚያም በጋራ ወደ ቤት ይከተታል። በነዚህ ሁሉ ሂደቶች ውስጥ ክርስቲያን ሙስሊሙ እርስ በርስ ይረዳዳል፤ ይደጋገፋል፤ ይተሳሰባል፤ ይተዛዘናል፤ አብሮ ይበላል፤ አብሮ ይጠጣል። አብሮ ይጫወታል፤ አብሮ ይዝናናል። ለምሳሌ የማሽላ ውቂያ በወሎ ከስራው ይልቅ፤ አብሮ ከመብላትና ከመጠጣት፤ አብሮ ከመደሰትና ከመዝናናት ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው።

ከመብልና ከመጠጥ ጋር በተገናኘ በማሽላ ውቂያ ወቅት የመዘርገፊያ መብልና መጠጥ አለ። በማሽላ ውቂያ የቆረቆንዳ ማውጫ መብልና መጠጥ አለ።በማሽላ መውቂያ የላዳ መጣያ መብልና መጠጥ አለ። በማሽላ ውቂያ የመስፈሪያ መብልና መጠጥ አለ። በማሽላ ውቂያ

---

[315] ዓለሙ ኃይሉ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 02 ቀበሌ።

[316] እንድሪስ ይመር፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- ቁጥር 14 ቀበሌ።

ማታ በመኖሪያ ቤት ውስጥ መብልና መጠጥ አለ። በማሽላ ውቂያ የማስጫኛ መብልና መጠጥ አለ። በዚህ ሂደት ሁሉ ከመብልና መጠጡ ጋር ተያይዞ መዝናናት አለ፤ መደሰት አለ[317]።

ለምሳሌ የጎረቤት ወንዶች ልጆች (ወጣቶቹ) ከመኖሪያ ቤታቸው ወይም ከቤተሰብ ተነጥለው ለመጀመሪያ ጊዜ ውጭ ማደር የሚፈቀድላቸው በማሽላ ውቂያ ወቅት ነው። በዚህ ወቅት ምርቱ ከአውድማ ላይ ለሳምንታት ያህል ስለሚቆይ የአገዳ ጎጆ ተሰርቶ ምርቱ ይጠበቃል። በዚህ ወቅት ክርስቲያን ሙስሊም ሳይባል የጎረቤት ልጆች በጋራ ተሰባስበው ምርቱን ሲጠብቁ ያድራሉ። የዚህ አይነቱ አጋጣሚ ለእነሱ የወጣትነት ዘመናቸውን አሀዱ ብለው የሚጀምሩበት ወቅት ነው። ወቅቱ የወጣትነት ዘመናቸው አንዱ አካል ነው። በዚህ ወቅት ጥርት ባለው ሰማይ ላይ የተሰደሩትን ከዋክብትና ጨረቃ እያደነቁ የተፈጥሮን ረቂቅነት የሚያደንቁት በዚህ ወቅት ነው።

በዚህ አውድማ ላይ በጋራ እየበሉ እየጠጡ፣ እየተጫወቱ እየተዝናኑ፣ የተፈጥሮን ውበት እያደነቁ፣ በአንድ የአገዳ ጎጆ ውስጥ ሙስሊም ክርስቲያን ሆኖ በጋራ መኖርን ይለምዳሉ። ይህንን እድል ለማግኘት መስፈርቱ ጉርብትና ብቻ ነው። የወሎ የጉርብትና መስፈርት ደግሞ የክርስቲያን አውድማ ነው፤ የሙስሊም አውድማ ነው ሳይሆን፤ በጥቅሉ "የጎረቤት አውድማ ነው!" በሚል ብሂል የተቃኘ ነው። ምክንያቱም ለክርስቲያኑ አውድማ ምርቱ ወደ ቤት እስከሚገባ ድረስ አግማሱ ሙስሊሙ ነው። በተመሳሳይ ለሙስሊሙ አውድማ አግማሱ ክርስቲያኑ ነው።

በዚህ መሰረት ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው ከሚኖሩባቸው እሴቶች መካከል አንዱ የማሽላ ውቂያና የአግማስ ትውፊት ነው። አግማስ በወሎ እንደ ወሎ ደጋጎች ሁሉ፤ የበረከት ምንጭ ነው፤ የመልካም ነገር ሰበብ ነው። የበረከት ምንጭና የመልካም ነገር ሰበብ በወሎ ቀደም ሲል በተለያዩ አብነቶች እንደተጠቀሰው ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ፤ ሙስሊሙ ለክርስቲያኑ ነው። የሃይማኖቶቹ ትውፊቶች ፋይዳም ተመሳሳይ ነው። በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ የሚገለፀው በነዚህ የጋራ እሴቶች አማካይነት ነው።

---

317 ዓሊ መሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አንጦ 04 ቀበሌ።

6.1.4፡- ጉርብትና በሃዘን

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከላይ በቀረቡት ንዑስ አርዕስት መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ በሰርጉ፣ በልደቱ፣ በክብረ-በዓላቱ፣ በእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቱ፣ በወንፈሉ፣ በጂጊው፣... ወዘተ እንዴት እንደሚገለጽ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ እነዚህ ማኅበራዊና ባህላዊ ትውፊቶች ደግሞ ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችሏቸው የጋራ እሴቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም በእነዚህ እሴቶች አማካይነት ወሎዬዎች አብረው ይበላሉ፤ አብረው ይጠጣሉ፤ እርስ በርስ ይረዳዳሉ፤ ይደጋገፋሉ፡፡ እርስ በርስ ይተሳሰባሉ፤ ይተዛዘናሉ፡፡ እርስ በርስ ይከባበራሉ፤ አንተ-ትብስ አንቺ-ትብሽ ይባባላሉ፡፡ እንዲሁም አንዱ ከሌላው ጋር ባለው ማኅበራዊ መስተጋብር አማካይነት በጋብቻም ሆነ በአበልጅ ትውፊት ቤተሰባዊ ትስስር ይመሰርታሉ፡፡ በዚህም በሰላምና በፍቅር አብረው ይኖራሉ፡፡

በሌላ በኩል ወሎዬዎች በደስታ አብረው እየበሉ፤ አብረው እየጠጡ እንደሚደሰቱና እንደሚዝናኑ፤ በሥራም እንደሚረዳዱና እንደሚደጋገፉ፣ በእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነታቸው እንደ ሚከባበሩና እንደሚተዛዘኑ ሁሉ፤ በሃዘንና በመከራም አብረው ያዝናናሉ፤ ያስተዛዝናሉ፡፡ ይረዳዳሉ፤ ይደጋገፋሉ፡፡ በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ የሚገለጸው በደስታ፣ በሥራ፣ በእለት ተእለት የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን፤ በሃዘንና በመከራ ጭምር ነው፡፡

በሃዘንና በመከራ ጊዜ ያለውን የወሎዬዎች የእርስ በርስ ግንኙነት፤ እንዲሁም የእርስ በርስ መረዳዳትና መደጋገፍ የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት "እስላምና ክርስቲያን በዚህ አገር አኗኗሩ የተጣመረ ነው፡፡ አብረን መብላታችን፣ አብረን መጠጣታችን፣ አብረን መስራታችን፣ በደስታውም በመከራውም፣ በሃዘኑም አብረን እንድንጓዝ ነው!" በማለት በሃዘን ወቅት በአካባቢ ያቸው ያለውን የክርስቲያንና የሙስሊም የእርስ በርስ ግንኙነት እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> አንድ ምሳሌ ልንገርህና በመምህርነት ሙያ አንድ ቦታ አስተምር ነበር፡፡ እዚያ አካባቢ የክርስቲያኖቹ ቁጥር ከ50 አይበልጡም፡፡ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በጣም እሚበዙበት አካባቢ ነው፡፡ እኔም እዚያው አብሬ እኖር ስለነበር፤ ያየሁት በጣም አስገራሚ ነገር አለ፡፡ እዚያ አካባቢ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች በሚሞቱበት ወቅት እስላሞቹ፤ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ገብተው መቃብር ይምሳሉ፡፡ እንደገና ከቤት ሂደው አስከሬኑን ተሸክመው ይዘው ሂደው ይቀብራሉ፡፡ ያነን እኔ አሁን ድረስ ህሊናየ ውስጥ አለ፤ አይጠፋም፡፡ ምን ያክል ነው እንግዲህ ሃይማኖቶቹን አሁን እንደሚወራው ሳይሆን፤ እንዴት መልካም እንደነበረ፡፡ ያነ እሴት ነው አሁን መቀጠል ያለበት[318]፡፡

---

[318] ገዳሙ በላይ፤ ቃለ-መጠየቅ፤ ነሐሴ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ጉባላፍቶ- አማየ ሚሜ፡፡

በዚህ ጥቅስ የቀረበውን ሃቅ ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ የሚያረጋግጡት "እንደውም እኔ እማስታውሰው እዚህ ወልዲያ ሃዳጎ አካባቢ አንድ መ·ሐመድ እሚባል ኃይለኛ ጉልበታም እስላም ነበረ፡፡ እሱ ነበረ የክርስቲያኑን መቃብር እሚቆፍረው፡፡ እና እስከዚህ ተግባብተን ስንኖር ነበር"[319] በማለት የራሳቸውን ምሳሌ ይጠቅሳሉ፡፡ እንድሪስ አህመድ በበኩላቸው በሃዘን ጊዜ ሃይማኖታዊ ከሆነው ሥርዓት ወይም መርህ ውጪ በሃዘን ጊዜ በወሎ በክርስቲያኑና በመ·ስሊመ· መካከል ልዩነት አለመኖሩን የሚገልጹት የሚከተለውን ምሳሌ ማስረጃ በመጥቀስ ነው፡፡

> እኔ በነበርኩበት አካባቢ በአብዛኛው ክርስቲያን ይበዛበታል፡፡ ስለዚህ ቅሬ ውስጥ በአብዛኛው ክርስቲያን ነው እሚበዛው፡፡ መ·ስሊመ· አነስተኛ ቁጥር ነው ያለው፡፡ በዚህ ጊዜ መ·ስሊመ· ሲሞት አስከሬኑን መ·ስሊሞቹ ያጥቡታል፡፡ ከተገነዘ በኋላ እየተራረፉ አስከሬኑን ተሸክመው እሚሄዱት ግን ክርስቲያኖቹና መ·ስሊሞቹ ናቸው፡፡ እዚያ ላይ ሰላት ለመስገድና አስከሬኑን ለማስተኛት ብቻ ነው፤ መ·ስሊሞቹ እሚቀበሉት እንጂ፤ ከዚያ ውጭ አፈር የሚመልሱትና አፈር የሚያቀርቡት በጋራ ነው፡፡ ምንም ልዩነት የለውም፡፡ ልዩነቱ አስከሬኑን ከአልጋ ላይ አንስቶ ወደ መቃብር ቦታ የሚያስገባው መ·ስሊመ· መሆኑ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም የመ·ስሊሙን አስከሬን ያው ክርስቲያን አይነካም፡፡ በተመሳሳይ የክርስቲያኑን አስከሬን መ·ስሊመ· አይነካም፡፡ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ስላለው[320]፡፡ በስተቀረ አስከሬን በመሸከም፣ አፈር በመመለስና ድንጋይ በማቅረብ ክርስቲያን- መ·ስሊም አይባልም፡፡ ከዚህም ሌላ በቤት ውስጥ አብሮ ያስተዛዝናል፡፡ ደሞ አሁን በመ·ስሊመ· ሰደቃ እሚባል አለ፡፡ ሦስት አለ፡፡ ሰባት አለ፡፡ እንደዚያ በሚደረግበት ጊዜ ለክርስቲያኑ ብቻ ይዘጋጃል፡፡ ከተዘጋጀ በኋላ መ·ስሊሞቹ ፀሎት አርገውበት፤ ክርስቲያኑ በልቶ "ነፍስ ይማር!" ብሎ ይሄዳል፡፡ እንጂ እንደዚህ አይነት መ·ስሊም ክርስቲያን እሚባል ነገር የለም[321]፡፡

ግራዝማች ብሩ ይማም ደግሞ የክርስቲያኑና የመ·ስሊመ· የእርስ በርስ ግንኙነት ሥረ-መሰረቱ የእትብት ዝምድና መሆኑን በመጥቀስ በሃዘን ጊዜ ያለውን ሁኔታ የሚገልጹት "በየጁ እስላመ·ም ሆነ ክርስቲያኑ ዘሩ አንድ ነው፡፡ በሃይማኖት ግን ያው የፊለገውን ሃይማኖት ይይዛል፡፡ አሁን የማስረጃ ያህል መርሳ እሚባለው አለ፡፡ የኛ እስልምና መጀመሪያ ሼህ ዑመር የመጡበት አገር

---

319 ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 6 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ -04 ቀበሌ፡፡

320 ከሞት ጋር ተያይዞ በወሎ የሚነገር አንድ ገጠመኝ አለ፡፡ይኸውም አንድ ቄስ እና አንድ ሼህ ወደ አንድ ሩቅ አገር አብረው በመሄድ ላይ እያሉ በድንገት ቄሱ በጠና ይታመማሉ፡፡ ከዚያም ከሞት አፋፍ ላይ ይደርሳሉ፡፡ ቄሱ ሊሞቱ መቃረባቸውን የተረዱት ሼህ፤ "መምሩ እንዴት አድርጌ ገንዘ እንደምቀብረዎት ከመሞተዎ በፊት ያሳዩኝ!" ይሏቸዋል፡፡ ቄሱም፤ "ሼሃችን እርሰዎ እንደሚያውቁት አርገው ገንዘው ይቅበሩኝ!" አሏቸው ይባላል፡፡

321 እንድሪስ አህመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ሚያዚያ 28 ቀን 2006 ዓ.ም.ወልዲያ- 03 ቀበሌ፡፡

ናት ይቺ። ሰው ይሞታል፤ እስላም ክርስቲያኖቹ ጠቅላላውን አብረው ይቀብራሉ። አብረው ያዝናሉ፤ አብረው ያስተዛዝናሉ። ልዩነት የለውም በይህ በኛ»[322]

ከላይ ከቀረቡት ጥቅሶች መረዳት የሚቻው መሰረታዊ ቁም ነገር የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ በሃዘንና በመከራ እንዴት እንደሚገለጽ ነው። በዚህ መሰረት በወሎ ክርስቲያኑ ሲያዝን ሙስሊሙም አብሮ ያዝናል። በተመሳሳይ ሙስሊሙ ሲያዝን ክርስቲያኑ አብሮ ያዝናል። አብሮ ያለቅሳል። የዚህ ሁሉ ምክንያቱ ደግሞ ብዙ ነው። ለምሳሌ ቀደም ሲል እንደተብራራው በወሎ ክርስቲያንና ሙስሊሙ አንዱ ከሌላው ጋር በጋብቻ የተሳሰረ ነው። በዚህም ክርስቲያኑ ለሙስሊሙ፤ ሙሰሊሙ ለክርስቲያኑ ሥጋ ዘመድ ነው።

በዚህ ምክንያት ወሎዬዎች በሥጋ፣በደምና በአጥንት የተዛመዱ ናቸው። በወሎ የጉርብትና ትውፊት የተቆራኙ ናቸው። በወሎ ክርስቲያኑና ሙስሊሙ በአንድ ገበታ አብረው የሚበሉና አብረው የሚጠጡ ናቸው። በወሎ ክርስቲያኑና ሙስሊሙ አብሮ አደግ ናቸው። በሚዜና በባልንጀርነት ትውፊት ተሳስረው በርካታ የሕይወት ትዝታዎችን፣ ገጠመኞችንና የሕይወት ልምዶችን የሚካፈሉ ናቸው። በእርጅና ዘመናቸውም ቢሆን ሙስሊሙና ክርስቲያኑ በአንድ ታላ ተቀምጠው ታሪክ የሚተርኩና ተረት የሚተርቱ ናቸው። በዚህ መሰረት የክርስቲያኑ በሞት መለየት ለሙስሊሙ ሃዘኑ ነው። ብቸኝነቱ ነው። በተመሳሳይ የሙስሊሙ በሞት መለየት ለክርስቲያኑ መከራው ነው። በመሆኑም በወሎ የአንዱ ሠርግ ለሌላውም ሠርጉ ወይም ደስታው እንደሆነ ሁሉ፤ የአንዱ ሃዘን ለሌላውም ሃዘኑ ነው።


ሃዘን በወሎ ከእስልምናው ሃይማኖት መርህ አንፃር ከወንዶቹ በስተቀር፤ ክርስቲያኖቹም ሆኑ ሙስሊሞቹ ሴቶች የሙስሊሙን አስከሬን የተወሰነ እርቀት ድረስ ከመሸኘት ያለፈ መቃብር ቦታ ድረስ ሂደው አይቀብሩም። የሞተው ክርስቲያን ከሆነ ግን የሁለቱም ሃይማኖት እምነት ተከታይ ሴቶች መቃብር ቦታ ድረስ ሂደው ይቀብራሉ፤ የሚያለቅሱትም ያለቅሳሉ።

በሌላ በኩል የሞተው ክርስቲያንም ይሁን ሙስሊም ሁሉም ሴቶች በቤት ውስጥ ሃዘኑን ያስተዛዝናሉ። የቅሬ ወይም የእድር አባላት ከሆኑ ደግሞ የሚደረገውን ነገር ሁሉ እኩል ያደርጋሉ። በተለይ በገጠሩ አካባቢ ክርስቲያንም ሞት ሙስሊም የወሎ ሰው በጥሩንባ የታጀበ ብዛት ያለው ለቀስተኛ አስከትሎ፣ የእዝን እንጀራና ወጥ አስይዞ ፈረስና በቅሎ ምስል አልብሶ

---

[322] ግራዝማች ብሩ ይማም፤ ቃለ-መጠይቅ፣ ሚያዚያ 15 ቀን 2006 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ።

በሚች ለቅሶ ላይ መገኘት የቅርብ ዘመድ ወይም የልብ ወዳጅ መሆኑን የሚገልጽበት የልቅሶ ባህል ነው። ይህም የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ መገለጫ እሴት ነው።



ፎቶግራፍ17፦ በሙስሊም ለቅሶ ጊዜ ወንዶቹ ወደመቃብር ቦታ ሲሄዱ፣ሴቶቹ ሸኝተው ሲመለሱ (ውርጌሳ)።

የዚህ አይነቱ የጋራ እሴት በወሎ ለሠርግ እንደሚከፈለው ብድር ሁሉ ለለቅሶም "አደጌር" በመባል ይታወቃል። የአደጌር ትውፊት በወሎ ብድር መመለስ ወይም ውለታ መክፈል ማለት ነው። የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ከብድር ሁሉ መጥፎ ነገር ወይም ዘመድን ከዘመድ ጎረቤትን ከጎረቤት የሚያቀያይምና የሚያቆራርጥ ወዳጅን ከወዳጅ የሚያራርቅ ምክንያት ቢኖር የልቅሶ አደጌር አለመመለስ ነው። "አደጌሬን በላው! አደጌሬን በላችው!" በወሎ በግለሰቡ ላይ ጥርስ የሚያስነክስ ጉዳይ ነው። በዚህ መሰረት በወሎ ሲሆን፣ ሲሆን አስበልጦ እንጂ፤ አሳንሶ አደጌር መክፈል ነውር ነው። ጭራሹን አደጌር አለመመለስ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው ኢ-ወሎዬነት ነው[323]።

የዚህ ጥናት መረጃ አቀባዮች እንደሚሉት ወሎዬዎች የግል እምነታቸውን እንደያዙ በአንድ ጣሪያ ስርም ሆነ፤ በጉርብትና በጋራ የሚኖሩት በአፀደ ሥጋ እያሉ ብቻ አይደለም። ባንፃሩ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላም በጉርብትና ይኖራሉ። ለዚህ ደግሞ የመቃብር ቦታቸው ተጠቃሽ ምሳሌ ነው። ተስፋው መርሻ የቂሌ ሃዳሜ ነዋሪዎችን የእርስ በርስ ፍቅርና መዋደድ የሚገልፁት በአፀደ ሥጋ ያሉትን ምሳሌ በመጥቀስ ብቻ አይደለም። የለሉትንም ምሳሌ በመጥቀስ ነው። ለዚህም፤ "...እዚያ አካባቢ ያለው ሁኔታ ኮ ይሄ ቤተክርስቲያን ሆኖ፤ እንደው

323 ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።

ሃምሳ ሚትር አይሆንም ልዩነቱ የመስሊሞቹ የመቃብር ቦታ በአጥር ብቻ ነው፤ ከለል ብሎያለው፡፡ ያነኛው የመስሊሞቹ የቀብር ቦታ ነው፤ ይኸኛው የክርስቲያኖቹ የቀብር ቦታ ነው[324]፡፡" በማለት የመቃብር ቦታቸው ሳይቀር የሃይማኖት መቻቻል እሴት ተምሳሌት መሆኑን ማስረጃ ይጠቅሳሉ፡፡ እንደመረጃ አቀባዩ ገለፃ ይህ ቦታ ለዓለም ሁሉ ስለ ሃይማኖት መቻቻል እሴት ማስተማሪያ ቦታ መሆን ነበረበት የሚል እምነት አላቸው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው በወሎ የክርስቲያንና የመስሊም የመቃብር ቦታ ወይ በመንገድ ይለያያል፤ ወይ ደግሞ በአጥር ይለያል፡፡ ለምሳሌ የዚህ ጥናት አቅራቢ በትክክል የሚያውቀው ኪቢ ቃሎ ሚካኤል (ወልዲያ ሚካኤል) እና እዚያው ስር ከመንገድ በታች ያለው የመስሊሞች የመቃብር ቦታ ነው፡፡ ይህም ማለት ሚካኤልና የመስሊሞቹ የመቃብር ቦታ የሚለየው በመንገድ ብቻ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከመንገድ በላይ የሚካኤል ግቢ እና የክርስቲያኖቹ መቃብር ቦታ አለ፡፡ ከመንገድ በታች ደግሞ የመስሊሞቹ የመቃብር ቦታ አለ፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በወሎ እናት ወይም አባት መስሊም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ባንፃሩ እናት ወይም አባት ክርስቲያን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ልጅ፣ አክስትና አጎት ደግሞ ከሁለት አንዱን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ሲያልፍ ባል ክርስቲያን ሚስት ደግሞ መስሊም፤ ወይም ሚስት ክርስቲያን ባል መስሊም ሆነው በአንድ ቤት ውስጥ በሰላምና በፍቅር ሊኖሩ እንደሚችሉ አይተናል፡፡ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ደግሞ ብዙ ሳይራራቁ በመንገድ ወይም በአጥር ብቻ ተለያይተው አጽማቸው ጎን ለጎን ያርፋል፡፡ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ የተቀበሩበት አጋጣሚም ብዙ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በወሎ ድርቅ ወቅት የተከሰተው ሁኔታ ለአብነት የሚጠቀስ ማስረጃ ነው፡፡

በሀዘንና በመከራ ወሎዬዎች እርስ በርስ የሚገናኙባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው፡፡ በሙስሊሙ የሰደቃ ትውፊት፣ በክርስትናው ሳልስት፣ ሰባት፣ አስራ ሁለት፣ አርባ፣ ሰማኒያ፣ ሙት አመት ወይም ተዝካር...ወዘተ እሚባሉት ከቀብር በኋላ ያሉ የሃዘን ሥርዓቶች የሚጠቀሱ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በነዚህ ትውፊቶች አማካይነት ወሎዬዎች እርስ በርስ ይገናኛሉ፤ ይረዳዳሉ፤ ይደጋገፋሉ፤ ይተዛዘናሉ፤ ይተሳሰባሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሁሉ ማኅበራዊና ባህላዊ ክዋኔዎች ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችሏቸው የጋራ እሴቶች ናቸው፡፡

---

[324] ተስፋው መርሻ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ፡፡

በወሎ ሃዘንና መከራ የሚገለፀው ሰው በሞት ሲለይ ብቻ አይደለም። ባንፃሩ ሃዘንና መከራ በመለያየት ይገለፃል። ለምሳሌ እሚወደው ቤተሰቡ፤ ዘመዱ ወይም ጎረቤቱ አሊያም አብሮ አደጉ በተለያዩ ምክንያቶች ከቀዬው ሲለይ ወይም ከጀማው ሲነጠል ሃዘንና መከራው ለሚለየውም አካል ብቻ ሳይሆን ለቀሪውም ጭምር ነው። ከዚህ አንፃር ወሎዬዎች በርካታ ሃዘንና መከራ በጋራ ተቀብለዋል። ለዚህ አባባል በ1965 ዓ.ም. እና በ1977 ዓ.ም. በወሎና በአካባቢው የተከሰተው ድርቅ ለአብነት የሚጠቀስ ማስረጃ ነው። በነዚህ የድርቅ ዘመናት ምክንያት በወሎ ባል ከሚስቱ፣ ሚስት ከበሏ፣ እናት ከልጇ፣ ለጅ ከናቱ፣ አባት ከልጁ፣ ልጅ ከአባቱ፣ ወይም ቤተሰብ ከቤተሰብ ተለያይተዋል። በነዚህ የድርቅ ዘመናት ምክንያት በወሎ ጎረቤት ከጎረቤት፣ ወዳጅ ከዘመድ፣ እንዲሁም ከወሎ አድባር ጋር ሳይቀር የወሎ ሰው ተለያይቷል። በወቅቱ ወሎዬዎች የሚችሉትን ያህል እርስ በርስ ተረዳድተውና ተደጋግፈው፤ በመጨረሻ ሃዘንና መከራውን እኩል ተቀብለዋል። ይህም የወሎዬዎች የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ ክስተት ሆኖ አልፏል።

ከዚህም ሌላ በወሎ በፖለቲካ ሊሂቃኑ አማካይነት በሙስሊሞቹ ላይ የደረሰውን መከራና እንግልት ክርስቲያኖቹ ከሙስሊሞቹ ጎን በመቆም በጋራ አሳልፈዋል። ለምሳሌ ከቦሩ ሜዳ የሃይማኖት ጉባዔ በኋላ የተፈጠረውን ችግር በጋራ ለማሳለፍ የተለያዩ ብልሃቶችን ቀይሰዋል። ለዚህም ሙስሊሞቹ "ቀን፣ ቀን ክርስቲያን፤ ሌሊት፣ ሌሊት ደግሞ ሙስሊም" (Hussien 2001: 147) እየሆኑ ችግሩን ሲያሳልፉ፤ ክርስቲያኖቹ ከጎናቸው ነበሩ። በዚህ ታሪካዊ ክስተት ወቅት ሙስሊሞቹ ከክርስቲያኖቹ ጋር በመሆን፤ ሙስሊሞቹ ሲሞቱ ቀን፣ ቀን አስከሬናቸውን ቤተ-ክርስቲ የተቀበረ በማስመሰል ሌሊት፣ ሌሊት ግን እውነተኛውን አስከሬን የእስልምናው መርህ በሚፈቅደው መሰረት በሙስሊሞቹ የመቃብር ቦታ እየወሰዱ ይቀብሩ ነበር። ከዚህ ክስተት ጋር በተገናኘ ውዱ ጣፈጠ የሚከተለውን ገጠመኝ ጽፈዋል።

> አንዳንዶቹ ክርስቲያን ሆነው ከክርስቲያን መንግሥቱ ጋር ተመሳስለው ከኖሩ በኋላ በሞት አፋፍ ላይ ሲደርሱ "በልባችን ሙስሊም ነበርን በሙስሊም መቃብር በእስልምና ሕግ መሰረት ቅበሩን" ብለው የተናገሩ፣ የተናዘዙና በቃላቸውና በኑዛዜያቸው መሰረት ቀበራቸው የተፈፀመላቸው አሉ። ለምሳሌ ደጃች መንገሻ አቦየ የተባሉ ታዋቂ የቃሎ አርበኛ እና ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በጥሩ የሥራ ግንኙነት የአካባቢው ገዥ ሆነው የኖሩ ነበሩ። ክርስቲያን ሆነው የኖሩ። ፍፃሜ እድሜያቸው በደረሰ ጊዜ "በልቤ ሙሰሊም ነበርኩ" በማለት ልጆቻቸውን በታዋቂው የጀማ ንጉሥ የሃይማኖት ቦታ እንድትቀብሩኝ ብለው ለቤተሰቦቻቸው አደራ ሰጡ። በቀብራቸው ቀን አልጋ ወራሽ በመጡ ጊዜ ለቤተሰቦቻቸው ጭንቅ ሆነ። መቼም መላ አይጠፋምና የእንጨት እርብራብ ተሰርቶ አልጋ ወራሽ በተገኙበት ደሴ መድኃኔዓለም ተቀበሩ። እሬሳቸው ግን በምስጢር በሌሊት ጀማ ንጉሥ እንዲቀበር ተደረገ (ውዱ 2004 ዓ.ም.፤ 213)።

በዚህ አይነቱ የመከራና የጭንቅ ጊዜ ሁሉ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጎን በመሆን ከላይ የተጠቀሰው አይነት ብልሃት አብሮ ፈጥሯል። በተግባርም ከሙስሊሞቹ ጋር አብሮ ተሳትፏል። በዚህ የመከራና የሃዘን ወቅት ከሙስሊም ጎረቤቶቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ጎን የቆሙት የአካባቢው ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ፤ የክርስትናው ሊቅ የሚባሉት መምህር አካለወልድ እና ቤተ-ክርስቲያኗ እራሷ ጭምር ከወሎ ሙስሊሞች ጎን ቁመው እንደነበር ጥናቶች ይጠቁማሉ[325]።

ለምሳሌ መምህር አካለወልድ ክርስቲያኖቹ ከሙስሊም ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጎን እንዲቆሙ ይሰብኩ ነበር። እንዲሁም ሙስሊሞቹ ክርስቲያን የባረከውን ሥጋ እንዲበሉ ሲገደዱ፤ ሙስሊሞቹ መጀመሪያ በሬውን እንዲባረኩ ካስደረጉ በኋላ ግማሹን ሥጋ እሳቸው ባርከው ለክርስቲያኖቹ ይሰጡ ነበር። በምስጢርም ክርስቲን የባረከው በማስመሰል የራሳቸውን ፀሎት እያደረሱ እርድ እንዲያከናውኑ ያበረታቱ ነበር። ከዚህም ሌላ ክርስቲኖቹ ሙስሊሞቹን በተለያየ መንገድ በመርዳት የፖለቲካ ሊሂቃኑ የፈጠሩትን ችግር በጋራ ማሳለፍ እንደሚገባ ጀግውን ያስተምሩ ነበር። የሚከተለውን ምሳሌ ለአብነት እንመልከት።

> መምህር አካለወልድ ብለዋቸው ግብጥ ነው ትምርተዎ ይላሉ። ደግ ሰው ነበሩ ይላሉ። እናንተ የሐዋኒስ [የዮሐንስ] አልጋ እኮ ነገ ለቃቂ ነው። እስላሞቹን ትልልቆቹን ምሁሮቹን እስላሞች ህዳችሁ አይታችሁ አታውቁም? የሰላም አገር ንጉሥ ህዳችሁ አይታችሁ አታውቁም? አስላሞቹን ቲበጠብጧቸው እየቤታችሁ አርጋችሁ አትይዟቸውም? ደህና ሰው ነበሩ ይላሉ። እያረዳችሁ ብሉ ቲባል ተስላም እረዱ ይላሉ አሉ። ተስላም እያረዱ ምን ቲሉ ምን ቲሉ አሉ (Rukya 2013 214-215)::

በሌላ በኩል የእርጥባን ትውፊት በወሎ፤ ወሎዬዎች በሃዘንና መከራ ወቅት እርስበርስ የሚረዳዱበትና የሚደጋገፉበት ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ጋር የተያያዘ የጋራ እሴት ነው። እርጥባን በወሎ ሰው በተለያየ ምክንያት ሃብትና ንብረቱን ያጣል ወይም ያልታሰበ አደጋ ይገጥመዋል። በዚህ ወቅት ወሎዬዎች ግለሰቡን መልሰው የሚያቋቁሙበት ባህል ነው።

---

[325] Memr Akalwold used to advise the people to live peacefully with the Muslims because the government of the King will not last forever but the people will live together even after the downfall of the King. He was very wise to advise the Muslims also to slaughter in the name of Allah in Muslims' way which will be reported as if they had slaughtered it in the name of God in the manner of Christians. He also advise the people to embrace their Muslim brothers & sisters to be with them at such bad times. Anothe informant stated that to show that the people belong to each othe, Memr Akalwold asked to divide the same ox between the Muslims & Christians. The Muslims slaughtered the ox first. Half of it was given to Christians who then cut it again in the name of their God. Others state that the Muslims used to hide in churches while the government forced them to be converted to Christianity (Rukya 2013: 216).

የዚህ አይነቱ ትውፊት የእርጥባን ትውፊት በመባል ይታወቃል። ትውፊቱ በሃዘንና በመከራ ጊዜ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ትውፊት ነው። የመተዛዘንና የመተሳሰብ እሴት ነው። ነገ በእኔም ይደርሳል ብሎ አርቆ የማሰብና የማስተዋል ጥበብ ነው።

በዚህ መሰረት የእርጥባን ትውፊት በወሎ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም የጋራ እሴት ነው። ለምሳሌ ሙስሊሙ በቁጥር ትንሽ ሆኖ ክርስቲያኑ በበዛበት አካባቢ የሙስሊሙን በሬ ወይም ሌላ ከብት አንድ እክል ቢገጥመው በሬውን ባርኮ ሥጋውን በቅርጫ መልክ የሚከፋፈለው ክርስቲያኑ ነው። ይህንንም የሚያደርገው በወሰደው የቅርጫ መጠን ልክ ገንዘብ አዋጥቶ ሙስሊሙ ሌላ ከብት እንዲገዛ ለማድረግ ነው። ይህም ማለት ሙስሊሙን ክርስቲያኑ መልሶ ለማቋቋም ነው። በተመሳሳይ የክርስቲያኑ ቁጥር ትንሽ ሆኖ ሙስሊሙ በበዛበት አካባቢ ባህሉ ተመሳሳይ ነው። ከዚህም ሌላ የክርስቲያኑ ወይም የሙስሊሙ ቤት ተቃጥሎ ሃብትና ንብረቱ ቢወድም ክርስቲያኑም ሙስሊሙም በጋራ ተባብሮ ተጎጂውን መልሶ ያቋቁማል፤ ቤቱን ይሰራል፣ ሃብትና ንብረቱን በተቻለ መጠን እንዲመለስ ያደርጋል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተብራሩት ዋና ዋና ነጥቦች ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው የሚኖሩባቸው የጋራ እሴቶች አንዳንዶቹ ከእትብት ዝምድና ጋር ይያያዛሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ከአብሮ አደግነትና ከባልንጀርነት ጋር ይገናኛሉ። የወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ግን የሁሉም ነገር ሥረ-መሰረት ነው። በወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ላይ የተመሰረተው የወሎዬዎች ማኅበራዊ መስተጋብር ደግሞ እስካሁን እንደተብራራው ከማኅበራዊና ባህላዊ የአኗኗር ዘይቤያቸው፣ ደንብና ሥርዓታቸው፣ ባህል፣ ወግና ልማዳቸው ጋር የተቆራኘ ነው። ይህም ከወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ጋር ይተሳሰራል። ምክንያቱም የወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተለያዩ አብነቶችን በመጥቀስ እንደተብራራው ጎራ ለይቶ ሳይሆን ተሰባጥሮ ነው። ጎራ ለይቶ ሳይሆን ተደባልቆ፣ ተቀላቅሎ፣ ተዋህዶ ነው።

ስብጥሩ ወይም ውህደቱ ደግሞ በሰዎቹ ብቻ ሳይሆን በከብቱ፣ በመሬቱ በወንዙ፣ በምንጩ፣ በአድባሩ፣ በአውጋሩ፣ በዛሩ፣ በመቃብር ቦታው...ወዘተ ጭምር ነው። ይህ ሁሉ እሴት ደግሞ በአንድ የወሎዬዎች የጋራ ማኅበራዊ ተቋም ተጠቃሎ ይታሰራል። ይህ የማሰሪያ ገመድ ወይም ክር በወሎ በከተማው እድር፤ በገጠሩ ቅሬ ይባላል። እነዚህ ሁለት ማኅበራዊ ተቋማት የተለያየ ስያሜ ይኑራቸው እንጂ፤ ዓላማቸውና ፋይዳቸው አንድ ነው። ይኸውም ወሎዬዎችን እርስ በርስ በማገናኘትና በማስተሳሰር በሰላምና በፍቅር አብረው እንዲኖሩ ማስቻል ነው።

አብረው እንዲበሉና አብረው እንዲጠጡ፣ አብረው እንዲደሰቱና አብረው እንዲያዝኑ፣ በስራና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ሁሉ አብረው እንዲረዳዱና እንዲደጋገፉ ማስቻል ነው።

6.1.5፦ጉርብትና በቅሬ (እድር)

ከላይ እንደተገለጸው በወሎ በገጠሩ አካባቢ ቅሬ ማለት በከተሞች አካባቢ እድር እየተባለ ከሚጠራው ማኅበራዊ ተቋም ጋር ተመሳሳይ ስያሜና ዓላማ አለው። ቅሬ እንደ እድር ሁሉ ከሃዘንና መከራ ጋር ይገናኛል። የገጠሩ ቅሬ ከከተማው እድር የሚለየው ቅሬው ከቀብር መልስ እንጀራና ወጥ የሚያመጣው ከየቤቱ መሆኑ ነው። ከለቅሶ ባሻገር ቅሬም ሆነ እድር ሌሎች የተለያዩ ማኅበራዊ ፋይዳዎች፣ ደንብና ሥርዓቶች አሉት። ለምሳሌ አቅም በፈቀደ መጠን በሃዘን ጊዜ ከቅሬ እንደማይቀር ሁሉ፤ በደስታ ወይም በሠርግ ወቅትም ቅሬ አይለይም። በሁለቱ አካላት መካከል ፀብ ወይም ቁርሾ ቢኖር እንኳን እርቅ ወርዶ የሃዘንም ሆነ የደስታ ተካፋይ እንዲሆኑ ይደረጋል። በተለይ በሃዘን ወቅት ያኮረፈው አካል እንዳኮረፈ ቢሆንም እንኳን በፀበኛው ሰው ሃዘን ላይ ይገኛል። በተመሳሳይ በሠርግ ወቅት ሠርጉን የሚያወጣው አካል ፀበኛው ተለይቶ እንዳይውል እርቅ እንዲወርድ እራሱ ግፊት ያደርጋል። የተበደለም እንኳን ቢሆን "ይቅር ለፈጣሪ!" ብሎ ፀበኛው የደስታው ተካፋይ እንዲሆን ያደርጋል። ይህ ካልሆነ ግን እስከመጨረሻው መቆራረጥ ይመጣል።

በወሎ ጎረቤት በሃዘንና በደስታ አንዱ ከሌላው ከተለየ እርስ በርስ የሚገናኙበት ድልድይ መፍረሱን፣ የሚተሳሰሩበት ክር መበጠሱን ያመለክታል። ምክንያቱም በወሎ መተሳሰሪያ ክሩ፣ መገናኛ ድልድዩ አንዱ ጎረቤት ከሌላው ጎረቤት ጋር ሲደሰት መደሰቱ፣ ሲያዝን ማዘኑ፤ ሲሰራ አብሮ መስራቱ፣ ሲቸገር መረዳዳቱ፣ ሲበሉ አብሮ መብላቱ፣ ሲጠጡ አብሮ መጠጣቱ...ወዘተ ነው። የዚህ ሁሉ ምንጩ ደግሞ የወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት ነው። የወሎዬዎች የጉርብትና ትውፊት በቅሬ ደንብና ሥርዓት ይጠበቃል። በዚህም የወሎዬዎች የጉርብትና ትስስር ተጠብቆ፤ "ከሩቅ ዘመዴ የቅርብ ጎረቤቴ!" ይሉት ብሂል ትውፊቱ ከትውልድ- ትውልድ ይሸጋገራል።

በዚህ መሰረት የቅሬ ወይም የዕድር ባህል በወሎ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ቅሬ ወይም እድር የሚመሰረተው በተለይ በገጠሩ አካባቢ የተወሰኑ ሰዎች ተመራርጠው ወይም ክርስቲያንና ሙስሊም ብለው ሳይሆን፤ በጉርብትና የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ሁሉ በጋራ ያጠቃልላል። ከዚህ ውጭ ከቅሬ ተለይቶ የሚወጣ ግለሰብ "እምበዳዴ!" የተባለ የዚያ

ማኅበረሰብ አካል ብቻ ነው። እምበዳዴ ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ከጀማው መለየት ማለት ነው።

ቅሬ ወይም እድር በወሎ የክርስቲያኑና የሙስሊሙ የጋራ ማኅበራዊ ተቋም ነው። በዚህ መሰረት በወሎ በተለይ በገጠሩ አካባቢ ክርስቲያኑ ለብቻው ቅሬ ወይም እድር የለውም። ሙስሊሙም ለብቻው ቅሬ ወይም እድር የለውም። ባንፃሩ ሁለቱም በአንድ ቅሬ ውስጥ ይሳተፋሉ። ምክንያቱም ከላይ እንደተጠቀሰው የወሎዬዎች የአኗኗር ዘይቤ ሃይማኖትን መሰረት አድርጎ ጎራ ለይቶ ሳይሆን በጉርብትና ተሰባጥሮ ስለሆነ ቅሬ ለመመስረት አይመራረጡም። የቅሬ መስፈርቱ በወሎ በአንድ አካባቢ መኖራቸው ብቻ ነው። ይህንን አባባል የአካባቢው ነዋሪዎች የሚያረጋግጡት ውርጌሳ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ዘጠኝ ቅሬዎችን (እድሮችን) ምሳሌ በመጥቀስ ነው። የሚከተለው ጥቅስ ለዚህ አባባል ማረጋገጫ አብነት ነው።

> በአካባቢያችን ባለሁበት ዘመን እዚህ እድሜ እስከምደርስበት ዘመን ድረስ በዚህ ባለሁበት ቦታ ላይ ከጥንት ጀምሮ ያው በአንድ በቅሬ ተዋህደን እምንኖር ነን። ባካባቢያችን ቅሬ በሃይማኖት ልዩነት የለም። ያው ሙስሊሙም ክርስቲያኑም አንድ ሥጋ ቤተሰብ ስለሆነ ተጣምሮ፣ በአንድ ላይ በልቶ፣ በአንድ ላይ ሰርቶ፣ በአንድ ላይ ተገዳድፎ ነው እሚኖረው። በዚያውም አሁን በዚች በከተማችን ውስጥ ዘጠኝ ቅሬዎች አሉ። ዘጠኙም ቅሬዎች በአንድ ነው። አሁንም የሃይማኖት ልዩነት የለም። በዚያውም ደካሞችን እየረዳን፣ የታረዘውን እያለበስን፣ የተራበውን እያጎረስን ነው እምንኖረው በአካባቢያችን[326]።

ቅሬ በወሎ በውርጌሳ ከተማ የተጠቀሰውን አብነት ይመስላል። ሙስሊሙና ክርስቲያኑ በአንድ ቅሬ ውስጥ ሲሰባሰብ የቅሬው ዳኛ ሙስሊሙ ሊሆን ይችላል። በቅሬው የአሰራር መርህ መሰረት ክርስቲያኑ ጥፋት ካጠፋ ሙስሊሙ የቅሬ ዳኛ ሊቀጣው ይችላል። ክርስቲያኑም የቅሬ ዳኛ ሊሆን ይችላል። ሙስሊሙ ካጠፋ ባሰራሩ መሰረት ሊቀጣው ይችላል። የክርስቲያንና የሙስሊም ትስስር በወሎ በዚህ ሁሉ ክር የተያያዘ ነው። ክርስቲያንና ሙስሊም በወሎ በጋብቻ ይተሳሰራል። በሚዜ ይተሳሰራል። በአበልጅ ይተሳሰራል። በቅሬ ይተሳሰራል። እነዚህ ሁሉ እሴቶች ደግሞ በወሎ የሃይማኖት መቻቻል እሴት መገለጫ አብነቶች ናቸው።

ባጠቃላይ የቅሬ ትውፊት በወሎ መሰረቱ፣ የወሎዬዎች የተጣመረ የአኗኗር ብሂል ነው። የጉርብትና ዘይቤያቸው ነው። የማኅበራዊ መስተጋብር ሁኔታቸው ነው። በነዚህ ሁሉ የጋራ እሴቶች ወሎዬዎች አብረው ይሰራሉ፤ ይተጋገዘዛሉ፤ ይረዳዳሉ፤ አብረው ይበላሉ፤ አብረው ይጠጣሉ፤ ሃዘንም ሆነ መከራ አብረው ይካፍላሉ። ማኅበራዊ ችግሮች ሲገጥማቸውም አንዱ

---

[326] መሪጌታ ቀለሙ ዳኛው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ውርጌሳ- 01 ቀበሌ።

ሌላውን በመርዳትና በመደገፍ ተዛዝነውና ተሳስበው በፍቅርና በሰላም በጋራ ይኖራሉ፡፡ የሚከተለውን ምሳሌ ለአብነት እንመልከት

> አሁን እኔ ወላጅ እናቴ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት እምነት ተከታይ ናት፡፡ ወንድሜ በቅርብ ጊዜ ሞተ፡፡ ድንኳኑን የተከለው ክርስቲያኑ ነው፡፡ መስሊመማ ሮመዳን ፆም ላይ ነበር፡፡ እኔም ፆም ላይ ነበርኩ ፡፡ እኔ አፉ ብያለሁ ድንኳን እንዳይተክልብኝ አልኩኝ ለምን? ፆም ነው እሚበላው የለም አልኩ፡፡ እነሱ ግን " እናትሽ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እምነት ተከታይ ስለሆኑ ድንኳኑን ተክለን ነቅለን እንሂዳለን፤ እኛ ችግር የለም እራት በልተን!" አሉ፡፡ እናቴን ለማክበር ማለት ነው፡፡ እሺ አልኩኝ፡፡ እኔም ሃዘን ተቀመጥኩ፡፡ ከገጠር ያለ ዘመድ አዝማድ እንዲመጣ አደረኩ፡፡ ክርስቲያኑ በጣም ከልክ በላይ፣ ከሚገባው በላይ ነው ያስተዛዘነኝ፡፡ የወንድሜን ሃዘን እንድረሳ አድርገውኛል፡፡ እኔ ይሽነን ምንም መርሻ የለኝም፤ እስከመጨረሻው፡፡ እና ሃይማኖት ምንም የሚገድበን ነገር በፍጹም የለም[327]፡፡

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ከተጠቀሱት የጋራ እሴቶች አንዣር የክርስቲያኑን እሴት መስሊመ፤ የመስሊሙን እሴት ክርስቲያኑ፤ ከማክበር ወይም አብሮ ለመኖር የማይከለክለው መሆኑን አምኖ ከመቀበል ባለፈ አንዱ የሌላውን እሴት ይጋራል፤ ይጠቀማል፡፡ በመሆኑም ወለዮዎች እርስ በርስ የሚገናኙባቸው፣ የሚተሳሰሩባቸው፣ የሚግባቡባቸው፣ የሚተሳሰቡባቸው፣ የሚተዛዘኑ ባቸው፣ የሚረዳዱባቸው፣ የሚደጋገፉባቸው፣ የሚከባበሩባቸው፣ የሚደሰቱባቸውና የሚያዝኑ ባቸው...ወዘተ የጋራ እሴቶች በርካታ ናቸው፡፡

በዚህ መሰረት መስሊመ ከክርስቲያኑ፤ ክርስቲያኑ ከመስሊመ ጋር አብሮ ከሰራ፣ አብሮ ከበላና አብሮ ከጠጣ፣ ችግሩን፣ ሃዘንና ደስታውን በጋራ ከተካፈለ፣ ከተሳሰበና ከተዛዘነ፣ ከተረዳዳና ከተባበረ፤ ባጠቃላይ አንተ ትብስ፣ አንች ትብሽ እየተባባለ በሰላምና በፍቅር አብሮ መኖር ከቻለ ክርስቲያንና መስሊም በወለዮ፤ "አንድ አካል አንድ አምሳል" ወይም ክርስቲያንና መስሊም በወለዮ፤ "ጥርስና ከናፍር ናቸው!" የሚለው ተምሳሌታዊ አገላለጽ በዚህ ምእራፍ ውስጥ በቀረቡት የጋራ እሴቶች አብነት በትክክል ወለዮዎችን ይገልፃል፡፡ እነዚህ የጋራ እሴቶች ድሞ ወለዮዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችሏቸው የጋራ ሃብቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለዮ የሚገለፀው በዚህ አይነቱ የወለዮዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ዘይቤ ወይም የጋራ እሴቶች አማካይነት ነው፡፡ የእሴቶቹም ፋይዳ የወለዬዎች የመገናኛ ድልድይ እና የእርስ በርስ መተሳሰሪያ ክር ሆኖ ማገልገል ነው፡፡

---

[327] ድርቤ ካሳው፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ግንቦት 12 ቀን 2006 ዓ.ም ወልዲያ-05 ቀበሌ፡፡

6.2፦ የሃይማኖት መቻቻል እሴት እና የዘመኑ መንፈስ በወሎ

ከዚህ በላይ በቀረቡት ምዕራፎች ውስጥ በተጠቀሱት የተለያዩ አብነቶች መሰረት በወሎ ክርስቲያኖቹ ከሙስሊሞቹ፤ ሙስሊሞቹ ከክርስቲያኖቹ ጋር በማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነታቸው አንድ ሆነው፣ ተዛዝነውና ተሳስበው፣ ተደጋግፈውና ተረዳድተው፣ ተከባብረውና በተለያዩ የማኅበራዊ መስተጋብር ክሮች እርስ በርስ ተሳስረው በሰላምና በፍቅር አብረው እንዲኖሩ የሚያስችሏቸው በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው።

እነዚህ የጋራ እሴቶች የተገነቡት፣ የዳበሩትና የጎለበቱት ደግሞ ወሎዬዎች የግል እምነቶቻቸውን ጠብቀው፤ የሌሎችንም አክብረው፤ በማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነታቸው ግን "ጥርስና ከናፍር" ወይም "አንድ አካል አንድ አምሳል" የሆነ የአኗኗር ዘይቤ ስለሚከተሉ ነው። በዚህም በወሎ የክርስቲያንና የሙስሊም የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ብሂል የሰምና የፈትል ያህል የተዋደደና የሰመረ ነው። ከዚህ አንፃር ወሎዬዎች የእኔ የራሴ የሚሉት የጋራ እሴት ወይም የማኅበራዊ ኑሮ ደንብና ሥርዓት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ባለቤቶች ናቸው። ለምሳሌ በሰላምና በፍቅር አብሮ መኖር፣ አብሮ መስራት፣ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት፣ አብሮ ማዘንና አብሮ መደሰት፣ መደጋገፍና መረዳዳት፣ ቤተ-እምነት ሳይቀር አብሮ በጋራ መስራት...ወዘተ የወሎየዎች የጋራ መገለጫ እሴቶች ናቸው።

በተመሳሳይ የሃይማኖቶቹ ትውፊቶችም ቢሆኑ በዚሁ አውድ መሰረት የተቃኙ ናቸው። ይህም ማለት በወሎ በእስልምናው በኩል ያሉት ተውፊቶችና የወሎ ደጋጎች በረካ ለሙስሊሞቹም ለክርስቲያኖቹም የጋራ እሴቶች ናቸው። የዚያኑ ያህል የክርስትናው ትውፊቶችም ሆኑ፤ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው የእግዚአብሔር ወዳጆች ለክርስቲኑም ለሙስሊሙም ተመሳሳይ ሚና አላቸው። የደብተራዎች፣ የቃልኞችና የጠንቋዮች ተውፊቶችም ቢሆኑ ከወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ጋር የተቆራኙ ጉዳዮች ናቸው። በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ የሚመነጨው፣ የሚገለፀውና ፋይዳውም ተለይቶ የሚታወቀው በነዚህ እሴቶች አማካይነት ነው። በመሆኑም በዚህ ጥናት መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት ማለት በወሎ፤ የሙስሊም ክርስቲያኑ የእርስ በርስ ትስስር፣ መረዳዳትና መደጋገፍ፣ መተዛዘንና መተሳሰብ፣ አብሮ መስራት፣ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት፣ አብሮ ማዘንና አብሮ መደሰት፣ ባጠቃላይ በሰላምና በፍቅር አብሮ መኖር ማለት ነው።

ከዚህ አንፃር ለዘመናት የነበረው የወሎዬዎች የሃይማኖት መቻቻል እሴት ወይም አብሮነት በዚህ አይነቱ የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ ዘይቤ አማካይነት የሚገለጽ ነው። ይህ ማለት ግን አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር እሴቱ እንዳለና እንደነበረ ቀጥሏል ማለት አይደለም። በተመሳሳይ ለወደፊትም ቢሆን ሳይለወጥና ሳይቀየር እንዳለና እንደነበረ ሊቀጥል ይችላል፤ ተብሎ አይታሰብም። ባንፃሩ እሴቱ ከዘመኑ መንፈስ ጋር አብሮ እየተለወጠ፣ በሌላ እየተተካና እየተቀየረ ሊሄድ ይችላል።

ለምሳሌ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው መጠሪያ ሥም በወሎ የክርስቲያን ወይም የሙስሊም መለያ አልነበረም። በተለይ ዓለማዊ የሆነው መጠሪያ ሥም የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ መገለጫ እሴት ነው። ከዚህ አንፃር ዓለም፣ ዓለሚቱ፣ ትርንጎ፣ የሽ፣ የሻረግ፣ ከበደ፣ አበበ፣ ደምሴ፣ ዓለሙ...ወዘተ የሚሉት መጠሪያ ሥሞች የሙስሊሙም የክርስቲያኑም የጋራ መጠሪያዎች ናቸው። ከዚህም ሌላ ከሃይማኖቶቹ ጋር የተያያዙ መጠሪያ ሥሞችን መነሻ በማድረግም ቢሆን ወሎ ውስጥ እከሌ ሙስሊም ነው፤ እከሌ ክርስቲያን ነው ለማለት አስቸጋሪ የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ለምሳሌ ጀማል፣ አብዱ፣ ሁሴን፣ ዓሊ...ወዘተ በሚሉት ከእስልምናው ጋር የተያያዙ መጠሪያ ስሞች ሳይቀሩ ክርስቲያኑ ይጠራባቸዋል። በሙስሊሙም በኩል ገብሬ ሁሴን፣ ኃ/ማርያም ዓሊ፣ ዮሐንስ ሞሐመድ...ወዘተ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። አሁን ግን ለውጦች እየታዩ ነው። በእስልምናው በኩል ያለውን ሁኔታ ሩቅያ ሐሰን የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ሁኔታ አብነት በመጥቀስ እንደሚከተለው በጥናታቸው ውስጥ ጽፈዋል።

ተመራማሪዋ እንደፃፉት ከመጠሪያ ሥም አንፃር ወንድ አያታቸው "ሽበሽ" ይባላሉ። ወላጅ አባታቸው ደግሞ "አረጋ" የሚል መጠሪያ ሥም ነበራቸው። በተመሳሳይ ሁለቱ ታላላቅ እህቶቻቸው ዓለምነሽና እማዋይሽ ይባላሉ። የእሳቸው መጠሪያ ሥም ግን ሩቅያ ነው። አሁን ግን የወላጅ አባታቸው መጠሪያ ሥም "ሐሰን" በሚል ተቀይሯል። በተመሳሳይ እህታቸው ዓለምነሽ "መሬማ" ተብለዋል። እማዋይሽ ግን ከሃይማኖት አንፃር ክርስቲያን በመሆናቸው መጠሪያ ሥማቸውን አልቀየሩም (Rukya 2013: 196)።

ለውጥ በፎክሎር የተለያዩ ምክንያቶች አሉት። ሂደቱም ተፈጥሯዊ ነው። መሰረታዊው ቁምነገር ግን በለውጡ ምክንያት የሚመጣው ውጤት አወንታዊ ወይም አሉታዊ ክስተት ከመሆኑ ላይ ነው። ከዚህ አንፃር የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት በወሎ ለሃይማኖት መቻቻል እሴት መሰረት በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚታዩት ለውጦች ከአወንታዊ

ጎናቸው ይልቅ አሉታዊ ገጽታቸው ያመዝናል። በዚህም ወሎዬዎች እርስ በርስ የተሳሰሩባቸው ክሮች እየላሉ፣ በጋራ የሚገናኙባቸው አጋጣሚዎች እየጠበቡ በመሄድ ላይ ናቸው። ያሲን ፍሬው በአካባቢያቸው የሚታየውን ለውጥ የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> ዱሮ የነበረው የሃይማኖት መቻቻል እሴት በጣም ጥሩ ነበር። የመረዳዳቱም፣ የመተጋገዙም፣ የመተባበሩም፣ የመተዛዘኑም ሁኔታ ዱሮ የተሻለ ነበር። አሁን-አሁን ግን ከዱሮው ጋር ስናነፃጽረው ዱሮ ከምንሰማውና አሁን ከምናየው አንፃር ትንሽ የተፈራቀቀና ከባህሉ እየወጣ የሚሄድበት አጋጣሚ አለ። ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች አሉት። አንዱ የዘመኑ ሁኔታ ወይም ስልጣኔው የፈጠረው ክስተት ነው። በዚህ ምክንያት ከባህሉ የመውጣት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ ባሁኑ ጊዜ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ሰርቶ፣ ለራሱ በልቶ፣ ለራሱ ብቻ የመጠቀምን ባህል እያዳበረ ነው። በዚህ ምክንያት ከማኅበራዊ ኑሮ አንፃር ስናየው የታመመን ያለመጠየቅ ነገር አለ። ለቀሶ ያለመድረስ ነገር አለ። ሠርግ ያለመጠራራት ሁኔታ አለ። ዱሮ እስላሙንና ክርስቲያኑን በደንብ አስተሳስረው የያዙ ባህሎችን የመተው ነገር አለ። ለምሳሌ ዱሮ እንደ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ቤት ቡሄ ይጋገር ነበረ። ቡሄ የሚጋገረው የክርስቲያን የሙስሊም ተብሎ ሳይሆን የሚታሰበው ‹ቡሄ ደርሷል! ዑመሬ ጅራፍ ግርፊያ ሲሄድ ይዞት የሚሄደው!› ብላ ነው፤ እናቱ ቡሄ የምትጋግርለት፤ ለሙስሊሙ ልጇ። አሁን እነዚህ እነዚህ ባህሎች እየቀሩ ነው። ባሁኑ ጊዜ ሌሎች ሌሎች ክፍተቶችም እየተፈጠሩ ነው። የዱሮው ግን የተሻለና የጠነከረ ማኅበራዊ ግንኙነት ነበር።[328]

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የወሎዬዎች አብሮነት የሚገለፀው አብሮ በመሥራት፣ አብሮ በመብላትና አብሮ በመጠጣት፣ በመረዳዳትና በመደጋገፍ፣ በመተዛዘንና በመተሳሰብ፣ ከእኔ ይልቅ ላንተ...ወዘተ በሚል ባህል ነው። ባንፃሩ ከላይ ከቀረበው ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው ከዘመኑ መንፈስ አንፃር ለውጥ እየታየ መሆኑን ነው። ለውጡም ሥረ-መሰረት ካለው የወሎዬዎች የአብሮነት ባህል፣ ወግና ልማድ፣ ደንብና ሥርአት ያፈነገጠ ነው። በዚህም ከእኔ ይልቅ ላንተ የሚለው የወሎዬዎች የመተሳሰብና የመተዛዘን ባህል፤ “ካንተ ይልቅ ለእኔ” በሚል አስተሳሰብ እየተተካ ነው።

ዘመኑ የፈጠረውን የዚህ አይነቱን አስተሳሰብ ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ የሚገልጹት፤ “ዱሮኮ አንዱ ለሌላው ከፍተኛ ክብር አለው። ለምን? እምነት አለው። ብልሹነት የመጣውኮ አሁን በቅርብ ጊዜ ነው። ውሸት የመጣው በቅርብ ጊዜ ነው። መከዳዳት የመጣው አሁን በቅርብ ጊዜ ነው። እምነት የሁሉም ነገር መሰረት ነው። እንደመሬት ያለ ነው። የዱሮው የተለየ ነው። ፍቅር ያለው ነው። ውሸት የለም። መከዳዳት የለም። እራስ ወዳድነት የለም።”[329] በማለት ነው። በተመሳሳይ ዓሊ መሐመድ ከላይ በቀረቡት አስተያየቶች ሙሉ በሙሉ ይስማማሉ። ለዚህም ለክርስቲያን ሙስሊሙ አብሮነት ቀድሞ የነበረው የወሎዬዎች

---

328 ያሲን ፍሬው፤ ቃለ- መጠይቅ፤ ሐምሌ 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- 03 ቀበሌ።

329 ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።

የማኅበራዊ ኑሮ ዘይቤ አሁን እየታየ ካለው የአኗኗር ብሂል የተሻለ መሆኑን የሚያነፃጽሩት ቀድሞ የነበረው እሴት እሱው ራሱ እንዲቀጥል ያላቸውን ፍላጎትና ምኞት በመግለጽ ነው። ለዚህም "እንደው አይሆንም እንጂ እሚሆንማ ቢሆን እንደኔ-እንደኔ እንደ ጥንቱ አኗኗር ክርስቲያኑም እስላሙም የሃይማኖት እንጂ የሀሳብ ልዩነት ሳይኖረው በሠርጉም በልቅሶውም፣ በሌላው-በሌላውም በማኅበራዊ ኑሮ በሚያገናኙን ጉዳዮች እንደ ጥንት አባቶቻችን ተሳስበንና ተከባብረን መኖር ነው እሚበጀን!" የሚል ምክንት ያቀርባሉ።[330]

መረጃ አቀባዩ ይህንን ሲሉ ግን ቀድሞ የነበረው የወሎዬዎች የአብሮነት እሴት ምንም ሳይለወጥ እንዳለና እንደነበረ ይቀጥል ማለታቸው አይደለም። ባንፃሩ በለውጡ ምክንያት አወንታዊ ፋይዳ ያላቸው መልካም እሴቶች እየተረሱ አሉታዊ ገጽታ ባላቸው አስተሳሰቦች አይተኩ ማለታቸው ነው። በዚህ መነሻ አወንታዊ ፋይዳ ያላቸው መልካም እሴቶች አሉታዊ ገጽታ ባላቸው አስተሳሰቦች እየተተኩ መምጣታቸውን አሰፋ አበጋዝ የሚገልጹት እንደሚከ ተለው የተለያዩ አብነቶችን በመጥቀስ ነው።

> የወሎን ማኅበራዊ ሕወት ስታየው እስላም ክርስቲያኑ አብሮ መኖርን፣ አብሮ መስራትን፣ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣትን፣ አብሮ ማዘንና አብሮ መደሰትን፣ መከባበርና መተዛዘንን፣ የሚችል ህዝብ ነው። አሁን-አሁን ስታየው ግን እስላሙም ክርስቲያኑም ቢሆን እሚያደርገው ነገር ልክ ያልሆነ ነገር አለ። ለምሳሌ አሁን ሠርግ ላይ ዱሮ የነበረ ነገር አሁን የለም፤ አታየውም። ዱሮ ሙስሊሙ ይጠምቅ ነበር፤ አሁን አይጠምቅም። ለምን? አሁን በክርስቲያን ፆም ወቅትኮ ሠርግ እያየን ነው። ዱሮ አልነበረም። ይኸ ለምንድን ነው? ቅድም እንደነገርኩህ ክርስቲያኖቹ ዘመዶቹ ናቸው። ጎረቤቶቹ ናቸው። ይጠራል ለዚያ አርዶ ነው። እሱ ባይጠጣኮ ለክርስቲያኑ ጠምቆ ነው። አሁን ይሄ የለም። እኔ አሁን ሃይማኖቱ የሚከለክለውን ነገር ያድርግ እያልኩ አይደለም። ግን ልክ ያልሆኑ የሚደረጉ ነገሮች አሉ። በተለይ ልጆቹ የሚያደርጉት ነገር። ትልልቆቹ የሚያደርጉት አይመስለኝም። ሙስሊሙም ላይ ክርስቲያኑም ላይ። ግን ልጆቹ በጣም እያራራቁት ያሉ ይመስለኛል። በተለይ ይኸ የተማርኩ ነኝ የሚለው አካል በብዙ መልኩ እያበላሸው ያለ ይመስለኛል። አሁንም ጥሩ ጥሩ ነገሮች እንዳሉ አለ። ግን ልጆቹ አካሄዳቸው አያምርም። ነገረ-ሥራቸው ከማንም አይገጥምም። እነዚህን እስከመቸ ነው የምንታገሳቸው የሚለው ነገር ሊያሳስብ የሚችል ነው።[331]

በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ በቀረቡት ምዕራፎች ውስጥ እንደተብራራው ወሎዬዎች የሃይማኖት ልዩነት ይኑራቸው እንጂ፤ በማኅበራዊ ኑሮ በኩል ከሚለያዩዋቸው ጉዳዮች ይልቅ እርስ በርስ የሚያስተሳስሯቸው እሴቶች እጅግ በርካታ ናቸው። ለምሳሌ በወሎ ሙስሊም ክርስቲያኑ በአንድ ቅሬ ወይም እድር ታቅፎ በሃዘንና በደስታ እየተገናኘ፣ እየተረዳዳና እየተደጋገፈ በመከባበር አብሮ ይኖራል። ነገር ግን እሴቱ አሁንም ድረስ በገጠሩ አካባቢ እንዳለና

---

330 ዓሊ መሐመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ሐብሩ- አንጦ- 04 ቀበሌ።

331 አሰፋ አበጋዝ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- ጎላ መቻሬ።

እንደነበረ የቀጠለ ቢሆንም፤ በከተሞች አካባቢ ግን አልፎ አልፎ ለውጦች እየታዩ ነው። በመርሳ ከተማ ያለውን የለውጥ ሂደት ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> ቀደም ሲል እስላምና ክርስቲያኑ ቅሬው አንድ ነበረ። ለሠርግም ሆነ፣ ለመከራም ሆነ፣ ለማንኛውም ጉዳይ አንድ ላይ ነበርነ። ልክ እንደ አንድ ሃይማኖት ሆኖ ይኖር ነበረ። በዚህ አይነት ስንኖር፣ ስንኖር በሂደት አንዳንድ ነገሮች ተፈጠሩና የእስላሙና የክርስቲያኑ ቅሬ አንድ ላይ መሆኑ በምግብ የእቃ መነካካት አለ፤ ይኸ እንዴት ነው? የሚል ቅሬታ ከአንዳንድ ሰዎች መነጨ። ከዚያ በኋላ እውነት ነው፤ የሚለው ነገር ተፈጠረ።[332] ከዚህ ጊዜ በኋላ ፍቅሩ እንዳለ ሆኖ፤ ቅሬው ክርስቲያኑ የብቻው፣ እስላሙ የብቻው ቅሬ እንዲመሰርት ተደረገ። ቅሬያችን ይለያይ እንጂ፤ በደስታና በመከራ ግንኙነታችን ግን አሁንም ያው የወንድም አማች አካል ነን።[333]

በተመሳሳይ የወልዲያ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ የየጁ ገነትን የእድር ሁኔታ የሚያስታውሱት በ"ነበር!" ነው። ይህንንም እንድህ በማለት ይገልጹታል። "በዚህ በእኛ በየጁ ገነት እድር እስላሙና ክርስቲኑ አንድ ላይ ነበር እድራችን። በዚህ አይነት በሃዘኑም በደስታውም ተባብረን እንኖር ነበረ። አሁን ግን እስላሙ ከክርስቲያን፣ ክርስቲያኑ ከእስላም በእድር በኩል ተለያይቷል፤ አይገናኝም። መለያየቱንም ያመጣው የአክራሪዎች ተንኮል ነው። በሌላው-በሌላው ያለው መተዛዘንና መረዳዳት ግን አሁንም እንዳለ ነው።"[334]

ከዚህ በላይ በቀረቡት አብነቶች መሰረት ከዘመኑ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ለወሎዬዎች አብሮነት አለታዊ ገጽታ አላቸው ተብለው የሚጠቀሱ የተለያዩ ጉዳዮች ቢኖሩም፤ በዋናነት ግን ከዘመኑ መንፈስ ጋር በተገናኘ ጎልቶ የሚጠቀሰው አንድ ርዕሰ-ጉዳይ ነው። ይህም የሃይማኖት አክራሪነት ነው። ጥናቶችም ሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚገልጹት በወሎ ከሃይማኖት አክራሪነት ጋር በተያያዘ የተለያዩ ሁነቶች ተከስተው አልፈዋል። እነዚህ ሁነቶች የተከሰቱት ደግሞ በዋናነት በደሴ፣ በኮምቦልቻና በኬሚሴ ከተሞች እና እነዚ ከተሞች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ነው። በነዚህ ከተሞችና አካባቢዎች በተለያዩ ወቅቶች በሃይማኖት ሰበብ በተከሰቱ ግጭቶች ምክንያት የሰው ሕይወት ጠፍቷል፤ ሃብትና ንብረት ወድሟል (Mohammed 2010: 97)።

---

[332] ዓለሙ ኃይሉ "እውነት ነው እሚለው ነገር ተፈጠረ" የሚለውን አስተያየት የሚገልጹት "ለእድር ተብሎ ለሙስሊሙም ለክርስቲያኑም በጋራ ከሚዘጋጀው ወጥ ውስጥ በተጨባጭ ሥጋ እየተጨመረበት መቅረብ ጀመረ" በማለት ነው። ለዚህ ደግሞ የክርስቲያኑና የሙስሊሙ እድር እንዲለያይ ፍላጎት በነበራቸው ግለሰቦች ሳይቀነባበር እንዳልቀረ ጥርጣሬ አላቸው። (ዓለሙ ኃይሉ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 11ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ 01 ቀበሌ)።

[333] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።

[334] ሃምሳ ለቃ መላኩ ተገኘ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 6 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ።

ባንፃሩ ይህ ጥናት በተካሄደባቸው የሰሜን ወሎ ክፍል በሆኑት ወረዳዎች ግን በሃይማኖት ሰበብ የተከሰተ ግጭትና በዚህ ምክንያት የጠፋ የሰው ሕይወትም ሆነ የወደመ ሃብትና ንብረት እንዲሁም የደፈረሰ ሰላም የለም። ይህ ማለት ግን ሙከራዎች አልነበሩም ማለት አይደለም። ሙከራዎች ነበሩ። ነገር ግን ሙከራዎቹ በሙስሊሞቹና በክርስቲያኖቹ የጠነከረ የአንድነት መንፈስና አርቆ አስተዋይነት ከሽፈዋል። በአካባቢው ታላላቆችና የወሎ ደጋጎች ብልሃትና በረካ መክነዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በመርሳ ከተማና በአካባቢው ተፈጥሮ የነበረውን ክስተት ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ የሚያስታውሱት እንደሚከተለው ነው።

> በውኑ ፈጣሪ ያውቃል። ካሁን በፊት ሃይማኖቶቹን ሰበብ አድርገን በእስላሞቹና በክርስቲያኖቹ መካከል ቅራኔ እሚባል ነገር አናውቅም። አንድ እኔ የማረሳው ነገር አለ። አንድ አምስት ስድስት አመት ሊሆን ነው። የክርስቲያኖቹ የጥምቀት በዓልና የእኛ በዓል አንድ ላይ ገጠመ። በዚህ ወቅት ከበዓሉ በፊት የእስላሙ ተማሪዎችና የክርስቲያኑ ተማሪዎች ተጋጩ እሚባል ነገር ተነገረኝ ለእኔ። ቀጥሎ በዓሉ መጣ። ወጥቼ በማይክሮፍ [በድምፅ ማጉያ] ምንድን ነው የተናገርኩት የመስጊድ ኃላፊው እኔ ነበርኩ፤ ጉዳዩን እንደተከታተልኩት ጥፋቱ በእስላሞቹ ተማሪዎች በኩል ሆኖ ተገኝቷል። በዓል መጥቷል። ፈጣሪ ይሁንብኝ። እኛ ወንድም አማኞች ነን። አንድ ልጅ፣ አንድ ሰው ጣልቃ ገብቶ የተገኘ እንደሆነ እኔ በክርስቲያኑ በኩል ነኝ። ለምን? በእነሱ በኩል ጥፋት የለም። ጥፋት ያለው በእኛ ልጆች በኩል ሆኖ ተገኝቷል። የልጆች ቤተሰቦች የሆናቸሁ ኃላፊነቱ የእናንተ ነው። በቀጥታ ከሃይማኖቱ ውጭ ነው እምናደርጋችሁ። ከማኅበራዊ ኑሮ ውጭ ነው እምናደርጋችሁ። ይህንን አውቃችሁ ልጆቻችሁን ያዙ ብየ የተናገርኩበት ወቅት አለ። ከዚያ ምንም አይነት ኮሽታ ሳይፈጠር እንደ ጥንተ ሥረ-መሰረታችን በዓሉን በሰላምና በደስታ አሳልፈናል። ባህላችን እዚህ ድረስ ነው።[335]

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው በወቅቱ ሊፈጠር የነበረው ግጭት የተጫረው የሁለቱን ሃይማኖቶችና የእምነቶቹን ተከታዮች የእርስ በርስ ግንኙነት ሥረ-መሰረት ጠንቅቀው በማያውቁ ወይም ይህንን እያወቁ ሥረ-መሰረቱ እንዲናጋ በሚፈልጉ አካላት አማካይነት ነው። ነገር ግን የወሎዬዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም አብሮነት በነዚህ አካላት በቀላሉ አልተናጋም፤ አልሻከረም። ባንፃሩ የእርስ በርስ ግንኙነቱ፣ መተሳሰሩና መከባበሩ ዘመን ተሻጋሪ ስለመሆኑ በእለቱ በተፈጠረው ክስተት በራሱ ተረጋግጧል። ይህንንም የአካባቢው ነዋሪዎች የሚገልጹት በክርስቲያኖቹ በኩል የነበረውን የወቅቱን ሁኔታ እንደሚከተለው ለአብነት በመጥቀስ ነው።

> በእስላሙም በክርስቲያኑም በኩል ያለው በሃይማኖት የመቻቻል እሴት አሁንም ያው ነው። አንድ ምሳሌ ላንሳልህ። ከአራት አምስት አመት በፊት ነው። ጥምቀትና የእስላሞቹ በዓል አንድ ቀን የዋለበት አጋጣሚ ነበር። እና መርሳ ከተማ ላይ ምን ተከሰተ መሰለህ፤ አንዳንድ ተቀጽላ ሃይማኖት የሚያራምዱ አካላት እስልምናውን ሽፋን በማድረግ ግጭት ሊፈጥሩ ሞከሩ። በዚህ ጊዜ የሃይማኖት አባቶችና ህዝቡ ምንድን ነው ያደረጉት፤

---

[335] ሼህ አሰን ዓሊ ሞሐመድ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- 01 ቀበሌ።

መጀመሪያ የእስላሞቹ በዓል ተከብሮ ይጠናቀቅና ታቦቱ ወደኋላ ቆይቶ ይግባ ተባለ። በቀጥታ የእስላሞቹን በዓል ቁሰቹም ሌላውም ሰው ሁሉ አብሮ አጅቦ ካከበረ በኋላ ወደ ታቦቱ ሄደ። ከዚያ ምንድን ነው የሆነው፤ ባንዳንድ መጥፎ ሰዎች ቀስቃሽነት ወደ ግጭት ሊያመራ የነበረው ሁኔታ ተቀይሮ፤ ሙስሊሞቹ ወደ ቤታቸው እንኳ ሳይገቡ ዱሮ እንደሚያደርጉት በቀጥታ ሚካኤልን በጭፈራና በሆታ አጅበው አስገብተዋል። ይኸ ገጠመኝ አለ በቅርብ።[336]

በምዕራፍ አምስት ውስጥ እንደተጠቀሰው መርሳ ሚካኤል አሁን ወዳለበት ቦታ እንዲዛወር የተደረገው በሙስሊሞቹ ጥያቄ ጭምር ነው። ቤተ-ክርስቲያኑ የተሰራውም ሙስሊሞቹ ባደረጉት የገንዘብና የጉልበት ትብብር አማካይነት ነው። እንዲሁም በያመቱ የጥር ሚካኤልን በጭፈራና በሆታ አመቀውና አድምቀው ወደማደሪያው የሚያስገቡት ክርስቲያኖቹ ብቻ ሳይሆኑ የአካባቢው ሙስሊሞችም ጭምር ናቸው። በዚህ መሰረት የክርስቲያንና የሙስሊም የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ የሚገለፀው በዚህ አይነቱ ሥረ-መሰረት ባለው የጋራ እሴት አማካይነት ነው።

ባንፃሩ ከላይ የተገለፀው ክስተት ግን ሥረ-መሰረት ካለውና ከነባሩ የወሎዬዎች ባህል፣ ወግና ልማድ፣ ደንብና ሥርዓት ያፈነገጠ ነው። ከአብሮነት ይልቅ መለያየትን የሚመርጥ ነው። ከመከባበር ይልቅ መናናቅን የሚያስቀድም ነው። ከፍቅርና ሰላም ይልቅ ጥላቻና ብጥብጥን የሚናፍቅ ነው። በሌላ አገላለጽ ቀድሞ የነበረውም ሆነ አሁን ያለው የክርስቲያንና የሙስሊም ግንኙነት በወሎ፤ አብሮ በመስራት፣ አብሮ በመብላትና አብሮ በመጠጣት፣ በመደጋገፍና በመረዳዳት፣ በመተባበርና በመከባበር፣ በሰላምና በፍቅር አብሮ በመኖር ላይ የተመሰረተ ነው። አልፎ አልፎ አሁን የሚታየው ክስተት ግን በፉክክርና በግጭት ላይ የሚያተኩር ነው። በጥርጣሬ፣ በመፈራራትና በትንኮሳ ላይ የተመሰረተ ነው። የዚህ አይነቱን አስተሳሰብ መነሻ ምክንያት የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚከተለው ይገልፁታል።

ይኸ ሁሉ የአክራሪዎች ስራ ነው። እንደውም እነሱ ነገሩ ይፋ እየወጣባቸው፣ እየተጋለጠባቸው ተቸግረው ነው እንጂ፤ ከቶውም እስላም የሆንክ ከክርስቲያን ሠርግ፣ ከክርስቲያን ክርስትና፣ ከክርስቲያን ሃዘን እንዳትቀላቀል እያሉ ይሰብካሉ። ግን ደሞ ከዚያው እርስ በርሳቸው እየተናቆሩ፤ "እንዴ! እኛ ወንድሞቻችን አሉ፣ እህቶቻችን አሉ፣ ቤተሰቦቻችን አሉ፣ ለምንድን ነው ከእነሱ የምንለየው!?" እያሏቸው፤ በዚህ የተነሳ ውስጥ ለውስጥ እየተናቆሩ ነው ያሉት፤ ይኸ የአክራሪዎች ሥራ ነው። አክራሪዎች ናቸው ይኸንን እሚያደርጉት እንጂ፤ ጎብረተሰቡማ ዝምድናውን፣ ጉርብትናውን፣ አብሮ መኖሩን ጠልቶት አደለም። ህዝቡ ዝምድናውን፣ ጉርብትናውን፣ አብሮ መኖሩን ይወዳል፤ ይፈልገዋል። የሃይማኖት ጉዳይ ያው ደሞ እስላሙም እስላም ነው። ክርስቲያኑም ክርስቲያን ነው። ሃይማኖቶቹ ይኸን ያህል አያራርቁትም ነበር። ይኸን ያህል ዘመን በሰላምና በፍቅር አብሮ ኑሯል። አሁን ካልኩህ ነው ትልቁ ተንኮል ያለው። መንግሥትም በዚህ በኩል የተለሳለሰ

[336] ተበጀ መኮንን፣ ቃለ-መጠይቅ፤ ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም. መርሳ- አዲራ።

> አቋም ስላለው ነው እንጂ፤ ነገሩ እየሰፋ የሄደው ሌላ መነሻ ምክንያት አልነበረውም። የአክራሪዎች ዋና ዓላማ እስላሙና ክርስቲያኑ የተሳሰረባቸው እሴቶች እንዲጠፉ፣ ባህል በጠቅላላው እንዲጠፋ ማድረግ ነው። የተለያየ ምክንያት እየፈጠሩ፣ "ይሽ ያንተ አደለም፣ ይሽኸ የእኛ አደለም" እያሉ፤ የመለያየት ሥራ ይሰራሉ። አሁን የሚታዩት አንዳንድ ልዩነቶችም በዚህ የተነሳ የመጡ ናቸው።[337]

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ይህ ጥናት በተካሄደባቸው ወረዳዎች ውስጥ ቀድሞ ከነበረው የሃይማኖት መቻቻል እሴት በተለየ ይህ ነው የሚባል ልዩነት ባይኖርም፤ ከላይ በቀረቡት ጥቅሶች ውስጥ የተጠቆሙት አሉታዊ እንቅስቃሴዎች ግን የዘመኑ መንፈስ ከወለዳቸው የሃማኖት መቻቻል እሴት አንፃር የሚገለጽባቸው አብነቶች ናቸው። የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት ክስተቶቹ እንኳንስ ለክርስቲያኖቹ ቀርቶ ለሙስሊሞቹም ያልተመቹና የማይበጁ ናቸው። የዚህ አይነቱን ክስተት እንድሪስ አህመድ የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> አሁን እኔ በዚያኛውም ወቅት፣ ስላለሁኝ አሁን በአብዛኛው ይሽ አክራሪነት ከመጣ ወዲህ፣ በተለይ እነዚህ ወሐቢይ እሚባሉት ሰወይ ከመጡ ወዲህ የመለያየቱ ሁኔታ እየታየ ነው። እነዚህ አካላት አልፊው ተርፊው ከክርስቲያኖች ጋር አትሂዱ እስከማለት የደረሱም አሉ። ክርስቲያን ጓደኛ አታድርጉ፣ ከክርስቲያኖች ጋር እንዳትበሉ፣ እንዳትጠጡ፣ እንደዚህ፣ እንደዚህ እንዳታደርጉ፣ እያሉ ለመነጣጠል ጥረት እሚያደርጉ አሉ። በአብዛኛው ይሽን ወጣቱን። አሁን ይሽ ትላልቁ አይለያይም፤ አሁንም ድረስ አልተለያየም። በመጨረሻ አሁን ግን ራሳቸው እየከሰሙ እየመጡ ነው። አሁን ከዛሬ ሁለትና ሦስት አመት በፊት የነበረውና አሁን ያለው ሁኔታ አንድ አይደለም። ምክንያቱም መለያየቱ ለማንም እንደማይበጅ ህዝቡም አወቀው። መንግሥትም የራሱን ሥራ መሥራት ጀመረ። እነዚያም ሰዎች እየተለዩ፣ እየተነጠሉ፣ አማኙም ራሱ አላስጠጋቸው እያለ ስህተት መሆኑን እያወቀ አሁን ወደ ጥሩ አቅጣጫ እየመጣ ነው።[338]

ከዚህ በላይ ከቀረቡት አስተያየቶች መረዳት የሚቻለው ዋና ቁም ነገር ከዘመኑ መንፈስ አንፃር በወለዳቸው የአብሮነት እሴት ላይ አሉታዊ ለውጦች እየታዩ መሆኑን ነው። ነገር ግን የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት እነዚህ አልፎ አልፎ የሚታዩ አሉታዊ ለውጦች ቢኖሩም እንኳ የወለዳቸው የአብሮነት እሴቶች ተናግተዋል ወይም ይናጋሉ ማለት አይደለም። እሴቶቹ አሁንም ድረስ እንዳሉና እንደነበሩ ናቸው። ወደፊትም አወንታዊ ገጽታቸውን እንደተላበሱ የሚቀጥሉበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ለዚህ ደግሞ አስካለ አበበ "የወለዳቸው የሃይማኖት መቻቻል እሴት በጠንካራ መሰረት ላይ የተገነባ ስለሆነ በቀላሉ ይናጋል የሚል እምነት የለኝም!" በማለት ምክንያታቸውን እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ።

> እኔ እስላምና ክርስቲያን እንደ አንድ ሰው ልጆች አድርጌ ነው እማያቸው። በተለይ በዚህ በኛ። ስለዚህ ዝምብለው ነው እንጂ፤ በፍጹም ሊለያዩን አይችሉም። እምልህ ሰው ከልጁ ይለያል? አይለይም! እሱ እስላም ቢሆን፣ ልጁ ክርስቲያን ናት። አሁን እዚያ ችግር ቢሆን

---

337 ግራዝማች ብሩ ይማም፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ነሐሴ 13 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 01 ቀበሌ።

338 እንድሪስ አህመድ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ሐምሌ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 03 ቀበሌ።

> አይቀር ከልጅ ቤት! በተለይ በወሎ አይሰራም። የሌላውን አገር እንጃ እንጂ፤ በዚህ በኛ ቢያደርጉትም፣ ቢሰሩትም ተገለባብጦ ያው ነው። ሊሆን አይችልማ! ምክንያቱም አባቱ እስላም እናቱ ክርስቲያን ስለሆነ። ሊለያዩት አይችሉም። እንደው ለወሬ ያህል ነው እንጂ። ስለዚህ እስላምና ክርስቲያን በዚህ በኛ አገር በወሎ በሃይማኖት ምክንያት ይለያያሉ ብየ አልገምትም።[339]

ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ ከላይ የቀረበውን አስተያየት፤ "ይኸ ወሎ የጁ ሲባል፤ የአንድ አባት፣ የአንድ እናት ልጅ ነው። አባቱ ክርስቲያን ሆኖ እናቱ እስላም የሆነች አለ። እናቱ እስላም ሆና አባቱ ክርስቲያን የሆነ አለ። በሥጋ፣ በደም፣ በአጥንት፣ በጅማት የተያያዘ ነው። የዚህ አይነቱ ትስስር ስላለ ነው፤ አክራሪዎች እስላሙንና ክርስቲያኑን ለመነጣጠል የተቸገሩት። ባህሉንም ማጥፋት ያልቻሉት!"[340] በማለት ሃሳቡን ይጋሩታል። ዮሴፍ ወርቁ በበኩላቸው ክርስቲያን ሙስሊሙ አሁን ባለው የዘመን መንፈስ የጋራ እሴቶቹ ተሸራርፈው አብሮነቱ ወይም ትስስሩ እንዳይላላ የሚያደርገውን ጥረት የሚገልጹት እንደሚከተለው ነው።

> አሁን እየታየ ያለውን አስቸጋሪ የሆነ የአክራሪነት ባህርይ በከፍተኛ ሁኔታ ህዝቡ ይዋጋዋል። ይቃወመዋል። ለምን? ይኸ ባህል እንዳይጣስ ነው። በቃ! ልዩነት እንዳይመጣ ለማድረግ በየቤተሰቡ፣ በየመስጊዱ፣ በየበተ-ክርስቲያኑ ምክክር ይደረጋል። ከዚህ የተነሳ በዚህ በውርጌሳ አንድም ቀን ብጥብጥ፣ አንድም ቀን ችግር ተፈጥሮባት አያውቅም። ችግር እንኳ ሊፈጠር ካለ ወዲያውኑ በውይይት ነው፤ እሚፈታው። ህዝቡ ተሰባስቦ በየሃይማኖቱ በጋራም በተናጠልም የሚፈታው ስለሆነ በኛ በዚህ በውርጌሳ አክራሪዎች የሚገቡበት ቀዳዳ የላቸውም።

ባጠቃላይ ይህ ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች ሙስሊም ክርስቲያኑ በሃይማኖት ተቻችሎ በፍቅርና በሰላም አብሮ የሚኖርባቸው እሴቶች አሁንም ድረስ ሥረ-መሰረታቸውን ሳይለቁ እንደቀጠሉ ናቸው። ከላይ እንደተገለጸው ለወደፊቱም ቢሆን ልዩነት እንዳይፈጠር ሙስሊሞቹም ሆኑ ክርስቲያኖቹ ክፍተቶችን እየደፈኑ ይገኛሉ። በሌላ በኩል ግን ሙስሊም ክርስቲያኑን ድርና ማግ በመሆን ይዘው የሚጓዙ የጋራ እሴቶች እንዲጠፉ ጥረት የሚያደርጉ አካላት አሉ። በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት እና የዘመኑ መንፈስ በወሎ የሚገለጸው በመልካም ገጽታው ብቻ ሳይሆን፤ ከላይ በተገለጹት አሉታዊ መንፈስ ባላቸው የለውጥ አስተሳሰቦች ጭምር ነው።

---

339 አስካለ አበበ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ።

340 ሃምሳ አለቃ መላኩ ተገኘ፤ ቃለ-መጠይቅ፤ ነሐሴ 17 ቀን 2007 ዓ.ም. ወልዲያ- 04 ቀበሌ።

ማጠቃለያና ይሁንታ

በዚህ ጥናት ሂደት ከመነሻው የጥናቱ ዓላማዎችና የጥናቱ ጥያቄዎች ተነድፈው፣ ቀደምት ጥናቶች ተከልሰውና ያሉባቸው ክፍተቶች ተለይተው፣ የጽንሰ-ሃሳብ፣ የንድፈ ሃሳብና የጥናቱ ዘዴዎች እንዲሁም የጥናቱ መተንተኛ ሥልቶች ተቀምረው ወደሥራ ተገብቷል። በዚህ መሰረት ለዚህ ጥናት የሚያገለግሉ መረጃዎች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት ተሰብስበዋል።በመጨረሻም እነዚህ መረጃዎች ተደራጅተውና ተተንትነው ጥናቱ ተካሂዷል። የዚህ ንዑስ ርዕስ ዋና ዓላማም ባጠቃላይ በዚህ ጥናት ምን ተጠንቶ ምን እንደተገኘ ወይም አጠቃላይ የጥናቱ ውጤት ምን እንደሆነ በየምዕራፉ የተነሱ ርእሰ-ጉዳዮችን በመጭመቅ ባጭሩ ማቅረብ ነው። እንዲሁም በራሱ በጥናቱ ግኝት ላይ የተመሰረተ ይሁንታ በመጠቆም ጥናቱን መቋጨት ነው።

ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ፤ የሚለው ርዕሰ-ጉዳ ነው። ዋና ዓላማውም የሃይማኖት መቻቻል እሴት ማለት በወሎ ምን ማለት እንደሆነ፣ በምንና እንዴት እንደሚገለጽ እና ምንን እንደሚሳይ የተለያዩ እሴቶችን በመመርመር፤ በወሎ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦችን እርስ በርስ አስተሳስረውና አስተባብረው፣ አግባብተውና አስማምተው፣ አዛምደውና አዋደው ድርና ማግ በመሆን በፍቅርና በሰላም ይዘዋቸው የሚጓዙ መሰረታዊ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶችን (common-bond/ fabric) አጥንቶ መግለጽ ነው። ይህ ርዕሰ-ጉዳይ ደግሞ በቀደምት ጥናቶች ያልተሞላ ወይም ያልተደ ፈነ የጥናት ክፍተት ነው።

በመሆኑም የዚህ ጥናት ክለሳ ድርሳናት በቀረቡበት በምዕራፍ ሁለት ውስጥ እንደተብራራው በኢትዮጵያ ከሃይማኖት ጋር በተገናኘ የተካሄዱ በርካታ ቀደምት ጥናቶች አሉ። ነገር ግን የነዚህ ቀደምት ጥናቶች ትኩረት በሃይማኖት መቻቻል እሴት ላይ አይደለም። ባንዳንዱ በሃይማኖቶቹ አነሳስ፣ አገባብና ሥርጭት፣ ስለ ሃይማኖቶቹ አስተምህሮ ወይም መርህ፣ ሃይማኖቹ ከቤተ-መንግሥቱና ከየቤተ-እምነቶቹ ጋር ስለነበራቸው ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ላይ ያተኮሩ ናቸው። እንዲሁም ሃይማኖቶቹ ስለገጠሟቸው መልካምና መጥፎ አጋጣሚዎች የሚያትቱ ናቸው። በተለይ የብዙዎቹ ጥናቶች ትኩረት በክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች መካከል የነበረው ግጭትና ፉክክር ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በሃይማኖት ስበብ የተከሰቱ ግጭቶች የቀደምት ጥናቶች ትኩረቶች ናቸው። ከዚህ አንፃር

እነዚህ ቀደምት ጥናቶች ግንኙነታቸው በዋናነት ከጀማው ወይም ከብዙሃኑ ጋር ሳይሆን ከፖለቲካው፣ ከኢኮኖሚውና ከሃይማኖቶቹ ሊሂቃን (Elites) ጋር የተሳሰረ ነው።

ባንፃሩ የዚህ ጥናት መነሻ (ትኩረት) በአብዛኛው ለአብሮነት መሰረት በሆኑ እሴቶች በተለይ በሃይማኖቶቹ ትውፊቶች፣ የእሴቶቹ ባለቤት በሆኑትና እሴቶቹም በተግባር በሚሰሩበት በህዝቡ አኗኗር ላይ የተመሠረተ ነው። በማኅበረሰቡ የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ወይም የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ ያተኮረ ነው። ይህም ማለት ቀዳሚዎቹ ጥናቶች በልዩነት ላይ ሲያተኩሩ ይሄ ጥናት ግን በእርስ በርስ ግንኙነቶችና በአብሮነት ላይ ያነጣጥራል። ትኩረቱን በመቻቻል፣ በመከባበር፣ በመተባበር፣ በመተሳሰብ፣ በመተዛዘን፣ በመረዳዳትና በመደጋገፍ ላይ ያደርጋል። አብሮ በመሥራት፣ አብሮ በመብላትና አብሮ በመጠጣት ላይ ያተኩራል።

ይህ ማለት ግን ይሄ ጥናት በሁለቱ ሃይማኖቶች እምነት ተከታዮች መካከል ያሉ ልዩነቶችን አልተመለከተም ማለት አይደለም። ባንፃሩ የሃያማኖት መቻቻል እሴቶቻቸው የተመረመሩት ከአንድነታቸውና ከልዩነታቸው አንፃር ነው። ፍቅር ጥላቻቸውን፣ ሃዘን ደስታቸውን፣ ማግኘት ማጣታቸውን፣ መለያየት መገናኘታቸውን...ወዘተ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በዚህ መሰረት የዚህ ጥናት ግኝት የተመሰረተው ተመርጠው በተጠኑ አወንታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሳይሆን፤ የተለያዩ ጉዳዮች ተብላልተውና ተጨምቀው ተጣርተው ነጥረው በወጡ ጉዳዮች ላይ የተገነባ ነው።

ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ ጨምሮ፤ የወለዬዎች ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ የሆኑ በአብዛኛው ፎክሎራዊ ጉዳዮች ተመርምረዋል። በዚህ መነሻ የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለዬ፤ በእስልምናውና በክርስት ናው ትውፊቶች እንዴት እንደሚገለጽ ተጠንቷል። እንዲሁም በወለዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ዘይቤ አማካይነት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወለዬ ምን ማለት እንደሆነና ምንን እንደሚያሳይ ተተንትኗል።


ይህም የተደረገው የጥናቱን ጽንሰ-ሃሳብ፣ ንድፈ-ሃሳብና የጥናቱን ዘዴዎች መሰረት በማድረግ ነው። በዚህ መሰረት ከጽንሰ-ሃሳብ አንፃር "ፎክ ማለት በአንድ በሆነ የጋራ እሴት የተሳሰሩና የሚገናኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሆኑ እና በጋራ ያስተሳሰራቸውን እሴት የኔ የራሴ ብለው የተቀበሉ የሰዎች ስብስብ ነው" (1965: 2) (አጽንዖት የኔ) የሚለው የአለን ዳንደስ መርህ ለዚህ ጥናት መነሻ መሰረት ሆኖ አገልግሏል። "ሎር" የሚለው መርህ ደግሞ "የሰው ልጅ በማኅበር ሲኖር

የፈጠራቸውና የሚጠቀምባቸው የአሰራር፣ የአኗኗር፣ የአስተዳደር፣ የአነጋገር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ...ወዘተ ዘዴዎች፣ ብልሃቶች፣ ፍልስፍናዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ጥበቦች፣ አመለካከቶች፣ እምነቶች፣ አምልኮዎች፣ የእርስ በርስ ግንኙነቶች፣ ገጠመኞች...ወዘተ" (1972: 2-4) (አጽንዖት የኔ) የሚለው የሪቻርድ ዶርሰን አስተሳሰብ ተግባራዊ ተደርጓል።

ከዚህም ሌላ የእሴቶቹን ትርጉም፣ ምንነት፣ ፋይዳ፣ ተግባርና ጥቅም ተረድቶ፣ የማኅበረሰቡን ስሜት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ማንነት፣ ፍልስፍና፣ አመለካከት...ወዘተ ተገንዝቦ፣ በዚያው በአካባቢው፣ በባህሉና በማኅበረሰቡ ኑሮ ላይ ተመስርቶ መረጃዎቹን ለመሰብሰብና ለመተንተን እንዲቻል፤ ጥናቱ በዓውዳዊ የንድፈ-ሃሳብ መርህ ተመርቷል። በዚህ መሰረት ይህ ጥናት የተካሄደው እሴቶቹ ተፈጥረው በሚኖሩበትና አገልግሎት በሚሰጡበት በዚያው አካባቢ፣ በአገሬው እውቀት፣ በራሱ በማኅበረሰቡ አመለካከትና ስሜት ላይ ተመስረቶ ነው። በአገሬው ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ተፈጥሯዊ፣ ዓውድ ውስጥ ነው።

የጥናቱም ዘዴም አይነታዊ ነው። በዚህ ዘዴ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር እየተገናኙ፣ እየተጎራበቱና እየተዛመዱ ተተንትነዋል። የተተነተኑት መረጃዎችም ከላይ በተጠቀሰው ዓውድ ውስጥ ከባለቤቶቹ መንጭተው እዚያው የተቀዱና በባለቤቶቹ ድምጽ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። በመሆኑም በዚህ መርህ ላይ በመመስረት በተደረገው ምርምር ወሎዬዎች ልዩ ልዩ የሃይማኖት መቻቻል ስልቶች እና ከስልቶቹ የሚመነጩ በርካታ የጋራ እሴቶች እንዳሏቸው ለማረጋገጥ ተችሏል።

በዚህ መሰረት የሃይማኖትመቻቻል እሴት በወሎ ምን ማለት እንደሆነ፣ እንዴትና በምን እንደሚገለጽ፤ እንዲሁም ምንን እንደሚገልጽ የወሎዬዎች ትውፊት በሆነው የቡና ሥርዓት እንደሚከተለው ተወክሎ ቀርቧል። ውክልናው ትዕምርታዊ ወይም ተምሳሌታዊ ነው። የውክልናው መሠረታዊ መነሻ ደግሞ ከላይ የተገለጸው የፎክሎር ጽንሰ ሃሳብ ነው። ይህ ጽንሰ-ሃሳብ በወሎ ክርስቲያኖቹና ሙስሊሞቹ በጋራ የእኔ የራሴ የሚሉት እሴት ባለቤቶች መሆናቸውን በተጨባጭ የሚያረጋግጥ የዚህ ጥናት ሥረ- መሰረት ነው።



ሥዕላዊ መግለጫ :- የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ ምን ማለት እንደሆነ፣እንዴት እንደሚገለፅና ምንን እንደሚገልፅ በወሎዎች የቡና ሥርአት ትውፊት ተምሳሌትነት ሲገለፅ

በዚህ ትዕምርታዊ ውክልና መሰረት የወሎዬዎች ማኅበራዊ ዓውድ የሚወክለው ቡናውን ሲሆን፤ ባህላዊ ዓውዱ ደግሞ ቡናው የሚፈላበትን ውኃ ይወክላል። ጀበናው የሚወክለው ወሎ የሚለውን መጠሪያ ስያሜ ወይም አገር ነው። በተመሳሳይ ሦስቱ ጉልቻዎች ፎክሎርን ይወክላሉ። ቡናው ከውኃው ጋር ፈልቶ እንዲዋሀድ የሚያደርገው ኃይል (እሳት) የተወከለው ደግሞ በሁለቱ ኃይማኖቶች እና በአገር በቀሉ ባህል፤ እንዲሁም በሁለቱ ቅልቅል ነው። በዚህ ኃይል በጀበናው ውስጥ የሚፈላው ቡና የወሎዬዎችን አጠቃላይ የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ወይም "ቅቡል/ ውጉዝ" የተሰኙ እሴቶቻቸውን ይወክላል። ስኒው ውስጥ የተቀዳው አቦል ቡና ደግሞ ወሎዬዎች "መልካም እሴቶቻችን (core values)" የሚሏቸውን ጉዳዮች ሁሉ ይወክላል። በዚህ መነሻ ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው በፍቅርና በሰላም አብረው እንዲኖሩ የሚያስችሏቸው የጋራ እሴቶች ይህ ተዕምርታዊ ውክልና የተሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው። የእሴቶቹ ትዕምርታዊነት፣ አግባብነትና የእርስ በርስ ግንኙነት እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል።

ጀበና፡- "ጀበና" ቡና-ቡና ሆኖ እንዲጠጣ የሚያስችል እቃ ነው። "ወሎ" የሚለው የአካባቢ መጠሪያ ሥም ደግሞ ወሎዬዎች "የወሎ ሰው" ይባሉ ዘንድ ወይም አንዲሆኑና ወሎዬ ተብለው እንዲጠሩ የሚያስችል አካባቢ እና የአካባቢ መጠሪያ ስያሜ ነው። ሥያሜ በፎክሎር ትዕምርታዊ ወይም ተምሳሌታዊ ነው። ፍችውም ይህንን መሠረት የሚያደርግ ነው። በዚህ መሠረት ትርጉሙ ስፋትና ጥልቀት አለው። ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ስነልቡናዊ...ወዘተ የሆነ ትርጉምና ፍቺ አለው።

ስለዚህ "ወሎ" የሚለው መጠሪያ ሥያሜና ወሎዬዎች በእትብት የተሳሰሩ ናቸው። ዝምድናቸውም ከማንነታቸው፣ ከሥጋና ደማቸው ጋር የተዋሀደ ነው። ይህም በመሆኑ ክርስቲያን ሙስሊሙ በወሎ፤ "ወሎዬ" በሚለው የጋራ ክር ይተሳሰራል፤ አንድ አካል አንድ አምሳልም ይሆናል። በዚህም የሃይማኖት መቻቻል እሴት ማለት በወሎ፤ በወሎና ወሎዬነት ጽንሰ-ሃሳብ ይገለፃል። እንዲሁም "የወሎ ጀበና መጀን!" እንዲሉ፤ ጀበና በወሎ፤ የወሎ ደጋጎችን በረካና ከራማ ይወክላል። የወሎ ደጋጎችን ዱዓና ቱፍታ ያስታውሳል። "በሼሆቹ በደጎቹ ወሎ መጀን!" የሚለውን ብሂል ይገልፃል። ከወሎ አድባርና አውጋር ጋርም ይገናኛል። ስለዚህ የጀበናው ውክልና ቡና ለማፍላት የሚያገለግል ብቸ ሳይሆን ጥሩውን ከመጥፎ ወይም ቅቡሉን ከውጉዙ የማጣራት ተግባርም ይጫወታል።

ሦስቱ ጉልቻዎች፡- ሦስቱ ጉልቻዎች የተወከሉት የፎክሎር መሠረታዊ መገለጫ ዘርፎች በሆኑት፤ ትዕምርቶች (Symbols)፣ የትውልዱ አርአያዎች ወይም ቀንዲሎች (Heroes) እና በሥርአተ-ከበራዎች (Rituals) አማካይነት ነው፡፡ በዚህም በትዕምርቶች የተወከሉት መሠረታዊ ጉዳዮች "ሎር" በሚለው የፎክሎር ጽንሰ-ሃሳብ ስር የተዘረዘሩት ነጥቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ነጥቦች ጀበናውን ደግፈው ከያዙ ሦስት ጉልቻዎች አንዱን ይወክላሉ፡፡

የትውልዱ አርአያዎች ደግሞ፤ትውልዱ የሚጓዝበት አቅጣጫ ጠቋሚ (Compass) በመሆን የሚያገለግሉ፣ ማኅበራዊ ሥርአቱ ወይም ባህሉ-ወግና ልማዱ ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር የሚያደርጉ አባቶች እና እናቶች ናቸው፡፡ ይህም ያለፈውን ትውልድ ታሪክና ባህል ወይም ትውፊት ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፉ አባቶች እና እናቶችን የሚወክል ነው፡፡ የሀገርንና የወገንን ደህንነትና ሰላም የሚጠብቁ ጀግኖችን የሚያሳይ ነው፡፡ሥነ-ምግባርን፣ ፍቅርን፣ መተባበርን፣ መረዳዳትን፣ ታማኝነትን...ወዘተ ለትውልዱ የሚያስተምሩ፣ ትውልዱን የሚመክሩና የሚገስጹ የሃይማኖት አባቶችን እና የሀገር ሽማግሌዎችን የሚጠቁም ነው፡፡ ፈጣሪንና ሰውን የሚያገናኙ ብፁአንን፣ የወሎ ደጋጎችናና አራት ዓይናዎች የሚመለከት ነው፡፡ ጥፋተኛን የሚቀጡ፣ የተጣላን የሚያስታርቁ፣ አባቶችን እና እናቶኝ ማለት ነው፡፡ የነዚህ ደጋጎች ከራማም ሆነ በረካ ከሁለቱ እምነት ተከታዮች ጋር በእጅጉ የተሳሰሩ ናቸው:: በእነሱ አማካይነት የተጣላው ይታረቃል፤ ቂም የቋጠረው ቂሙ ይሽራል:: የጠፋው ይገኛል፤ የተሰወረው ይገለጣል፡፡ በዱዓቸውና በቱፍታቸው የታመመው ይድናል፤ የተለከፈው ይፈወሳል:: የትውልዱ አርአያዎች ሲባልም እነዚህን አካላት የሚመለከት ነው፡፡

ትውልዱ "አባቶች እንዳሉት፣እናቶች እንደተናገሩት፣ እንዳደረጉት...ወዘተ" በማለት የሚጠቅሳቸው የሚከተላቸው...ወዘተ አባቶችንና እናቶችን ወይም የሚጠቀሱ ሊቃውንት፣ የሚጠቀሱ ጀግኖች፣ የሚጠቀሱ የሃገር ሽማግሌዎች፣ የሚጠቀሱ የአካባቢ መሪዎችና አስተዳዳሪዎች...ወዘተ ማለት ነው፡፡ ባጠቃላይ እነዚህ የትውልዱ አርአያዎች በሕይወት ያሉ እና በሕይወት የሌሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በእውን መይም በአፈ-ታሪኮች የሚገለጹ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ የትውልዱ አርአያዎች ወሎን ደግፎና ጠብቆ የያዘው ሁለኛው ጉልቻ ተደርገው የሚወከሉ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

ሦስተኛው ጉልቻ ደግሞ በሥርአተ-ከበራዎች (Rituals) የተወከለ ነው። ሥርአተ-ከበራዎች በፎክሎር ጽንሰ-ሃሳብ መሠረት የአንድ ማኅበረሰብ ነፍሶች ወይም የሕይወት ምዕራፎች ናቸው:: እነዚህ ሥርአተ-ከበራዎች ወሎዬዎችን በአንድ ያሰባስባሉ፤ ያገናኛሉ፤ ያስተሳስራሉ። በዚህም ልዩ ልዩ መስተጋሮች ይፈጠራሉ። በዚህ ጥናት ውስጥ በስፋት እንደተብራራው ለዚህ አይነቱ ተራክቦ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች እጅግ በርካታ ናቸው። ለምሳሌ ሀገረሰብአዊ ሙዚቃው፣ መንዙማው፣ ዚያራው ወይም ሃይማኖታዊ ሥርአቶችና ልዩ ልዩ ከበራዎች፣ ፌስቲቫሎች፣ የልደት፣ የሠርግ፣ የሞት ሥርአት ክንውኖች፣ የዚህ ውክልና መገለጫ አብነቶች ናቸው።እንዲሁም ርግማኑ፣ ምርቃኑ፣ መሃላው፣ ድግምቱ፣ ኮከብ ቆጠራው፣ ጥንቆላው፣ አስማቱ፣ ክታቡ፣ ጠልሰሙ፣ ቀሳፊ ቃላቱ፣ ርኩስ መንፈሱ፣ ቡዳው፣ ድንጋጣዩ፣ ቅጠል በጣሸና ሥር ማሸ...ወዘተ ሁሉ የነዚህ ሥርአተ-ከበራዎች አብነቶች ናቸው። ስለሆነም ሦስተኛው ጉልቻ በነዚህ ጽንሰ-ሃሳቦች ተወክሏል።

ዱቄት ቡና/ ውሃ፡- ቡናው እና ቡናው የሚፈላበት ውኃ የተወከለው በወሎዬዎች ማኅበራዊና ባህላዊ ዓውዶች አማካይነት ነው። ምክንያቱም ዓውድ የዚህ ጥናት መነሻና መድረሻ ነው። ይህም ማለት ባህላዊ አውዱ የወሎዬዎችን የጋራ እሴቶች፣ እንዲሁም በእሴቶቹና በራሳቸው በወሎዬዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ይመለከታል። እንዲሁም በእሴቶቹ የፍች ሥርዓቶችና ትዕምርታዊ (ተምሳሌታዊ) የግንኙነት መርሆዎች ላይ የሚያተኩር ጉዳይ ነው። ማኅበራዊ አውዱ ደግሞ በወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መዋቅርና ግንኙነት ላይ የተመሰረተ አስተሳሰብ ነው። አስተሳሰቡ ማኅበራዊ፣ ግለሰባዊና ተቋማዊ አውዶችን በውስጡ ያካትታል። ከዚህ አንፃር ቡናው በውኃ እንደሚዋሃድ ሁሉ ወሎዬዎችም የነዚህ ማኅበራዊና ባህላዊ አውድ ውህድ ወይም ውጤቶች ናቸው። እሴቶቻቸውም በዚሁ ዓውድ ውስጥ የተፈጠሩ፣ የሚኖሩ፣ አገልግሎት የሚሰጡና በዚሁ አንፃር የተጠኑ ናቸው።

ኃይል (እሳት)፡- ኃይል ወይም እሳት በቡና አፈላል ሂደት ቡናው ከውኃ ጋር ተዋህዶ መልካም ቃናና መዓዛ ያለው አቦል ቡና እንደሚያስገኝ ሁሉ፤ በተመሳሳይ የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብሮች ከባህላዊና ማኅበራዊ ዓውዳቸው ጋር ተስማምተውና ሰምረው እንዲሁም ተዋህደው በአቦል ቡና የተወከሉት የጋራ እሴቶች እንዲገኙ የሚያስችሉት ባህላዊ ጉዳዮቹ፣ የሃይማኖቶቹ ትውፊቶችና የሁለቱ ቅልቅል የሆኑ ጉዳዮች ናቸው።

ጀበና ውስጥ ያለ ቡና፡- ጀበና ውስጥ ያለው ቡና የሚወክለው ደግሞ የወሎዬዎችን አጠቃላይ የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ነው። የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር በበኩሉ ከራሳቸው ከወሎዬዎች ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና

ተፈጥሯዊ ከሆኑ ሁነቶች ጋር የሚተሳሰር ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ሁነቶች የወሎዬዎች አብሮነት የሚገለጽባቸው የጋራ እሴቶች ናቸው፡፡ ከእሴቶቹ አንፃር በጀበናው ውስጥ ያለው ቡና የሚወክለው በማኅበረሰቡ ዘንድ "ጥሩ-መጥፎ ወይም ቅቡል-ውጉዝ" ተብለው የሚገለጹ የጋራ እሴቶችን ባጠቃላይ ነው፡፡

ስኒ ውስጥ የተቀዳ ቡና፡- በስኒው ውስጥ የተቀዳው ቡና በወሎዬዎች "ቅቡል" ወይም "መልካም" የተሰኙ የጋራ እሴቶችን ይወክላል፡፡ እነዚህ የጋራ እሴቶች የማኅበረሰቡ የአኗኗር ሥርአት፣ የማኅበራዊ ሕይወት መመሪያና የሥነ-ምግባር መርሆዎች የሚለካባቸውና የሚገለጽባቸው፣ የማኅበራዊ ሥርአቱ ሕግና ደንብ የሚፀናባቸው የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር መሰረቶች ናቸው፡፡

በዚህም እሴቶቹ አብሮነትን ያስተምራሉ፤ መለያየትን ይቃወማሉ፡፡ መከባበርን፣ መተባበርን፣ አብሮ መስራትን፣ መረዳዳትን፣ መደጋገፍን፣ መተሳሰብን፣ መተዛዘንን፣ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣትን ያስተምራሉ፡፡ መናናቅና ራስ ወዳድነትን ይቃወማሉ፡፡ መልካምነትን ይሰብካሉ-ክፋትን ያወግዛሉ፡፡ ቅቡል ምግባሮችን ያበረታታሉ፤ ጥዩፍ ባህርያትን ይኮንናሉ፡፡ ጀግንነትን ያበረታታሉ-ፍርሃትን-ይቃወማሉ፡፡ ይሃም የሚሆነው ከላይ እንደተገለፀው ጀበናው ጥሩውን ከመጥፎው የማጣራት ሥራ ስለሚሰራ ነው፡፡

በዚህ መሰረት ከጀበናው ወደ ስኒው የሚቀዳው አቦል ቡና የሚወክለው በወሎ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦችን እርስ በርስ አስተሳስረውና አስተባብረው፣ አግባብተውና አስማምተው፣ አዛምደውና አዋህደው ድርና ማግ በመሆን በፍቅርና በሰላም ይዘዋቸው የሚጓዙት መሰረታዊ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶችን ነው፡፡ እሴቶቹ የወሎዬዎች መገናኛ ድልድይ እና የእርስ በርስ መተሳሰሪያ ክር ናቸው፡፡ ከውክልናው መረዳት እንደሚቻለው እነዚህ የእርስ በርስ መተሳሰሪያ ክሮች ማኅበራዊና ባህላዊ ዓውዶቹ በባህላዊ ጉዳዮቹ፣ በሃይማኖቶቹ ትውፊቶችና በሁለቱ ቀልቅል ተዋህደውና ነጥረው፣ በወሎ ተምሳሌትነት ተጣርተው የሚፈጠሩ የወሎዬዎች የማኅበራዊ ኑሮ መስተጋብር ውጤቶች ናቸው፡፡ የመተሳሰሪያ ክሮቹ በትውልዱ አርአያዎች፣ በማኅበረሰቡ ትዕምርቶችና ሥርዓተ-ከበራዎች ይደጋፋሉ፤ ይጠበቃሉ፡፡ ስለዚህ "የሃይማኖት መቻቻል እሴት" ማለት በወሎ አብሮነት ማለት ነው፡፡ የወሎዬዎችን "ጥርስና ከናፍርነት" ወይም "አንድ አካል አንድ አምሳልነት" የሚወክል ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡

ይህም የሚያሳው ወይም የሚገልፀው መሰረታዊ ጉዳይ ከመለያየት ይልቅ፤ መሰባሰብን ወይም አንድነትን፣ ከመናናቅ ይልቅ፤ ትህትናና መከባበርን፣ ከመጠራጠር ይልቅ፤ መተማመንን፣ ከኔ

ይልቅ ላንት መባባልን፣ ወይም አንተ ትብስ-አንቺ-ትብሽ መባባልን፣ አብሮ መሥራትን፣ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣትን፣ አብሮ ማዘንና አብሮ መደሰትን፣ መተጋገዝን፣ መረዳዳትን፣ መደጋገፍን፣ መተባበርን፣ በሰላምና በፍቅር አብሮ መኖርን፣...ወዘተ የሚለውን የወሎዬዎች አስተሳሰብ ነው። የዚህ አይነቱን የወሎዬዎች ባህል፣ ወግና ልማድ ነው። የወሎዬዎችን የማኅበራዊ መስተጋብር ደንብና ሥርዓት ነው።

በሌላ በኩል በዚህ ጥናት አጠቃላይ ግኝትና ከላይ በቀረበው ውክልና መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ በወሎዬዎች ማኅበራዊና በህላዊ ዓውድ አማካይነት ይገለፃል። በወሎዬዎች ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ተፈጥሯዊ ሁነቶች አማካይነት ይገለፃል። በወሎዬዎች የማህበራዊ ኑሮ መስተጋብር ዘይቤ በኩል ይገለፃል። በሃይማኖቶቹ ትውፊቶች አማካይነት ይገለፃል። በወሎ ደጋጎች፣ በወሎ አድባር፣ በወሎ አቦል ቡናና በራሱ ወሎ በሚለው ሥያሜ ይገለፃል። በማኅበረሰቡ አርአያዎች፣ ትዕምርቶችና ሥርዓተ-ከበራዎች አማካይነት ይገለፃል። በዚህ መሰረት የሃይማኖት መቻቻል እሴት በወሎ የተለያዩ ትውፊቶች ውጤት ነው። የፎክሎርና የሃይማኖት ቡራኬ ነው፤ የዱዓና የቱፍታ በረከት ነው። የመላዕክት፣ የፃድቃን፣ የነቢያትና የሰማዕታት ችሮታ ነው፤ የፈጣሪም ፀጋ ነው። የተፈጥሮና የወሎዬዎች መስተጋብር ስጦታ ነው፤ የገበያም እሴት ነው። የወሎዬዎች የእርስ በርስ ግብኙነት ብሂል ትሩፋት ነው።

ባጠቃላይ ከዚህ ጥናት መረዳት እንደሚቻለው ወሎዬዎች እርስ በርስ የሚተሳሰሩባቸውና ለአብሮነታቸው መሰረት የሆኑ በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው። ይህም በመሆኑ ወሎዬዎች በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሳይቀር ግማሹ ሙስሊም ግማሹ ክርስቲያን በመሆን በሰላምና በፍቅር አብረው ይኖራሉ። አንዱ ከቁስ ሌላው ከሼህ ተዋልደው በሥጋና በደም፣ በአጥንትና በጅማት ይተሳሰራሉ። በሃይማኖቶቹ ትውፊቶች በረካ ይቀበላሉ። በወሎ አድባርና በወሎ ደጋጎች ይጠበቃሉ። በጉርብትና ብሂላቸው ደግሞ አብረው ይሰራሉ፤ አብረው ይበላሉ አብረው ይጠጣሉ። በጋራ ያዝናሉ በጋራ ይደሰታሉ። ይደጋገፋሉ ይረዳዳሉ። በዚህም በሰላምና በፍቅር አብረው ይኖራሉ። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በዚህ ጥናት የፎክሎር ፅንሰ-ሃሳብ ማብራሪያ ውስጥ እንደተገለፀውና በጥናቱም በተግባር እንደተረጋገጠው ወሎዬዎች የእኔ የራሴ የሚሉት የጋራ የሆነ የሃይማኖት መቻቻል እሴት ስለፈጠሩና ስላዳበሩ ነው።

ይሁንታዎች

በዚህ ጥናት የተለያዩ አብነቶችን በመጥቀስ እንደተብራራው ወሎዬዎች በሃይማኖት ተቻችለው እንዲኖሩ የሚያስችሏቸው በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው። ይህ ማለት ግን በአሁኑ ዘመን በወሎ ለሃይማኖት መቻቻል እሴት ተምሳሌት የሆኑ የወሎዬዎች የጋራ እሴቶች እንዳሉና እንደነበሩ ቀጥለዋል ማለት አይደለም። ለወደፊትም እሴቶቹ ሳይለወጡና ሳይቀየሩ እንዳሉና እንደነበሩ ሊቀጥሉ ይችላሉ፤ ተብሎ አይታሰብም። ባንዳሩ ከዘመኑ መንፈስ ጋር አብረው እየተለወጡ፣ በሌላ እየተተኩና እየተቀየሩ ሊሄዱ ይችላሉ።

ለውጥ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ውስጥ የነበረ፣ ያለና የሚኖር ተፈጥሯዊ ሂደት ነው። መሰረታዊው ቁምነገር ግን በለውጡ ምክንያት የሚመጣው ውጤት አወንታዊ ወይም አሉታዊ ክስተት ከመሆኑ ላይ ነው። ከዚህ አንፃር በወሎየዎች የአብሮነት መሰረት በሆኑ እሴቶች ላይ አሉታዊ መንፈስ ያላቸው ለውጦች እየታዩ ነው። ስለዚህ ወሎዬዎች እርስ በርስ የተሳሰሩ ባቸው ክሮች እንዳይበጠሱ፣ የሚገናኙ ባቸው ድልድዮች እንዳይፈርሱና በዚህ የተነሳ የሚለያዩባቸው አጋጣሚዎች ተፈጥረው እንዳይራራቁ ከዚህ ጥናት አንፃር የሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

1፦በወሎ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ ማኅበረሰቦችን እርስ በርስ አስተሳስረውና አስተባብረው፣ አግባብተውና አስማምተው፣ አዛምደውና አዋህደው ድርና ማግ በመሆን በፍቅርና በሰላም ይዘዋቸው የሚጓዙ መሰረታዊ የሃይማኖት መቻቻል እሴቶች በዚህ ጥናት ተመርምረዋል። አብነቶችም ቀርበዋል። ነገር ግን እነዚህ የጋራ እሴቶች ከዘመኑ መንፈስ አንፃር በተለያዩ ምክንያቶች እየተሸረሸሩና እየተዳከሙ በመሄድ ላይ እንደሚገኙ የእሴቶቹ ባለቤቶች ይናገራሉ። በዚህ መሰረት ምክንያቶቹን ከሥረ- መሰረታቸው መርምሮ መፍትሄ ለማበጀት እንዲቻል በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ጥናትና ምርምር ማካሄድ።

2፦ለውጥ ወይም ስልጣኔ ማለት አንድ ማኅበረሰብ የነበረውንና ያለውን ባህል፣ ወግና ልማድ፤ ደንብና ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ በመተው ወይም ከዚያ አፈንግጦ በመውጣት ልዩነት መፍጠር ማለት አይደለም። ባንዳሩ ነባሩን እያሻሻሉና ዘመኑ ከሚጠይቀው ነባራዊ ሁኔታ ጋር እያጣጣሙ መጠቀም ማለት ነው። ከዚህ አንፃር በየደረጃው ከቤተሰብ እስከ መንግሥት ኃላፍነት ወስዶ ትውልዱ እሴቶቹን እንዲያውቅ፣ እንዲጠብቃቸው፣ እንዲንከባከባቸውና እንዲጠቀምባቸው ማስተማር። ለዚህ ደግሞ የትናትና ምርምር ሥራዎች በተለያዩ ዘዴዎች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ። ለምሳሌ በዚህ ጥናት የተነሱ የጋራ እሴቶችን ለአብነት መጠቀም ይቻላል።

ዋቢ መፃሕፍት (References[341])

1፡- አማርኛ

ሞላ መኮንን፤ "በጉባላፍቶ ወረዳ የሼህ ለጋ ባህላዊ የግጭት ቁጥጥርና አፈታት"፤ ኤም.ኤ.፤ አ.አ.ዩ፣ 1999 ዓ.ም.፡፡

ቦጋለ ተፈሪ፤ *ትንቢተ ሸህ ሁሴን ጅብሪል*፡፡ አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም.፡፡

ታየ ገብረ ማርያም፤ *የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ*፡፡ አዲስ አበባ፤ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት፣ 1958 ዓ.ም.፡፡

አክሊሉ ገብረ ኪሮስ፤ "የኢትዮጵያ ሊቃውንት ስለ ጥንታዊ ስልጣኔ ያላቸው አስተያየት"፡፡ *Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies.*vol.2, Addis Ababa (IES),1963, pp.188-196.

ኤፍሬም እሼቴ፤ *አክራሪ እስልምና በኢትዮጵያ*፡፡ USA: Silver Spring, 2000 ዓ.ም.፡፡

ውዱ ጣፈጠ፤ "የሃይማኖት መቻቻል በኢትዮጵያ"፤ አርታኢ፣ ሽፈራው በቀለ፤ *ባህልና ልማት በኢትዮጵያ*፤ አ.አ፤ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ 2004 ዓ.ም.፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤ *ክብረ-ነገሥት*፤ አ.አ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1994 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሰ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሰ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ክልዳተ ክርስቶሰ እሰከ ጵጵ*፤ አ.አ፤ ሚጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፤ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፤አ.አ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም፡፡

ጌታቸው መኮንን፤ *ወለ፡- "የአገር ድባብ"* ፤ አ.አ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም፡፡

ጌታዋ ሞላ፤ "የፎክሎር ምድር"፤ "Contemporary Issues in Ethiopian Folklore" ለተባለ ኮርስ የቀረበ፤ አ.አ.ዩ፣ 2004 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፤ *የሥነ-ቃል መምሪያ*፤ አ.አ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991 ዓ.ም፡፡

_____፤ "Contemporary Issues in Ethiopian Folklore"፤ አ.አ.ዩ፣ 2004 ዓ.ም፡፡

341 በዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ የዋሉ የዋቢ መፃሕፍት አጠቃቀስ፣ በሙሉ የ‹‹MLA›› የዋቢ መፃሕፍት የአጠቃቀስ ሥልት መሠረት ያደረገ ነው፡፡

2:- English

2.1:- Books:

Abdi Khalil. *Harar Jugal: Historical Quality to Treasure: UNISCO's 2003 Laureate City for Diversity, Tolerance, Peace, and Unity*. Harar: Dire Printing sh. Co., 2007.

Abir, Mordechai. *Ethiopia: The Era of the Princes, the Challenge of Islam and the Reunification of the Christian Empire, 1769-1855*. London: Longmans, 1968.

Aspen, Harald. *Amhara Traditions of Knowledge: Spirit Medium and their Clients.* Wiesbaden: Harrassowitz Verlag, 2001.

Bahru Zewude. *A History of Modern Ethiopia 1855-1974*. Addis Ababa: Addis Ababa University Press, 1991.

Bairu Tafla (trans. & ed.). *Atsma Giorgis and His Work: History of the Galla and the Kingdom of Shewa.* Stuttgart: Franz Steiner Verlag Wiesbaden GMBH,1987.

Bauman, Richard. "The Field Study of Folklore in Context." *Handbook of American Folklore*. Ed. Richard M. Dorson. Bloomington: Indiana University Press, 1983. 362-368.

____.ed. *Folklore, Cultural Performance, and Popular Entertainments: A Communication-Centered Handbook*. New York: Oxford University Press, 1992.

_____.*Story, Performance, and Event: Contextual Studies of Oral Narratives*. New York: Cambridge University Press, 1986.

_____.*Verbal Art as Performance. Prospect Heights*. IL: Waveland Press, 1977.

Ben-Amos, Dan. "The Context of Folklore: Implications and Prospects". The *Foremost of Folklore*. Ed. William R. Bascom. Boulder: West view Press, 1977.

_____.ed. *Folklore Genres*. Austin: University of Texas Press, 1976.

Ben-Amos, Dan, and Kenneth, Goldstein, eds. *Folklore: Performance, and Communication.* The Hague: Mouton, 1975.

Benzing, Brigitta. "Ethiopia-Cultures and Traditions-an Introduction." *in Ethiopia: an Introduction into Culture, Economics, Politics & Cooperation.* (ed.) Christian Fellner. Sudwind: Brandes and Apsel, 2000.

Bojoviç, Aleksandra Prodanoviç. *Jewelry of Ethiopia.* Belgrade: The Museum of African Art, 2010.

Kefyalew Merahi. *Peace and Development in the New Ethiopian Millennium.* Addis Ababa: Commercial P.E., 2005.

Central Statistical Agency (CSA). *The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia.* Addis Ababa: Branna Printing Enterprise, 2010.

Cliford, James. *The Predicament of Culture: Twentieth-Century Ethnography, Literature, and Art.* Cambridge, mass.: Harvard University Press, 1988.

Creswell, John W. *Research Design: Qualitative, Quantitative, and Mixed Methods Approach.* 4th ed. Thousand Oaks, CA: SAGE, 2014.

Crotty, Michael. *The Foundations of Social Research: Meaning and Perspective in the Research Process.* Thousand Oaks, CA: SAGE, 1998.

Dorson, Richard M., ed. *Folklore and Folk life: An Introduction.* Chicago: University of Chicago Press, 1972.

_____."Folktale Performance." *Handbook of American Folklore.* Ed. Richard M. Dorson. Bloomington: Indiana University Press, 1983. 287-300.

_____."Who are the Folk?" *Frontiers of Folklore.* Ed. william R. Bascom. Boulder: West view Press, 1977. 17-35.

Dundes, Alan. *Analytic Essay in Folklore.* The Hague: Mouton: 1975.

_____.*Folklore Matters*. Knoxville: University of Tennessee Press, 1989.

_____.ed. *International Folkloristic: Classic Contributions by the Founder of Folklore*. Latham: Bowman and Littlefield, 1999.

_____."Texture, Text, and Context." *Interpreting Folklore*. Ed. Alan Dundes. Bloomington: Indiana University Press, 1980. 21-31.

_____."What is Folklore?" *The Study of Folklore*. Ed. Alan Dundes. Englewood Cliffs, N.J.: Prentice — Hall, 1965. 1-3.

_____."Who are the Folk?" *Interpreting Folklore*. Ed. Alan Dundes. Bloomington: Indiana University Press, 1980. 1-19.

Erlich. Haggai, Staven Kaplan, and Hagar Salomon. *Ethiopia: Christianity, Islam, Judaism*. Ed. Haggai Erlich. Tel-Aviv: Open University of Israel, 2003.

Freud, Sigmund. *A General Introduction to Psychoanalysis*. New York: Perm Books, 1953.

Geertz, Clifford. *The Interpretation of Culture*. New York: Basic Books, 1973.

_____.*Local Knowledge: Further Essays Interpretive Anthropology*. New York: Basic Books, 1983.

Georges, Robert A., and Michael Owen Jones, eds. *Fokloristics: An Introduction*. Bloomington: Indiana University Press, 1995.

Gibald, Joseph. *MLA Handbook for Writers of Research Papers*. 6th ed. New York: Modern Language Association of America, 2003.

Gish, Steven. *Ethiopia: Culture of the World*. New York: Marshal Cavendish, 1996.

Glassie, Henry. *Material Culture*. Bloomington. Indiana University Press, 1999.

Goldstein, Kenneth S. *A Guide for Fieldworkers in Folklore*. Hatboro, Penna.: Folklore Associates, Inc., 1964.

Hammersley, Martyn, and Paul Atkinsion. *Ethnography Principles in Practice*. London: Routledge, 1991.

Hobsbawm, Erich, and Terence Ranger, eds. *The invention of Tradition.* Cambridge: Cambridge University Press, 1983.

Hussein Ahmed. *Islam in Nineteenth-Century Wallo, Ethiopia: Revival, Reform, and Reaction*. Leiden: Brill, 2001.

Hymes, Dell H. "The Contribution of Folklore to Sociolinguistics Research." *Toward New Perspectives in Folklore*. Eds. Americo Paredes and Richard Bauman. Austin: University Press of Texas Press, 1972.35-71.

_____."The Ethnography of speaking." *Anthropology and Human Behavior*. Eds. Thomas Gladwin and William Sturtevant. Washington, D.C.: Anthropological Society of Washington, 1962. 15-53.

Jackson, Bruce. *Fieldwork*. Urbana and Chicago: University of Illinois Press. 1987.

Jones, Michael Owen, ed. *Putting Folklore to Use*. Kentucky: University Press of Kentucky, 1994.

Last Jill. *Ethiopian Festivals: Sports, Games, Celebrations, Occasions, Pilgrimages*. Addis Ababa: Ethiopian Tourism Commission,1982.

Leach, Maria, and Jerome Fried, eds. "Folklore." *Funk and Wagnall's Standard Dictionary of Folklore, Mythology, and Legend.* 2vols. New York: Crowells, 1949. 398-417.

Levi-Strauss, Claude. *The Structural Study of Myth. Structural Anthropology*. Trans. Claire Jacobson and Brooke Grunsfest. New York: Basic Books. 1963.

Lincoln, yvonna.s., and Egon Guba. *Naturalistic Inquiry*. Beverly Hills, CA: SAGE, 1985.

Malinowski, Bronislaw. *Myth in Primitive Society*. London: Kasgan Pau, French, trubner, 1926.

Marshall, Catherine, and Gretchen Rossman. *Designing Qualitative Research*. 5th ed. Thousand Oaks, CA: SAGE, 2011.

Maxwell, Joe A. *Qualitative Research Design: An Interactive Approach*. 2nd ed. Thousand Oaks, CA: SAGE, 2005.

Merriam, S.B. *Qualitative Research and Case Study Applications in Education*. San Francisco: Jossey-Bass, 1998.

Mesfin Welde Mariam. *Suffering Under God's Environment: A Vertical Study of the Predicament of Peasant in North Central Ethiopia*. Berne: Wads Worth pub. Com, 1991.

Miles, M.B., and Huberman A.M. *Qualitative Data Analysis: A Source Book of New Methods.* California: SAGE, 1984.

Munro, Hay-Stuart. *Ethiopia: The Unknown Land: A Cultural and Historical Guide.* London. New York: 1.B. Tauris and Coltd, 2002.

Norheim, Ragnar and Norheim Ingrid. *Church history*. Debre Zeit: Christian Education Curriculum program work shop, 1973.

Oring, Elliott, ed. *Folk Groups and Folk Genres: An Introduction*. Logan: Utah State University Press, 1986.

Østebø, Terje. Localizing Salafism: *Religious Change Among Oromo Muslims in Bale, Ethiopia*. Sweden: Stockholm University, 2008.

Paredes, Américo, and Richard Bauman, eds. *Toward New Perspectives in Folklore*. Bloomington: Trickster Press, 1972.

Propp, Vladimir. *Morphology of the Folktale*. Trans. Laurence Scott. Rev. ed. Austin and London: University of Texas Press 1953.

Schoemaker, George H., ed. *The Emergence of Folklore Everyday Life: Field Guide and Sourcebook*. Bloomington, Indiana: Trickster Press, 1990.

Schwab, Peter. *ETHIOPIA: Politics, Economics and Society*. London: Frances Pinter, 1985.

Sergew Hable Slassie. *Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270*. Addis Ababa: United Printers, 1972.

_____ (ed.). *The Church of Ethiopia: a Panorama of History and Spiritual Life*. Addis Ababa: Ethiopian Orthodox church,1970.

Sumner, Claude. *Ethiopian philosophy. Volume-I: The Book of the Wise Philosophers*. Addis Ababa: Central Printing Press, 1974.

_____.*The Ethiopian Philosophy of Greek Origin*. Stuttgart: Franz Steiner Verlag Wiesbaden, 1988.

Taddesse Tamrat. *Church and State in Ethiopia 1270-1527*. London: Oxford University Press, 1972.

Thompson, Stith. *Motif-Index of Folk-Literature*. 6 vols. Bloomington: Indiana University Press, 1972.

Toelken, Barre. *The Dynamic of Folklore*. Logan, Utah: Utah State University Press, 1996.

Trimingham, J. Spencer. *Islam in Ethiopia*. 2nd ed. London: Frank Gass & CO. LTD, 1965.

Utley, Lee Francis. "Falk Literature. An Operational Definition." *The Study of Folklore*. Ed. Aland Dundes. Englewood Cliffs, N.J.: Prentice-Hall Inc, 1965. 8-13.

Workman, Mark. "Folklore and Literature: From Text to Context." *Introduction: Children and Folklore*. Ed. Blatt, Gloria T. New York and London: Columbia University Press, 1993. 131-139.

2.2:- Articles in Periodicals, Conference, & Seminar papers

Abba Gorgorios. "Social Ministry of the Ethiopian Orthodox Church in the Past and the Present." *Proceedings of the Tenth International Conference of Ethiopian Studies.* Vol.-1. Addis Ababa: Addis Ababa University (IES), 1994, pp.391-396.

Abir, Mordechai. "Trade and Christian-Muslim Relations in Post Medieval Ethiopia." *Proceedings of the Fifth International Conference of Ethiopian Studies*. Ed. Robert L. Hess. Chicago: 1978, pp. 411-14.

Ahmed Hassen. "A Preliminary Note on Religious Tolerance in Ethiopia: A Historical Review of Discourse about Islam." *Proceedings of Conferences on Enhancing Religious Tolerance in Ethiopia in the New Ethiopian Millennium*. Addis Ababa: Inter Africa Group, Graphic Printers, 2008.

Alula Pankhurst. "Reflections on Pilgrimages in Ethiopia." *Proceedings of the 12th International Conference of Ethiopian Studies.* vol.-2. Addis Ababa: Addis Ababa University (IES),1994, pp. 933-953.

____."Indigenizing Islam in Wällo: Ajäm, Amharic Verse Written in the Arabic Script." *Proceedings of the Eleventh International Conference of Ethiopian Studies.* vol.-1. Addis Ababa: Addis Ababa University (IES),1994, pp. 257273.

Amsalu Aklilu and Habte M. Marcos. "The Dialect of Wollo." *Mimeographed*. Haile Selassie I university, 1969.

Bascom, William R. "Folklore and Anthropology." *JAF*[342] 66 (1953): 283 — 290

_____."four Functions of Folklore." *JAF* 67 (1954): 333-349.

Bauman, Richard. "Differential Identity and the Social Base of Folklore." *JAF* 84 (1971): 31-43.

Ben-Amos, Dan. " 'Context', in Context". *Western Folklore* 52 (1993): 209-226.

Braukämper, Ulrich. "Notes on the Islamization and the Muslim Shrines of the Harar Plateau." *Proceedings of the Second International Congress of Somali Studies.* Hamburg: 1984, pp. 145-174.

_____."The Islamization of the Arissi Oromo." Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies. vol.-1. Addis Ababa: Addis Ababa University (IES), 1989, pp. 767-777.

_____."On Food Avoidance in Southern Ethiopia: Religious Manifestation and Socio-Economic Relevance." *Proceedings of the Seventh International Conference of Ethiopian Studies.* Addis Ababa: Addis Ababa University (IES),1984, pp. 429-445.

_____."Folklore in African Society" *Research in African Literature.* Vol. 6.2 (1975): 165-198.

_____. "Toward a Definition of Folklore in Context." *JAF* 84 (1971): 3-15.

Caulk, Richard A. "Religion and the State in Nineteenth Century Ethiopia." JES[343] 10.1 (1972): 23-42.

Crummey, Donald. "Cäcäho and the Politics of the Nothern Wallo-Bagémder Border." *JES* 13.1 (1975): 1-10.

342 "JAF":- Journal of American Folkore
343 "JES":- Journal of Ethiopian Studies

Dundes, Alan . "From Etic to Emic Units in the Structural Study of Folktales." *JAF* 75 (1962): 95-105.

Ephraim Isaac and Cain Felder. "Reflection on the Origins of the Ethiopian Civilization." *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*. Vol. 1.1988, pp. 71-83.

----------."Tolerance: Christianity and Islam in Ethiopia from a Historical Perspective. " *Proceedings of Conferences on Enhancing Religious Tolerance in Ethiopia in the New Ethiopian Millennium*. A.A: Inter Africa Group, Graphic Printers, 2008.

Hussein Ahmed. "Coexistence and/or Confrontation: Towards a Reappraisal of Christian-Muslim Encounter in Contemporary Ethiopia." *International Journal of Ethiopian Studies*. Vol. 2. 1-2 (2006): 194-205.

_____."The Historiography of Islam in Ethiopia." *JES*. 3.1 (1992): 15-46.

_____."Introducing an Arabic Hagiography from Wallo." *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*. Vol.1. 1988, pp. 185-97.

_____."Islam and Islamic Discourse in Ethiopia (1973-1993)." *New Trends in Ethiopian Studies: Papers of 12th International Conference of Ethiopian Studies*. Ed. Harold G.Marcus. Lawrenceville's, N.J.: Vol.1. 1994, 775-801.

_____."The Life and Career of Shaykh Talha b. Jafar (c.1853-1936)."*JES* 22(1989): 13-30.

_____."Studies on Ethiopian Islam: Retrospect and Prospect." *Proceedings of the 2nd Annual Seminar of the Department of History*. Vol. 2. Addis Ababa University, 1984, pp. 40-55.

_____."Traditional Muslim Education in Wallo". *Proceedings of the Ninth International Congress of Ethiopian Studies*. Moscow: Vol. 3. 1988, pp. 94-106.

_____."Two Muslim Shrines in South Wallo (Ethiopia)." *Proceedings of the Fifth Seminar of the Department of History.* Addis Ababa University, 1990, pp.61-74.

Leslaw, Wolf. "The Arabic Origin of the Ethiopic Qollé 'Spirit'."(reprinted from *Arabica*). Leiden: in his *MISCELLANEA 2.* vol.- 5. 1958, pp. 194-196.

_____."An Ethiopian Argot of people possessed by a Spirit." (reprinted from *Africa*). London: in his *MISCELLANEA* 1.vol.-19. 1949, pp. 204-212.

Levine, Donald. "The Promise of Ethiopia Public Action: Civic Forgiveness, Creative Power." *Proceedings of Conference on Fostering Shared Core National Values and Expanding Common Political Space in the New Ethiopian Millennium.* A.A: Inter Africa Group, Graphic Printers, 2008.

Lewis, Herbert S. "Spirit Possession in Ethiopia: An Essay in Interpretation." *Proceedings of the Seventh International Conference of Ethiopian Studies.* vol.-7. University of Lund, 1984, pp. 419-427.

_____."Values and Procedures in Conflict Resolution Among Shoan Oromo". *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies.* vol.-2. Addis Ababa: Addis Ababa University (IES),1989, pp. 673-678.

Merid welde Aregay. "Population Movements as a Possible Factor in the Christian-Muslim Conflict of Medieval Ethiopia." *Symposium Leo* Fresenius: Munich, 1974.

_____."Political Geography of Ethiopia at the Beginning of the Sixteenth Century." *Proceedings of the Fourth International Conference of Ethiopian Studies.* vol.-2. Rome: Addis Ababa University (IES),1974, pp. 613-631.

Messing, Simon D. "Group Therapy and Social Status in the Zar Cult of Ethiopia." Menasha Wisconsin: (reprinted from *American Anthropologist*).Vol.-60, no.-6. 1958, pp. 1120-1126.

Molla Tikuye. "The Rise and Fall of the *Yajju* Dynasty (1784-1930)." *Proceedings of the Eleventh International Conference of Ethiopian Studies.* vol.-1. Addis Ababa: Addis Ababa University (IES), 1994, pp. 197-216.

Natving, Richard. "Oromos, Slaves and the Zar Spirits: A Contribution to the History of the Zar Cult." *The International Journal of African Historical Studies.* 20 (4),1987.

Reminick, Ronald A. "The structure and functions of Religious Belief Among the Amhara of Ethiopia." *Proceedings of the First United States Conference on Ethiopian Studies.* East Lansing: African Studies Center, Michigan State University, 1995, pp. 25-42.

_____."The Evil Eye Belief Among the Amhara of Ethiopia." In Anthropology *MESCELLANEA* 3. Cleveland State University, 1976, pp. 237-249.

Samuel, V.C. "Christianity and Indigenization." *Journal of Ethiopian Studies* (JES). Addis Ababa: HSIU (IES),1976, pp. 60-92.

Taddesse Tamrat. "Processes of Ethnic Interaction and Integration in Ethiopian History: the case of Agaw." *Proceedings of the Ninth International Congress of Ethiopian Studies.* vol.-6. Addis Ababa: Addis Ababa University (IES),1988, pp. 192-206.

Tessore, Alberto. "Development of International Cultural Relations of Ethiopia: A Review of Foreign Institutions." *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies.* vol.-2. Addis Ababa: Addis Ababa University (IES),1989, pp. 491-503.

Torrey E. Fulle "The Zar Cult in Ethiopia." *Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies.* vol.-3. Addis Ababa: HSIU (IES),1966, pp. 51-59.

Tsegay B. Gebrelibanos. "The Ethiopian Salt Trading System in the 20th Century: A View from Mäqäla, Northern Ethiopia." *Proceedings of the Sixteenth International Conference of Ethiopian Studies.* vol.-1. Addis Ababa: Addis Ababa University (IES), 2009, pp. 185-201.

Yassin Mohammed Abera. "Muslim Institutions in Ethiopia: The Asmara Awqaf." *Journal: Institute of Muslim Minority Affairs.* Vol. 5.1. (1984): 203-223.

Young, Allan. "Magic as 'Quassi-Profession', the Organization of Magic and Magical Healing Among Amhara, Ethnology." *An International Journal of Cultural and Social Anthropology.* vol. 14, no. 3, University of Petersburg, 1975.

_____."Why Amhara Get Kureynya [Qurañña] Sickness and Possession in an Ethiopian Zar Cult." In Anthropology *MISCELLANEA* 4. Case Western Reserve University,1975.

2.3:- Thesis

Afework Hailu. "Religious Tolerance in Addis Ababa, 1991-1997". M.A. Thesis, Addis Ababa University, IES, 2009.

Assefa Balcha. "Traditional Medicine in Wallo: Its Nature and History." M.A. Thesis in history, Addis Ababa University, 1992.

Asnake Ali. "Aspects of the Political History of Wallo: 1872-1917." M.A. Thesis, Addis Ababa Univerisity, 1983.

Assefa Mamo. "Some Prominent Feature of the Menzuma Genre as Practiced in the Wollo Region." M.A. Thesis, Addis Ababa University, 1987.

Awoke Asmare. "The Career of Ras Gugsa Wale (ca.1877-1930)." M.A.Thesis in history, Addis Ababa University, 1996.

Belay Guta. "Muslim Evangelism in Ethiopia." USA: Msc Thesis in Inter Cultural Studies, School of World Missin,1997.

Berhanu Gebeyehu. "Islamic Oral Poetry in Wollo: A Preliminary Descriptive Analysis." M.A. Thesis, Addis Ababa University, 1998.

Daniel Dejene. "Land Tenure Reform and Its Impact on Tenancy in Wàdlà Delàntà *Awrajja* (Wallo). M.A. Thesis in history, Addis Ababa university, 2009.

Endris Nigus. "The Wallo Famine of 1972-1974 with Special Reference to *Yajju Awrajja*. B.A. Thesis in history, Addis Ababa University, 1986.

Fekadu Begna. "Land and the Peasantry in Northern Wollo, 1941-1974, *Yejju* and *Rayya* and *Qobbo Awrajja*." M.A. Thesis, Addis Ababa University, 1990.

_____."A Tentative History of Wallo, 1855-1908." B.A. Thesis in history, Addis Ababa University, 1973.

Gashaw Mohammad. "Administrative History of Wollo: 1941-1974" M.A. Thesis, Addis Ababa University, 2003.

Habtamu Mossa. "A Thematic Approach to the Manzuma (Poems) of Sheikh Muhammad Yassin (1895-1972) in South Wollo." M.A. Thesis, Addis Ababa University, 2010.

Haileyesus Muluken. "Religious Tolerance and Tension between Orthodox Christianity and Islam in Gondar Town, North West Ethiopia." M.A. Thesis, Addis Ababa University, 2011.

Israel Arage. "A History of Wadla Dälanta Awrajja-1855-1974". M.A. Thesis in history, Addis Ababa University. 2011.

Kalklachew Ali. "Religion, Rituals, and Mutual Tolerance in Wollo." M.A. Thesis, Addis Ababa University, 1997.

Mallery, Suzane T. "Zar Possession as Psychiatric Diagnosis Problems and Possibilities." Dissertation inpsychology. Fuller Theological seminary, 1997.

Mengistu Abebe. "Land and Peasantry in Ambassal Awrajja (Wallo): 1941-1985." M.A. Thesis in history, Addis Ababa University, 2013.

Mohammed Yimam. "Inter-Faith Relations in Urban Centers of North- Eastern Ethiopia (Amhara National Reginal State): The Case of Dásé, Kámbolcha and kámesé." M.A. Thesis, Addis Ababa University, IPSS, 2010.

Molla Tikuye. "System of Land Tenure and Peasant Protest in Gubalafto Warada from (c.a.1785-1974)." B,A Thesis in history, Addis Ababa University, 1984.

Rukya Hassen. "Ethnography of Communication of the Amharic Speaking Muslim Community of South Wollo." PhD Dissertation, Addis Ababa University, 2013.

Sibkete Ermias Kebede. "The Dynamics of Religious Movement During the Late 19th and Early 20th Centuries: The Career of Shaykh Zakaryas /Newaya Kerestos/." M.A. Thesis, Addis Ababa University, IES, 2009.

Taddesse Esubalew. "Traditional and Cultural Beliefs on Magical Prayers (Ethiopic Amulets) and their influence on Women's Life. M.A. Thesis in Philology, Addis Ababa University, 2008.

Teferi Abate. "Land Capital and Labor in the Social Organization of Peasants: a Study of Village-level Dynamics in Southwestern Wallo, 1974-1993. M.A. Thesis in social anthropology, Addis Ababa University, 1993.

Tekalign Fanta. "Managing Religious Conflicts: A Study of the Legal Framework with Particular Reference to the 2006 Muslim-Christian Conflict in Oromiya." L.L.M. Thesis, Addis Ababa University, 2008.

Tesfaye Aklilu. "A History of Mäqét Wäräda: 1941-1991." M.A Thesis in history, Addis Ababa University, 2013.

Wudu Tafete. “A Political History of Wag and Lasta.” M.A. Thesis in history, Addis Ababa University, 1995.

Zelalem Temesgen. “The 2006 Religious Conflict on Didessa and Gomma *Woradas* of Western Oromia.” M.A. Thesis, Addis Ababa University, IES, 2010.

Zergaw Asfera. "Some Aspects of Historical Development in Amhara-Wallo (c.a.1700-1815)". B.A. Thesis in history, Addis Ababa University, 1973.